አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣
ስነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣
ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በፎክሎር የፒኤች. ዲ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

የአማርኛ ቃልግጥሞች ምደባ፣አውዳዊ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ

በ
አማረ ሞላ

አዲስ አበባ፣
ህዳር 2009 ዓ.ም.

የአማርኛ ቃልግጥሞች ምደባ፣አውዳዊ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣
ስነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣
ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በፎክሎር የፒኤች.ዲ. ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
አማረ ሞላ

አማካሪ
ዘሪሁን አስፋው(ተባባሪ ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ፣
ህዳር 2009 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

«የአማርኛ ቃልግጥሞች ምደባ፣ አውዳዊ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ›› በሚል ርእስ፣ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ፣ በአማረ ሞላ የቀረበው ይህ ጥናት፣ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለ ማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ይፈረማል።

አማካሪ

_____ ፊርማ _____ ቀን _____

ፈታኝ

_____ ፊርማ _____ ቀን _____

ፈታኝ

_____ ፊርማ _____ ቀን _____

አጠቃሎ

ይህ ጥናት «የአማርኛ ቃልግጥሞች ምደባ፤ ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ» በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ነው። ለጥናቱ መነሻ ምክንያቶች የሆኑት፣ ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጠ የኖረ በመሆኑ፣ ብሶቱንና ቁጭቱን፣ ጥላቻውንና ተቃውሞውን፣ ወዘተ. የሚገልጽባቸውን ቃልግጥሞች እየፈጠረ፣ ስሜቱን ሲያንጸባርቅ ቆይቷል። አካባቢው የእርስ በርስና የመከላከል ጦርነቶች የተካሄዱበት ነው። የርሀብና የድርቅ አደጋዎችም ገጥመውታል፤ እንደሌላው የሀገራችን ህዝብ ገዥዎች ተፈራርቀውበታል። በነዚህ ሁሉ ገጠመኞች ሳቢያ ማህበረሰቡ የፈጠራቸው ቃልግጥሞች ተሰብስበው አልተጠኑም ። ከዚህ በተጨማሪ አሁን ባሉት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች፣ቃልግጥሞች የሚከወኑባቸው ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች እየተለወጡና እየቀሩ በመሆናቸው፤ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፉ የነበሩ ቃልግጥሞች እየተረሱ፣ እየተለወጡ፣ በሂደትም እየጠፉ የመሄድ አጋጣሚያቸው ሰፊ እየሆነ መጥቷል። በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ይህ ጥናት አስፈላጊ ሆኗል።

ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጡት አካባቢዎች፤ በሰሜን ወሎ ዞን የሚገኙት ቆቦ፣ ጉባላፍቶና ሀብሩ ወረዳዎች ናቸው። የጥናቱ ዋና አላማ፤ በተመረጡት አካባቢዎች የሚገኙትን ቃልግጥሞች መሰብሰብ፣ መመደብና መተንተን ሲሆን፤ ዝርዝር አላማዎቹ ደግሞ፣ የግጥሞቹን ይዘቶችና ጭብጦች መሰረት አድርጎ ምደባ ማድረግ፤ የቃልግጥሞቹን የመከወኛ አጋጣሚዎችና የክዋኔ ስልቶች ማሳየት፤ በየምድቡ ካሉት ቃልግጥሞች የተወሰኑትን እያደራጁ ናሙና በመውሰድ፣ አውዳዊ መረጃን መሰረት አድርጎ መተንተንና ፋይዳቸውን መግለጽ ነው::

እነዚህን አላማዎች ለማሳካት፣ መስክ ላይ የተሰበሰቡት ቃልግጥሞች ከ1500 በላይ ናቸው። ከዚህ ውስጥ ከ650 በላይ ቃልግጥሞች በስምንት ዋና ዋና ምድቦች ተመድበዋል። ከዚህ በኋላ 400 ያህል ቃልግጥሞች ትንተና ተደርጎባቸዋል።ቃልግጥሞቹን ለመሰብሰብ የተጠቀምኩባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፤ ምልከታ፣ቃለ መጠይቅና ሰነዶች ሲሆኑ፣ እነዚህ ዘዴዎች በካሴት ቀረጻና በማስታወሻ የታገዙ ናቸው።

ከተሰበሰበው የቃልግጥም መረጃ በመነሳት የተገኙት የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች በስምንት ዋና ዋና ምድቦች የተከፈሉ ናቸው። እያንዳንዱ ምድብ ቢያንስ ሁለት ንኡሳን ምድቦች አሏቸው። ከዋናዎቹ ምድቦች በመነሳትና ካላቸው ማህበራዊ ፈይዳ አንጻር፤ ቃልግጥሞቹ፤ የሙገሳና የውዳሴ፣ የትችት፣ የጀግንነትና የፈሪነት መግለጫዎች፣ የቁንጅናና የፍቅር

መግለጫዎች፣ ብሶትንና ቁጭትን፣ እንዲሁም ጥላቻንና ማንኳሰስን የሚያመለክቱ ናቸው። ከፖለቲካና ከእርስ በርስ ጦርነቶች አንጻር የተገኙት ቃልግጥሞች፤ የደርግንና የኢህአዲግን መንግስታት፤ የሚተቹ፣ የሚደግፉና ትዝብታዊ በሆነ መንገድ የቀረቡ ናቸው። ቆየት ያሉትን የታሪክ ሁኔታዎችና፣ ከኢትዮ- ኤርትራ ጋር የተደረገውን ጦርነት የሚያስታውሱም አሉ። ከዚህ በተጨማሪ፤ በድርቅና በርሃብ ዘመናት የታዩትን ሁኔታዎች የሚያመለክቱ፣ እንዲሁም፤ አሁን በሀገራችን ያሉትን ወቅታዊ ችግሮች፤ ማለትም በሽታን፣ ስደትን፣ ቤት ማፍረስን፣ የሚመለከቱ ቃልግጥሞች ተገኝተዋል።

በእያንዳንዱ ምድብ በተደረገው ትንተና መሰረት፣ ጥናቱ ከደረሰባቸው ግኝቶች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው። የሙገሳና የውዳሴ ቃልግጥሞቹ አካባቢዎችንና ሰዎችን፤ እንዲሁም፣ እንስሳትን የሚያሞግሱ ናቸው። የትችት ቃልግጥሞቹ ሴቶችንና ወንዶችን የሚተቹ ሲሆኑ፣ ሴቶችን የሚተቹት ከሴቶች የሙያ ባልትና እና ከቁጠባ ጋር በተያያዘ ነው፤ ወንዶችን ግን፣ ከግብርና ስራና ተያያዥ ጉዮች ጋር በተገናኘ ነው። ከጀግንነትና ከፈሪነት ጋር ተያይዘው የተተነተኑት ቃልግጥሞች ሁሉም ወንዶችን ብቻ የሚመለከቱ ናቸው። አካላዊ ቁንጅናንና ፍቅርን የሚያመለክቱት ቃልግጥሞች በአብዛኛው ከሴቶች አካላዊ ቁንጅናና ውበት ጋር የተያያዙ ሆነው ታይተዋል። የብሶትና የቁጭት ቃልግጥሞች በአብዛኛው ወንዶችን ብቻ የሚመለከቱና የውስጥ ስሜታቸውን ያንጸባረቁባቸው ሰሆኑ፤ የጥላቻና የማንኳሰስ ቃልግጥሞች ግን፣ በሴቶች ላይ ብቻ ያተኮሩ ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ ቃልግጥሞቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ፤ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ባህላዊ ገጠመኞች የሚያሳዩ ስለሆነ፤ የሚመለከታቸው የማህበረሰብ አጥኝዎች፣ የታሪክና የስነ ሰብ ተመራማሪዎች፣ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ሰዎች፣የትምህርት ባለሙያዎች፣ ወዘተ. ይህንን ጥናት እንደመነሻ በመጠቀም፣ ለማህበረሰቡ ለማስተዳደርም ሆነ ለእድገትና ለልማት ቢገለገሉበት የተሻለ ይሆናል።

ምስጋና

ከ 1990 ዓ.ም. ጀምሮ በማስተማርና በማማከር እዚህ እንድደርስ የረዱኝን አማካሪየን ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋውን እና ሌሎችንም መምህራኖቼን በጣም አመሰግናለሁ። በተለይ አማካሪየ፣ “አማረ ! ስራ ላይ አትቆይ፣ መማር አለብህ...” ያሉኝ ምክርና ሀሳብ ለኔ ትልቅ የማንቂያ ደወል ነበረና ምንጊዜም አልረሳቸውም ። በዚህ ጥናት ላይ ያላቸው ድጋፍ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ደግሜ አመሰግናቸዋለሁ።

መረጃ ለመሰብሰብ ወልዲያና መርሳ በቆየሁባቸው ጊዜያት፣ መረጃ ሰጭዎችን እያፈላለገ በማገናኘትና ሌሎችም ሰዎች እንዲረዱኝ በቅንነት የተባበረኝን አድኖ ተካየ አስፋውን፣ መረጃ ሰጭዎቼን በሙሉ፣ በተለይ መምህር አብርሀ ሽፈራው፣ አቶ ተበጀ መኮንንና አቶ አሊ መሀመድን፣ በጣም አመሰግናለሁ። በሁለቱም ዙር የመስክ ላይ እንቅስቃሴ፣ ከኔ ሳይለዩ አብረውኝ መረጃ በመሰብሰብ የረዱኝን ወንድሞቼን በላይ ደሳለ፣ አበራ ሞላ፣ ዘውዱ ፈንታየ፣ እንዲሁም፤ መምህር ፈንታየ አሸብርንና ሌሎችንም አመሰግናለሁ።

የትምህርት እድሉን በመፍቀድና፣ የምርምር ወጪ ድጋፍ በማድረግ ለረዱኝ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ እንዲሁም፣ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ አስተዳደር ካውንስልን አመሰግናለሁ። በልዩ ልዩ መንገድ የረዱኝን ጓደኞቼንና ባልደረቦቼን፣ ጌታቸው አንተነህን፣ የሸጥላ መንግስቱን፣ዳዊት ፍሬህይወትን፤ ቴዎድሮስ ታደሰን፣ ተስፋየ ገዛኸኝን፣ አህመድ ሙስጠፋን፣ ውቤ ታደግን፣ እንዲሁም፣ ወንድሜን ደሳለ ይግዛውን አመሰግናለሁ።

በዚህ ጥናት ውስጥ በማጣቀሻነት የተጠቀምኩባቸውን መጻህፍትና መጣጥፎች፣ እንዲሁም በመደርደሪያየ ላይ ካሉት የፎክሎር መጻህፍት፣ ግማሽ ያህል የሚሆኑትን፣ ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ፎቶ ኮፒና ፕሪንት እያደረግን እንድንወስድ የሰጡን፣ ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ናቸው። በእኔ እምነት ከዚህ የበለጠ እርዳታና ስጦታ የለም ! እግዚአብሄር ይስጥልኝ !!

በአሳለፍኩት የትምህርት ውጣ ውረድ ሁሉ ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ከኔ ሳትለይ፣ ፍጹም በሆነ ርህራሄና ደግነት፣ አብራኝ ታግላለች፤ ወጥታለች፤ ወርዳለች። በተለይ እንድማር ያላትን ጽኑ ፍላጎትና አቋም ሳስበው፣ ከሁሉም በላይ ይደንቀኛል። ይህን አስተሳሰቧን በተለየ

አይን እንድመለከተውም ያስገድደኛል !! በመሆኑም፣ ባለቤቴን ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ ገዛኸኝን እጅግ አድርጌ አመሰግናታለሁ።

ማውጫ

ይዘት

ገጽ

አጠቃሎ I

ምስጋና II

ምዕራፍ አንድ፣ መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ..... 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶችና አስፈላጊነት 3
1.3 የምርምር ጥያቄዎች 6
1.4 የጥናቱ አላማዎች..... 6
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች..... 7
1.6 የጥናቱ ወሰን 8
1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች 8
1.8 የጥናቱ አደረጃጀት 10
1.9 የቁልፍ ቃላት ብያኔዎች 10

ምዕራፍ ሁለት ፡- የሰሜን ወሎ ማህበረሰባዊና መልክአ ምድራዊ ዳራዎች...16

2.1 ማህበረሰባዊ ዳራ..... 16
2.2 መልክአ ምድራዊ ዳራ 26
2.3 የርሀብ ዘመናት በሰሜን ወሎ አካባቢዎች 31

ምዕራፍ ሶስት፡- ክለሳ ድርሳናት.....35

3.1 የተጠኑ ጥናቶች ዳሰሳ 35
3.2 ጽንሰ-ሀሳባዊ ብያኔዎች..... 38
3.2.1ፎክሎር፤ ስነቃልና ቃልግጥም 38
3.2.1.1 ፎክሎር..... 38
3.2.1.2 ስነቃል 42
3.2.1.3 ቃልግጥም..... 43
3.3 ክዋኔ 46
3.4 አውድ 49
3.5 ማህበራዊ ሩይዳዎች 50
3.6 ንድፈ-ሀሳባዊ ማዕቀፎች 54

ምዕራፍ አራት፡- የጥናት አካባቢዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ መቼቶች፣ የምርምር አይነትና የመተንተኛ ዘዴ 59

4.1 የጥናት አካባቢዎች አመራረጥ.....59
4.2 የመስክ ተግባራትና..... 60
4.3 የጥናት አይነት.....65
4.4 የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች.....66
4.4.1 ምልከታ.....66
4.4.2 ቃለመጠይቅ..... 67
4.4.3 ሰነዶች.....68
4.4.4.ቀረጻና ማስታወሻ.....69

4.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች..... 69
4.6 የትንተና ዘዴዎች.....70

ምዕራፍ አምስት፡- የአማርኛ ቃልግጥሞች የክዋኔ ስልቶችና የመከወኛ አጋጣሚዎች.....72

5.1 የአማርኛ ቃልግጥም የክዋኔ ስልቶች..... 72
5.1.1 ባህላዊ ዘፈኖች..... 73
5.1.1.1 አዳሬ ሙናዬ..... 74
5.1.1.2 አማሮዬ..... 75
5.1.1.3 እንከል እንከል..... 76
5.1.1.4 አሆየ..... 77
5.1.2 ባህላዊ ጭፈራዎች..... 78
5.1.2.1 ኮርማ ጋፋ ላሌ..... 79
5.1.2.2 አሲና ጋማየ..... 80
5.1.2.3 ሆይ ላሌ መገና..... 80
5.1.2.4 ገና ነው፤ ገና ነው..... 81
5.1.2.5 እያያ አያ ሚና አበሎ..... 82
5.1.2.6 ሚሌ ወሬን ሀራ / ላልወይ ሰመራ..... 84
5.1.3ቀረርቶ..... 85
5.2 የአማርኛ ቃልግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች..... 86
5.2.1 ሰርግ..... 87
5.2.2 አመት በአላት ወይም ሀይማኖታዊ በአላት..... 87
5.2.3 የስራ አካባቢዎች..... 88
5.2.4 የመዝናኛ ቦታዎች..... 89

ምዕራፍ ስድስት፡- ምደባ እና ትንተና.....90

6.1 ምደባ..... 90
6.2. ትንተና እና ትርጎማ..... 92
6.2.1. የሙገሳና የውደሳ ቃልግጥሞች..... ..93
6.2.1.1. አካባቢንና ሰዎችን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ 94
6.2.1.2. በሬንና ገበሬን የሚያሞግሱና የሚያወዱሱ 109
6.2.1.3. ሴቶችና ወንዶችን የሚያሞግስና የሚያወድሱ.....114
6.2.1.4. እንስሳትን (ላሞችን)የሚያሞግስና የሚያወድሱ 119
6.2.2. ስንፍናን የሚተቹ.....122
6.2.2.1. ሴቶችን ብቻ የሚተቹ.....123
6.2.2.2.. ወንዶችን ብቻ የሚተቹ.....129
6.2.3. ጀግንነትን የሚያበረታቱ፣ ፈሪነትን የሚተቹና የሚነቅፉ ቃልግጥሞች 135
6.2.3.1. አጠቃላይ ጀግንነትን የሚያበረታቱ ቃልግጥሞች..... 136
6.2.3.2. ለታዋቂ ግለሰቦችና ጀግኖች የተገጠሙ ቃልግጥሞች.....143
6.2.3.2.1. ስለ ደጃዝማች ጎበና አመዴ የተገጠሙ..... 144
6.2.3.2.2. ስለ ቀኛዝማች አባተ ሀይሉ የተገጠሙ..... 146
6.2.3.2.3. ስለ አቶ ምስጋን በላይ የተገጠሙ..... 148
6.2.3.3. ፈሪነትን የሚተቹ ቃልግጥሞች.....150
6.2.4.አካላዊ ቁንጅናንና ፍቅርን የሚያሳዩ ቃልግጥሞች..... .155
. 6.2.4.1. አካላዊ ቁንጅናን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች..... 157
. 6.2.4.2. አጠቃላይ የፍቅር ስሜትን የሚገልፁ ቃልግጥሞች..... 169

6.2.5. ብሶትን፤ ቁጭትን፤ ጥላቻንና ማንኳሰስን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች.....173
6.2.5.1. የብሶትና የቁጭት ቃልግጥሞች.....174
6.2.5.2. የጥላቻና የማንኳሰስ ቃልግጥሞች.....185
6.2.6. ከፖለቲካና ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር ተያይዞ የታዩትን ፖለቲካዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚያንፀባርቁ ቃልግጥሞች.....189
6.2.6.1. የፖለቲካ ድጋፍና ተቃዉሞ የተንፀባረቀባቸው ቃል ግጥሞች.....191
6.2.6.1.1. ከደርግ ስርዓት ጋር የተያያዙ የድጋፍና የተቃዉሞ ቃልግጥሞች191
6.2.6.1.2. ኢህአዴግን የሚመለከቱ የድጋፍና የተቃዉሞ ፖለቲካዊ ቃልግጥሞች.....196
6.2.6.1.3. ትዝብታዊ ቃልግጥሞች.....200
6.2.6.2. ሙስናንና አድሏዊ አሰራርን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች.....204
6.2.6.2.1. ከደርግ ጋር የተያያዙ ቃልግጥሞች.....205
6.2.6.2.2. ከኢህአዴግ ጋር የተያያዙ ቃልግጥሞች.....208
6.2.6.3. ጥርጣሬንና ስጋትን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች.....210
6.2.6.4. የእርስ በርስ ጦርነትና ታሪካዊ ሁኔታዎችን የሚያስታዉሱ ቃልግጥሞች.....212
6.2.6.4.1. በደርግና በኢህአዴግ መካከል የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች.....212
6.2.6.4.1.1. ደርግን የሚደግፉና የሚቃወሙ ቃልግጥሞች....212
6.2.6.4.1.2. ኢህአዴግን የሚደግፉ የሚቃወሙ ቃልግጥሞች..... .216
6.2.6.4.1.3. ትዝብታዊ ቃልግጥሞች.....218
6.2.6.4.2.የኢትዮ- ኤርትራን ጦርነት የሚመለከቱ ቃልግጥሞች...223
6.2.6.4.3. ታሪካዊ ሁኔታዎችንና እውነታዎችን የሚያስታውሱ ቃልግጥሞች.....228
6.2.7.ከድርቅና ከርሀብ ጋር ተያይዞ የታየውን ሁኔታ የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች.....239
6.2.7.1. ድርቅ ጠቋሚ ቃልግጥሞች.....240
6.2.7.2. የርሀብ ወቅት ቃልግጥሞች.....242
6.2.7.3. ድህረ ርሀብ ቃልግጥሞች.....247
6.2.8. ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ ቃልግጥሞች.....251
6.2.8.1. ስደት.....251
6.2.8.2. በሽታ.....255
6.2.8.3. ግንባታ.....256
ምዕራፍ ሰባት ፡ ማጠቃለያና አስተያየት.....258
7.1 ማጠቃለያ 258
7.2 አስተያየት.....265
ማጣቃሻ መፃህፍት.....267
ሀ. በእንግሊዝኛ የተፃፉ 267
ለ. በአማርኛ የተፃፉ.....270
አባሪዎች፡-..... 272

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ ..... .272
አባሪ ሁለት፡- የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች 273
አባሪ ሶስት፡- የእንግሊዝኛ እና የአማርኛ ሙዳየ ቃላት 356
አባሪ አራት፡- ከመረጃ አቀባዮች ጋር የተደረጉ ቃለ- መጠይቆች 364
አባሪ አምስት፡- ልዩ ልዩ ፎቶ ግራፎች 383
አባሪ ስድስት:- አዋጅ 392

ምዕራፍ አንድ ፡- መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

የስነቃል ጥናት በአፍሪካ እንዲሁም በኢትዮጵያ መካሄድ የጀመረው ከ19ኛው ምዕተ አመት አጋማሽ /ማለትም ከ1850ዎቹ/ ጀምሮ እንደ ሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ:: የጥናት ስራውንም የጀመሩት ከሌሎች ሀገሮች የመጡ ተመራማሪዎች እንደሆኑ Finnegan (1970 እና Okpewho (1992) ያስረዳሉ:: Finnegan (1970:27-28) አንደገለፁት አውሮፖውያን የአፍሪካውያንን ስነቃል ማጥናት ሲጀምሩ አላማቸው ለንፅፅራዊ ጥናት የሚሆኑ ስነቃሎችን /ማለትም ተረቶችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን፣ ዘፈኖችን /ቃልግጥሞችን/፣ ወዘተ./ ለመሰብሰብ ስለነበር እነዚህን ቴክስቶች ሲሰበስቡ የነበራቸውን ማህበራዊ ፋይዳ እና ስነፅሁፋዊ ጠቀሜታ እንዲሁም አውዳዊ መረጃ ለመሰብሰብ የተደረገው ጥረት አነስተኛ ነበር::

Okepwho (1992:12-15) እንደሚሉት ፣ የአፍሪካን የስነቃል ጥናት ለማየት ስንነሳ እስከዛሬ የነበሩትን የጥናት ሁኔታዎች መመርመር አስፈላጊ ነው ካሉ በኋላ የተመራማሪዎቹ ፍላጎት ባህልን፣ ህብረተሰብንና ስነፅሁፍን ለማጥናት ስለነበረ ይከተሏቸው የነበሩት መንገዶችና እይታዎች ከስነቃሉ አፈጣጠርና ባህሪ ጋር የተዛመደ አልነበረም:: አያይዘው ሲገልፁም፣ ስነቃሉን በተጠቃለለ /summarized/ ሁኔታ ስለሚሰበስቡት ውበቱንና ስልቱን ለማሳየት ፍላጎት ስላልነበራቸው የጥናት ሂደቱ የአፍሪካን ስነቃላዊ ሀብትና የፈጠራ ችሎታ በእጅጉ ጎድቶታል በማለት ይተቻሉ::

በአውሮፖውያን የተጀመረው የስነቃል ጥናት እያደገ ሂዶ በአፍሪካውያን የስነቃል ተመራማሪዎች መጠናት ሲጀምር ግን ስነቃልን ለንፅፅር ከማጥናት ይልቅ ለውበቱና ለፈጠራዊነቱ ማጥናት ይበልጥ እየታወቀ እንደመጣና በዚህ ደረጃ ከሚጠቀሱት መካከልም የናይጄሪያው፣ Adeboye Babalola “የዩሩባ ኢጃላ ቅርፅና ይዘት”፤ (1966) የDaniel P. Kunen፣ “የባሶቶ የጀግና ግጥም”፤ (1971) ጥቂቶቹ ሲሆኑ፣ እነዚህ ተመራማሪዎች የአፍሪካን የስነቃል ጥናት ወደተሻለ ደረጃ እንዳደረሱት (Okpewho 1992:12-15) ያስረዳሉ::

ይህንን ሀሳብ በመደገፍም Finnegan (1970:43) የሚከተለውን ፅፈዋል:: “... በጣም ወጥ ስራ መሰራት የተጀመረው በራሳቸው ቋንቋ ውስጥ ያለውን ስነቃል በሚያጠኑ አፍሪካውያን ነው:: እነዚህ ተመራማሪዎች ሌሎች አውሮፓውያን ተመራማሪዎች ሳያስተውሉት የቀሩትን

መመርመር በመቻላቸው ገለፃቸውና ትንተናቸው ስፋትና ጥልቀት ያለው ለመሆን ችሏል›ይላሉ፡፡

ከስነቃል ጥናት ጋር ተያይዞ በተፈጠረው አጋጣሚና ሁኔታ ቃልግጥምን ለይተው ለማጥናት የሞከሩት የሙዚቃ ባለሙያዎች እንደሆኑ Finnegan (1970:42) ሲያብራሩ እነዚህ ተመራማሪዎች በርካታ የዘፈን ግጥሞችን መሰብሰብና ማጥናት በመጀመራቸው ትኩረት ያላገኘውን የስነቃል ዘርፍ /አይነት/ የማጥናት ተነሳሽነት በወቅቱ ታይቷል ይላሉ:: በተለይ ስለቃልግጥም ያለመጠናት ሁኔታና ስለዘርፉ ያላቸውን ስሜት በሌላው መፅሀፋቸው መቅድም ውስጥ Finnegan (1977፣x-xii) የሚከተለውን ብለዋል “... አስደሳች ነገር ግን የተረሳ /የተተወ/ መስክ ነው::... መስኩ በጣም የበለጸገ (rich field) በመሆኑ የተካኑ ምሁራን በራሳቸው ቋንቋ በሚያደርጉት የተሟላ የጥናት ሁኔታ የቃልግጥምን ጥናት ወደተሻለ ደረጃ ሊያደርሱት ይችላሉ” በማለት ይገልፃሉ::

የአፍሪካ ስነቃልና የፈጠራ ሁኔታ ከአውሮፖ ስነቃልና ፈጠራ ጋር ሲነፃፀር በምንም የማይተናነስ መሆኑን በጠቆሙበትመ ፅሀፋቸው ቋንቋዎችን ለማጥናት የተጀመረው እንቅስቃሴ ዝርው ቅርፆችን ብቻ ከመሰብሰብና ከማጥናት ወደ ቃልግጥም ጥናት እንደተሸጋገረና በዚህም የፍቅር፣ ምፀታዊ፣ የጦርነት፣ ኤፒክ፣ ሙሾ፣ ትምህርታዊ፣ ሀይማኖታዊ ቃልግጥሞችን /ዘፈኖች/ ሰብስቦ በማጥናት Seidle የተባለው ተመራማሪ ዘርዝሮ ለማሳየት ያደረገውን ጥረት በወቅቱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና የአፍሪካን ስነፅሁፋዊ ቅርፆች ያስተዋወቀበት እንደነበር አመልክተዋል Finnegan [1970 32]፡፡

ወደ ሀገራችን የስነቃል አሰባሰብና የጥናት ሁኔታ ስንመለስ ባንድ በኩል፤እንደሌላው የአፍሪካ ሀገር የኛም በውጭ ሀገር ሰዎች መሰብሰብና መጠናት እንደጀመረ፤በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች እሰበሰቡ ማሳተም እንደጀመሩ ፈቃደ(2001 እና1991) ይገልፃሉ፡፡ ሁኔታውን ሲያብራሩ ... የአፍሪካ ስነቃል ጥናት የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ሁሉ፤የኢትዮጵያም ስነቃል በአውሮፓ መፅሄቶች መታተም የጀመረው በዚሁ ምእተ አመት ነው(2001፡49) ይላሉ፡፡ከዚህ በተጨማሪ፤ በሌላ ስራቸው ሲገልጹም ቀንቀዎቹ የማይገቡዋቸው የውጭ ሀገር ሰዎች እየሰበሰቡ ከሚያሳትሙ ይልቅ የባህሉ ባለቤት የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦችና ተመራማሪዎች ቢያጠኑትና፤ስብስቡንም ከጥናቱ ጋር አያይዘው ቢያቀርቡት ቅርስ ማስቀረት ይሆናል በማለት ፈቃደ(1991፡45) ያስረዳሉ፡፡

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶችና አስፈላጊነት

ለጥናት በተመረጠው አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጠ የኖረ በመሆኑ፣ ብሶቱን፣ ጭንቀቱን፣ በአጠቃላይ ሀዘንና ደስታውን የሚገልፅባቸውን ቃልግጥሞች እየፈጠረ ሲናገር ቆይታል:: አካባቢው፣ ከመሀል ወደ ሰሜን፣ ከሰሜን ወደ መሀል፣ ለተደረጉ የእርስ በርስ እና የመከላከል ጦርነቶች ሁሉ የመሸጋገሪያና የጦርነት ቀጠና እየሆነ የኖረ አካባቢ ነው:: እንዲሁም በሀገራችን የተከሰቱት የድርቅና የርሃብ አደጋዎች በተለያዩ ጊዜያት ደጋግመው ያጠቁት አካባቢ ነው:: እንደሌላው የሀገራችን ክፍል ሁሉ፣ ይህ አካባቢ ልዩ ልዩ ገዥዎችም ተፈራርቀውበታል:: በነዚህ ሁሉ ገጠመኞች ማህበረሰቡ የፈጠራቸው ቃልግጥሞች ተሰብስበው አልተጠኑም ወይም አልተሰነዱም:: በዚህ ምክንያት ቃልግጥሞቹ እየተረሱ፣ በሂደትም ከትውስታ ውጭ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው:: በተለይ አሁን ባለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ቃልግጥሞቹ የሚከወኑባቸው ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎች እየቀሩና እየተለወጡ ስለሆነ፣ ቃልግጥሞቹ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉበት እድልና ሁኔታ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል:: ለምሳሌ፣ የሰርግ ስነ ስርአት ከባህላዊ ወደ «ዘመናዊ» እየተለወጠ በመምጣቱ ከባህላዊ ዘፈኖች ይልቅ ቴፕ ማጫወት እየተለመደ ነው:: በእርሻ ማሳ ጥበት የተነሳ፤ በደቦ ማረስ፣ በወንፈል ማረምና ማጨድ እየቀረ ነው:: እንዲሁም ለሁለትና ለሶስት ቀን ይደረግ የነበረው የውቂያ ተግባር፣ ከአንድ ቀን የማይበልጥ እየሆነ ነው:: እነዚህና ሌሎች ችግሮች ለቃልግጥሞቹ መረሳት ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው:: በነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ምክንያት (ለምሳሌ፣የትምህርት መስፋፋት፣ ስደት፣ «የከተማ ኑሮ»፣ ወዘተ.) በአጠቃላይ የስነቃል በተለይ የቃልግጥም ፈጠራና ተስተላልፎው፣ እየቀረና እየተረሳ መጥቷል:: ስለሆነም፣ እስከዛሬ የተፈጠሩት ቃልግጥሞች ከመረሳታቸውና ከመጥፋታቸው በፊት መሰብሰብና ማጥናት፣ የማህበረሰቡን ማንነት ለማወቅና ለማጥናት፣ የማህበረሰቡን ያለፈ ታሪክ ለማስታወስና ለማወቅ፣ ያለፈውንና አሁን ያለውን ሁኔታ ለይቶ በማወቅ፣ ማህበረሰቡን ለሚመሩና ለሚያስተዳድሩ አካላት ጠቃሚ መረጃ ስለሚሆን፣ ጥናቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: ይህንን በሚመለከት አንዳንድ የስነቃል ወይም የፎክሎር ተመራማሪዎች ልዩ ልዩ አስተያየቶች ይሰጣሉ::ለምሳሌ፣ እንደ ጌቱ (2001፣3) አገላለጽ:-

> ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የቃልግጥሞቹ ስነጥበባዊና አውዳዊ አገልግሎት እየደበዘዘና እየጠፋ ነው:: ስለዚህ፣ ቃልግጥሞችን ሰብስቦ ከወቅት አኳያ ያላቸውን ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ ማጥናቱ የገጠሩን ህዝብ

> መንፈሳዊና ቁሳዊ አስተሳሰብ ለመረዳትና ከዘመናዊ ... እውቀት ጋር በወጉ ለማስናኘት ከፍተኛ ግልጋሎት አለው። ... ግጥሞቹ ለታሪክ፣ ለባህል፣ ለትምህርት፣ ለስነልቦና፣ ለስነ ጽሁፍና ለቋንቋ የጥናት መስኮች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታመናል። ... ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቃልግጥሞችና ባህላዊ ዘፈኖች ለልማት፣ ለመልካም አስተዳደር፣ ለፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጥናቶች ... መረጃወችን እያበረከቱ ለመሆኑ በጥናትና ምርምር ተደርሶበታል በማለት ያስረዳሉ።

Ben Amos (1982፣ 133-134) እንደሚሉት ደግሞ፣ "አፍሪካ ውስጥ በሚገኝ በእያንዳንዱ ባህል ውስጥ ያለውን የፎክሎር ተግባቦት መርሆዎችና ስነቃላዊ ቅርፆችን ለመለየት በምንሞክርበት ጊዜ የቅርፆቹን ወይም የስነቃል አይነቱን አእምሮአዊ፣ ገላጭ እና ማህበራዊ ገፅታዎችን ለይተን በመተንተን መጀመር አለብን" ይላሉ:: የስነቃል አይነቱ ስያሜውና ምድቡ እንዴት እንደሆነ፣ አስቀድሞ መለየት አስፈላጊ ይሆናል:: ስያሜዎች ሚና ስላላቸው ባህላዊ ፅንሰ ሀሳቦችንና ፋይዳዎችን ለማንፀባረቅ ይረዳሉ:: ከዚህ አኳያ የአማርኛ ቃልግጥሞች በአብዛኛው መከሰቻቸው ዘፈን ፣ ቀረርቶና፣ ጭፈራ፣ ወዘተ. ስለሆነ፣ ይህንን ተከትሎ ለማጥናት መሞከር አስፈላጊ ነው ማለት ነው:: Ben Amos (1982፣149) ገላጭ ገፅታዎችን በሚመለከትም፣ የስነቃል አይነቱ በሚከወንበት የዜማ ስልት፣ በመክፈቻና በመዝጊያ ቀመሩ፣ ወይም በቴክስቱ፣ በስልቱ፣ በጭብጥና መዋቅሩ፣ እየተለየ መጠናት እንዳለበት በሰፊው ያስረዳሉ::

ከዚህ አንፃር ለጥናት በተመረጠው አካባቢ እስካሁን የተገጠሙት ቃልግጥሞች በተሟላ ሁኔታ ተስብስበው፣ የተጠናከረ መረጃ ያለው ትንተና የቀረበባቸው አይደሉም:: ስለሆነም፡- አንደኛ፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ በሰሜን ወሎ ቆቦ ወረዳ ተወልጀ ያደግሁ በመሆኑና ቤተሰባዊ ዳራየና አስተዳደጌ፣ ከአርሶ አደር ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ስለነበረ፣ በአካባቢው ሲከወኑ የነበሩትን፣ የዘፈን፣ የጭፈራ፣ የቀራርቶ፣ ወዘተ. ቃልግጥሞችን እየሰማሁ አድጌያለሁ።

ሁለተኛ፣ እነዚህ አካባቢዎች በታሪክም ሆነ በባህል እንደሚታወቀው ተደጋጋሚ የገበሬዎች የአመፅ ተግባራት እና የቡድን ዘመቻዎች ይካሄዱባቸው የነበሩባቸው አካባቢዎች ናቸው:: የጁ ከራያ ጋር፣ ራያ ከዋግ ጋር፣ እንዲሁም የጁና ራያ ከአፋር ጋር፣ ግጭቶች ሲያደርጉ ኑረዋል። በየዘመቻዎችም ሆነ በየአመፆቹ የተሳተፉት ግለሰቦች፣ በአካባቢው እንደ ጀግና የሚቆጠሩ ሰዎች፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ባሉት ዘፋኞች፣ ጨፋሪዎች፣ ወዘተ. አማካኝነት

ግጥም እየተገጠመ፣ ይዘፈንላቸዋል፣ ይነገርላቸዋል፣ ይወደሳሉ፣ ይሞገሳሉ። በደግነት፣ በለጋስነት፣ በጎበዝ ገበሬነት፣ ወዘተ. የሚታወቁ ግለሰቦችም ይዘፈንላቸው፣ ይገጠምላቸው እንደነበር አስታውሳለሁ።

ሶስተኛ፣ በተለይ በራያ አካባቢ ከሚታወቁት የባህል ተጫዋቾች (አዝማሪዎች) መካከል አንዱ አቶ ተገኘ ገባይ ነው። ይህ ሰው በአካባቢው የሚታወቀው በድምፀ ማማርና በግጥሙ ይዘት ብቻ ሳይሆን እንደማንኛውም የህብረተሰቡ አባል የራሱ መሳሪያ (ትጥቅ) ፣ በቅሎና ፈረስ የነበረው፣ የሚጫወትባቸው ቦታዎችም የተመረጡ፣ የሚያወድሳቸውና የሚገጥምላቸው ግለሰቦችም በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ በአንድ ተግባር በበጎ የሚታወቁ፣ ወዘተ. ነበሩ። በተለይ በሁለቱ ራያዎች ውስጥ የነበሩትን ስመ-ጥር ሰዎች በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ውስጥ እነማን እንደነበሩ ያስታውሳል፣ ያውቃል። ለእንደነዚህ ያሉ ሰዎች የገጠማቸው ግጥሞች፣ በአጠቃላይ ስለ አካባቢው የተጫወታቸው ግጥሞች አልተሰበሰቡም።

አራተኛ፣ ከ1970ዎቹ ጀምሮ በሰሜን ወሎ አካባቢዎች / በተለይ ከትግራይ ክልል ጋር ኩታ-ገጠም በሆኑት አካባቢዎች/ በወቅቱ ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ ይባሉ በነበሩት ታጋዮችና፣ በመንግስት ወታደሮች፣ እንዲሁም በአካባቢ ህዝባዊ ሰራዊቶች (ዞብል-አምባ፣ ዘንዶ እና አዞ ሰራዊቶች) መካከል በየጊዜው ውጊያ ይካሄድ ነበር። ይህ የእርስ በርስ ጦርነት፣ በአመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ይደረጋል። ጦርነቱም እስከ 1983 ዓ.ም ዘልቆ የመንግስትን ለውጥ አስከትሏል። ይህንን የርስ በርስ የጦርነት ታሪክ የዘገቡ፣ የታዩትን ሁኔታዎች የሚያንፀባርቁ፣ ቃልግጥሞች በብዛት ተፈጥረዋል። እነዚህ ግጥሞች አጠቃላይ የነበረውን ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁኔታ መዝግበው የያዙ የታሪክ ማስረጃዎች ቢሆኑም፣ ከተፈጠሩበት አጋጣሚና ሁኔታ አንፃር፣ ተሰብስበው ያልተጠኑ ናቸው።

አምስተኛ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታየ ባለው የባህል ለውጥ እና ዘመናዊ የግብርና እንቅስቃሴ ምክንያት፣ ከዚህ በፊት ይከወኑ የነበሩት ቃልግጥሞች እየተረሱ፣ እየተለወጡና እየጠፉ ሊሄዱ ይችላሉ። ይህ ከመሆኑ በፊት ቃልግጥሞቹን ሰብስቦና ሰንዶ ማስቀረት ጠቀሚ መሆኑን በመረዳትና፣ በተለያዩ ጊዜያት ወደ አካባቢው በምመላለስበት ጊዜ በየአጋጣሚው የሰማኋቸውና ለመሰብሰብ የሞከርኳቸው ቃልግጥሞች ሲታዩ ገላጭ፣ ቁጥብ፣ ስሜት የሚስቡ እና የቋንቋ አጠቃቀማቸው ቅኔያዊ፣ ዘይቤያዊና አካባቢዊ ዘየ ያላቸው መሆናቸውን አስተውያለሁ። የስነቃል ተመራማሪዎችም እንደሚሉት የራሳቸውን ባህል ለማጥናት የሚሞክሩ፣ ከሌሎች

የተሻለ ጥናት ሊያቀርቡ የሚችሉ መሆኑን ያስረዳሉ። ለምሳሌ (Finnegan፣ 1970፣ 43) እንደሚሉት:-

> *... በጣም ወጥ የጥናት ሰራዎች መታየት የጀመሩት በራሳቸው ቋንቋ ውስጥ ያለውን ስነቃል በሚያጠኑት ... አፍሪካዊያን ተመራማሪዎች ጥናቶች ውስጥ ነው:: ... ካጋሜ፣ በሩዋንዳ ቃልግጥም፣ ባባሎላ በአደን ቃልግጥሞች፣ ... ኒሴትያ በአካን መዚቃና ስነዕሁፍ፣ ... ላይ ያደረጉት ምርምር ሌሎች ቀደምት ተማሪዎች ያልጠበቁትንና ሳያስተውሉ የቀሩትን መመርመር ችለዋል:: በማህበራዊና በስነዕሁፋዊ ገለፃዎቻቸው አማካይነት ጥናታቸው ጥልቀት እንዲኖረው አድርገዋል ይላሉ::*

1.3 የምርምር ጥያቄዎች

በመስክ የሚሰበሰቡት ቃልግጥሞች በየጊዜው በአካባቢው የታዩትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህላዊ እንቅስቃሴዎች ነፀብራቅ ስለሚሆኑ፣ ስለአካባቢው ማህበረሰብ ያለፉ ታሪክ፣ ባህል፣ አመለካከት፣ እምነትና አስተሳሰብ፣ ለማወቅና ለማጥናት እንደ አንድ የመረጃ ምንጮች ይሆናሉ:: በመሆኑም፣ጥናቱ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል::

1. ቃልግጥሞች በምን በምን ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው?
2. ቃልግጥሞቹ የማህበረሰቡን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረ-ባህላዊ፣ እንዲሁም፣ ተፈጥሯዊና ሰው-ሰራሽ ችግሮች አንፀባርቀዋል?
3. ማህበረሰቡ ቃልግጥሞቹን የሚከውንባቸው አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው?
4. ቃልግጥሞቹ የሚከወኑባቸው የክዋኔ ወይም የዜማ ስልቶች ምን ምን የሚባሉ ናቸው?
5. በቃልግጥሞቹ ውስጥ የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀም እንዴት ነው? የሚሉት ጥያቄዎች በጥናቱ የሚመለሱና የሚታዩ ናቸው።

1.4 የጥናቱ አላማዎች

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች የተነገሩትን ቃልግጥሞች በብዛትና በአይነት መሰብሰብ፣ መመደብ፣ እና ትንተና ማድረግ ነው። ይህንን ተግባር ለማሳካት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር፣ ነገር ግን፣ እርስ በርስ የተያያዙ አላማዎች አሉት::

1.የሚሰበሰቡት ቃልግጥሞች በምን በምን ጉዳዮች ላይ ተመስርተው እንደተገጠሙ መመርመርና ምደባ አድርጎ መግለፅ፣

2.ቃልግጥሞቹ የሚያንፀባርቁትን ማህበራዊ፤ ፖለቲካው፤ ኢኮኖሚያዊ፤ እና ታሪካዊ እውነታዎችን ማሳየት፤

3.ቃልግጥሞቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ስልቶች ለይቶ ማሳየት፣

4. በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ያሉትን ቃልግጥሞች አውዳዊ መረጃን መሰረት አድርጎ መተንተን፤

5. በቃልግጥሞቹ ውስጥ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም በትንተናው ውስጥ በማካተት፣ አላማቸውንና ፋይዳቸውን ማሳየት ናቸው።

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ቃልግጥም እንደማንኛውም የስሜት መግለጫ፣ በለት ተለት ህይወታችን ውስጥ የሚያጋጥመንን ችግር፣ የሚሰማንን ስሜት፣ ለመግለፅ ወይም ለማሳየት ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ ነው ማለት ይቻላል። ለጥናት በተመረጠው አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ምናልባት በየዘመኑ ካጋጠመው ችግር ሳቢያ ይመስላል፣ ሀሳቡን በቃልግጥም የመግለጥ ልማድ እንዳለው፣ በተለያየ አጋጣሚ ለመሰብሰብ ከሞከርኳቸው ቃልግጥሞች ለመረዳት ችያለሁ። በአካባቢው ለሚታዩ ክስተቶች ገላጭ የሆኑ ቃላዊ ግጥሞች የመፍጠር ልማዱ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ፣ እነዚህን ግጥሞች ሰብስቦ ማጥናትና መሰነድ በተከታይ ለሚደረጉ ተመሳሳይ ጥናቶችና፣ በሌሎች የሙያ ዘርፎች ለሚደረጉ ጥናቶች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ከዚህ አንፃር ቃል ግጥሞቹ ማህበረሰቡ ያለፈባቸውን ልዩ ልዩ የህይወት አጋጣሚዎች ሊያንፀባርቁ ስለሚችሉ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

1. ቃልግጥሞቹ፣ ለታሪክ፣ ለፖለቲካ፣ ለማህበራዊና ለባህል፣ ተመራማሪዎች የማህበረሰቡን ታሪክ፣ ማህበራዊ ህይወት፣ ማንነት፣ ባህልና ቋንቋ፣ እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት ቃልግጥም ፈጣሪዎችን ጥበባዊ ፈጠራና ምናብ ለማጥናት ለሚፈልጉ ሁሉ እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ሊያገለግሉ ይችላሉ፤

2. የአካባቢው ማህበረሰብ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቹ በቃልግጥሞቹ ውስጥ ሊንፀባረቁ ስለሚችሉ፣ በሂደትም የማህበረሰቡን ስነልቦና እና ፍላጎት ተረድቶ አካባቢውን ለማልማት በሚደረግ እንቅስቃሴ ጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፤

3. በትምህርት ተቋማት ለሚሰጡ የስነፅሁፍና የስነቃል ኮርሶች ጠቃሚ የመረጃ ምንጭ ሊሆን ይችላል:: እንዲሁም፣ በማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ሂደት፣ ቃልግጥሞቹ እንደ ይዘት ተካትተው ሊቀርቡ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጠቃሚታ ይኖረዋል::
4. ስብስቡ (መረጃው) በተለይ ለስነግጥምና ለቃልግጥም፣ በአጠቃላይ ለስነፅሁፍና ለስነቃል ንፅፅራዊ ጥናቶች፣ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
5. የቃልግጥሞቹ ስብስብ ለዘመናዊም ሆነ ለባህላዊ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ለጥበባዊ ስራቸው እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ በመሆን፣ ጥናቱ ሊጠቅም ይችላል ተብሎ ይታመናል:፡

1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ትኩረት አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ በቃል እየተፈጠሩ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የኖሩትን ቃልግጥሞች በመሰበሰብና በመተንተን ላይ የተወሰነ ነው:: የጥናቱ አካባቢዎችም በአማራ ብሄራዊ ክልል፣ በሰሜን ወሎ ዞን፣ በሚገኙት አጎራባች ወረዳዎች ውስጥ ቆቦ፣ ሀብሩና ጉባላፍቶ ናቸው::

ይህ ጥናት በእነዚህ አካባቢዎች፣ በተከታታይ በታዩት የፖለቲካ ለውጦች እና እንቅስቃሴዎች፣ በነበሩት የርስ በርስ ግጭቶች፣ በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱት የድርቅና የርሀብ አደጋዎች፣ ወዘተ. ሳቢያ፣ ተፈጥረው የተነገሩ ቃልግጥሞችን ሰብስቦ በመመደብና በመተንተን፣ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ያለመ ስለሆነ፣ በቀብር ስነ ስርአት ላይ፣ አልቃሽና አስለቃሽ እየደረደሩ የሚከውኗቸውን ግጥሞች፣ የውቂያ፣ የአጨዳ፣ የጥበቃ፣ የልመና፣ የልጆች ዘፈኖችን (ሆያሆየ፣ ምሻምሾ፣ ሶለል)፣ ሀይማኖታዊ ግጥሞችን፣ አይመለከትም:: እነዚህ ቃልግጥሞች አንዳንዶቹ በተለያየ ደረጃ በተናጠል ጥናት ሲደረግባቸው የቆዩ በመሆኑና፣ በየአካባቢውም የተለያዩ ሊሆኑ ይችላል ብሎ አጥኝው ስለሚገምት፣ እንደ አንድ የጥናት ርዕስ፣ ለብቻ ተለይተው ቢጠኑ የተሻለ ስለሚሆን፣ በዚህ ጥናት አይካተቱም፡፡

1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በሁለቱ ዙር የመስክ ስራ ወቅት አንዳንድ ችግሮች አጋጥመው ነበር፡፡ በተለይ በመረጃ አቀባዮች በኩል የታዩት ችግሮች የሚከተሉት ነበሩ፡፡ አንደኛው ፍርሀት ነው፡፡ በአካባቢው ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ምክንያት፣ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ቃልግጥሞች ለመናገር መፍራት ይታይ ነበር፡፡ መስከኛውን ጭምር በመጠራጠርና በመፍራት እንደነዚህ አይነት ግጥሞችን ብዙዎቹ ላለመናገር ይፈልጉ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ወገናዊነት ባለው ሁኔታ እየለዩ ይናገሩ ነበር፡፡ ይኸውም፣ አሁን ያለውን መንግስት በማሞገስና በማወደስ፣ ወይም

በመተቸት፣ የቀደሙትን በማወደስና በመደገፍ ላይ የሚያተኩር ይዘት ያላቸውን ቃልግጥሞች ብቻ እየመረጡ ይናገራሉ፡፡

ሁለተኛው፣ የማስታወስ ችግር ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ይነገሩ የነበሩትን ቃልግጥሞች መረጃ አቀባዮች በቀላሉ እያስታወሱ ለመናገር ይችገሩ ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለማስወገድ ለአንዳንዶቹ የሚፅፉበት ወረቀትና እስክርቢቶ በመስጠት፣ ግጥሞቹ ትዝ ሲሏቸው፣ እየጻፉ እንዲይዙ በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ ተችሏል፡፡

ይህ አሰራር፣ በተለይ መርሳና ቆቦ ላይ በሰፊው ጠቅሟል፡፡ሶስተኛው ችግር፣ የበአል ቀናት (በተለይ ጥምቀት) በተመሳሳይ ቀን፣ በሁሉም አካባቢዎች ስለሚከበር፣ በሁሉም ቦታ ተገኝቶ መረጃ መሰብሰብ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሁለት ቴፖች፣ ወልዲያና ቆቦ ዙሪያ የነበረውን የጭፈራ ግጥሞች በረዳቶች አማካኝነት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

አራተኛው ችግር የነበረው ‹‹ ግጥም መሰብሰብ ምን ያደርጋል? ይኸ ደግሞ ትልቅ ጉዳይ ነው እንዴ?›› በሚል ስሜት ለጉዳዩ ትኩረት መንፈግና ችላ ማለት ነበር፡፡ ይህንንም የሚሰበሰበው መረጃ ለባህል፣ ለታሪክ፣ ወዘተ. ጥናት ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በማስረዳትና በማሳመን ችግሩን ለማለፍ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ችግሮች በተጨማሪ የገንዘብ ችግር አጋጥሞ ነበር፡፡ ወልዲያ ላይ የወንድሜን ቤት ለማረፊያነት ባላገኝ ኖሮ፣ ከቆቦ እስከ መርሳ እየተዘዋወሩ መረጃ መሰብሰብ አስቸጋሪ ይሆን ነበር፡፡ እነዚህን ችግሮች በመቋቋም ከላይ የተጠቀሰውን ያህል የቃልግጥም መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በሁለት ዙር የተሰበሰቡትን ቃልግጥሞች አጣርቶ መፃፍ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም፣ በካሴት የተሰበሰቡትን ወደ ወረቀት በመገልበጥ ሂደት፣ አንዳንድ ነገሮችን ለማስተካከል ተሞክሯል፡፡ ለምሳሌ የቀረርቶ ግጥሞቹ ወደ ወረቀት ሲገለበጡ፣ ሁለትና ሶስት ቀረርቶ የሚያሰሙ ግለሰቦችንና፣ ግጥም የሚያቀብሉ ታዳሚዎችን ግጥሞች፣ ለየብቻ ሳይሆን፣ ባንድ ላይ ተጽፈዋል፡፡ እንዲሁም፣ በጭፈራ ላይ የተሰበሰቡትንም፣ ጭፈራውን የሚያወጡት ወጣቶችና፣ የጭፈራ ቡድኖቹ የተለያዩ ስለነበሩ፣ በየቡድኑ ከተቀዱት ካሴቶች ውስጥ፣ የጭፈራው አይነት ቶሎ ቶሎ በመለወጡ፣ የግጥም ድግግሞሽ ስለነበረው፣ በተቻለ መጠን ድግግሞሹን በማስቀረት ለመገልበጥ ተችሏል፡፡

ግጥሞቹን በወረቀት ላይ በምጽፍበት ጊዜ፣ አንዳንድ የአካባቢ ዘየ ቃላት ይታዩባቸው ስለነበር፣ በተቻለ መጠን እንዳሉ አንዲጻፉ ተደርጓል። በትንተናው ውስጥ ትርጉማቸው እየተብራራ ቀርቧል። በግጥሞቹ ውስጥ በብዛት የታዩት የድምጽ ዘዬዎች፣ ‹‹ኽ›› ‹‹ይ›› ናቸው። እነዚህ ድምፆች፣ በቃል መነሻና መድረሻ ላይ በግጥሞቹ ውስጥ ባሉት ቃላት የሚታዩ ናቸው። እነዚህ ድምፆች በሚገኙባቸው ቃላት ውስጥ የተለያየ ሰዋሰዋዊ ተግባር ይዘው ነው የሚታዩት። አንደንዶቹ ብዛትን፣ ሌሎቹ ደግሞ ጾታን የሚያመለክቱ ሲሆኑ ቀሪዎቹ መስተዋድዶች ናቸው።ለምሳሌ፤ጎበዞይ፣ ልጆይ፣ ተባረቀይ፣ ጨኻለይ፣ ኽቤት፣ ኽቀረ፣ በሚሉት ቃላት ውሰጥ በመድረሻ ያለችው /-ይ / በቅደም ተከተል ብዛትና ጾታ አመልካች ስትሆን፣ /ኽ- / ደግሞ መስተዋድድ ናት። ቃላቱ በመደበኛው አጻጻፍ ቢጻፉ፤ጎበዞች፣ ልጆች፣ ተባረቀች፣ ጨኻለይ፣ ከቤት፣ ከቀረ፣ ይሆናሉ።

ሌላው በቋንቋው ድምጾች ውስጥ በቅርጽ ሊከስት የማይችል፣ ግን በአንደበት (በንግግር) ጊዜ፣ የሚሰማ ድምጽ፣ በቃላቱ ውስጥ አጋጥሟል። ለምሳሌ፣ ሌዶ፣ ዳውሪ፣ ደዶ፣ ዳቡሌ ገውስ፣ ዲሌ፣ ወዘተ. በመሳሰሉት ቃላት ውስጥ ያላችው (-ድ) ወይም (ድ-) ድምፅ በአማርኛ ቋንቋ ስነ ድምፅ፣ ባህሪ ንባቢ፣ እግድ፣ ነዛሪ ሲሆን፣ መካነ ንባቢ ደግሞ፣ድዳዊ ነው። ይች ድምፅ ግን፣ በነዚህ ቃላት ውስጥ፣ ነዛሪ ሳይሆን ኢነዛሪ ባህሪ ነው ያላት። ስለዚህ፣ ይችን ድምጽ፣ የነዛሪውን ድምጽ ባህሪ እንደያዘች ተጽፋለች። ልዩነቱ የሚታየው የአካባቢው ሰዎች (በተለይ ፊደል ያልቆጠሩትና ከእርባታ ጋር የተያያዘ ገጠመኝ ያላቸው ሰዎች) ቃላቱን ሲጠሩ ብቻ ነው። አንዳንድ ቃላት በባህሪያቸው አጥብቆ ማንበብን የሚፈልጉ ሆነው ታይተዋል። ለምሳሌ ‹‹በዋ›› የሚለው ቃል ሲነበብ ‹‹ዋ›› መጥበቅ አለበት። እንዲሁም አንዳንድ ቃላት የግጥሙን ዜማ በማይጎዳ ሁኔታ ፊደላቱ ተውጠው ተዕፈዋል። ለምሳሌ፣ ገድሎ፣ ደግሞ፣ ደጅአዝማች፣ ቀኝአዝማች፣ የመሳሰሉትን ቃላት እንደ ቅደም ተከተላቸው፣ ገሎ፣ ደሞ፣ ደጃማይ፣ ቀኛማይ፣ እየተባሉ ተጽፈዋል። ወደፊት በትንተናው ሂደት በሚቀርቡት መንቶዎችና አርኬዎች ውስጥ ያሉትን የተለዩ ቃላት፣ ትርጉማቸውና ዘያቸው እየተብራራ ስለሚቀርብ፣ ወደ ወረቀት የመገልበጥ (Transcription) ስራው በዚህ መንገድ ተከናውኗል።

1.8. የጥናት አደረጃጀት

ይህ ጥናት ሰባት ምዕራፎች አሉት። በእያንዳንዱ ምዕራፍ የተነሱና የተዳሰሱ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።ምዕራፍ አንድ አጠቃላይ የጥናቱ መግቢያ የቀረበበት ነው። በዚህም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ አብይና ንዑስ አላማዎች፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎችና የጥናቱ ወሰን (ገደብ) በዝርዝር

ቀርበዋል፡፡ ከነዚህ ጋር ተያይዞ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች፤የጥናቱ አደረጃጀትና የቁልፍ ቃላት ብያኔዎች አብረው ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት፤ ስለ ሰሜን ወሎ ዞን መልክአ ምድራዊና ማህበረሰባዊ ዳራ የቀረበበት ነው፡፡ ስለማህበረሰቡ ታሪክ፣ ማለትም ለጥናት ስለተመረጡት አካባቢዎች ማህበረሰብ አመጣጥና አሰፋፈር፣ የጥናት ዳሰሳ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ዳሰሳ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ በሰሜን ኢትዮጵያ ስለተካሄዱ የመከላከልና የእርስ በርስ ጦርነቶች በአጭር በአጭሩ ገለፃ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ስለ ርሃብ ዘመናት የተወሰኑ ሀሳቦችን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመልክአ ምድራዊ ዳራው፣ ስለዞኑ የመሬት አቀማመጥ፣ ስለ አየር ሁኔታው፣ ስለ ግብርና እንቅስቃሴዎች፣ ወዘተ. ማስተዋወቂያ ተድርጓል፡፡

ምዕራፍ ሶስት፣ ክለሳ ድርሳናት የተካሄደበት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ በቃልግጥም ላይ የተጠኑ ጥናቶች፣ ስለ ፎክሎር፣ ስለስነቃል፣ እና ስለቃልግጥም፣ እንዲሁም ስለ ክዋኔ፣ አውድ፣ ስለ ቃልግጥም ማህበራዊ ፋይዳዎች፣ጽንሰ-ሀሳባዊ ብያኔዎችና አስተያየቶች፤ከንድፈ-ሀሳብ ማእቀፎች ጋር ቀርቧል፡፡ በንድፈ ሃሳባዊ ቅኝቱ፤ አምስት ያህል ንድፈ ሀሳቦች ከተዳሰሱ በኋላ፣ ለዚህ ጥናት የሀሳብ ማጎልበቻና ጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡት ንድፈ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

ምዕራፍ አራት፣የጥናት አካባቢዎች፤ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችና መቸቶች፤የጥናት አይነትና የትንተና ዘዴዎች የቀረቡበት ነው፡፡ ጥናቱ የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና መሳሪያዎች፤ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰነዶች፣ ማስታወሻና ቀረጻዎች ሲሆኑ፣ መቼቶቹም፣ የበአል ከበራና ሰርግ ናቸው፡፡ በምእራፍ አምስት የቀረበው ስለአማርኛ ቃልግጥሞች የክዋኔ ስልቶችና የመከወኛ አጋጣሚዎች ነው፡፡ የክዋኔ ስልቶቹ፣ ባህላዊ ዘፈኖችና ባህላዊ ጭፈራዎች፣ እንዲሁም ቀረረቶ ሲሆኑ፣ የመከወኛ አጋጣሚዎቹ ደግሞ፣ ሰርግ፣ ክብረ-በአላት፣ ስራና የመዝናኛ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡

ምዕራፍ ስድስት፣ምደባና ትንተና የተደረገበት ነው፡፡ የተሰበሰበው የአማርኛ ቃልግጥም ከማህበራዊ ፋይዳዎች አንጻር ሲመደብ፣ በስምንት አይነት ዋና ዋና የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ በነዚህ ዋና ዋና ምድቦች ስር ንዑስ ምድቦችም አሉ፡፡ በስምንቱ ዋና ዋና ምድቦች ውስጥ ከ600 በላይ መንቶዎች እና አርኬዎች ቀርበዋል፡፡ (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)፡፡ ምድቦቹም፤ የሙገሳና የውደሳ፣ የትችት፣ የጀግንነትና የፍርሀት፣ የቁንጅናና

የፍቅር፣ የማንኪሰስና የቁጭት፣ የፖለቲካና የጦርነት፣ የድርቅና የርሀብ፣ ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያመለክቱ ናቸው።።

በመሆኑም በስምንት ዋና ዋና ምድቦች የተመደበው የአማርኛ ቃልግጥም፣ትንተና እና ትርጎማ የተደረገበት ነው። ትንተናው፣ በእያንዳንዱ መንቶና አርኬ ውስጥ ባለው ይዘትና ጭበጥ፣ላይ አውዳዊ መረጃን መሰረት አድርጎ፣ ከየምድቡ ግጥሞችን እየጠቀሱ በማብራራት፣ ፍቻቸውን ወይም መልክታቸውን በማስረዳት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በትንተናው ሂደት በቃልግጥሞቹ ውስጥ የታየውን የቋንቋ ለማበራራት ተሞክሯል። በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ከ 400 በላይ ቃልግጥሞች ትንተና ተደርጎባቸዋል ማለት ነው። ምእራፍ ሰባት፣ የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት የቀረበበት ነው። በዚህ መሰረት በትንተናው አማካኝነት የተገኙትን ዋና ዋና ሀሳቦች፣ በአጭር በአጭሩ ቀርበዋል።

1.9 የቁልፍ ቃላት ብያኔዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚከተሉት ቃላት በሚከተለው ፍች ጥቅም ላይ ውለዋል:: የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ ወጥነትና ስምምነት እንዲኖር የታሰቡ ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ከተሰበሰበው መረጃ (ቃልግጥም) አንፃር የሚዘፈነው፤ የሚጨፈረው እና የሚቅራራው ግጥም ባብዛኛው ተለይቶ ስለሚታወቅ በትንተናው ሂደት ላይ የሚያገለግሉ ስለሆኑ ነው::

1.ቃልግጥም፡- የዜማ ስልቱና አቀራረቡ እንደ ባህሉ እና እንደ አካባቢው የተለያየ ሆኖ፤ በቃል ተደርሶ በቃል የሚከወን፣ በቃል የሚተላለፍና የሚሰራጭ፣ እንዲሁም እንደገና ተመልሶ በቃል የሚነገር ግጥም ነው:: ቃልግጥምን ለመበየን የሚያስችሉ ሶስት መሰረታዊ መንገዶች አደራረሱ፣ ስርጭቱ እና አከዋወኑ ናቸው:: አንዳንዶቹ ሀገረሰብ ዘፈኖች ይሉታል:: ይህም የፍቅር ዘፈኖችን፣ የልጆች ዘፈኖችን፣ የስራ ዘፈኖችን፣...ሀይማኖታዊ ዘፈኖችን እና ሌሎች ብዙ አይነቶችን የሚያጠቃልል ነው (Abrhams፣ 1981፣ 66)::

2.መንቶ፡ ‹‹በሀሳብና በስሜት አንድነትና ተመሳሳይነት ያላቸው ስንኞች መንቶ ይባላሉ።። መንቶ ዝቅተኛው የግጥም መዋቅር ሆኖ እንደ ሙሉ ግጥም ተዘውትሮ የሚገኘው በአማርኛ ቃልግጥም ውስጥ ነው›› (ብርሃኑ፤1999፣ 192-195) ይላሉ:: ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ በሆነ አገላለፅ Finnegan (1970፣109) ስለ ቃልግጥም ድግግሞሽ፣ ስልትና መዋቅር ባብራሩበት ክፍል ውስጥ ‹‹መንቶ፣ሶስቶ፣አራቶ፣ወዘተ. አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ችለው የተሟላ ግጥም

ይሆናሉ...›› በማለት ይገልፃሉ:: ስለዚህ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው የተሟላ ሀሳብ ያላቸውን፣ ባለሁለት ስንኞችን መንቶ በሚለው መጥራትና፣ ከሁለት በላይ ለሆኑት ስንኞች ደግሞ፣ አርኬ የሚለውን መጠቀም የተሻለ ሆኗል።

3.አርኬ፡- ከተሰበሰበውና ከተመደበው ግጥም ውስጥ፤ ከሁለት በላይ ስንኞች ያሏቸውን ግጥሞች አርኬ በሚለው ስያሜ ጥናቱ ይጠቀማል:: አለማየሁ (1948፣ 12) እንደሚሉት ‹‹ባንድ ቤት የሚመታ የግጥም ሰብስብ አርኬ ይባላል›› ይላሉ:: በዚህ አገባብ ግጥም ያሉት ስንኝ እንደማለት ይመስላል:: የስንኝ ቁጥሩም እስከ አስር ሊደርስ እንደሚችል ይጠቁማሉ:: ብርሃኑ (1999፣ 198) አርኬንና አንጓን ለተመሳሳይ ስያሜ የተገለገሉበት ይመስላል:: ‹‹አንጓ በአንድ ግጥም ውስጥ ስንኞች በቡድን በቡድን ሆነው የሚመሰርቱትና፣ የሀሳብ... አንድነት ያላቸው ስንኞች መዋቅር ነው›› ይላሉ።። ነገር ግን፣ ከአንጓ ይልቅ አርኬ የሚለው ስያሜ ለቃልግጥም ተስማሚ ይሆናል ብየ አስባለሁ።።

4.ዘፈን:- የዜማ ስልቱ የተለያየ ሆኖ፣ ብዙ ጊዜ ወጣት ሴቶችና ወንዶች የሚጫወቱት ዜማ ነው:: አብዛኛውን ጊዜ፣ አንድ / አንዲት አቀንቃኝ ያለው፣ ታዳሚውም በማጨብጨብ፣ በመቀበል በእስክስታ፣ ወዘተ. የሚሳተፍበት ጨዋታ ሆኖ፣ ከታዳሚዎች መካከልም ግጥም ለማቀበልና ለማቀንቀን የሚያስችል እድል የሚሰጥ የጨዋታ አይነት ነው::

5.ጭፈራ:- ጭፈራ በተለያየ ባህላዊ አውድና አጋጣሚ ላይ ወንዶች ብቻ የሚከውኑት እና የሚታደሙበት ሆኖ፣ ስልቱም የተለያየ አይነት የሆነ ባህላዊ ጨዋታ ነው:: በባህሉ የጭፈራ ታዳሚዎች ወጣትና ጎልማሳ ወንዶች ብቻ ናቸው::

6.ቀረርቶ:- በከፍተኛ ድምፅ፤ አንድ ወይም ሁለት ከዋኞች በየተራ የሚያሰሙት እና፣ ወንዶች ብቻ የሚከውኑት የዜማ ስልት ነው:: ክዋኔው ሰርግ ላይ ሲሆን፣ ከምሽት ጀምሮ ሌሊቱ እስቲ ነጋ ድረስ ሊሆን ይችላል:: ይህም፣ ብዙ ጊዜ ወጣት ወንዶችና ጐልማሶች እንደ ችሎታቸው ከዋኝ የሚሆኑበትና፣ ታዳሚ ወንዶችም ግጥም እያቀበሉ ስሜታቸውን፣ ግብራቸውን፣ ወዘተ. የሚገልፁበት የዜማ ስልት ነው:: ቀረርቶ እርሻ ላይ፣ ጥበቃ ላይ፣ ለብቻ ሊከወንም ይችላል።።

7.አውዳዊ ትንተና:- አውድ የአንድ ስነቃላዊ ቅርጽ የሚነገርበት ወይም የሚከወንበት ቦታና ሁኔታ ቢሆንም፣ Okpewho (1992፣ 105-107) እንደሚሉት አውድ በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች አንጻር የሚታይ ነው።። ይኸውም፣ ከገጣሚው ሰብዕና፣ ከክዋኔው ቦታና ሁኔታ፣

ከአካባቢው ባህላዊ ወይም ማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመድ ሆኖ፣ የገጣሚው ቤተሰባዊ ዳራ፣ ልምድ፣ ስልጠና፣ በአውድ ውስጥ ይካተታሉ። ክዋኔውና ቴክስቱ ከሚኖረው ሙዚቃ፣ አካላዊ እንቅስቃሴና ከታዳሚ ጋር ይያያዛሉ። ከማህበራዊ ወይም ከባህላዊ ሁኔታዎች አንጻር ደግሞ፣ ማዝናናትና ማስደሰትን፣ ማስተማርንና፣ መገሰጽን ይመለከታል። ይሁን እንጅ፣ በዚህ ጥናት፣ አውዳዊ ትንተና ማለት ቃልግጥሞቹ በውስጣቸው የያዙትን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ታሪካዊ መረጃዎችን እየጠቀሱ፣ ገለጻና ትንተና ማድረግን የሚመለከት ነው። በመሆኑም፣ የትንተናው መሰረት የቃልግጥሞቹ ይዘት፣ የተፈጠሩበት አጋጣሚዎችና ምክንያቶች፣ እንዲሁም ትርጉማቸው ወይም ፍቻቸው ምንድነው? የሚሉትን ሁሉ የሚያካትት ነው።

8.ማህበራዊ ፋይዳ፡- ፋይዳ ማለት ጠቀሜታ፣ አገልግሎት፣ አላማ፣ እንደማለት ሲሆን፣ ማህበራዊ ደግሞ፣ የቃልግጥሞቹ ሃሳብና መልዕክት በሰዎች መካከል የሚኖራቸው የጋራ ወይም የተናጠል ስሜትን የሚመለከት ነው። በመሆኑም፣ ማህበራዊ ፋይዳ ማለት በእያንዳንዱ የቃልግጥም አይነት ውስጥ ባሉት መንቶዎች ወይም አርኬዎች አማካኝነት የሚተላለፉት ይዘቶችና መልክቶች የሚኖራቸው ስነልቦናዊ፣ ተግባራዊና ታሪካዊ ጠቀሜታ፣ወይም አገልግሎት፣ እና አላማ፣ ማለት ነው።

9. ይዘትና ጭብጥ፡- ይዘት ማለት በእያንዳንዱ ቃልግጥም ውስጥ የሚገኘው መረጃ ነው። በእያንዳንዱ ስንኝ ውስጥ በሚገኙት ቃላትና ሀረጋት አማካኝነት የሚተላለፈው ሀሳብ ወይም መልክት ይዘት ይባላል።ጭብጥ፤ገጣሚው ሊያሳየው ወይም ሊያስተላልፈው የፈለገው የህይወት ገጠመኝና በግጥሙ ውስጥ ዳብሮ የወጣ ማእከላዊ ሃሳብ ወይም ገጣሚው ግጥሙን ለመፃፍ ያነሳሳው ምክንያት ወይም ውስጣዊ ነውጥ ነው።(ብርሀኑ፤1999፤298) ስለዚህ የይዘት ትንተና ማለት በእያንዳንዱ ቃልግጥም ውስጥ ያለውን ሀሳብ፣ መልክት፣ አላማ፣በአጠቃላይ ጭብጡን ከተጨማሪ ፍች ጋር እያብራሩ መግለጽና ማስረዳት ማለት ነው።

10.ማንጸባረቅ፡- ማንጸባረቅ ማለት ማሳየት ማለት ነው። ይህም በቃልግጥሞቹ ውስጥ ያለውን አጠቃላይ መልክት የሚመለከት ይሆናል። ይህንን በሚመለከት Finnegan (1970፣ 263) «...ማንኛውም የስነጽሁፍ ውጤት በተዘዋዋሪና በቀላሉ በሚታይ መንገድም ቢሆን የሚገኝበትን ማህበረሰብ ማንጸባረቅ አለበት»ይላሉ።

11. የግጥም አይነቶች፡- አይነት ማለት የሃሳብ፣የመልዕክት፣እንዲሁም የአላማ ተመሳሳይነት፣ ተቀራረቢነትና አንድነት ማለት ነው። ስለዚህ፣ በእያንዳንዱ መንቶ ወይም አርኬ ውስጥ ባለው የይዘትና የጭብጥ ተመሳሳይነትና አንድነት፣ እንዲሁም ባላቸው ማህበራዊ ፋይዳ አማካኝነት በተደረገው ምደባ፣ በዚህ ጥናት ስምንት ዋና ዋና የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች ተለይተዋል።

ምዕራፍ ሁለት:- የሰሜን ወሎ ማህበረሰባዊና መልክአ ምድራዊ ዳራዎች

በዚህ ምዕራፍ፣ ስለዞኑ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ስለ አየር ሁኔታው፣ ስለግብርና ስራ፣ ስለታሪካዊ ቦታዎች፣ ወዘተ. ዳሰሳ ቀርቧል። በአካባቢው ከአለው ማህበረሰብ መካከልም፣ ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች ስለሚኖረው ማህበረሰብ፣ ታሪከዊ ዳሰሳ ተደርጓል። በአካባቢው ስለነበሩት ህዝቦች ታሪክ፣ በየዘመኑ ስለ ተከሰቱ አንዳንድ ሁኔታዎች፣ ገለጻ ቀርቧል:: በአካባቢው፣ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ስለታዩ የርስ በርስ ግጭቶች፣ ስለተከሰቱ የርሀብ ችግሮች፣ አንዳንድ ነጥቦች ተነስተዋል::

2.1 ማህበረሰባዊ ዳራ

አሁን ሰሜን ወሎ በሚለው መጠሪያ ውስጥ ያሉት የወረዳና የከተማ አስተዳደሮች የሚከተሉት ናቸው:: ጉባላፍቶ፣ ሀብሩ፣ ዋድላ፣ መቄት፣ ዳውንት፣ ላስታ፣ ግዳን፣ ቡግና እና ራያ ቆቦ የገጠር ወረዳ አስተዳደሮች ሲሆኑ፣ ወልዲያ፣ ቆቦ፣ ላሊበላና መርሳ ከተሞች፣ በከተማ አስተዳደር መዋቅር የታቀፉ ናቸው:: በየከተሞቹ ከሚኖረው ህዝብ መካከልም በግብርና ስራ የሚተዳደረው ህዝብ ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል:: የህዝቡ በዛት አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሶስት ሽ ሁለት መቶ ሰማኒያ ሶስት (1 503 283) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 754 354 ወንዶች ሲሆኑ 748 929 ሴቶች ናቸው (CSA፣ 2008)።

ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ባለው ታሪክ ከማህበረሰቡ ጋር የሚኖሩ ግለሰቦች ባብዛኛው ራሳቸውን የሚገልጹት፣ ከአካባቢው ስያሜ ጋር በተያየዘ እንደነበር ይታወሳል:: ለምሳሌ አንድ የየጁ ወይም የራያ አካባቢ ሰው ስለማንነቱ ሲጠየቅ ‹‹የጁየ» ... ወይም ‹‹ራያ›› ነኝ ይላል እንጂ ከብሄር ጋር አያይዞ ሲናገር አይስተዋልም ነበር። የላስታውም እንዲሁ ‹‹ላስቴ›› ነኝ ነበር የሚለው:: በማህበረሰቡ መካከል ይታይ የነበረው ልዩነት ብሄረሰባዊ ሳይሆን፣ ሀይማኖታዊ ይመስላል:: ይህም የሚገለፀው በሁለት ሰዎች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ችግሩን የሚገልፁበት ቋንቋ ነው። አባባሉም፣ ‹‹ከእንግዲህ እኔና አንተ እስላምና አማራ ነን›› የሚል ስለነበር፣ በዚህ አገባብ ‹‹አማራ›› የሚለው ‹‹ክርስቲያን›› ማለት ነው እንጂ፣ የብሄረሰብ መለያ አልነበረም ማለት ይቻላል::

በአብዛኛው ክርስቲያን የሆነው ህዝብ የሚኖረው በዞኑ ደጋማ አካባቢዎች፣ ማለትም በላስታ፣ በዋድላ ደላንታ፣ በቡግና፣ እና በግዳን፣ እንዲሁም በመቄት ወረዳዎች ሲሆን፣ በነዚህ አካባቢዎች ውስጥ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም አብረው ይኖራሉ:: የእስልምና እና የክርስትና ሀይማኖት ተከታይ የሆነው የማህበረሰብ ክፍል ባብዛኛው የሚኖረው፣ በቆላማውና በከተሞች አካባቢ ነው ማለት ይቻላል:: እነዚህ አካባቢዎች፣ ቆቦ፣ ጉባላፍቶና፣ ሀብሩ፣ ወረዳዎችን[12] የሚያካትት ነው:: የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሀይማኖቶችን የሚከተሉ ሰዎችም፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር አንድ ላይ እንደሚኖሩ ይታወቃል::

የጥናቱን አካባቢዎች ማህበረሰብ ታሪካዊ ዳራ በሚመለከት፤ ቀደም ሲል፣ የጁ አውራጃ እና ራያና ቆቦ አውራጃ ይባሉ በነበሩት አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ቀደምት ነዋሪዎች ‹‹ዶባ››፣ ‹‹ቀዳ›› እና ‹‹አንጎት››› ይባሉ እንደነበር (Fekadu፣ 1990) እና (Agizew፣ 2000) እንደገለፁት ህዝቦቹም እስልምና እና ‹‹ሀይማኖት የለሽ›› እንደነበሩ፣ እንዲሁም ከንጉስ ዘርዐ ያዕቆብና ከበዕደ-ማሪያም ጋር በተደጋጋሚ በመዋጋት ችግር ይፈጥሩ እንደነበር ያስረዳሉ:: የበዕደ-ማሪያምን ዜና መዋዕል ጠቅሰው Fekadu (1990፣ 8-9) እንደ ገለጹት፣

> ጃን አሞራና ጃን ቀንጠፋ በሚባሉት ሁለት የጦር ሀይሎቹ በተደረገው ዘመቻ እነዚህ ህዝቦች የሚኖሩበትን ዋና ቦታ፣ ዙብልን ተቆጣጠረ:: ...ተዋጊወቹም የትም ለመንቀሳቀስ ስላልቻሉ፣ ከፍተኛ እልቂት ደረሰባቸው:: ከእልቂቱ የተረፉትም ክርስቲያን እንዲሆኑ ተደረጉ:: ... እዚያ አካባቢ እንዲቆይ የተደረገው ሀይል አማርኛ ተናጋሪ ስለነበር፣ ምናልባትም የመጀመሪያው አማርኛ ተናጋሪ ቡድን (ሰው) ለመጀመሪያ ጊዜ የሰፈረው በዚያን ጊዜ ይሆናል ...

---

[1] እነዚህ ወረዳዎች ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ሆነው የተመረጡት ናቸው:: አሁን ቆቦ ወረዳ ተብሎ የተዋቀረው አካባቢ ከ1983 ዓ.ም. በፊት ራያና ቆቦ አውራጃ እየተባለ በሁለት ወረዳዎች ተከፍሎ የነበረው ነው:: አንደኛው አላማጣ ወረዳ ሲሆን ሁለተኛው ቆቦ ወረዳ ነው:: አላማጣ ወረዳ ከዋጃ ጀምሮ ወደ ክልል አንድ /ትግራይ ብሄራዊ ክልል/ ስር ሲጠቃለል ቆቦ ወረዳ ግን በክልል 3 /በአማራ ብሄራዊ ክልል/ ውስጥ ይገኛል:: ጉባላፍቶና ሀብሩ ወረዳዎች ቀደም ሲል የጁ አውራጃ በሚባለው ውስጥ የነበሩ ሁለት ወረዳዎች ናቸው:: አውራጃ የሚለው የአስተዳደር መዋቅር ስለቀረ ወረዳዎች ሆነዋል ማለት ነው::

በማለት ያስረዳሉ:: ከዚህ ሀሳብ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ Agizew (2000፣ 7) መርድ ወልደ አረጋይን ጠቅሰው እንዲህ ይላሉ፣ ‹‹ከድሉ በኋላ እዚያ እንዲቆይ የተደረገው ሀይል፣ ክርስትና የተቀበሉትን በጋብቻ በመያዝ (በመጋባት) በህዝቦች መካከል የጋብቻ ትስስር እንዲፈጠር የተደረገበት ሁኔታ ተፈጠረ:: ... በአካባቢው ሸሽተው የተሰደዱትን ሰዎች፣ ከብቶቻቸውን እየወሰዱ ክርስትና ለተቀበሉት ሰዎች እንዲሰጣቸው ተደረገ›› በማለት ያብራራሉ::

ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ አንስቶ (ከ1550-1650) ባለው ጊዜ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሰሜን ወሎ አካባቢ፣የጦርነት አካባቢና የጦር ሀይል መሸጋገሪያ በመሆኑ ምክንያት፣ ማህበረሰቡ ለተለያዩ ችግሮች በተደጋጋሚ ተጋልጧል ማለት ይቻላል:: የአፄ ልብነ ድንግል[3] በግራኝ መሸነፍና ወደ ሰሜን አቅጣጫ ማፈግፈግ፣ እንዲሁም ግራኝ ንጉሱን እየተከተለ ባደረገው ጦርነት በአጠቃላይ በአካባቢው ከፍተኛ ውድመትና ችግር እንዳስከተለ Agizewe (2000) ያመለክታሉ:: አፄ ልብነ ድንግል ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ዞብል[4] ላይ በቆዩበት ጊዜ ብዙ ቤተ-ክርስቲያን እንዲሰራ አድርገው ስለነበር፣ በኋላም ግራኝ ወደ አካባቢው ሲገባ የተሰሩትን ቤተክርስቲያኖች በማውደም፣ ማህበረሰቡም እስልምና ሀይማኖት እንዲቀበል አድርገዋል በማለት Agizew (2000፣ 9-10) ይገልፃሉ:: አፄ ልብነ ድንግል ዞብልን ለቀው ወደምእራብ አቅጣጫ ሲሸሹ አሁን ‹‹ንጉስ-ጋሌ››[5] አየተባለች ከምትጠራ የገጠር መንደር አካባቢ ጦራቸውን ሰብስበው በቁጣ እንደተናገሩ አፈታሪክ ይናገራል::

ከግራኝ ወረራ በኋላ እሱን ተከትሎ ወደ አካባቢው ዘልቆ የገባው ‹‹የኦሮሞ ንቅናቄ››[6] በሚል የሚታወቀው የኦሮሞዎች እንቅስቃሴ እንደነበረና ይህም በሀገሪቱ ታሪክ ከፍተኛ የህዝብ እንቅስቃሴ የታየበት፣ የህዝብ አሰፋፈርና ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ የተለወጠበት፣ እንደነበር

---

[3] አጼ ልብነ ድግል የነገሱት ከ1505-1540 እ.ኤ.አ. እንደ ነበር ባህሩ (2002) ‹‹A History of Modern Ethiopia:1855-1991›› ገጽ 9 ላይ ይገልጻሉ::

[4] ዞበል የሚባለው አካባቢ ከቆቦ ወደምስራቅ አቅጣጫ ከጨርጨር አስከ ወርቁ ድረስ ባለው ቦታ የሚገኘው ሰንሰለታማ ተራራ ሲሆን፣ከአፋር ጋር ኩታ ገጠም ስለሆነ ለግጭት የተጋለጠ ነው:: የልብነ ድንግል፣የግራኝ ፣በኋላም የአጼ ዮሀንስ ጦር እንደ እስትራቴጅካዊ የጦር ሰፈር ይጠቀሙበት እንደነበር ይታወቃል::ልብነ ድንግል አርባ አራት ቤተክርስቲያን በማሰራት ህዝቡ ክርስትናን እንዲቀበል ቢያደርጉም፣ግራኝ ሲገባ ቤተክርስቲያኑን አቃጥሎ ሰውን እስልምና እንዲቀበል አደረገው ይባላል::

[5] ‹‹ንጉስ-ጋሌ›› የሚለው ስያሜ የተፈጠረው አፄ ልብነ ድንግል ጦራቸውን ከዞብል አስነስተው ወደ ተራራማው የምዕራብ ክፍል ሲሸሹ እዚህ አካባቢ ትንሽ ረፍት አድርገው ነበር ይባላል:: በጦራቸው መሀል ቁመው ሀይል በተሞላበት ሁኔታ ሲናገሩ በመታየታቸው ‹‹ምነው ዛሬ ንጉሱ ጋል ጋል እያሉ ይናገራሉ›› ብሎ ከመካከል አንዱ ስለተናገረ ከዚያ በኋላ፣አካባቢው ‹‹ንጉስ-ጋሌ››ተባለ ይባላል::/የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ፣የታሪክ አስተማሪዬ ሲናገር የሰማሁትና የማስታውሰው/

[6] ባህሩ /2002/ ይህንን የህዝብ ንቅናቂ ማዕበል /tidal-wave / በማለት በሀገሪቱ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ፣ የሀገሪቱን የህዝብ አሰፋፈር፣ ቅርፅና ፖለቲካዊ መልካምድሯን የለወጠ፣ ከፍተኛ የህዝብ ንቅናቂ ነው ይላሉ::

(Bahru፣ 2002፣ 9) ይገልፃሉ:: ይህ የህዝብ ፍልሰትና እንቅስቃሴ፣ በሰሜን ወሎ ዞን ባሉት በራያና ቆቦ[7]፣ በየጁና በሀብሩ ወረዳዎች ወስጥ፣ በተለየ ሁኔታ አሻራው አሁንም ድረስ ይታያል:: ለምሳሌ ቆቦ ወረዳ ጨምሮ እስከ አላማጣ ድረስ፣ እንዲሁም የጁና ሀብሩ ወረዳዎች ውስጥ ያሉት የቦታ ስሞች፣ የእፅዋት ስሞች፣ የሰው ስሞች፣ ሌሎችም ከኦሮምኛ ቋንቋ የተወሰዱ ናቸው ማለት ይቻላል:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ‹‹ጋሪያ ሌንጫ›› (የተራራ ስም)፣ ‹‹በደና›› (የዛፍ ስም)፣ ‹‹ደንቢ›› (የቦታና የዛፍ ስም)፣ ‹‹ጮራ›› (የቦታ ስም)፣ ‹‹ገርቢ›› (የዛፍ ስም)፣ ‹‹ለገ-እዋ›› (የቦታ ስም)፣ ‹‹ጮራ-ሰዶማ›› (የቦታ ስም)፣ ‹‹ጉባ ላፍቶ›› (የቦታ ስም)፣ ‹‹አራርሳ፣ ዋዩ፣ ባቦ፣ ገለታ፣ ሞቲ፣›› (የሰው ሰሞች)፣ እንዲሁም ‹‹መ·ጫ›› (ትንሽ)፣ ‹‹ሎላ›› (የተቋተ ውሃ)፣ ወዘተ. የሚሉት ቃላት የተወረሱት ከኦሮምኛ ቋንቋ እንደሆነ መረዳት ይቻላል::

አጼ ቴዎድሮስና አፄ ዮሀንስ በነገሱባቸው ዘመናትም ቢሆን የአካባቢው ማህበረሰብና አካባቢው ከጦርነት ነፃ መሆን አልቻለም ማለት ይቻላል:: አፄ ቴዎድሮስ ማእከላዊ መንግስት ለመመስረት ባደረጉት ትግል፣ የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች የጦርነት አውድማዎች እንደነበሩ ይታወሳል:: አፄ ዮሀንስም ወደ ስልጣን ሲመጡ፣ በሁለቱ ራያዎች አካባቢ ቀደም ሲል የሰፈረው ኦሮሞ በፈጠረው ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ፣ ማህበረሰቡ እስልምና ሀይማኖት የሚከተል መሆኑን እንደተገነዘቡ፣ ከተለያዩ አካባቢዎች ህዝብ እያነሱ፤ወደ አካባቢው ማስፈር ጀምረው ነበር:: ከላሰታ (እስከ ደብረ-ታቦር ድረስ ያለውን አካባቢ ጨምሮ) እና ከትግራይ አካባቢዎች፣ ብዙ ሰው አምጥተው አስፍረው ሲመለሱ፣ የአካባቢው ሰው፣ በጎበዝ አለቆቹ እየተመራ ‹‹መጤውን›› እያባረረ በማስቸገሩ ‹‹ … ደም ያለደም አይጠራም … ›› በሚል መፈክር፣ አካባቢውን በሀይል ከደመሰሱ በኋላ፣ ያንኑ የሰፈራ ተግባራቸውን አጠናክረው በመቀጠል የአካባቢው ሰው እስልምናን እየተወ ክርስትናን እንዲቀበል፣ አልቀበል የሚል ከተገኘ፣ መሬቱ ተነጥቆ ክርስቲያን ለሆነ እንዲሰጥ በማድረግ፣ በኦሮሞ ንቅናቂ ጊዜ የነበረው የህዝብ አሰፋፈር ለሁለተኛ ጊዜ እንደተለወጠ (Fekadu፣ 1990፣ 15) ያስረዳሉ:: በዚህ ሂደት፣ የአካባቢው ማህበረሰብ እየተጋባ በመዋለድ፣ እየተዋለደ በመዋሀድ፣ ዛሬ ያለው ማህበረሰብ በአካባቢው የሚኖርበት አጋጣሚ እንዲፈጠር ሆኗል::

[7] አሁን ቆቦ ከተማ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ ስያሜውን ያገኘው በዚያን ጊዜ እንደነበር አፈታሪክ ይናገራል:: ይኸውም ኦሮሞዎች እዚያ አካባቢ ደርሰው አካባቢውን ሲመለከቱ ብዙ የጉሎ ተክል በሜዳው ላይ ያስተውላሉ:: ከዚያም አንዱ በኦሮምኛ… ‹‹ይኸማ ቆቦ ብቻ ነው››(ማል ኩን ቆቦ ሚቲ) በሎ ተናገረ አሉ:: በዚያው ስያሜውን አገኘ:: በኦሮምኛ ቆቦ ማለት በአማርኛ ጉሎ ማለት ነው::

አፄ ምኒልክ ከነገሱ በኋላም፣ በአካባቢው ጎልቶ የሚታወሰው ታሪካዊ ሁኔታ ወደ አድዋ ጦርነት ሲጓዙ፣ ጦራቸው ያለፈበትና የተመለሰበት አካባቢ መሆኑ ነው:: ይህ ሁኔታም በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጊዜ ወደ ማይጨው ጦርነት ለተደረገው ዘመቻ አካባቢው መሸጋገሪያና የጦርነት ቀጣና እንደነበረ ይታወሳል:: በነዚህ የዘመቻ እንቅስቃሴዎች ሳቢያ የአካባቢው ማህበረሰብ ለችግር ሊጋለጥ እንደሚችል ይታመናል:: ዘማቹ ሀይል በየደረሰበት፣ ንብረት እየቀማ፣ ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት እየፈጸመ፣ ያገኘውን ሁሉ በሀይል ለማንበርከክ ስለሚፈልግ በዘማቹና በማህበረሰቡ አባላት መካከል ግጭቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ይታሰባል:: ከዚህ አንፃር በታሪክ የሚታወቀው የማይጨው ጦርነት በጣሊያን ‹‹አሸናፊነት›› ሲደመደም ከጦርነቱ ተርፎ ወደ መሀል አገር የሚመለሰውን ዘማች ሀይል፣ የራያ አካባቢ ሰዎች እንዳንገላቱት እና እንደዘረፉት፣ በዚህ ቂም የተነሳ፣ ከነፃነት በኋላ በአካባቢው የመንግስት ጦር ዘምቶ ህዝቡ እንደ ተጨፈጨፈ፣ እና ልዩ ልዩ አይነት ቅጣት እንደተጣለበት ይታወሳል:: ይህንን ሁኔታ Bahru (2002፣ 157) ሲገልፀው ‹‹ወታደሩ ባገኘበት መንገድ ወይም አቅጣጫ እንዲያፈገፍግ በተደረገው ሁኔታ ከጦርነቱ ባልተናነሰ ጦሩን ዋጋ አስከፍሎታል:: ይህም የሆነው በ1920ዎቹ ገደማ የራያና የአዘቦ ህዝብ ከብት ዘርፋችኋል[8] በሚል ሰበብ ለመቀጣጫ የሚሆን ዘመቻ በመንግስት ተደርጎበት ስለነበር ነው:: በዚህ ቂም ሰበብ ህዝቡም ወታደሩን ያለርህራሄ ዘርፎታል፣ ገፍፎታል፣ አካላዊ ጉዳትም አድርሶበታል›› በማለት ያስረዳሉ::

የአፄ ሀይለስላሴ መንግስት በተለይ በሁለቱ ራያዎች (ራያ ራዩማ... ነው ይባል የነበረው) ተደጋጋሚ የሆነ ችግር ወይም አመፅና ግጭት እየታየ መሆኑን በመረዳት ችግሮቹን በጦር ሀይል ለመፍታት በተደረገው እንቅስቃሴ (ጦርነት) ብዙ ህዝብ አልቋል፣ ብዙ ንብረት ወድሟል፣ አያሌ ከብት ተዘርፏል፤ ማለት ይቻላል:: ሁኔታውን ለመቆጣጠርና መፍትሄ ለማበጀት ታስቦ፣ ሁለቱን ራያዎች በሁለት የመንግስት አስተዳደር ግዛቶች (በወሎና በትግራይ) ስር እንዲተዳደሩ ተደርጎ እንደነበር ይታወቃል:: በዚህ ምክንያት ይመስላል፣

‹‹ኧረ ምን ታሰበ ምን ተጠረጠረ
ራያ መሀሉ በሸቦ ታጠረ›› [9]

---

[8] ይህ የከብት ዘረፋ ተግባር በየጁ ‹‹የወያኔ›› /የወፋ ውጊያ/ በራያ ደግሞ ‹‹የጋዛ ዘመቻ›› እየተባለ የሚታወቀው ነው:: የከብት ዘረፋው የሚካሄደው በአፋር ላይ ነው:: ይህ እንቅስቃሴ እስከ 1960ዎቹ ድረስ የዘለቀ ነበር ማለት ይቻላል:: ይኸውም የተወሰኑ ግለሰቦች ወደ አፋር ወርደው ከብት በመዝረፍ ወደ ላይ ያመጡና ህጋዊ ገበያ ውስጥ ሳያስገቡ በዱር ‹‹የነበዝ ገንዘብ›› በሚል መግዛት ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው ይሸጡ እንደነበር አጥኚው ያስታውሳል::

[9] የመጀመሪያውን መንቶ ያነበብኩት አለሙ ካሳ ረታ እና ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ የተባሉ የራያ ተወላጆች በ2005 ዓ.ም ካሳተሙት መፅሀፍ ገፅ 217 ላይ ነው:: ሁለተኛውን መንቶ የሰማሁት በ1985 ዓ.ም ይመስለኛል ቤተሰቦቼን ለመጠየቅ ቆቦ ሂጄ ሳለ ጓደኞቼ የነገሩኝ ነው::

የሚል ቃልግጥም እንደተገጠመ ይታወሳል:: ይኸው ሁኔታ ከ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ በኋላ ‹‹ራያና ቆቦ አውራጃ›› ይባል የነበረውን አካባቢ፣ አንደኛውን ወረዳ ማለትም አላማጣን ይዞ እስከ ዋጃ ድረስ ያለውን፣ ወደ ትግራይ ክልል (ክልል አንድ)፣ ቆቦ ወረዳን ወደ አማራ ክልል (ክልል ሶስት) በመካለሉ ምክንያት ተመሳሳይ ቃልግጥም ተገጥሞ እናገኛለን፡፡ ይኸውም፣

‹‹ደሞ ምን ተሰማ ምን ተጠረጠረ
ራያ መሀሉ በሸቦ ታጠረ››

የሚል ነው:: የሁለቱ መንቶዎች ሀሳብ የተቃውሞ ስሜት የተንፀባረቀበት ነው:: በየመንቶዎቹ ካሉት ቃላት መካከል ‹‹ሸረ›› እና ‹‹ደሞ›› የሚሉት ቃላት፣ ድምፀታቸው የፍርሀት፣ የጭንቀት፣ የጥላቻ፣ የመሰልቸት፣ ወዘተ. ስሜት የሚታይባቸው አገላለጾች ናቸው::

በራያ ቆቦ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ባህላዊ አመጋገቡና አለባበሱ የተለየ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ባህላዊ አመጋገቡ እንጀራ በወጥና ቂጣ በወተት ነው፡፡ አልፎ አልፎ በቁርስነት ገንፎ በቅቤና በአይብ የሚቀርብበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ቂጣ በቅቤ ተፈትፍቶ (ጨጨብሳ፣ ጨዋቃ) ለወጣት ልጆች፣ በተለይ ለወንዶች ይቀርባል፡፡ ለእንጀራ የሚሆኑት እህሎች ማሽላና ጤፍ ናቸው፡፡ የጤፍ እንጀራ የሚዘወተረው በአብዛኛው ሀብታም ናቸው በሚባሉ ሰዎች ቤተሰብ ውስጥ ነው፡፡ ለወጥ የሚሆኑት፣ የአተር፣ የባቄላና የሽንብራ ሰብሎች ናቸው፡፡ ሀብታም በሚባሉ ቤተሰቦች እንጀራ በወጥ ሲቀርብ፣ እርጎ በመጠጫ ወይም በማእዱ ዙሪያ አብሮ ይሰጣል፡፡ ወተት እንደ ባህላዊ ምግብ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀብት መገለጫ ስለሚሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ ለዚህም ይመስላል፡-

ጤፍ እንጀራ በርጎ እንብላ ብላት
የጠመንማኒት ልይ ጎመን አማራት

ተብሎ የተዘፈነው፡፡ ባህላዊ አልባሳቱ በሸማኔ የተሰሩ ናቸው፡፡ ወንዶች ጋቢና ጎንቢሶ፣ ሴቶች ነጠላና ጥብቆ (ቀሚስ) ይለብሳሉ፡፡ ጎልማሳ ወንዶች ከላይ የሚለብሱት ጋቢ ሲሆን፣ ከታች የሚታጠቁት ጎንቢሶ ይባላል፡፡ ወጣቶችና ጎልማሶች ከላይና ከታች የሚለብሱትን፣ በቅቤ ነክረው እንዲለብሱ ባህሉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶችም እንዲሁ ነጠላቸውንና ቀሚሳቸውን ቅቤ ነክረው መልበስ ይችላሉ፡፡ አሁን አሁን እንዲህ አይነቱ አለባበስ እየተሻሻለና

እየተለወጠ መጥቷል። ባህላዊ መጠጦቹ ጠላና ጠጅ ናቸው። ጠላ የሚጠመቀው ከማሽላ፣ ከገብስና ከበቆሎ እህሎች ነው። ጠጅ ደግሞ ከማርና ከስኳር ይሰራል። የማር ጠጅ የሚጠጡት የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው ግለሰቦች ናቸው።

የጉባላፍቶና የሀብሩ ወረዳዎችን ማህበረሰብ ታሪካዊ ዳራ በሚመለከት የነበረው ሁኔታ እንደ ራያና-ቆቦ አካባቢዎች ተመሳሳይ ገፅታ ያለው ይመስላል:: ምናልባት በሁለቱ አካባቢዎች የተለየ ነገር ቢኖር በዮሀንስና በሀይለስላሴ ዘመነ መንግስታት ጊዜ የከፋ የጦርነት ችግር ያልገጠማቸው መሆኑ ነው ማለት ይቻላል:: አካባቢውም ቢሆን የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የአፋር፣ ብሄረሰቦች በተለያየ ቦታ ሰፍረው የሚኖሩበት ነው:: ማህበራዊ መስተጋብሩ ግን፣ በአማራና በኦሮሞ ተወላጆች መካከል ጠንከር ያለ ይመስላል። በጋብቻ፣ በሀይማኖት፣ በባህል፣ አብሮ በመኖርና በመረዳዳት ወዘተ. በመሳሰሉት ማህበራዊ ግንኙነቶች የሁለቱ ህዝቦች ውህደት ከፍተኛ ነው:: የነዚህን አካባቢዎች ማህበረሰብ በሚመለከት ከቀረቡ ጥናቶች መካከል የFekadu (1990) እና የAgizew (2000) ጥናቶች ተጠቃሾች ስለሆኑ፣ ከነዚህ ጥናቶች አንዳንድ ሀሳቦችን መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል። ለምሳሌ Fekadu (1990፣ 10-11) ባለው ውስጥ ስለአካባቢዎቹ እንዲህ በማለት ይተርካሉ::

> ... የአሁኑ የጁና አንጎት አካባቢዎች በአጠቃላይ የምዕራቡ ክፍል በክርስቲያኑ አማራ የተያዘ ነበር:: ... ከግራኝ ጦርነት በፊት የክርስቲያኑ አካባቢ የነበረው ‹‹ገነቴ›› ነው:: በአህመድ ግራኝ ጦርነት ጊዜ ክርስቲያኑ አሁን የጁ እየተባለ የሚጠራውን አካባቢ ብቻ ይዞ ቀረ:: ... በወቅቱ የነበሩት ጳጳስ ‹‹የጁን ያግኝ›› ብለው ስለረገሙት ከዚያ በኋላ የጁ ተባለ:: ... በግራኝ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያለው አፋርና ኦሮሞ በአሁኖቹ የራያና ቆቦ እንዲሁም በየጁ አካባቢዎች የመስፈር እድል አጋጥሟቸዋል:: ... ከግራኝ ወታደሮች ጋር ምናልባትም የአረብ ዝርያ ያላቸው እስልምናን የሚየስተምሩ፣ ... ሸህ ኡመር የሚባሉት በኋላ የየጁን ባላባታዊ ቤተሰብ መመስረት የቻሉት፣ መጀመሪያ የሰፈሩት መርሳ ላይ ነበር:: ... ከግራኝ ጦርነት በኋላ በየጁና በራያ አካባቢ የሰፈሩት ኦሮሞዎች የመጡት ከአዋሽ ማዶ (Awash-Gama) እንደ ነበር በአፈ ታሪክ ይነገራል:: ... ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ ታች-ጮሬ፣ ለገ-እዋ፣ ጮሬ-ሰዶማ፣ የሚባሉት አካባቢዎች ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ ኦሮምኛና አፋርኛ ቋንቋዎችን ይናገሩ ነበረ:: በአሁኑ ሰአት ወደ ምስራቅ ጫፍ

ባሉት ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖሩ ጥቂት ሰዎች ኦሮምኛ ይናገሩ እንደሆነ እንጅ ሌላው አማርኛ ተናጋሪ ብቻ ሆኗል::..

በማለት በሰፊው ያብራራሉ:: የሆነ ሆኖ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የአካባቢው ማህበረሰቦች በባህል፣ በጋብቻ፣ በቋንቋ፣ ተዋህደው በሀይማኖት ተቻችለው፣ የሚኖሩበት አካባቢ ነው:: ውህደቱ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ፣ የትኛው ባህል የየትኛው ማህበረሰብ እንደ ነበር መለየት በማይቻልበት ደረጃ ደርሷል ለማለት ያስደፍራል::

የጁና ሀብሩ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖረው ማህበረሰብም እንዲሁ፣ በራያ ቆቦ አካባቢዎች ከሚኖረው ማህበረሰብ ጋር፣ በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በአመራረት፣ ወዘተ. ተመሳሳይ ነው:: በደጋመው የሰሜን ወሎ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ግን፣ በአለባበሱ፣ በአመጋገቡ፣ በባህላዊ ጨዋታዎቹ፣ ወዘተ. ከቆላማው ማህበረሰብ የተለየ ነው ማለት ይቻላል:: በደጋማው አካባቢ በብዛት የሚመረተው ሰብል፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ምስር፣ አጃ፣ ወዘተ. ናቸው:: አመጋገቡም ከነዚህ ሰብሎች ጋር የተያያዘ ስለሆነ:-

የደገኛ ልይ ናት የገብስ በላው
ከንፈሯን ኩርሽሜ ምን አደረገው፣ ተብሎ ተገጥሟል::

ከእርስ በርስ ጦርነት ታሪካችን መካከል ለዚህ ትውልድ የቅርብ ጊዜ ትውስታ የሆነው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የርስ በርስ ግጭት አንዱ ነው:: የጥናቱ አካባቢ ማህበረሰብም፣ በዚህ የርስ በርስ ጦርነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቂም ተካፋይም ስለነበር፣ ስለግጭቶቹ አንዳንድ ሀሳቦችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል::

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለረጅም ጊዜ ከዘለቁት የእርስ በረስ ጦርነቶች (Civil Wars) መካከል ከአጼ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት አንስቶ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ያለውን የታሪክ ዘመን የሚሸፍነው አንዱ ነው:: በዚህ ዘመን ውስጥ አይለው በወጡ ታጋዮችና ሀገሪቱን በሚያስተዳድሩ መንግስታት መካከል የተደረጉት ትግሎችና ጦርነቶች የሀገሪቱን ሃብትና ንብረት በከፍተኛ ደረጃ ያወደሙ፣ የብዙ ዜጎችን ህይወት ያጠፉ፣ አካል ያጎደሉ፣ ነበሩ:: ከነዚህ የርስ በርስ ጦርነቶች መካከል፣ በቀድሞዋ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደ አንድ ክፍለ ሀገር ትጠራ በነበረችው ኤርትራ ውስጥ በተነሱት ሀይሎችና በኢትዮጵያ መንግስታት መካከል የተደረገው አንዱ ነው:: ከእነዚህ ሀይሎች መካከል ‹‹ሻቢያ›› ና ‹‹ጅብሀ›› ወይም የኤርትራ

ህዝብ ነፃነት ሀይሎች (EPLF) እና የኤርትራ ነፃነት ግንባር (ELF) በመባል የሚታወቁት ከሀገሪቱ መንግስታት ጋር በጦር መሳሪያ ትግል አደርገዋል:: እነዚህ ሀይሎች ከመንግስት ጦር ጋር መራር ትግል በማካሄድ፣ ዛሬ ኤርትራ የምትባለው ሀገር ከኢትዮጵያ ለይተው እያስተዳደሩ ይገኛሉ፡፡ ይህንን የትግል ታሪክ፣ Bahiru (2002፣ 219-259) በሰፊው እንዲህ በማለት ያብራሩታል::

> የመጀመሪያው የአመፅ እንቅስቃሴ ... የኤርትራዊያን ነፃነት ንቅናቄ (Eriterean Liberation Movement) በሚል የተጀመረ ነው፡፡ ... የንቅናቄው አባሎች ብዙዎቹ እስልምና ሀይማኖት ተከታይ የነበሩና ... በኋላም እንቅስቃሴው ወደ የኤርትራ ነፃነት ግንባር (Eriterean Liberation Front) ተለውጦ፣ ወዲያው ወታደራዊ ትግል መጀመሩንና ... ከሱ ቀጥሎ የኤርትራ ህዝብ ነፃነት ሀይሎች (Eritrean Peoples Libration Forces) በሚል ከተፈጠረው አማፂ ሀይል ጋር በመሆን እስከ ደርግ መንግስት መፍረስ ድረስ በመዋጋት ታግለዋል:: ... ከአቢዮቱ ፍንዳታ ማግስት እነዚህን አማፂዎች ለመደምሰስ የደርግ መንግስት የሞከረበት ስልት፣ ከአርሶ አደሩ በተውጣጣ ሀይል መዋጋት ነበር:: በታሪክ የሚታወቀው የራዛ ዘመቻ (Raza-campain) ከወሎ ክፍለ ሀገር ወደ 10000 የሚጠጋ የገበሬ ጦር ወደ ኤርትራ እንዲዘምት ቢደረግም ... በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ አቢዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) (EPRP) ወታደራዊ ክንፍ በነበረው ሀይልና በትግራይ ህዝብ ነፃነት ሀይል ወይም ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ሀይሎች አማካይነት እድለ ቢሱ የገበሬ ጦር የታሰበውን አላማ ሳያሳካ ከወዲሁ ተበታትኖ ቀረ::...

በማለት በወቅቱ የነበረውን የኤርትራን ዘመቻና የርስ በርስ ጦርነት ታሪክ ዘግበውታል:: በተለይም ስለ ራዛ ዘመቻ ሁኔታ ሲታወስ፣ ለውድቀቱ ሃላፊዎች ናቸው የሚባሉት የመንግስት ባለስልጣናት እንደሆኑ ይነገራል:: ለምሳሌ ለገበሬው ጦር የታደለው የመሳሪያ አይነትና የጥይት ብዛት ኋላ-ቀር ከመሆኑ በተጨማሪ አንዳንድ የጥይት እርሳሶች ባሩድ የሌላቸው እንደነበር ከዘመቻ የተመለሱት አባቶች ይናገራሉ::[10]

---

[10] ዛሬ ጎብየ ከተማ ውስጥ የሚገኙት አበራ ካሳው የሚባሉት አዛውንት የዚህ ጥናት አቅራቢ የቅርብ ዘመድና መረጃ ሰጭ የሆኑት ይህንን ሁኔታ በደንብ ያስታውሱታል::እሳቸውም ሞተዋል ተብሎ መርዶ መጥቶ ከተለቀሰላቸው በኋላ፤ቆይቶ ወደ ትውልድ ቀያቸው በደህና ስለተመለሱ፤

‹‹ሀሰን ወዳጆንም ብጠራው ዝም አለኝ

አበራ ካሳው ነው ስጠራው ወይ ያለኝ›› ተብሎ ተገጥሞላቸዋል::

በ1967 ዓ.ም አካባቢ የትጥቅ ትግል እንደጀመረ የሚታወሰው ሌላው ሀይል፣ ቀደም ባለው ስያሜ ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ተብሎ በሚታወቀው ድርጅት የተጀመረው ነው:: የዚህ ሀይል እንቅስቃሴ ትግራይ ውስጥ ተጀምሮ እየተጠናከረ በመምጣት ሌሎች ድርጅቶችን በመፍጠርና በማቀፍ አሁን በመንግስት ስልጣን ላይ ያለውን ሀይል መፍጠር ችሏል:: የህወሀት እንቅስቃሴ ወደ ሰሜን ወሎ ዘልቆ መግባት የጀመረውም በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው:: በ1972 ዓ.ም መስከረም ወር አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቆቦ ከተማና አካባቢው ዘልቆ በመግባት፣ ሌሊት ላይ ጦርነት ከፍቶ ከከተማው ፖሊስና ከቀበሌ ታጣቂዎች ጋር፣ እንዲሁም ማይክሮዊቭ የሚባለውን ተቋም እንዲጠብቁ ከተመደቡ ጥቂት የመንግስት ወታደሮች ጋር ተዋግቶ፣ ሌሊት አካባቢውን ለቆ ወደ መጣበት መመለሱ ይታወሳል:: ይህ ሌሊት የማጥቃትና ሌሊት የመውጣት የውጊያ ስልት፣ እስከ 1976 ዓ.ም ድረስ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በራያ አካባቢዎች ይደረግ የነበረ ነው:: በዚህም አካባቢው የጦርነትና የስጋት ቀጣና በመሆን ለአመታት ዘልቋል ማለት ይቻላል::

ይህ በሌሊት የመግባትን በሌሊት የመውጣት የውጊያ ስልት፣ በ1976 ዓ.ም ባልተለመደ ሁኔታ፣ ውጊያው በጧት ተጀምሮ፣ ወደ ማታ፣ በህወሀት አሸናፊነት ከተማዋ (ቆቦ) በነሱ ቁጥጥር ስር ሆነች:: ለሶስት ቀን ያህል ከተቆጣጠሩት በኋላ፣ ከማይጨው ተንቀሳቅሶ በመጣ የመንግስት ጦር ከተማዋን ለቀው እንዲወጡ ሲደረጉ፣ በወቅቱ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያገኙትን ማንኛውንም እቃ በሰው ትከሻ (በየመንገዱ ያገኙትን ሰው እየያዙ) ያጓጉዙ ስለነበር፣

የወያኔ አህዮች ሁለት እግራ ናቸው
ቆቦ የተጫኑ ዳንዶ አራገፏቸው ፣ ተብሎ ተገጠሚል::

ከሶስት ቀን በኋላ፣ ከማይጨው ተንቀሳቅሶ የመጣውን የመንግስት ጦር ‹‹ጮቢ በር›› ከምትባል ቦታ መሸገው በመጠበቅ ግማሽ ቀን በፈጀ ውጊያ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አልቋል:: በመንግስት በኩል ውጊያው በከባድ መሳሪያና በሄሊኮፕተር የታገዘ ቢሆንም፣ በቀላሉ ምሽጉን ሰብሮ ማለፍ ባለመቻሉ ብዙ ወታደር እንዳለቀ ይነገራል:: ይህንንም ሁኔታ

የወታደር ኳዳ ወድቆ አይሰበርም
ጮቢ በርን ያየ ክፉ አይናገርም ፣ በሚለው ቃልግጥሙ መስክሮታል::

በአካባቢው የተካሄደው ይህ የርስ በርስ ጦርነት እስከ 1980ዎቹ ድረስ እየተስፋፋና እየተጠናከረ በመምጣት፣ የኢትዮጵያ ህዘቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የትግራይን አካባቢ በመቆጣጠር ወደሌሎች አካባቢዎች ለመሸጋገር ችሏል። ለምሳሌ፣ በ1982 ዓ.ም ነሀሴ ወር መጨረሻ ላይ የኢህአዴግ ጦር ‹‹ቆረጣ›› በሚባለው የውጊያ ስልት፣ በሰሜን ወሎ፣ ራያና ቆቦ አካባቢ፣ በከፍተኛ ሁኔታ፣ በዘመናዊ የጦር መሳሪያ[11] ታግዞ መጠነ-ሰፊ ጥቃት አደርጎ እንደነበር አጥኚው ያስታውሳል። ጦርነቱም ሰባት ቀናት ያህል እንደፈጀ፣ ከሁለቱም ወገን ከፍተኛ የሆነ ተዋጊ ሀይል እንደሞተና እንደቆሰለ፣ የንብረት ውድመት እንዳደረሰ ይታወቃል። በዚህ ጦርነት፣መንግስት አካባቢውን በመልቀቅ ወደ ደቡብ ወሎ በማፈግፈጉ፣ አካባቢውን እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ፣ ኢህአዴግ ‹‹ነፃ መሬት›› (ሀራ መሬት) በማለት እየተዋጋና እያዋጋበት ቆይቷል። በርስ በርስ ጦርነቱ ጊዜ የታየውን ሁኔታ የአካባቢው ሰዎች በቃልግጥሞቻቸው አንፀባርቀውታል፣ ዘግበውታል፣ ማለት ይቻላል።

2.2 መልክአ ምድራዊ ዳራ[12]

በታሪካዊ ዳራው እንደተገለጸው፣ ዞናዊ ስያሜው የተጀመረው በ1981 ዓ.ም አካባቢ፣ ቀደም ሲል ወሎ ክፍለ ሀገር ይባል የነበረውን ሰፊ ክፍለ ሀገር፣ ለሁለት በመክፈል ሰሜንና ደቡብ ወሎ በሚሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች በተከፋፈለበት ጊዜ ነው። ዞኑ የሚገኘው በክልሉ ሰሜን ምስራቅ አካባቢ ሲሆን፣ ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ፣ በ560 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ፣ የዞኑ ዋና ከተማ ወልዲያ ትገኛለች፡በነበረው የአውራጃ መዋቅር የዞኑ አውራጃዎች የነበሩት ዋግ፤ላስታ፤ዋድላ ደላንታ፤የጁ እና፤ ራያና-ቆቦ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ዞኑ የአውራጃ መዋቅሩን በመለወጥ በወረዳና በከተማ የአስተዳደር መዋቅሮች ተከፋፍሏል። ዞኑ ሲዋቀር ከነበሩት አውራጃዎች መካከልም የዋግ አውራጃ እንደ አንድ ብሄረሰባዊ ዞን በመሆን በ1986 ዓ.ም ከሰሜን ወሎ ተለይቶ ለብቻው ሁኗል። ዞናዊ ስያሜውም ‹‹ዋግህምራ ››ተብሏል። የሰሜን ወሎ ዞን የገጠርና የከተማ አስተዳደራዊ መዋቅሮች በዝቅተኛው የአስተዳደር ቀበሌ

---

[11] በዚያ ጦርነት ወቅት ታጋዮቹ ታጥቀውታል ተብሎ ከሚጠረጠረው ዘመናዊ መሳሪያ አንዱ ‹‹ግራርፒ›› የሚባለው ነው። ይህ መሳሪያ ከተራራ ጀርባ ተጠምዶ ከተራራው ፊት ያለውን አካባቢ ለመምታተ የሚያስችል ነው። በ1982ቱ የነሀሴ ወር ጦርነት ጊዜ መሳሪያው ዞብል ተራራ ጀርባ ወራጋ እሚባል ስፍራ ላይ ተጠምዶ ከተራራው ፊት ባለው ማይክሮዊቭ ዙሪያ መሸጎ በነበረው የመንግስት ጦር ምሽግ ውስጥ በማሳረፍ ውጊያውን ከምሽግ ወደ ጨበጣ ውጊያ እንዲቀየር አድርጎት እንደነበር በወቅቱ ይታወቃል። በዚህ ጊዜ

‹‹ወራጋ ላይ ሁና ግራርፒን ብትለቀው
መንጌ ሀይለማሪያም፤አዲስ አበባ ሆኖ፤ወሬው አስጨነቀው›› ተብሎ ተገጥሟል።

[12] በዚህ ክፍል ውስጥ የሚነሱት ሀሳቦች የተገኙት በዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት አማካይነት ተዘጋጅቶ ከቀረበ የሪፖርት ሰነድ ውስጥ ነው። ይህ ሰነድ በ2005 ዓ.ም ተዘጋጅቶ፤ በሶፍት ኮፒ ጽ/ቤቱን ይመራ ከነበረ ባለሙያ የኮምፒውተር ፋይል ውስጥ የተወሰደ ነው። በጊዜው ሌላ አማራጭ ስላልነበረ ከባለሙያው ጋር በመተባበር ፋይሉን በማተም /Print በማድረግ /ለመጠቀም ተችሏል።

መዋቅር በ278 የገጠር እና በ20 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ በ298 ቀበሌዎች የተዋቀረ ነው (2005:1)

አስተዳደራዊ ዞኑን የሚያዋስኑት አካባቢዎች፣ በሰሜን፤ የትግራይ ደቡባዊ ዞን የሆነው ራያና አዘቦ እና የዋግ ኽምራ ዞኖች ናቸው:: በደቡብ፤ ከደቡብ ወሎ ዞንና፣ በምስራቅ፣ ከአፋር ብሄራዊ ክልል መንግስት፣ ሰሜናዊ ዞኖች ጋር ይዋሰናል:: በምዕራብ ደግሞ ከደቡብ ጎንደር ዞን አካባቢዎች ጋር አዋሳኝ ነው:: የዞኑ የቆዳ ስፋት 12410 ስኩየር ኪሎሜትር ሲሆኑ መልክአ ምድራዊ አቀማመጡም፣ የታላቁ የስምጥ ሸለቆና፣ የአባይ፣ የተከዜ እና የአዋሽ ተፋሰሶችን በሚያካትተው አካባቢ ውስጥ ያለውን ከፍተኛና ወጣ ገባ አካባቢዎች የሚያካልል ነው:: (2005፣ 1)

የዞኑ አካባቢዎች መልክአ ምድራዊ ሁኔታ ሲታይ በብዛት ተራራማ፣ አልፎ አልፎ ሜዳማና ወጣገባ አካባቢዎች የሚገኙበት ነው:: ተራራማው አካባቢ የሚገኘው፣ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ የሚወስደውን የመኪና መንገድ መነሻ አድርጎ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ያለውን ቦታ የሚሸፍን ነው:: በተራራማው ቦታ ላይ ለእርሻ ስራ እና ለመኖሪያ የሚሆኑ ሜዳማ አካባቢዎች አሉ:: ሜዳማው አካባቢ በስፋት የሚታየው ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ባሉት አካባቢዎች ነው፡፡ ለምሳሌ የቆቦ ከተማ፣ አልፎ አልፎ ተራራማ ቦታዎች የሚገኙበት ቢሆንም ዙሪያውን ሜዳማ ነው:: ወጣ ገባ አካባቢዎችን በሚመለከት በዞኑ ምስራቃዊ ክፍል ባሉት አካባቢዎች የሚገኝ ነው::

በዞኑ ውስጥ ከሚጠቀሱት ተራራማ አካባቢዎች መካከል፤ አቡነ ዮሴፍ፣ ዞብል፣ አባይሆይ ጋራያ፣ ነቢላ፣ ገደመዩ፣ ጋሪያ ሌንጫ፣ አርበት፣ ጠበለት፣ ቃሊም፣ ጥቂቶቹ ናቸው:: የዞኑ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ቦታዎች ከባህር ወለል አንፃር ሲታዩ ከ3500 ሜትር በላይ እና እስከ 1500 ሜትር በታች ባለው ውስጥ የሚካተቱ ናቸው (2005፣ 2)፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ በአካባቢው ለሚታዩት መልካምድራዊ ገጽታዎች ቃልግጥሞችን እየፈጠረ መዝፈን የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

ወግድ ጋሪያ ሌንጫ ቆቦ ሰው ልይበት
የሚጠቀለለው ሽንጣ እንደ ወረቀት፡፡
ተሮ በሩ፣ዞብል በራ በሩ
እንኳን ሰው ቁሞበት ያስፈራል ግራሩ፡፡

የሰሜን ወሎ ዞን የሚታወቀው በዝናብ አጠርነት ቢሆንም አርሶ አድሩ በመኸርና በበልግ የተለያዩ ሰብሎችን ያመርታል:: አሁን አሁን በከርሰ-ምድር ውሃ (በተለይ ቆቦ አካባቢ) በመጠቀም፣ ወንዞችን በመጥለፍ (በመስኖ)፣ የተለያዩ የሰብል አይነቶችን ማምረት እየተለመደ መጥቷል:: ቀደም ሲል በነበረው የግብርና ባህል (ጤፍና ማሽላ በብዛት የማምረት ልማድ) በቆላማው አካባቢ እየተለወጠ ስለመጣ፣ ሽንኩርትና አትክልቶችን ማምረት ተጀምሯል:: በዞኑ ባሉት በደጋማዎቹ አካባቢዎች አተር፣ በቂላ፣ ምስር፣ ጓያ፣ ገብስና ስንዴ፣ የመሳሰሉት ሰብሎች ሲመረቱ፣ በቆላማዎቹ አካባቢዎች ደግሞ፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ በቆሎ የመሳሰሉት ይመረታሉ:: እንደ ኑግና ተልባ ያሉት የቅባት እህሎች በደጋው ሲመረቱ፣ እንደ ጥጥና በርበሬ ያሉት ደግሞ በቆላማው ይመረታሉ::

በዞኑ ውስጥ ከሚጠቀሉት ወንዞች መካከል አላ ውሃ (ጥቁር ውሃ)፣ ጎሊ፣ ሆርማት፣ ጨረቲና፣ ሌሎች ይጠቀሳሉ:: ጨረቲ ወንዝ ሀብሩ ውስጥ የሚገኝ ነው:: አላ ውሃ በራያና በየጁ ወረዳዎች መካከል የሚገኝ ሲሆን የሁለቱ አካባቢዎች ድንበር ተደርጎ ይወሰዳል:: ጥቁር ውሃ የሚባለው ከወልዲያ ወደ ሳንቃ በሚወስደው መንገድ ድልድይ ስር አልፎ የአካባቢውን ተራራማ ቦታ ለሁለት ከፍሎ በታች በኩል ከወልዲያ ወደ ቆቦ የሚወሰደውን አሰፋልት መንገድ አቋርጦ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ አፋር ክልል የሚገባው ወንዝ ነው:: ሆርማትና ጎሊና ደግሞ፣ ቆቦ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከላይ ከደጋማው አካባቢ ተነስተው ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመውረድ፣ ወርቁ መሻገሪያ ሲደርሱ፣ አንድ ላይ ይሆኑና ወደ ጎመጅ (አፋር) ይገባሉ:: እነዚህ ወንዞች አፋር አካባቢ ሲገቡ አላና ጎሊና በሚል መጠሪያ ሁለት ወንዞች ይሆናሉ ማለት ነው:: ወንዞችም እንደተራዎቹ፡-

> የጨርቋ ማጠቢያ ጎሊና ነው ወንዙ
> አሁን አልደርስም ወይ ለማጠማዘዙ፣ እየተባለ ይዘፈንላቸዋል::

የዞኑ የአየር ንብረት ሲታይ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ቆላማ፤ ደጋማ፤ ወይናደጋ፤ ነው:: ቆላማ የሚባለው ዞኑን ለሁለት ከፍሎት ከሚያልፈው ከአዲስ አበባ- መቀሌ መንገድ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ያለውን ክፍል የሚሸፍነውን አካባቢ ነው:: ደጋማው ደግሞ ከዚሁ አስፋልት መንገድ ወደ ምእራብ አቅጣጫ ያለውን ተራራማ ቦታ የሚያካልል ነው:: ወይናደጋው በተለያየ አካባቢ የሚገኝ ነው:: ለምሳሌ ከቆቦ ከተማ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ያለው ሰንሰለታማ ተራራ

(ዙብል) ወይና ደጋ የሚባል ነው:: ወልዲያና መርሳ ከተሞች አካባቢ ያለው ቦታም እንዲሁ ወይናደጋ የሚባል ነው::

በዞኑ ውስጥ ብዙ ታሪካዊ ቤተክርስቲያናትና መስጊዶች ይገኛሉ:: የላሊበላ ውቅር ቤተክርስቲያናት፣ የአቡነ አሮን ገዳም፣ የእማሙዝ ገዳም፣ የራማ ኪዳነ ምህረት ገዳም፣ ወዘተ. በክርስትናው በኩል ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆኑ፣ የዳና እና የመርሳ አባገትየ መስጊዶች በእስልምናው በኩል የሚጠቀሱ ናቸው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአካባቢው የመስጊዶች ቁጥር እየጨመረ እንደመጣም ይታወቃል::

የዞኑን የእንስሳት ሀብት በሚመለከት በቆላማውና በደጋማው አካባቢ ያለው እርባታ የተለያየ ነው:: በደጋማው አካባቢ የጋማ ከብቶች (አህያ ፈረስ በቆሎ) በግና ፍየሎች በብዛት ሲገኙ የቀንድ ከብቶች እርባታ ከቆላማው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው:: ይህም ከመሬቱ አመችነትና ጥበት ጋር የተያያዘ ነው:: ቆላማው አካባቢ ከእርሻ ተግባሩ ደርቦ ከብት በብዛት ያረባል:: ለዚህ የተመቹውም የአካባቢው ሜዳማና ለግጦሽ የሚሆን ቦታ ከደጋማው አካባቢ በተሻለ መኖሩ ነው:: የቆላማው አካባቢ በምስራቅ በኩል ከአፋር ጋር በመዋሰኑ እና የአፋር መሬትም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የማይታረስ ስለነበር፣ ከአፋር ጎሳዎች መካከል አንድ ሰው ጓደኛ (በአፋርኛ ከታይሳ ይባላል) በመያዝ ወዳጅነት ከመሰረተ በኋላ፣ ከብቶቹን ይዞ ወደ አፋር በመሄድ በጓደና ማርባት የተለመደ ነው:: ወይም መሳሪያ ይዞ፣ ድንበር አካባቢ በረት እያጠሩ፣ ጎጆ እየሰሩ፣ በጋራ ያጓድኑና ከብቶቻቸውን እንደልብ ሳር በማብላት ስለሚያረቡ የቆላማው አካባቢ ገበሬዎች በከብት ብዛት ከደጋማው ይበልጣሉ:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም ልዩ ልዩ ቃልግጥሞች ተገጥመዋል:: ለምሳሌ፡-

አንችን ከሚከፋሽ እኔን ይክፋኝ ብየ
ገባሁልሽ ከሎ ቀጮየን አዝየ
አላይና ጎሊና ጊደር ካላበሉ
ታቹን ብሩ ጎራ ወይ ካላጓደኑ
አሁን ወይት ይገኛል ወተት ሞይዘር ቢሉ፣

እየተባለ ይዘፈናል::

ካርታ አንድ፡- የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታዎች



Source: Redraw fron ETHIO-GIS, 2005 and CSA, 2007

ካርታ፡ሁለት፡- የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር አካባቢዎች



2.3 የርሀብ ዘመናት በሰሜን ወሎ አካባቢዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ የድርቅና የርሀብ ዘመናት መንስኤዎች ተብለው ሊጠቀሱ ከሚችሉት መካከል ጦርነት፣ የዝናብ እጥረትና የእንሰሳት በሽታዎች፣ የአንበጣ መንጋና የአእዋፍ ወረራዎች ናቸው:: መንግስትና ህዝብ ከውጭም ሆነ ከውስጥ በሚነሱ ጦርነቶች በሚጠመድበት ጊዜ በምርት ተግባር ላይ የሚካሄደው እንቅስቃሴ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መስተጓጎሉ አይቀርም:: በተለይ ጦርነቱ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ለምርት ስራ የማይመቹ ስለሚሆኑ የምግብ እጥረት ያጋጥማል:: በኢትዮጵያ ዋና የሰብል ምርት ማግኛ ዝናብ ስለሆነ፣ ዝናብ ከሌለ ወይም የሚያስፈልገውን ያህል ካልጣለ፣ ምርት ይቀንሳል፣ ይጠፋል:: አርሶ አደሩም ለምርት ስራ (ለግብርና) የሚገለገልባቸው የቀንድ ከብቶችና ሌሎች እንሰሳት በተለያየ የበሽታ ወረርሽኝና በድርቅ ሰለሚያልቁ ለግብርና ስራው የሚገለገልባቸውን እንስሳት አጥቶ ለችግር ይጋለጣል:: የአንበጣ መንጋና የአእዋፍ ወረራዎችም የበቀሉ ሰብሎችንና የደረሱ እህሎችን በመብላት የምርት እጥረት ወይም ችግር እንዲኖር ያደርጋሉ:: ትላትሎችም እንዲሁ ሰብልን በማጥፋት አርሶ አደሩን በተለይ፣ በአጠቃላይ ማህበረሰቡን ለርሃብ አደጋ ሊያጋልጡ ይችላሉ:: ተምችና አንበጣ ከሰብል እህል በተጨማሪ ለእንሰሳት ግጦሽ የሚሆነው ሳርና ቅጠላቅጠል በማጥፋት (በመብላት) እንሰሳት ለረሀብ እንዲጋለጡ ያደርጋሉ:: ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ከተከሰቱት የረሀብ ዘመናት መካከል አንዱን Bahiru (2002፣ 71-72) እንደሚከታለው ይገልፁታል፣

> ይህ ዘመን በኢትዮጵያዊያን አጠራር ክፉ ቀን እየተባለ የሚታወቀው ከ1882-1884 ዓ.ም የተከሰተው ነው::... ኢትዮጵያ በውስጣዊና በውጫዊ ምክንያቶች ... በከባድ ችግር ውስጥ ወደቀች:: የግዛት ማስፋፋት ሂደቶች በከፊልም ቢሆን ለማህበራዊ መቅሰፍቶች መነሻ ሆነዋል:: ርሀቡ በሰሜን ኢትዮጵያ በጣም የጠነከረ ስለነበረ ... በነዚህ አካባቢዎች የማህበራዊና የኢኮኖሚ መናጋት ተፈጠረ:: ... እንደነውር የሚቆጠሩ ነገሮች ተበሉ ... በልዩ ልዩ በሽታ የሞቱ እንስሳትን ስጋ ... ሰዎች ይበሉ ነበር:: ተስፋ በመቁረጥ ራሳቸውን የገድሉም ... ነበሩ::

በማለት የዚያን ጊዜ የርሀብ ዘመን ገልፀውታል:: ይህንን ዘመን መሰፍን (2005፣ 118) ላይ ‹‹በኢትዮጵያዊያን አጠራር ክፉ ቀን የሚባለው፣ ሰበቡ ጣሊያኖች በምፅዋ በኩል ያስገቡት

የቀንድ ከብት በሽታ እየተዛመተ አገሩን ስላዳረሰ ... ላምና በሬ ሁሉ አለቀ፣ ከባድ ችግር አገሩን ሁሉ አጠቃው›› በማለት ይገልፃሉ::

እንደ Fekadu (1990) ጥናት ከሆነ በአካባቢው የረሀብ አደጋ መከሰት የጀመረው ከ1916 ማለትም ከሰገሌ ጦርነት በኋላ እንደሆነ ነው:: ለረሀቡ መከሰት ምክንያቶች የሚላቸውም የአንበጣ መንጋ፣ የርስበርስ ጦርነት፣ የዝናብ እጥረት ናቸው:: እነዚህ የረሀብ ሰበቦች በአካባቢው በተለያየ ጊዜ እየተከሰቱ በማህበረሰቡ ላይ በተደጋጋሚ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል:: በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሶስት ሩብ አመታት ማለት እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ የጁና ራያ፣ እንዲሁም ሌሎች አካባቢዎች በከፋ ድርቅ በተደጋጋሚ ተመትተዋል Fekadu (1990፣100) በማለት ያስረዳሉ::

የ1965/66 ዓ.ም እና የ1976/77 ዓ.ም የረሀብ ጊዜያቱን ስንመለከት የሁለቱም ጊዜያት የረሀብ መንስኤዎች የዝናብ እጥረት እንደሆነ ይታወቃል:: በ1965/66 ዓ.ም የምርት ዘመን የተዘራው ማሽላና ጤፍ ለማደግ፣ ለመውለድና ለማፍራት የሚያስፈልገውን የዝናብ መጠን ባለማግኘቱ ተሸፍኖ ቀረ:: ማሽላና ጤፉም ለከብት መኖ ብቻ ሆነ:: በወቅቱ እንደ ጥንቅሽ አገዳ ሆኖ ያገለግል የነበረው ‹‹ኮርትም›› በመባል የሚታወቀው አገዳ ነው:: የዚህን የረሀብ ሁኔታ Fekadu (1990፣ 104-106) እንዲህ ይገልጹታል፤

> በ 1971 (እ.አ.አ. መሆኑ ነው) ራያና ቆቦ ዝናብ የለም:: ጥቂት ዝናብ የጁ ጥሏል:: የዝናብ መቋረጡ በ1972 ና በ1973 በሁለቱ አውራጃዎችና በአጎራባቾችም ጭምር ተከሰተ:: ... በየቀኑ ከ50 ሰው በላይ በየመንገዱ ይሞት ጀመር:: ... በ1973 የርሀቡ አደጋ፣ አዲስ አበባ ላይ፣ ፓርላማ ተወያይቶበት እርዳታ እንዲላክ ተወሰነ:: ... ንጉሱ በሄሊኮፕተር ጉብኝት አድርገው ለራያና ቆቦ እንዲሁም ለየጁ አንዳንድ አካባቢዎች ለተጎዱት ሰዎች ዳቦና እራፊ ጨርቅ ከአንድ ብር ጋር አድለዋል:: ... ችግሩ በውጭው አለም በመሰማቱ ... የእርዳታ መስጫ ጣቢያዎች በራያና በየጁ አካባቢዎች መቋቋም ሲጀምር፣ የአለም ሉተራን ፌዴሬሽን፣ የሆላንድ ውስጣዊ ተልዕኮ ማህበረሰብ እና የአለም ጤና ድርጅት (W.H.O) የሚባሉት የርሀብ አደጋውን ለመታደግ ተካፋይ ሆኑ:: ...

ይላሉ:: እንደዚሁም በ1976/77 ዓ.ም በአካባቢው በደረሰው የርሀብ አደጋ ለችግር የተጋለጠውና የችግሩ ሰለባ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ብዙ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ

ነው:: ይሽኛው የድርቅ ዘመን ከ1965/66 የሚለዩት አንዳንድ ገፅታዎች አሉት:: በ1965/66 የድርቅ ጊዜ ከብቶች የሚበሉት ስላልታጣ፣ በአንዳንድ ቤተሰብ ዘንድ ወተት አልጠፋም ማለት ይቻላል:: የእህል ዋጋም ሆነ፣ የእንሰሳት ዋጋ በጣም ርካሽ ስለነበር ገንዘብ ያላቸው ሰዎች በቀላሉ የሚፈልጉትን እየሸመቱ/ እየገዙ መጠቀም ይችሉ ነበር:: የእርዳታው ሁኔታ ዘግይቶ መድረስና፣ በወቅቱ የነበሩት አስተዳዳሪዎች ተጎጅውን በአግባቡ ለመርዳት እንቅፋት እየሆኑ ቢያስቸግሩም የተደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ነበር ማለት ይቻላል::

ወደ 1976/77 ዓ.ም የርሀብ ዘመን ስንመጣ ከላይ እንደተጠቀሰው ዋናው መንስኤ የዝናብ አለመኖር ነው:: የ1976 ለ77 ዓ.ም የምርት ዘመን ታስቦ የሚደረገው የእርሻ ተግባር በተለመደው ወራት ተጀምሮ እንቅስቃሴ ቢደረግም፣ ተፈላጊው የዝናብ መጠን ቀርቶ፣ ዳመና ሰማይ ላይ በወጉ ሳይታይ፣ ወደ ሰባ ሰባት ተሸጋገረ:: በ76 የተጀመረው ርሀብ በሰባ ሰባት የከፋ ሆነ:: መሬት ተቃጠለች፣ እንሰሳት የሚግጡት ሳር፣ የሚበጥሱት ቅጠል፣ ጠፋ:: ሰው የሚልሰውና የሚቀምሰው አጥቶ መጠውለግ ጀመረ:: ይህ ወቅት ከየጁና ከሀብሩ ይልቅ፣ በራያና በላስታ አካባቢዎች የከፋ ሁኔታ የታየበት ነበር:: ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ለከብት ቀለብ የሚሆን አገዳና ድርቆሽ ወደ መርሳ አካባቢ ይገኛል እያሉ ከብቶቻቸውን ይዘው ይሄዱ ስለነበር ነው::

ይህንን የድርቅ አደጋ ለመከላከል የተለያዩ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል:: በተለይ ቆቦ ውስጥ የመንግስት ድርጅት የሆነው የእርዳታ ማከፋፈያና ማስተባበሪያ ኮሚሽን (እማማኮ)፣ ቀይ መስቀል፣ የካቶሊክ ሚሲዮን፣ (አሁንም ድረስ ቆቦ ይገኛል) የሚባሉ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ስንዴ፣ ዱቄት፣ ዘይት፣ የተለያዩ እሽግ ምግቦችን በማደል ህዝቡን በተቻለ መጠን ረድተዋል:: የየድርጅቶቹን የእርዳታ አሰጣጥ ሁኔታ በማስተዋል አንዳንድ ቃልግጥሞችም ተገጥመዋል::ለምሳሌ፡-

«ቀይ መስቀል ካፊያ ነው
ኮሚሽን ቅቅት ነው
አንጆት የሚያርሰው አባ ዝናቡ ነው»

 የሚለው የተገጠመው በዚያን ጊዜ ነው:: ህዝቡ የካቶሊኮች ድርጅት ሰራተኞችንና ሀላፊዎችን ‹‹አባ›› ይላቸዋል:: ለዚህ ምክንያቱ ሀላፊዎቹ መነኮሳት የሚለብሱት ረጅምና ጥቁር ልበስ ስለሆነ፣ እነዚህን ሰዎች የአካባቢው ሰው የሚጠራቸው አባ እያለ ስለነበር ነው::

የ1977 ዓ.ም የርሀብ ጊዜ መውጫው ላይ የተከሰተው አሳዛኝ ነገር፣ በእንስሳት ላይ የታየው ነው:: አመቱን ሙሉ የቤት ክዳን ሳር ሳይቀር እየተመዘዘ፣ ዛፍ እየተቀፈቀፈ፣ ወዲ (ቁልቋል) እየተለበለበ፣ ለከብቶች ቢሰጥም ከሰው ችግር በበለጠ የከብቶቹ ችግር በረታ:: ከብቶች ሆዳቸው ዋሻ መስሎ ጎድጎዶ፣ አጥንታችው ገጦ፣ በቁማቸው ደረቁ:: በዚህ አይነት ሁኔታ የነበሩት ከብቶች፣ 77 ለ 78 ዓ.ም ክረምት በጣለው ዝናብ ድርቅ የከረመበት ሰውነታቸው ባለመቻሉ፣ ከየበረታቸው እየወደቁ በዚያው ቀሩ:: ከብቶችን እየጎተቱ መጣል በወቅቱ በርሀብ ለተንገላታው ሰው አስቸጋሪ ሆነ::

ምዕራፍ ሶስት፡- ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በቃልግጥም ላይ ከተጠኑ ጥናቶች መካከል የተወሰኑ ጥናቶችን በመከለስ በስነቃል ላይ የተሰጡ ብያኔዎችና አስተያየቶች ተዳስሰዋል፡፡ እንዲሁም፣ ስለፎክሎር፣ ስለስነቃል፣ ስለቃልግጥም ምንነት፣ ጽንሰ-ሀሳባዊ ብያኔዎችና ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ንድፈ-ሀሳቦች ስለሚያነሷቸው ጉዳዮች ገለጻ ከተደረገ በኋላ ለዚህ ጥናት ሊያገለግሉ ይችላሉ የተባሉት ንደፈ-ሀሳቦች ተመርጠዋል፡፡

3.1 የተጠኑ ጥናቶች ዳሰሳ

በቃልግጥም ላይ ከተሰሩት ጥናቶች መካከል የዳንኤል ለገሰን (1998) የብርሃኑ ገበየሁን (1989) የመስፍን መሰለን (2000) የደስታን ካሳን (1985) እና የሌሎችንም ለማየት ተችሏል፡፡ የዳንኤል ለገሰ ጥናት፣ ጎጃምና ጎንደር ውስጥ በደርግ ጊዜ በተፈፀመው የቀይ ሽብር አደጋ ምክንያት የተፈጠሩትን ቃልግጥሞች ከጭብጥ አንፃር የመረመረ ነው:: አላማው በቀይ ሽብር ሰበብ የተፈጠሩትን ቃልግጥሞች በመሰብሰብ፣ አውዳዊ ትንተና ማድረግ ነው:: መረጃውን ሲሰበስብ የተጠቀመበት ዘዴ፣ በተለያየ ቦታ ተዘዋውሮ መረጃ አቀባዮችን በማነጋገር ሀሳብ ከሰበሰበ በኋላ፣ የቡድን ተኮር ውይይት በማካሄድ፣ በቃልግጥሞቹ ይዘትና ጭብጥ ላይ ተሳታፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ ነው:: ቃልግጥሞቹን በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ከፋፍሏቸዋል:: የቃልግጥሞቹ ጭብጥ፣ አካላዊና ስሜታዊ ጉዳቶች እና አልሸነፍም ባይነትን የሚያመለክቱ እንደሆኑ ዘርዝሮ አሳይቷል:: ግርፋት፣ ትልተላ፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ነፃ እርምጃ፣ ጥልቅ ሀዘን፣ ፍርሀት፣ ጭንቀት፣ ስደትና ድንገተኛ ጥቃት፣ የሚያመለክቱ እንደሆኑ አሳይቷል:: ይህ ጥናት በአካባቢም ሆነ በጥናት ትኩረት ከዚህ ጥናት ጋር አይመሳሰልም::

የብርሀኑ ጥናት ከእስልምና ሀይማኖት ጋር የተያያዙ ሀይማታዊ ቃልግጥሞች ላይ የተመሰረተ ነው:: የአጠናን ዘዴው ገላጭ ትንተና ሲሆን በማንኛውም የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ማህበረሰብ ውስጥ እስላማዊ ቃልግጥሞች የሚነገሩባቸው መደበኛ ወቅቶች ወይም በአላት፣ ኢድና ወዳጃ ናቸው:: የቃልግጥሞቹ መከወኛ በአላትን፣ እነማን እንደሚከውኗቸው፣ በየትኛው ማህበራዊና ባህላዊ አውድ የትኞቹ ቃልግጥሞች እንደሚከወኑ፣ በገለፃ አሳይቷል::

መስፍን መሰለ የአባውዴ ቃልግጥምን ባጠናበት ስራው፣ ስለአባውዴዎች ታሪክ፣ መኖሪያ አካባቢ፣ ወዘተ. ገለፃ በማድረግ ጥናቱን ይጀምራል:: የጥናቱ አላማ የአባውዴ ቃልግጥሞችን

ክዋኔና አውድ በመመርመር፣ አደራረሱን፣ አከዋወኑን፣ ተስተላልፎውን፣ እና አመዳደቡን መመርመር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የቃልግጥሞቹን ጭብጥ፣ ተግባር፣ ስልት፣ በመመርመር ትንተና ያደርጋል:: የአባውዴ ቃልግጥሞች በአይነት ሲከፈሉ፣ የሙገሳ፣ የሀዘን፣ የስድብ፣ የምርቃት፣ እና የርግማን ጭብጥ ያላቸው እንደሆነ አሳይቷል:: በተለይ ስለምደባ ባቀረበው ገለፃ የቃልግጥምን ለመመደብ ስድስት መመዘኛዎችን መሰረት ማድረግ እንደሚቻል ያብራራል:: እነዚህም፣ ጭብጥ፣ ተግባር፣ አውድ፣ የከዋኝ ማንነት፣ መዋቅር እና ስልታዊነት እንደሆኑ ይዘረዝራል::

የደስታ ካሳ የባችለር ዲግሪ ማሚያ ጥናት በደርግ ዘመን በተገጠሙት ቃልግጥሞች ላይ ያተኮረ ነው:: አላማው በመንግስት ላይ ህዝቡ ምን አይነት አመለካከት እንደነበረው ለሚያጠኑ ሰዎች መነሻ እንዲሆን ነው:: መረጃውን የሰበሰበው በልዩ ልዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች አማካኝነት ሲሆን፣ ከመፃህፍትና ከጋዜጦችም ጭምር እንደሰበሰበ ይገልፃል:: ቃልግጥሞቹ አስተዳደራዊ ጉድለትን፣ በስልጣን መባለግን፣ ጉቦና ምዝበራን፣ ቀይሽብርን፣ ውትድርናን፣ ስደትን፣ ሰፈራን፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀትን፣ ለትግል መነሳሳትን፣ የሚያመለክቱ ናቸው ይላል::

በሰሜን ወሎ አካባቢዎች፣ በቃልግጥም ላይ ጥናት ካደረጉት መካከል፣ የሞላ መኮንን (1986) «በቆቦ ወረዳ የተነገሩ ፖለቲካ ቀመስ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና» በሚል ርዕስ፣ ከ1966-1985 ዓ.ም ድረስ የተገጠሙትን ተመልክቷል:: ትንተናውም በቃልግጥሞቹ ላይ የተመሰረተ ሆኖ፣ በሰፈራ ምክንያት ሌላ አካባቢ ቆይተው ከተመለሱ ግለሰቦች ስለሰፈሩበት አካባቢ የሚያወሱ ቃልግጥሞች የተካተቱበት ጥናት ነው:: ሌላው፣ የሽመልስ ፍሬው (1974) ጥናት ሲሆን፣ «በአምባሰልና በየጁ አውራጃዎች የወያኔዎች ውጊያና ግጥሞቻቸው» በሚል ርዕስ ያቀረበው ነው:: ይህ ጥናት በአንድ ቡድን (በውጊያ በሚሳተፉት) ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የቃልግጥሞቹን ቅርፅና ይዘት የተነተነ ነው::

ተክለሀይማኖት ገ/ፃድቅ (1988) «በራያ ለጋዛ ዘማቾች ይቀርቡ የነበሩ የጀግንነትና የማነሳሻ ግጥሞች» በሚል ያቀረበው፣ በሁለቱ ራያዎች ላይ የተደረገ ጥናት ነው:: መረጃ የሰበሰበባቸው አካባቢዎች ሲታዩ፣ ዛሬ ትግርኛ ተናጋሪ ተብለው ወደ ትግራይ ክልል በተከለሉት አካባቢዎች ስለሆነ፣ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ የተገጠሙ እንዳልሆኑ እንረዳለን:: (ገፅ 9) ላይ እንደጠቆመው «የተሰበሰቡት ቃልግጥሞች በትግርኛ ጭምር የተገጠሙ ናቸው» ይላል:: ስለዚህ ከዚህ ጥናት ጋር በአካባቢ ቢቀራረብም፣ በቋንቋ የተለየ ነው:: አልማዝ አበበ (1974) «አዝማሪና ግጥሞቹ

በየጁ አውራጃ» በሚል ርዕስ ያቀረበችው ጥናት፣ አዝማሪዎች የት ቦታ ላይ ግጥም ሊያቀርቡ እንደሚችሉ በመከፋፈል ያሳየችበት ነው:: በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት፤ የሞላ መኮንን፣ የሽመልስ ፍሬው፣ የተክለሃይማኖት ገብረጻዲቅ፣ የአልማዝ አበበ ጥናቶች በሰሜን ወሎ አካባቢዎች ለመጀመሪያ ዲግሪ ሚሚያ የቀረቡ ናቸው::

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበው የተስፋየ መሰለ (2007) ጥናት፣ በአካባቢው ከተደረጉት ጥናቶች አንዱ ነው:: ርዕሱም «subject matter Analysis of Amharic lyric Poetry in Raya» የሚል ሲሆን፣ በአምስት ምድቦች ከፋፍሎ በማቅረብ፣ «love, marriage, elegiac, Topical, እና work poetry» በማለት ይተነትናል:: የተስፋየ ጥናት በሁለቱ ራያዎች ውስጥ በአማርኛ በተነገሩት ቃልግጥሞች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል:: በሚሸፍነው አካባቢና ከሱ ጥናት በኋላ የተገጠሙትንና ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችን የማያካትት በመሆኑ፣ ይህ ጥናት ከተስፋየ የተለየ ይሆናል ማለት ነው።

ከነዚህ ጥናቶች በተለየ የአማርኛ ቃልግጥሞችን ሰብስቦ ለማጥናት የቻለ ጥናት፣ የሸበሽ ለማ (1986) «A Thematic Approach to Famine-Inspired Oral Poetry»፣ በሚል ርእስ የቀረበው ነው። ይህ ጥናት፣ ትኩረት ያደረገው በድርቅ ወይም በርሃብ ወቅት ሰዎች የገጠማቸውን ችግሮችና ፈተናዎች፣ ያንፀባረቁባቸውን ቃልግጥሞች ሰብስቦ በመተንተን ላይ የተመሰረተ ነው። የጥናቱ አላማ፣ የቃልግጥሞቹን፣ ጭብጥ በመመርመርና በመተንተን፣ የተጠቂዎቹን ስነልቦና፣ ስሜት፣ ተስፋ፣ ወዘተ. ማስተዋልና መለየት ይቻላል የሚል ነው። አካባቢውም በወሎና በሸዋ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመላው ሀገሪቱ ለእርዳታ ተግበር በተሰማራባቸው አካባቢዎች ሲዘዋወር ያገኛቸውን (የሰማቸውን) ቃልግጥሞች በማሰባሰብ ነው። የሰበሰባቸውንም ቃልግጥሞች በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች መድቦ አቅርቧቸዋል። እነሱም፣ ጭንቀትና ስቃይ፣ አለመረጋጋት፣ ከቅዠት መንቃት፣ ቅሬታና ብስጭት፣ ምስጋና እና ጥንካሬ፣ የሚያመለክቱ ናቸው በማለት፣ ተንትኖ ጥናቱን ይደመድማል። ይህ ጥናት፣ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በድርቅና በርሀብ ወቅት የተገጠሙትን ቃልግጥሞች ሰብስቦ የሚተነትን መሆኑ ነው። ነገር ግን፣ ከሱ ጥናት በሁዋላ የተገጠሙትንና ሌሎች ይዘቶችን የማያካትት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል።

3.2 ጽንሰ-ሀሳባዊ ብያኔዎች

ብያኔ በማንኛውም የምርምርና የሙያ መስክ ቀዳሚና መነሻ ተግባር ሊሆን ይገባል:: በመሆኑም በዚህ ንዑስ ክፍል፣ ስለፎክሎርና ስለስነቃል፣ ስለቃልግጥም ምንነት፣ ስለክዋኔና

አውድ ተዛማጅነት ያላቸውን ሀሳቦችና ብያኔዎች በማብራራት፣ የቃል ግጥምን ማህበራዊ ፋይዳዎች እንዳስሳለን::

3.2.1 ፎክሎር፤ ስነቃልና ቃልግጥም

በዚህ ንኡስ ክፍል ስለፎክሎር ታሪካዊ ብያኔዎች፤እንዲሁም ከፎክሎር ጋር በተያያዙ ፅንሰ-ሃሳቦች ዙሪያ፤ስለ ስነቃልና ተያያዥ ሃሳቦች የተወሰኑ ሃሳቦችን ይዳስሳሉ፤ስለ ቃል ግጥም ብያኔዎችና ፅንሰሃሳቦች ስነጽሁፋዊ ዳሰሳ ወይም ቅኝት ይደረጋል፡፡

3.2.1.1 ፎክሎር

‹‹ብያኔዎች ሁልጊዜም ቢሆን ችግር ያለባቸው እና በቀላሉ የማይታለፉ ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው›› (Fekade፣ 2010፣ 47) ይላሉ:: ይህ አጠቃላይ ሀሳብ ከፎክሎር ብያኔ አንፃር ሲታይ እውነታው የጎላ ነው :: ፎክሎር የሚለው መጠሪያ በእንግሊዛዊው William Thoms እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር በ1846 ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ለሙያው መጠሪያና ለጥናት መስኩም በጋራ የሚያገለግል ስያሜ ሆኖ ቆይቷል:: እንደማንኛውም የሙያ መጠሪያ ስለ ቃሉና ስለ ጥናት ትኩረቱ፣ የተለያዩ አስተያየቶችና ብያኔዎች በተለያዩ ተመራማሪዎች ሲቀርቡ ታይተዋል:: Bauman (1992፣ 29) ላይ የThomsን ብያኔ በመጥቀስ ‹‹Thoms ፎክሎርን የበየነው በመሰረቱ አስፈላጊ የሆኑትን አንዳንድ ቅርጾችን በመዘርዘር ነው፡፡ ይኸውም ፎክሎር የጥንት ዘመን ሁኔታዎችን (manners)፤ ልማዶችን (customs)፤ ክበራዎችን (observances)፤ እምነቶችን (superstitions)፤ አወዳሽ ግጥሞችን (ballads) ተረትና ምሳሌዎችን ወዘተ. የሚያጠቃልል ሆኖ ስያሜው ለልማዳዊና ለባህላዊ ቅርጾች መጠሪያና እነሱን ለሚያጠናው የሙያ ዘርፍ ጭምር የሚውል ነው፡፡...›› በማለት ስለ ፎክሎር ምንነትና ስለ ጥናት መስኩ ይገልጻሉ::

በሌላ በኩል ፎክሎር (Folk-Lore) የሚለው መጠሪያ የሁለት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ጥምረት ሲሆን፤ እነሱም‹‹ፎክ›› (Folk) እና ‹‹ሎር›› (Lore)፣ናቸው፡፡ ይህ በራሱ አከራካሪ እንደሆነ ይታወቃል:: የቃላዊ ፈጠራ ባለቤት የሆነው አንድ የተወሰነ ቡድን፣ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት የጋራ እውቀቱ ወይም ሎሩ፣ ያንን ቡድን በተለያየ ደረጃና አተያይ እንዲገለፅ አድርጎታል:: ቀደም ያሉትን ጥናቶች ጠቅሰው Schoemaker (1990፣ 4) እንዳብራሩት «ፎክ» የሚለው ቃል ወይም ስያሜ እንደ ጀርመናዊያኑ ወንድማማቾች (Jacob and Wilhelm Grimm) ‹‹ሀገር›› (nation) ሲሆን፣ እንደ Edward B.Tylor ደግሞ፣ ‹በስልጣኔ ደረጃ ላይ ያልደረሰ የህብረተሰብ ክፍል ነው› ይላሉ:: እንደ Robert Redfield አገላለፅ ደግሞ፣

‹ቡድኑ አነስተኛ፣ የተነጠለ፣ ያልተማረ፣ እና አንድ ወጥ ሆኖ፣ የቡድናዊ አንድነቱና ስሜቱ ጠንካራ የሆነ› በማለት እንደገለፁት ያስረዳሉ:: እነዚህ ገለፃዎች በአንዳንድ የስነቃል ተመራማሪዎች ዘንድ እንደ ነውር (taboo) ተደርገው ስለሚቆጠሩ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው::

ፎክሎርን እንደ አንድ ፅንሰ ሀሳብ አድርጎ በመበየን ረገድ፤ የተሻለ ብያኔ ሆኖ የሚወሰደው የAlan Dundes ብያኔ ነው:: እሳቸው እንደሚሉት የፎክሎር ብያኔ ማከራከር የጀመረው ቃሉ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ከገለፁ በኋላ፣ የራሳቸውን ብያኔ ‹‹ ጀማሪው ፎክሎርን ምን ማለት እንደሆነ ሊረደው በሚችለው መንገድ መበየን ይቻላል፡፡ይኸውም ፎክ (folk)ንና ሎርን (lore) ለየብቻ በመበየን ነው፡፡... ፎክ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ማንኛውም የሰዎች ቡድን ሆኖ፤በማንኛውም ሁኔታ ቡድኑ ቢያንስ አንድ የጋራ ባህሪ ያለው፤ በማንኛውም መንገድ የራሴ ብሎ የሚያስባቸው ልማዶች ያሉት ነው (Dundes in Fekade፣ 2003፣ 105-106) በማለት ይገልጻሉ:: ይህ ብያኔ በአንዳንድ ተመራማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ስለፎክሎር ብያኔ በሚነሱ አስተያየቶች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል:: ለምሳሌ Bauman (1992፣29-30) ‹‹folklore›› በሚለው ንኡስ ክፍል ወይም መጣጥፍ ውስጥ፣ ስለ ‹‹ፎክ›› አከራካሪነት እና ስለነበረው የተዛባ አስተያየት ካብራሩ በኋላ የራሳቸውን የተሻለ አማራጭ የብያኔ አቅጣጫ ጠቁመዋል፡፡ ‹‹ስለፎክሎር ብያኔ ስናስብ ከሚይዛቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ተነስተን ወደ አንድ ማጠቃለያ ብያኔ ለመድረስ መሞከር የተሻለ ነው:: ለፎክሎር አንድ ነጠላ ብያኔ ከማቅረብ ይልቅ ልማዳዊነትን፣ ማህበራዊ መሰረትን፣ እና ስነውበታዊነትን፣ አጠቃሎ በያዘ ሁኔታ መሆን እንዳለበት Bauman (1992፣ 30-40) ያስረዳሉ::

ከዚሁ ጋር በማያያዝ፣ ልማድ በተለምዶ መንታ ስሜት በሚሰጥ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውል ነው:: ይኸውም የአንድን ባህላዊ መሰረታዊ ነገር ወይም ባህሪ በጊዜ ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ ሂደት እና በዚህ ሂደት ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ የሚተላለፈው መሰረታዊ ነገር አንድ ላይ ሆነው የሚታዩበት ፅንሰ ሀሳብ ነው (ገፅ 31) ይላሉ:: ከማህበራዊ መሰረት አንፃር መነሻ የሚሆነው ማህበራዊ ቡድኑን የተመለከተ ነው:: ይህም ከላይ የተጠቀሰውን የDundesን አጭር ብያኔ ‘አንድ የጋራ ባህሪና የኔ የሚለው ልማድ ያለው’ እንደሆነ ይጠቅሳሉ (ገጽ 35)፡፡ ስነ ውበታዊነቱን በሚመለከት መሰረታዊ ባህሪያቱ የሚሏቸው ጉዳዮች ቃላዊነት እና በጥበብ የተሞላ መሆን ናቸው፡፡ ይህንን አስተያየት የቤን አሞስን አጭር ብያኔ በማካተት ‹ፎክሎር በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚታይ የፊት ለፊት ጥበባዊ ተግባቦት

ነው በማለት፣ የቤን አሞስ እና የአለን ደንደስ ብያኔዎች በፎክሎር ጥናትና ብያኔዎች ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንደሆኑም Schoemaker (1990፣39) ጨምረው ይገልጻሉ::

ጥበባዊ ተግባቦትን በሚመለከት የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር እንደመሆኑ በለት ተለት ህይወቱ ውስጥ የተግባቦት ስሜትና ፍላጎት ይኖረዋል:: አንድ ግለሰብ ከሌላው ግለሰብ፣ አንድ ቡድን ከሌላው ቡድን፣ አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር የመወያየት የመቀራረብ፣ በአጠቃላይ የመግባባት ፍላጎት ይኖረዋል:: ይህ ፍላጎት በጋራ በሚፈጠር መስተጋብር ይንፀባረቃል:: እንዲሁም ይህ የመግባባት ዘዴ ጥበባዊ ባህሪ ይኖረው ዘንድ ከተራውና ከለት ተለት የመግባባት መንገድ ለየት ብሎ መቅረብ አለበት:: ተግባቦቱ ትኩረት የሚስብ፣ ገላጭና መሳጭ መሆን ይኖርበታል:: ይህን ጥበባዊ ተግባቦት በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች መድቦ ማየት እንደሚቻል Schoemaker (1990፣ 3) ላይ ‹‹ሰው የሚናገራቸው ነገሮች (things people say)፣ ሰው የሚያደርጋቸው ነገሮች (things people do) እና ሰው የሚሰራቸው ነገሮች (things people make)›› በማለት ይዘረዝራሉ::

እነዚህ ነገሮች በፎክሎር ብያኔ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ናቸው:: እንደ ከበራዎች፣ ድራማዊ ሁነቶች፣ ሙዚቃዊ ክዋኔዎች፣ የጥበብ ኤግዝቢሽኖች፣ ወዘተ. ያሉት ሰው ለሚያደርጓቸው ነገሮች እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ሲሆኑ፣ እነዚህም የባህል ገላጭ ቅርፆች በመሆናቸው ከሌላው ተግባቦት በግልፅ ተለይተው የሚታወቁ ናቸው:: ሰው የሚናገራቸው ነገሮች ሲባል ደግሞ፣ በሁለት ሰዎች መካከል በሚደረግ ተግባቦት ውስጥ በሚፈጠረው መስተጋብር ያለውን ሁኔታ የሚመለከት ነው:: ሰዎች በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ መወያየት ቢፈልጉ ያንን ጉዳይና ሀሳብ የሚለዋወጡበት መንገድ ከወትሮው ለየት ያለ መሆን አለበት:: ሀሳቡን አጠናክሮና ሳቢነት እንዲኖረው አድርጎ ለማቅረብ በሚያስችል አገላለፅ ማቅረብ ያስፈልጋል:: ለዚህ የሚረዱት ደግሞ፣ እንደ ተረትና ምሳሌዎች፣ ቀልዶች፣ ግጥሞች፣ አባባሎች፣ ወዘተ. ያሉት ናቸው:: እነዚህ ቅርፆች ተግባቦቱን ጥበባዊና ማራኪ እንዲሆን የሚያደርጉ በመሆናቸው በፎክሎር ብያኔ ውስጥ ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ናቸው::

ሰው በሚሰራቸው ነገሮች ላይ የተለያዩ ነገሮችን ያደርጋል:: ለምሳሌ፣ በሚለብሰው ባህላዊ ልብስ ላይ የሚያደርጋቸው ጌጣጌጦችና ጥልፎች ልብሱን ከመሰራት ጨምሮ አንዱ ከሌላው የተለያየ ነው:: እንዲሁም፣ በባህላዊ የቤት እቃዎች ላይ የሚያደርጋቸው ማስዋቢያዎች፣ በባህላዊ ቤት ጣሪያና ግድግዳ ላይ የሚያደርጋቸው የተለያዩ ነገሮች (ቅቦች፣ ስዕሎች፣ ቅርፆች፣) በአጠቃላይ በቁሳዊ ባህሉ ላይ የሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ነገሮች ትኩረት ከመሳብ

አልፈው፣ ማንነትን፣ ባህልን፣ አኗኗርን፣ አካባቢን፣ እስከ ማመልከት ይደርሳሉ። እነዚህ የሰው ልጅ መስተጋብሮች በፎክሎር ብያኔና ምንነት ላይ ትርጉም ያላቸው ስለሆኑ ጠቃሚ ናቸው።

ፎክሎር የሚለውን የሙያ መጠሪያና የጥናት መስክ ለመበየን ሲፈልግ ከሁለት ዘርፎች አንፃር እየታየ መሆን እንዳለበት Schoemaker (1990፣ 5) እንዲህ ይላሉ ‹‹... ፎክሎር የሚለው ስያሜ ሰፊ ትርጉም ያረገዘ ቃል ሆኖ፤ ትርጉሙ ባህላዊ (cultural) እና ስነማህበረሰባዊ (sociological) ዘርፎች (dimenssion) ያለው ነው። በባህላዊ ዘርፉ ሲታይ ከገላጭ ባህሎች ጋር የተያያዘ ሲሆን፤በስነማህበረሰባዊ ደግሞ፤ ከሀገረሰባዊ ቡድኑና እሱን ከሚመሰርቱት ጽንሰ ሀሳቦች ጋር የተያያዘ ነው።››

ስለፎክሎር ምንነት ይህንን ያህል የመነሻ ሀሳብ ካገኘን፣ በዚህ የጥናት መስክ ውስጥ ተካትተው የሚጠኑት ነገሮች ወይም ጉዳዮች ምንድን ናቸው የሚለውን ጥያቄ ጠቅለል አድርገው የሚጠኑትን ነገሮች (Bascom፣ 1972፣ 2-5) ዘርዝረው ያቀርባሉ።

እነዚህም አራቱ የፎክሎር ዘርፎች የሚባሉት ሲሆኑ፣ እነሱም፣ ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ና ሀገረሰባዊ ልማዶች ናቸው። እነዚህ ዘርፎች ለየብቻ ሲታዩ በውስጣቸው የተለያዩ ነገሮችን አቅፈው የያዙ ናቸው። በስነቃል ውስጥ፤ ዝርው ተረኮች፣ ቃል ግጥሞችና አጫጭር ቅርፆች የሚባሉት ይገኛሉ። እነዚህም በፈንታቸው የተለያ አይነቶች በውስጣቸው አሏቸው። በቁሳዊ ባህል ውስጥ የባህላዊ ቤት አሰራር፣ አልባሳት፣ የባህላዊ ምግቦች አሰራር፣ በአጠቃላይ በአይን የሚታዩትን በእጅ የሚዳሰሱትን የሰው ልጅ ፈጠራዎች የሆኑትን ቁሳቁሶች የሚያጠቅል ሲሆን፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የሚባሉት ደግሞ ባህላዊ ዘፈኖች ወይም መዚቃዎች፣ ባህላዊ ጭፈራዎችና ዳንሶች፣ እንዲሁም ባህላዊ ድራማዎችን የሚያጠቃል ነው። ሀገረሰባዊ ልማዶች የሚባሉት ከአንድ ህብረተሰብ ባህላዊ እምነትና አስተሳሰብ ጋር ተያይዞ በአንድ በተወሰነ ቦታ፣ በአንድ በተለየ ወቅትና ጊዜ፣ ሰዎች በጋራ የሚያደርጓቸው ነገሮች ናቸው። የሽግግር ስርአት ከበራዎች፤ የመዚቃ፣ የዳንስና የአልባሳት ፌስቲቫሎች፣ ወዘተ. በሀገረሰብ ልማድ ውስጥ የሚጠኑ ነገሮች ናቸው። ስለዚህ፣ ፎክሎር ማለት፣ ስነቃልን፣ ቁሳዊባህልን፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን፣ እና ሀገረሰባዊ ልማድን በአንድ ላይ አጠቃሎ የሚያጠናውን የሙያ መስክና ሙያው የሚጠራበትን ስያሜ ባንድ ላይ አጣምሮ የያዘ ስያሜ ወይም መጠሪያ ማለት ነው።

3.2.1.2 ስነቃል

ስነቃል ለዝርው ተረኮች ወይም ለሀገረሰብ ተረኮች፣ ለቃልግጥሞች፣ እና ለአጫጭር ቅርፆች የጥቅል መጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል ስያሜ ነው:: ይህንን የጥቅል መጠሪያ የዘርፉ ተመራማሪዎች በተለያየ መንገድና አተያይ ይበይኑታል:: ለምሳሌ፣ ዘሪሁን (1992፣ 20) እንደሚሉት ‹‹ስነቃል በመነገር፣ በመተረት፣ በመዜም፣ በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን፣ የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ እንዲሁም ታሪክ፣ ማስተላለፊያና፣ ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ፣ ኪነጥበብ ነው›› በማለት ይገልጹታል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ ስነቃል በአንድ ማህበረሰብ ወይም በህዝቦች መካከል በሚኖር መስተጋብር ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን አገልግሎት በተለያዩ አንቀፆች እንደሚከተለው አቅርበውታል::

> በስነቃል ህዝቦች... ሀዘን ደስታቸውን ምኞት ተስፋቸውን ፍቅር ጥላቻቸውን... ድጋፍ ተቃውሞአቸውን ... ያንፀባርቁበታል::..ሰናይ የሚሏቸውን ማህበራዊ እሴቶች ... ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ፤ እኩይ የሚሏቸውን ደግሞ እንዲወገዱ ያደርጉበታል:: በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ስደት፣ ርሀብ፣ በሽታ፣ ጦርነት ... በስነቃል ይገለጻሉ፣ ይታወሳሉ::... በተለያየ ማህበራዊ አጋጣሚዎችና ተግባራት ላይ ለማህበረሰቡ ጀግኖችና ተደናቂ ግለሰቦች የሚዜሙና የሚነገሩ ግጥሞች ... ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች... ያሉበትን ሁኔታ በማጤን... ድጋፍ ተቃውሞቸውን ይገልፃሉ፣ ያለፈውን ያስታውሳሉ፣ የወደፊቱን ይተነብያሉ፣ ... ለህልውናቸው ምክንያት ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች ያሞግሳሉ፣ ድክመትና ጥንካሬን ይመረምራሉ፣ ህፃናቱንና ወጣቶችን ያስተምራሉ:: (ዘሪሁን፣ 1992፣ 20-21)

በአፍሪካ ስነቃል ጥናትና ምርምር ላይ ሰፊና ጥልቅ ጥናት እንዳደረጉ ከሚጠቀሱት የስነቃል ተመራማሪዎች መካከል Finnegan (1970) እና Okpewho (1992) ናቸው ማለት ይቻላል:: እነዚህ ተመራማሪዎች ለስነቃል የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል:: ለምሳሌ Finnegan (1970፣ 2) ላይ ‹‹የስነቃል ፍች በቃል ከሚያበጀው (formulate) ከዋኝና በሚከወንበት አጋጣሚ ላይ የተመሰረተ ነው:: ከዚህ ውጭ እንደ ስነጽሁፋዊ ውጤት ለመረዳት የሚቻልበት ሌላ መንገድ የለም» በማለት ይገልፁታል:: በዚህ ገለፃ እንደሚስተዋለው ስነቃል ከከዋኙ፣ ከቃላዊነቱ፣ አንባር እና የተለየ የክዋኔ አጋጣሚ የሚፈለግ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: የስነቃል ከዋኝ

አንድን ስነቃላዊ ቅርፅ ከሌሎች ጋር በመሆን፣ በአንድ በተወሰነ ቦታና አጋጣሚ በቃል ይከውናል፣ ሌሎቹም በቃላቸው ሰምተው በሌላ አጋጣሚና ሁኔታ መልሰው ይከውኑታል ማለት ነው::

ስነቃል የፎክሎር አንድ ቃላዊ ገፅታ (Verbal aspect of folklore) እንደ ሆነ በመጠቆም ስለብያኔው የ Nandwa እና የ Bukenyaን ትርጉም (ፍች) በመውሰድ ‹ ስነቃል ምናልባት ሊበየን የሚችለው ተነገረም፤ ተደረደረም፤ ወይም ተዘፈነ፤ አገላለጹ፤ አደራረሱ፤ እና አከዋወኑ በሚደነቅ ደረጃ የሚታይ ሆኖ፤ ትክክለኛ ምልከታ የጠራ ምናብ እና እጹብ ድንቅ አገላለጹ ጥበባዊ የሆነ በሚለው ነው› (Okpewho፣1992፣4-5) ይላሉ:: ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው፣ የሚዘፈነውም ሆነ የሚደረደረው፣ ወይም የሚነገረው ስነቃል፣ በክዋኔው ሂደት በሚደነቅ ሁኔታ፣ ጥበባዊ ባህሪ የሚታይበት ሆኖ፣ ትክክለኛ ምልከታና ደማቅ ምናብ የሚታይበት፣ እፁብ ድንቅ የሆነ አገላለፅ ያለው ሁሉ፣ በስነቃል ደረጃ ሊታይ የሚችል ነው::

ብርሃኑ (1995፣3-5) Albert Lordን እና Okpewhoን ጠቅሰው እንዳስረዱት ‹...ስነቃል ማለት ቃላት በጥበብ መልክ በሚደመጡበት ጊዜ ነው::... በቀላል አገላለጽ ስነቃል በአንደበት የሚገለጽ ስነጽሁፍ ነው::› ካሉ በኋላ ‹‹ስለ ስነቃል ምንነትና ብያኔ ከመቸገር ይልቅ ተለይቶ የሚታወቅባቸውን ባህሪያቱን በማሳየትና በማብራራት ስለ ምንነቱ፣ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ይቻላል ...፣ስነቃል ከሌሎች የጥበብ ዘርፎች ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህሪያቱ ክዋኔ፣ አውዳዊነት (የመከሰቻ አጋጣሚ ፈላጊነት)፣ የተደራሲያን መኖር፣ ተለዋዋጭነትና ልማዳዊነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው››ይላሉ::

3.2.1.3 ቃልግጥም

ቃልግጥም በአንዳንድ የስነቃል ተመራማሪ ስራዎች ውስጥ ስያሜው የተለያየ ሆኖ ይገኛል:: ለምሳሌ Okpewho (1992፣ 127-138) የቃል ግጥምን ሁኔታ በሰፊው የመረመሩበትን ክፍል ስናየው ስያሜያቸው «ዘፈኖችና መዝሙሮች» የሚል ሆኖ እናገኘዋለን:: በዚህ ንዑስ ክፍል እንደተብራራው ትኩረት ሰጥተው ያቀረቡት ገለፃና ትንተና በቃልግጥሞች አመዳደብ፣ ባህሪያትና አቢይ ጭብጦች ላይ የተመሰረተ ነው::

Ben Amos (1982፣ 20-22) ‹‹ስነፅሁፍና ሀገረሰብ ስነፅሁፍ›› በማለት ባቀረቡት ገለፃ ውስጥ ‹ከሰለጠኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር የሀገረሰብ ግጥም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያልደረሰ

ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግጥም ነው› መባሉን ይገልፃሉ:: ይህ አስተሳሰብ ያልሰለጠነው የማህበረሰብ ክፍል ከሰለጠነው ማህበረሰብ ጋር የሚነፃፀር ቃላዊ ፈጠራ የለውም፤ የከያኒው ወይም የፈጣሪውም ሆነ የታዳሚው ችሎታ ከሰለጠነው የማህበረሰብ ክፍል ጋር የሚወዳደር አይደለም የሚል አንድምታ ያለው ነው::

Finnegan (1977፣ 7) Lord ን ጠቅሰው እንደገለፁት '... ቃልግጥም መፃፍና ማንበብ በማይችሉ ሰዎች በቃላዊ ክዋኔ ውስጥ የተደረሰ ግጥም ሆኖ ... ከልማዳዊና ከሀረገሰባዊ ግጥም ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው' ይላሉ:: ምንም እንኳ አስተሳሰቡን የስነቃል ተመራማሪዎች የማይደግፉት ቢሆንም፣ ብያኔው ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው:: መፃፍና ማንበብ የማይችሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደ ሰለጠኑት ህዝቦች የተወሳሰበ የስነፅሁፍ እድገት ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም፣ የፈጠራ ስራቸውም ከራሳቸው ተፈጥሮአዊ ክልል የሚወጣ አይደለም የሚል አስተሳሰብ ያለው ነው:: Finnegan (9-13) አያይዘው እንዳብራሩት፣ የቃልግጥም አይነቶች የሚባሉት፣ ኤፒክ (Epic)፣ ባላድ (Ballad) ፣ እና ሊሪክ (Lyric) ናቸው:: ኤፒክና ባላድ ረጃጅሞችና በተወሰነ የአለም ክፍል የሚገኙ ሲሆኑ፣ ሊሪክ ግን በአንፃራዊነት አጭርና ተራኪ ያልሆነ፣ በሰው ልጅ ባህል ውስጥ በስፋት ተሰራጭቶ የሚገኝ፣ ምናልባትም አለማቀፋዊ ቅርፅ (አይነት) ነው:: ሊሪክ ከአለማቀፋዊነቱ በተለየ፣ አፍሪካ ውስጥ በሰፊው እንደሚገኝ Finngan (1970፣ 241) እንዲህ ይላሉ «ከሰሀራ በታች (sub-Saharan) ባሉት የአፍሪካ አገሮች ምናልባት በብዛት የሚገኘው የግጥም ቅርጽ ሊሪክ ነው።... ሊሪክ አጭርና የሚዘፈን ሆኖ፣ ከአፍሪካ የስነቃል አይነቶች አንዱና በጣም ጠቃሚው ነው::»

ስለ ቃልግጥም ብያኔ፣ ብርሃኑ (1995) እና ፈቃደ (1991) ተመሳሳይ ሀሳብ ሰንዝረዋል:: ለምሳሌ ፈቃደ፣ (1992፣ 84-86) ስለቃልግጥም ባቀረቡት ገለፃ ውስጥ ብያኔውን በሚመለከት የሚያስጠነቅቁት ሀሳብ አላቸው:: «ቃል ግጥም ማለት በቃል ተደርሶ በቃል የሚከወን፣ በቃል የሚተላለፍ ግጥም ሁሉ ነው ብለን ብንበይን ስህተተ ላይ እንወድቃለን» ካሉ በኋላ፣ ቃልግጥምን እንዲህ በማለት ይበይኑታል:: «ቃልግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮ እና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው» ይላሉ:: በዚህ ብያኔ መጨረሻ ላይ የምናገኘው «ህዝባዊ ግጥም» የሚለው ቃላዊ ቅርፁን (ግጥሙን) ማንኛውም የዚያ ቡድን ወይም ማህበረሰብ አባል የሆነ ሁሉ፣ ችሎታው እስከፈቀደለት ድረስ እያስታወሰ፤እየጨመረ፤እየቀነሰ ሊያዜመው እንደሚችል ለማመልከት ነው::አብዛኛውን ጊዜ

ህዝባዊ ባህሪ ሊኖረው የሚችለው በስርጭቱ (በተስተላልፎው) እና በክዋኔው ነው፣ ፈጠራው ግን፣ ግለሰባዊ ነው ማለት ይቻላል::

እንዲያውም አንዳንዶቹ ቃልግጥሞች፣ ከፈጠራቸው ግለሰብና ከተፈጠሩበት ምክንያት ጋር ለረዥም ጊዜ ሲታወሱ የመኖር እድል ያላቸው ይመስላል:: ለምሳሌ፣ ለዚህ ጥናት በተመረጠው አካባቢ የሚገኙት ባህላዊ ተጫዋቾች፣ (አዝማሪዎች)፣ ያቀነቀኗቸው ግጥሞች ባብዛኛው በውል የሚታወቁባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ አጥኚው ያስታውሳል:: የአዝማሪ ተገኘ ጉባይና የበሪሁን አብተው፣ ቀደም ካሉት ደግሞ የአሊ ጡሀና የታየ ለገሰ ግጥሞች ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው:: በተለይ ማህበራዊ እውቅና ላላቸው የማህበረሰቡ አባላት ለሆኑ ግለሰቦች ማወደሻና ማሞገሻ የተገጠሙ ቃልግጥሞች፣ እንዲሁም በአካባቢው ለተከሰቱ ክስተቶች የተገጠሙ ቃልግጥሞች፣ ወዘተ. አንዴ ከተፈጠሩና ከተዜሙ በኋላ በማህበረሰቡ ዘንድ እየታወሱ ይኖራሉ እንጂ፣ ለሌላ ግለሰብ ወይም ለሌላ ሁኔታ ደግመው አገልግሎት የሚሰጡበት አጋጣሚ ብዙም አይስተዋልም:: በየዘመኑ የሚነሱ ሌሎች ማህበራዊ እውቅና ያላቸው ግለሰቦችና አዳዲስ ክስተቶች ሲታዩ፣ ለነሱ ተስማሚ የሚሆኑ አዳዲስ ቃልግጥሞች ይፈጠራሉ፣ ተለውጠውና ተሻሽለው ይገጠማሉ እንጅ፣ የአንዱ ለሌላው ተደግሞ አይከወንም::

ብርሃኑ (1995፣31) ቃልግጥምን በሚከተለው ሁኔታ ይበይኑታል::‹‹ቃልግጥም ሙዚቃዊነት በሚሰማባቸው በዘፈን፣ በቀረርቶ፣ በእንጉርጉሮ፣...የሚከወኑ ጥበቦችን የሚጠቀልል ... ነው:: ቃልግጥም፣ እጅጉን የሚዘወተር፣ በጣሙን ደግሞ ልዩ ልዩ መልኮች ያሉት ጥበብ በመሆኑ እያንዳንዱን ዘፈን፣ እንጉርጉሮ፣ ቀረርቶ...፣ ከሌላው ጋር ... ለይቶ ለመመደብ አስቸጋሪ ነው:: ቃልግጥምን ለመመደብ መሰረታዊ የሚሆኑት መንገዶች ቀያዊ ስያሜዎች፣ ጭብጦች እና አውዶች አንደሆኑ››

ጨምረው ያስረዳሉ::በቃልግጥም ጥናት ታሪክ አብዛኛውን ጊዜ በምሳሌነት እየተጠቀሱ የምናገኛቸው የኤፒክና የባላድ ቅርፆችን ነው:: ለምሳሌ Finnegan (1977፣58) እንደሚያስረዱት የእነዚህ ቅርፆች ፈጠራ (ድረሳ) መሰረቱ ትውስታ ነው የሚሉ ወገኖች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ ሁኔታው ሲታይ ግን ከቅርፆቹ መርዘም የተነሳ ትውስታ ለቃል ግጥም መፈጠር እንደ ዋና መሰረታዊ ባህሪ መታየት የለበትም በማለት ይተቻሉ::

ከዚህ አንፃር፣ እንደነዚህ አይነት ቅርፆች በኛ ሀገር በጥቅሉ፣ በተለይም ለጥናት በተመረጠው አካባቢ ይገኛሉ ተብሎ ስለማይታሰብ፣ ስለቃልግጥም አፈጣጠርና ስርጭት ስናስብ ከራሳችን አውድ ጋር የተገናዘበ ሊሆን ይገባል ማለት ነው:: ስለሆነም፣ በኛ ሀገር (በተለይ ለጥናት በተመረጠው አካባቢና ክልል) እያንዳንዱ አጋጣሚና ክስተት፣ የየራሱ ቃልግጥም ይገጠምለታል / ይገጠምበታል:: በየዘመኑ የሚገኙት ገጣሚዎች ክስተቱን፣ በአጠቃላይ የዘመኑን መንፈስ፣ መነሻ አድርገው ቃልግጥሞችን ይፈጥራሉ:: እንደነዚህ አይነት የዘመን አሻራ ያረፈባቸው ወይም የሚንፀባረቅባቸው ቃልግጥሞች ለታሪክ ማጣቀሻነት ያገለግላሉ::

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የቃላዊ ግጥም ቴክስቶች፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ወይም በዚያው በዘመኑ ባለው ትውልድ መካከል እየተላለፉ የሚመጡ የዘፈን ግጥሞች ይኖራሉ:: እነዚህም በቅብብሎሽ ሂደት እየተለወጡ፣ እየተሻሻሉ፣ ቃላት ወይም ሀረጋትን እየጨመሩና እየቀነሱ፣ ለሚከወኑበት አውድና ሁኔታ ተስማሚ እንዲሆኑ ተደርገው የሚዜሙ ይሆናል:: በእንደዚህ አይነቶቹ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ውስጥ፣ ገጣሚው አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ ታዳሚውን የማስደሰትና የመፍጠር ችሎታውንም ሊያሳይ የሚችልበት እድል ያገኛል (Finnegan ፣1977፣ 133)ይላሉ::

3.3 ክዋኔ

ክዋኔ በስነቃል ጥናት ሂደት አስፈላጊና ሊታለፍ የማይገባው መሰረታዊ የምርምር ተግባር እየሆነ መምጣቱን የስነቃል ተመራማሪዎች ያስረዳሉ:: "በስነቃል ጥናት ውስጥ ... የክዋኔ ጥናት አንደኛው አስደሳችና አበረታች እድገት እየሆነ መጥቷል" (Opkewho፣ 1992፣ 42):: ይህ ተግባር ስነቃሉን ወይም ቃልግጥሙን በተገኘበት አካባቢ ባለው ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ ተመርኩዞ የማጥናትን አስፈላጊነት የሚያስገነዝብ ነው:: ክዋኔያዊ የስነ ቃል ጥናት መሰረቱ መስክ ላይ የሚሰበሰበው አውዳዊ መረጃ ነው:: ክዋኔ የስነቃል አይነቱ (ቅርፁ) የተሟላ ህልውና የሚያገኝበት የተግባቦት ሂደት ነው:: አንድ የስነቃል አይነት እስካልተከወነ ድረስ ህልውናው አስቸጋሪ ይሆናል:: የቃልግጥም ክዋኔ ከዜማ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ የግጥሙ ውበትና መልዕክት ጎልቶ የሚታየው በክዋኔ ሂደት ነው:: ይህንን በሚመለከት፡-

> ቃልግጥም ... ቃላዊ ቴክስት አለው ... ወደ ተሟላ ደረጃ እንዲዳረስ ከተፈለገ መከወን አለበት:: ቴክስት ብቻውን ቃልግጥሙን የተሟላ አያደርገውም:: ይህ የቃልግጥም አቢይ ገፅታ፣ አንዳንድ ጊዜ እየተረሳ

> መጥቷል ... ቃላዊ ባህሪያቱ ማለትም ስልቱና ይዘቱ፣ ምናባዊነቱ፣ ተስተላልፎው፣ ወሳኝ ቢሆኑም ክዋኔ ግን ሙሉ ያደርገዋል ። ... እንዳይጠፋና ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል። ... የከዋኙ ክሂልና ስብዕና፣ የታደሚው አይነት፣ የክዋኔው አውድ፣ ጠቃሚ ናቸው (Finnegan፣ 1977፣ 28-29) ይላሉ።

በመሆኑም የቃልግጥም ክዋኔ ከሚከወንበት ርዕሰ ጉዳይና ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው። በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የሚከወኑት የቃልግጥም አይነቶች ለሚከወኑበት ጉዳይና አውድ ተስማሚ መሆን አለባቸው። በምን አይነት ሁኔታና አጋጣሚ የትኛው አይነት ቴክስት ይቀርባል የሚለውን መለየት ያስፈልጋል ማለት ነው። ለምሳሌ፣ሰርግ ላይ የሚቀርቡ ቃልግጥሞች፣ ከሰርጉ ድባብ ጋር የተያያዙ ሙገሳዎችና ውደሳዎች መሆን አለባቸው እንደማለት ነው።

ከዚህ ጋር ተቀራራቢ በሆነ መንገድ ስለክዋኔ ምንነትና ሁኔታ ሰፊ ገለፃ የምናገኘው በMartha C. Sims እና Martine Stephens (2005፣ 128-129) ማብራሪያ ውስጥ ነው። «ክዋኔ ግላዊያዊ ድርጊት ሆኖ፣ተሳታፊ የሚፈልግ፣ ደስታን የሚጨምርና ምላሽ መስጠትን የሚጋብዝ ነው። ክዋኔ እንዲኖር ተቀባይነት ያለው መቼት፣ ተሳታፊዎች፣ ከዋኝ-ተደራሲ፣ መኖር አለባቸው።» ክዋኔ ተሳታፊ የሚፈልግ ነው ሲባል በክዋኔው ውስጥ እነማን ይሳተፋሉ? እድሜያቸውን፣ ጾታቸውን፣ ማህበራዊ ደረጃቸውን፣ ወዘተ. የሚመለከቱ ማህበረ ባህላዊ ስምምነቶችን የሚመለከት ነው። ሴቶችና ወንዶች በየትኞቹ ክዋኔዎች በአንድ ላይ ወይም ለየብቻ ይሳተፋሉ? ወጣቶችና ጎልማሶች፣ እንዲሁም በእድሜ የገፉ የማህበረሰሰቡ አባላት የሚሳተፉባቸውና የማይሳተፉባቸው፣ የሚሉት ጉዳዮች ከክዋኔ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።

ክዋኔ ደስታን ይጨምራል ሲባል የቃላዊ ግጥሙን ጥበባዊ ፋይዳ የሚያሳይ ይሆናል። ከሚዘፈነው ዘፈን፣ ከሚጨፈረው ጭፈራ፣ ወዘተ. እንዲሁም ከአቀንቃኙ የድምፅ አወራረድና ቃና፣ ከሚደረደሩት ስንኞች ይዘት፣ ተነስተን ከራሳችን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘን ስንረዳው የሚኖረን ደስታ፣ ባጠቃላይ ስሜት ነክ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህንን የስሜት መነሳት በሚመለከት «ቃልግጥም ልዩ ችሎታ ባለው ታዋቂ ዘፋኝ እንደገና የሚፈጠርና የሚተላለፍ ነው» (Dorson፣ 1972፣ 86) ይላሉ። ክዋኔ ምላሽ መስጠትን ይጋብዛል ሲባል በክዋኔው ውስጥ የሚታደሙ ተሳታፊዎች፣ የክዋኔው አይነት በሚፈቅደው

ባህላዊ ደንብ መሰረት በተለያየ መንገድ እና ደረጃ መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ለምሳሌ፣ በመቀበል፣ በማጀብ፣ በማገዝ፣ በአጠቃላይ በንቃት በመሳተፍ የክዋኔውን ጥበባዊነትና ተጨባጭነት በቀላሉ ለማስተዋል ይቻላል ማለት ነው::

Elizabeth C.Fine (1984፣ 1) እንደሚሉት ደግሞ ከ1970ዎቹና ከ1980ዎቹ ጀምሮ የስነቃል ጥናት ትኩረቶች ክዋኔና አውድ ተኮር ዘዬዎች እየሆኑ እንደመጡ ነው:: ስለክዋኔ ሲገልፁም «... ክዋኔ ከቃላት በላይ ነው:: ... ስለክዋኔ እስካሁን የምናውቀው በጣም ትንሽ ነው:: ... ይህም የሆነበት ምክንያት... ክዋኔ አጭር ጊዜ የሚፈጅና አላፊ-ጠፊ በመሆኑ ነው»:: የክዋኔ ከቃላት በላይ መሆን መገለጫዎቹ ማጀቢያዎቹና አካላዊ እንቅስቃሴዎቹ ናቸው:: የቆይታ ጊዜውም እንደሚከወነው የስነቃል አይነትና እንደከዋኙ/ኞቹ ሁኔታና ተነሳሽነት ወይም መቀስቀስ የሚወሰን ይሆናል:: ለዚህም ይመስላል ክዋኔን በቀላሉ ለመያዝ አስቸጋሪ ነው የሚባለው::

በአጠቃላይ ማንኛውንም ስነቃል ተከዋኝ በመሆኑ ከድርጊት ጋር የተሳሰረና በበርካታ ጉዳዮች የተደራጀ ነው:: እነዚህ ጉዳዮች የክዋኔውን ቦታና ጊዜ፣ የክዋኔውን ምክንያት፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና፣ የከዋኙን ጥበባዊ አቀራረብ፣ የሚመለከቱ ናቸው:: እንደ Ben Amos (1982፣ 11) አገላለፅ «የስነቃል ተግባቦቶች (የጊዜና የቦታ፣የክዋኔ ምክንያት፣የተሳታፊዎች ማንነትና ሚና፣ የክዋኔው ጥበባዊ አቀራረብ) ከሌሎች ተግባቦቶች የሚለዩት በአውዳዊ ስምምነቶች ነው:: እነዚህም ጊዜ፣ ቦታና፣ ማጀቢያዎች ናቸው» ይላሉ:: እያንዳንዱ የክዋኔ አላማ ወይም ጉዳይ የየራሱ ወቅትና ጊዜ አለው፤ የትኛው የስነቃል አይነት መቼ? የት? በማን? ለማን? እና እንዴት? እንደሚከወን ባህላዊና አውዳዊ ስምምነቶቹ ወሳኞች ናቸው:: በመሆኑም ክዋኔ አንድ ሰው ወይም ቡድን በአንድ በተወሰነ ቦታና ጊዜ አንደበታዊ እና አንደበታዊ ባልሆነ መንገድ፣ ከሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ጋር የሚያከናውነው ጥበባዊ ተግባር ነው::

ከክዋኔ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ባህላዊ ክዋኔዎች እርስ በርሳቸው የተያያዙ ሶስት አጠቃላይ ተግባራት እንዳሏቸው እነ Turner በ Schoemaker (1990፣ 86) ውስጥ ያስረዳሉ:: እነዚህ ተግባራት ስነማህበረሰባዊ፣ ስነልቦናዊ እና ባህላዊ ተግባራት ናቸው:: ከስነማህበረሰባዊ ተግባር አንፃር እነማን ሊሳተፉ ይችላሉ? ተሳታፊዎቹ ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት እንዴት ይንፀባረቃል? የሚሉትን የሚመለከት ሲሆን፣ ከስነልቦና ተግባር አኳያ ደግሞ በክዋኔው ሂደት የሚሳተፉት ግለሰቦች ያሉባቸውን ስነልቦናዊ ጫናዎችና ሰዋዊ ስሜቶች የመተንፈሻ መንገድ ሆኖ ማገልገል፤ ወይም አለማገልገሉን የሚመለከት ነው:: ከባህላዊ ተግባር አንፃር በባህላዊ

አውዱ ውስጥ የትኞቹ ባህላዊ ልማዶች ይከወናሉ? ሚናውስ ምንድን ነው? የሚሉትን ጉዳዮች የሚያሳይ ነው:: እነዚህ ተግባራት ምንም እንኳ በከበራ (ritual) ክዋኔ ጊዜ የሚንፀባረቁ ናቸው ተብሎ ቢታሰብም በሌሎች የስነቃል አይነቶች የክዋኔ ሂደትም ሊንፀባረቁ የሚችሉ ናቸው::

3.4 አውድ

ክዋኔ ከድርጊት ጋር የተያያዘ ሲሆን አውድ ደግሞ ድርጊቱ የሚከናወንበት ጊዜና ቦታ ወይም መቼት ነው:: ክዋኔ ያለመቼት፣ መቼትም ያለክዋኔ፣ በስነቃል ጥናት የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ናቸው:: ቆየት ያሉ የስነቃል ምርምሮች በስነቃሉ ቴክስት ላይ ብቻ የተመሰረቱ እንደነበር ይታወሳል:: እንዲህ አይነቱ የምርምር ተግባር በዚያን ዘመን ተገቢነት ቢኖረውም አውዳዊ መረጃ ከሌለው ጥናቱ የተሟላ ሊሆን አይችልም በማለት የሚከራከሩ አሉ:: ለምሳሌ Bascom (1954፣ 335) «ቴክስት በጣም አስፈላጊ ቢሆንም፣ ያለ አውድ ህይወት አልባ ሆኖ ይቀራል» ይላሉ::

አውድ የስነቃል አይነቱ በሚከወንበት ጊዜ ለክዋኔው ተስማሚ የሆኑ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ተሟልተው መኖራቸውን የሚጠቁም ነው:: አውድ ለስነቃሉ መነገር ወይም መከወን ምክንያት የሆነው ክስተት ወይም አጋጣሚ፣ መቼ? የት? ማን? ለምን? ወዘተ. እንደፈጠረው ወይም እንደከወነው የሚያመለክቱ መረጃዎችን አካትቶ በማሳየት፣ ትርጉሙን በተብራራ መንገድ ለመረዳት ወሳኝና አጋዥ ይሆናል። «... አውድ ቴክስቱንና ክዋኔውን አቅፈው የያዙትን ሁሉንም ነገሮች ይመለከታል:: ... የቡድኑ አባላት ስነቃሉን የሚጋሩበት አካላዊ መቼት እና ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም በከዋኙና በተደራሲያኑ መካከል የሚኖረው ግንኙነት ባንድ ላይ የክዋኔ አውድ ይመሰርታል» (Sims and Stephens 2005፣ 137) ይላሉ:: በመሆኑም አውዳዊ የቃልግጥም ጥናት መሰረት ማድረግ ያለበት በተከወነበት ወይም በተፈጠረበት አካባቢ በሚሰበሰበውና በሚገኘው አውዳዊ መረጃ ላይ ይሆናል ማለት ነው:: ቃልግጥሞች አብዛኛውን ጊዜ የየዘመኑን መንፈስና ገጠመኝ ተመርኩዘው የመፈጠር ባህሪ ስላላቸው፣ ይዘታቸውም ይህንኑ ባህሪ ማለትም የተፈጠሩበትን ምክንያት ከነሁኔታውና ከነድርጊቱ፣ ቦታውንም ጭምር የሚያመለክቱ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ::

3.5 ማህበራዊ ፋይዳዎች

ቃልግጥም አብዛኛውን ጊዜ በመዘፈን ወይም በመዜም የሚቀርብ በመሆኑ የግጥሙ ለዛና ውበት ከአቀንቃኙ / ከከዋኙ የድምፅ አወራረድ ውበት ጋር የተያያዘ ነው:: በቃልግጥም ፈጠራና ክዋኔ ሂደት የከዋኙ ክህሎት ብቻ ሳይሆን የታዳሚው ድርሻም ከፍተኛ ስለሆነ ታዳሚው እንደከዋኙ ለዜማው የሚበቃ የድምፅ አወራረድ፣ ውበት እና በአጠቃላይ የማቀንቀን ብቃት ባይኖረውም፣ በአካባቢው ካሉት ነባራዊና ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አዛምዶ ቃልግጥም ፈጥሮ ወይም አስታውሶ የማቀበል መብትና እድል ባህሉ ይፈቅድለታል ተብሎ ይታመናል::

እንዲህ አይነት ሁኔታና ድባብ የሚፈጠረው ደግሞ በሰርግ ላይ በሚከወኑ ዘፈኖች፣ ቀረርቶዎች፣ በመጠጥ ቤት በሚደረጉ መዝናኛዎች (ጨዋታዎች)፣ በስራ ቦታና፣ ከስራ መልስ በሚደረጉ ክዋኔዎች፣ ወዘተ. ላይ ነው:: በዚህ ሂደትና እንቅስቃሴ የቃልግጥሞቹ ይዘት፣ ብዙ ጊዜ መገሳና ውደሳ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ድርጊቶች እና አስተሳሰቦች የሚተቹበት አጋጣሚ የሚፈጠርበት ይሆናል:: የመገሳና የውዳሴ ግጥሞች በተለይ በማህበረሰቡ ዘንድ፣ ማህበራዊ እውቅና ላላቸውና፣ መልካም እና ደግ የሚባሉ እሴቶችን ለተላበሱ አባላት ማወደሻ እና ማሞገሻ ሲሆኑ፣ በአንፃሩ አንዳንድ የማህበረሰቡ አባላት እነዚህን ተግባራትና እሴቶች አውቀው እንደነሱ እንዲሆኑ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ እና እድል የሚፈጠርበት አጋጣሚ ይሆናል::

ቃልግጥም የሚከወንባቸው ሁኔታዎች እንደየባህሉና እንደየአካባቢው የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ:: ማህበረሰቡ በረጅም ጊዜ ልምዱ፣ የባህሉ አንድ ገፅታ አድርጎ የሚያፀድቃቸው ማህበረ-ባህላዊ ስምምነቶች ይኖሩታል:: እነዚህ ስምምነቶች በሚፈቅዱት መሰረት የቃልግጥም አይነቱ ሊቀርብ ይችላል:: "... ቃልግጥም ለሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ወይም ለህዝቡ ሁልጊዜ እኩል ሊቀርብ አይችልም:: የትኛው የግጥም አይነት በማንና? ለማን? እንደሚቀርብ ባህላዊ ስምምነቶች ይወስናሉ:: ... ለጎሳ መሪዎችና ለአለቆች፣ እንዲሁም ታላቅ ጀብድ ወይም ገድልና ጀግንነት ለፈፀሙ ሰዎች የሚቀርቡ ቃልግጥሞች፣ ከእነሱ ተግባራት ጋር የተያያዙና ይህንኑ የሚገልፁና የሚያስተውሱ ይሆናሉ::... ለአንድ ባህላዊ አውድ የሚቀርብ ቃልግጥም ለሌለው የሚውልበት እድል ጠባብ ነው፣ ወይም ጨርሶ የማይፈቀድበት ሁኔታ ይኖራል (Finnegan in Bauman፣ 1992፣ 125) ይላሉ:: ከዚህ አንጻር፣ በቀረርቶ፣ በዘፈን፣ በጭፈራ፣ ወዘተ. የሚቀርቡት ቃልግጥሞች የተለያዩ ይሆናሉ ማለት ነው::

ቃልግጥሞች በሚከወኑባቸው አውዶችና በሚታደሙ ተደራሲያን ወይም ተሳታፊዎች አንፃር የተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች (አላማዎች) ይኖሯቸዋል:: አብዛኛውን ጊዜ ፋይዳዎቹ ከታዳሚ ተሳታፊ አንፃር የሚታዩ ቢሆኑም፣ ለከዋኙም የሚሰጡት ጥቅም ይኖራል :: በተለይ በሂስና በትችት ላይ የሚያነጣጥሩ ቃልግጥሞች የከዋኙን የውስጥ ስሜት የማስተንፈሻ መንገዶችና አጋጣሚዎች ይሆናሉ:: በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ልዩ ልዩ ችግሮች ማለትም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እንዲሁም፣ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ክስተቶችንም ጭምር በቃል ግጥም አማካይነት ይንጸባረቃሉ::

ቃልግጥም በሚከወንበት ሁኔታ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚታዩ ልዩ ልዩ ማህበራዊና ባህላዊ መስተጋብሮች ውስጥ የሚከናወኑትን ማህበራዊና ባህላዊ ተግባራትን ለማሳየት ጥቅም ላይ ይውላል:: በመሆኑም ቃልግጥም በማሞገስ ፋይዳው ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችን በማህበረሰቡ ውስጥ ከማስረጽ በተጨማሪ፣ የተለየ እውቅና ያላቸውን ግለሰቦችን፣ ጀግኖችን፣ ወዘተ. ለማወደስና ለማሞገስ ሊያገለግል ይችላል:: በሰርግ ቦታዎች፣ በመጠጥ /በመዝናኛ/ ቦታዎች፣ በስራ አካባቢዎች፣ የሙገሳና የውዳሴ ግጥሞች ይቀርባሉ:: በሰርግ ላይ የሚከወኑ ቃልግጥሞች በአጠቃላይ ከሰርግ ድባብ ጋር የሚዛመዱ ሆነው የሰርጉን ዝግጅትና አጠቃላይ ታዳሚውን ጭምር የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ:: በስራ ቦታ የሚከወኑት ደግሞ፣ ከስራው አይነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት የሚመለከቱ ሆነው ሰራተኛውን ለማበረታታት የሚያግዙ ይሆናሉ:: በአጠቃላይ የሙገሳና የውዳሴ ቃል ግጥሞች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው እሴቶች ላይ ተመስርተው የሚከወኑ ናቸው (Finnegan ፣ 1970፣ 120) ይላሉ::

ቃልግጥሞች በህይወት ኡደት ውስጥ የሚታዩትን ልዩ ልዩ የሽሽግር ስርአቶችን በተለይ በልደት፣ በሰርግ እና በሞት ጊዜ ያለውን ስነስርአት ለማክበርና ለመመዝገብ፣ እንዲሁም ከአንድ የድል ተግባር በኋላ /ከጦርነት፣ ከአደን፣ ወዘተ./ በሚዘጋጁ ሁነቶች የግለሰቦችንና የጎሳ አለቆችን ወይም የጀግኖችን ተግባር ወይም ገድልና ድል በማውሳት፣ በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ተሞክሮና የጀግኖችን ታሪካዊ ገጠመኝ ለመመዝገብ ይረዳሉ Finnegan (1970፣ 141) እና Okpewho (1992፣ 118-122) ይናገራሉ:: እንዲሁም፣ በአንዳንድ ባህሎች በሚች የቀብር ስርአት ላይ ሚችን በሙሾ መልክ ማወደስ የተለመደ ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ የሙገሳ ቃልግጥሞች የቀብር ስነስርአት በሌለበት ሁኔታ ሚችን አስታውሶ የመነገርና /የመከወን/ የማወደስ አጋጣሚ ሊኖራቸው ይችላል::

ቃልግጥሞች ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማንፀባረቅ ይጠቅማሉ:: በማህበረሰቡ ዘንድ በሚታዩ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፖለቲካዊ ይዘትና መልክት ያላቸው ቃልግጥሞች ይገጠማሉ፣ ይዘፈናሉ:: ትኩረታቸውም ትችት ለማቅረብ፣ ጫና ለመፍጠርና፣ ለቅስቀሳ ሆኖ፣ የህዝብን አመለካከት ማንፀባረቅ ይሆናል:: ስድብ አዘልና ምፀታዊ ቃልግጥሞች ለፖለቲካ ተግባር በሚውሉበት ጊዜ እንደ ጦር መሳሪያ ሊያገለግሉ ይችላሉ:: በአንፃሩም፣ ለፖለቲካዊ ግፊት መፍጠሪያ፣ ወዘተ. ይሆናሉ (Finnegan፣ 1970፣ 272-284) ይላሉ:: ፖለቲካዊ ይዘት እና መልዕክት ያላቸው ቃልግጥሞች በአንድ ቡድን አባላት መካከል በሚከወኑበት ጊዜ የቡድኑን የጋራ ስሜትና አንድነት ከማጠናከር አልፎ ተቀናቃኞችን ለመቃወም ይረዳሉ:: ቡድናዊ ስሜትን እና አንድነት በማጠናከር ቡድናዊ ወገናዊነትን ለማንፀባረቅ ቃልግጥሞች ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ (Finnegan፣ 1977፣ 217-221)::

ሰዎች በለት ተዕለት የተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ ለዕለት ኑሮአቸውም ሆነ ለዘላቂ ህይወታቸው የሚያከናውኗቸው ስራዎች ይኖራሉ:: አንዳንዶቹ ተግባራት አካላዊ ብርታትንና ጥረትን የሚጠይቁ ይሆናሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ አካልን እና አእምሮን አቀናጅቶ መስራትን የሚፈልጉ ይሆናሉ:: በእንዲህ አይነት አድካሚ የጉልበትና የአእምሮ ስራዎች ውስጥ ቃልግጥሞች ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው:: በሚዘፈኑበት ጊዜ፣ የስራውን ድባብ በመለወጥ ደስታንና ብርታትን እንዲሁም የማዝናናት ስሜት በመፍጠር ስራውን በቀላሉ ለማከናወን ይረዳሉ (Okpewho፣ 1992፣ 106-108)::

ቃልግጥሞች በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን፣ በአስተዳደራዊ ችግሮች ምክንያት የሚታዩ በደሎችን፣ ጭቆናዎችን፣ ለማንፀባረቅ፣ የስርአቱ አካላት የሆኑ ግለሰቦችና አስተዳዳሪዎች አስፈሪ በሚሆኑበት ጊዜ ስሜትን እና ፍላጎትን እንዲሁም ብሶትን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለፅ ያገለግላሉ:: በተለይ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በሚፈጠሩ አሉታዊ ችግሮች ሳቢያ ስሜትን በአደባባይ አውጥቶ መናገር በማይቻልበት ሁኔታ ቃልግጥሞች እንደመተንፈሻ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ (Finnegan፣ 1977፣ 223-227) በማለት ይገልጻሉ::

ስነቃል በአጠቃላይ፣ ቃልግጥሞች በተለይ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውንና ለወቅቱ ተስማሚና በጣም ጥሩ የሚባሉትን ባህሪያት እና አሰተሳሰቦች የማህበረሰቡ አባላት እንዲማሩባቸው የማድረግ ፋይዳ ወይም አላማ አላቸው:: ዘመናዊ ትምህርት ባልተስፋፋበት ሁኔታ፣ ማህበረሰቡ ስለራሱ ማንነት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ እሴቶች፣ ወዘተ. ለተከታዩ

ትውልድ ማስተላለፍ የሚችለው በስነቃሉ አማካይነት ነው:: የማህበረሰቡ አባላት፣ ስለራሳቸው ማንነት፣ ስለአመጣጣቸው እና ስለግንኙነታቸው፣ እንዲሁም ከሌለው ተለይተው እንዲታወቁ ያደረጋቸው የአኗኗር ባህሪ፣ ወዘተ. በዘፈኖች፣ በተረቶች፣ በምሳሌዎች አማካይነት መረጃውን እንዲያገኙ ይደረጋል:: ስነቃሎች ወይም ቃልግጥሞች አሁን ያሉት የማህበረሰብ አባላት ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ፣ ማህበረሰቡም እንደ ማህበረሰብ ይቀጥል ዘንድ ጠቃሚ ተግባራት የትኞቹ እንደሆኑ ያሳያሉ:: መደበኛ ባልሆነ መንገድ ማህበረሰቡ በሚሰጣቸው ትምህርቶች ወይም በሚያስተላልፋቸው መልዕክቶች፣ አስተሳሰቦች፣ አባላቱን ያንጸባቸዋል፡፡ ከማህበረሰቡ አመለካከትና እምነት ውጭ፣ ለመውጣት የሚሞክሩትን አባላትንም ያስተምርበታል፣ ይገስጽበታል፣ ያገልበታል (Okpewho፣ 1992፣ 115-118) ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ የቃልግጥም ፋይዳ ወይም ተግባር በሚመለከት (Finnegan in Bauman፣ 1992፣ 126) ጠቅለል ባለመንገድ እንዲህ ይዘረዝሩታል::

> *... የቃልግጥም ተግባር በሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን፣ እነሱም አመፅን መግለፅ ፣ በስልጣን ላይ ጫና ማድረግ ወይም ለውጥን ማበረታታት ናቸው:: ... ብዙ ጊዜ የተለመዱ የፖለቲካና የተቃውሞ ዘፈኖች ቢሆኑም ... ቃልግጥሞች በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች መካከል በሚታዩ ሀይማኖታዊ፣ ክብረበአላዊ፣ ጥበባዊ እና ተዝናኖታዊ፣ ሁኔታዎች ውስጥ የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ:: ... ስለሆነም፣ የቃልግጥም አላማዎች ብዙ ሲሆኑ፣ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ ጥላቻን ወይም ፍቅርን ለመግለፅ፣ ችግሮችን ለማጋጋል ወይም ለማብረድ፣ለማስደሰት ፣ ለማሳፈር፣ ለማዋረድና ለማቃለል፣ ... ለህዝባዊ ሁነቶች ክብርና ሞገስ ለመስጠት፣ ወይም ምናብን በተዋበ ቃላት ሸፍኖ ለማቅረብ፣ ያገለግላል::*

ስለ ቃልግጥም ተግባር ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች በሚያጠነክር ሁኔታ ደሳለኝን ጠቅሰው፤ Getie (2000፣ 3) እና (2001፣ 1) ቃልግጥሞች የሚከተሉት አምስት ተግባራት አሏቸው ብልው ይዘረዝራሉ፡፡

1ኛ. የማህበረሰቡን ህዝባዊና ማህበራዊ ንቃተ-ህሊና ማሳየት ይችላሉ፤
2ኛ. የማህበረሰቡን የሞራልና የእሴት ስርአቶችንና ህጎችን ያመለክታሉ፤
3ኛ. የግለሰቦችን ወይም የቡድኖችን ማህበራዊ ግንኙነቶች ይወሰናሉ፤

4ኛ. በተለይ ጽህፈት ባልዳበረባቸው ወይም በሌላቸው ሀገሮች ውስጥ የመቃወሚያ መንገዶች ሆነው ያገለግላሉ፤

5ኛ. ቢያንስ ቢያንስ ታሪካዊ ክስተቶችን በመመዝገብና በማሳየት ለታሪክ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ።

3.6 የንድፈ-ሀሳባዊ ማዕቀፎች ቅኝት

የፎክሎር ባለሙያዎች፣ ሙያው የራሱ የሆኑ የንድፈ ሀሳብ መነሻዎች የሌሉት ቢሆንም ከሌሎች ሙያዎች በፈለቁ ንድፈ ሀሳቦች አማካይነት መስኩ ጥናት ሲደረግበት እንደቆየ ያመለክታሉ:: ለምሳሌ Alun Dundes (2005፣ 387-388) ስለፎክሎር ሙያ መዳከም እንደ አንድ ዋና ችግር የሚያነሱት ‹‹ቀጣይነት ያለውና የተሟላ አውራ ንድፈ ሀሳብ አለመኖርን ነው::›› አያይዘውም ‹‹በፎክሎር ጥናት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉት ንድፈ ሀሳቦች የመጡት ከሌላ ሙያ ነው›› ይላሉ:: እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች ከሌሎች ሙያዎች የተወሰዱ ቢሆንም፣ ከፎክሎር ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ ናቸው ብለው ይመክራሉ::

ከቃልግጥም ጋር በተያየዘ ጥናት የተደረገበት ንድፈ ሀሳብ፣ መዋቅራዊ የፎክሎር ንድፈ-ሀሳብ ነው:: ጀማሪዎቹም Milman Parry እና Albert Lord እንደሆኑና፣ ጥናታቸውም በዩጎዝላቪያ ቃላዊ ኤፒክ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ትኩረቱም በቃልግጥሙ ቀመራዊ ሁኔታ ላይ ስለነበር ቀመራዊ ንድፈ ሀሳብ እስከመባል የደረሰ ነው:: የሆሜርን ኤፒክ አሁን ካለው የአውሮፓውያን የጀግና ግጥም ጋር አነፃፅሮ በማሳየት የተደረሰበት መደምደሚያም በእያንዳንዱ መስመር ውስጥ ቀመር፣ መሸጋገሪያ እና ጭብጡም የግጥሙን መዋቅር /ቅርፅና ይዘት/ የሚያመለክት እንደሆነ (Dorson፣ 1963፣ 108-111) ይገልፃሉ::

Dorson (1972፣ 7-12) ወደ አስራ ሁለት የሚሆኑ ንድፈ ሀሳቦች እንዳሉ ዘርዝረው፣ አንዳዶቹን ከንድፈ ሀሳብ ይልቅ ዘዴዎች (methods) ናቸው ይሏቸዋል:: ለምሳሌ የፊላንዱ ታሪካዊ መልካምድራዊ (Historical geographical) እና ታሪካዊ እንደገና ማዋቀር (Historical reconstraction) ዘዴዎች ሊጠቀሱ ከሚችሉት መካከል ናቸው::

በዚህ ውስጥ ከተጠቀሱት ንድፈ ሀሳቦች መካከል አንዱ “ርዕዮተ አለማዊ” የሚባለው ሲሆን ይህ ንድፈ ሀሳብ በአንዳንድ ሀገሮች /ለምሳሌ በጀርመን፣ በኖርዌ፣ በፊላንድ፣ ወዘተ./ ተመራማሪዎች ዘንድ ትኩረት ያገኘና ወደኋላ ላይ ለጀርመንና ለሩሲያ ፖለቲካዊ ርዕዮተ

አለም ማራመጃ በመሆኑ ምክንያት አሉታዊ ስያሜ በመስጠት ሰይጣናዊ ንድፈ ሀሳብ አስከመባል የደረሰ ነው (Dorson፣1963፣97) :: በዚህም የናዚ ጀርመንና የሩሲያን ፎክሎር ለርዕዮተ አለም ማራመጃ ሲሉ ስነቃልን ተጠቀመውበታል:: ጀርመኖች የዘር የበላይነትን ከደምና ባህል ጋር ሲያዛምዱት፣ ሩሲያ ደግሞ ዘፈኖችንና አፈታሪኮችን ከሰራተኛው ክፍል ጋር በማዛመድ ለማህበራዊና ለአብዮታዊ የተቃውሞ መንፈስ መቀስቀሻ አድርገውታል (Dorson፣ 1963፣ 97-98፤ 1972፣ 17-18):: በዚሁ መንፈስ በመነሳሳት የሶቪየት ተመራማሪዎች ስለራሳቸው ፎክሎር ብያኔ የሚከተለውን አስተያየት እንደሰጡ ሲገልጹ፣ «ፎክሎር ያለፈውን የሚያስተጋባ ብቻ ሳይሆን አሁን ያለውንም ለማሳየት የሚችል ሀያል ድምፅ ስለሆነ ለመደብ ትግል እንደ አንድ መሳሪያ ሆኖ መቀጠል አለበት ... ፎክሎር ህዝቡ በመሬት ባለቤቶችና በገዥዎች ላይ ያደረገውን እውነተኛ ትግል ያንፀባርቃል፣ ቃልግጥም ደግሞ ከራሱ ሀይለኛ ባህሪ በመነጨ የስራ ተግባራትን መሰረት ያደርጋል» ይላሉ::

ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ እንደምንረዳው በተለይ ቃልግጥም፣ በአጠቃላይ ደግሞ ስነቃል፣ በአንዳንድ ሀገሮች እንደመቀስቀሻ መሳሪያ በመሆን ለፕሮፖጋንዳ ተግባር የሚውል መሆኑን ነው:: እንዲህ አይነቱ ተግባር በጥንቃቄ ካልተያዘ በስተቀር በሀገሮች ወይም በህዝቦች መካከል ሊኖር የሚገባውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መቀራረብ የተዛባ እንዲሆን ያደርጋል:: የስነቃል ተግባርና ምርምር፣ ህዝቡ ያለፈበትን ህይወት ወይም እየኖረ ያለውን ተጨባጭ ህይወት በመመርመርና በማሳየት፣ ከህዝቡ ፍላጎትና እምነት በመነጨ ሁኔታ፣ የሚፈልገውንና የማይፈልገውን ለይቶ በማወቅ፣ ወደተሻለ ማህበረ - ባህላዊ ህይወትና እድገት እንዲሸጋገር ለማድረግ በሚደረግ ጥረት ውስጥ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት እንጅ በማህበረሰብ መካከል ዘላቂ ችግር የሚፈጥር መሆን የለበትም::

ሁለተኛው ንድፈ ሀሳብ የተግባራዊያን ንድፈ ሀሳብ የሚባለው ሲሆን የዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች Bronislaw Malinowski እና A.R. Radcliffe- Brown ሲሆኑ በሙያቸው ስነስበኞች ናቸው:: (Sims and Stephens፣ 2005፣ 175) እንደሚሉት ‹‹የነዚህ ተመራማሪዎች መነሻ፣ ባህልንና ማህበረሰብን በምልአት የሚመለከት በመሆኑ የፎክሎር ባለሙያዎችን እያጓጓ የመጣ ንድፈ ሀሳብ ነው:: በህዝቡ እና በገላጭ ባህሉ መካከል ያለውን ተፈጥሮአዊ ግንኙነት ለማየት ጠቃሚ ንድፈ-ሀሳብ እንደሆነ›› ይገለጻሉ::

የተግባራዊያን ንድፈ ሀሳብ ትኩረቱ፣ ማህበራዊ ተቋሞች፣ በግለሰቦች ላይ ስለጣሏቸው እገዳዎች፣ የግለሰቡ ፍላጎት እና እርካታ በባህላዊና በማህበራዊ ማእቀፎች ውስጥ ባለው

ግንኙነት የሚወሰን መሆኑን፣ ግለሰቦች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከማህበረ ባህላዊ ስምምነቶች አኳያ፣ የሚፈልጓቸውን ሰዋዊ ፍላጎቶች በማእቀፉ ውስጥ ሆኖ ማሟላት የሚችሉ መሆኑን (Barnard፣ 2004፣ 61) የሚገልጹ ናቸው::

ይህንን ንድፈ ሀሳብ መሰረት አድርገው ከፎክሎር ጥናት ጋር ለማያያዝ ከሞከሩት ተመራማሪዎች መካከል William R. Bascom አንዱ ሲሆኑ፣ እሳቸውም ያቀረቡት ገለፃና ትንተና የንድፈ-ሀሳቡን ጠቀሜታ አጉልቶ የሚያሳይ ነው:: በዚህም ስነቃል የማስተማር ፣የማስመለጥ፣ የማረጋገጥ፣ እና የመቆጣጠር ተግባራት አሉት (1954፣ 343-346) በማለት ዘርዝረውታል:: ነገር ግን እነዚህ ተግባራት እንደ አንድ ዋና ተግባር በመቁጠር “ፎክሎር ባህልን አፅንቶ፣ አረጋግቶና አጠናክሮ ለማስጠበቅና ለማስከበር እንደ ዋና መሳሪያ ነው” (Sims and Stephens 2005፣ 176) በማለት ያጠቃልሏቸዋል:: ለዚህም እንደምክንያት የተነሳው አቀራረቡ በጣም ሰፊ በመሆኑ በተለያዩ አውዶችና ክዋኔዎች ላይ ተግባራዊ ትንተና ለማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ ነው::

Bascom (1954፣ 334-336) እንደሚሉትም የሰውልጅ በተፈጥሯዊ ድክመቱ፣ በማህበረሰባዊ ጫናዎቹና፣ ባካባቢው ባለው መልክአምድራዊ ሁኔታ፣ከሚፈጠርበት ፍርሀትና ጭንቀት ለማምለጥ ሲል የሚፈጥራቸው ስነቃሎች ለጊዜውም ቢሆን ከዚህ ፍርሀትና ጭንቀት ነፃ እንዲሆን ያደርጉታል:: አንዳንድ ተግባራት እንደ ነውር (ፀያፍ) ማህበረሰቡ ቆጥሮ የሚጥላቸው ገደቦች፣ በግለሰቦች ላይ ጫና ስለሚያሳድሩ፣ ጫናውን ለመርሳት ሲባል ግለሰቡ የሚፈጥራቸው ስነቃላዊ ቅርፆች ለጊዜውም ቢሆን ጊዜያዊ እረፍት ይሰጡታል ተብሎ ይታሰባል:: እንዲሁም ግለሰቦች በሚፈጥሯቸው ቃላዊ ፈጠራዎች፣ ውስጣዊ ፍላጎቶቻቸውን በስውር በመግለፅ ከእገዳዎች የማምለጫና ከማህበረሰቡ ጫና የመተንፈሻ መንገድ ያበጃሉ ማለት ነው::

በትምህርታዊ ተግባሩ ሲታይ መነሻው ያልተማሩ የማህበረሰቡ ክፍሎች ስነቃልን እንደማስተማሪያ ዘዴዎች በመጠቀም “ልጆችና ወጣቶችን መልካም የሚባሉትን ባህሪያት አስርፀው መጥፎ የሚባሉትን ባህሪያት እንዲያስወግዱ ለማድረግ ይጠቅማል” (ፈቃድ፣1991፣20) የሚል ነው:: ከዚህ አንፃር በማህበራዊ እሴቶቻችንና በግለሰባዊ ማንነታችን መካከል ያለው ግንኙነት በመልካም መሰረት ላይ የተገነባ እንዲሆን የስነቃል ፈጠራዎቻችን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው:: በመልካም ገፅታቸው የሚታዩት እንደ መተሳሰብ፣ መፈቃቀር፣ መከባበር፣ መቻቻል፣ ወዘተ. ያሉት የጋራ እሴቶችና መልካም ባህሪያት ቀጣይነት

እንዲኖራቸው፤ የእነዚህ ተቃራኒ የሆኑት ደግሞ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ስነቃል ትልቅ ሚና ይጫወታል ማለት ነው:: ስለፈሪዎች፣ ስለንፉጎች፣ ስለተንኮለኞች፣ ወዘተ. የሚገጠሙት ግጥሞችና የሚዘፈኑት ዘፈኖች፣ የሚነገሩት ተረቶችና ቀልዶች፣ በአጠቃላይ የሚፈጠሩት ቃላዊ ፈጠራዎች ትምህርታዊ ይዘት ስላላቸው የማህበረሰቡን አመለካከትና ፍላጎቶች ለማወቅ ይረዳሉ ተብሎም ይታመናል::

ከተግባራዊ ንድፈ-ሀሳብ ጋር የሚመሳሰለው ሌላው ንድፈ ሀሳብ ስነልቦናዊ ተግባራዊ የሚባለው አንዱ እንደሆነ እና ይህም፣ ለስነልቦናዊ ፍላጎት ምላሽ የሚሆኑት ገላጭ ባህሪያት በስነቃሉ ውስጥ ይገለጻሉ:: እነዚህ ባህሪያት ግለሰቡን ወይም ቡድኑን ከተጫነባቸው ጫናዎች እንዲወጡ ከማድረግ አልፈው፣ እነዚህን ጫናዎች የሚተነፍሱባቸው ምቹ መሳሪያዎች ተደርገው ይወሰዳሉ:: በሌላም በኩል አንድ ቡድን፣ በራሱ በቡድኑ መካከል በሚያደርገው ተሳትፎ ውህደት ለመፍጠር የሚችልበት አጋጣሚ እንዲያገኝ በማድረግ በጋራ ተሳትፎ፣ በሂደት ከጭንቀቱና ከጫናው ለመላቀቅ ወይም እሴቶቹን ለማስተዋወቅ የሚያስችለውን ቡድናዊ ስሜትና ማንነት ለማጠናከር ይረዳል በማለት (Burns፣ 1977፣ 122-125) ያስረዳሉ:: በአጠቃላይ እንደ ተግባራዊያን ንድፈ ሀሳብ እይታ፣ ገላጭ ባህሪያት ለግለሰቡም እና ለማህበራዊ ፍላጎቶች በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት ተፈላጊና ጠቃሚዎች ናቸው::

ከላይ ከተጠቀሱ ንድፈ ሀሳቦች በተለየ ሁኔታና መንገድ ገላጭ መረጃዎች ታሪክ በመፃፍ ሂደት ውስጥ ጥቅም እንዳላቸው የሚያመለክተው ንድፈ ሀሳብ ታሪካዊ ጠቀሜታ የሚባለው ነው:: በዚህ ንድፈ-ሀሳብ እይታ፣ ገላጭ መረጃዎች በሁለት መንገድ ዋጋ ያላቸው ናቸው:: በአንድ በኩል ታሪካዊ መረጃ ይይዛሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ መረጃዎች ከተገኙበት ቡድን አንፃር ቢመረመሩ የቡድኑን ፍርሀቶች፣ ፍላጎቶች /ምኞቶች/ እሴቶች፣ አመለካከቶች፣ ወዘተ. የሚያንፀባርቁ ማህበራዊ ሰነዶች ተደርገው ይወሰዳሉ (Burns፣ 1977 ፣121-122) ይላሉ:: በኛ ሀገር ሁኔታ ሲታይ ይህ ንድፈ ሀሳብ በብዙዎቹ ብሄረሰቦቻችን ውስጥ ያለውን እውነታ የሚያመለክት ነው :: አብዛኞቹ ቃላዊ ግጥሞች፣ ተረትና ምሳሌዎች፣ አፈታሪኮች፣ የተፈጠሩበትን ወይም የተነገሩበትን ዘመንና ሁኔታ የመጠቆምና የማሳየት ሀይል አላቸው:: በመሆኑም ገላጭ መረጃዎችን ከሌሎች የመረጃ ምንጮች ጋር በማጣመር እንደ ዋና ታሪካዊ መረጃ ወስዶ የተፃፈ ታሪክና መረጃ የሌላቸውን ቡድኖች ታሪክ ለመፃፍ ይጠቅማል በማለት Burns ያብራራሉ::

ለማጠቃለል ያህል ከመጨረሻው ንድፈ-ሀሳብ ጋር በእጅጉ የሚዛመድ ማብራሪያ Jan Vansina (1985፣ xi-xii) እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፣

> *የቃል ባህል አስደናቂው ጉዳይ ካለፈው የቀረው እውነተኛ መልዕክት ነው:: ይህም ገና በተከታታይ የሚገኝ አይደለም :: ... አእምሮ በትውስታ አማካይነት ባህልን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፋል::... ቃላዊ ባህል ለርዕዮተአለም፣ ለህብረተሰብ፣ ለባህል፣ ለስነልቦና፣ ለጥበብ እና ለማህበረሰብ በመጨረሻም፣ ለታሪክ ተማሪዎች ማዕከላዊ ቦታ መያዝ ያለበት ነው:: ከልዩ ልዩ አይነት ታሪካዊ ምንጮች መካከል ባህል የተለየ ቦታ ይይዛል:: መልክቶች አሉት፣ ግን አልተፃፉም፣ በህዝቡ ተከታታይ ትውልዶች ትውስታ ውስጥ እውነታን ጠብቆ ለማቆየት ይችላሉ::*

ስለሆነም ይህ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት ንድፈ ሃሳቦች በሃሳብ ማጠናከሪያነትና በደጋፊነት ሊጠቀምባቸው የሚችሉት የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፎች፣ የተግባራዊያን፣ የስነልቦና-ተግባራዊያን እና የታሪካዊ ጠቀሜታ ይሆናሉ ::

ምዕራፍ አራት፡- የጥናት አካባቢዎች፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና መቸቶች፤ የምርምር አይነትና የትንተና ዘዴዎች

4.1 የጥናት አካባቢዎች ናሙና አመራረጥ

ከ1983 ዓ.ም በፊት የሰሜን ወሎ ዞን ተብለው የተዋቀሩት አውራጃዎች አምስት ሲሆኑ እነሱም፣ ዋግ፣ ላስታ-ላሊበላ፣ ዋድላ ደላንታ፣ ራያና ቆቦ፣ እንዲሁም፣ የጁ ነበሩ፡፡ በየአውራጃዎቹ ውስጥ ቢያንስ፣ ሁለት ሁለት ወረዳዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ ራያና ቆቦ አውራጃ አላማጣና ቆቦ ወረዳዎች፣ የጁ አውራጃ ደግሞ፣ ጉባላፍቶና ሀብሩ ወረዳዎች ነበሯቸው፡፡ ከ1983 ወዲህ በመጣው፣ የመንግስት ለውጥ ዞኑን እንደገና በማዋቀር፣ ዋግ አውራጃ፣ ራሱን ችሎ፣ እንደ አንድ ዞን በመሆን ሲዋቀር ሌሎቹ አውራጃዎች ግን በነበረው መጠሪያ በአስር የገጠር ወረዳዎችና በሶስት የከተማ አስተዳደር በማደራጀት፣ ዞኑ አስራ ሶስት ወረዳዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡ ስለዚህ፤ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ አካባቢዎችን አመራረጥ በተመለከተ የታቀደ ናሙና (deliberate sampling) ተግበር ላይ ውሏል፡፡ይህ የናሙና አይነት አላማ ተኮር (purposive) ወይም ወሳኝ ናሙና (non probability sampling) ስለሆነ ከአጠቃላዩ የተወሰኑትን በአላማና በታቀደ ሁኔታ የመምረጥ እድል የሚሰጥና ሁሉንም አካባቢ ሊወክል የሚችል ነው (Kothari፤2004፤15) ይላሉ፡፡ይህንን በሚመለከት ያለው (2006፤140) ላይ‹‹...ጥናቱ አይነታዊ ከሆነ ተመራማሪው መጠቀም ያለበት የንሞና ዘዴ ወሳኝ የንሞና ዘዴ ነው ››በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘው የሚከተለውን ማብራሪያ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡፡

> ... በተለያዩ ምክንያቶች ... ተመራማሪው ወሳኝ የንሞና ዘዴን ለመጠቀም ይገደዳል፡፡ በወሳኝ ንሞና ዘዴ ከጥናቱ አካላይ መመረጥ የሚኖርባቸውን የናሙና አባላት የሚወስኑት ተመራማሪው፤ የምርምሩና የጥናቱ አካላይ ባህሪ ይሆናል፡፡ይህም ማለት እነማን ወይም የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ናሙና ሆነው መመረጥ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚ ወስነው እጣ ወይም አጋጣሚ ሳይሆን፤...ተመራማሪው መረጃውን ከተወሰኑ ሰዎች...እንዲሰበስብ ሲገደድ፤እነዚህን ብመርጣቸው በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ ሲወስን... ነው፡፡...በአላማ ያለው ናሙና ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታ ፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ አላማ አንፃር ነው፡፡...ያለው (2006፤135-136)፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎች እንዲሆኑ የተመረጡት ሀብሩ፣ የጁና ቆቦ ወረዳዎች ናቸው። እነዚህ ወረዳዎች የጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎች እንደሆኑ ሲታሰብ፣ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ሶስቱም በምዕራብ በኩል ያሉትን የዞኑን ወረዳዎች ያዋስናሉ። ማህበረሰቡም በገበያና በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ይገናኛል። እነዚህ አካባቢዎች፣ በምስራቅ በኩል የሚያዋስኑት የብሄረሰብ ክልል፣ የአፋር ክልል ነው። ሶስቱም ወረዳዎች በብዛት በቆላማው የአየር ጠባይ ውስጥ ስለሚገኙ፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው እና የመሬት ይዞታው ከደጋማው ይለያል። በእነዚህ ወረዳዎች የሚኖረው ማህበረሰብ፣ እርሻን ከእርባታ ጋር አጣምሮ ስለሚያከናውን፣ በአኗኗሩ፣ ከደጋማው ማህበረሰብ የተለየ ነው ማለት ይቻላል። በሰፊው ማረስ፣ ብዙ ማምረት፣ ብዙ ማርባት፣ የሚታየው ከደጋማው ይልቅ በቆላማው ነው።ይህ በመሆኑ፣ የሰርጉ፣ የበአሉ፣ የእርስ በርስ ግንኙነቱ፣ ሰፋ ብሎ የሚገኘውም በነዚህ አካባቢዎች ነው። በቆላማውና በደጋማው ወረዳዎች፣ የባህል ተመሳሳይነትና ልዩነትም በጉልህ ይታያል። አለባበሱ፣ ዘፈኑ፣ ጭፈራው፣ በቆላማዎቹ ተመሳሳይ ነው። በመሆኑም፣ በነዚህ ወረዳዎች ውስጥ በሚኖሩ መረጃ አቀባዮች፣ በበአል ጭፈራዎች፣ በሰርግ አጋጣሚዎች አማካኝነት፣ አሁን የተሰበሰበው የቃልግጥም መረጃ ሊሰበሰብ ችሏል።

4.2. የመስክ ተግባራትና ገጠመኞች

ለዚህ ጥናት የመስክ ተግባር የተከናወነው በሁለት ዙር ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በአንደኛው ዙር ሁሉንም አካባቢዎች መድረስ ባለመቻሉና በቂ መረጃ ባለማግኘት ነው። በመሆኑም፣ ከ2006 ዓ.ም ከታህሳስ ወር ጀምሮ የመስክ መረጃ የመሰብሰብ ተግባርን ማካሄድ ጀምሬያለሁ።

ለጥናት ወደ ተመረጠው አካባቢ የተጓዝኩት በታህሳስ ወር መጨረሻ ሳምንት ነበር። ታህሳስ 27 ቀን 2006 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በመነሳት ከዞኑ ርዕሰ ከተማ ወልዲያ በዚያው እለት ገባሁ። በማግስቱ ወደ ዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሄድ፣ የመጣሁበትን አላማ በቃል ካስረዳሁ በኃላ፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የተሰጠኝን የትብብር ደብዳቤ በማሳየትና፣ ለዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ማመልከቻ በማቅረብ፣ በ28/4/2006 ዓ.ም " ለሁሉም ወረዳዎች ባሉበት" የሚል የትብብር ደብዳቤ ተሰጠኝ። ከዚያ በኃላ ከዞኑ ባህልና ማስታወቂያ መምሪያ ባለሙያዎች ጋር በመተዋወቅ ‹‹መነሻ ሊሆን የሚችል መረጃ ካለ›› በሚል አቶ አሰፋ አበጋዝን አነጋገርኩ። እሳቸውም ቀደም ሲል ከየወረዳዎቹ የተሰበሰቡና ለዞን ሪፖርት የተደረጉ አስር ያህል ሰነዶችን አውጥተው ሰጡኝ። እነዚህ ሰነዶች የያዟቸውን

የስነቃል መረጃዎች ስመለከት፤ ግጥሞቹ፣ የአጨዳ፣ የውቂያ፣ ወዘተ. ነበሩ። ከነዚህ መካከል ስንፍናን የሚተቹትንና ጉብዝናን የሚያበረታቱትን ቃልግጥሞች ለመነሻ እንዲሆኑ በማስታወሻ ወሰድኳቸው።

እነዚህን እንደ መነሻ በመውሰድ፣ መረጃ አቀባዮችን ማፈላለግ ጀመረኩ። ወልዲያና መርሳ የተገኙትን ግለሰቦች ያገናኘኝ፤ በየጁ ባህልና ታሪክ ላይ ጥናት በማድረግ ላይ የሚገኝ፣ አድኖ ተካየ በሚባል ወጣት አማካኝነት ሲሆን፤ የተከናወነው እስከ ጥር 7/5/2006 ዓ.ም ድረስ ባሉት ቀናት ውስጥ ነው። በነዚህ ቀናት ከተዋወቅኋቸው መረጃ አቀባዮች መካከል፣ አምሳ አለቃ መላኩ ተገኝ እና አቶ አዳነ ጥላሁን ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ግለሰቦች የተወሰኑ ቃልግጥሞችን በጽሁፍ፣ ማለትም እነሱ እየነገሩኝ፣ እኔ በወረቀትና በማስታወሻ በመፃፍ መረጃ መሰብሰብ ጀመርኩ።

ከጥር 10-12/2006 ዓ.ም ባሉት ሶስት ቀናት የጥምቀት በአል የሚከበርባቸው ቀናት በመሆናቸው የአካባቢው ሕዝብ በብዛት ወጥቶ በአሉን ያከብራል፣ ያደምቃል። በመሆኑም፣ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም፣ ወልዲያ፣ ቆቦና ሮቢት አካባቢዎች በበአሉ ጭፈራ ላይ እየተገኙ በካሴት የሚቀዱ ወጣቶችን በማዘጋጀት፣ በሶስቱም አካባቢዎች በአሉ በሚከበርባቸው ቀናት፣ ባህላዊው ጭፈራ የሚደምቅበትን ቦታና ሁኔታ እየለዩ፣ የሚደጋገመውንም እየተው፣ ጭፈራዎቹን በካሴት እንዲቀዱ በማስረዳት ወደየአካባቢዎቹ ተልከዋል።

በተለምዶ ጭፈራ የሚጨፈረው፣ ታቦታቱ ከቤተ-መቅደሳቸው ወጥተው ወደ ከተራው ቦታ እስኪደርሱና፣ ከከተራው ወደ ቤተ-መቅደሳቸው ተመልሰው እስኪገቡ ድረስ ባለው የጉዞ ሂደት ላይ ነው። በዚህ ሂደት ላይ ወጣት ወንዶችና ጎልማሶች በቡድን በቡድን እየሆኑ በተለያየ የጭፈራ ስልት እየተቀባበሉ ታቦታቱ አስቲያርፉ ወይም እስቲገቡ ድረስ ይጨፍራሉ። ወጣት ሴቶችና እናቶችም ታቦታቱን የሚመለከቱ ዜማዎችን እያሰሙ ያጅባሉ። በተለይ በአስራ ሁለት (የሚካኤል እለት) በአሉ እንደሚደምቅ ስለሚታወቅ ወልዲያ፣ ሮቢትና ቆቦ አካባቢዎች ረዳቶችን በመላክ በተቻለ መጠን በቴፕ እንዲቀዱ ተደርጓል።

በካሴት ተቀድተው ወደ ወረቀት የተገለበጡት ግጥሞችም ሆኑ በአንዳንድ ቡድኖች በመጠጋት የተሰሙት ግጥሞች ታቦታቱን የሚያወድሱ ሳይሆኑ፣ ጀግንነትን፣ ጉብዝናን፣ ደፋርነትን የሚያበረታቱ፣ ፈሪነትን፣ ሴሰኝነትን፣ ወዘተ. የሚተቹ ነበሩ። በመሆኑም፣ ወልዲያ ሁለት የቴፕ ካሴት፣ ቆቦና ሮቢትም እንዲሁ ሁለት የቴፕ ካሴት በአጠቃላይ አራት የቴፕ ካሴት

በጭፈራ ላይ መቅዳት ተችሏል። ከነዚህ ካሴቶች የተደጋገሙትን በማስቀረት ወደ አንድ መቶ አስር የሚሆኑ ቃልግጥሞች ተሰብስበዋል።

በጥምቀት በአል አከባበር ጊዜ አዳዲስ ገጠመኞች፣ (ምናልባትም በስራ ምክንያት የትውልድ አከባቢየን ለቅቄ አሁን ወደምኖርበት የስራ አካባቢ ከሄድኩ በኋላ፣ የተፈጠሩ ናቸው ብየ አስባለሁ) ለማየት ችያለሁ። ቆቦና ወልዲያ ታቦታቱ ሲወጡም ሆነ ሲገቡ፣ ማለትም ከቤተክርስቲያኑ ወደ ከተራው፣ ከከተራው ወደ ቤተክርስቲያኑ፣ ሲሄዱ ከፊት ለፊት ቀጤማ (ጉዝጓዝ) በመኪና ተጭኖ፣ በመንገዱ ላይ እየተጎዘጎዘ ነው። ይህ ሁኔታ አካባቢው ጥሩ ሽታ (ጠረን) እንዲኖረው አድርጓል። ከዚህ ሌላ፣ በየቡድኑ ከሚጨፍሩት ወጣቶች መካከል ጥቂት ሴቶች በጭፈራው ውስጥ አብረው ሲጨፍሩ ታይተዋል። ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል በነበረው ባህላዊ የጭፈራ ክዋኔ ላይ ያልነበረ አዲስ ክስተት ይመስላል። በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በሚከውኗቸው የታቦት ማጀቢያዎች ላይ ከሴቶቹ ጋር በመሆን ወንድ ወጣቶች (ምናልባት የሰንበት ተማሪዎች ይሆናሉ) እያጨበጨቡ የቤተ-ክርስቲያን ዘፈን ሲያወጡ ታይተዋል። ወቅቱ ከአረብ አገር ስደት ተመላሾች ወደ አካባቢያቸው የገቡበት ጊዜ ስለነበር በጭፈራው ላይ ሴቶቹ መታየታቸው፣ምናልባት የባህል ናፍቆታቸውን ለመወጣት የተሳተፉ ይመስላል። ወንዶቹም ቢሆኑ፣ ሴቶቹን በጭፈራው ሂደት ችግር እንዳይደርስባቸው በመሀል አድርገው እንዲጨፍሩ ማድረጋቸው ይህንኑ የተረዱላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ከዚህ ሌላ፣ ቆቦ ላይ ከ7-10 አመት የሚሆናቸው ልጆች፣ በአንድ ላይ ሆነው ሲጨፍሩ፣ (ጭፈራ ሲለማመዱ ማለት ይሻላል) የታየው፣ ሌላው ገጠመኝ ነው። በሁለት ወጣቶች አስተባባሪነት ልጆቹ ሲጨፍሩ ተስተውሏል። ይህ ሁኔታ ቀደም ባለው ጊዜ ያልነበረ፣ ካለም በሆያ ሆዬ፣ እና በሌሎች የልጆች በአላት ጊዜ የሚታይ ነበር። እንዲሁም፣ ቆቦ ላይ በነበረው በአንድ የጭፈራ ቡድን ውስጥ፣ አንድ አካል ጉዳተኛ ወጣት፣ በወጣቶች ትከሻ ላይ ሆኖ ጭፈራ ሲያወጣ ተስተውሏል። እነዚህ ሁኔታዎች (ገጠመኞች) ለባህሉም ሆነ፣ለእኔ አዳዲስ ገጠመኞች ናቸው ማለት ይቻላል።

ከላይ እንደጠቀስኩት መስክ ላይ ካጋጠሙኝ ገጠመኞች አስቸጋሪና ፈታኝ የነበረው ሁኔታ፣ የበአል ቀናት በየአካባቢዎቹ በተመሳሳይ ቀንና ስአት የሚካሄድ መሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በተለይ ቆቦ አካባቢ፣ የሰርግ ቀን በአብዛኛው እሁድ ቀን የሚከናወን በመሆኑ፣ ብዙ የሰርግ ስነ ስርአት በአንድ ቀን ይፈጸማል። ለምሳሌ፣ ጥር 18/2006 ዓ.ም. በገጠርና በከተማ ከአስር ያላነሰ የሰርግ ስነ ስርአት እንደተፈጸመ ለመረዳት ችያለሁ። እንዲህ አይነቱ

አጋጣሚ ለአንድ መስከኛ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይታወቃል። ምክንያቱም፣ መስከኛው በሁሉም ቦታ መገኘት ስለማይችል ነው። በየአካባቢው መገኘት ይቅርና፣ በአንድ አካባቢ ባለው የበአል ቀን እንኳ፣ በየቡድኑ የሚደረገውን ጭፈራ ለመቅዳት የሚያስቸግር ሁኔታ ነበር። የተሻለ አጋጣሚ ሆኖ ያገኘሁት፣ በወቅቱ ከስደት የተመለሱ ወጣቶች በጥምቀት በአል ላይ በብዛት ተገኝተው ይጨፍሩ የነበረ መሆኑ ነው። እነዚህ ወጣቶች በቡድን በቡድን እየሆኑ ይጨፍሩ ስለነበር፣ በየቡድኑ እየገቡ በካሴት ለመቅዳት ምቹ አጋጣሚ ፈጥሯልኛል።

ከጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ቆቦ ውስጥ በሚደረጉ የሰርግ ስነ ስርዓቶች ላይ ተገኝቸ፣ መረጃ ለመሰብሰብ በማቀድ፣ ጥር 18 ቀን 2006 ዓ.ም በነበረው ሰርግ ላይ አንድ ካሴት የቀረርቶ ቃልግጥሞችን መሰብሰብ ችያለሁ። በዚህ አጋጣሚም፣ ከአቶ ደሳለ ፈንታው፣ ከአቶ ሞላ ገበየሁና፣ ከሌሎችም ግለሰቦች በቀረርቶ ያልተባሉ የተለያዩ ታሪካዊ ቃልግጥሞች መሰብሰብ ተችሏል። በተለይ፣ የጭፈራ፣ የዘፈን፣ የጦርነትና የረሀብ ቃልግጥሞች በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ አበራ ሞላ፣ ፈንታየ አሸብር፣ ዘውዱ ፈንታየ፣ አስማማው አንባው፣ እና ሌሎችም መረጃ በመስጠትና፤መረጃ ሰጭዎችን በማገናኘት፤ በከፍተኛ ሁኔታ አግዘዋል። በመሆኑም፣ እስከ ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ በተቻለ መጠን የተደጋገሙትን በመለየት ወደ አምስት መቶ ሃምሳ ያህል ቃልግጥሞችን በመሰብሰብ ወደ አዲስ አበባ ለምዝገባ ተመልሻለሁ።

ሁለተኛውን ዙር የመስክ ተግባር ለማከናወን ምክንያት የሆነው፣ በዞኑ ውስጥ ለጥናት ከተመረጡት ወረዳዎች መካከል አንዱን ወረዳና፣ በአንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተገጠሙ ግጥሞች፣ በቂ መረጃ ባለመሰብሰቡ ምክንያት ነው። የሀብሩ ወረዳም በመጀመሪያው ዙር መረጃ ያልተሰበሰበበት ስለነበር፣ የሁለተኛው ዙር የመስክ ተግባር ተካሂዷል።

በዞኑ ባለሙያዎች እይታ፣ የዞኑ ወረዳዎች ቆላማና ደጋማ ወረዳዎች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ የሚችሉ ናቸው። ቆላማ ወረዳዎች የሚባሉት ከአዲስ አበባ እስከ መቀሌ የሚዘልቀውን የመኪና መንገድ መነሻ አድርጎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ያሉትን አካባቢዎች የሚያካትት ነው። ደጋማ ወረዳዎች የሚባሉት ደግሞ ይህንኑ መንገድ መነሻ አድርጎ፣ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ፣ ያሉትን ተራራማ አካባቢዎች የሚሸፍን ነው። ስለሆነም፣ በተመረጡት ቆላማ አካባቢዎች በቂ መረጃ ባለመሰብሰቡና የጥናት አካባቢዎቹ ባለመሸፈናቸው ምክንያት፣ የሁለተኛው ዙር የመስክ ተግባር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የሁለተኛውን ዙር የመስክ ተግባር ለማከናወን ሌላው ምክንያት በአንደኛው ዙር በቀላሉ ሊገኙ ባልቻሉት የመረጃ አቀባዮችና የቃልግጥም አይነቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ፣ ከላይ እንደተጠቀሰው በአንደኛው ዙር ሀብሩ ወረዳ ላይ ምንም አይነት መረጃ አልተሰበሰበም ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በሁሉም አካባቢዎች፣ የፖለቲካ፣ የእርስ በርስ ጦርነትን የሚያመለክቱ፣ እንዲሁም የረሀብ ጊዜያት ቃልግጥሞች የተፈለገውን ያህል መሰብሰብ አልተቻለም ነበር። በመሆኑም፣ በሁለተኛው ዙር የመስክ እንቅስቃሴ ከሚያዚያ ወር 2006 ዓ/ም መጨረሻ ጀምሮ እስከ ሰኔ ወር 2006 ዓ/ም ድረስ ተከናውኗል።

በዚህ መሰረት፣ በ9/9/2006 ዓ.ም.ሳንቃ በለስ ቀበሌ ውስጥ፣ አቶ አያሌው አሰፋ ከሚባሉ ግለሰብ የተለያዩ ቃልግጥሞችን መሰብሰብ ተችሏል። እንዲሁም፣ መርሳ ላይ (አቧሬ) ከምትባል ቀበሌ ከ12-16/2006 ዓ/ም ድረስ ባሉት ቀናት በመመላለስ፣ ብዙ ቃልግጥሞች ተሰብስበዋል። መርሳ ላይ መረጃ የሰጡኝ ግለሰቦች፣ መ/ር አብረሃ ሺፈራው፣ አቶ ተበጀ መኮንን እና አቶ አሊ መሀመድ የሚባሉ አባቶች ናቸው። ሁሉም ቃልግጥምን አስታውሶ የመናገር ችሎታቸው፣ እጅግ ከፍተኛ ነው። በአራት ቀን ምልልስ፣ ወደ አምስት መቶ የሚደርሱ ቃልግጥሞች ተሰብስበዋል። ከሁሉም ለየት የሚለው የአቶ አሊ መሐመድ ሁኔታ ነው። በ14/9/2006 ዓ/ም በአካል ከተገናኘን በኋላ፣ የተወሰኑ ቃልግጥሞችን በመሰብሰብ፣ በአቶ ተበጀና በመ/ር አብርሃ አግባቢነት በ16/9/2006 ዓ.ም ከጧቱ 4፡00 ስአት ጀምሮ እንድንገናኝ ቀጠሮ ተያዘ። በተባለው ቀን መርሳ ላይ፣ ከአቶ አሊ መሀመድ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። እሳቸው እንደሌሎች ሰዎች ቀስ እያሉ አይናገሩም (ግጥም አይነግሩም)። ለምሳሌ፣ የዘፈን ቃልግጥሞችን ሲናገሩ፣ በዘፈን የዜማ ስልት በእግራቸው መሬቱን፣ በእጃቸው ጭናቸውን፣ እየመቱ ነበር የሚዘፍኑት። በመሆኑም፣ ከረፋዱ አራት ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ 6፡30 አካባቢ ድረስ፣ በቴፕ መቅዳት ተችሏል። በዚህ ወቅት ስለራሳቸውም አንዳንድ ጥያቄዎችን እያነሳን ተጨማሪ መረጃ ተሰብስቧል። በተለይ፣ በሚያዩትና በሚሰሙት ጉዳይ ላይ፣ በቃላቸው ግጥም የመግጠም ችሎታቸው የተለየና አስደናቂ እንደሆነ ተረድቻለሁ።

እንዲሁም፣ በሁለተኛው ዙር የመስክ ተግባር ወቅት፣ በአካባቢው (ከራያና ቆቦ እስከ ራያ አዘቦ ድረስ) ስሙ ይታወቅ የነበረውን፣ የታዋቂውን የባህል ተጫዋች (አዝማሪ ተገኘ ጉባይ)፣ ቃልግጥሞች ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት ነው። በዚህም፣ አንዳንድ ግለሰቦች የእሱን ግጥሞች እያስታውሱ እንዲናገሩ በተደረገው ጥረት፣ ከወጣት ሞገስ አያሌውና ከጓደኞቹ፣ እንዲሁም ከአቶ ይላቅ ደጉ፣ የተወሰኑ ግጥሞችን መሰብሰብ ችያለሁ። ከዚህ በተጨማሪ፣ በአጋጣሚ በህይወት በነበረበት ጊዜ፣ የተቀዳ ካሴትም ለማግኘት በመቻሉ፣

ድግግሞሹን በማስወገድ፣ ወደ120 ቃልግጥሞች ተሰብስበዋል። በአጠቃላይ በሁለቱ ዙር የመስክ ተግባራት፣ ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ ቃልግጥሞች መሰብሰብ ተችሏል። ከዚህ መረጃ ውስጥ ሰባት መቶ ያህሉ ቃልግጥሞች፣ በስምንት ዋና ዋና ምድቦች በይዘት ወይም በጭብጥ ተመድበዋል። በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ፣ ሌሎች ንዑሳን ምድቦችን በመለየት፣ ገለፃ ከተደረገ በኋላ፣ አራት መቶ ያህሉ ትንተና ተደርጎባቸዋል።

4.3 የጥናት አይነት

የማህበራዊ ሳይንስ ወይም የፎክሎር ጥናቶች አይነታዊ የምርምር አይነቶች ናቸው። ለአይነታዊ ጥናትና ምርምር የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚባሉት፣ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና መጠይቅ ናቸው:: ከዚህ አንጻር የስነቃል ጥናት አይነታዊ ምርምር ስለሆነ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ዋናዎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ይሆናሉ ማለት ነው:: ይህንን በሚመለከት ያለው (1989፣ 20) ‹‹አይነታዊ ምርምር በተፈጥሮአዊ መልኩ ምልከታ ማካሄድን፣ ያዩትንና ያስተዋሉትን መመዝገብና በተገቢው መንገድ መግለፅ፣ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ አማካይነት ከእያንዳንዱ ግለሰብ የሚገኘውን አስተያየት በጥንቃቄ መመዝገብ ወይም መቅዳትና፣ ይህንኑ በትንተናው ውስጥ እያካተቱ ገለፃ ማድረግ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ነው›› ይላሉ።

የስነቃል አጠናን፣ ቴክስት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስለሆነ ጥናቱ ባለ ሶስት ደረጃ ሞዴልን (tripodal- Scheam) ተከትሎ የሚሰራ እንደነበርና፣ ደረጃዎቹም መሰብሰብ (collecting)፣ መመደብ (classifying) እና መተንተን (analyzing) ናቸው በማለት (Ben Amos፣ 1982፣16) ይገልጻሉ። እንዲህ አይነቱ ጥናት አውዳዊ መረጃዎችን ስለማያካትት ኋላቀር ነው ቢባልም መስከኛው መስክ ላይ በሚቆይባቸው ጊዜያት አውዳዊ መረጃዎችን እየጠየቀ መሰብሰብ ከቻለ ሞዴሉ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል::በዚህ ጉዳይ ላይ Getie (2001፣19) የተለያዩ የስነቃል ተመራማሪዎችን ጠቅሰው እንደገለጹት ‹‹በአፍሪካ ስነቃል ጥናት ውስጥ አካባቢያዊ ግጥሞችንና ዘፈኖችን ሰዎች በሚገጥሙበት፣ በሚደረድሩበት፣ እና በሚከውኑበት ጊዜ ተገቢ የሆነው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድና የገለጻው ትኩረት መሆን ያለበት የክዋኔውን ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ አውዶችን ከመግለጽ ላይ ነው»ይላሉ።

ከምልከታና ከቃል መጠይቅ በተጨማሪ ለአይነታዊ ምርምር የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች /ምንጮች/ ሆነው ሲያገለግሉ የሚችሉት ቡደን ተኮር ውይይቶች እና መዛግብት እንደሆኑ /ፈቃደ፣ 1991፣ 120)፤ (ያለው፣1989፣151-152) ያስረዳሉ:: እነዚህን መንገዶች ከመጠቀም

አንጻር ጠቅለል ባለ ሁኔታ፣ አንድ የፎክሎር ባለሙያ የፎክሎር መረጃዎችን ሊያገኝባቸው ይችላል የሚባሉትን ሶስት መሰረታዊ መንገዶች Dorson (1972፣ 46) ‹‹ አንድ ፎክሎረኛ ወይም መስክኛ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን በሶስት መሰረታዊ መንገዶች ሊያገኝ ይችላል። እነሱም በመስክ ላይ (through field work)፤በቤተ መዛግብት (from archive)እና ከህትመት ዋና መንገዶች የሚፈለገውን የፎክሎር መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ናቸው። በመሆኑም፣ ይህ ጥናት የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰነዶች፣ ቀረጻና ማስታወሻ ናቸው።

4.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው ለማህበዊ ሳይንስና ለፎክሎር ጥናትና ምርምሮች አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚባሉት ምልከታ፤ቃለ መጠይቅ፤ሰነዶች፤ወዘተ. ናቸው።ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመሆን ያገለገሉት የሚከተውት ናቸው።

4.4.1 ምልከታ

በዚህ ጥናት ምልከታ እንደመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥቅም ላይ ሲውል በክዋኔ ወቅት /በጭፈራ፣ በዘፈን፣ በቀረርቶ/ እና በውይይት ወቅት ወይም በክዋኔ ላይ የሚያወርዷቸውን ቃልግጥሞች እየሰበሰቡ፣ ያለውን ሁኔታ በሚመለከት መረጃ መሰብሰብን የሚመለከት ይሆናል:: ምልከታ ከውጭ ሆኖ የተመለከቱትን መግለፅ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የስሜት ህዋሳት አማካይነት የሚሰማውንና የሚታየውን እስከ ማካተት የሚደርስ መሆኑን (Goldstein፣ 1964፣ 77) ያመለክታሉ::

ምልከታ መስክ ላይ እንደሚገኘው አጋጣሚና ምቹነት እየታየ የሚካሄድ የመስክ ተግባር ነው። በመሆኑም፣ መስክ ላይ በነበርሁበት ጊዜ የተገኘሁባቸው አጋጣሚዎች የጥምቀት በአልና ሰርግ ናቸው። በነዚህ የክዋኔ አጋጣሚወች በመገኘት ለዚህ ጥናት መረጃ የሚሆኑ ግጥሞች መሰብሰብ ተችሏል። ሰርግ ላይ በነበረው የምሽት ቀረርቶ አንድ ካሴት የሚሆን መረጃ ተቀድቷል።በምልከታው ላይ እንደተስተዋለው፤ በክዋኔው ሂደት አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢፈጠሩም በተቻለ መጠን በጥራት የሚደመጠውን ቀረርቶ ለመቅዳት ጥረት ተደርጓል። ሰርጉ ላይ ከገጠር አካባቢ የመጡ የተለያዩ ግለሰቦች ስለነበሩ፣ በሞቅታ መንፈስና ስሜት የቀረርቶውን ድባብ አስቸጋሪ አድርገውት ነበር ማለት ይቻላል። ሲያቅራሩ አይደማመጡም ወይም አንዱ ባንዱ ላይ ይደረብ ነበር። እንደዚሁም፤ በጥምቀት በአል ላይ በተገኘው አጋጣሚ ቆቦ፣ ወልዲያና ሮቢት አካባቢዎች በአሉን ለማክበር በቡድን በቡድን እየሆኑ ከሚጨፍሩት

ወጣቶች አምስት ያህል ካሴቶች መቅዳት ተችሏል። የጨፋሪው ቡድን ብዛት ብዙ ስለነበር በሁሉም ቡድን አየገቡ መቅዳት አስቸጋሪ ነበር።

4.4.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ማለት በቃል የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን፤በተለይ ለአይነታዊ የምርምር ዘዴ ጥሩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆን ያገለግላል(ያለው፤2006፤183)።ቃለ መጠይቅ ለስነቃል መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥቅም ላይ ሲውል ከተለያየ አቅጣጫ መሆን አለበት። አንድ መረጃ አቀባይ ስነቃሉን እንዲነግረን ከማድረግ አንስቶ የግል ህይወቱን፣ የፈጠራ ችሎታውን፣ የመከወን ብቃቱን፣ የስነቃሉን ትርጉም (ፍች) እና ፋይዳ፣ ወዘተ. እስከሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት እስከመጠየቅ የሚደርስ ይሆናል። ባዶ ቴክስት (ግጥም፣ ተረት...) መሰብሰብ ብቻ በትንተና ወቅት የተሟላ ገለፃ እንዳይኖር ስለሚያደርግ በተቻለ መጠን፣ ስለሚሰበሰቡት የስነቃል መረጃዎች የተሟላ ሀሳብ እየጠየቁ መሰብሰብ የመስክኛው ግዴታም፣ ተግባርም ነው።

በመስክ ላይ በቃለመጠይቅ ዘዴ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ሁለት አይነት መሰረታዊ የአጠያየቅ ዘዴዎች እንዳሉ Macdonald (in Dorson፣ 1972፣ 420) ፣ Jakson (1987፣ 96)፣ Goldstein (1964፣ 108-112) ይገልፃሉ። እነሱም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ናቸው። በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ላይ ሁለቱን እያፈራረቁ ወይም በተለያየ መንገድ እያቀረቡ መረጃ መሰብሰብ እንደሚቻል (Macdonald፣ 420) ያስረዳሉ። በቀጥተኛ (directive) ዘዴ መስክኛው ልዩ የሆኑ ጥያቄዎችን ለመረጃ ሰጪው እያቀረበ መልስ የሚሰበሰብበት ሲሆን ቀጥተኛ ያልሆነ (non directive) ዘዴ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለመረጃ ሰጭው ክፍት የሆኑ ጥያቄዎች በመጠየቅ እና መረጃ ተቀባዩ ደግሞ በንቃት የሚያዳምጥበትን ሁኔታ የሚፈጥር ነው (Jakson፣ 96)።

በቃለ መጠይቅ ሂደት (ወቅት) አንዳንድ ጊዜ በቃል ለመግባባት፣ በቴፕ ለመቀዳት የተጠየቁትን በቀላሉ ለመረዳት የማይችሉ ወይም ፈቃደኛ የማይሆኑ ሰዎች ሊገኙ ይችላሉ። በሌላ በኩል ብዙ የስነቃል አይነቶች ሰብስበን ስለነሱ ያለን መረጃ ወይም ገለፃ አነስተኛ የሚሆንበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። እንዲህ አይነት አጋጣሚ በሚፈጠርበት ጊዜ መፍትሄው ደግሞ ቃለ መጠይቅ ማድረግ እንደሆነ (Borland in Schoemaker፣ 1990፣ 187-190) ይመክራሉ። አያይዘውም በቃለ መጠይቅ አማካይነት ጥሩ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ እና እንደልምድ መያዝ ያለባቸው ደንቦች (rule of tumb) የሚሏቸው አንደኛ በተቻለ መጠን ግልፅ ሆኖ

መቅረብና አብሮ እንደሚሳተፍ ማስረዳት፣ ሁለተኛ፣ የቃለመጠይቁን ሁኔታ በተቻለ መጠን የተዝናና እና መደበኛ ያልሆነ ለማድረግ በመጣር ሰዎች በነፃነት እርስ በረስ እንዲወያዩ ማድረግ፣ እና ሶስተኛ፣ መረጃ አቀባዮች በየትኛው የስነቃል አይነት እውቀት እንዳላቸው እና እንደሌላቸው መለየት ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ::

ስለሆነም፣ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ማለትም ጥያቄዎች ተዘጋጅተው፣ ተጠያቂዎቹ ግለሰቦች አንዲያውቋቸውና እንዲዘጋጁባቸው ተደረጎ ሳይሆን የታሪክና የባህል አውቀትና ገጠመኝ ይኖራቸዋል ተብለው ከተመረጡ ሰዎች ጋር በመወያየት በተካሄደ መንገድ ነው:: ዘዴው፣ በተለይ ስለ አንዳንድ ግጥሞች ይዘት ግለሰቦቹን ተጨማሪ ሀሳብ በመጠየቅ ለመያዝ እንዲቻል ረድቷል:: በዚህ ዘዴ መርሳ ውስጥ ሶስት መረጃ ሰጭዎች፤ ወልዲያ አራት፤ ቆቦና ጎብየ ውስጥ ሰባት ሰዎችን በድምሩ አስራ አምስት ግለሰቦችን በመጠየቅ የጥናቱን ከፍተኛ ቁጥር የሚሸፍነውን ግጥም መሰብሰብ ተችሏል:: ግጥሙ ሲሰበሰብ የተወሰነውን በማስታወሻና በወረቀት በመጻፍ ሲሆን፣ የተወሰነውን ደግሞ በቴፕ በመቅዳት ነው:: በተለይ ከአቶ አሊ መሃመድ የሰበሰብኳቸውን ግጥሞች በሙሉ በቴፕ እየቀዳሁ ነው:: ምክንያቱም፣ እሳቸው ግጥም ሲገጥሙ ወይም ሲናገሩ አከታትለው ስለሆነ፣ በወረቀት ወይም በማስታወሻ መያዝ አይቻለምና ነው::

4.4.3. ሰነዶች

ሰነዶች እንደየመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ የመስክኛውን ልዩ ትኩረት የሚሹ ናቸው:: በሰነዶቹ ውስጥ የተገኘው መረጃ እውነተኛነት፣ ከወገናዊነት ነፃ የመሆኑ ሁኔታዎች የተሟላ ሀሳብ ያለው ከመሆን አንፃር፣ እየታየ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል:: አሁን ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በአካባቢው ያሉ አንዳንድ ተቋማት ስነቃልን የመሰብሰብ ልማድ እያዳበሩ ስለሆነ ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች ተጠርዘውም ይሁን በህትመት መልክ ቃልግጥሞች ተሰብስበው የሚገኙባቸው ሰነዶች ከተገኙ እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ:: መዛግብት /ሰነዶች/ በዕሁፍ መልክ ተዘጋጅተው፣ ታትመው ወይም ሳይታተሙ በልዩ ልዩ ቦታና ሁኔታ በግለሰቦች ወይም በተቋማት ውስጥ የሚገኙ ስለሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ (ያለው 1989፣ 197) በማለት እንደመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መጠቀም እንደሚቻል ይገልጻሉ::

በመሆኑም የዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ባለሙያዎች በዞኑ ውስጥ ባሉት አካባቢዎች አንዳንድ የስነቃል መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሙከራ አድርገዋል:: ከየዎረዳዎቹ የተላኩትን የስነቃል

ስብስቦች ለመነሻ እንዲሆነኝ ስለሰጡኝ፣ ከነዚህ ሰነዶች ጥቂት ግጥሞችን ማግኘት ችያለሁ። ከነዚህ ሰነዶች ያገኘኋቸውን ግጥሞች ከግለሰቦች ላይ እንደገና ስላገኘኋቸው ሃሳባቸውን እያጠነከርሁ መረጃ ለመያዝ አስችሎኛል። በተመለከተኳቸው ሰነዶች ውስጥ ከፖለቲካ፣ ከርስ በርስ ጦርነት፣ እንዲሁም ከርሀብ ዘመን ጋር ተያይዞ የተገጠሙና የተነገሩት ግጥሞች በፍጹም አልተካተቱባቸውም። ከነዚህ ሰነዶች አንድ መቶ ያህል ግጥሞች መሰብሰብ ተችሏል። ከነዚህ ሰነዶች በተጨማሪ አቶ ተገኘ ጉባይ ሲጫዎት ከተቀዳቸው ሁለት ካሴቶችና የሱን ግጥሞች ከሚያስታውሱ ወጣቶች አንድ መቶ ሀያ የሚሆኑ ግጥሞች መስክ ላይ መሰብሰብ ችያለሁ።

4.4.4 ቀረጻና ማስታወሻ

የስነቃል ጥናት መረጃ በማስታዎሻ ከመጻፍና ፎቶ ከማንሳት በተጨማሪ በቴፕ መቅዳት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ከዋኔው በባህሪው ፈጣን ስለሆነና መረጃ ሰጭዎችም ቀስ እያሉ መረጃ ማቀበል ስለሚቸገሩ ቀረጻ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም፤ በሁለቱ ዙር የመስክ ተግባራት፤በጥምቀት በአል ይከወኑ(ይጨፈሩ) ከነበሩ ባህላዊ ጭፈራዎች፤ሰርግ ላይ በነበሩት ቀረርቶና ባህለዊ ዘፈኖች እንዲሁም በቴፕ ከተቀዱ መረጃ ሰጭዎች፤ አስር ካሴቶች በመቅዳት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። ጭፈራዎቹንም በቴፕ ከመቅዳት በተጨማሪ፣ በቪዲዎ ካሜራ ለመቅረጽ ተሞክሯል።

4.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች

የስነቃል መረጃ ለመሰብሰብ ወደመስክ በሚወጣበት ጊዜ የመስክ ሁኔታውና የሚሰበሰበው የስነቃል አይነት ወሳኝ ይሆናሉ:: መስክኛው የሚሰበሰበውን የስነቃል አይነት መቼ? የት? በምን አይነት ሁኔታ? ወዘተ. ሊያገኝ እንደሚችል ከወዲሁ ማሰብ ይገባዋል:: ምንም እንኳ የመስክ ላይ እንቅስቃሴው የተመቸ ይሆናል ተብሎ ባይታሰብም በተቻለ መጠን የመስክ ተግባርን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን በጥበብና በትዕግስት ማለፍ የመስክኛው ሃላፊነትና ብቃቱም የሚወሰንበት ይሆናል ነው::

ከዚህ አንፃር መስክ ላይ የስነቃል መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የመስክ መቼቶች፣ ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሰራሽ (አርቲፊሻል)፣ እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼቶች ናቸው (ፈቃደ፣ 1991፣ 122-124):: ተፈጥሮአዊ መቼት የሚባለው የስነቃል አይነቱ በባህል ወይም በተለምዶ የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ሲሆን የቃልግጥም ተፈጥሮአዊ መቼቶች ሊሆኑ

ከሚችሉት መካከል የሰርግ የስራ ክብረ በአላቶች ልዩ ልዩ መዝናኛ ቦታዎች፣ ጥቂቶቹ ናቸው:: በእነዚህ ቦታዎች መስከኛው እየተገኘ መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ቃልግጥሙ በተፈጥሮአዊ መቼቱ ከነሙሉ ክዋኔው እና ከታዳሚዎቹ አኳያ እየታየ የተሟላ መረጃ ለመያዝ ያስችላል ማለት ነው::

በሌላ በኩል መስከኛው የስነቃል አይነቱ በተፈጥሮአዊ መቼቱ ሲከወን ባልተገኘበት ጊዜ ወይም አጋጣሚ፣ ወይም ደግሞ የስነቃል አይነቱ ከክዋኔ ውጪ ሆኖ እየተረሳ፣ እየተለወጠ በሚሄድበት ሁኔታ ያለን ስነቃላዊ አይነት ቅርስ የማስቀረትና የመሰነድ አስፈላጊነት ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ ሲፈጠር የሚሰበሰብበት መቼት ሰው ሰራሽ /አርቲፊሻል/ መቼት ይሆናል:: ሰው ሰራሽ መቼት ባንድ በኩል፣ ከዚህ በፊት ይከወን የነበረ፣ ዛሬ ግን የሌለን የስነቃል አይነት ክዋኔውን እያስታወሱና እያስመሰሉ የሚከወኑበት መቼት ሲሆን፣ በሌላ በኩል አንድን የስነቃል አይነት ከአውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ቦታና ጊዜ መስከኛው እየጠየቀ ስነቃሉን የሚሰበሰብበት መቼት ነው (ፈቃደ፣ 1991፣ 123) ይላሉ:: በመሆኑም፣ ይህ ጥናት ተፈጥሯዊ እና አርቲፊሻል መቼቶችን በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል::

4.6 የትንተና ዘዴዎች

ይህ ጥናት አይነታዊ ስለሆነ፤ትንተናው ኢትኖግራፊክ (Ethnographic) እና ተንታኝ የሚባለው ነው:: ኢትኖግራፊክ ማለት የአንድ ቡድን ሰዎችን የማጥናትና የመማር ሂደት ሆኖ ስለነዚህ ሰዎች ወይም ቡድኖች የተመለከተውን መግለፅና መተንተን ነው Sims (2005፤202) ይላሉ:: በመሆኑም የተጠኝው ማህበረሰብ ባህል፤ልማድ፤እምነት፤ወዘተ. በስነቃሉ ውስጥ ስለሚንፀባረቅ የዚህ አይነቱ ጥናት የማህበረሰቡን አጠቃላይ ባህልና አስተሳሰብ አውጥቶ ለማሳየት ያስችላል ማለት ነው::

በሌላ በኩል ተንታኝ የምርምር አይነት የሚባለው በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (በተለይ በምልከታና በቃለመጠይቅ) የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከተለያየ አቅጣጫ እየተመለከቱ የሚደረግ ትንተናን የሚጋበዝ ነው:: ይህን በሚመለከት Kothari (2004፤3) ላይ ‹‹ተንታኝ ምርምር (Analyitical Research) ተመራማሪው በእጁ ያሉትን እውነታዎች ወይም መረጃዎች በመጠቀም እነዚህን እየተነተነ ስለመረጃው ጥልቅ ግምገማ የሚያደርግበት ነው›› በማለት ይገልፃሉ:: ስለሆነም ይህ ጥናት በእነዚህ የምርምርና የትንተና ዘዴዎች መሰረት ትንተና አድርጓል::

ምዕራፍ አምስት፡- የአማርኛ ቃልግጥሞች የክዋኔ ስልቶችና የመከወኛ አጋጣሚዎች

ይህ ምዕራፍ በአማርኛ ቃልግጥም ክዋኔ ወቅት ግጥሞቹ የሚቀርቡበትን የዜማ ስልት መሰረት በማድረግ ገለጻ የሚደረግበት ይሆናል። ገለጻው ትኩረት የሚያደርገው በመስክ ላይ በታየው አጋጣሚና ከመረጃ ሰጭዎች ጋር በነበረው የውይይት ሁኔታ መሰረት ነው። ይህንን ለማድረግ የፈለግሁት እስከዛሬ በታዩት፤ ለምሳሌ በተስፋየ መሰል (2007)፤ በሞላ መኮነን (1986)፤ በተክለሀይማኖት ገብረጻዲቅ (1981)፤ በአልማዝ አበበ (1974) ጥናቶችም ሆነ፤ በአካባቢው ያሉት የባህል ባለሟያ ሰራተኞች በሰሯቸው የባህል ጥናት ሙከራዎች ውስጥ፣ የዘፈኖቹንም ሆነ የጭፈራዎቹን አካባቢያዊ ስያሜና የአከዋወን ሁኔታ በተገቢው መንገድ ስላልቀረበ ነው። ይህን ሀሳብ በሚደግፍ ሁኔታ፣

> ...አንድ ፎክሎራዊ ቅርጽ በተለምዶ የሚከወንባቸውን ተፈጥሯዊ አውዶች መመርመር ተገቢ ነው። እሱን ለመገንዘብ ሁለት ተዛማጅ አቀራረቦች ሊኖሩ ይችላሉ። እነሱም፣ ታሪካዊና፣ ማህበረ-ባህላዊ ምልከታዎች ናቸው። ... የሚጠናው የስነቃል ቅርጽ ቀደም ባለው ጊዜ በምን አይነት ሁኔታ፣ ስለምን ምክንያት፣ በነማን፣ እንዴት ይከወን እንደነበር ታሪካዊ ዳራውን መመርመር ተገቢና ተቀባይነት ያለው ነው። ተመራመሪው በመስክ ባልነበረበትና ክዋኔውን ለመመልከት ባልቻለበት ወቅት ወይም ዘመን በማህበረሰቡ ውስጥ ሁኔታዎች ምን ይመስሉ እንደ ነበር ... የመግለጥ ፍላጎት ይኖረው ዘንድ ተገቢ ነው (ብርሀኑ፣ 1995፣47)።

ስለሆነም፣ በተወሰነ የዜማ ስልት የሚቀርቡትን የክዋኔ ስልቶችና የመከወኛ አጋጣሚዎች እንደሚከተለው እንመለከታለን።

5.1. የአማርኛ ቃልግጥሞች የክዋኔ ስልቶች

የዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ በሆኑት አካባቢዎች ውስጥ የአማርኛ ቃልግጥሞች ከሚቀርቡባቸው መንገዶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ባህላዊ ዘፈኖች፣ ባህላዊ ጭፈራዎች፣ ቀረርቶዎች ናቸው። እነዚህም ከBen Amos የአካባቢ ስያሜዎች ጋር የተያዙ ስለሆኑ፣ በስነቃል ጥናት አስፈላጊዎች ናቸው።

ባህላዊ ዘፈኖች፣ በአብዛኛው የደስታ ስሜት የሚንፀባርቅባቸው ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ የናፍቆት፣ የብሶትና የትዝታ ስሜቶችም ይገልፁባቸዋል። ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ እንዲሁም ጎልማሶችና እናቶች ሊያዜሟቸውና ሊከውኗቸው ይችላሉ። ባህላዊ ጭፈራዎች እና ቀረርቶዎች ግን ብዙውን ጊዜ ሀይለኛ ስሜቶች የሚንፀባረቅባቸው ስለሆኑ ወጣት ወንዶችና ጎልማሶች ይከውኗቸዋል እንጂ ሴቶች አይሳተፉባቸውም፣ አያዜሟቸውም። እንጉርጉሮ የውስጥ ስሜት መተንፈሻ የብቻ ዜማ ነው። በአብዛኛው የመከፋት፣ የማዘን፣ የመበደል፣ የመሳሰሉት ስሜቶች የሚንፀባረቁባቸው ግጥሞች ያሉበት (የሚገኙበት) ነው። በአለማዊ ህይወት ውስጥ ያለ ሰው ሲያንጎራጉር የሚያሰማቸው ግጥሞች በመንፈሳዊ ህይወት ካለው ይለያሉ። በመንፈሳዊ ህይወት ያለ ሰው፣ ከፈጣሪው ወይም ከአምላኩ ጋር በመንፈስ የሚገናኝበት ዜማ ነው። ከነዚህ መሰረታዊ ሀሳቦች ተነስተን የባህላዊ ዘፈኖችን፣ ጭፈራዎችንና ቀረርቶዎችን፣ ከአካባቢያዊ ስያሜዎች ጋር እያያዝን ቀጥለን በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን።

5.1.1 ባህላዊ ዘፈኖች

በዚህ ጥናት ውስጥ ባህላዊ ዘፈኖች ማለት መረጃው ከተሰበሰባቸው አካባቢዎች መካከል በተለይ በቆቦ ወረዳ ባሉ አካባቢዎች የሚኖሩ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የሚያዜሟቸውንና፤ ዘፈኑ ወይም ዜማው የራሱ አካባቢያዊ መጠሪያ ያለውን ባህላዊ ዘፈን ነው። እነዚህ ባህላዊ ዘፈኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከወኑ ሲሆኑ፣ ይዘታቸው የተለያየ ነው። ለምሳሌ በሰርግ ላይ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፋኞች ብዙ ጊዜ ይዘታቸው የፍቅር፣ የቁንጅ እና የውበት፣ የሙገሳና የውዳሴ፣ የናፍቆትና ትዝታ፣ ወዘተ. ስሜቶች የሚንፀባረቅባቸው ናቸው። የሙሽራይቱ ጓደኞች፣ ማታ ማታ እየተሰበሰቡ ይዘፍናሉ፣ የሙሽራው ሚዜዎችና ቤተዘመድ በሰርጉ እለት ምሽት እንግዳ ከተሸኘ በኋላ፣ ከቤተ ዘመድ ጋር እየዘፈኑ ያመሻሉ፣ ያነጋሉ።

ባህላዊ ዘፈኖች በሰርግ ላይ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አጋጣሚዎችና ቦታዎች ይከወናሉ። ገበሬው በማሳው ላይ ሲያርስ፣ በማማው ላይ ወፍ ሲጠብቅ፣ ቡቃያውን ሲያርም፣ ወዘተ. እየዘፈነ ያንጎራጉራል፣ በሬውን እያሞገሰ ይዘፍናል። አገዳና እሸቱን በልቶ ሲደሰት፤ የሚወዳትን እያስታወሰ ይዘፍናል፣ ያንጎራጉራል። እረኛው በከብት ጥበቃው፣ የተለያዩ ዘፈኖችን እየዘፈነ ይውላል። ሴቶች በእንጨት ሰበራ፣ በወፍጮ ስራ፣ ወዘተ. የናፍቆት፣ የፍቅር፣ የብሶት ይዘት ያላቸው ግጥሞች እየዘፈኑ ያንጎራጉራሉ።ታዳሚ ባለበት በሚከወኑት ባህለዊ ዘፈኖች

ውስጥ፤በተለይ ‹‹እንከል እንከል›› ከሚለው ዘፈን ውጭ የሚታየው ክዋኔ አውጨው/ዋ ዘፈኑን በሚያወጣበት/በምታወጣበት ጊዜ ከታዳሚዎች መካከል በመቆም ወይም በመቀመጥና በማጨብጨብ ነው፡፡እስክሳ/ታ/ የሚመቱ ከሁለት እስከ አራት የሚሆኑ ሰዎች (ሴቶች፤ ወንዶች፤ሴትና ወንድ ሊሆኑ ይችላሉ)፤ከታዳሚው መካከል ሆነው እያጨበጨቡና እያሸበሸቡ በየመካከሉ በወገባቸውና በትከሻቸው እስክሳ ይመታሉ፡፡ የደከማቸው ሲያርፉ ሌሎች ይነሳሉ፤አውጭውም በተመሳሳይ በሌላ ሊተካ ይችላል፡፡የእስክሳው አመታት ከወገብ በላይ ባለው የሰውነት ክፍል በወገብና በትከሻ ሆኖ፤ነጠላ ወይም ጋቢ ወገብ ላይ በመታጠቅ (በማሸረጥ) ነው፡፡ የታዳሚው ድርሻ ማጨብጨብና መቀበል፤እስክሳ የሚመቱትን ማበረታታት ነው፡፡ የነሸጠውም ካለ ተነስቶ እስክሳ መምታት ይችላል፡፡እስክሳ የሚመቱት ፊት ለፊት በመተያየትና ቦታ በመለዋወጥ ነው፡፡ በአካባቢው ተዘውትረው ከሚዘፈኑት ባህላዊ ዘፈኖች መካከል፣ አዳሬ ሙናዬ፣ አማሮዬ፣ እንከል እንከል፣ እና አሆዬ፣ ጥቂቶቹ ስለሆኑ፣ እነሱን እንመልከት፡፡

5.1.1.1 አዳሬ ሙናዬ

ይህ ባህላዊ ዘፈን አውጭና ተቀባይ ያለው ሆኖ፤ ዘፋኙ / ኟ የዘፈኑን ግጥሞች እየደረደረ/ች ሲዘፍን/ስትዘፍን ታዳሚው “አሀሀሀ...” በማለት ይቀበላል፡፡ “አዳሬ ሙናዬ” የሚለው የዘፈኑ መጠሪያ ሀረግ በየግጥሞቹ ተደጋግሞ በመምጣት እንደ አዝማች ያገለግላል፡፡ የአዘፋፈን ስልቱም፣

ዘፋኙ/ኟ፡- አዳሬ ሙናዬ...
እስቲ እርግ እርጉን አይኔ ይንከራበት
ተቀባይ፡- አሀሀ.....
ዘፋኙ/ኟ፡- አዳሬ ሙናየ...
እንደልቡ አይበላም እረኛ ያለው ከብት
ተቀባይ፡- አሀሀ.....
ዘፋኙ/ኟ፡- አዳሬ ሙናዬ...
ጋሪያ ሌንጫ ሎሚ ጮቢ በር እንኮይ
ተቀባይ፡- አሀሀሀ.....
ዘፋኙ/ኟ፡- አዳሬ ሙናዬ...

ያንን እየበላሽ ቆቦ አትገቢም ወይ

ተቀባይ፡- አሀሀሀ.....

እየተባለ ዘፋኙ/ኟ እስኪደክም / እስክትደክም ድረስ ይዘፈናል፣ ታዳሚውም ይቀበላል፡፡ በሂደትም ሌላ ዘፋኝ ሊተካ ይችላል፡፡ ተተኪው ዘፋኝ ሌላ ዘፈን ሊያወጣ ይችላል ወይም ያንኑ ይቀጥላል፡፡ አሁን አሁን ዘፋኙ/ኟ የግጥሙን ስንኞች ጨርሶ የማዜም ስልት እየተለመደ መጥቷል፡፡

ዘፋኝ/ኟ፡- አዳሬ ሙናዬ....

እስቲ እርግ እርጉን አይኔ ይንከራበት

አባካኝዋየ...

እንደልቡ አይበላም እረኛ ያለው ከብት

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

እየተባለ ይዘፈናል፡፡ይህ አዘፋፈን ከአንድ በላይ ስንኞችን በተከታታይ እየደረደረ የመዝፈን እድል የሚሰጥ ነው፡፡

5.1.1.2 አማሮዬ

ይህ የዘፈን ስልት ልክ እንደ ላይኛው አንድ/ አንዲት ዘፋኝ የሚመራውና ታዳሚ የሚቀበለው ነው፡፡ ከላይኛው የሚለየው የግጥሙን ስንኝ በአንድ ጊዜ አለመጨረሱ ነው፡፡ ዘፋኙ ሀረጎቹን እየከፈለ ስለሚዘፍን ተቀባዩ በመሀል እየገባ ይቀበላል፡፡

ዘፋኙ/ኟ፡- አማሮዬ እንደው አማሮዬ

ተቀባይ፡- አሀሀሀ.....

ዘፋኙ/ኟ፡- አማሮዬ...

ልሂድ መንደፈራ

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

አማሮዬ...

ዘፋኙ/ኟ፡- ከአበበው ዶረት

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

ዘፋኙ/ኟ፡- አማሮየ...

ሲሆን ማር ይገኛል

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

ዘፋኙ/ኟ፡- አማሮየ....

አለዚያ ወተት

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

በማለት ስንኞችን እየደረደሩ ይዘፈናል፡፡ ይህ ስልት በዘፋኙ/ኟ እና በተቀባዮች መካከል ያለው ቆይታ አጭር ነው፡፡ ዘፋኙ/ኟ ሀረጉን ሲጠራ/ስትጠራ ወዲያው ተቀባዩ “አሀሀ...” እያለ ይቀበላል፡፡

5.1.1.3 እንከል እንከል

ይህ የዜማ ስልት ተከታታይነት ባለው ስልት አዝማቹን ሀረግና ተከትለው የሚመጡ ስንኞችን በመደርደር የሚዜም ነው፡፡ ዘፋኙ/ኟ የቻለውን / የቻለችውን ያህል ስንኝ በአንድ የዜማ ሂደት መደርደር ያስችለዋል / ያስችላታል፡፡

ዘፋኝ/ኟ፡ አማሮዬ፣ እንደው እንከል፣ እንከል

ሸጋዋየ፣ እንደው እንቡዲዲ

ጎበላላየ፣ ያረገኛል እሳ

ራቴን በልቼ ማዱ ሳይነሳ

ተቀባይ፡- አሀን፣አሀን፣ አሀን.....

ዘፋኝ/ኟ፡- እንደው እንከል፣ እንከል...

አማሬዋ፣ ያረገኝ ጀመር፣ ጎብላላዋ...

የሷ ፍቅር አልቆ የኔ ሲጀምር

ተቀባይ፡- አሀን፣ አሀን፣ አሀን.....

ዘፋኙ/ኟ፡- እንደው እንከል እንከል

ሙጫ ጤፍ አለችኝ ሸጋየዋ

ያችን ስላልቁ

ሽቋር መንገሻ አገር

መሄዴ ነው ወርቁ

ተቀባይ፡- አሀን፣ አሀን፣ አሀን፣.....

እየተባለ ይዘፍናል። ለዚህ ዘፈን የሚመታው የከበሮ ስልት ከሌሎቹ ዘፈኞች የተለየ ነው። ጭብጨባና አስክስታ አይታይበትም።ወደ እንጉርጉሮ የሚጠጋ፤ግን ተቀባይ ያለው ነው። የከበሮው አመታት የድቤ አመታት አይነት ነው።በዚህ ባህሪው ድምቀት አይታይበትም ማለት ይቻላል።

5.1.1.4 አሆየ

ይህ የዜማ ስልት አንድ / አንዲት ዘፋኝ የሚያቀነቅንበት / የምታቀነቅንበት ሆኖ የዘፈኑ መጠሪያ ሀረግ እንደ አዝማች በመሆን በጣልቃ እየገባ የሚዘፈን ነው።

ዘፋኙ/ኟ፡- አሆየ፣ አሆየን አሆየ
አደ ሙለታየ
ተቀባይ፡- አሆየ አሆየን አሆየ
አደ ሙለታየ
ዘፋኝ/ኟ፡- አሆየ.....
አንቺን ያለው መጣ
ሰው ነገር አያጣ
ተቀባይ፡- አሆየ.....
አንቺን ያለው መጣ
ሰው ነገር አያጣ
ዘፋኙ/ኟ፡- አሆዬ.....
አንቺን ያለውን
በአስሊ ግንባሩን
(በሳንጃ ሆዱን)
ተቀባይ፡- አሆየ.....
አንቺን ያለውን
በአስሊ ግንባሩን
(በሳንጃ ሆዱን)
ዘፋኙ/ኟ፡- የቡጢ ባቤ አገር ስሙ ካዳ ቡራ
በልጅግ ይሸሽጋል የቅንድቧ ጭራ
እጠይቅሻለሁ እኔ እንዳንቺ አልኮራ

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

ዘፋኙ/ኟ፡- ከቀመሌ በላይ ስሙ ነው ዱር ለበስ
አሳውካ መላየ.....
እርቦዋን አንጥፎ ድርምሟን ነው መልበስ

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

ዘፋኙ/ኟ፡- በዋንጉስ ጋሌ ጭንጫ እየመሰለ
ያበቅላል ሽጋ ልጅ እያዘናፈለ
በዋ ንጉስ ጋሌ ስንደዶ ማለፊያ
ወገቧ ቀጭን ነው እንደ አሳመጥለፊያ

ተቀባይ፡- አሀሀ.....

እየተበለ ይዘፈናል፡፡ በዚህ አዘፋፈን ዘፋኙ በእያንዳንዱ ስንኝ ላይ ሌላ ማጀቢያ ቃላትን እያስገባ መጠቀም ይችላል፣ ተቀባይም የዘፋኙን ሁኔታ እየተከተለ ዜማውን እስቲጨርስ እየጠበቀ ይሄዳል፡፡

እነዚህን ባህላዊ ዘፈኖች አንድ አንድ አቀንቃኝ እና ብዙ ታዳሚ ያላቸው ናቸው፡፡ ተቀባዮች እያጨበጨቡ፣ ከበሮ እየመቱ፣ “አሀሀ.....”በማለት ብቻ ይቀባለሉ፡፡ ከታዳሚዎች መካከል ሁለት ሆነው እስክስታ የሚገጥሙም ይኖራሉ፡፡ ዘፋኙ/ኟ ብቻውን / ዋን ሆና በተለያየ ቦታና ሁኔታ ሲዘፍን / ስትዘፍን እንደ እንጉርጎሮ ይሆናል፡፡ ይኸውም እንደተሰማው ስሜትና እንዳለበት ሁኔታ፣ ከግጥሞቹ እያስታወሰ ያንጎራጉራል / ታንጎራጉራለች ማለት ነው፡፡ ባህላዊ ዘፈኖች የደስታ ስሜትና ድባብ ባላቸው ቦታዎች የሚከውኑ ናቸው፡፡ በበአል ጊዜ ታቦት ከገባ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ (ብዙ ጊዜ ሴቶች ናቸው) ይዘፈናል፡፡ ወንዶች በጋራ መጠጥ ቤት ገብተው እየጠጡ ይዘፍናሉ፡፡ የግጥሞቹ ይዘቶች ግን ያው የፍቅር፣ የናፍቆት፣ ቁንጅናን የማድነቅ፣ አካባቢን የማወደስ፣ ወዘተ. ስሜት የሚገለፅባቸው ይሆናሉ፡፡

5.1.2. ባህላዊ ጭፈራዎች

ባህላዊ ጭፈራ ወጣት ወንዶችና ጎልማሶች በትር (ዱላ) ይዘው፣ በቡድን በቡድን ሆነው፣ እየዘለሉ፣ መሬቱን በእግራቸው እየመቱ፣ ወዘተ. የሚከውኑት ጭፈራ ነው፡፡ ባህላዊ ጭፈራዎች እንደ አካባቢው የተለያዩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የጭፈራ አይነቶቹም እንደ

አካባቢው የተለያየ ስያሜ ይኖራቸዋል። በዚህ ጥናት ውስጥ የሚቀርቡት የባህላዊ ጭፈራ አይነቶች በሰሜን ወሎ አካባቢዎች በተለይም በራያና በየጁ አካባቢዎች የሚጨፈሩ ናቸው። ልክ እንደ ባህላዊ ዘፈኖቹ ባህላዊ ጭፈራዎቹም የየራሳቸው ስያሜና የክዋኔ ስልት አላቸው። ባህላዊ ጭፈራዎች የሚከወኑት በወጣት ወንዶችና ጎልማሶች ብቻ ነው። በአካባቢው ከሚታወቁት መካከል የሚከተሉትን ጥቂቶቹ ናቸው።

5.1.2.1 ኮርማ ጋፋ ላሌ

የጭፋራው መጠሪያ ከኦሮምኛ ቋንቋ የተወረሰ ነው። የአማርኛው ትርጉም ‹‹ኮርማው ቀንዱን ወደ ላይ አሹሏል ››የሚል ነው። ይህ ጭፈራ ቀደም ሲል ይከወን የነበረው ወንዶች በበዓል ጊዜ “ጎፈር” ራሳቸው ላይ አድርገው ትንሽ ከበሮ እየመቱ ነበር። የከበሮው አመታት ከዜማው ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ነው። ጭፈራውን የሚመራው ወንድ (አውጭው) ከጓደኞቹ መሀል በመሆን ሲያወጣ የጭፈራው ተሳታፊዎች የሚቀበሉት የጭፈራውን መጠሪያ ‹‹አሀሀ ኮርማ ጋፋ›› የሚለውን ብቻ ነው።

አውጭ፡- አላ ኮርማ ጋፋ ላሌ[13]

ተቀባይ፡- አሀሀ ኮርማ ጋፋ

አውጭ፡- ላሞቹን ንዷቸው

ተቀባይ፡- አሀሀ ኮርማ ጋፋ

አውጭ፡- አቧራው ይነሳ

ተቀባይ፡- አሀሀ ኮረማ ጋፋ

አውጭ፤- ይከተል የለም ወይ

ተቀባይ፡- አሀሃ ኮርማ ጋፋ

አውጭ፡- ኮርማው እያገሳ

ተቀባይ፡- አሀሀ ኮርማ ጋፋ

አውጭ፡- በሰላጤ ቀንዱ

ተቀባይ፡- አሀሀ ኮርማ ጋፋ

አውጭ፡-ምድር እየበሳ

ተቀባይ፡-አሀሀ ኮረማ ጋፋ

[13] አውጭ ማለት ጭፈራውን እየመራ ግጥም የሚያረድረው ግለሰብ ሲሆን፤ተቀባይ ደግሞ የጭፈራውን አይነት እየተከተለ በመቀበል አብረው የሚጨፍሩትን ወጣቶች ማለት ነው።

እያለ ጭፈራው ይከወናል። አውጭው የግጥሙን አንድ ሀረግ ሲጠራ፣ ተቀባይ የጭፈራን ሀረግ ያሰማል። ይህ የጭፈራ አይነት አሁን አሁን እየተረሳ መጥቷል።

5.1.2..2 አሲና ጋማየ

ይህ ባህላዊ ጭፈራ ከላይ እንደተጠቀሰው የዜማ ስልት ያለው ሆኖ ተቀባዩም ዜማውን እየተከተለ የሚጨፍርበት ነው። አውጭው በጭፈራው መጠሪያ ይጀምርና ሌሎች ግጥሞችን እየደረደረ ሲያወጣ፣ ተቀባዩም ‹‹እያሀ አሲና ጋማየ›› የሚለውን ስንኝ እየጠራ፣ በዜማው ስልት ይቀበላል።

አውጭ፡- አጋማየ ኢሲና ጋማየ
ተቀባዩ፡- እያሀ አሲና ጋማየ
አውጭ፡- አጋማየ በለው በመዋጣ
ተቀባይ፡- እያሀ አሲና ጋማየ
አውጭ፡- አጋማየ ከግንበሩ ላይ
ተቀባዩ፡- እያሀ አሲና ጋማየ
አውጭ፡- አጋማየ እናቱም ትርገብገብ
ተቀባይ፡- እያሀ አሲና ጋማየ
አውጭ፡- ውሽማውም ትይ
ተቀባዩ፡- እያሃ አሲና ጋማየ

በማለት አውጭው የተለያዩ ግጥሞችን እደረደረ ይጨፍራል፣ ያስጨፍራል። ዜማ መቀየር ወይም እረፍት ማድረግ ሲያስፈልግ ሁሉም አንድ ላይ በአካል እንቅስቃሴ የታጀበ አንድ አይነት እርግጫ (በእግር መሬትን መምታት) አድርገው፣ ስልት ይቀይራሉ፣ አውጭውም ሊቀየር ይችላል።

5.1.2..3 ሆይ ላሌ መገና

ይህ ባህላዊ የጭፈራ አይነት ፈጠን ያለ ስለት ያለው ሆኖ አውጭው ጭፈራውን ሲጀምር “ሆይ ላሌ ሆይ ላሌ / ሆይ ላሌ መገና” በማለት ሲሆን፣ ተቀባዩም “አሀይ ላሌ ጉማ” ይላል።

አውጭ፡- ሆይ ላሌ...

ተቀባይ፡- አሀይ ላሌ ጉማ

አውጭ፡- የሴቶቹ ወዳጅ

ተቀባይ፡- አሀይ ላሌ ጉማ

አውጭ፡- አለንጎ ዘለጎ

ተቀባይ፡- አሀይ ላሌ ጉማ

አውጭ፡- ክፉ ሲናገሩት

ተቀባይ፡- አሀይ ላሌ ጉማ

አውጭ፡- ይመልሳል በጎ

ተቀባይ፡- አሃይ ላሌ ጉማ

እያለ አውጭው ግጥም እስቲመጣለት ወይም ጭፈራው እስቲሞቅ ድረስ የጭፈራውን ሀረግ መደጋገም ይችላል፡፡ ተቀባዩ ግን ያንኑ ብቻ ማለትም "አሃይ ላሌ ጉማ" የሚለውን ሀረግ ብቻ ይላል፡፡

ፎቶ ሁለት፡- ወጣቶች በጥምቀት በአል ጭፈራ ላይ

5.1.2..5 ገና ነው፤ ገና ነው

ይህ ባህላዊ ጭፈራ እንደ ላይኛው ተቀባዩ አንድ ሀረግ ብቻ በመጥራት ተሳታፊውም ‹‹እህም ነው ገና›› የሚለውን ሀረግ እየተቀበለ የሚጨፈር ነው፡፡ አውጭው ጭፈራውን ‹‹ገና ነው ገና

ነው›› እያለ ማውጣት ሲጀምር፣ ተቀባዩ “እህም ነው ገና” የሚለውን ሀረግ ወይም ስንኝ በማለት ይቀበላል፡፡

አውጭ፡- ገና ነው ገና ነው
ተቀባይ፡- እህም ነው ገና
አውጭ፡- ተቀበል ተቀበል
ተቀባይ፡- እህም ነው ገና
አውጭ፡- ተቀበል ነባዜ
ተቀባይ፡- እህም ነው ገና
አውጭ፡- አህያም ያናፋል
ተቀባዩ፡- እህም ነው ገና
አውጭ፡- ጨሌ ባየ ጊዜ
ተቀባዩ፡- እህም ነው ገና

በዚህ የጭፈራ ስልት ልክ እንደ ላይኛው አውጭው የተለያዩ ግጥሞችን እያስታወሰ ሀረግ ሀረጉን ብቻ ሲል ተቀባዩም “እህም ነው ገና ” የሚለውን ብቻ ይላል፡፡ ይህ የጭፈራ አይነት “ሆይ ላሌ መገና” ከሚለው የጭፈራ ስልት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የአጨፋፈር ስልቱ ፈጠን ያለ ነው፡፡ አውጭው የየግጥሙን አንዳንድ ሀረግ ብቻ ስለሚል ተቀባይም ፈጠን ብሎ ይቀበለዋል፡፡

5.1.2..5. እያያ አያ ሚና አበሎ

ይህ ባህላዊ ጭፈራ ሲከወን የዜማ ስልቱ ከሌሎቹ የተለየ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ተቀባይ “እያያ አያ ሚና በሎ” የሚለውን ሀረግ ሲያዜም ቀስ ብሎ ነው አያፈጥነውም አውጭውም የዜማውን ስልት ዘለግ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ሲጀምርም “እያያ አያ ሚና አበሎ” የሚለውን ስንኝ ደጋግሞ የማለት እድል አለው፡፡ ይህን የሚያደርገውም ጭፈራውን ለማሟቅና ተቀባዩን ለመሳብ ይመስላል፡፡

አውጭ፡- እያያ አያ ሚና አበሎ
ተቀባይ እያያ አያ ሚና አበሎ
አውጭ፡- ሰሰበሌ፣ እንዴት ነው ጎበዙ
ተቀባይ፡- እያያ አያ ሚና አበሎ

አውጭ፡-ሰሰበሌ፤ለሴቶቹ ይምሰል

ተቀባይ፡-እያያ አያ ሚና በሎ

አውጭ፡- ሰሰበሌ አግድመው ቢሮጡ

ተቀባዩ፡- እያያ አያ ሚና አበሎ

አውጭ፤- ሰሰበሌ፤ ያዳልጥ የለም ወይ

ተቀባዩ፡- እያያ አያ ሚና አበሎ

አውጭ፡- ሰሰበሌ፤ ሳሩ ሰንበሌጡ

ተቀባዩ፡- እያያ አያ ሚና አበሎ

በዚህ የጭፈራ ስልት አውጭው ግጥሙን ከማሰማቱ በፊት “ሰሰበሌ” የሚለውን ወይም ሌላ ቃል ከየሀረጉ በማስቀደም እየደጋገመ ይጠቀማል፡፡ይህን በማድረጉ የጭፈራው የዜማ ስልት ዘለግ እንዲል አስችሎታል፡፡

ፎቶ ሶስት፡ ወጣቶች በጥምቀት በአል ጭፈራ ላይ

5.1.2 .6 ሚሌ ወሬ ሀራ / ላልወይ ሰመራ

ይህ የጭፈራ አይነት ከአፋርኛ ወይም ከኦሮምኛ የተወረሰ ሳይሆን አይቀርም “ሚሌ” የወንዝ ስም ነው። መነሻው ወሎ ውስጥ ሆኖ፣ መድረሻው ግን አፋር ውስጥ ነው። “ሀራ” የሚባለው አካባቢ ደግሞ ከዶሮ ግብር አልፎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ የገጠር ከተማ ነው። ከ1983 ዓ.ም. በፊት የገጠር መንደር የነበረና አፋሮች ከታች መጥተው ሲገበያዩ ውለው የሚመለሱበት፣ የአካባቢው ማህበረሰብም እንዲሁ የልዩ ልዩ እንስሳት ግብይት ሲያደርግበት የነበረ፣ አሁንም ያለ ነው።

ጭፈራው አሁን አሁን እየተለወጠ መጥቷል። በየትኛውም አጋጣሚ ሲጨፈር፤ የጭፈራ ስልቱ ከሌሎቹ የተለየ ነው ማለት ይቻላል። በተለይ ተቀባዩ የሚያሰማው ሀረግ በአማርኛ ቋንቋ የተለመደ አይመስልም። አውጭው “ሚሊ ወሬን ሀራ” ሲል ተቀባዩ “መጋሌ ሰመራ›› ይላል። የጭፈራው መጠሪያና የተቀባዩ ምላሽ የአማርኛ ቋንቋ ቃላት አይሁን እንጂ የሚደረደሩት ግጥሞች ግን አማርኛ ናቸው።

አውጭ፡- ሚሌ ወሬ ሀራ
ተቀባዩ፡- መጋሌ ሰመራ
አውጭ፡- የት አለ ግመሉ
ተቀባዩ፡- መጋሌ ሰመራ
አውጭ የት አለ ሀርሞው
ተቀባዩ፡- መጋሌ ሰመራ
አውጭ፡- በረጅም ምንሽር
ተቀባዩ፡- መጋሌ ሰመራ
አውጭ፡- የተወረረው
ተቀባዩ፡- መጋሌ ሰመራ

በማለት ይጨፈራል። አውጭው የቻለውን ያህል ግጥም እየደረደረ መጨፈር ይችላል። የግጥሞቹ ይዘት ከወረራና ከጀግንነተት ጋር የተያያዘ ነው።

ባህላዊ ጭፈራዎች ከፍተኛ ጉልበትና ረዘም ያለ ሰዓት የሚጠይቁ ስለሆነ ወጣት ወንዶችና ጎልማሶች ብቻ የሚሳተፉባቸው ናቸው። አጨፋፈሩም ወይም አከዋወኑ፣ ተሳታፊው አንድ ላይ እጅብ ይልና ወደ ፊት ቀስ እያለ በመሮጥ ወይም አንድ ቦታ ክብ ተሰርቶ ነው። ተሳታፊው ዙሪያውን ሆኖ ሲቀበል አውጭዎቹ መሀል ላይ ይሆናሉ። ቀስ ብሎ በመሮጥ ሲከወን አውጭዎቹ መካከል ይሆኑና፣ ተሳታፊው ከግራ ከቀኝ፣ ከፊት ከኋላ፣ሆኖ ወደ ላይ እየዘለለ፣ የተለያየ የአካል እንቅስቃሴ እያደረገ ይጨፍራል።

5.1.3. ቀረርቶ

ይህ የክዋኔ ስልት እንደ የአካባቢው እና እንደከዋኙ የዜማ ስልትና ችሎታ የተለያየ ነው። የዜማ ስልቱ የተለያየ ቢሆንም በብዙ የአማራ ክልል አካባቢዎች እንደሚታወቀው የቀረርቶ ዜማ ከፍ ባለ ድምፅ የሚቀርብ ነው። የዚህ ጥናት መረጃ በተሰበሰበት አካባቢ በተለይ በራያና ቆቦ ዙሪያዎች ባሉት የገጠር አካባቢዎች ቀረርቶ የሚጀመርበት ሁኔታ ከሌለው የክልሉ አካባቢ የተለየ ነው። ይህ የተለየ ሁኔታ የሚስተዋለው ሰርግ ላይ በሚከወንበት ጊዜ ነው። ይኸውም ለማቅራራት የሚነሳው ወይም የሚፈልግው ግለሰብ ዋናውን ቀረርቶ ከማሰማቱ በፊት እንደ መግቢያ በሚያገለግል መንገድ ዜማና ግጥም ይደረድራል። ታዳሚውም በመቀበል ቀረርቶ የሚጀመር መሆኑን ይረዳል፣ ጫጫታ ወይም ዘፈን ካለ ይቆማል። አጀማመሩም አንዲህ ነው፡-

አቅራሪ፡- አስፋው ገብናኔ
ታዳሚ፡- አሀሀ.....
አቅራሪ፡- አስፋው ገብናኔ
ታዳሚ፡- አሀሀ.....
አቅራሪ፡- የቅርጫ ስጋ
ታዳሚ፡- አሀሀ.....
አቅራሪ፡- ዝንብ የወረረው
ታዳሚ፡- አሀሀ.....
አቅራሪ፡-እንቢ አለ ሆዴ
ታዳሚ፡- አሀሀ.....
አቅራሪ፡- ክልብሽ እያለው
ታዳሚ፡- አሀሀ.....

አቅራሪ፡- እንደው ምናምን

ታዳሚ፡- አሀሀ.....

አቅራሪ፡- ሳልለው እኮ

ታዳሚ፡- አሀሀ.....

አቅራሪ፡- አገኘዋለሁ

ታዳሚ፡- አሀሀ.....

አቅራሪ፡- ሆዴ ታውኮ

አቅራሪ፡- ኤ....ኤ.....

ታዳሚ፡- ኤ....ኤ.....

ከተባለ በኋላ ዋናው ቀረርቶ ይጀመራል፡፡ አቅራሪዎች አንድ ወይም ሁለት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አቅራሪዎቹ ብዙ ጊዜ ከዳሱ መሀል ቁመው የዳሱን ቋሚዎች ወይም አግዳሚዎች በአንድ እጃቸው እያያዙ በመንጎራደድ ያቅራራሉ፡፡ በቅብብሎሽ ማለትም በተራ ሲያቅራሩ አቅራሪዎች በተወሰነ ርቀት ላይ ሆነው በተራ እየተደማመጡ ነው፡፡ ታዳሚው እያዳመጠ መደሰት፣ ማድነቅና፣ አንዳንዱም ሞቅ ሲለው፣ ግጥም ያቀብላል፡፡ አሁን አሁን ተከልክሎ ቀረ እንጂ ጥይትም ይተኮሳል፡፡ ከሰርግ ውጭ እርሻ ላይ፣ ማማ ላይ፣ ወዘተ. ሲከወን ከላይ የቀረበው መግቢያ አይኖርም፣ አቅራሪው ብቻውን ሆኖ ሊያቅራራ ስለሚችል መግቢያው አያስፈልገውም ማለት ነው፡፡ ሰርግ ላይ በሚደረግ የቀረርቶ ክዋኔ ላይ፣ በነገር የሚፈላለጉ ሰዎች በግጥም ሊተነኳኮሱ ይችላሉ፡፡ ቀረርቶ ከተጀመረ በኋላ የመግቢያውን ዜማ የመድገም ሁኔታ አይታይም፡፡ ምናልባት ከተደገመ፣ የዘፈን ጨዋታ ሲዘፈን ቆይቶ እንደገና ወደ ቀረርቶ ለመሸጋገር ሲፈልግ ይሆናል እንጅ፣ እንደ ባህላዊ ዘፈኖች ወይም ጭፈራዎች የሚደጋገም አንድ አይነት ስንኝ፣ ሀረግ የለውም ማለት ይቻላል፡፡ የመደጋገም ሁኔታ የሚታይ ከሆነ አቅራሪው በሚደረድረው ግጥም ውስጥ ብቻ የሚከሰት ይሆናል፡፡

5.2. የአማርኛ ቃልግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች

ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች ቃልግጥም የሚከወንባቸው አጋጣሚዎችና ቦታዎች ዋና ዋና የሚባሉት አንደኛ፣ ሰርግና ተያያዥ ሁኔታዎች ሁለተኛ፣ አመት በአላት ሶስተኛ፣ የሥራ ተግባራትና አካባቢዎች አራተኛ፣ የመዝናኛ ቤቶች ወይም መጠጥ ቤቶች ናቸው፡፡ ስለ እያንዳንዳቸው ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ እንመለከታለን፡፡ ገለፃው መስክ ላይ መረጃ

የተሰበሰበባቸውን አጋጣሚዎች ብቻ ሳይሆን ቃልግጥም ይከወንባቸዋል ተብለው የሚታወቁትንም የሚመለከት ነው።

5.2.1 ሰርግ

በተለይ በገጠር አካባቢ ሰርግ የሚደገሰው፣ በማሳ ላይ ያለ አዝመራ ተሰብስቦ ካበቃ በኋላ ነው። የድግሱ መጠን ከወቅቱ አዝመራ ጋር ይያያዛል፣ ብዙ ምርት ከተገኘ ድግሱ በሰፊው ይሆናል። እንደሚጠራው እንግዳ ብዛት ተገምቶ ጠላ ይጠመቃል፣ ጠጅ ይጠጣል፣ ፍሪዳ ይታረዳል። በሰርግ ጊዜ የሚከወኑት ባህላዊ ዘፈኖች፣ ጭፈራዎችና ቀረርቶ ናቸው።

በሰርጉ ሰሞን በሙሽራይቱ ቤተሰቦች ቤት፣ የሙሽራይቱ ሚዜዎችና ጓደኞቿ ማታ ማታ እየተሰበሰቡ የባህል ዘፈኖች እየዘፈኑ ያመሻሉ። ሙሽራው ሲገባና ሲወጣም ሚዜዎችና ቤተዘመድ ይዘፍናሉ። ይህ የሚሆነው ከዳሱ ውጪ ባለ ቦታ ላይ ነው፣ ዳሱ ውስጥ ደግሞ እድምተኛው ወይም እንግዳው ሲበላና ሲጠጣ ባህላዊ ተጫዋቾች (አዝማሪና አረሆ) ከእንግዶች መካከል የሚያውቋቸውን ሰዎች በስም እየጠቀሱ በማሞገስ ይዘፍናሉ፣ ገንዘብ ይሸለማሉ። ሙሽራው ራቅ ካለ አካባቢ ተነስቶ የመጣ ከሆነ ከሙሽራይቱ ቤተሰቦች ዳስ፣ ሚዜዎቹ እየዘፈኑ፣ እያቅራሩ ያድራሉ እንጂ አይተኙም።

የወንድ ሚዜዎች ጭፈራ የሚጨፍሩት ከሙሽራው ቤት ተነስተው እስከ ሙሽራይቱ ቤት እስከሚደርሱ ድረስ ባለው ቦታና ጊዜ ነው። በተለይ ከወንድ ቤት ሲወጡና ወደ ሴቷ ቤት አካባቢ እስኪጠጉ ድረስ ጭፈራው አይቋረጥም። ሙሽራው ሙሽራይቱን ይዞ ጫጉላ ቤት ከገባ በኋላ የተወሰኑ ሚዜዎች ወደ ሙሽራይቱ ቤተሰብ የምስራች ለመንገር ይሄዱና የምስራቹን ካበሰሩ በኋላ ከቤተ ዘመድ ጋር እየዘፈኑ ይውላሉ። ከዚህ በኋላ የሙሽራው ሚዜዎች ሁሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ የሚሰበሰቡት ሙሽራው ከጫጉላ ቤት በሚወጣበት ጊዜ ነው።

ሙሽራው ለአንድ ወር ያህል ተጨጉሎ ሲወጣ ሚዜዎቹ ይሰበሰቡና ሌሊት ወንዝ ወዳለበት ሄደው ገላቸውን ታጥበው፣ ልብሳቸውም አጥበው እየጨፈሩ ይመለሳሉ። በገበያ ቀን ከረፋድ ጀምሮ ገባያውን እየዞሩ ሚዜዎቹ ይጨፍራሉ፣ ከሰዓት በኋላ መጠጥ ቤት ገብተው ይዘፍናሉ። ከሰርግ ጋር የተያያዘው የክዋኔ ሁኔታና አጋጣሚ ከሞላ ጎደል ይህ ነው።

5.2..2 አመት በአላት ወይም ሀይማኖታዊ በአላት

በሃይማኖታዊ በዓላት ጊዜ ወጣት ወንዶችና ጎልማሶች እንዲሁም ወጣት ሴቶችና እናቶች ሃይማኖታዊ በዓሉን ለማጀብ የሚያሰሟቸው ልዩ ልዩ ዘፈኖች ይኖራሉ። ወጣት ሴቶችና እናቶች በእለቱ የሚከበረውን ታቦት ስም እየጠሩ የውዳሴና የሙገሳ ግጥሞች ይደረድራሉ። በተለይ በጥምቀትና በአስተርዮ ማርያም በዓላት ጊዜ ሴቶች የታቦት ማጀቢያ ዜማዎች ይዘፍናሉ። እነዚህና የመሳሰሉት ሃይማኖታዊ አመት በዓላት በሚከበሩበት አካባቢዎች የሚገኙ ወጣት ወንዶችና ጎልማሶች የሚያስሟቸው ጭፈራዎች ባብዛኛው ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ሳይሆኑ፣ የተለመዱት ባህላዊ ጭፈራዎች ናቸው። ባህላዊ ጭፈራዎቹ ከላይ በተለገፀው ስልት የሚከወኑት የጭፈራ አይነቶች የሚቀርቡ ናቸው። ለምሳሌ፣ የቅዱስ ዮሐንስ (የዘመን መለወጫ) በአል ሲከበር የአካባቢው ወጣቶችና ጎልማሶች ወደ ወንዝ ሄደው ንጋት ላይ ገላቸውን ይታጠባሉ። ገላቸውን ለመታጠብ ሲሄዱና ታጥበው ሲመለሱ ባህላዊ ጭፈራ ይጨፍራሉ። ለቡሄ ጅራፍ ለመጋረፍ ሲመጡና፣ ሲጋረፉ ሲጫወቱ ውለው አንዱ ሲያሸንፍ አሸናፊ ቡድን ባህላዊ ጭፈራ ይጨፍራል። እንደ ባህል እስፖርት እየተቆጠረ ያለው የትግል ጨዋታ (ውድድር) ተጫውተው ሲጨርሱ፣ ወጣቶች ወደ የመጡበት አካባቢ እየጨፈሩ ይመለሳሉ። እነዚህ ሁሉ ለባህላዊ ጭፈራ የመከወኛ አጋጣሚዎች ናቸው።

በሰሜን ወሎ አካባቢዎች በድምቀት የሚከበሩት አመት በአላት የጥምቀትና የአስተርዮ ማርያም ናቸው። አስተርዮ፣ የማሪያም ቤተክርስቲያን ባለበት አካባቢ የሚከበር ነው። የጥምቀት በአል በቆቦ፣ በወልዲያ፣ በሮቢት፣ በጎብየ እና በሌሎቹ የሰሜን ወሎ ወረዳዎች በድምቀት ይከበራል። በነዚህ አካባቢዎች ወጣቶችና ጎልማሶች በባህላዊ ጭፈራና በሆታ፣ ወጣት ሴቶችና እናቶች በሃይማኖታዊ ዘፈኖችና በባህላዊ ዘፈኖች አመት በአሉን ያጅባሉ፣ ያደምቃሉ። ምንም እንኳ አመት በአሉ ሃይማኖታዊ ቢሆንም በበአሉ ላይ የሚከወኑት ጭፈራዎች ባህላዊ ናቸው። በጭፈራው ውስጥ ሃይማኖታዊ በአሉን የሚመለከት ይዘት ያላቸው ግጥሞች በጣም ጥቂት ናቸው። ይህ ወንዶችን የሚመለከት ሲሆን ሴቶች ግንታቦታቱ ወጥተው እስቲገቡ ድረስ የሚያሰሟቸው ዘፈኖች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ናቸው።

5.2..3 የስራ አካባቢዎች

በሰሜን ወሎ አካባቢዎች አርሶ አደሩ የግብርና ስራውን የሚያከናውነው በጋራ ወይም በተናጠል ነው። በተናጠል ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ እርሻ፣ ወፍ ጥበቃና ከብት ጥበቃ ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ ከብቻ ይልቅ በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ ያመዝናል።

በጋራ ከሚሰሩባችው መንገዶች መካከል ወንፈል፣ ደቦ ወይም ጅጌ (ቆቦ አካባቢ “ጅጋ” ነው እሚባለው) ናቸው፣ ወንፈል የሚባለው ወንዶች ተመራርጠው በዙር ተራ የአረም ወይም የአጨዳ ስራ የሚሰሩበት መንገድ ነው። ደቦ ወይም ጅጌ ግን አቅም የሌላቸውን ሰዎች ለመርዳት በጋራ የሚደረግ የድጋፍ ሥራ ነው። ስራው ብዙ ጊዜ እርሻ፤ አጨዳና ቆረጣ ላይ ብቻ የሚደረግ ነው። ስለዚህ ሰዎች በደቦ ወይም ወንፈል የግብርና ተግባራትን ሲያከናውኑ በስራ ላይ እያሉ ድካምን የሚያስረሳ ዘፈን ይዘፍናሉ፤ ስራ ጨርሰው ወደ ቤት ሲመለሱ ባህላዊ ጭፋሪ ይጨፍራሉ።

ብዙ ጊዜ እንደሚታመነው ከበድ ከበድ ያሉ የግብርና ስራዎች ሴትን ልጅ ለአደጋ ያጋልጣሉ ስለሚባል ስራዎቹ የሚከናወኑት በወንዶች ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ በራያ አካባቢ ከብቶችን በጓደና ወይም በዱር መጠበቅ የወንድ ልጅ ተግባር ነው፣ ላሞችን ማለብ፣ እርሻ ማረስ፣ አጨዳ ማጨድ፣ የወንዶች ነው። የሴቶች ድጋፍ የሚታየው በአረም፣ ነዶ በማንሳት፣ ቅርጫት መሸከም፣ ወዘተ. ላይ ነው። እነዚህንና የመሳሰሉት ተግባራት ወንዶች በሚከናውኑበት ወቅት ባህላዊ ዘፈኖች፣ ቀረርቶዎችን እና ጭፈራዎችን ሊከወኑ ይችላሉ። ሴቶችም ለብቻቸው ሲያርሙ፣ እንጨት ሲሰብሩ፣ ወዘተ. ባህላዊ ዘፈኖችን ያንጎራጉራሉ፣ ይዘፍናሉ።

5.2 .4 የመዝናኛ ቦታዎች

የመዝናኛ ቦታዎች ተብለው የሚጠቀሱት የገጠሩ ማህበረሰብ ቀን የግብርና ተግባሩን ሲያከናውን ውሎ ማታ ላይ ለድካሙ መርሻ፣ ለሰውነቱ ማፍታቻ የሚሆነውን ተስማሚ መጠጥ (ጠላ፣ ጠጅ) ገዝቶ የሚጠጣባቸውን የመጠጥ ቤቶች ነው። እነዚህ ቦታዎች ስራ ላይ የዋሉ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ አቅሙን ፍላጎቱ ያላቸው ግለሰቦች አብረው እየጠጡ የሚጫወቱባቸውና የሚዝናኑባቸው ናቸው። በተለይ “ታዋቂ” የሚባሉት የመጠጥ ቤቶች ባህላዊ ተጫዋቾች / አዝማሪና አረሆ) አዘውትረው የሚጫቱባቸው ቦታዎች ናቸው። አልፎ አልፎ ከጫጉላ ቤት የወጡ ሙሽሮችና ሚዜዎች፣ ወይም ከአመት በአላት ከበራ በኋላ አብረው ለመጫወት የሚፈልጉ ጓደኞችና ግለሰቦች በእንደነዚህ አይነት የመጠጥ ቤቶች ተሰብስበው ባህላዊ ዘፈኖችን እየዘፈኑ ሊጫወቱና ሊዝናኑ ይችላሉ። ወደየአካባቢያቸው ሲመለሱ ደግሞ እየጨፈሩ ይሄዳሉ። በተለምዶ በመጠጥ ቤቶች ተዘወትሮ የሚሰማው ጨዋታ (ዘፈን) የባህላዊ ተጫዋቾች ማሲንቆና ዜማ ነው። ለመዝናናት የሚፈልጉ ግለሰቦችም ቢሆኑ

እሚገቡበት መጠጥ ቤት የትኛው ተጫዋች አዘውትሮ እንደሚጫወት አጣርተው በመለየት ይሆናል።

ምዕራፍ ስድስት፡- ምደባና ትንተና

6.1 ምደባ

በስነቃል የጥናት ሂደት ውስጥ ከሚታዩ ተግባራት አንዱ ምደባ ነው:: ምደባ የሚደረገው የተሰበሰበ መረጃ ሲኖር ነው:: ይህ የተሰበሰበ መረጃ ምደባ ከተደረገበት በኋላ ለትንተና ዝግጁ ይሆናል ማለት ነው:: ስለምደባ የተለያዩ የስነቃል ተመራማሪዎች የተለያዩ አስተያየቶችንና ምክር አዘል ሀሳቦችን ያቀርባሉ:: ስለምደባ ብርሃኑ (1995፣ 18-19) ሲገልጹ፣

> ምደባ ማለት ማዋገን ሲሆን ... ቃሉ በነገሮች መካከል ያለ ተመሳሳይነትንና /similarity/ ልዩነትን /difference / መፈለግን ያመለክታል ... በማዋገን ሂደት ውስጥ የሚደረገውም ሁሉን አቀፍ መስፈርት በመጠቀም መለየት፣ ማመሳሰል፣ ነጥሎ ማውጣት፣ ማቀናጀትና ለምድቡ ስያሜ መስጠት፣ እንደሆነና ... ምደባ /ማዋገን/ እንደ አንድ አካዳሚያዊ እሳቤ የልዩነቶችና የተመሳስሎዎች ጥምረት ነው::.. ነገሮችን በአምሳያ የማቀናጀት፣ የማደራጀት፣ የመጠቅለል ... ተግባር ነው:: ... ነገሮችን በልዩነት የመከፋፈል ወይም በሴማው በሴማው ማደራጀትና ስርአት የማስያዝ ተግባር ነው... ይላሉ፡፡

የምደባን አስቸጋሪነትና ውስብስብነትን ካሳዩት የስነቃል ተመራማሪዎች መካከል Okepwho አንዱ ናቸው:: ዘፈኖችና መዝሙሮች በሚለው ንኡስ ምዕራፍ ላይ በጣም ታዋቂ የሚባሉ የአውሮፓና የአሜሪካ ምሁራን እንደሚመክሩት ምንም አይነት የምደባ ስርአት ተጠቅመን የአንድን ህዝብ ስነቃል ስንመደብ የግድ መሰረት ማድረግ ያለብን ማህበረሰቡ ራሱ በልማድ የሰጠውን /ያበጀውን/ ስርአት መሆን እንዳለበት (Okepwho፣ 1992፣ 127-130) ሲገልጹ፣

> ... በነባሩ ላይ ብቻ ተመስርተን አስተያየትና ውሳኔ በምናደርግበት ጊዜ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዳናይ ሊያደርገንና ሊያስቸግረን ይችላል:: በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወኑ ስነቃሎችን ልዩ ልዩ መመዘኛዎች ተጠቅመን ለመከፋፈል ስንነሳ ነገሩ ቀላል ይመስላል:: ነገር ግን በተግባር ሲታይ አስቸጋሪ ነው:: በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ስነቃላዊ ቅርጽ በመመደብ ተግባር ውስጥ ያ ማህበረሰብ እውቅና በሰጠው ላይ ብቻ ከተወሰንን እንጨነቃለን:: ... ስነቃሉን በርዕሰ ጉዳይ፣ በማጀቢያ መሳሪያ አይነት፣ በአዘፋፈን ስልት፣ በከዋኙ ማንነት፣ በከዋኔው አጋጣሚ፣ ወዘተ. መነሻ አድርገን ብንመድብ

> የምናገኘው ውጤት አጥጋቢ አይሆንም፣... ዘፈኑን በዘፋኙና በአዘፋፈን ስልቱ እንለይ ብንል መመዘኛው ብዙም ጠቃሚ አይሆንም፡፡ ... የምደባው ተግባር ትርጉም እንዲሰጥ ከተፈለገ በቃልግጥሙ ላይ መሰረት ማድረግ እንጅ አካባቢያዊ መመዘኛዎችን ብቻ የሙጥኝ ማለት ብዙም ጥቅም የለውም:: ጭብጣዊ ዘይን በማለዘብ የስነቃሉን መሰረታዊ ጭብጥ ወይም ትኩረት በመመርመር መመደብ እንችላለን፡፡

ቃልግጥም በተለያየ መንገድ ወይም ስልት ሊከወን ይቻላል:: ለምሳሌ የስነቃሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰባዊ ቡድን፣ የሚዘፈነውን፣ የሚጨፈረውን፣ የሚያቅራራውን፣ የሚያንጎራጉረውን፣ ወዘተ. ግጥም ለማወቅና ለመለየት ብዙም አይቸገርም:: የዚህ ጥናት አካባቢ በሆነው ማህበረሰብ ዘንድ ‹‹ጃሎ በል›› ሲል ‹‹አቅራራ›› እንደማለት ነው:: ‹‹ሆ በል›› ሲል ደግሞ በተለያየ ስልት ጨፍር ማለት ነው:: ‹‹ዝፈን›› በሚልም ጊዜ እንዲሁ በተለያየዩ የዜማ ስልቶች መዝፈንን፣ መጫዎትን፣ የሚጋብዝ ነው:: የቀረርቶው፣ የጭፈራው፣ የዘፈኑ፣ ወዘተ. አቀራረብና ስልት የተለያየ ቢሆንም በግጥሞቹ የሚንፀባረቀው ግን፣ የማህበረሰቡ ማህበራዊ ህይወት፣ ስነልቦናዊ ጭንቀት ወይም ደስታ፣ ፓለቲካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣ ወዘተ. ናቸው:: እነዚህ ቀያዊ ስያሜዎች በአካባቢው የሚታወቁ ቢሆኑም፣ እነሱን ብቻ መሰረት አድርጎ ምደባ ማድረግ በተግባር ሲታይ የሚያስቸግር ይመስላል::

የአማርኛ ቃልግጥምን ለመመደብ የተለያዩ መስፈርቶችን መጠቀም እንደሚቻል ብርሃኑ (1995፣ 31-32) ያስረዳሉ:: አንደኛው፤ቀያዊ ስያሜዎችን መሰረት በማድረግ የባህሉ ባለቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ስያሜዎች መነሻ አድርጎ ቃልግጥሞቹን መመደብ ይቻላል፣ የሚል ሲሆን፣...ሌላው ደግሞ፣ ጭብጥን መሰረት አድርጎ መመደብ ነው:: በዚህም፣ የፍቅር፣ የፖለቲካ፣ የሀይማኖት፣ የሀዘን፣ ወዘተ. ግጥሞች እያሉ መመደብ ነው:: የክዋኔ መቼቶችን መሰረት አድርጎ መመደብም ይቻላል፡፡ ስነቃሉ የሚከወንባቸውን የበአላት አጋጣሚዎች፣ እንደ የገና በአል፣ የመስቀል በአል፣ የጥምቀት በአል፣ ወዘተ. እያሉ መመደብ አንድ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል ነው::

ከዚህ በላይ ለማየት እንደተሞከረው የስነቃል በአጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ የቃልግጥም ምደባ፣ አንድ ወጥ በሆነ መስፈርት መመደብ አስቸጋሪ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: ከዚህ በመነሳት ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመወጣት እያንዳንዱ ተመራማሪ በየባህሉ የሚያገኛቸውን ስነቃሎች ወይም ቃልግጥሞች በልዩ ልዩ መንገድ እያደራጀ መመደብ እንደሚችል የሚያመላክት ነው::

ለማዋገን የሚጥርበት መንገድና የሚያገኘው ውጤት ግን የመረጃውን አብዛኛውን ክፍል ወይም ሁሉንም ስብስብ የሚያጠቃልል ባይሆንም፣ ምድቡ ለተፈለገው የትንተና ተግባር የሚበቃና የጥናቱን አላማ ማሳየት የሚችል መሆን አለበት፡፡

ይህ ጥናት የተሰበሰበውን መረጃ ለመመደብ የተከተለው ዘዴ ይዘትን መሰረት አድርጎ፣ በእያንዳንዱ መንቶ ወይም አርኬ ውስጥ ያለውን ሀሳብ በመመርመር፣ ለማስተላለፍ የታሰበውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ነው:: መረጃው ሲሰበሰብ አንዳንዶቹ ቃልግጥሞች በባህላዊ የክዋኔ አጋጣሚዎች ላይ ስለነበር የግጥሞቹን መንፈስ እና ሀሳብ ለመያዝ አስቸጋሪ አልነበረም:: ከዚህ በታች በሚታየው ምደባ ውስጥ እንደሚስተዋለው፣ በተቻለ መጠን በመረጃ ሰብሳቢው እና በመረጃ ሰጭዎች አማካኝነት እያንዳንዱ መንቶ ወይም አርኬ ያስተላልፋል ተብሎ የተገመተውን መልእክት በመረዳት፣ በየምድቡ ለቅሞ ለማደራጀት ተችሏል:: በመሆኑም፣ በጭፈራና በቀረርቶ መልክ ሲከወኑ በቴፕ የተቀዱትን፣ በቃለ መጠይቅ ከተለያዩ ሰዎች በወረቀትና በማስታወሻ ደብተር እየተጻፉ የተሰበሰቡትን እና የተጠራቀሙትን ቃልግጥሞች፣ በስምንት ዋና ዋና ምድብ ተመድቧል፡፡

ዋናውን ምደባ ለማከናወን ይቻል ዘንድ በመረጃ መሰብሰብ ሂደት ላይ የተገኘውን ቃልግጥም እየደጋገሙ በማንበብ በእያንዳንዱ መንቶ ወይም አርኬ ውስጥ ጎልቶ የሚንፀባረቀውን ሀሳብ በየመንቶው ወይም በየአርኬው ፊት በአጭር በአጭሩ መጻፍና ሀሳቡን መረዳት አንዱ ተግባር ነበር:: በዚህም እያንዳንዱ መንቶ ወይም አርኬ ያስተላልፋል ተብሎ ከተገመተው መልክት አንፃር የሙገሳ፣ የትችት፣ የፍቅር፣ የጥላቻ፣ ወዘተ. እየተባለ በየምድቡ እንዲካተት ሆኗል:: በዚህ አይነት ሁኔታ ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸውን መንቶዎች እና አርኬዎች አንድ ላይ በማደራጀት ለምድቡ አንድ አጠቃላይ ስያሜ በመስጠት፣ በስሩ ደግሞ ሌሎች ንዑሳን ሀሳቦችን የሚወክሉ ስያሜዎችን ለማበጀት ጥረት ተደርጓል፡፡የተሰበሰበው መረጃ ሲመደብ ስምንት ዋና ዋና ምድቦች ሆኗል:: በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ የተለያየ ብዛት ያላቸው መንቶዎችና አርኬዎች አሉ:: በዋናው ምድብ ስርም ሌሎች ንዑሳን ምድቦች አሉ::

6.2 ትንተና እና ትርጎማ

ትንተና ማለት በተሰበሰበው መረጃ ላይ በመነሳት ማብራሪያ የመስጠት፣ ፍች የመፈለግ፣ ትርጉም የመስጠት፣ ተግባር ነው:: ትርጎማም እንዲሁ መረጃው የቀረበበትን ቋንቋና ይዘት መሰረት አድርጎ፣ ከባህልና ከልምድ ጋር እያዛመዱ፣ በአንደምታ ጭምር፣ ማብራራት፣

ማፍታታት፣ ወዘተ ይሆናል:: ስለዚህ፣ ትንተና ትርጎማ ተያያዥነት አላቸው ማለት ነው:: Abrams (1981፣ 84) እንደሚሉት፣‹‹*ትርጎማ በጠባቡ ሲታይ አንድን የስነ ፅሁፍ ስራ የቋንቋውን ትርጉም በመተንተን በመልሶ መግለፅ፣ በአንድምታ፣ ... የትርጉም ዘዬዎች ሀሳቡን ግልፅ ማድረግ ነው* :: ብዙ ጊዜ ትኩረቱ ለመረዳት አሻሚና ዘይቤያዊ በሆኑ ምንባቦች ላይ ነው:: በሰፊው ሲታይ ደግሞ መተርጎም ማለት አንድን የስነ ፅሁፍ ስራ፣ ጠቅላላ ፍች ግልፅ ማድረግ ነው::...››

6.2.1 የሙገሳና የውደሳ ቃልግጥሞች

እነዚህ የሙገሳ የውዳሳ ቃልግጥሞች የማህበረሰቡን የመኖሪያ አካባቢዎች፣ የአርሶ አደሩን ተግባርና ውሎ፣ በማህበራዊ ባህላዊ ግንኙነት ወቅት የማህበረሰቡ አባላት የሆኑትን ግለሰቦች፣ እንዲሁም በአርሶ አደሩ ህይወት ውስጥ እንደ ትልቅ ፀጋና ሀብት የሚቆጠሩትን እንስሳት በማሞገስ፣ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ፣ ህይወትና ማህበራዊ ግንኙነት፣ ለማሳየት የሚችሉ ናቸው:: በተለይ ቆቦ ዙሪያ ያሉትን የገጠር አካባቢዎች ከግለሰቦች ጋር እያዛመዱ ማሞገስ የተለመደ ይመስላል:: ጎበዙን ገበሬ ከበሬው ጋር አዛምዶ ማሞገስ፣ ሃብታሞች፣ ጀግኖች፣ ወዘተ. የኖሩባቸውን አካባቢዎች ሰዎቹንና አካባቢውን እያነሱ ማሞገስ፣ በቃልግጥሞቹ ውስጥ ታይቷል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ የሙገሳ ቃልግጥሞቹ ሴቶችንና ወንዶችን፣ በአንድ ወቅት በህይወት የነበሩና ብዙ ሰው በስም ለይቶ የሚያውቃቸውን ሰዎች በማስታወስ የተገጠሙ ናቸው:: የአርሶ አደሩ ህይወት በእርሻና በእንስሳት እርባታ ላይ በዋናነት የተመሰረተ በመሆኑ በሚያገኘው የምርት መጠን በሚኖረው የእንስሳት ብዛት ይወደሳል፣ ይሞገሳል:: እንስሳቱም አብረው ይወደሳሉ ይሞገሳሉ:: በመሆኑም በሬና ላሞችን የሚያወድሱ ቃልግጥሞች በምድቡ ተካትተዋል:: እነዚህ የሙገሳና የውዳሴ ቃልግጥሞች የሚከወኑት በተለያየ ቦታ ነው:: ገበሬው በማሳ ላይ የእርሻ ስራውን ሲያከናውን /ሲያርስ/ በሬውን እያሞገሰ ይዘፍናል፣ ያቅራራል:: እረኛው በከብት ጥበቃ ላሞቹን በዘፈን ያሞግሳል፣ ስለላሞቹ ይዘፍናል ያቅራራል:: እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ማለትም በሰርግ፣ በመዝናኛ ቦታዎች፣ በቀረርቶ፣ በዘፈን፣ በጭፈራ፣ የሙገሳ ቃልግጥሞች ይከወናሉ፣ ይነገራሉ፣ ይዘፈናሉ:: በዚህ የሙገሳ ምድብ ውስጥ ወደ 98 ያህል መንቶዎችና አርኬዎች ቀርበዋል::

ማሞገስ አዎንታዊ በሆነ መንገድ አንድን ነገር ከፍ ከፍ ማደረግ፣ የዚያን ነገር መልካም ባህሪና ገጽታ አጉልቶ ማሳየት ነው:: ማወደስም እንዲሁ የአንድን ነገር ጥሩ ገጽታና ባህሪ

በቃላት አማካኝነት መግለጽ ማለት ነው። ስለዚህ ማሞገስና ማወደስ ተመሳሳይነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው። Okpewho (1992፣ 142) እንደሚሉት “ሙገሳ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከመውደድ ጋር ተመሳሳይ ነው። የሙገሳ መነሻው ከበጎ አስተያየትና ስሜት የሚመነጭ ሲሆን፣ ይህ በጎ አስተያየትና ስሜት መሰረት የሚያደርገው ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር ከሚኖረን አድናቆት ላይ ነው። ብዙ ጊዜ የሚታወቀው የሙገሳ አይነት ሌሎችን ከማሞገስ ላይ ሆኖ፣ በተለይ ታዋቂና ዝነኛ የሆኑትን የማህበረሰቡ አባላት ከማሞገስ ከማወደስ ላይ ያተኩራል” ይላሉ። በመሆኑም፣ በዚህ ክፍል የምንተነትናቸው ቃልግጥሞች በተለያየ አጋጣሚና ሁኔታ፣ የአካባቢውን መልክአ ምድራዊ ተፈጥሮን ከሰዎች ጋር፣ ወንዶችንና ሴቶችን ለብቻ፣ በሬውንና ገበሬውን በአንድ ላይ፣ ወዘተ. የሚያሞግሱትንና የሚያወድሱትን ይሆናል።

6.2.1.1 አካባቢንና ሰዎችን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ

አርኬ 1-ክልካይ አባ መሬ
የክልካይ ካቦ አገር
የቸኮለ አሊ አገር
ያነ ማዶ፣ ተሮ በሩ
ያነ ማዶ፣ ዞብል በሩ
እንኳን ሰው ቁሞበት ያስፈራል ግራሩ
አርኬ 2-ያነ ማዶ፣ ዞብል በሩ
የቀኛማይ አገር
የአሰፋ ሀይሉ አገር
ጌጡ ጎበዜ አገር
የነምስጋን አገር፣ የነምስጋን አገር፣ የነምስጋን በላይ
ያነ በሩ፣ ተሮ በሩ፣ ዞብል በሩ
እንኳን ሰው ቁሞበት ያስፈራል ግራሩ

እነዚህን አርኬዎች እየገጠመ ሲያቅራራ የነበረው አዲሱ አሰፋ የሚባል የዞብል ተወላጅ ነው። ጥር 18/2006 ዓ.ም ከምስጋን ጌጡ ልጅ (ጥሩ ሴት ምስጋን) ሰርግ ላይ መስከኛው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ተገኝቶ በከሴት ቀድቶታል። በአርኬዎቹ ውስጥ ‹‹ያነ ማዶ ተሮ በሩ ዞብል በሩ›› የሚሉት ሀረጎች ተደጋግመው ተነግረዋል። የድግግሞሹ አላማ አካባቢውን (ዞብልን) ለይቶ ለማመልከት ነው። ይህንን አላማ በሁለተኛው አርኬ አምስተኛው መስመር

ላይ ባለው ስንኝ በግልፅ ማስተዋል ይቻላል:: ገጣሚው የነምስጋን አገር የሚለውን ከደገመ በኋላ የአባቱን ስም ይጠራል:: ይህ ሰው (ምስጋን በላይ) በዞብል አካባቢ ስሙ የተጠራ ነው:: እሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሰዎች በአርኬዎቹ ስማቸው ተጠቅሷል:: አካባቢው የጀግና አገር እንደነበር በማስታወስ የአካባቢውን ግርማ ሞገስ (አስፈሪነት) ያሳያል:: ወደ ኋላ በምድብ 3.3 ላይ እንደምናየው ምስጋን በላይ በአካባቢው እንደ ጀግና የሚጠራ ሰው ነው:: ጀግንነት መገለጫው ብዙ ቢሆንም እሱ ከከብት እርባታ (ባለ ብዙ ከብት በመሆኑ) እና ከአፋር ጋር በነበረው ግንኙነት ተለይቶ ይታወቃል:: በእርባታ ህይወቱ፣ እድገቱና ኑሮው አፋር አካባቢ ነበር ማለት ይቻላል:: ዞብልና የአፋር አካባቢዎች ኩታ ገጠም በመሆናቸው አልፎ አልፎ ግጭነት ይፈጠራል:: አካባቢው ለአደጋ የተጋለጠ ስለሆነ፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው የምስጋን በላይ ጀግንነት የሚንፀባረቀው::

ምንም እንኳ ገጣሚው በታሪካዊ ዳራው ውስጥ ስለ ተጠቀሰው የዞብል አካባቢ ታሪክ፣ የቀረቡትን ሀሳቦች ያውቃቸዋል ተብሎ ባይታሰብም፣ እያሞገሰው ያለውን ግለሰብ ታሪክ በውል የተገነዘበ ይመስላል:: ገጣሚው ትውልዱም፣ እድገቱም፣ ኑሮውም፣ እዚያው ዞብል ስለሆነ፣ አካባቢውን ሲያሞግስ ከታዳሚዎቹ መካከል የዞብል ሰዎችም ስለነበሩ፣ አካባቢው ሲጠራ የነበራቸው ስሜት ከፍተኛ ነበር:: ‹‹ኑማ››፣ ‹‹አጅብ ነው››፣ ‹‹አየ ያነ ጋሪያ፣ መገን ዞብል›› የመሳሰሉትን ቃላት በስሜት ከመናገር በተጨማሪ፣ መሳሪያ ለመተኮስ እስከ መገላገል ደርሰዋል::

‹‹ያነ ማደ›› የሚለውን ሀረግ ደጋግሞ በመጠቀሙ ታዳሚውንም ሆነ አድማጩን በአይነ ህሊና ወደ አካባቢው እንዲሄድና አካባቢውን እንዲያስታውስ በአገሩ የነበሩትን ታዋቂ ሰዎች እያስታወሰ እንዲያስባቸው ቀስቅሷል:: ከዋኔው ቆቦ ውስጥ መሆኑም ገጣሚው ሀረጉን እየደጋገመ ሲጠራ ታዳሚውን በሀሳብ ወደ ስፍራው ያመላለሰዋል ማለት ነው::

ከታች ባሉት አርኬ 3 እና 4 ይኸው አካባቢ እንደገና ሲነሳ እናያለን:: ዞብል ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ሆኖ የአካባቢው ማህበረሰብ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ተግባሮች በየአካባቢዎቹ አንጻር ተጠቅሶ የታያል::

አርኬ 3- ወይ እንደ ቆቦ ልይ
ነጭ ጤፍ ማሽላ ወስደው ኻላቀኑ
ወይ እንደ ጨርጨር ልይ

ቡሻ ኽመዳፊያው ጊደር ኻላበሉ
ወይ እንደ ዞብል ልይ
እገጭ እገው ሲል ልብን ኻላመኑ
አሁን ወይት ይገኛል ወተት ሞይዘር ቢሉ

አርኬ 4- እኔ ለቆቦ ልይ፣ እኔ ለዞብል ልይ
እኔ ለጉራ ልይ፣ እኔ ለወርቁ ልይ
እኔ ለአማያ ልይ፤ እኔ ለጮቢ ልይ
እኔ ለበዋ ልይ፣ በዋ ንጉስ ጋሌ፣አያስማኝ ክፉ
እኔ ለራያ ልይ፣ አያሰማኝ ክፉ
እንኳንስ ልጆቹ፣ አይቆረጥ ዛፉ
እንኳን ጎበዞቹ፣ አይነካ ዛፉ

አርኬ 3፣ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች የተገለፀበት ነው:: አንደኛው የምርት አይነት ሁለተኛው እርባታ፣ ሶስተኛው ጀግንነት ናቸው:: ቆቦ ዙሪያውን ሜዳና ለእርሻ አመች ስለሆነ አርሶ አደሩ ብዙ ምርት ማምረት የሚችልበት አካባቢ ነበር:: ብዙ ባመረተ ቁጥር፣ ለገባያ የሚያቀርበው እህል ከፍተኛ ይሆናል:: በጎተራ የተሰበሰበው ነጭ ጤፍ፣ በጉድጓድ የሞላው ማሽላ፣ ገበሬው የሚቀጥለውን የምርት ሁኔታ እያገናዘበ ለገባያ ያቀርባል:: ማቅናት ማለት መሸጥ ማለት ነው:: የሚሸጠው እህል ሌሎች ወጪዎችን ከመሸፈን አልፎ ለወተት የሚሆኑ ላሞችን፣ ለራስ መጠበቂያ የሚሆን መሳሪያ (ሞይዘር) እስከ መግዛት የሚያስችል ነው:: ይህንን ሁኔታ ነው ገጣሚው ‹‹...ነጭ ጤፍና ማሽላ ካልሸጡ የሚፈልጉትን ማግኘት አይቻልም›› በሚል ስለ አካባቢው ማህበረሰብ የገለፀው:: ቆቦን ለብቻ ሲጠቅስ በዙሪያው ያሉት የገጠር አካባቢ ሰዎችም እህል የሚያቀኑት ሰኞና አርቢት ገባያዎች (ቆቦ ውስጥ) ስለሆነ ሁሉንም የሚያጠቃልል ነው:: የአካባቢው አርሶ አደር ብዙ በማምረት የሚታወቅ ስለነበረ ገጣሚው ይህንን መነሻ አድርጎ ነው ሀሳቡን የሚጀምረው:: አርሶ አደሩ እህሉን የሚሸጠው ለከተማው ነዋሪና ከሌላ አካባቢ እየመጡ እህል ለሚሸምቱ የእህል ነጋዴዎች እንደነበር አጥኚው ያስታውሳል::

ገጣሚው ‹‹ወይ እንደ ጨርጨር ልይ / ቡሻ ኽመዳፊያው ጊደር ኻላበሉ›› ሲል በንዳና የከብት እርባታን የሚመለከት ነው:: ቡሻ፣ ለራያ አካባቢዎች አጎራባች የሆነ የአፋር አካባቢ ነው:: ከዋጃ ምስራቃዊ አካባቢዎች ባሉት ቀበሌዎች አንስቶ እስከ ጨርጨር (አዘቦ ውስጥ) ድረስ ያለው የአካባቢው አርሶ አደር (ሁሉም ሳይሆን ብዙ ከብት ያላቸው ሰዎች) ከብቶቻቸውን ወደ አፋር አካባቢዎች ይዘው በመሄድ፣ እዚያው በረት አጥረው፣ ጎጆ ሰርተው ይጠብቃሉ::

እንደሚታወቀው የአፋር አካባቢ አይታረስም ነበር:: ከሌላ አካባቢ መጥቶ ከብት ለማርባት የሚፈልግ ሰው አንድ አካባቢ ሰፍሮ፣ መሳሪያ ይዞ፣ በጋራ በመጠበቅ ወይም ከአንድ የአፋር ጎሳ አባል ከሆነ ሰው ጋር ጓደኝነት (በአፋርኛ ከታይሳ ይባላል) በመመስረት ነበር:: በጋራ የመጠበቅ ሁኔታ አስቸጋሪ ነው:: ቀን በዱር፣ ሌሊት በሰፈር መሳሪያውን ይዞ በንቃት መጠበቅ አለበት:: በዱር የሚቀማ ወይም በረት የሚከፍት ጠላት ሲመጣ መከላከልና መጋደል ይኖራል:: ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ነው ገጣሚው አጉልቶ በማሳየት የአካባቢውን ማህበረሰብ አባላትና አካባቢውን የሚያሞግሰው:: ‹‹ወይ እንደ ዞብል ልይ፣ እገጭ እገው ሲል፣ ልብን ኻላመኑ›› የሚለው ስንኝ የሚያመለክተው ችግር ሲፈጠር፣ ወረራ ሲመጣ፣ ቀየ ሲደፈር፣ ተረጋግቶ መቋቋምና መከላከልን ነው:: እገጭ እገው ማለት በዚህ አገባብ የመሳሪያ ድምፅ ሲሰማ፣ ተኩስ መለዋወጥ ሲጀመር፣ እንደ ማለት ነው:: በመጀመሪያዎቹ አርኬዎች ለማሳየት እንደ ተሞከረው የዞብል አካባቢ ከአፋር ጋር ለሚደረግ ድንገተኛ ግጭት ተጋላጭ ነው:: ይህንን ለማስታወስና ለማሰብ ይመስላል አካባቢውንና ሰውን እያቀራረበ ያሞገሰው::

የዚህ አርኬ ዋና ሀሳቦች፣ ወተትና ሞይዘር ናቸው:: ወተት በዘይቤ የቀረበ ነው፣ ላሞችን ያመልክታል:: ሞይዘር የመሳሪያ ስም ነው:: እህል ተሸጦ ከብትና መሳሪያ ይገዛል:: ከብቶቹ ወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ ከመሳሪያው መከበርና መፈራት ይገኛሉ:: ከብቶች ሲረቡ ወይፈንና ጊደር እየተሸጠ መሳሪያ ይገዛ ነበር:: ስለዚህ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ የእርሻ ምርቱ፣ የእንስሳት እርባታው፣ እና የመሳሪያ ፍላጎቱ በአርኬው ውስጥ ተገልጧል ማለት ነው:: ማምረት እና ማርባት ለመገሳና ለውደሳ የሚያበቁ ስለሆነ የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሰው፣ በዚህ አስተሳሰብና ተግባር እንዲታነፅ የሚያነሳሳ መልክት ያለው ነው::

አርኬ 4 የተገጠመበት ምክንያትና መቼቱ በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ነው:: ቀኑ የጥምቀት ወይም የአስተርዮ በአል የሚከበርበት አጋጣሚ ሲሆን፤ ቦታው ቆቦ ውስጥ ነው:: ገጣሚው አካባቢውንና የአካባቢውን ማህበረሰብ አባላት ከማሞገስ አልፎ፣ ስለደህንነታቸው የሚቆረቆር ነው:: ከሰዎቹ ህይወት ባልተናነሰ፤ስለ አካባቢው ደን የተቃውሞ ስሜቱን ገልጿል:: ታሪኩ እንዲህ ነው፤ በአሉን ለማክበር በየአካባቢው ወደ ቆቦ ከተማ የመጡት ወጣቶች በቡድን በቡድን ሆነው፣ በጭፈራ ታቦቱን ያጅባሉ:: የበአሉ አከባበር ካለቀ በኋላ ወጣቶቹ ጭፈራቸውን ይቀጥላሉ:: በወቅቱ በአሉን በክብር ለማጀብ የመጡት የመንግስት ወታደሮች ወጣቶቹ ወደ ግጭት እንዳይገቡ ይጠብቁ ነበር:: ጭፈራው ቀጥሎ ወደ አስራ አንድ ሰአት አካባቢ ደረሰ:: በዚህ ጊዜ ከወታደሮቹ አንዱ ጭፈራውን ለማስቆም አስቦ ጥይት መተኮስ ይጀምራል::

ወጣቶቹ ከመበተን ይልቅ መቀሬቆስ (መጋጨት) ስለጀመሩ ወደ ሰማይ መተኮሱን ትቶ ወጣቶቹ ላይ ይተኩሳል:: ወደ ሰባት የሚሆኑ ወጣቶች በጥይት ተመትተው ወደቁ::

የገጣሚው ሙገሳ በውስጡ ብሶትና ተቃውሞ ያለበት ነው:: አጀማመሩ ‹‹እኔ ለቆቦ ልይ፣ እኔ ለዞብል ልይ ...›› እያለ ነው:: በዚህ አርኬና በሌሎችም አርኬዎች ወይም መንቶዎች ውስጥ ‹‹ልይ›› ማለት ልጅ ማለት ነው:: በአገባቡ፤ ቆቦ፣ ዞብል፣ በዋ፣ ንጉስ-ጋሌ፣ ወዘተ. ተወልዶ ያደገ ልጅ ማለት ነው:: ገጣሚው የተቃውሞ ሀሳቡንና ሀዘኑን ለማስተላለፍ የሞከረው በዘዴ ነው:: በጥይት የተመቱት ወጣቶች የበዋ፣ የንጉስ-ጋሌና የጮቢ ወጣቶች ናቸው:: የግጥሙ መነሻ ሀሳብ ይኸ ሆኖ ሳለ፣ ገጣሚው በቀጥታ ከነዚህ አካባቢዎች አልጀመረም:: ይህም በወቅቱ ከነበረው የመንግስት አካላት እንግልት አድኖታል::[14] ገጣሚው በአካባቢው ስለሚኖረው ማህበረሰብ ያለውን ስሜት ለመግለፅ የሞከረው የወጣቶቹን እልቂት ብቻ ሳይሆን የአካባውን ደን ጭፍጨፋ በመቃወም ጭምር ነው::

በዚህ አርኬ ውስጥ የድግግሞሹ ብልሀት የተለየ ነው:: ድግግሞሹ በመነሻና በመድረሻ ሀረጎች ውስጥ ሆኖ፣ በነዚህ ሀረጎች መነሻና መድረሻ ቦታዎች ላይ ድግግሞሹ ቀርቧል:: በተደጋገሙት ቃላት መካከል ባለው ቦታ ራያ ቆቦ ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎች ተጠቅሰዋል:: በመሆኑም ተናጋሪው በነዚህ አካባቢዎች ለሚኖሩት ወጣቶች ከፍተኛ ፍቅር ያለው መሆኑን «እኔ» በሚለው ደጋግሞ ተናግሯል:: የተቃውሞ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጠቆመው «አያሰማኝ ክፉ» እና «እንኳን ጎበዞቹ አይቆረጥ ዛፍ» በሚሉት አገላለጾች ነው:: ተቃውሞው ድንገተኛና ስሜትን መቆጣጠር የማያስችል በመሆኑ፣ በአድማጩ ወይም በአንባቢው ስሜት ውስጥ የመንፈስ መረበሽንና መደናገጥን ይፈጥራል::

አካባቢውንና የአካባቢውን ሰዎች የሚያሞግሱት ግጥሞች እነዚህ ብቻ አይደሉም:: ከዚህ በታች ያሉት መንቶዎችና አርኬዎች፣ ቆቦንና አካባቢውን፣ እንዲሁም አፋር ውስጥ ስለነበሩ ባላባት ሰዎች የሚያስታውሱ ናቸው::

አርኬ.5.እንደምነው ቆቦ ያባ ዘበን አገር
እንዴነህ በሉልኝ በቀኑ ቁጥር

[14] ይህንን ሁኔታ ያጫወቱኝ የገጣሚው ተገኘ ጉባይ የእህት ልጅ የሆነችው ወ/ሮ አበሩ ፈንታና ባሏ አቶ አበራ ወራሽ ናቸው::

ያባ ዘበን አገር የፈንታ ኩቢን
ቆቦን ያቀና ሰው ለምን ይኮነናል
እንኳን የሰው ልጁ ውሻው ጤፍ ይበላል
መንቶ 6.በጣሳ ቢሸመት ስስት የለብሽ
ያባ ዘበን አገር ቆቦ እንደምነሽ
አርኬ 7.እውር ያለመሪ የሚሄድብሽ
አረቂ በጠርሙስ ጠጅ በበርሌ የሚጠጣብሽ
ያባ ዘበን አገር ቆቦ እንደምነሽ
አርኬ 8.ባገኝ እበላለሁ ባጣም ጦሜን ልደር
ልሂድ መንደፈራ ከሶስቱ አበበ አገር
ልሂድ መንደፈራ ከአበበው ዶረት
ሲሆን ማር ይገኛል ያለዚያ ወተት
አርኬ 9.አረንጓዴ ለብሶ ይደንሳል አሳ
ምነው የቀድሞውን አናነሳም እሳ
የቡጢ ባቤ አገር እንዴነሽ ፎቂሳ
መንቶ 10.ጠመንጃው ሞይዘር ነው ጥይቱ ዘጠና
የዳውድ አደም አገር እንዴነሽ አላይና
አርኬ 11.አትንኩት ያመኛል ጎመጅ አፋፉን
አትንኩት ያመኛልኝ አራቱ ጋሪያን
ዲህኒኖየ ባቤ፣ቃሲሞየ ባቤ፣የቆዩበትን
የከፋው ወንድ ልጅ አሳዳጊውን
በረጅሙ ከርፎ የሚያጠጣውን

ከአምስት እስከ ሰባት ባሉት ግጥሞች በስም የተጠቀሱት የአካባቢው ባላባት ፈንታ ኩቢ የሚባሉት የአባ ቦና ኩቢ ልጅ ናቸው::[15] እሳቸውም ቢሆኑ በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት በግዞት ወደ ሀረር ተወስደው፣ በኋላ በማይጨው ጦርነት ጊዜ፣ ከሀረር ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው በጦርነቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል ይባላል:: ገጣሚው ቀደም ሲል የነበሩትን የአካባቢ ባለባቶች በማስታወስ፣ የአሁኑን ትውልድ ወደኋላ በሀሳብ በመመለስ፣ ከቀደሙት ትውልዶች

[15]ታሪኩን ለማወቅ ለሚሹ የራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄና የማዕከላዊ መንግስታት ምላሽ .../2005/ የሚለውን መፅሀፍ ማንበብ ይቻላል::

ጋር በታሪክ ለማስተሳሰር የፈለገ ይመስላል:: አካባቢውን የሚያወድሰው በመሬቱ አቀማመጥ፣ በመሬቱ ምርታማነትና ለኑሮ ተስማሚነት፣ የኑሮ ችግር ያልነበረበት መሆኑን በመግለፅ ነው:: ገጣሚው በታሪክ ወደኋላ ተመልሶ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ያስታውሳል:: በአጼ ዮሀንስና በአጼ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት በአካባቢው የነበረው ሁኔታ በግጭት የተሞላ ነበር:: አፄ ዮሀንስ የፈንታ ኩቢን አባት ወግተዋቸዋል ይባላል:: አፄ ሀይለ ስላሴም፤ ፈንታ ኩቢን ወደ ሀረር አግዘዋቸዋል:: ይህንን ሁኔታ ለመግለፅ ሳይሆን አይቀርም ገጣሚው ‹‹ቆቦን ያቀና ሰው ለምን ይኮነናል›› በማለት የገለፀው::

ሰምንተኛው አርኬ ቆቦ ወረዳ ከሚገኙት የገጠር መንደሮች አንዱን መሰረት ያደረገ ነው:: መንደሩ የሚገኘው ከቆቦ በስተሰሜን ምስራቅ፣ በግምት ስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው:: በዚህ መንደር ከሚኖሩት ሰዎች መካከል ሶስት ግለሰቦች (መኩሸዎች) ተጠቅሰዋል:: እነሱም አበበ ጣውነህ፣ አበበ መለሰና፣ አበበ በርሄ ይባሉ የነበሩ ናቸው:: እነዚህ አባቶች በቀንድ ከብት ብዛት፣ በግብርና ስራና ምርት፣ እንዲሁም፣ በለጋስነትና በደግነት በአካባቢው የሚታወቁ ነበሩ:: የሚታለበው ላም፣ የሚጠመደው በሬ፣ የሚመረተው እህል፣ ብዙ ነበር:: የግጥሙ መነሻ ስንኝ ሀሳቡ ትክክለ እንዳልሆነ የምንረዳው በሁለተኛው ስንኝ የሰዎቹን ስም ተጠቅሶ ስናገኝ ነው:: የአካባቢው ማህበረሰብ ሰዎቹን በትክክል ስለሚያውቃቸው የገጣሚውን ሀሳብ አይቃወመውም:: ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው የመጨረሻው ስንኝ የቀረበበት ሁኔታ ነው:: ማርና ወተተ በአርሶ አደሩ ህይወት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ስለሆኑ ማር ቢጠፋ ወተት እንደማይታጣ ይገልፃል:: ገጣሚው ይህንን መሰረት አድርጎ ነው አካባቢው የሃብታሞች አገር፣ መብል መጠጡ፣ ማርና ወተቱ እንደልብ የሚገኝበት እንደነበር የገለፀው::

ከ 9 እስከ 11 ባሉት አርኬዎችና መንቶዎች ውስጥ፣ እስካሁን ከቀረቡት የሙገሳ ግጥሞች የተለየ ሀሳብ የተንፀባረቀባቸው ናቸው:: በግጥሞቹ ውስጥ የተጠቀሱት የሰውና የቦታ ስሞች የሚገኙት አሁን አፋር ክልል ውስጥ በተካተቱት የክልሉ የሰሜን ዞን አካባቢ ነው:: ቡጢ ባቤ፣ ዲህኒኔ ባቤ፣ ቃሲም ባቤ፣ ወንድማማቾች የአፋር ጎሳ አባለት ሲሆኑ፣ ቡጢ ባቤ የጎሳው መሪ የነበሩ ናቸው:: የእሳቸው ልጅ ደአራባ ቡጢ፣ የኢሰፓ አባል እንደነበር አጥኚው ያስታወሳል:: ዳውድ አደም፣ የነዚሁ ሰዎች የቅርብ ዘመድ ሲሆን፣ ‹‹ጥይት የማያስመታ›› መድሀኒት አለው እየተባለ የሚነገርለት ነበር:: ፎቂሳና አላይና የአካባቢ ስሞች ሲሆኑ እነዚህ የጎሳ አለቆችና ባላባቶች የኖሩባቸው ናቸው::

ገጣሚው የአፋር ባለባባቶችን በመጥቀስ አካባቢውንና ጎሳውን ያሞግሳል:: የሙገሳው መልክት የተንፀባረቀው በአስራ አንደኛው አርኬ የመጨረሻዎቹ ሁለት ስንኞች ነው:: ይኸውም አርኬ ሶስት ላይ እንደተጠቆመው በሁለቱ ራያዎች የሚኖረው ማህበረሰብ አባላት ከብቶቻቸውን ሳር የሚያበሉትና በጓዳና የሚያረቡት አፋር ውስጥ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ከመንግስት ወይም ከግለሰቦች ጋር የተጋጨና በህግ የሚፈለግ ሰው ሸፍቶ የሚደበቀው ብዙ ጊዜ አፋር ውስጥ ነው:: ‹‹ከርፎ›› ከእንጨት ተጠርቦ የተሰራ የወተት ማለቢያ ሲሆን፤ እስከ አምስት ሊትር ወተት ሊይዝ ይችላል:: ቀደም ሲል በነበረው ባህል አፋር አካባቢ ባሉ መንደሮች ሲታለፍ አረፍ ተብሎ ‹‹ዳጉ›› (መረጃ ከተለዋወጡ) በኋላ ለእንግዳው ወይም ለመንገደኛው የሚርብለት ወተት ነው:: ለዚህ ነው ገጣሚው ‹‹በረጅሙ ከርፎ የሚያጠጣውን›› በማለት የገለፀው:: አርኬ አስራ አንድ ላይ ያሉ የመነሻዎቹ ሁለት ስንኞች የተቃውሞ ስሜት የተንፀባረቁባቸው ናቸው:: ቦታዎቹ ከራያና ቆቦ ወረዳ ወጥተው ወደ አፋር ክልል የተካተቱ ናቸው:: ለራያ ከፊል አርብቶ አደር ሰዎች የማንደኛ አካባቢዎች ነበሩ:: እነዚህ ግጥሞች በአፋሩና በአካባቢው ማህበረሰበ መካከል የነበረውን ማህበራዊ ግንኙነት የሚያስረዱ ናቸው::

የድግግሞሹ አላማና ፋይዳ ተቃውሞን ማስተጋባትና ጩኸትን ማስማት ነው:: በዚህ አርኬ ውስጥ ድግግሞሹ የሚገኘው በስንኞቹ መነሻ ላይ «አትንኩት ያመኛል» የሚለው ሀረግ ሲሆን፣ በሶስቱ ተከታታይ ስንኞች የቀረበ ነው:: በነዚህ ስንኞች የመድረሻ ሀረጎች ላይ ከ1983 ዓ.ም በፊት በነበረው አስተዳደራዊ መዋቅር በሁለቱ ራያዎች ውስጥ የነበሩ አካባቢዎች በስም ተጠቅሰዋል:: እነሱም «አራቱ ጋሪያ» ና «ጎመጅ» የሚባሉት ናቸው:: እነዚህ አካባቢዎች አፋር ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ፣ አሁን ባለው አከላለል የአፈር ክልል አካባቢዎች ናቸው:: «በደና ለኮ»፣ «ቡታና መርፈታ» ደግሞ በትግራይ ክልል ለውጥ የተካተቱ ናቸው:: የተናጋሪው የተቃውሞ መነሻ ይኸ ነው ማለት ይቻላል:: በነዚህ በተጠቀሱት አካባቢዎችና በሌላው የራያ አካባቢ በሚኖረው ማህበረሰብ መካከል የቆየ ባህላዊና ማህበራዊ ግንኙነት ስለነበር፣ የአርኬው አላማ ይህን የቆየ ግንኙነት የሚያደናቅፍ የመሰለውን አስተዳደራዊ አወቃቀር መንቀፍና መቃወም ነው::በሁለቱ ራያዎች የሚገኙ አርቢ ገበሬዎች ጓደና የሚያጓድኑት አፋር ውስጥ ነው ማለት ይቻላል:: በተለይ የጓደናንና የእርባታን ህይወት በሚመለከት የሚከተለው አርኬ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል::

አርኬ 12. የዳሞቶ ሽታ፤

የእንቦሳ ጫጫታ የለመደ ልጅ

ቅቤ በገበታ የለወሰ ልጅ
አይሄድም ርቆ ይከፋ እንዲሁ እንጅ

አርኬው ምስል ከሳች ነው:: በባህሉ ውስጥ ላደገ ለኖረ ሰው፣ የሚያሸተው፣ የሚያዳምጠውና የሚቀምሰው ነገር በስሜት ህዋሳቱ ይገባል፡፡ ለአፍንጫው የሚሸተው ጠረን፣ ለጆሮው የሚሰማው ድምፅ፣ ለምላሱ የሚቀምሰው ጣዕም፣ በግጥሙ ውስጥ አለ:: ዳሞቶ የሳር አይነት ነው:: ከብቶች እሱን ሲበሉ ወተታቸውም ሆነ ትንፋሻቸው ደስ ይላል:: እንቦሳ ሳር መብላት ያልጀመረ ጥጃ ነው:: ቃሉ ለአንድ ጥጃ ሳይሆን ለብዙ ጥጆች መግለጫ ነው:: እንደ ጥቅል መጠሪያ የሚያገለግል ነው:: ለምሳሌ አንድ በረት ላም በሚለው ሀረግ ውስጥ ላም በነጠላ ነው የቀረበው:: የከብቶቹ ቁጥር የተለካው አንድ በረት በሚለው ነው:: እንዲሁም የእንቦሳ ጫጫታ (ተደጋጋሚ ጩኸት) በሚለው ሀረግ ውስጥ እንቦሳ ነጠላ ነው፣ ጫጫታ ከሚለው ጋር ግን ብዙ ጥጆች እንደሆኑ ያመለክታል:: የጫጫታው ምክንያት ለየብቻ የዋሉትና ለየብቻ ያደሩት፣ ላሞችና ጥጆች የመፈላለግ ነው:: ጥጆቹ ስለራባቸው ላሞቹ ጡታቸው ስለአጋተ (ወተት ስለሞላ) ለማጥባትና ለመጥባት ነው፡፡

‹‹ቅቤ በገበታ የለወሰ ልጅ›› የሚለው ስንኝ በጓደና ህይወት (ኑሮ) ውስጥ ከብት የሚጠብቁ እረኞች (አርቢዎች) እንጀራ በወጥ አያገኙም:: የዘወትር ምግባቸው ቂጣ (መንገሌ) በወተት ነው:: ወተት ገፍተው ቅቤ ሲያወጡ ከትኩስ መንገሌ ላይ ትኩስ ቅቤ ያደርጉና ይፈተፍቱታል:: ይህም ጨዋቃ ወይም ጨጨብሳ የሚባለው ነው:: ገጣሚው የእንሰሳቱን ጩኸት፣ ከጩኸታቸው ጋር አየሩን የሚቀላቀለው የእንሰሳት ትንፋሽ ላሞቹን ሲያጣባ (ወተት ሲያልብ) የወተቱ ሽታ፣ በቅቤ የተፈተፈተ ቂጣ በወተተ እያማጉ ሲበሉት ያለውን ጣዕም በአንባቢው ወይም በአድማጩ የስሜት ህዋሳት ውስጥ እንዲሰርፅ አድርጓል::

ሳር መብላት ያልጀመሩ እንቦሳዎች ሲጮኹ ትንፋሻቸውም ሆነ ድምፃቸው የደስታ ስሜት የሚሰጥ ነው:: እንቦሳ የማይጮህበትና የማይፈነጭልበት፣ ልጅ የማይጫወትበቅ ቀየ፣ ወይም ግቢ፣ እንደ ኦና ይቆጠራል:: በተለይ አካባቢው ብዙ ከብት የነበራቸው ሰዎች ወይም ግለሰቦች ይኖሩበት የነበረ ከሆነ አካባቢውን ለሚያውቀው ሰው የሚጭርበት ስሜት የተለየ ይሆናል:: የነበረውን እያስታወሰ ያዝናል:: የግጥሙ መሰረታዊ ሀሳብ ከእንሰሳት (ከከብቶች) ጋር ለሚኖር ማህበረሰብ የከብቶቹ ፍቅር ከፍተኛ ስለሆነ እነሱን ተለይቶ መኖር አይችልም ወይም አይፈልግም:: ችግር ቢመጣ ከነሱ ጋር አብሮ ይቸገራል፣ እንጂ ከነሱ መለየት የሞት ያህል ይከብደዋል:: ለአርብቶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የከብቶቹ ጠረንና ድምፅ

የደስታ ምንጩ ናቸው:: በተለይ ላሞች ለእንደዚህ አይነት ማህበረሰብ የብዙ ነገሮች ምንጭ ናቸው:: በግጥሙ ውስጥ ልጅ የሚለው ቃል በውክልና የቀረበ ነው ማለት ይቻላል:: ውክልናው ከእንሰሳት ጋር ለሚኖረው ማህበረሰብ ሆኖ፣ በተለይ በከብት ብዛትና የሚታወቁትን የማህበረሰቡን አባላት የሚያመለክት ነው:: ሁኔታው ‹‹ከቀየው የተነጠለ ከእርስቱ የተነቀለ›› ወይም ‹‹ከከብቶችና ከወተት የተለየ ዘላለም የደኸየ›› እንደማለት ይሆናል::

አካባቢንና ሰዎችን ከሚያሞግሱትና ከሚያወድሱት ቃልግጥሞች መካከል የሚከተሉት ሁለት አርኬዎች ለየት ባለመንገድ የቀረቡ ናቸው:: ለየት የሚያደርጋቸወ አንደኛው ድግግሞሹ ሲሆን፣ ሁለተኛው የድግግሞሹ ስልት ነው:: አንዱ በመነሻ ሁለተኛው በመድረሻ ላይ የታዩ ናቸው:: የመነሻው ድግግሞሽ ‹‹ዙረው ዙረው አለኝ...›› በማለት የቀረበው ሲሆን፤ ገጣሚው ያደገበትን ቀየና መንደር፣ ወንዙን፣ ተራራውን፣ ወዘተ. ለማየት መነሳሳቱንና መጓጓቱን የሚያመለክት ነው:: ዞሮ ለማየት የሚፈልጋቸው አካባቢዎች ሁሉም ራያ ውስጥ የሚገኙ ናቸው::

በቃልግጥም ውስጥ የመደጋገም ሁኔታ ስለሚታይ የድግሞሹን ፋይዳ መመርመርና መተንተን አስፈላጊ መሆኑን Okpewho (1992፤71-72) እንዲህ በማለት ዘርዝረው ያስረዳሉ::

> ድግግሞሽ አንዱና መሰረታዊ የስነቃል መለያ ገፅታ ነው::... በስነቃል ውስጥ ስነ ውበታዊና ተግባራዊ ጠቀሜታ (aesthetic and utilitarian valve) አለው:: ስለሆነም ድግግሞሽ የመሳብና የማሳመር ስሜት ይፈጠራል:: ... በመሰረታዊነት የቃላቱ፣ የሀገጋቱ፣ እና የስንኞቹ መደጋገም ለዘፈኑ ዜማዊ ጥራትና ውበት ይሰጡታል::...ድግግሞሽ ... ስነውበታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ትኩረት እንዲጣቸው ለሚሹ ነጥቦች አፅንኦት ለመስጠት ይረዳል:: ጥልቅ ከሆነ ጭንቀትና ፍርሀት ወይም ደስታ በመነጨ ሁኔታ፣ የመንፈስ መረበሽን ወይም የመደናገጥ ስሜትን ይፈጥራል::

ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን አርኬዎች እንመልከት::አርኬዎቹ በድግግሞሽ ስልት የተገነቡ ስለሆነ ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ ያጠናክራሉ ማለት ይቻላል::

አረኬ.13.ዙረው ዙረው አለኝ ቆቦ ሜዳውን
ዙረው ዙረው አልኝ ዞብል አፋፉን

ዙረው ዙረው አለኝ ቆባ ጠጣራን
ዙረው ዙረው አለኝ ቅልሻ በሩን
ዙረው ዙረው አለኝ፣ ራማና ቦረን፣ ራስ አሉላን
እንዴነህ በሉልኝ አርበት ጠበለትን
እንዴነህ በሉልኝ በዋ ንጉስ ጋሌን
እንዴነህ በሉልኝ ዴላና ብረይሊን
እንዴነህ በሉልኝ ወርቁ ጎራውን
ደህና ደህና ጎበዝ የቆየበትን
የቸገረ ጊዜ የማዋየውን

አርኬ 14.ዞባል በራ በሩን ብዞረው ብዞረው
አላይና ጎሊናን ብዞረው ብዞረው
ጠቢሳ መለኩሳን ብዞረው ብዞረው
ቡታና መርፈታን ብዞረው ብዞረው
ታቹን ጉባ ጋላን ብዞረው ብዞረው
ካቡ ብቻ ቀረ የማይናገረው
ቀየው ብቻ ቀረ የማይናገረው

በነዚህ አርኬዎች ውስጥ ያለው መደጋገም ለተለየ አላማ የቀረበ ይመስላል:: ይኸውም የተጠቀሱት አካባቢዎች ባዶ መሆናቸውን፣ ሰው አልባ መሆናቸውን፣ ማመልከት ነው:: ለገጣሚው ሰው ማለት ቀደም ሲል በአካባቢዎቹ ይኖሩ የነበሩት ጀግኖች፣ ጎበዞች፣ ሀብታሞ፣ ወዘተ. ናቸው :: በመሆኑም የመነሻው ድግግሞሽ ፋይዳ፣ ናፍቆትን ለመወጣት ወይም የናፈቁትን አካባቢ ለማየት መነሳሳትን፣ መጓጓትን የሚያመለክት ነው :: የሰው ልጅ በተለምዶ መጀመሪያ አገሬ የሚለው የተወለደበትን አካባቢ ነው:: ሌላው ሁሉ የሚመጣው ከዚህ በኋላ ነው :: የመጀመሪያው የሀገር ፍቅር ስሜት የሚጠነሰሰውም በተወለዱበት አካባቢ ነው ማለት ይቻላል :: ስለሆነም ‹‹እንዴነህ በሉልኝ ...›› የሚለው ሀረግ በናፍቆት ለማየት የተነሳሳለት አካባቢ በአንድ ባልታወቀ ምክንያት በአካል ተገኝቶ ለማየት እንዳልቻለና እንዳልተሳካለት የሚያመለክት ነው :: በአካል ባይገኝም በሌላ መንገድ መጠየቅ ፈልጓል ወይም የመረጠ ይመስላል :: ድግግሞሹ፣ ትውስታን እየቀሰቀሰ አካባቢው በአይነ ህሊና ለማየት ማስቻል ነው፡፡

ሶስተኛው ድግግሞሽ ‹‹ብዞረው ብዞረው›› የሚለው ሲሆን ይህም የገጣሚው ጥልቅ ሀዘንና ጩኸት የተሰማበትና የተንጸባረቀበት ነው :: ገጣሚው በአካል ተገኝቶ ለማየት የፈለገውን

አካባቢ እንደጓንለት ሆኖ አላገኘውም :: ያገኘው ባዶውን ባድማና ደረቅ ካብ ብቻ ነው:: ሁሉም ግዑዝና የማይናገሩ ናቸው :: መናገር ቢችሉ ቀደም ሲል የነበሩት ስመ-ጥር ሰዎች እነማን እንደነበሩ ይመስክሩ ነበር::

ከላይ ለመጥቀስ እንደ ተሞከረው የሶስተኛው ድግግሞሽ በመድረሻ ሀረጎቹ ላይ መሆኑ የድግግሞሹን ስልት ከሌሎቹ የተለየ እንዲሆን አስችሎታል :: በግጥሙ ውስጥ የቃላት ድግግሞሽ ብቻ ሳይሆን የድምጽ ድግግሞሽ እንዲሰማበት አድርጓል :: ብዞው ብዞረው በሚሉት ቃላት መድረሻ ላይ ካለው ሳድስ ፊደል ጋር ተደርቦ የሚሰማው ድምፅ /-ኡ/ ነው:: ይኸ ድምፅ በየሀረጎቹ አንጻር ሲቀመጥ /-ኡ-ኡ/ ይሆናል :: በዚህም የእሪታና የጩኸት መጀመሪያ መሆኑን ያመለክታል :: በሌላ በኩል የሰባቱን ስንኞች የመጨረሻ ድምጽ ወደ ጎን ብናስቀምጠው /-ኡ-ኡ-ኡ-ኡ-ኡ-ኡ-ኡ/ የሚል ነው :: ይኸ ደምፅ የእሪታና የድረሱልኝ ጥሪ ያስተጋባል :: በናፍቆት ለማየት የተጓጓለት አካባቢ ባዶ ኦና፣ የተወረረ፣ የጠፋ፣ እስቲመስል አጉልቶ ለማሳየት ችሏል :: በመሆኑም፣ ገጣሚው ጥልቅ ሀዘኑን አንፀባርቆበታል፣ ጭንቀቱን ተንፍሶበታል ማለት ይቻላል::

በሁለቱ ግጥሞች ውስጥ ድግግሞሹ በተለያየ መንገድ የቀረበ ነው:: አቀራቡ በሁለቱም አርኬዎች በመነሻና በመድረሻ ሆኖ፣ «ዙረው ዙረው አለኝ» የሚለው ሀረግ፣ ትንሽ ለወጥ ብሎ በመድረሻ ላይ «ብዞረው ብዞረው» በማለት ቀርቧል:: የመጀመሪያው ዙረው ዙረው አለኝ የሚለው፣ በከንቱ መናወዝን ማስረገጥ ነው:: በሁለቱም አርኬዎች ያሉት መደጋገሞች አላማቸው፣ በስም በተጠቀሱት አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ጀግኖች፣ ደጋግ ሰዎች፣ አሁን በህይወት የሌሉ፣ በተለያዩ ምክንያቶች ማለቃቸውንና አካባቢዎቹም ሰው አልባ፣ ኦና መሆናቸውን በማሳየት፣ በዚሁ ሰበብ የተፈጠረውን ፍርሀትና ጭንቀት ማስተጋባት ነው:: ለተናጋሪው፣ ሰው ማለት በደህናው ዘበን በአካባቢዎቹ ይኖሩ የነበሩት ጀግኖች፣ ሀብታሞችና ደጋግ ሰዎች ናቸው:: እሱ ያገኘው ግን፣ ደረቅ ካብና ባዶውን ባድማ ነው ::

በዚህ አርኬዎች ውስጥ የሚሰማው ሌላው ድግግሞሽ፣ የድምፅ መደጋገም ነው::«ብዞረው ብዞረው» በሚለው ድግግሞሽ ውሰጥ፣ በየቃላቱ መጨረሻ /-ኡ-ኡ/ የሚል ድምፅ ይሰማል:: በዚህም የጩኸትና የእሪታ ድምፅ እንዲሰማ አድርጓል ማለት ነው:: «ዙረው ዙረው አለኝ›› በሚለውም ያለው የድምፅ ድግግሞሽ /-አ-ኡ/ ተመሳሳይ ነው::እነዚህ ድምጾች የድረሱልኝ እሪታና ድምፅ ያስተጋባሉ ማለት ይቻላል:: በመሆኑም ድግግሞሹ የአካባቢዎቹን ባዶነት አጉልቶ ለማሳየት የቻለ ነው:: የተናጋሪውንም ጥልቅ ሀዘን በማንፀባረቅ ጭንቀቱን

ተንፍሶበታል፤ ወደ ሌላው አድማጭ ወይም አንባቢ አስተላልፎበታል ማለት ነው። በሁለቱም አርኬዎች ያሉት ድግግሞሾች በሀሳብ ይዛመዳሉ፣ በስሜትና በመልክት ይመሳሰላሉ። ሀሳባቸው አካባቢዎቹን ከነዋሪዎቹ ጋር አገናኝቶ ማስታወስ ነው። ስሜታቸው የቁጭት፣ የናፍቆት፣ የሀዘን ሲሆን፣ አላማቸው የትውልድ ክፍተት መፈጠሩን ማመልከት ነው ።

አርኬ 13 በሰውኛ ዘይቤ የቀረበ ነው ። መወያየትና ሰላምታ መለዋወጥ የሰው ልጅ ተግባራት ናቸው። ገጣሚው ‹‹የቸገረ ጊዜ (ችግር ሲፈጠር) የማዋየውን›› በማለት አካባቢዎቹን እንደሰው አድርጎ አቅርቧቸዋል። እንዴነህ በሉልኝ በሚለው ሀረግ ለአካባቢዎቹ ሰላምታ እንዲደርስለት ይወተውታል። አካባቢዎቹን እየጠራ ለነዋሪዎቹ ሰላምታ ያቀርባል። አካባቢዎቹ ከሱ ርቀው በመገኘታቸው ምክንያት ሌሎች ሰዎች ሰላምታ እንዲያቀርቡለት ይጠይቃል። ሰላምታው በሌላ ወገን አልፎ ነው ከአካባቢዎቹ ጋር ገጣሚውን በሀሳብ የሚገናኘውና ሰላምታ የሚለዋወጠው። ግጥሞቹ ከአርኬ አምስት እስከ አስራ አንድ ካሉት ግጥሞች ጋር በሀሳብ ይዛመዳሉ፣ በስሜትና በመልክት ይመሳሰላሉ፣ ማለት ይቻላል።

ከዚህ በላይ በቀረበው ትንተና ለማሳየት እንደተሞከረው አንዳንዶቹ ግጥሞች ከሙገሳና ከውደሳ በተጨማሪ በውስጣቸው የተቃውሞ ሀሳብ የተቀላቀለባቸው ናቸው። ተቃውሞው በፊት ለፊት የቀረበ ሳይሆን በረቀቀ፣ ባልታሰበና አሳቻ በሆነ ዘዴ ነው። የተቃውሞውን ሀሳብ ለመረዳት የቃል ግጥሞቹን መቼትና የመፈጠራቸውን ምክንያት ከአንዳንድ የአካባቢው ሁኔታዎች ጋር አዛምዶ መረዳትን የሚጠይቅ ነው።

የሰው ልጅ ይወለዳል፤ ያድጋል፤ ያረጃል፤ ይሞታል። ይህ ሂደት የማይለወጥና የማይቀር የተፈጥሮ ህግ ነው። በዚህ የተፈጥሮ ህግ ውስጥ የሰውልጅ የሚያልፍባቸው የህይወት እርከኖች አሉ። ከነዚህ መካከል አንዱ ጋብቻ ነው። ጋብቻ በሁለት ተቃራኒዎች ጾታዎች መካከል የሚመሰረት የአብሮ መኖር ስምምነት ነው። በማህበረሰባዊ መዋቅር የታችኛው መሰረት የሚጀመረው በሁለቱ ተጋቢዎች ነው። ከዚያ በኋላ ወደላይና ወደ ጎን በሚቆጠር የቤተሰብ ዝምድና ቤተሰብ ይፈጠራል።እንዲህ እያለ ወደ ማህበረሰብ ያድጋል ማለት ነው።

ስለሆነም ሰርግ፣ ወላጆች አለማቸውን የሚያዩበት፣ የሚደሰቱበት፣ የሚኮሩበት፣ ቤተሰብ የሚተዋወቅበት፣ የሚረዳዳበት አጋጣሚ ነው ። ሰርግ የተጋቢ ቤተሰቦች የሚወደስበት፣ የሚሞገስበት፣ አጋጣሚ የሚፈጠርበት ማህበረ- ባህላዊ አውድ ነው ። በተለይ በራያ አካባቢ የሰርግ ማህበራዊነት መገለጫው ተጋባዥ (የተጠራው እንግዳ) ከሚጥለው አደየር (ገንዘብ

መስጠት) ጀምሮ አጋዥ እስከሚጠምቀው ጠላ፣ ከዳስ ስራ እስከ አሳላፊነት ድረስ የሚደረገው መረዳዳትና ትብብር ሁሉ ነው :: አደየር ማለት የተጠራው እንደ አቅሙና እንደ ዝምድናው የሚሰጠው ገንዘብ ነው። የሚከተሉት የሙገሳና የውደሳ ግጥሞች ሰርግ ላይ ከሚነገሩት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው::

አርኬ 15 እኔን ደስ እሚለኝ[16]
እንደ ጥሩ ሴት አባት በሬ የሚነዳ
ባረባባ ድግስ አይሸኝም እንግዳ
ቅዱ እንደለ ውሎ ቅዱ እንዳለ ነጋ
አርኬ 16 ያነ ምስጋን ጌጡ
እሱ ሽጋ ማንቆርቆሪያው ሽጋ
ዳሱ ሽጋ ይች ሚስቱ ሽጋ
አሳላፊው ሽጋ
ቅዳ እንዳለ ውሎ ቅዳ እንዳለ ነጋ
መንቶ 17 እከሌ አባበሉ ጠንካረው ገበሬ
ደግሶ ይድራል በሶስት አመት ጥሬ
መንቶ 18 የሙሽሪት እናት ቁሚ ተጠየቂ
የጠመቅሽው ጠላ ጠጅ ነው አረቂ
መንቶ 19 እንደው መዳደሩን ዘብል ተዳዳር ጨርጨር ተዳዳር
እንደ ጥሩ ሴት አባት ዳሱን አሳምር
መንቶ 20 ረጅም ነው ዳሱ ሸንበቆም አይደርሰው
አባት የሰራውን ልጅም አያፈርሰው
መንቶ 21 ቢቀዳው ቢቀዳው አያልውም ድግሱ
የመቻሬን ሜዳ የመሰለው ዳሱ
መንቶ 22 የሙሽሪት አባት ደስ ይበልህ ደስ
ፈረስ ያስጋልባል ያሰረኸው ዳስ

[16] አርኬ 15፤ 16፤ እና መንቶ 19፤20ን የሰማኋቸው አዲሱ አሰፋ ሲያቅራራ ሲሆን፤ ሌሎቹን መርሳ ነው።

አርኬ 15 እና 16 እየተሞገሰና እየተወደሰ ያለው ዋናው ነገር፣ የድግሱ መጠንና የደጋሹ አቅም ነው:: ‹‹ባረባባ ድግስ አይሸኝም እንግዳ›› የሚለው ስንኝ የሚያመለክተው ይህንን ነው:: «... በሬ የሚነዳ » የሚለው ሀረግ በሁለት ፍች የገባ ይመስላል:: አንደኛው ጎበዝ ገበሬ ሲሆን፣ የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ከብት የሚነግድ መሆኑን ነው:: ግብርናው ብዙ ምርት እንዲያገኝ የሚያስችለው ሲሆን ንግዱ ደግሞ ትርፍ ገንዘብ ያስገኛል:: ሁለቱን አጣምሮ የሚሰራ ስለሆነ፣ ድግሱ የሞላ የተረፈ ይሆናል:: «ያረባባ ድግስ» ማለት ለእንግዳ የሚቀርበው መብልና መጠጥ በጥራቱም ሆነ በብዛቱ አነስተኛ የሆነ ነው:: የመጠጡና የምግቡ ጥራት የሚሞገስበት ወይም የሚተችበት ሁኔታ ነው:: የድግሱ ጥራት የቤተሰብን ስም በበጎ ያስነሳል፤ ያስሞግሳል:: «ቅዳ እንዳለ ውሎ ቅዳ እንዳለ ነጋ» የሚለው ስንኝ ድግሱ ሙሉ መሆኑን የሚያመለክት ነው::

የጠላው ጥራት የሚነፃፀረው ከጠጅና ከአረቂ ነው:: የሙሽራይቱ እናት በጠመቀችው የጠላ ጥራት ስትወደስ አባት ደግሞ በግብርና ሙያው ይወደሳል:: ጎበዝ ገበሬ በያመቱ ብዙ ምርት ስለሚያመርት ከአመት ወደ አመት የሚሸጋገረው፣ ችግር ሳይገጥመው ነው:: የማሽላ ምርት በጉድጓድ ስለሚቀመጥ ለተወሰኑ አመታት ሳይበላሽ መቆየት ይችላል:: ዘመኑ በተከታታይ ምርት የተገኘበት ከሆነ የከረመውን ማሽላ አውጥቶ ይሸጠዋል ወይም ይደግስበታል:: ይህንን ለመግለፅ ነው፤ደግሶ ይድራል በሶስት አመት ጥሬ በማለት አጋኖ ያቀረበው::

እንደሚታወቀው ባብዛኛው የኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች ድንኳን አይታወቅም ነበር:: ለሰርግ፣ ለክርስትና፣ ለሀዘን፣ ወዘተ. ዳስ ይሰራል:: የዳሱ ስፋት እንደሚፈለገው አገልግሎትና እንደሚታደመው ሰው ይወሰናል:: ስለዳሱ የቀረቡት ሙገሳዎች የዳሱን ሰፋት አጉልቶ በሚያሳይ መንገድ የቀረቡ ናቸው:: ዳሱ ከመቻሬ ሜዳ ጋር ተነፃፅሮ ቀርቧል:: ወልዲያ አካባቢ ሜዳማ ከሚባሉት አካባቢዎች አንዱ መቻሬ ነው:: ማሽላ በብዛት የሚመረትበት አካባቢ ነበር:: ገጣሚው የዳሱን ስፋት ከመቻሬ ሜዳና ለፈረስ ግልቢያ ከሚያመቹ ሰፊ ሜዳ ጋር አነፃፅሮ በማቅረቡ የዳሱን ስፋትና ትልቅነት በዚያውም የድግሱን መጠን ማሳየት ችሏል:: ስለዳሱም ሆነ ስለድግሱ የተነገሩት ግጥሞች ዞሮ ዞሮ የሰርጉን ባለቤቶች ከፍ አድርጎ ለማሳየት ያለሙ ናቸው:: ‹‹ዳሱን አሳምር›› የሚለው ሀረግ በገባበት ፍች ዳስ ማስጌጥን ሳይሆን መብልና መጠጡ፣ አስተናጋጁ /አሳላፊው/፣ ወዘተ. በጥሩ ሁኔታ መሟላትን ነው:: ድግሱ ሞልቶ ሲተርፍ ቤተሰቡም ሆነ ታዳሚው ይደሰታል ባህላዊ ጨዋታ /ዘፈኑ ቀረርቶው/ ይደምቃል:: ቤተዘመድ ይወደሳል፤ ይሞገሳል፤ ሌሎች ሰዎችም ይወደሳሉ፤ ይሞገሳሉ::

6.2.1.2 በሬንና ገበሬን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ

በምዕራፍ ሁለት ለማሳየት እንደተሞከረው ቆላማዎቹ የሰሜን ወሎ የግብርናን ስራ ከእንስሳት እርባታ ጋር የሚያካሂድ ማህበረሰብ ያለበት አካባቢ ነው። የኢኮኖሚ መሰረቱ መሬቱ እና እንስሳቱ ናቸው። ህይወቱ ከመሬቱና ከእንስሳቱ ከሚያገኘው ጥቅም ላይ የተመሰረተ ነው። የግብርና ስራ አድካሚ በመሆኑ በሬና ገበሬ ይፈተኑበታል። መሬቱን ገምሶ፣ አይሞ፣ እና ሰልሶ፣ በሚያዝያ ማሽላውን፣ በሀምሌ ጤፉን ይዘራ ነበር። ሚያዝያ ካለፈበት ወይም አፍላው ካመለጠ ማሽላ የማምረት ሁኔታ ይቀራል። በሀምሌ ጤፍ ካልዘሩ የዝናቡ ወራት አጭር ከሆነ ለፍሬ አይደርስም። እነዚህና ሌሎች በልምድ ያካበታቸውን እውቀቶች ተጠቅሞ ገበሬው ስራውን ያከናውናል። በማሳው ላይ ሲያርስ በሬውንና ራሱን ከሚያወድስባቸው ቃልግጥሞች በተጨማሪ በሚዝናናበትና በአንዳንድ ባህላዊ ግንኙነቶች በሬውንና እራሱን ያሞግሳል ወይም ሌሎች ያሞግሱታል። የሚከተሉት ግጥሞች ይህንን ያሳያሉ።

መንቶ 23 በሬው አመለኛ ያገኘ አይጠምደው
ጧት የተጠመደ ማታ እሚፈታው
መንቶ 24 ፋሚሌው ሸጋ ነው የሚተኛበቱ
በሬው ጆቢራ ነው ጆቢራ በብርቱ
አርኬ 25 አለው ሸጋ በሬ ቀዳም የማይፈራ
አለው ወደል ግመል ሸኸም የማይፈራ
የለኝ ብሎ አይለምን አለኝ ብሎ አይኮራ
ሲጫወት ይውላል ከእኩዮቹ ጋራ
መንቶ 26 ኧረ በሬው ንጉስ፤ኧረ በሬው ሌዶ፤ እንሀድ ቦይ ለቦይ
ኻረባው ደጃማይ እኛ አንሻልም ወይ
መንቶ 27 ኸጠጅ ቤት ገብቶ ያለው ቅጅ ቅጅ
የበሬውን ጫንቃ ተማምኖ ነው እንጅ

በነዚህ ግጥሞች በሬው ብቻ ሳይሆን የሚሞገሰው በበሬው ጉልበት የሚመካው ገበሬ ጭምር ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በአጠቃላይ የጭነት አገልግሎት የሚሰጠው ግመልም አብሮ ይወደሳል። ቀደም ሲል አህያ ይሰጠው የነበረውን አገልግሎት አሁን አሁን ግመል አየሰጠ ነው። ግመል ለከፊል አርሶ አደሩም ሆነ ለአርብቶ አደሩ እንደ ሀብት መገለጫ ይቆጠራል።

የነዚህ ግጥሞች ዋና ሀሳብ የበሬውን ሀያልነት ብርቱነት አይደክሜነት ማረጋገጥ ነው። የብርቱነቱና የአይደከሜነቱ መገለጫ ከጧት እስከ ማታ መታረሱ ነው። ጆቢራ ማለት በተራ ፍቸው ቁመቱ ረጅም አጋዱ ሰፊ ቀንዱ ረጃጅም የሆነ ማለት ነው። በዘይቤ ግን ሀይለኛ ጉልበተኛ እንደማለት ነው። ጆቢራ በብርቱ ሲል ከጧት እስከማታ ተጠምዶ እየታረሰ ቢውል ማለትም ሌላ አጋዥ በሬ ሳይለወጥለት ፈፅሞ የማይደክም ማለት ነው። ‹‹... ቀዳም የማይፈራ›› የሚለው ሀረግ እንዲሁ የበሬውን ሃያልነት የሚያመለክት ነው። ቀዳም ማለት ገበሬው ሲያርስ ወይም ሲያርምና ሲያጭድ በተወሰነ ርቀት ለክቶ የሚሰራበት ርቀት ነው። ቀዳሙ ረጅም ሲሆን በሬዎቹና ሰዎቹ ይጎዳሉ ወይም ስራው አይሰልጥም ተብሎ ይታሰባል። ረጅም ቀዳም የሚስብ በሬ ጉልበተኛ ነው። ለዚህ ነው ‹‹በሬው ጆቢራ ነው ጆቢራ በብርቱ›› የሚለው ስንኝ ‹‹ቀዳም የማይፈራ›› በሚለው ሀረግ እንደገና የሚነሳው ::

በመንቶ 26 ገጣሚው ለበሬው ማዕረግ እና ውበት ይሰጠዋል። በፖለቲካም ይሁን በአስተዳደር እርከን ንጉስ የሁሉም የበላይ ነው። ሁሉን አድራጊ ፈጣሪ ተደርጎ ይቆጠራል። ‹‹ሌዶ›› አፋር ውስጥ የሚገኝ የዛፍ ስም ነው። ከዚህ ዛፍ በትር ይቆረጣል። በትሩ አባጣ ጎባጣ የሌለው ቀጥ ያለና እንደ ቀርቀሀ ከዘራ ጠንካራ ነው። የበሬውን ውበት ያነፃፀረው ከሌዶ በትር ጋር ነው። ፍችውም ሽጋ፣ የሚምር፣ ወዘተ. ... እንደማለት ነው። «እንህድ ቦይ ለቦይ» ማለት ጠንክረን እንረስ ማለት ነው። «ቦይ» የተባለው መሬቱ ሲታረስ የሚወጣው መስመር /ፈር/ ነው። በረጅም ማረሻ በሰፋፊ ድግር መሬቱን ሲገምሰው የሚወጣው ፈር፣ ልክ ለመስኖ እንደተቀደደ ቦይ ሰፊ ይሆናል። ቦይ ከፈር ሰፋ ስለሚል ነው ከሱ ጋር ያመሳሰለው። ያንን ያህል ስፋት እየቀደዱ ማረስ ከባድ ነው። የግጥሙ ሀሳብ በፊውዳል ኢትዮጵያ ዘመን ከፍተኛ የስልጣን እርከን ከነበረው ደጃዝማች ከሚለው ሹመት ጋር አነፃፅሮ ነው። «እኔና አንተ ከአንድ ደጃዝማች እንበልጣለን» በማለት ያሞካሸዋል። ገበሬው ሀይለኛ በሬ ስላው፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለበሬው በኩራት ይናገራል፤ የፊለገውን ያረጋል። ለዚህ መተማመኛው ደግሞ የበሬው ትከሻ /ጫንቃ/ ስለሆነ፣ እንደልቡ ይዝናናል፤ ይናገራል፤ ማለት ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ግጥሞች ማስተዋል እንደሚቻለው የግጥሞቹ ዋና ሀሳብ በሬውን ከማሞገስ ላይ ያተኮረ ቢሆንም፣ ገበሬውም አብሮ ተወድሷል፤ ተሞግሷል። ሙገሳውና ውደሳው ተደጋጋፊ ናቸው ማለት ነው። የገበሬውን ታታሪነት በሚያመለክቱ ግጥሞችም ስለበሬው ተጠቅሶ ይገኛል።

አርኬ 28 ገበሮይ ጥመዱ ማለዳ ተነሱ
ገበሮይ ተነሱ ከቀዳሙ እረሱ
ከባልንጀራ ፊት እንደትደግሱ
መንቶ 29 እርሻ እረሱ አትፍቱ በጊዜ
ጎተራው ኽሞላ አይታጣም ሚዜ
መንቶ 30 የግራውን በሬ፤ ኻላውረገረጉት፤ በዋጮ ጉማጅ
ባንገታም ብርሌ አይገኝም ጠጅ
አርኬ 31 አምሮህ እንደሆነ እምብርታም ጊደር
አምሮህ እንደሆነ ዳውሪ ጊደር
አምሮህ እንደሆነ ድንቡሎ ሞይዘር
ደሞ እንደ ዋጃ ላይ ኽመሌው እደር
አርኬ 32.እኒህ ገዳዶየ
እኒህ አባይ ጋሞ
እኒህ ውርቴ በታይ
እኒህ ገደመዩ ግብርና አነጠሩ
ጤፍ እንደ ማሽላ በመሬት ሰፈሩ
ምነው ባለ ግመል ባለ ጊደር ሆኑ
መንቶ 33 መጋላ በሬ የጠመደ ሰው
እንኳን ለራሱ ይተርፋል ለሰው

የመገላው ወይም የውዳሴው ሀሳብ የሚመጣው ከግጥሞቹ በስተጀርባ ባለው ሀሳብ ነው:: በተለይ ከ28-30 ያሉት ግጥሞች ቅድሚያ መስጠት የሚገባቸውን ተግባራት የሚመለከቱ ናቸው። «በርትተህ ካልሰራህ የምትፈልገውን ማግኘት አትችልም» የሚል መልክት ያላቸው ናቸው:: ከጓደኛ በፊት ቀድሞ ለመደገስ፣ ጓደኛ ለማፍራት፣ የምትፈልገውን ለመጠጣት፣ ጠንክረህ ማረስ ይኖርብሀል። በጧት ተነስቶ ቀዳም እስተቀዳም የሚያርስ ገበሬ ቤቱ የተሟላ ይሆናል:: በበህሉ ደግሶ ማብላትና ማጠጣት ያስሞግሳል፤ ያስወድሳል:: ሚዜ የሚለው ቃል በአገባቡ ጓደኛ ከሚለው በተጨማሪ አብሮህ የሚበላና የሚጠጣ፣ አብሮህ የሚውልና የሚዝናና ወዘተ. አይጠፋም፤ ሁል ጊዜ በሰዎች ታጅበህ ትከበራለህ:: ቤትህ ሙሉ ከሆነ ሰው ሁሉ ወዳንተ ይቀርባል ማለት ነው:: አቀራረቡ በማህበር፣ በበአል፣ በጋብቻ፣ ወዘተ. ግንኙነት ለመዛመድ ተፈላጊነት ይኖርሃል የሚል ነው:: ካልሆነ ግን «የሌላው ልብ የለው ያጣ ዘመድ የለው» እንደሚባለው ትሆናለህ የሚል መልክት አለው:: ጠንክሮ ማረስ፣ እንደልብ ተዝናንቶ

መኖርን፣ የተሻለ ህይወት መምራትን፣ በማህበረሰቡ ዘንድ መከበርን፣ የማግኘት እድል ያስገኛል::

አርኬ 31 ና 32 የሚያነሱት ሀሳብ የአካባቢው ማህበረሰብ በተለይ አርሶ አደሩ ተለይቶ የሚታወቅባቸውን እውነታዎች ነው:: አርሶ አደሩ ለጦር መሳሪያና ለእንስሳት (ለከብቶች) ያለው ፍቅር ከፍተኛ ነው:: መሳሪያው (ጠመንጃው) ራሱን፤ ቤተሰቡን፤ ሀብቱን፤ መጠበቂያው ሲሆን ጌጡም ነው:: እንስሳቱ የባለፀጋነት መለያዎቹ ናቸው:: የጠመንጃውና የእንሰሳቱ መገኛ ደግሞ ከማሳው የሚያገኘው የሰብል ምርቱ ነው:: ከከብቶች በተጨማሪ በአካባቢው ግመል ዋናው የሀብት መገለጫ ነው:: በዋጋው (ሲሸጥ ወይም ሲገዛ) ከፍተኛ ነው:: አገልግሎቱም ያንኑ ያህል ነው:: አሁን አሁን ምርት ከአውድማ ወደ ቤት የሚጫነው በግመል ሆኗል፤ ለአካባቢው አርሶ አደር ዋና የሀብት መገለጫና የሀብት ምንጭ ነው:: ለዚህ ነው፣ ገጣሚው ገደመዩ እሚባለው አካባቢ ያሉ አርሶ አደሮችን ሲያወድስና ሲያሞግስ ‹‹ምነው ባለግመል ባለጊደር ሆኑ›› የሚላቸው:: የዚህ አካባቢ አርሶ አደሮች ከሌላው አርሶ አደር በሀብት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ያመለክታል:: ገዳዶየ፣ አባይጋሞ፣ ውርቱ በታይ፣ የሚባሉት ከቆቦ በስተምስራቅ በኩል የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ናቸው::

የአርኬዎቹ ግነት ለየት ባለ መንገድ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል:: በግብርና ተግባር ውስጥ የተመረተው ምርት የሚቀመጥበት ቦታና ሁኔታ፣ በተለምዶ የሚታወቅና የተወሰነ ነው:: በተለይ ጤፍና ማሽላ በብዛት በሚመረትባቸው አካባቢዎች፣ የማስቀመጫ ቦታዎቹና ሁኔታዎቹ የተለያዩ ናቸው:: ማሽላ በጉድጓድ ውስጥ እስከ ሁለትና ሶስት አመት መቀመጥ ይችላል:: በጉድጓድ ውስጥ እንዲቀመጥ አስገዳጁ ሁኔታ የምርቱ መብዛት ሲሆን፣ ምቹ ሁኔታው ደግሞ የፍሬው ጥንካሬ ነው:: ጤፍ በጎተራና በጎታ ይቀመጣል እንጅ በጉድጓድ አይቀመጥም:: ምክንያቱም እንደማሽላ ብዛቱም ሆነ ፍሬው በጉድጓድ ውስጥ እንዲቀመጥ አያስችልም፣ ይበሰብሳልና ነው:: ዘይቤው ይህንን ተለምዷዊ የግብርና ተግባር በመጣስ ነው የጤፉን የምርት ብዛት አጉልቶ ለማሳየት የሞከረው:: የግነቱ አላማ በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚኖረው አርሶ አደር በሌላው አካበባቢ ከሚኖረው አርሶ አደር በሀብት ብዛትና በግብርና ችሎታ ተወዳዳሪ እንደሌላቸው ማሳየትና ማስረገጥ ነው:: ማረጋገጫወቹም «ምነው ባለ ግመል ባለ ጊደር ሆኑ» የሚሉት እንስሳት ናቸው:: እነዚህ እንስሳት ለአካባቢው ማህበረሰብ እንደ ትልቅ የሀብት መገለጫዎች ናቸው::

የነዚህን አርሶ አደሮች የምርት መጠን የገለፀው እጅግ በተጋነነ ስልት ነው:: የራያ አካባቢ አርሶ አደር ጤፍና ማሽላ የሚያኖረው በጎተራና በጉድጓድ ነበር:: ጎተራ ለጤፍ ሲሆን ጉድጓድ ለማሽላ ነው:: የማሽላ ምርት ብዙ ስለሆነ በጎተራ ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ የጤፍ ምርቱን ብዛት ለመግለጽ ‹‹ጤፍ እንደማሽላ በመሬት ሰፈሩ›› ነው ያለው፡፡ በመሬት ሰፈሩ ማለት የጤፍን ምርት በጉድጓድ ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡

ገጣሚው ተፈላጊ የሆኑትን እንስሳት /ላሞች/ መልክና ቁመና ያሳያል:: «እምብርታም ጊደር» እና «ዳውሪ ጊደር» የሚሉት ሀረጎች የሚያመለክቱት የጊደሮቹን የሰውነት ክፍልና መልክ ነው::እምብርት በጡቷ መካከል ባለው የሆዷ ክፍል ወደታች የተንጠለጠለ ቆዳ ነው:: ከቁመናዋና አብሮ ሲታይ እንደ ጥሩ ዝርያ ማሳያ ይቆጠራል:: አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ በልምድ የከብቶችን ተክለ ሰውነታቸውን አይቶ ዝርያቸውን ለመገመት ይችላል:: «ዳውሪ» ማለት ከጥቁር ቆዳ ላይ ነጫጭ ነጠብጣብ ያለበት መልክ ነው:: ገጣሚው «እምብርታቸው ረጃጅም፣ መልካቸው ዳውሪ፣ ላሞች እንዲኖሩህ የምትፈልግ ከሆነ፣ ዝናብ ብቻ አምነህ አትቀመጥ፤ ወንዙን በመስኖ እየጠለፍክ ማሳህን ማጠጣት አለብህ:: ይህንን ስታደርግ የምትፈልገውን ታገኛለህ» ይላል፡፡ ረጅም ምንሽር፣ አጭር ምንሽር፣ እንደሚባለው ሁሉ፣ «ድንቡሎ ሞይዘር» ማለት አጭር ሞይዘር ማለት ነው:: ድንቡሎ ሞይዘር በትከሻ ሲያዝሉት ወይም ሲያነግቱት፣ ከሰውነት ቁመት ወይም ከትከሻ ስፋት፣ ብዙ ተርፎ አይታይም:: ለሚይዘውም ሆነ ለሚያየው ሰው ያምራል፤ የኩራት ምንጭ ይሆናል:: ከሚያምሩ ከብቶች በተጨማሪ መሳሪያ አንዲኖርህ የምትፈልግ ከሆነ ጠንክረህ መከሰብ አለብህ የሚል መልክት ያለው ነው፡፡

መንቶ 30ን ለየት የሚያደርገው አንድ ነገር ወይም ሀሳብ አለ:: ይህም ገጣሚው ‹‹የግራውን በሬ ...›› ለምን አለ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው:: በአርሶ አደሩ አስተሳሰብና ልምድ በግራ የሚጠመድ በሬ ሀይለኛና ጉልበተኛ ነው ይባላል:: ወይፈን ማረስ የሚለማመደው (የሚቀናው) በቀኝ እየተጠመደ ነው:: ወይፈኑ ፈር ለማበላሸት ሲሞክር በግራ የተጠመደው በሬ በሻምዳ (በቀንዱ) ይመታዋል:: ከፈሩ እንዳይወጣ ጎትቶ ይይዘዋል:: ከቀዳሙ ሲዞሩ ጎትቶ ወይም ገፍቶ ወደ ፈሩ ያስገባዋል:: ሙሉ ቀን ተጠምዶ ሲያርስ ይውላል እንጅ፣ አጋዥ (ተለዋጭ) በሬ አይገባለትም:: በመሆኑም መልክቱ፣ በግራ የተጠመደውን በሬ በደንብ ካላረስክበት እንደልብ መዝናናት አይገኝም የሚል ነው:: ከሚጠመድበት አንፃር ብቻ ሳይሆን የበሬውንም መልክ በመጨረሻው መንቶ እናገኛለን:: መጋላ በሬ ማለት ጥቁር ወይም ቀይ ያልሆነ በሁለቱ መካከል የሚሆን ቀለም (መልክ) ያለው በሬ ነው:: ልክ በግራ

እንደሚጠመደው በሬ እንዲህ አይነት መልክ ያለው በሬ ሀይለኛ ነው ተብሎ ይታሰባል:: ከግጥሙ እንደምንረዳው በእንዲህ ያለ በሬ የሚያርስ ገበሬ ከራሱ አልፎ ለሌሎች እንደሚረዳ ነው::

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ግጥሞች እንደተረዳነው የሙገሳውና የውደሳው ትኩረት፣ ከበሬው ሃያልነት፣ ከገበሬው ታታሪነት፣ ከምርቱ ብዛት፣ ወዘተ. ጋር የተያያዙ ናቸው:: በሀይለኛ በሬ የሚያርስ ታታሪ ገበሬ ከፍተኛ ምርት በማምረቱ የሚፈልገውን ሁሉ ማሟላትና ማድረግ እንደሚችል ያሳያሉ::

6.2.1.3 ሴቶችንና ወንዶችን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ

የሙገሳ የውደሳ ቃልግጥሞቹ አካባቢንና ሰዎችን፣ በሬንና ገበሬን፣ ከማሞገስ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ በአንድ ወቅት በአካል የነበሩ፣ በስምና በመልክ ተለይተው የሚታወቁ ሴቶችና ወንዶችን የሚያወድሱ ሆነው ተገኝተዋል:: በየዘመኑ ለሚታዩ ቆንጆዎችና ጀግኖች፣ በዚያው በዘመናቸው ግጥም ተገጥሞላቸዋል፤ ዘፈን ተዘፍኖላቸዋል፤ የሚከተሉት ይህንን የሚያመለክቱ ናቸው::

መንቶ 34 ማረይ ገብሳን ብየ ስሄድ አጥር ላጥር
ዋጋየን አገኘሁ ሰባት አመት ንጥር
መንቶ 35 ማረይ ገብሳ ታማ ገብሳየ ሲጨነቅ
ሰላሳው ደገኛ ከነአህያው ይለቅ
መንቶ 36 ሰላሳው ደገኛ ጭቁኑ ምን አርጎ
እሷ ትሙት እንጅ የበላችው በእርጎ
አርኬ 37 አረገረገ አሉ ዋጃ ከተማው
አረገረገ አሉ ቆቦ ከተማው
ሽጋ አንባሻ ታየ ስታልፍ እረግጣው
መንቶ 38 ዋጃ ኸኮረረው ይሰራልኝ ማማ
ሽጋ አንባሻ ታየ ሲሏት እንድሰማ
መንቶ 39 አሁን አልደርስም ወይ ብሮጥ ብንደረደር
ከአንባሻ ታየ አገር ዋጃ ላይ ለማደር

አርኬ 40 አሸቼ እንዳልበላ መሀል እጀ ታሞ
ሽቋር መንገሻ አገር ወርቁ ገለሂሞ
ሙጫ ጤፍ አለችኝ ያችን ሰላልቁ
ሽቋር መንገሻ አገር መሄዴ ነው ወርቁ

ከመንቶ 34-36 ባሉት ግጥሞች ውስጥ በስም የተጠቀሰችው «ማረይ ጉብሳ» ትኖር የነበረው ዋጃ ከተማ በታች ባሉት የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ነው:: በ1977 ዓ.ም ከአባቷ ጋር ቆቦ ከተማ አጥኝው አይቷታል:: መልኳ ቀይ ቁመቷ መካከለኛ የሚባል ነው:: አጥኚው ሲያያት በጣም ወፍራም አልነበረችም:: ገጣሚው ይችን በህይወት የነበረችና በስም ተለይታ የምትታወቅ ሴት ከነቤተሰቧ ስማቸውን እየጠቀሰ ለማወደስ ያነሳሳው ምንድን ነው? ከሷ የበለጡ (በቁንጅናም ይሁን በሌላ) ሴቶች በአካባው አልነበሩም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ:: እንደነዚህ አይነት ግጥሞች ሊፈጠሩ የሚችሉት ምንአልባት በእረኞች ወይም ለአቅመ አዳም በደረሱ ወጣቶች ይሆናል:: እነዚህ ወጣቶች በአካል የሚያዋቸውን ሴቶች መልካቸውን፣ አለባበሳቸውን፣ ፀጉራቸውቸውን፣ ጥርስና ከናፍራቸን፣ ወዘተ. ያስተውሉና፣ ይህንን አስታውሎታቸውን የሚገልጹት በዘፈን ይሆናል:: አንዱ ፈጥሮ የዘፈነው ግጥም፣ በስሚ ስሚ ወደ ሌላው እየተላለፈ ከተሞጋሹ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ እስቲደርስ ድረስ ይዛመታል:: እንዲህ አይነት የሙገሳ ግጥም የሚገጠምላቸው ሴቶች በተለያየ ምክንያት ከጋብቻ ውጭ ሆነው ሲገኙ ይመስላል:: ለዚህ ነው፣ «ዋጋየን አገኘሁ ሰባት አመት ንጥር» በማለት እህቷን ጭምር ለማወደስ የሞከረው:: ዋጋየ፣ ለሰባት አመት ያህል ተጠብቃ እንደኖረች አርጎ ገልጿታል:: የሰባት አመት ንጥር ቅቤ፣ የሚኘው ከሀብታም ቤት ስለሆነ፣ የአባታቸው ሀብታምነት በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቁሟል ማለት ነው።

እነዚህ መንቶዎች በተለያዩ ግለሰቦች የተፈጠሩ ይመስላል፤ ምክንያቱም በመካከላቸው ምልልስ አለ:: ይህ ምልልስ የገጣሚዎቹን ማንነት የሚያመለክት ነው:: ይኸውም የአንደኛውን ፍርደ ገምድልነት፤ የሌላውን ጠበቃነት፤ የሚያመለክት ነው።። ለአንዲት ሴት ህይወትና ለቤተሰቧ ጭንቀት፣ ፈዳ እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ሰላሳ ሰዎች ከነአህዮቻቸው ነው:: «ፈዳ» ማለት አንዱ ሌላውን ተክቶ መሞት ማለት ነው:: ለዚህ ሀሳብ ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ መንቶ 36 ላይ እናገኛለን:: «እሷ ትሙት እንጅ የበላችው በእርጎ» የሚለው ስንኝ የኑሮ ደረጃዋን ጭምር ያሳያል::

አርኬ 37 ላይ የተጠቀሰችው ሴት ሰውነቷ ወፍራም፣ ገላዋ ለስላሳ፣ ቁመቷ መካከለኛ፣ ይመስላል:: ሁለቱ ከተሞች (ዋጃና ቆቦ) የሴትዮዋን ክብደት መሸከም ባለመቻላቸው፣ ተንቀጠቀጡ፤ ተብረከረኩ፤ ይላል :: በዚህ አገላለፅ አረማመዷና የሰውነቷ ውፍረት ተጠቁሟል:: ገጣሚው በአካላዊ ቁንጅናዋ ከመማረክ አልፎ፣ ስሟ ሲጠራ መስማት እንደሚያስደስተው ይናገራል:: የመውደድ ስሜቱን ከሷ ጋር አብሮ በማሳለፍ ወይም እሷ በምትኖርበት አካባቢ በማደር፣ ናፍቆቱ መወጣት እንደሚፈልግ ይገልፃል::

የሙገሳ ግጥሞቹ ሴቶችን ብቻ የሚመለከቱ አይደሉም:: በጊዜያቸው በአካልና በስም እንዲሁም በመኖሪያ አካባቢያቸው ይታወቁ የነበሩ ወንዶች፣ በተለያየ ምክንያት ለገጠሟቸው ችግሮች በሰጡት ምላሽ፣ ግጥም የተገጠመላቸው አሉ:: ከዚህ በታች ያሉት ግጥሞች በነዚህ ሰዎች ሰበብ የተፈጠሩ ናቸው::

አርኬ 41 እከደከ ብረት አይመታም መስሏቸው[17]
ያንድ ሊቀመንበር ያንድ አገር ሰው ናቸው
ተመለሱ እያለ እየለመናቸው
ከጉድባው ውስጥ ሆኖ ኸኮባው ጣላቸው
ያ ይርጋ አባ ምንጃ ገትሮ አዋላቸው
እነ አይመከሬ ካላኮርሜ ናቸው
መንቶ 42 ና ተያዝ፣ ና ታሰር፣ ዳኝነት ባልነበር
አንድ ሰው ላንድ ሰው መይ ይሸነፍ ነበር
መንቶ 43 ጥጆቹ ተርበው እርሾ ሲግቷቸው
ወንዱ ራስ ጀበና ወርዶ አገናኛቸው
መንቶ 44 እንኳን አላማጣ ቢጣፍ ለላይ ደሴ
መግደሉን አይተውም ከወየ ደረሴ
መንቶ 45 የብረይሊ ልጆይ ጠብቃችሁ እረሱ
ከወየ አረጀ አሉ የብረይሊ ዋሱ::
መንቶ 46 የአደም ወዳጆ ላም ዳቡሌ ገውስ
ማነው የሚነዳሽ እኔ አፈር ሳልቀምስ

[17] ከመንቶ 43-45 ያሉት ግጥሞች ታሪክ የነገረኝ ፈንታየ አሸብር ሲሆን ሌሎቹን ይላቅ ደጉ ነው።

መንቶ 47 የአደም ወዳጆ ልይ አንተ አፈ ወደሉ
ዳቡሌ ገውስን አስወሰድኻት አሉ
መንቶ 48 ሴቱ ሽብራር ሲጭን ወንዱ ላም ሲያጣባ
የአደም ወዳጆ ልይ ገሏል በማለዳ በሱቢ ገማማ
መንቶ 49 አቢልች ብለው እሱ አምርሮ ኑሮ
ገዳይ በምንሸር የዱር ፍሬ በልቶ

የአርኬ 41 እና 42 ባለታሪክ ትውልዱም እድገቱም «አርበት» ከሚባል የገጠር አካባቢ ነው:: አቢዮቱ ከፈነዳ በኋላ፣ መሳሪያ ያለው የአካባቢው ሰው መሳሪያውን ለመንግስት እንዲያስረክብ ይገደድ ነበር:: አንዳንድ ሰዎች ግን፣ ደብቀው ሳያስረክቡ ቀሩ ይባላል:: ከነዚህ መካከል በዚያን ጊዜ ወጣት የነበረው በስም የተጠቀሰው «ይርጋ አባምንጃ» የሚባለው ነው:: የአካባቢው ገበሬ ማህበር ጥቆማ ስለደረሳቸው፣ በአንድ የለቅሶ አጋጣሚ ወጣቱን ለመያዝ ያስባሉ::

እሱም ይጠራጠርና ተዘጋጅቶ ይጠበቃቸዋል። ሊይዙት እንደሆነ ሲረዳ፣ ከለቅሶው መሀል ወጥቶ መሳሪያውን ይዞ ወደ ተራራ ይወጣል:: ከተራራው ወገብ አካባቢ በተፈጥሮ እንደ ምሽግ የሆነ ቦታ ያገኝና፣ እዚያ ውስጥ ይገባል:: ሊይዙት ከመጡት ታጣቂዎችና ከገበሬ ማህበሮች ጋር ሲታኮስ ይውላል:: እነሱ በአውቶማቲክ መሳሪያ፣ እሱ ተራ በተራ በሚተኩስ መሳሪያ፣ ሲታኮስ ውሎ ወደ ማታ ጥይት ሲያልቅበት፣ በራሱ ጥይት ራሱ ገድሎ ተገኘ:: የግጥሙ መነሻ ታሪክ ይኸ ነው::

የገጣሚው አስተውሎት፣ በጊዜው ህግን ተገን እያደረጉ፣ ግለሰቦችን የሚያንገላቱ፣ የሚያሳስሩ፣ የሚያስገድሉ፣ ሰዎችን የሚመለከት ነው:: ባለታሪኩ ሊይዙት የመጡትን ሰዎች ይለማመጥ፣ እባካችሁ ተውኝ፣ እያለ ይለምን እንደነበር ‹‹ተመለሱ እያለ እየለመናቸው/ እነ አይመከሬ...›› በሚለው ስንኝ ተገልጿል:: ይህንን ተማፅኖውን የተቀበሉት አይመስልም:: አብረው ይኖሩ የነበሩ ሰዎች፣ አንዱ ወገን የአቢዮት ደጋፊና ተሟጋች፣ ሌላው /ባለታሪኩ/ የመሳሪያ ፍቅርና አልደፈር ባይነት አጣልቷቸው፣ ውጤቱ የህይወት መጥፋት ሆነ:: ገጣሚው ሚዙን በማሞገስ፣ ሌሎቹን በጎንዮሽም ቢሆን በማንኳሰስ ወቅሷቸዋል::

የመንቶ 43 ታሪክ የተፈፀመው፣ ከወልዲያ በታች፣ ዶሮ ግብር አካባቢ ነው:: ወደ ኋላ፣ ስለ ቀኛማይ አባተ ሀይሉ የተገጠሙት ቃል ግጥሞች ሲተነተኑ ይታያል:: ራስ ጀበና የተባለው ሰው ዋና ስሙ ፈንታቢል አስፋው ነው:: ‹‹የወፋ ውጊያ›› ወይም ‹‹የወያኔ ውጊያ›› ሲደረግ፣

የጎበዝ አለቃ እየሆነ ያዋጋ የነበረ ሰው ነው ይባላል:: እና አባተ ሀይሉ የሚባለው ባላባት፣ አሽከሮቹን ይዞ፣ ዶሮ ግብር አካባቢ ባለው የእርሻ ቦታ ላይ የነበሩትን የአካባቢውን ከብቶች ሰብስቦ ያግትና፣ ሁለት ያህሉን አሳርዶ ከአሽከሮቹ ጋር ስጋ ሲበላ የአካባቢው ገበሬ /ከብቶቻቸው የተወሰደባቸው/ በእሪታ ተጠራርተው ይሰበሰባሉ:: ወልዲያ ሰው ልከው አቤቱታ ቢያቀርቡም፣ ለጊዜው መፍትሄ ሳያገኙ ይቀራሉ:: የፖሊስ ሀይል በቦታው ቢደርስም፣ የገበሬዎቹን ከብቶች አስለቅቆ ማስመለስ ባለመቻሉ፣ ፍጥጫው ወደ ጦርነት ይለወጣል:: አቶ አባተም 30 የሚሆኑ አሽከሮች ይዞ መታኮስ ይጀምራል:: ከሁለቱም ወገን ሰዎች ሞተዋል:: ለሶስት ቀን ያህል ከእናቶቻቸው ተነጥለው የቆዩት ጥጆች፣ ባለቤቶቻቸው እርሾ እያጠጡ አቆይተዋቸዋል:: ይህንን ሁኔታ ነው የአካባቢው ሰው አስተውሎ፣ ከላይ የቀረበውን መቶ የገጠመው:: ግለሰቡን ለአካባቢው እንደ «ተፋላሚ ጀግና» አድርጎ ነው ያሞገሰው::

ከመንቶ 44-49 ባሉት ግጥሞች በስም የተጠቀሱት ሰዎች ይኖሩ የነበረው ወርቁ አካባቢ ባሉት የገጠር ቀበሌዎች ነው:: አካባቢው ከአፋር አካባቢ ጋር አጎራባች ስለሆነ ግጭት አይጠፋም:: በግጭቱ ከሁለቱም በኩል ሰው ሊሞት ይችላል:: ሰው ሲሞት ለመንግስት አቤቱታና ክስ ይቀርባል:: መንግስት በህግ ሲቀጣ የአካባቢው ባህላዊ ሽምግልና ደግሞ በእርቅ ችግሩን ይፈታል:: ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው ባለታሪኩ እነዚህን መፍትሄዎች የሚቀበል አይመስልም:: ‹‹እንኳን አላማጣ ቢጣፍ ለላይ ደሴ›› በማለት መንግስትን ጭምር የማይፈራ መሆኑን ገልጧል:: በከብቶቹና በሱ ለሚመጣ ማንኛውም ጠላት ከመግደል ወደ ኋላ አይልም:: ግለሰቡ በጀግንነት ብቻ ሳይሆን በጎበዝ ገበሬነቱ የሚታወቅ ይመስላል:: ‹‹ከወየ አረጀ አሉ የብረይሊ ዋሉ›› የሚለው ስንኝ በሁለት መንገድ የሚፈታ ነው:: አንደኛው፣ ከወየ እስካለ ድረስ፣ ብረይሊን የሚደፍር ሰው አይመጣም፤ እሱ ካለ አካባቢው አይደፈርም፤ ይከበራል፤ ማለት ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ በክፉ ቀን እህል የሚያበድረው ጎበዙ ገበሬ /ከወየ/ ስለደከመ ሌሎቻችን ለችግር እንዳንጋለጥ በርትተን እንረስ የሚል ነው::

ሌላው ባለታሪክ አደም ወዳጆ የሚባል የወርቁ ሰው ነው:: ይህ ባለታሪክ ሰርግ ላይ መንቶ 46 ላይ ያለውን ያስገጥማል አሉ:: «ዳቡሌ ገውስ» የላሚ ስም ነው:: ከከብቶቹ ሁሉ እሷ ተመርጣ የተገጠመላት በተለያየ ምክንያት ይሆናል:: በአካባቢው በላሞቹና በበሮቹ ስም ግጥም መግጠምና መዝፈን የተለመደ ስለሆነ ይህንን ባህል መሰረት አድርጎ ነው መንቶው የፈለቀው:: ከመንቶ 46-49 ያሉትን ማየት እንደሚቻለው የሁለት ሰዎች ምልልስ የሚታይበት ነው:: አንደኛው ባለታሪኩ ሌላው ትችት አቅራቢው ናቸው:: እና በስም የተጠቀሰችውንና ሌሎቹን

ላሞች አፋር ወሰዳቸው አሉ:: በዚህ ጊዜ መንቶ 46 ን ያስታወሰና የላሞቹን መወሰድ የሰማ ሰው፣ መንቶ 47 ን ገጠመበት::

አንድ ነገር በተግባር ሳያሳዩ አስቀድሞ መናገር ያስገምታል፤ በአደባባይ ያስተቻል:: ገጣሚው ይህንን ማህበራዊና ባህላዊ እውነታ መነሻ አድርጎ ነው መንቶውን ያፈለቀው:: ተወቃሹ ባለታሪክ በገጣሚው ላይ ጥላቻ አላሳደረም:: ከዚህ ይልቅ ለሌላ ተግባር ራሱን ያዘጋጃል:: ሌሊቱን ሲጓዝ አድሮ፣ ማለዳ ተኩስ ከፍቶ፣ ከብቶቹን ይዞ ወደ አገሩ ይመለሳል:: ይህንን ካደረገ በኋላ፣ በሌላ አጋጣሚ ላይ መንቶ 48 ን ገጠመ ይባላል:: «ሽብራር» ማለት ከፍየል ቆዳ የሚሰራ፣ የአፋር ሴቶች ውሃ የሚቀዱበት፣ የውሃ መያዣ ስልቻ ነው:: «ማጣባት» ማለት ጥጆችን ከናቶቻቸው ጋር በማገናኘት እንዲጠቡ ማድረግና፣ ወተት ማለብ ነው:: «ሱቢ ገማማ» ማለት፣ ሌሊቱ ሊነጋጋ ሲል ማለት ነው:: ሱቢ ጧት ሲሆን ገማማ ወገግ ሲል እንደማለት ነው::

ይኸ ሁኔታ በአካባቢው ተሰማና እንደገና ለሌላ መንቶ መፈጠር ሰበብ መሆን ቻለ:: የመጨረሻው መንቶ፣ የገጣሚውን ሁለት ስሜቶች ማንፀባረቅ የቻለ ነው:: አንደኛው፣ ተግባሩን ማድነቅ፣ ወንድነቱን መመስከርና፣ በፊት የተናገረውን ማስተባበል ነው:: ሁለተኛው፣ ስጋቱንና ፍርሀቱን መግለፅ ነው:: ከዚህ በኋላ እኔንም አይለቀኝም በሚል ስጋት አስቀድሞ በማሞገስ ይቅርታ ይለምናል:: በቀልድ አስመስሎ ያቀረበው መዛበቻ፣ ስጋት ስለፈጠረበት ትችቱን ያስተባብላል::

በአጠቃላይ ከቀረበው ትንተና ማስተዋል እንደሚቻለው፣ ሰዎችን በስም እየጠቀሱ የማሞገስና የማወደስ ባህል፣ በዚያ አካባቢ በሚኖው ማህበረሰብ አባላት ዘንድ የተለመደና ተቀባይነት ያለው ይመስላል:: እንዲህ አይነቱ ባህልና ልማድ፣ በተከታታይ ትውልዶች ውስጥ ለሚፈጠሩ ተመሳሳይ አጋጣሚዎችና ግለሰቦች፣ ስም እየጠቀሱ፣ ቃልግጥም እየፈጠሩ፣ መዝፈን ወይም ማቅራራት ስለሚቻል፣ የቃልግጥም ፈጠራው የሚቀጥል ይሆናል ማለት ነው::

6.2.1.4 እስሳትን (ላሞችን) የሚያሞግሱና የሚያወድሱ

የሰሜን ወሎ ምስራቃዊ አካባቢዎች ከአፋር ክልል ሰሜናዊ አካባቢዎች ጋር የሚዋሰኑ ናቸው:: የአፋር አካባ የማይታረስ ስለሆነ ወይም ስለነበረ ለከብቶች የሚሆን የሳር ግጦሽ አይታጣም::

በጓዳና ከብቶችን ማርባት የተለመደ ነው:: ይህንን ሁኔታ የሚገልጹ ግጥሞች የሚከተሉት ናቸው::

መንቶ 50 ባሰሚት ነው እንጅ ያች ላም ጨኻለይ
አሻግሮ እሚተኩስ እረኛ ብላለይ
መነቶ 51 አንቺን ከሚከፋሽ እኔን ይክፋኝ ብየ
ገባሁልሽ ከሎ ቀጮየን አዝየ
መንቶ 52 ያልታደሉ ላሞይ፤
እንደው በኛ ጊዜ፤
እንደው በኛ ወራት ኸኛ ተጠግተው
ጋታቸው አረረ ያመለ ጭድ በልተው

መንቶ 50 ላይ ገጣሚው የላሟን ጨኸት የተረዳበት ሁኔታ የተለየ ነው:: ከብቶች አንድ ቦታ ተወስነው ወይም ታግደው ሲውሉ፣ ሳር እንደልብ ላያገኙ ይችላሉ:: ስለዚህ ሳር ወዳለበት አካባቢ መሄድ ይፈልጋሉ:: ይህንን ፍላጎታቸውን ለማሟላት ጎበዝ እረኛ መኖር አለበት:: መሳሪያ ይዞ የሚጠብቃቸው ባለቤት ካለ፣ በየትኛውም አካባቢ እንደልብ በመዘዋወር ሳር ማብላት ይቻላል:: ይህን ለማድረግ ማጓደን ያስፈልጋል። በጓዳና ከብት መጠበቅ ለተለያዩ ችግሮች ያጋልጣል:: የከብት ዘረፋና የተኩስ ልውውጥ ይኖራል:: ይኸ ደግሞ መሞትና መግደልን ያስከትላል:: ከብቶችን ከአውሬ መጠበቅም ሌላው ችግር ነው:: ይህንን ሁኔታ ለማሳየት ነው መንቶ 51 ላይ ‹‹አንቺን ከሚከፋሽ እኔን ይክፋኝ ብየ›› በሚለው ስንኝ ጭንቅቱንና ችግሩን ያንፀባረቀው:: «ከሎ» ማለት አፋር ውስጥ የሚገኝ ቦታ ስለሆነ ያስፈራል:: «ቀጮ» የወተት መያዣ ቅል ነው:: በጓዳና ህይወት ቂጣ በወተት እንጅ፤ እንጀራ በወጥ የለም:: ለዚህ ነው ላሚቱን «አንቺ ከምትራቢ፣ ከምትከሽ፣ እኔ ልቸገር፣ እኔ ልንገላታ» የሚላት::

መንቶ 52 ላይ የቀረበው ሀሳብ ይህንን የሚያጠናክር ነው:: ‹‹በኛ ጊዜ›› በሚል የተጠቆመው የአሁኑ ዘመን ትውልድ ወይም ሰው ማለት ነው:: ከዚህ በፊት የነበሩ ሰዎች ላሞቻቸውን ሳር ወዳለበት እየወሰዱ ያበሉ ነበር፤ አሁን ግን ያ ባህል እየቀረ በመምጣቱ የከብቶች ቀለብ ጭድ /ገለባ/ ሆነ፤ ከብቶቹም ነጠፉ፣ ይላል:: ገጣሚው በተዛዋሪ መንገድ የዛሬውን ትውልድ ድክመት፤ «ድሮ ነበር እንጅ ዛሬማ ምን ወንድ አለ፤ ጀግና የለም፤» በማለት ያሳያል::

ከዚህቀጥሎ ባሉት ደግሞ ላሞቹ ከነባለቤታቸው በስም ተጠቅሰው የሚያወድሱ ግሞች እናገኛለን::

መንቶ 53-የምስጋን በላይ ላም መገን ዲሌ ሮይታ[18]
አላስነካም አለይ ኸራሳው ተኝታ
መንቶ 54-የምስጋን በላይ ላም ዋርሌ ቀይቱ
ምንሸሩን ይዛ ገባይ ኸበረቱ
አርኬ 55-ከምስጋን ወንድሞይ ኸተወለዱቱ
ከምስጋን ጓደኛይ አብረው ኸበሉቱ
አብራ ጋደም አለይ ዋርሌ ላሚቱ
መንቶ 56-የምስጋን በላይ ላም፤ አትበላም ገለባ፤ አትጠጣም ልማት
እንደው ዝም ብለህ ደራይቶ ንዳት

በነዚህ ግጥሞች ውስጥ የሁለት ላሞች ስምና ተግባር ተገልጿል:: ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ምስጋን በላይ የሚባለው የዞብል (የአንጎት ቀበሌ ነዋሪ) ተወላጅ፣ ከግብርና ስራ በተጨማሪ በከብት እርባታ (ብዙ ከብቶች እንደነበሩት) ይታወቃል:: ከብቶቹን አፋር ውስጥ ሳር ሲያበላ አፋሮች ያገኙታል:: እነሱ እንጅ፣ እሱ ስላላያቸው፣ አንደኛው አፋር ተኩሶ ይመታዋል:: ከዚያ መሳሪያውን ለመግፈፍ ሲሞክሩ፣ ላሞቹ ባለቤታቸው ከወደቀበት ሆነው በሀይል በመጮህ፣ ማፋረስ ይጀምራሉ:: መሳሪያውን ለመግፈር የመጣውን አፋር ለመውጋት ሲታገሉ ይቆያሉ:: ከዚያ የቁስለኛው ቤተሰብና የአካባቢው ሰው በእሪታ ወርዶ ቁስለኛውን በቃሬዛ ይዘው ወደ ቤቱ ይገባሉ:: ይህ ሁኔታና ተግባር ነው ላሞቹን እንዲወደሱ ያደረገው:: የአካባቢው አርብቶ አደርም ሆነ አርሶ አደሩ፣ ለከብቶቹ ስም ያወጣል:: የስም አወጣጡ ደግሞ፤ ከመልካቸው፣ ከቁመናቸው፣ ወዘተ.ጋር የተያያዘ ነው::

በነዚህ ግጥሞች ውስጥ «ዲሌ ሮይታ» እና «ዋርሌ» የሚሉት የላሞቹ ስሞች ናቸው:: «ዲሌ» ማለት በቀይ መልክ ላይ ጥቋቁር ነጠብጣብ ያለባቸው ላሞች ወይም በሬዎች መለያ መልክ ነው፤ የነብር መልክ ይመስላል:: «ሮይታ» ና «ዋርሌ» የሚሉት ቃላት ከአፋርኛ የተወረሱ ሳይሆኑ አይቀርም::

ላሞቹ ባለቤታቸው በጥይት ተመትቶ ሲወድቅ፣ እንደ ሰው ለመሸሽ፣ እንደ እንስሳ ለመበርገግ፣ አልፈለጉም:: ቁስለኛ ባለቤታቸውን ሳያስነኩ ከወደቀበት ከበው ተከላክለዋል፤

[18] ከመንቶ 53-56 ያሉትን ከነታሪኩ የነገሩኝ ዘውዱ ፈንታየ እና ተስፋየ ሞላ ናቸው::

መሳሪያውን ከመገፈፍ አድነዋል:: ገጣሚው፣ ላሚቱን የባለቤቷን መሳሪያ እንደሰው አስይዞ ነው የሚያሞግሳት:: 55ኛው አርኬ ላሞቹን ከሰዎች ጋር ያነፃፅራቸዋል:: ከወንድሞቹና ከጓደኞቹ ይልቅ ላሞቹ አብረውት ሊሞቱ እንደቆረጡ አርጎ አቅርቧቸዋል:: ‹‹አብራው ጋደም አለይ...›› ሲል ባለቤቷ ተመትቶ ሲወድቅ ላሚቱም አብራው ወደቀች ማለት ነው:: በዘይቤ ‹‹አብሬህ ልሙት አለች›› ማለት ነው::

የመጨረሻው መንቶ ለየት ባለ ሁኔታ የተሰነዘረ ማህበራዊ ትችት ይመስላል:: ባል ሲሞት የባል እኩያ የሚሆን ሌላ ሰው ማግባት አያስተችም፤ የግጥሙ ትኩረት እዚህ ላይ ነው:: ‹‹አትበላም ገለባ አትጠጣም ልማት›› የሚለው ስንኝ በኋላ ያገባውን ወንድ፣ የሚነቅፍ ይመስላል:: «ልማት» በዚህ አገባብ፣ የቧንቧ ውሀ ማለት ነው:: የጀግናው ላሞች የሚኖሩትና የሚረቡት በከተማ ሳይሆን፣ የለመዱት በጓዳና፣ ደራይቶ አካባቢ፣ አፋር ውስጥ ነው:: ላሚቱ ወይም ላሞቹ ሲሞገሱና ሲወደሱ፣ የሚቹ ስም ገኖ ታይቷል፣ ደጋግሞ ተሞግሷል፣ ይታወሳልም::

6.2.2 ስንፍናን የሚተቹ ቃልግጥሞች

በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ የሚጠሉ፣ የሚወገዙ፣ ባጠቃላይ ተቀባይነት የሌላቸውንና ተቀባይነት ያላቸውን ተግባራትና ባህሪያት፣ እንደ ማህበራዊ ደንብ ተደንግገውና በጋራ ስምምነት አግኝተው የማህበረሰቡን አባላት የሚገዙ፣ የሚያስተዳድሩ፣ የሚያስተምሩ፣ ወዘተ. ማህበራዊ ህግጋት ሆነው የሚያገለግሉ ደንቦች ይኖራሉ:: እነዚህ ህግጋት በማህበራዊ ተቋሞች ማለትም በጋብቻ፣ በቤተሰብ፣ በእድር፣ በሀይማኖት፣ ወዘተ. ውስጥ የሚኖሩትን ግለሰቦች ለተቋማቱ ህጎች ተገዥ እንዲሆኑ የማድረግ፣ ከዚህ ወጣ ለማለት ሲሞክር ደግሞ የማስጠንቀቅና የመምከር፣ ብሎም እስከመቅጣት የሚያደርስ ጫና የመፍጠር ሀይል ያላቸው ናቸው:: የነዚህ መገለጫዎች ደግሞ ስነቃላዊ ቅርፆች ናቸው:: ቀልዱናተረቱ፣ ዘፈኑና ጭፈራው፣ ቀረርቶው፣ እንጉርጉሮው፣ ወዘተ. የሚያንፀባርቋቸው ጉዳዮች፣ እነዚህን ህጎችና ደንቦች እንዲሁም ተቋማት አክብሮ ተግባራዊ ማድረግንና በውጤቱም መሞገስን፣ ከዚህ ውጭ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ትችትና ነቀፌታን መቀበልን፣ እስከ መገለል ማስከተልን ነው:: ይህም ከስነቃል ወይም ከፎክሎር ተግባራት መካከል የሚጠቀስ መሆኑ ይታወቃል::

በመሆኑም፣ በዚህ ምድብ ውስጥ ሴቶችንና ወንዶችን በስንፍናቸው የሚተቹ ቃልግጥሞች አንድ ላይ ተደራጅተው ቀርበዋል::እንደሚታወቀው ባህላዊ ጋብቻ ሴትና ወንድ ግለሰቦች የሚመሰርቱት ቤተሰባዊ ተቋም ነው::የጋብቻ ውሉና ስምምነቱ ከሴቷ አንፃር ‹‹ደጃፍ በመለሰ

ጓዳ በታቀፈ›› ያለውን ቤተሰባዊ ሃላፊነት በመሸከም ‹‹ በእንዝርቴ በደጋኔ ...›› ተብሎ ቃል የሚገባበት ነው:: ከወንዱ አንባር ደግሞ ‹‹በሞፈሬ በቀንበሬ፤ አርሽ አፍሼ የሚገኘው የጋራችን...›› ተብሎ የጋብቻ ውል ይፀድቃል:: ይህ ተቋማዊና ማህበራዊ ህግ ተጋቢዎቹ አምነው የሚቀበሉት ይሆናል:: ከዚህ እምነትና አስተሳሰብ ውጭ ሆነው የሚታዩት ደግሞ በዘፈን፣ በተረት፣ በቀልድ፣ ይተቻሉ፣ ይሰደባሉ፣ አጠቃላይ ከፍተኛ ማህበራዊ ነቀፌታ ያጋጥማቸዋል:: በተለይ ወንዶቹን የሚተቹት ቃልግጥሞች ከጋብቻ ጋር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሰርቶ ከመኖር፣ ራስን ከመቻልና፣ ቤተሰብን ከማኖር፣ ለሀገርና ለወገን አለኝታ እስከመሆን ድረስ የተጣለበትን ሃላፊነት አለመወጣትን፣ ጠንክሮ አለመከሰብን፣ ስነምግባራዊ ባልሆነ አስተሳሰብ መለከፍን፣ ጥገኛ መሆን መፈለግን፤ዋልጌና ሰነፍ መሆንን፣ የሚኮንኑ ናቸው::

ስነፍና በአንድ ሙያ ወይም ስራ ላይ ውጤታማ አለመሆን ነው:: በባህላዊ አስተሳሰብ ስንፍና ከልዩ ልዩ ተግባራት ጋር የተያያዘ ነው:: ሴቶች ይጋግራሉ፣ ይጠምቃሉ፣ ይፈትላሉ፣ ወዘተ:: እነዚህንና የመሳሰሉትን የሴቶች ተግባራት መወጣት የማይችሉት ሴቶች እንደ ሰነፍ ይቆጠራሉ፤ በማህበረሰቡ ዘንድ ይተቻሉ፣ ለቁምነገር አይታጩም:: በአርሶ አደር ህይወት ውስጥ የግብርና ስራ የሚፈልገውን ማንኛውንም ስራ ማከናወን ያለበት ወንድ ነው:: ቤተሰቡ ለችግር እንዳይጋለጥ የማድረግ ሀላፊነት በአብዛኛው በወንድ ላይ የወደቀ ነው:: ስለዚህ፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እንዲህ አይነቱን ተግባር መወጣት ካልቻሉ በሚኖሩበት ማህበረሰብ ዘንድ ይተቻሉ፣ ይሰደባሉ:: ከዚህ አንጻር ስንፍና ማህበራዊ ችግር ነው ማለት ነው::

ከስነ-ቃል ፋይዳዎች (ተግባራት) መካከል አንዱ በማህበረሰቡ አመለካከት ተቀባይነት የሌላቸውን ባህሪያት መተቸት፣ ማውገዝ፣ ማጥላላት፣ የመሳሰሉት ናቸው:: በማህበራዊ ተቋማቱ ተቀባይነት የሌላቸውን ተግባራትን ወይም ባህሪያትን የሚያሳዩ የማህበረሰቡ አባላት ይመከራሉ፣ ይማራሉ፣ ይተቻሉ፣ ይወገዛሉ፣ ወዘተ:: ይህም በምዕራፍ ስድስትና በክለሳ ድርሳናቱ የተጠቀሱትን የሚያረጋግጥ ነው ::

በመሆኑም ከዚህ በታች ባሉት አርኬዎችና መንቶዎች ስለ ሴቶች ስንፍና፣ የባልትና (የሙያ) ችሎታ ማጣት፣ አባካኝነት፣ ሆዳምነት፣ እንዲሁም ስለወንዶች ስንፍና፣ የጠባቂነት ፍላጎት፣ ወራዳነት፣ ሰበብ ፍላጊነት፣ ሴሰኝነት፣ ወዘተ. የሚያንፀባርቁ ቃልግጥሞችን እንመለከታለን:: እነዚህ መንቶዎችና አርኬዎች የተሰበሰቡት አንዳንዶቹ በዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ሰራተኞች ከተሰበሰቡ ሰነዶች ሲሆን፤ሌሎቹ መረጃ አቀባዮችን በመጠየቅ ነው::

6.2..2..1 ሴቶችን ብቻ የሚተቹ

አርኬ 57 ዘንድሮ ሚስቲቱን እኔ አግብቻታለሁ
ማልዶ ስንነሳ እኔ እቀድማታለሁ
በጧት ተነስቼ፣
በሮቹን ጠምጄ
ምራን ተበጥሶ ልቀጥል ብመጣ
አይኗን እየዳጠች ገና ደይ ልትወጣ
አርኬ 58 ውሃም እንዳትቀዳ ውሃ ልማት መጣ
እንጨት እንዳትሰብር ኩንታል ከሰል መጣ
ወፍጮም እንዳትፈጭ ካባሜንቶ መጣ
ወንዱ መነመነ ሴቱ ቂጥ አወጣ
ሸማግሌ ናና ይህን ጉድ ፍረደኝ
ምሳዋን ትብላና ቤቴን ትልቀቅልኝ
መንቶ 59 አራሹም እኔ ነኝ ፈጭታው ፈረንጅ
እንደው ለንትርክ ተጋብተናል እንጅ

እነዚህ ግጥሞች የሴትን ልጅ ስንፍና የሚያንፀባርቁ ናቸው። አርኬ 57 የሴቷን ሰንፍና የሚገልፀው በረቀቀ ስልት ነው። የመጀመሪያውን ስንኝ ስናነብ በጋብቻው የተደሰተ ይመስለናል። ወደ ሁለተኛው ስንኝ ስንሻገር ግን በባህላዊ አስተሳሰባችን ዘወትር የሚታወቅ ተግባር ይጠቀሳል። በባልና ሚስት ህይወት ወደ ምኝታ ቀድሞ የሚሄደው (የሚተኛው) ባል ነው። ሚስት የቤቷን እቃ ከዳድና ስትጨርስና ሌሎች ተግባራትን ካከናወነች በኋላ ነው የምትተኛው። እየሆነ ያለው ግን የተገላቢጦሽ ነው። ሁለተኛው ስንኝ ውስጥ ማታ ቀድማ የምትተኛው ሚስት ናት። ጧት ቀድሞ የሚነሳው ባል ነው። በአርሶ አደር ህይወትና የግብርና ተግባራት ወቅት ማለዳ ተነስታ ለገበሬዎችና ለሰራተኞች ምሳና ውሃ አዘጋጅታ መሸኘት ያለባት ሚስት ስትሆን በግጥሙ ውስጥ ይህን ተግባር መወጣት አልቻለችም። በመሆኑም፣ የስንፍናዋ መጠን የሚገለፀው በመጨረሻው ስንኝ ነው። ገበሬው የግብርና ስራውን በጧት ተንስቶ በማከናወን ላይ ሳለ(እርሻውን በማረስ ላይ) ከግብርና እቃዎቹ አንዱ (ምራን) ስለተበላሸበት ሌላ ምራን ከቤቱ ወስዶ ስራውን ለመቀጠል እቤት ሲመጣ ሚስቱ ገና ከእንቅልፏ ተነስታ ወደ መፀዳጃ ለመሄድ ስትነሳ ያገኛታል። ከግጥሙ ሀሳብ በመነሳት

ምናልባት ረፋድ ላይ ይሆናል። ማታም በጊዜ ቀድማ ትተኛለች፤ ጧትም አርፍዳ ትነሳለች። ሚስት የአጋርነት ድርሻዋን የምትወጣ አልሆነችም ማለት ነው።

ከዚህ አርኬ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ያለው ደግሞ፣ አርኬ 58 ነው። በዚህ አርኬ ውስጥ የቅናት ስሜት የተቀላቀለበት ሀሳብ ተንፀባርቋል። «ውሃ ልማት» ና «ካባሜንቶ» የሚሉት ቃላት ከእድገት ጋር የተያያዙ ሀሳቦች የተገለፁባች ናቸው። ውሃ ልማት ማለት፣ የቧንቧ ውሃ ማለት ሲሆን፣ በየቤቱ ወይም በጋራ አንድ አካባቢ የሚገኝ ነው። ካባሜንቶ ማለት ደግሞ ዘመናዊ የእህል ወፍጮ ነው። እነዚህ የልማትና የእድገት ውጤቶች የሴቶችን የስራ ጫና በእጅጉ ቀንሰዋል። ቀደም ባለው ጊዜ (ምናልባት አሁንም) ሴቶች የማገዶ እንጨት ለማምጣት ወደ ጫካ (ዱር) ይሄዳሉ። የመጠጥ ውሃ ለመቅዳት ወንዝ ወዳለበት ሂደው በጀርባቸው ተሸክመው ይመጣሉ። ለምግብ የሚሆን እህልና ለወጥ የሚሆን ጥራጥሬ በድንጋይ ወፍጮ ይፈጫሉ። ከእንደነዚህ አይነቶች አድካሚ ስራዎች ለጊዜውም ቢሆን ሴቶች ነፃ የመሆን እድል ስለተፈጠረላቸው በወንዱ በኩል ድጋፍ ያገኘ አይመስልም። ወንዶች በአድካሚ የስራ ሁኔታ ውስጥ በመኖራቸው የአካል ጉስቁልና ገጥሟቸዋል። በአንፃሩ ሴቶች በተሻለ የአካል ሁኔታ ላይ ናቸው። ሴቷ ምንም ስለማትሰራለት ጋብቻው እንዲፈረስ ወንዱ ይጠይቃል።

ከስንፍናዋ በተጨማሪ ባህሪዋ የማይመች መሆኑ የተገለፀው በመንቶ 59 ነው። ይህ መንቶ ከአርኬ 58 ጋር ይያያዛል። በመጀመሪያው ስንኝ ውስጥ ‹‹...ፈጭታው ፈረንጅ›› የሚለው ሀረግ በአርኬ 58 ውስጥ በተጠቀሰው ‹‹ካባሜንቶ›› ጋር ተመሳሳይ ነው። ‹‹ፈረንጅ›› የሚለው እህሉን ወደ ቋቱ እያስገባ የሚያስፈጨውን ባለሙያ ማለት ነው። «በውጭ ያለውን የጉልበት ስራ የምሰራው እኔ፣ በቤት ያለውን ስራ የሚሰራው ሌላ፣ የእኔና የአንቺ ጋብቻ ምን ፋይዳ አለው፤ ከጭቅጭቅና ከንትርክ በቀር ጥቅም የለውም» የሚል ነው።

ከዚህ በታች በተጠቀሱት መንቶዎች ውስጥ የሴቶች ሙያ-ቢስነት፣ ሆዳምነት፣ አባካኝነት ተገልፆ ይገኛል።

መንቶ 60 አጓምዳና አጓምዳ የጋገሩት ቂጣ
ካሪያው ተለምጦ በመሳጊያ ወጣ
መንቶ 61 ሴቶች ተማሩና ሆኑ ፍርድ ሸንጎ
እንግዲህ ደህና ሁን ድስትና ምጣኻ

መንቶ 62 ከዘራሁት እህል ዳጉሳ ነፍስ አውቆ
ድርሱልኝ አለይ ጉሮሮዋን አንቆ
መንቶ 63 እንደው ወጣ ገባ በይበት ኸቤቱ
የሞያውን ነገር ያውቃል ጎረቤቱ

በመንቶ 60 ውስጥ ቂጣውን የሚጋግሩት ሴቶች ሁለት ናቸው። ባህሪቸው ወሬኛ መሆኑን በመጀመሪው ስንኝ ‹‹አንምዳና አንምዳ» በሚሉት ቃላት ተጠቁሟል። አንምዳ ማለት ውሸታም፣ ወሬኛ እንደማለት ነው። እነዚህ ሁለት ሴቶች የጋገሩት ቂጣ በጣም ወፍራም በመሆኑ ከምጣዱ ለማውጣት አስቸጋሪ ሆኗል። የመሰቅሰቂያ ካሪው አልችል ብሎ፣ በመሳጊያ ነው የወጣው። «መሳጊያ» ማለት ትልቅ ጠፍጣፋ መሳይ (እንደ ጣውላ ያለ) እንጨት ነው። የሴቶቹ ሙያ-ቢስነት የተፈተነው ወይም የተገለፀው በቂጣ መጋገር ተግባር እንጅ የሴቶችን ሙያ በእጅጉ በሚጠይቀው በእንጀራ መጋገር ሙያ አይደለም። ይህንን ሙያ የሚጠይቀው የሴቶች ስራ በመንቶ 61 ላይ ቀርቧል።

ይኸ መንቶ የተነገረው በ1970ዎቹ ጀምሮ ባሉት አመታት ውስጥ እንደሆነ ይታወቃል። በደርግ ዘመን ሴቶች በማህበር ተደራጅተው ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያደርጉ እንደነበር ይታወሳል። ይህም የሚጠቁመው በመንቶው የመጀመሪያ ስንኝ ውስጥ ነው። በወቅቱ በገበሬ ማህበራት ውስጥ ከሚደራጁት የዳኝነት ስርአቶች አንዱ ፍርድ ሸንጎ የሚባለው ነው። ይህም ዝቀተኛው የፍትህ ስርአት መሆኑ ነው። በዚህ ውስጥ የሴቶች ማህበራት አመራር የሆኑ ሴቶች በሸንጎ አባልነት ይሳተፉ ነበር። በመሆኑም የቤት ውስጥ ስራቸውን መስራት ባለመቻላቸው ወይም ባለመፈለጋቸው ምክንያት የተገጠመ ነው ማለት ይቻላል። ድስትና ምጎጎ የሚሉት ቃላት ወጥ መስራትንና እንጀራ መጋገርን የሚያመለክቱ ናቸው። የመንቶ ሀሳብ ከሙያ ቢስነት በተጨማሪ፣ ፖለቲካዊ ተቃውሞ የተንፀባረቀበት ነው።

በመንቶ 62 የተገለፀው ሀሳብ የሴቷን ሆዳምነት የሚያመለክት ነው። ሆዳምነቷን ከሌሎች የእህል ዘሮች የሚዘጋጁ ምግቦች ሊቋቋሙት አልቻሉም። በሴቷ ሆዳምነት የተበሳጨው የዳጉሳ እህል (ዳጉሳ በሰውኛ የቀረበ ነው)፣ ሆዳሟን ሴት ጉሮሮዋን ያንቃታል። እንደሚታወቀው ከዳጉሳ እህል የሚዘጋጅ ምግብ በጣም ደረቅ በመሆኑ በቀላሉ የሚበላና የሚዋጥ አይደለም። በቀላሉ ለመዋጥ እንዲቻል፣ የሚያርሰው ነገር ይፈልጋል። ሴቷ ግን ሆዳም ከመሆኗ የተነሳ የምግብ ምርጫ እንኳ የሌላት መሆኑን እንረዳለን። መንቶ 63 ከላይ በቀረቡት መንቶዎች ውስጥ የተገለፀውን ሙያ-ቢስነት አጠቃሎ ያሳያል። ይኸውም የሴቷ

በቤት ውስጥ መኖር ‹‹ሴት አለች›› ከማለት ያለፈ ፋይዳ የለውም፤ በማለት ይገልፀዋል፡፡ መንቶው እንደሚገልጸው፣ የሴቷን ሙያ-ቢስነት በጎረቤት ያለው ሰው ሁሉ የሚያውቀው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህ በታች ባሉት መንቶዎች የሴቷ ሱሰኛነትና የፈትል ሙያ ችሎታ የሌላት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ዘመናዊ አልባሳት ባልነበሩበት ዘመን የቤተሰቡ አባላት የሚለብሱት ልብስ የሚሰራው እናቶች ከሚፈትሉት ፈትል ነው፡፡ በተለይ አባውራው የሚለብሰውን ጋቢ እና ጎንቢሶ ፈትሎ የማሰራትና የማልበስ ሃላፊነት የእማውራዋ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በገጠር አካባቢ አሁንም እንዳለ ነው፡፡ መንቶዎቹን እንመልከት፡፡

መንቶ 64 ጀበና ታቦቱ ሲኒ ልቃቂቱ
መገነጣ ጠፋ እናቷ ቢሞቱ
መንቶ 65 ማለዳ ተነስተሽ ቡና ቡና በይ
የጥጡማ ነገር ቀርቶ የለም ወይ
መንቶ 66 በአስራ አምስት አመቷ ብታሰራ ኩታ
እናትና አባቷ ሊሞቱ በደስታ

የሴቷ ቡና ሱሰኛነት እጅግ በተጋነነ ሁኔታ ቀርቧል፡፡ በመንቶ 64 እና 65 የተገለፀው ይኸው ነው፡፡ ለሷ ጀበና እና ሰኒዎቹ ከምንም በላይ ናቸው፡፡ እንደታቦት ታምንባቸዋለች፣ ቀኑን ሙሉ ቡና እያፈላች ብትውል የምትደሰት ይመስላል፡፡ ይህ የቡና ሱሰኛነቷ ተጋልጦ የሚታየው በችግር ጊዜ ነው፡፡ በህይወት ሂደት ሞት የማይቀር ነው፡፡ በማህበራዊ ህይወት ወይም በቤተሰብ ደረጃ የሞት አጋጣሚ ሲመጣ የሟችን አስክሬን በተገቢ ሁኔታ እንዲዘጋጅ የሚደረግ ሃላፊነት በቤተሰብና በጎረቤት ወይም በወዳጅ ዘመድ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

ሟቹን ማማሟት፣ መገነዝ፣ ማጠብ፣ መከፈን፣ በሞት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡ ለመግነዝ የሚሆነውን ፈትል፣ ለከፈን የሚሆነውን ጨርቅ፣ የማቅረብ ሃላፊነት የቤተሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ሁለት መንቶዎች የሴቷ ሙያ-ቢስነት እና የቡና ሱሰኛነት ከመንፀባረቁ በተጨማሪ ቤተሰባዊ ገበናዋ ተጋልጦ የታዩባቸው ናቸው፡፡ ፈታይ እናቶች ለአንድ ጋቢ የሚሆን ፈትል (ልቃቂት) የሚያደርሱት (ያውም ከሌሎች ተጓዳኝ ስራዎች ጋር) ቢበዛ በሁለትና ሶስት ወራት ይሆናል፡፡ መንቶ 66 ግን ይህንን ሁኔታ እጅግ አጋኖ ያመለክታል፡፡ ለአንድ ኩታ የሚሆን ፈትል ከወራት አልፎ አመታት እንደፈጀ ነው የተገለፀው፡፡ አቀራርቡ

ግነትና ስላቅ ያለበት ነው፤ ግነቱ በፈጀው አመት ሲገለፅ፣ ስላቁ ደግሞ በወላጆቿ ደስታ ተንጸባርቋል፡፡

ከሙያ-ቢስነት እና ሱሰኛነት ሌላ የሴቶች አባካኝነት በተከታዮቹ ግጥሞች ተንፀባርቆ ይገኛል፡፡ ሙያ-ቢስነቱ የሚያያዘው ከፈትል ችሎታ ጋር ነው፡፡ የፈትል ችሎታ (ሙያ) በማህበረሰቡ አባላት እንደ ትልቅ ሴትነት (ባለሙያነት) የሚያስቆጥር ይመስላል፡፡

መንቶ 67 እንደ አገልግሉ ጥጥ ጤፍ ቢበረክት
አመት በበላን ሳንለፋ ሳንታክት
መንቶ 68 ጣቷ ረጃጅም ነው ቂጣ ለመጋገር
እንዝርት አታሳዩዋት ትጠፋለች ካገር
መንቶ 69 ጤፍ ብሸምትላት ምንም አልጠቀማት
ጥጥ ብመዝንላት አመት አከረማት
መንቶ 70 የእንቅልፍ አጀቡ ባል በሩቅ ያስታውቃል
ከእግር እስተራሱ ባቡጀዲ ደምቋል

እንደ ላይኞቹ ግጥሞች የሙያ ቢስነትና የሆዳምነት ትችቶች በነዚህ መንቶዎችም ተንፀባርቆ ይገኛል፡፡ መንቶ 67 የሚያመለክተው የፈትል ሙያ የሌላት መሆኑን ነው፡፡ አንድ አገልግል ጥጥ ፍትሎ ለመጨረስ ብዙ ጊዜ እንደሚፈጅባት ነው፡፡ ለዕለት ቀለብ የሚሆነው የጤፍ እህል ግን በአጭር ጊዜ ያልቃል፡፡ ቁጠባ እሚባል ባህል አታውቅም ወይም ሆዳም በመሆኗ እህሉ አይበረክትም ማለት ነው፡፡ ይኸው ፈትል የመጥላት ሀሳብ በመንቶ 68 እንደገና ይነሳል፡፡ በባህሉ ወይም በልማድ እንደሚታወቀው የእጅ ጣታቸው ረጃጅም የሆኑ ሴቶች (እናቶች) የፈትል ሙያ ችሎታ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመንቶው የተጠቀሰችው ሴት ግን የጣቷ መርዘም ለቂጣ መጋገር እንጂ ለፈትል አይሆንም፡፡ የመንቶ 69 ሀሳብ ከሁለቱ መንቶዎች ሀሳብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በየትኛውም ማህበረሰብ ዘንድ ስንፍና ተቀባይነት ያለው አይደለም፤ በአደባባይ ያስተቻል፣ ያሰድባል፣ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ችግር ያስከትላል፡፡ የባል ድክመት በሚስትና በቤተሰብ አባላት ላይ ችግር እንደሚያስከትል ሁሉ፣ የሚስት ስንፍናም በባልና በቤተሰብ አባላት ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ በመንቶ 70 ላይ የተንፀባረቀው ጉዳይ ይህንን የሚመለከት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ አቡጀዲ አባውራ የሚለብሰው የልብስ አይነት ሳይሆን

ልጆችና የከብት እረኞች የሚለብሱት ነው። በባህላዊ ፈትልና በሸማኔ የሚሰራ አይደለም፤ ከገበያ ወይም ከመደብር የሚገዛ ነው። እንዲህ አይነቱ ልብስ በእድሜ ወደ ጎልማሳነት ደረጃ የደረሱ አባውራዎችና ፈታይ ሚስት ያላቸው ባሎች አይለብሱትም። የአባውራው አለባበስ የእማውራዋን ሙያ ያንፀባርቃል ማለት ነው። እንቅልፋም በመሆኗ ወይም የፈትል ሙያ ስለሌላት፣ ባሏ የታጠቀው ጎንቢሶ፣ የለበሰው ጋቢ አቡጀዲ ነው።

ከዚህ በላይ በምሳሌነት እየተጠቀሱ በተብራሩት ቃልግጥሞች የሴቶች ሙያ ቢስነት፣ ሆዳምነት፣ አባካኝነት፣ የመሳሰሉት እንከኖች ተንፀባርቀዋል። እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ያስድባሉ፤ ያስንቃሉ፤ ማለት ይቻላል። የቃልግጥሞቹ ፋይዳም ከዚሁ ሀሳብ የሚመነጭ ይሆናል። በትዳር ህይወት ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች እንደነዚህ አይነት ድክመቶች እንዳይገኙባቸው ያስጠነቅቃሉ፤ ያስተምራሉ።

6.2..2..2 ወንዶችን ብቻ የሚተቹ

በብዙ ማህበረሰቦች አመለካከት የወንዶችና የሴቶች የስራ ድርሻዎች ተለይተው ይታወቃሉ። አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች ከፍተኛ ጉልበትና ጥንካሬ በሚጠይቁ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። ከቤት ውጭ ያለውን የስራ ሃላፊነት ወስዶ ቤተሰብን ማስተዳደር የወንድ ድርሻ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህንን ቤተሰባዊና ማህበራዊ ሃላፊነት የማይቀበል ወይም የማይወጣ ወንድ ማህበራዊ ነቀፌታ ይደርስበታል። ማህበራዊ ነቀፌታዎቹ የሚገለፁት በማህበረሰቡ አባላት በሚነገሩ ስነ ቃላዊ ቅርፆች አማካኝነት ይሆናል። በቃልግጥሞ ይዘፈንበታል፤ ወይም ይዘፈንለታል። የሚዘፈንበት ማህበረሰቡ እንደ ነውር የሚቆጥራቸውን ተግባራት አድርጎ ሲገኝ ነው፤ የሚዘፈንለት ደግሞ ጥሩ የሚባሉትን ሲያደርግ ነው። በመሆኑም ከዚህ በታች ባሉት ቃልግጥሞች ውስጥ፣ ወንዶች እንዴት እንደተተቹ እንመለከታለን።

መንቶ 71 አያርስም ወይ አይጠምድም ወይ ማልዶ
ፈትተሽ ነይ ይላታል የሴት ጥሬ ለምዶ
መንቶ 72 አያርስም ወይ አይጠምድም ወይ ማልዶ
ማን ፈታይ የሚለው የሴት ጥሬ ለምዶ
መንቶ 73 አጋሙን መንጥሮ እንዳይዘራ እህል
አሻግሮ ይመኛል የሰውን ክምር

በነዚህ ሶስት መንቶ የተንፀባረቀው አጠቃላይ ሀሳብ በራሱ ድካምና ልፋት ያልተገኘን ሃብት ወይም የሌሎች ሰዎች የድካም ውጤት የሆነን የምርት ውጤት መመኘት ላይ የተመሰረተ ነው። በፍች ጊዜ የሚፋቱት ባልና ሚስት ያፈሩትን ሀብት ይካፈላሉ። በእንዲህ አይነት ቤተሰባዊ ችግር፣ አጋጣሚውን ለመጠቀም የሚፈልጉ ግለሰቦች አይታጡም። በፍች ጊዜ ሴቷ የምትካፈለውን እህል ለመጠቀም የሚከጅል ወንድ የተፈታችውን ሴት ያገባል። ይዛው የመጣችው እህል ሲያልቅ ጋብቻው ይፈርሳል። በእንዲህ አይነት አስተሳሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ጥረው ግረው የራሳቸውን ሀብት ከማፍራት ይልቅ የሌሎችን አሻግሮ በማየት የተጠመዱ ናቸው። መንቶ 71 እና 72 ይህንኑ ያሳያሉ። ሁለቱም ተመሳሳይ መልክት ያላቸው ናቸው። አርሶና አንደፋረሶ ህይወቱን እንደመምራት ሌሎች የለፉበትን በመመኘት ጊዜውን ያሳልፋል ማለት ነው። እነዚህ ተመሳሳይ መንቶዎች በርትቶ ማረስን፣ መከሰብን፣ የሚመክሩ ሲሆን፣ ባንፃሩ የሌሎችን የልፋት ውጤት ለመቀማት መፈለግ ጥሩ እንዳልሆነ ይተቻሉ። የእነዚህን መንቶዎች ሀሳብ በሚያጠናክር ሁኔታ መንቶ 73 በተለየ መንገድ ተገልጿል። ይህም «ለእርሻ የሚሆን መሬት በራሱ ጥረትና ልፋት አልምቶ የራሱ የሚሆን የሰብል እህል ማምረት እየቻለ፣ ለምን የሌሎችን የስራ ውጤት እየተመኘ ይኖራል» የሚል መልክት ያለበት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት መንቶዎች ደግሞ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደመጥፎ የሚታዩ ባህሪያትና ተግባራት ተንፀባርቀው ይታያሉ። የተንፀባረቁት መጥፎ ባህሪያት፣ ወሬኛነት፣ ሰርቆት፣ የማይሆኑ ምክንያቶን በመደርደር ቤተሰብን ለችግር ማጋለጥ፣ በመንቶዎቹ ተመልክቷል። የሚከተሉትን እንመልከት።

መንቶ 74 ምን ያደርግልሀል የምላስ ጉልበት
አጋሙን መንጥረህ እህል ዝራበት
መንቶ 75 ማረስ ነው እንጂ እጅ እስቲቆስል
ምንድን ነው መላስ ውሻ ይመስል
አርኬ 76 ሰኔን ጠሀይ ፈራ ሀምሌ ጭቃ ፈራ
ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ
ልጁስ አለቀሰ እንደው ዝም ብሎ
ከራብ የበለጠ ምን ጅብ አለ ብሎ

መንቶ 74 ላይ በመነሻው ስንኝ ባለው የመጨረሻ ሀረግ ‹‹የምላስ ጉልበት›› የሚለው፣ ፍችው ወሬኛነት ማለት ነው። ወሬኛነት ምንም የሚያስገኘው ጥቅም የለም። ከዚህ ይልቅ ዱሩን፣ ጫካውን መንጥሮ፣ አርሶና አለስልሶ እህል ቢዘራ ተጠቃሚ እንደሚሆን ይሞክራል። መንቶ 75ም እንዲሁ ጠንክሮ መስራትን የሚመክር ይዘት ያለው ነው። ወሬኛነት የተነሳዐረው ከውሻ ተግባር ጋር ነው። ውሻ በየቦታው እየዞረ ያገኘውን እንደሚቃርም ሁሉ፣ ስራ የማይወድ ሰውም እንዲሁ፣ ያገኘውን እየለመነ፣ እየቀላወጠ ያስቸግራል። ‹‹ ምንድን ነው መላስ›› የሚለው ሀረግ መጨረሻ ላይ ያለው ቃል ሲነበብ ‹‹ ምላስ›› ወደሚል ይጠጋል። ምላስ፣ ማለት የሆነውንና ያልሆነውን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላ ሰው በማስተላለፍ፣ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖር የሚያደርግ ተግባር ነው።

አርኬ 76 ላይ የተነሳው ሀሳብ ከቤተሰባዊ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው በቤተሰብ ህይወትና ሃላፊነት ውስጥ የአባት ድርሻ ከፍተኛ ነው። አባት የልጆቹንና የቤተሰቡን ፍላጎቶች የማሟላት ግዴታ አለበት። በግጥሙ ውስጥ ግን አባት ይህንን ቤተሰባዊ ግዴታ ሲወጣ አይታይም። ለዚህ ምክንያቱ ወቅቱን ጠብቆ የግብርና ተግባሩን ባለማከናወኑ ነው። በሰኔ የፀሃይ ሀሩር ከፍተኛ ነው። በክረምት ጭቃው አስፈጋሪ ነው። እነዚህን ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎ እንደ ሰበብ እያደረገ፣ እነሱን ተቋቁም የግብርና ስራውን ማካሄድ አልቻለም። ይህ የግብርና ስራ በወቅቱ ባለመከናወኑ ለልጅቱና ለቤተሰቡ ቀላል የሚሆን ምርት ማምረት አልቻለም። በመሆኑም ልጆቹ ለርሀብ ተዳርገዋል። ልጆቹን የምግብ ጥያቄ ለማስቆም የሚጥረው በጅብ እያስፈራራ ነው። ነገር ግን ልጁ ርሀቡ ስለጠናበት በርሀብ ከመስቃየት በጅብ መበላትን ይመርጣል።

እንዲህ አይነቱ ችግር (ሃላፊነትን አለመሸከም) በማህበረሰቡ ዘንድ ያስገምታ፤ ያስንቃል፤ ያሰድባል። በተከታዮቹ መንቶዎች የወንዶች የስንፍና ሁኔታ የሚንፀባረቀው በተለየ መንገድ ነው። ይኸውም ለድህነቱ ምክንያት ወይም ተጠያቂ የሚያደርገው እሱን እራሱን ሳይሆን ሌሎችን ነው።

መንቶ 77 ሲቆፍሩ አይቆፍር ሲያርሱ አያርስምና
ሰው ዋለብኝ ይላል መላ ተገኘና
መንቶ 78 ተጋድሞ እየዋለ ከቤቱ በላይ
ውለውብኝ ይላል አያጣም ጠንቋይ

በአንዳንድ ሰዎች አመለካከት ባለፀጋነት (ሀብታምነት) ጥሮ-ግሮ የሚገኝ ሳይሆን በተለየ አጋጣና ሁኔታ እንደሚገኝ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በአንዣሩ ለድህነት ምክንያት ተደርገው የሚመካኝ አጉል እምነቶ አሉ፡፡ በነዚህ ሁለት መንቶዎች ለድህነት ሰበብ ተደርጎ የሚጠቀሰው «እንዳልሰራ ባለጋራ በድግምት አፈዘዘኝ፣ አስደገመብኝ›› እንጂ የሚል ማምለጫ ምክንያት ያቀርባል፡፡ በአንደኛው መንቶ (77) «እንደ ማምለጫ ወይም ማመካኛ ሲሆን፣ በሁለተኛው መንቶ አዋቂ (ጠንቋይ) ነገረኝ» በሚል ስንፍናውን ይሸፍናል፡፡

በተከታዮቹ መንቶዎች የወንዱ ስንፍና የሚነገረው ከአለባበሱ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ነው፡፡ ታታሪ ገበሬ በስራ ወቅት ለስራው ተስማሚና ምቹ የሆኑ የስራ ልብሶቹን ለብሶ የግብርና ስራውን ያከናውናል፡፡ በአንዣሩ ሰነፎች አለባበሳቸውን ማሳመር እንጅ፣ ሙያ ቢስ መሆናቸውን የሚከተሉት መንቶዎች ያመለክታሉ፡፡

መንቶ 79 በቦላሌ ሱሪ መይ ታድርልህ አለይ
ከረጅም ጭንቁላ እጂን ካልከተተይ
መንቶ 80 ከንፍሮው ጭንቁላ እጂን ካልዶሏት
ሴት አትቀመጥም ጉንጪን ቢስሚት
መንቶ81 የላሬ ዘበን ልጅ እናቱ አኮራችው
የሽ ብር ሸርጥ እያስታጠቀችው
መንቶ 82 በሽ ብር ሸርጥ እያለ እርሽም እርሽም
እናቱ እምትበላው ቁና ጤፍ አላሸም
መንቶ 83 እነ ባለ ሸርጥ እነጣቱ ለምለም
ኸቤቱ ሲገባ እሚቀመስ የለም

መንቶ 79 እና 80 ተመሳሳይ ሀሳብ የተንፀባረቀባቸው ናቸው፡፡ ሴቶችን ወይም ሚስትን በትዳር ህይወት ውስጥ ለማቆየት የሚቻለው በቤት ውስጥ የምግብ እህል እንደልብ ሲገኝ ነው ይላሉ፡፡ በመንቶቹ ውስጥ ‹‹ጭንቁላ›› ማለት ከሸክላ የተሰራ ትልቅ የንፍሮ መቀቀያ እቃ ነው፡፡ መጠኑ እንስራ ወይም ትልቅ ገንቦ ያህላል፡፡ ‹‹ከረጅም ጭንቁላ ወይም ከንፍሮ ጭንቁላ እጂን ካላስገባች ማለት የንፍሮ እህል በብዛት ቀቅላ፣ ለራሷ፣ ለልጅቷ ወዘተ.. ማብላት የሚስችላትን እህል ከላገኘች እንደማለት ነው፡፡ የግጥሙ አላማ የሚያነጣጥረው ወደ ወንድየው ነው፡፡ ልብስህን አሳምረህ (ቦላሌ ሱሪ) እወድሻለሁ አፈቅርሻለሁ፣ እያልህ ብታባብላት ዋጋ የለውም፡፡ አርስህና አምርተህ፣ የምግብ እህል እንደልብ ስታቀርብ ነው፤ አንተ ግን ሰነፍ ነህ

የሚል ማህበራዊ ትችት ያለበት ነው። ግጥሞቹ ሚስት አግብተህ በትዳር ለመኖር ከፈለግህ ጎበዝ ገበሬ መሆን አለብህ የሚል መልክት ያላቸው ናቸው።

መንቶ 81 ባሉት ስንኞች ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ልብስ አለ። እሱም ሸርጥ ነው። ሸርጥ በፋብሪካ የሚሰራ ሲሆን፣ ቀደም ባለው ጊዜ የስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ ሰዎች ይለብሱት የነበረ ነው። የጥራት ደረጃው የተለያየ ስለሆነ ዋጋውም እንደዚው ነው። አሳበረንዳ የሚባለው ሸርጥ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለውና በውድ ዋጋ የሚገዛ ነው። በከፍተኛ ዋጋ የሚገዛውን ሸርጥ የሚለብሱ ሰዎችም የኢኮኖሚ ደረጃቸውን አመላካች ነው። ሀብታም ሰዎች ወይም የሀብታም ልጅ የሆኑት ናቸው፣ በውድ ዋጋ የሚገዛውን ሸርጥ የሚታጠቁት። ይህ አለባበስ በአካባቢው ወጣቶች አመለካከት እንደ ፋሽን የሚቆጠርም ነው። የግጥሞቹ ሀሳቦች፣ ፋሽን (ዘመናዊ አለባበስ) ተከታይ የሆነው ወጣት አርሶ አደር፣ የግብርና ሰውን ትቶ አለባበሱን ብቻ አሳምሮ ይኖራል እንጅ ለቤተሰቦቹ የሚሆን ምርት እያመረተ አይደለም የሚል ነው። መንቶ 81 እንደሚነግረን አሁን ያሉት ወጣቶች በወላጆቻቸው ትክሻ ላይ የሚኖሩ ናቸው የሚል ነው። የዛሬ ዘበን ልጅ ማለት አሁን ባለንበት ጊዜ ያለ ወጣት ወይም ትውልድ ማለት ነው። ይህ ትውልድ ራሱን ችሎ የሚኖር አይደለም። በልማዱ እንደሚባለውም ለአንዳንድ ልጆች መበላሸት ተጠያቂዎች እናቶች ናቸው። ‹‹... እናቱ አኮራችው/ የሽ ብር ሸርጥ እያስታጠቀችው›› የሚለው ሀረግና ስንኝ ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው።

መንቶ 82 እና 83 ደግሞ የሚያመለክቱት ይኸው የዘበኑ ወጣት በምርት ስራ ላይ የማይሳተፉ፣ ራሱን ያልቻለ፣ ቤተሰቡን የማይደግፍ ሰነፍ መሆኑን ነው። ‹‹እርሽም እርሽም›› የሚለው ቃለ አረማመዱን የሚመለክት ነው። ሲሄድ ቀብረር፣ ኮራ ብሎ ነው። ኩራቱ ግን ባዶ መሆኑን ሁለተኛው ስንኝ «ለእናቱ ቀለብ የሚሆን አንድ ቁና ጤፍ እንኳ አላመረተም» በማለት ያጋልጠዋል። ይህ ወጣት ስራ የማይወድ መሆኑ የተጠቆመበት ሌላው ማሳያ ‹‹ እጣተ ለምለም›› የሚለው ሀረግ ነው። ጣተ ለምለም ማለት የእጅ ጣቶቹ በጣም ለስላሳ የሆኑ ማለት ነው።

በአጠቃላይ የግጥሞቹ መልዕክቶች ራስንና ቤተሰብን ለማኖር በርትቶ መስራትን የሚያስገነዝቡ ናቸው። አለባበስን ማሳመር ብቻውን ማህበራዊ ተቀባይነት የማይኖረው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ትዳርን ለመምራት፣ ቤተሰብን ለመርዳት በርትቶ መስራት ያስፈልጋል የሚል መልዕክት የተንፀባረቀባቸው ግጥሞች ናቸው።

በሚከተሉት ሁለት መንቶዎች ወንዶች ሰነፍ ብቻ ሳይሆኑ ሴሰኞች እንደሆኑ የሚያለክቱ ናቸው። ስንፍናም ሆነ ሴሰኝነት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚጠሉ፣ የሚተቹ፣ እንደ ነውር የሚቆጠሩ ተግባራት ናቸው ማለት ይቻላል። መንቶዎችን እንመልከት!

መንቶ 84 ማለዳ ተነስተህ በሮችህን ንዳ
ሴትን ቢጠብቁት አይከፈልም አንድ እዳ
መንቶ 85 እነግራለሁ እንጂ እኔ አላሸሚጥጥም
ሴት ያበዛ ጎበዝ ሩጦ አያመልጥም

የመጀመሪያው ግጥም፣ የመነሻው ስንኝ የሚገልፀው ሀሳብ በጧት ተነስተህ በሮችህን ጥመድና እርሻህን እረስ የሚል ነው። ጎበዝ ገበሬ ሌሊት ተነስቶ በሮችን አብልቶ፣ ወደ እርሻው ከሄደ በኋላ፣ ወቅት ሳያልፍ መሬቱን አርሶና አለስልሶ ለዘር ዝግጁ ያደርጋል። በደንብ በተዘጋጀ ማሳ ላይ የሚዘራ ዘር (እህል) ጥሩ ምርት ያሳገኛል። ምርት ከተገኘ ደግሞ ማንኛውንም ማህበራዊና ቤተሰባዊ ጉዳይ ለማሟላት ያስችላል። በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰው ወንድ ግን ከዚህ ተግባር የራቀ ይመስላል። ‹‹ ሴትን ቢጠብቁት...›› የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው ከሴት ጋር መዋልን፣ ሴሰኝነትን ነው። ከሴት ጋር መዋል የሚያስገኘው ማህበራዊ ፋይዳ የለም፤ እንዲያውም መጥፎ ስም ያሰጣል።

መንቶ 85 ይህኑ ማህበራዊ ነቀፌታ በተለየ መንገድ ይጠቁማል። ‹‹ ሩጦ ማምለጥ፤ አባሮ መያዝ›› የወንድነት መለኪያ ተደርጎ ይታሰባል። ሴሰኛ ወንድ ጉልበቱ በወሲብ ያልቃል ተብሎ ሰለሚገመት ለከፍተኛ ማህበራዊ ተግባር አይመረጥም። ማህበራዊ ተቀባይነቱ ዝቅተኛ ነው፤ ለጋብቻ፣ ለእርሻ ስራ፣ ለጦርነት፣ በአጠቃላይ ወንድ ልጅን ለሚፈትኑ ተግባራት አይመረጥም፤ አመኔታ የሚጣልበትም አይሆንም ማለት ነው። በመሆኑም በሁለቱ መንቶዎች የተላለፈው መልክት ስንፍናና ሴሰኝነት ማህበራዊ ተቀባይነት ስለሌላቸው ከነዚህ ባህሪያት ነጻ በመሆን፣ ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው ተግባር ላይ ተሰማርተህ ኑር የሚል ነው። የሚከተሉት መንቶዎች ስንፍናን ለየት ባለ አገላለፅ ያቀርባሉ። ላይ ላዩን ሲታዩ አትረስ፣ አትስራ የሚሉ ይመስላሉ። ሀሳቡን ስንመረምር ግን ከዚህ በተቃራኒ የሆነ መልክት አላቸው።

መንቶ 86 አንተ አትረስ ይረስ አገሩ
ያንገላታህል እርፍና ጓሉ

መንቶ 87 አንተ አትረስ ይረስ አባትህ
አፈር ይነካል ቦቼሌው ባትህ

‹‹አንተ አትረስ...›› የሚለው ሀረግ ተጠቃሹን ወንድ እንዳይንገላታ አስበውለት፣ አዝነውለት፣ ወዘተ. ሳይሆን፣ ሲያሸሚጥጡት ነው፡፡ እርሻ ማረስ ከእርፍና ከጓል ጋር መታገልን፣ ጉልበትና ዕናትን የሚጠይቅ፣ በፀሀይ መቃጠልን፣ በጭቃ መጨማለቅን የሚያስከትል የግብርና ስራ ነው፡፡ አገዳና ጋራጣው እግርን ይወጋል፣ ጓሉ ያንገላታል፣ ጎንበስ ቀና ማለቱ ወገብ ይቆርጣል፡፡ ስለዚህ አንተ አትረስ ሲል ይህንን ፈታኝ ተግባር የሚችል ወንድነትና ብርታት የለህም፤ለፈስፋሳ ነህ ማለቱ ነው፡፡ ‹‹ ቦቼሌው ባትህ›› ማለት የሚያምረው፣ ወፍራም ባትህ ማለት ነው፡፡ እርሻ የምታርስ ከሆነ የእግርህ ውበት ይበላሻልና አትረስ የሚል ይመስላል፡፡ በባህሉ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ አባቱን ያግዛል፤ ለወንድሞቹ ጋሻ መከታ፣ ለአገሩ ለቀየው መኩሪያና መመኪያ ይሆናል፣ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የተጠቀሰው ወንድ ግን ለምንም የማይጠቅም፣ ለፈስፋሳና ሰነፍ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተተነተኑት ቃል ግጥሞች በማህበረሰቡ ዘንድ የማይደገፉ፣ የሚጠሉ፣ የሚተቹ፣ የሚወገዙ፣ ወዘተ. ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በሴቶና በወንዶች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ እንደ እፀፅ የሚቆጠሩትን ስንፍናን፣ ወሬኛነትን፣ ሴሰኛነትን፣ ወዘተ. የሚያንፀባርቁ ስለሆነ፣ የማህበረሰቡን አባላት የሆኑ ወንድና ሴት እነዚህን ባህሪያት እንዲጠሉና፣ ተገቢ የሆነውን ማህበራዊ ልማድና ተግባር እንዲከተሉ የማስተማር ፋይዳ ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

6.2..3 ጀግንነትን የሚያበረታቱ ፤ፈሪነትን የሚተቹና የሚነቅፉ ቃልግጥሞች

በዚህ ምድብ ውስጥ ወደ 123 ያህል ቃልግጥሞች ቀርበዋል:: እነዚህ ግጥሞች በሶስት ንኡሳን ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው:: አንደኛው ክፍል አጠቃላይ ጀግንነትን በሚመለከት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነው:: ስለዚህ የጀግንነት ባህሪንና ተግባርን አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው ማለት ይቻላል:: ይህ የምድቡ አንድ ገፅታ ሲሆን ከምድቡ 38 ያህል ግጥሞች ናቸው:: ሁለተኛው ገፅታ ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ዝና እና ክብር ያላቸው ግለሰቦች፣ ከጀግንነት አንፃር እንደ ምሳሌ ወይም እንደ ተምሳሌት ሊቆጥራቸው የሚችሉ ታዋቂ ግለሰቦችን የሚመለከቱ ግጥሞች ያሉበት መሆኑ ነው:: እነዚህ ታዋቂ ግለሰቦች በፖለቲካዊውም ሆነ በማህበራዊ ህይወታቸው ተለይተው የሚታወቁ፣ በአንድ ወቅት በህይወት የነበሩና በስም ተለይተው የሚታወቁ ሰዎች ናቸው:: ደጃዝማች ጎበና አመዴና

ቀኛዝማች አባተ ሀይሉ በፊውዳል ኢትዮጵያ ዘመን ባለ ከፍተኛ ማእረግ የነበሩ ሰዎች ናቸው። ደጃዝማች ጎበና፣ በጣሊያን ወረራ ጊዜ በአርበኝነት ለሀገራቸው የታገሉ አርበኛ ነበሩ። ቀኛዝማች አባተም የአልጋ ወራሽ ደጋፊና ወታደር አሰልጣኝ እንደነበሩ አምሳ አለቃ መላኩ ተገኝ አጫውተውኛል። ምስጋን በላይ የሚባለውም ዞብል አካባቢ ባለው ማህበረሰብ ዘንድ እንደ ጀግና ስሙ የሚጠራ ነበር። ኑሮውና አሟሟቱ ለቃልግጥሞች መፈጠር ምክንያት ሆኗል። ስለነዚህ ሶስት ግለሰቦች የሚናገሩት መንቶዎችና አርኬዎች 37 ያህል ናቸው።

ከዚህ በተዛባ ፈሪነትን የሚተቹ ቃልግጥሞች በዚህ ምድብ ውስጥ ወደ 48 ያህል ናቸው። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ማህበረሰቡ የማይፈልጋቸውን ባህሪያት የሚተችበት አንደኛው መንገድ ስነቃሉ ነው። በማንኛውም ማህበረሰብ ማለት በሚቻል ሁኔታ ፍርሀት ተቀባይነት ያለው አይመስልም። ራሱንና ቤተሰቡን፣ ጎሳውንና አባላቱን ቀየውንና መንደሩን፣ እንዲሁም ሀገሩን፣ ከጠላት ይከላከል፣ ይጠብቅ ዘንድ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እስከ መስዋትነት ድረስ የሚደርስ ሃላፊነት በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ የተጣለ ግዴታ ነው ማለት ይቻላል። ይህንን ማህበራዊ ግዴታ መወጣት አለመቻል ያስተቻል፣ ያስንቃል፣ ያሰድባል። በእያንዳንዱ ፍርሀትን በሚተች መንቶ ወይም አርኬ ግልባጭ ወይም በስተጀርባ ጀግንነትን የሚያበረታታ ሰሜት ይታያል ማለት ነው።

ጀግንነትና ፈሪነት በተለያየ ማህበረሰብ በተለያየ መንገድ ይገለፃል። የቤተሰብ አባል የሆነ ሰው በሌላ ሰው ጥቃት ሲደርስበት፣ ጥቃቱን መከላከል፣ ሲገደል ደም መመለስ፣ ወዘተ. እንደ ጀግንነት ይቆጠራል። ብዙ ማምረት፣ ማርባት፣ አድኖ መመለስም እንዲሁ የሚቆጠርበት ሁኔታ ይኖራል። ፈሪነት እንዲሁ በተለያየ መልክ ይገለፃል። ለምሳሌ ጠላትን አለመታገል (አለመከላል)፣ መሸሽ፣ በአጠቃላይ የጀግና ተግባራት የሚባሉትን አለማድረግ እንደ ፈሪ ያስቆጥራል። በመሆኑም ጀግንነትና ፈሪነት በሚከተሉት ቃልግጥሞች እንዴት እንደተንፀባረቁ በተራ እንመከታለን። እነዚህ ግጥሞች መረጃ በተሰበሰበባቸው አካባቢዎች ያሉትን የማህበረሰብ አባላት አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ወዘተ. የሚያሳዩ ናቸው ማለት ይቻላል።

6.2.3.1 አጠቃላይ ጀግንነትን የሚያወድሱና የሚያበረታቱ ቃልግጥሞች

በዚህ ክፍል የምንተነትናቸው ቃልግጥሞች የተለያየ አቀራረብ ያላቸው ናቸው። አንዳንዶቹ አካባቢን ሳያመለክቱ አጠቃላይ የሆነውን የጀግንነት ተግባራት የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ አካባቢን ከነዋሪዎች ጋር እየጠቀሱ የሚያወድሱ ናቸው። የቀሩት በአንድ ወቅት በህይወት የነበሩ ሰዎችን በስም ጠቅሰው የሚዘክሩና የሚያወድሱ ናቸው።

መንቶ 88 የአባግርሻ ሚዜ ጎብላሌው ቶሎና
አንተን እሚያስፈልግ አግኝቶኛልና
መንቶ 89 ከአባግርሻ ጋራ ከተነጋገሩ
ክላሽ ሞንሚናይቱ ተባረቀይ በሉ
መንቶ 90 ኧረ በሬ ቁጠር፣ በሬ ቁጠር
በጭፍና እሚጠመድ እማይጠረጠር

‹‹አባ ግርሻ›› ማለት ወጣቶችና ጎልማሶች በጀግንነቱ የሚተማመኑበትን፣ በሙያው የሚኮሩበትን ጓደኛቸውን አሞካሽተው የሚጠሩበት መጠሪያ ነው። በአገባቡ ሀይለኛ፣ ቁጡ፣ ደፋር፣ እንደ ማለት ይሆናል። በመንቶ 88 ውስጥ ባሉት ስንኞች ይህንን ጓደኛውን የሚፈልገው ግለሰብ፣ አስፈጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያለ ነው። «.... አንተን እሚያስፈልግ አግኝቶኛልና›› ሲል፣ «ብቻየን መቋቋም የማልችለው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብቻለሁና ቶሎ ድረስልኝ» የሚል ነው። ይህ ጥሪ የሚቀርብለት ‹‹ጀግና›› ባህሪው በመንቶ 89 ውስጥ ተጠቁሟል። ይኸውም ትዕግስት የሌለው፣ ቁጡና ሀይለኛ ነው። ይህ ጀግና ከሰዎች ጋር ከተጣላ፣ ተኩሶ ለመግደል ወደኋላ የማይል ነው። ‹‹ ከአባግርሻ ጋር ከተነጋገሩ›› የሚለው ስንኝ፣ ከሰዎ ጋር ማጣላትን፣ ክፉና በጎ መነጋገርን የሚያመለክት ሲሆን፣ የሚጣሉበት ወይም የሚነጋገሩበት ጉዳይ ምንም ይሁን ምን ተኩሶ ከመግደል የማይመለስ መሆኑን ያሳያል። «ተባረቀ›› ማለት ድንገት ተተኮሰ ማለት ነው። በመሆኑም በግጥሞቹ ውስጥ የተጠቀሰው ጀግና ፈጣን በሆነ ሁኔታ ጠላትን የማጥቃት አቅም ያለው መሆኑን ይገልፃል።

መንቶ 90 ላይ የጀግንነት ተግባር የተገለፀው በንፅፅር ነው።በበሬውና በጀግናው መካከል ያለው የማንፀሪያው ጉዳይ ‹‹ በጭፍና መጠመድ›› ሲሆን፣ ጭፍና ማለት ደግሞ አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ያለበት የዝናብ ወቅት፣ ጥቅጥቅ ካለ ደመና ጋር የማያባራ የካፊያ ዝናብ ያለበት፣ መሬቱ ጭቃ የበዛበትና ለመራመድ አስቸጋሪ የሆነበት፣ ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ እርሻ የሚያርስ በሬና ገበሬ እንደጉልበተኛ፣ ሐይለኛ የሚቆጠር ነው። የግጥሙ ሀሳብ ‹‹ ጀግና ጀግና ሰው ፈልጉ፤ ጀግና ጀግና ሰው ምረጡ›› የሚል ነው። እነዚህ ሰዎች በችግር ጊዜ የሚጋፈጡ፣ የማይሸሹ፣ የማይፈሩ፣ ወዘተ.. ናቸው። ከበሬም ጉልበተኛ፣ ሀይለኛ፣ እንዳለ ሁሉ፣ ከሰውም ጀግና፣ ደፋር፣ ልቡ እማይሸበር፣ ሀሞቱ እማይላላ፣ አለና ለችግር ጊዜ ይሆናል የሚል ነው።

ከዚህ በታች ያሉት መንቶዎች የጀግንነት ተግባራትን በተለያየ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ናቸው። በጀግና ጓደኛ መመካትን፣ ጥቃት መላሽነትን፣ ልበ ሙሉነትን፣ የሚያመለክቱ ሀሳቦች የተንፀባረቁባቸው ናቸው።

መንቶ 91 ያባ ይርጋ ሚዜ አለህልኝ ወይ
ዲቡን ጠጋ ብየ ልበላቸው ወይ
መንቶ 92 እኔ ጀግና ብሎ ዲንጋ ሲፈነቅል
የአባይርጋ ሚዜ አኖጋው እንደቅል
መንቶ 93 አርኬ መሳሪያህን ያሙታል ሰደፉን
ዘወር አርገውና አሳያቸው አፉን
መንቶ 94 ጠመንጃው ምንሽር አስር አስር ጎራሽ
እንኳን የወንድሙን ያማቹን ደም መላሽ
መንቶ 95 እንኳን አማርኛ ቢናገር ትግርኛ
በጠባብ ወስኮ ነው የቀናነው እኛ
መንቶ 96 ብታስር እጁን ነው ፣ ብገረፍ ጎኔን ነው
አመጠኛው ልቤ አሁንም ገና ነው

‹‹አባ ይርጋ›› የሚለው ሀረግ የጓደኛ ማሞካሻና መጠሪያ ነው። በዚህ አገባብ የሚሞካሸው ግለሰብ ‹‹ ይርጋ›› የሚባል ልጅ ያለው ይመስላል። በመሆኑም ‹‹የይርጋ አባት›› እንደማለት ይሆናል። በባህሉ አባቶች፣ መጀመሪያ ወንድ ልጅ ከተወለደ፣ በወንድ ልጅ ስም ይጠራሉ። ‹‹አባ›› ማለት ‹‹አባት›› እንደማለት ነው። ስለዚህ ‹‹ የይርጋ አባት፣ የበላይ አባት ፣ ወዘተ... እየተባለ ይጠራል ማለት ነው። መንቶ 91 እና 92 የሚያንፀባርቁት ሀሳብ ‹‹ አንተ ካለህልኝ ማንንም አልፈራም፤ እፋለማቸዋለሁ፤» የሚል ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ ጠላት ጥቃት ለማድረስ ሙከራ ሲያደርግ፣ የአንተ ጓደኛ የሆነው (የአባ ይርጋ ሚዜ) ቀድሞ አሸነፈው፤ በማለት ጀግንነቱን ያደንቀዋል። ‹‹... አኖጋው እንደቅል›› ማለት ጭንቅላቱን በሀይል መታው፣ ራሱን በሀይል መትቶ (ገምሶ) መሬት ላይ እንዲወድቅ አደረገው፣ ማለት ነው። በሁለቱ መንቶዎች ውስጥ በጀግንነት የሚጠራው ግለሰብ፣ ከራሱ አልፎ ለጓደኞቹ መመኪያ እስከመሆን የደረሰ ነው ማለት ይቻላል።

መንቶ 93 ላይ የተጠቀሰው ጀግና ትዕግስተኛ ይመስላል። ነገር ግን ትዕግስተኛነቱ ከፍርሀት የተቆጠረበት መሆኑ፣ በግጥሙ ውስጥ ተጠቅሷል። ‹‹አርኬ መሳሪያህን ያሙታል ሰደፉን››

የሚለው ስንኝ ‹‹ጓደኛችሁ መሳሪያ የተሸከመው ለይስሙላ ነው እንጂ ጀግንነት የለውም ›› የሚል ሀሜት የተጠቆመበት ነው፡፡ ይህን ሀሜት የሰማው ጓደኛ ‹‹በያዝከው መሳሪያ ተኩሰህ ምታበት›› በሚል መልዕክት ጓደኛውን ይቀሰቅሰዋል፡፡ ‹‹አርኬ›› ማለት ጓዴ፣ጓደኛየ ማለት ነው፡፡ መንቶዎቹ ጀግንነትን የሚቀሰቅሱ፣ የጀግና ጓደኛ (አርኬ) መሆን የሚያኮራ፣ የሚያስከብር፣ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው፡፡

መንቶ 94.ላይ የተገለፀው የጀግንነት ተግባር ደም ከመመለስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የቤተሰብ አባል የሆነ (አባት፣ ወንድም፣ አጎት) ሰው፣ በሌላ ሰው ጥቃት ሲደርስበት (ሲገደል፣ ሲደበደብ) የተጠቃው ወገን አጥቂውን መልሶ ካላጠቃ ይሰደባል፣ ይተቻል፣ ይናቃል፣ ማህበራዊ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡ ጥቃቱን ለመመለስ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ፣ ማህበረሰቡ በአወንታዊ ጎኑ ይቀበለዋል እንጂ ብዙም አይቃወመውም ማለት ይቻላል፡፡ በተለምዶ የተጠቂ ወገኖች አቅም ከሌላቸው በስተቀር ወደ ህግ የሚሄድ አስተሳሰብ አይስተዋልም ‹‹ደምን በደም መመለስ›› እንደጀግንነት ሲታይ፣ ለመንግስት አቤት ማለት እንደተሸናፊነት ይቆጠራል፡፡ በግጥሙ ውስጥ የተገለፀው ሀሳብ የቤተሰብ አባልን ደም ከመመለስ ያለፈ ነው፡፡ ከራሱ ቤተሰብ አልፎ የሚስቱን ዘመዶች ጥቃት የሚመክት ጀግና ነው፡፡

መንቶ 95 እና 96 ላይ የሚንፀባረቀው የጀግንነት ሁኔታ ልበ ሙሉነትን፣ ደፋርነትን፣ አለመጨነቅን፣ ወዘተ. አመላካች ነው፡፡ ‹‹በጠባብ ወሰኮ ነው የቀናነው እኛ›› የሚለው ስንኝ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ማለፍን፣ ችግርን ፊት ለፊት ተጋፍጦ ማሸነፍን፣ አይበገሬነትን፣ የሚያመለክት ነው፡፡ «ወስኮ» ማለት ቀንበር ማለት ነው፡፡ ለእርሻ የደረሰ ወይፈን ቀንበር ተሸክሞ ይገራል፣ ይቀናል፡፡ መቅናት በዚህ አገባብ መገራት፣ መልመድ፣ ማረስ መቻል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የማለፍ፣ ታግሎ የማሸነፍ ብቃት ስላለን ማንም ቢመጣ አንፈራም፣ የሚል የማነሻሻ መልዕክት ያለው ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ መንቶ 96 ይደግመዋል፡፡ ምንም አይነት እስራትና ግርፋት ሊደርስብኝ እንደሚችል ባውቅም፣ ማንኛውንም ጥቃት ለመሸከም ወይም ለመቀበል የሚችል ሀሳብ የለኝም፤ ከዚህ ይልቅ ጠላትን መፋለምን፣ አለመገዛትን እመርጣለሁ በማለት የጀግናውን የአቋም ፅናት፣ ቁርጠኝነት ያንፀባርቃል፡፡

የሚከተሉት አርኬዎች ጀግንነትን የሚያንፀባርቁት አካባቢን ከነዋሪዎች ጋር በመጥቀስ ነው፡፡ በተጠቀሱ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ግብርናን ከእርካታ ጋር አብሮ የሚያወራ በመሆኑ

በሚኖረው የክብት ብዛትና ጥራት፣ በሰዎች ዘንድ የመሞገስና የመወደስ አጋጣሚ ያገኛል። ይኸው ሁኔታ በግጥሞቹ ውስጥ ተንፀባርቆ ይታያል። አርኬዎቹን እንመልከት!

አርኬ 97 መጠጣቸው ወተት መብላቸው መንገሌ
ብረታቸው ሞይዘር ጥይታቸው ጦሬ
ቁመታቸው ሎጋ ልብሳቸው ገመሌ
አገራቸው በዋ፣ በዋ-ንጉስ-ጋሌ
በዋ ንጉስ-ጋቤ፣ አዩብና ጮቢ ጭድ አትቆልሉበት
ረመጥ አይጠፋም እሳት ኸቆየበት
አርኬ 98 እንደምነው እዩብ የዋጮው ግድም
እንደምነው ጮቢ የዋጮው ግድም
እንዴት ነው አማያ የዋጮው ግድም
እንደምነው በዋ የዋጮው ግድም
እንኳን ነካክተውት ይሸታል ደም ደም
አርኬ 99 እኒህ ያርበት ልጆይ ምንኛ ቀበጡ
መትረየስ ሲያጓራ ከታንክ እሚወጡ
እንደግልገል ፈረስ የሚቅበጠበጡ
አርኬ 100 ቆቦን ከቀየው ላይ የደፈሩ እንደሆን
ቅልሻን ብሰጭት ያሳዩት እንደሆን
አርበትን በዱላ የቃጡት እንደሆን
ዙብልን ከላሙ፣ ወርቁን ከጊደሩ፣ የወረሩ እንደሆን
አይለቅም በዋዛ ምድር ቃጤ ሳይሆን

አርኬ 97 ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ተጠቁመዋል። የሚጠጣው፣ የሚበላው፣ የሚያዘው የመሳሪያ አይነት፣ አለባበሳቸው፣ ቁመናቸው በየስንኞቹ ተገልፀዋል። «መንገሌ» ማለት በብረት ምጣድ፣ ወይም በምጣድ የሚጋገር ቂጣ ነው። በወተት እየተሟገ ወይም በቅቤ ተፈትፍቶ (ጨዋቃ ሆኖ) ይበላል። «ገመሌ» የወጣት ልጆች (ወንዶች) የአለባበስ አይነት ነው። «ጦሬ» ማለት የሞይዘር ጥይት ሆኖ፣ በዝናር የሚታጠቁት ነው። መሳሪያው ሞይዘር የሚባለው አይነት ነው። ይህ የመሳሪያ አይነት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተመራጭነት ያለው ነው። ከላይ የተጠቀሰው አመጋገብ፣ አለባበስ፣ ወዘተ. በብዛት የሚታየው በገጠራማው የቆቦ ወረዳ አካባቢዎች ሲሆን፣ በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱት አካባቢዎች በዋ፣ ንጉስ-ጋሌ፣

አዩብና ጮቢ ናቸው። በግጥሙ ውስጥ ባሉት የመጨረሻ ሁለት ስንኞች ቀደም ሲል በእነዚህ አካባቢዎች ጀግኖች ይኖሩባቸው እንደነበሩ የሚያመለክቱ ናቸው። ‹‹ ጭድ አትቆልሉበት›› ማለት በአገባቡ ያለው ትርጉም፣ ጦርነት የሚያስነሳ፣ ግጭት የሚቀሰቅስ ተግባር አትፈፅሙ እንደማለት ነው። እንዲህ አይነት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ አሁን ያሉትም አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጥራሉ የሚል ነው። የእሳቱ ውክልና የቀድሞ ጀግኖችን ሲሆን፣ ረመጡ ደግሞ የአሁኑን ትውልድ የሚያመለክት ነው።

አርኬ 98 ወደኋላ ተመልሶ የቆየ የታሪክ እውነታ የሚያስታውስ ነው። በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱት አዩብ፣ ጮቢ፣ አማያ፣ በዋ፣ የሚባሉት የገጠር አካባቢዎች የሚገኙት ከቆቦ ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ ነው። በየጁና በራያ ባላባቶች መካከል በነበረው የስልጣን ሽኩቻ ምክንያት፣ በእነዚህ አካባቢዎች የሁለቱ ባላባቶች ጦርነት አካሂደዋል። ይህንን የታሪክ እውነታ አለሙ ና ሲሳይ (2005፣ 94-100) ተርከውት ይገኛል። በተለይ ጮቢ የሚባለው አካባቢ ከፍተኛ የሆነ ጦርነት የተካሄደበት አካባቢ እንደነበር

> “አስፋው ወሌን ዞብል፣ አቡየን ጮቢ ላይ ፈትፍቼ ባጎርሰው
> እንቢ አለ እንጂ አመዴ እጄን ያልቀመሰው”

የሚለው መንቶ ያረጋግጣል። አስፋው ወሌና አቡየ የሚባሉት የየጁ ባላባቶች ናቸው። የራያ ባላባቶች የነበሩት ፈንታ ኩቢ፣ ይመር መሸሻና ሮብሶ ደንሳራን፣የመሳሰሉት ናቸው። በእነዚህ ባላባቶች መካከል በተደረገው ውጊያ ጮቢ-በር ላይ ከፍተኛ የሰው እልቂት ደርሷል። በዚህ ታሪካዊ ቦታም በደርግና በኢህአዲግ የርስ በርስ ጦርነት በተደረጉ ውጊያዎች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተዋጊ ሀይል ያለቀበት ቦታ እንደሆነ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች በሚኖረው ማህበረሰብ ላይ የጠብ አጫሪነት ተግባር ማሳየት የከፋ ችግር ያስከትላል የሚል መልዕክት የተላለፈ መሆኑን እንረዳለን። ይህንን ሀሳብ የሚያረጋግጠው ‹‹እንኳን ነካክተውት ይሸታል ደም ደም›› የሚለው ስንኝ ነው።

አርኬ 99 እና 100 ጀግንነትን የሚያመለክቱት እንደ ላይኞቹ አርኬዎች በአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በማያያዝ ነው። «አርበት» የሚባለው አካባቢ ከቆቦ ከተማ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ የገጠር ቀበሌ (አካባቢ) ነው። በዚህ አካባቢ ያሉ አንዳንድ ወጣቶች በደርግና በኢህአዴግ የርስ በርስ ጦርነት ጊዜ (በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ) የመንግስት ጦር ራያን አካባቢ እየለቀቀ ሲወጣ፣ ከመሳሪያ ጋር ባላቸው ፍቅር ምክንያት አስቸግረው እንደነበር ይነገራል። በታንክና

በመትረየስ የሚደረገውን ውጊያ ከምንም ሳይፈሩ «መሳሪያ ለማግኘት» በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ታንክ ላይ እስከመውጣት ድርሰው ነበር ይባላል። ያልተገራ ፈረስ ቀበጥባጣ እንደሆነ ሁሉ፣ እንደነዚህ አይነት ወጣቶችም የመሳሪያውን አይነትና ተኩስ ሳይፈሩ ያሳዩትን ድፍረት የሚያመለክት ግጥም ነው።

ቆቦ፣ የራያና ቆቦ ዋና ከተማ ናት። ቅልሻ፣ ከዋጃ በላይ የሚገኝ የገጠር መንደር ነው። ዞብል ከቆቦ ከተማ በስተምስራቅ የሚገኝ ስንሰለታማ ተራራ ያለበት አካባቢ ነው። ወርቁ (ጉራ ወርቁ) እንዲሁ ከዞብል በስተደቡብ የሚገኝ አካባቢ ነው። ዞብልና ወርቁ ለአፋር አካባቢዎች አጎራባቾች ናቸው። የአርኬ 100 ዘይቤ በስመሀዳሪ የሚባለው ሲሆን በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ለተለያዩ ችግሮ ሲጋለጥ የሚያሳየውን ምሳ የሚያመለክት ነው። ቀየን (አካባቢ) የሚደፍርና በክፉ የሚያይ ባላጋራ ሲመጣ፣ ከብቶችን ለመቀማት (ለመዝረፍ) የሚመጣ ወራሪ ሀይል ከታየ፣ ብዙ ህይወት ሳይጠፋ (ምድር ቃጠ ሳይሆን) ችግሩ በቀላሉ አይበርድም እንደማለት ነው።

በአጠቃላይ ከአርኬ 97-100 ባሉት ግጥሞች የተንፀባረቀው የጀግንነት ሁኔታ በዘይቤ መልክ የቀረበ ሆኖ፣ አካባቢውን እየጠቀሰ ነዋሪዎችን የሚያወድስና የሚያስታውስ ነው። የአሁኑ ትውልድም እንደቀደሙት ትውልዶች ሀይለኞች፣ ደፋሮች፣ ጀግኖች፣ ወዘተ. እዲሆኑ ያበረታታል ማለት ነው።

በሚከተሉት መንቶዎችና አርኬዎች የተንፀባረቀው የጀግንነት ሁኔታ ባብዛኛው በየጁ አካባቢ ባለው ማህበረሰብ ውስጥ በነበሩ ጅግኖች ላይ መሰረት ያደረገ ነው። በእነዚህ ግጥሞች አማካይነት በራያ አካባቢ እንደተጠቀሱት አካባቢዎች ሁሉ፣ መኖሪያውን ጠርቶ ነዋሪውን የማወደስና የማስታወስ ተመሳሳይ ፋይዳ ያላቸው ናቸው። ግጥሞቹን እንመልከት!

መንቶ 101 ምንቸገረኝ ብየ ወሬ እጠይቃለሁ
አገሬ ላይ መርጦ መሆኑን አውቃለሁ
መንቶ 102 ከአባተ ሀይሉ አገር የጁ ተወልጀ
በነጋ በጠባ ይታሰራል እጀ
አርኬ 103 ትናገር ከሆነ ቀጥ ብለህ ተናገር
አታድበክብክና ቀጥ ብለህ ተናገር
አገሬ ገዶ ነው፣ አገሬ የጁ ነው፣ ከነጨፍጭፍ አገር

አርኬ 104 ታይ መርጦን ጠይቀው የጦር መላ ያውቃል
ጃርሶንም ጠይቀው የጦር መላ ያውቃል
መቻሬን ጠይቀው የጦር መላ ያውቃል
ይኸ ምናምኑ እንዴት አርጎ ያውቃል
አርኬ 105 እኔ ኸየጁ ልይ ፈሪ ቢገኝብኝ
እኔ ኸራያ ልይ ፈሪ ቢገኝብኝ
በመኪናው መንገድ ጋሪ ይነዳብኝ

በግጥሞቹ ውስጥ የተጠቀሱት አካባቢዎች መርጦ፣ ገዶ፣ ጃርሶና መቻሬ ናቸው። እነዚህ አካባቢዎች የሚገኙት የጁ (ወልዲያ) አካባቢ ነው። በግጥሞቹ የተነገረው ሃሳብ፣ የመጣ ቢመጣ ማንንም አንፈራም፣ የሚል ይመስላል። ወደኋላ እንደምንመለከተው በየጁ አካባቢ የሚታወቀው፣ አባተ ሀይሉ የሚባለውን እያስታወሱ፣ እንደ እሱ ሀይለኛ መሆናቸውን ይገልፃሉ። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የአንድ ጀግና መፈጠር፣ ለሌሎች ጀግኖች መነሳሳት ምክንያት ሲሆን ይችላል ማለት ነው።

የጁ፣ ደጃች ጎበና አመዴና አባተ ሀይሉ የሚባሉት ባለታሪክ ጀግኖች የነበሩበት አገር ስለሆነ፣ የነዚህ ግለሰቦች ታሪክ አሁን ላለው ትውልድ እንደ መመኪያና መኩሪያ ሆኗል ማለት ነው። በሁለቱ (በራያና በየጁ) አካባቢዎች የሚገኙ ወጣቶች ለጀግንነት ተግባር እንዲነሳሱ የሚቀሰቅሱት ስንኞች ‹‹እኔ ለየጁ ልይ፣ እኔ ለራያ ልይ ፈሪ ቢገኝብኝ...›› የሚሉት ናቸው።

በአጠቃለይ የጀግንነት ማወደሻና ማሞገሻ ቃልግጥሞች ይዘታቸው ወይም አጠቃላይ መልክታቸው ጀግንትን፣ ደፋርነትን፣ ቁርጠኛነትን፣ ወዘተ. በማህበረሰቡ አባላትና ወጣቶች ላይ የማስፈን፣ የመትከልና የማስረፅ ፋይዳ ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ፍርሀትን፣ ጥቃትን፣ የሚቀበል አስተሳሰብና ስብዕና፣ እንዳይኖር ያስተምራሉ፣ ያበረታታሉ፣ ያደፋፍራሉ።

6.2.3.2 ለታዋቂ ግለሰቦችና ጀግኖች የተገጠሙ ቃልግጥሞች

ከዚህ በታች በሚተነተኑት ቃልግጥሞች፣በየጁና በራያ አካባቢ በሚታወቁ ሶስት ታዋቂ ጀግች ህይወትና ተግባር ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ሁለቱ በመንግስት ደረጃ ይታወቁ የነበሩ ሲሆን፣ አንዱ ግን በራያና ቆቦ (ዙብል አካባቢ በሚገኘው) ማህበረሰብ መካከል እንደ ባህላዊ ጀግና የሚታይ ግለሰብ ነው። ከእነዚህ ባለታሪኮች መካከል፣ ደጃች ጎበና አመዴ ከጣሊያን ወረራ በፊት ጀምሮ የየጁ ባላባትና ገዥ የነበሩ ሲሆኑ፣ አባተ ሀይሉ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ባለው

የአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት የልዑል አልጋ ወራሹ (የአስፋው ወሰን) ባለሟልና የወታደር አሰልጣኝ እንደነበሩ ይነገራል። ከዚህ ከጥሎ ስለ እያንዳንዳቸው የተገጠሙትን ቃልግጥሞች እየጠቀስን እንመለከታለን።

6.2.3.2.1 ስለ ደጃዝማች ጎበና አመዴ የተገጠሙ

ደጃዝማች ጎበና አመዴ፣ በ1928 ዓ.ም ጣሊያን አገራችንን በወረረ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ጦር ‹‹ሲሸነፍ››፣ የመጀመሪውን የአርበኝነት ትግል ከጀመሩት የሰሜን ኢትዮጵያ አርበኞች መካከል አንዱ ናቸው ይባላል። ደጃች ኃይሉ ከበደ (የዋጉ) የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ አስተባብረው ለጣሊያን አልገዛም፣ በማለት ሲዋጉ መሞታቸውን ታሪክ ያስታውሳል። እንደዚሁም፣ ጎበና አመዴ የጁንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ይዘው ለጣሊያን አልተገዙም ይባላል። እስከ 1960ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በህይወት የነበሩ ሲሆን፣ በራያ ገበሬዎች አመፅ ህይወታቸው እንዳለፈ ይታወሳል። የሚከተሉት መንቶዎች ከጣሊያን ጋር ያደረጉትን የአርበኝነትና የጀግንነት ተጋድሎ የሚያንፀባርቁ ናቸው።

መንቶ 106 ጎበና አመዴ ለጉድ ተወልዶ
ዘጠኝ ቲሊንቲ ባንድ ቀን ማልዶ
መንቶ 107 ነጃ በለኝ ብሎ ሸንኮር አመለጠ
ቀረ እንጅ ቲሊንቲ አይኑ እንዳፈጠጠ
አርኬ 108 ካልቆሰቆሱበት አይፈላም ጀበና
ከሀይለ ስላሴ ይሻላል ጎበና
እያንገራገረ አልተገዛምና
አርኬ 109 ካልቆሰቆሱበት አይፈላም ጀበና
ላይኛው መርጦ ነው ታችኛው ገላና
አባ ጉመድ ጉቤ ሾተል ጅራፉ ና

«ቲሊንቲ» ማለት የጣሊያን ወታደር የሆነ ሰው (ወታደር) ነው። ሸንኮር የሚባለው ግለሰብ ከጣሊያን ጋር ተሰልፎ ይዋጋ የነበረ የአካባቢው ተወላጅ ነው። ይህ ግለሰብ ከጎበና አመዴ ጋር ውጊያ ሲያደረግ፣ አሸናፊነቱ የእሳቸው መሆኑን ቀድሞ በመረዳቱ እግሬ አውጭኝ ብሎ በመሸሽ ከሞት እንደተረፈ ነው። ከሁለቱ መንቶዎች እንደምንረዳው፣ ግማሽ ቀን ባልሞላ ውጊያ ዘጠኝ የጣሊያን ወታደሮች እንደተገደሉ ነው። አርኬ 108 የንጉሱን መሸሽ የሚያመለክት ሀሳብ የተንፀባረቀበት ነው። ‹‹ከሀይለ ስላሴ ይሻላል ጎበና›› የሚለው ስንኝ

ይህንን የሚያረጋግጥ ነው። ንጉሱ በተለያየ ምክንያት ከሀገር መውጣታቸው ባብዛኛው ህዝብ አመለካከት እንደሸሸት ይቆጠር ስለነበር፣ ይህንን ሁኔታ በሚመለከት የሚከተለው እንደተገጠመ ይታወሳል።

‹‹ ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ
ከማይማይጨው ገስግሶ ሸዋ ገባላችሁ›› ተብሏል።

በመሆኑም ደጃች ጎበና በአልገዛም ባይነት መንፈስ፣ የአምስቱን አመት የአርበኝነት ትግል በጀግንነት የተወጡ አርበኛ ነበሩ ማለት ነው። አርኬ 109 የሚያስገነዝበው ደጃች ጎበና በውጊያ ላይ የሚማርኳቸውን የጣሊያን ወታደሮች በሾተል እጃቸውን ይቆርጧቸው እንደነበር ነው። «መርጦና ገላና» በሚባሉት የየጁ አካባቢዎች እየተንቀሳቀሱ ጣሊያንን አስቸግረውት እንደነበር እንገነዘባለን። ግጥሞቹ ለታሪክ ማስረጃነት ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ናቸው።

ቀጥሎ ባሉት መንቶዎች የምንረዳው ደግሞ፣ ደጃች ጎበና ከራያ ገበሬዎች ጋር በነበራቸው የመሬት ግጭት ምክንያት የተገጠሙ ናቸው። ስለደጃች ጎበና የአሚሚት ሁኔታ አለሙና ሲሳይ (2005፣ 206-216) ባሉት ገፆች በሰፊው ተርከውታል። (ለተጨማሪ መረጃ አባሪ 3 ይመልከቱ) ። መንቶዎቹን እንመልከት!

መንቶ 110 የጉበን መኪና ስሟ ዘነበች
አጥንቷን ለቃቅማ ወልዲያ ገባች
መንቶ 111 እሮብ ተደልድሎ ሀሙስ ተገበየ
የሰው እርሻ አይነካም ይህንን ጉድ ያየ
መንቶ 112 አሁን ምን ያረጋል ይህ ሁሉ ጥይት
ማንም አልደረሰ ጎበና ሲሞት

ደጃች ጎበና የላንድሮቨር መኪና ነበራቸው። ይችን መኪና የአካባቢው ሰው «ዘነበች» የሚል ስም አውጥቶላት እንደነበር ከግጥሙ እንረዳለን።በመሆኑም፣መንቶው የደጃች ጎበናንና የአሽከሮቻቸውን ሬሳ ይዛ ወልዲያ ያደረሰችው እሷ መሆኗን ይጠቁማል። ለመገደላቸው ምክንያት የነበረውም፣ የአካባቢውን ገበሬዎች መሬት በጉልበት በመያዛቸው እንደሆነ ይነገራል። የተገደሉትም ጎለሻ አካባቢ ሀሙስ ቀን ነው ይባላል። ይኸውም ሮብ ቀን የገበሬዎች አመፅ መነሳቱ ከታወቀ በኋላ፣ በማግስቱ ወደ አካባቢው አሽከሮቻቸውን አስከትለው እርሻ

ቦታቸው ሲደርሱ ነው፣ ተኩስ ተከፍቶ የተገደሉት። አስክሬናቸው ወልዲያ ሲገባና የቀብር ስነስርአታቸው ሲፈፀም፣ ከፍተኛ የሆነ የመትረየስ ጥይት ይተኮስ ስለነበር ለመንቶ 112 መፈጠር ምክንያት ሆኗል።

6.2.3.2..2 ስለ ቀኛዝማች አባተ ሀይሉ የተገጠሙ

ቀኛዝማች አባተ ሀይሉ፣ ዝናው ጎልቶ የሚታወቀው በየጁ ተወላጅነቱ (ወረሼክነቱ) ቢሆንም የቆባ ተወላጅነት እንዳለው ከመረጃ አቀባዮቼ መካከል አንዱ ይናገራሉ። (ታሪኩን ከአባሪው ይመልክቱ)። ቀኛማይ አባተ፣ ልክ እንደ ደጃች ጎበና በገበሬዎች አመፅ ምክንያት የተገደለ ነው።ተክለ ሰውነቱ አጠር ደልደል ያለ ሆኖ፣ ጎፈሬው ትልቅና ዒሙ የበዛ ነበር። የሰውነቱ ፀጉር እጅግ የበዛ ከመሆኑ የተነሳ፣ በሸሚዙ ኪሌታዎች እና እጅጌዎች ውስጥ ዘልቆ የሚታይ፣ ባለግርማ ሞገስና፣ በጣም ዘመናዊ መኪና የነበረው ሰው እንደነበር ይነገራል። የሚከተሉት መንቶዎች ስለቀኛማይ አባተ ሀይሉ ጀግንነትና አማሚት የሚያስታውሱ ናቸው።

መንቶ 113 የአባተ ሀይሉ አገር መርሳና ስሪንቃ
ለየጁ ለራያ ለሁሉ እሚበቃ
አርኬ 114 ሽዋም እኛን ምሰል
ትግሬም እኛን ምሰል
እንቢ ብለህ እንዱ፣
የበፍታ አምነው ልይ፤
አባ ከስክስ ሀይሉ ያረግሀል ከሰል
አርኬ 115 ወንዱ አባተ ሀይሉ፣
የብረት ምሶሶ የብረት ማገር
አዳልና ትግሬን ይቀጣው ጀመር
መንቶ 116 ቆቦ ከተማ ላይ ሰርጉን የበላችሁ
ደሞ ከወደይህ ይላሉ ጉድ ጉድ ምላሽ ሊጠሯችሁ
መንቶ 117 የማይሆንለትን ነብር ጋር ተጣልቶ
ጎርፉን ጎርፍ ወሰደው መርሳ ውሃ ሞልቶ
አርኬ 118 ሀይሉ መሸሻ ልይ፣ የበፍታ አምነው ልይ
ወንዱ አባተ ሀይሉ ሱሪው ተቀዶበት
አመለኛው ጋሜ ሱሪው ተቀዶበት
ብቻውን ነው መሰል ጉልበቱን አዩበት

መንቶ 119 የአባተ ሀይሉ እናት አይዞሽ አታልቅሽ
ሰባቱን ገሎ ነው የሞተው ልጅሽ
መንቶ 120 የአባተ ሀይሉ እናት ታጠቂ በገመድ
ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ

የመጀመሪው መንቶ የአባተ ሀይሉን የመኖሪያ አካባቢ የሚያመለክት ነው። ስሪንቃ፣ ሀብሩ ወረዳ (መርሳ) ውስጥ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት። ጀግንነቱ ግን፣ በሁለተኛው ስንኝ ‹‹ለየጁ፣ ለራያ፣ ለሁሉ እሚበቃ›› በማለት ተገልጿል። ወደኋላ እንደምንመለከተው፣ ጎርፉ ተሰማ ከሚባሉ ግለሰብ ጋር በነበራቸው የመሬት ግጭት ሰበብ፣ ህይወት እስከ መጠፋፋት ተዳርሰዋል። ጎርፉን ከገደላችው በኋላ፣ የጎርፉ ወንድም በፖሊስ ለማስያዝ ሲያስፈልገው ድንገት ተገናኝተው እሱንም ገሎታል ይባላል። የጎርፉ ወንድም ቆቦ ከተማ ይኖሩ ስለነበረ ነው፣ ‹‹ለየጁ ለራያ...›› ተብሎ የተገጠመው። መንቶ 114 እና 115 ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሀሳብ የተንፀባረቀባቸው ናቸው። ቀኛማይ አባተ፣ የአልጋ ወራሽ ደጋፊ ነው እየተባለ ይነገራል። ‹‹ሸዋም እኛን ምሰል፤ ትግሬም እኛን ምሰል...›› የሚለው ስንኝ ይህንን ለመጠቆም የገባ ይመስላል። «የሸዋና የትግራይ ሰው አልጋ ወራሽን ደግፈህ የማትነሳ ከሆነ ብርቱ ቅጣት ይጠብቅሀል» የሚል ነው። በሽፍትነት ጊዜው ፖሊስ ‹‹ፈልጎ›› ሊይዘው ባለመቻሉ፣ ከጎርፉ ሞት በኋላ፣ የአፋር ተወላጅ የሆነ ሌላ ሰው ገሏል ይባላል።

በቀኛማይ አባተ እና በጎርፉ መካከል የነበረውን ግጭትና፣ የግጭቱን ውጤት የሚያመለክቱ መንቶዎች 116 እና 117 ናቸው። ቀኛማይ አባት ቆቦ ከተማ መጥቶ ሲዝናና፣ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ከፍተኛ ድብደባ ይደርሰበታል። በቤተሰቡ አማካኝነት ወልዲያ ሆስፒታል ተኝቶ ከታከመ በኋላ ይድናል። ይህንን የድብደባ ተግባር አቀናብረው አስመትተውታል ተብሎ የሚታመኑት ጎርፉ ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ ዶሮ ግብር በታች በሚገኝ የእርሻ መሬት ሳቢያ ሁለቱ ጠብ የነበራቸው ስለሆነ ነው። ‹‹ቆቦ ከተማ ላይ ሰርጉን የበላችሁ›› የሚለው ስንኝ አባተን ‹‹ የደበደባችሁ ወይም ያስደበደባችሁ›› እንደ ማለት ነው። ‹‹የምላሽ ጥሪው›› አባተ ጥቃቱን ለመመለስ እየተዘጋጀ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህንንም መንቶ 117 ላይ እናገኛለን።

የሁለቱ ግጭት በአልጋ ወራሹና በንጉሱ መሳፍንትና መኳንንት ዘንድ ተሰምቶ የነበረ በመሆኑ፣ ሁለቱም ለስራ ጉዳይ አዲስ አበባ ደርሰው ሲመለሱ፣ አባተ መርሳ ላይ ቀድሞ

በመጠበቅ፣ ድንገት ሲተያዩ አባተ ቀድሞ ተኩሶ ጎርፉን መታው ይባላል። በእለቱ መርሳ ላይ ዝናብ ጥሎ ስለ ነበር ነው ‹‹ጎርፉን ጎርፍ ወሰደው›› የተባለው።

ከመንቶ 118-120 ያሉት ግጥሞች ስለቀኛማይ አባተ የአማሚት ሁኔታ የሚያስታውሱ ናቸው። የአማሚቱ ታሪክ እንደሚያስረዳው (አባሪን ይመልከቱ)፣ አባተና ዶሮ ግብር አካባቢ የሚገኙት አርሶ አደሮች ይጋጫሉ።እሱ በትራክተር ለማሳረስ ሲሞክር፣ የገበሬዎቹን አቤቱታ ከምንም ሳይቆጥር ወደ ሰላሳ የሚጠጉ አሽከሮቹን አስከትሎ ዶሮ-ግብር ይወርዳል። አናሳርስም ያሉትን ገበሬዎች በጥይት ካባረረ በኋላ በአካባቢው የነበረውን የአርሶ አደር ከብት ሰብስቦ ያግትና ወደ ወልዲያ ማስነዳት ይጀምራል። ከታገቱት ከብቶች መካከል ሁለት ከብቶች አርዶ ስጋ ሲበሉ፣ ‹‹ወየ አንባ›› እሚባል ተራራ ላይ አንድ ገበሬ ዘልቆ ‹‹የጎበዝ ያለህ ...›› ብሎ እሪታ በማሰማት አንድ ጥይት ተኩሶ የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሰበሰብ አደረገ። ህዝቡም ዙሪያውን በመክበብ ተኩስ ተከፈተ። አባተም መሸጎ ከነበረበት ካብ ወጥቶ ከአሽከሮቹ ጋር ሆኖ ሲታኮስ በጥይት ተመትቶ ወደቀ። አሽከሮቹም የገበሬውን ሀይል መቋቋም ስላልቻሉ ብዙ ተገደሉ። ቁስለኛው አባተ፣ በገበሬዎች እጅ ሞተ ይባላል። ‹‹ወንዱ አባተ ሀይሉ፣ አመለኛው ጋሜ፣ ሱሪው ተቀዶበት›› የሚለው ስንኝ፣ ክፉ ቀን እንደገጠመው፣ የማይችለው ባላጋራ (ጠላት) እንደተነሳበት፣ የሚያመለክት ነው። አባተ መጀመሪያ የተመታው ጉልበቱ ላይ ነው ይባላል። ‹‹ሱሪው ተቀዶበት›› ማለት ለችግር ተጋልጦ፣ በጭንቅ ላይ ሆኖ፣ እንደማለት ነው። ‹‹ጉልበቱን አዩበት›› የሚለው፣ ባንድ በኩል ጉልበቱ ላይ መመታቱትን፣ በሌላ በኩል፣ የሚረዳው፣ የሚደርስለት ሀይል (አጋዥ)፣ አለማግኘቱን የሚያመለክት ሀረግ ነው።

መንቶ 119 እና 120 ባሉት ግጥሞች የማዕናኛ ሀሳቦች የተንፀባረቁባቸው ናቸው ማለት ይቻላል። በገበሬው በኩል የሞተው ሰው ቁጥር እንዳልታወቀ ይነገራል። ከአባተ አሽከሮች ግን፣ ብዙ ሰዎች እንደተገደሉ ይነገራል። የገበሬውን ሀይል አስተባብሮ በመዋጋት የሚታወቀው በቅፅል ስሙ “ራስ ጀበና” ተብሎ የሚታወቀው ነው።

6.2.3.2.3 ስለ አቶ ምስጋን በላይ የተገጠሙ

አቶ ምስጋን በላይ የኖረው ቆቦ ወረዳ ውስጥ ዞብል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ፣ ልዩ ስሙ ‹‹አንጎት›› በሚባለው ቀበሌ ነበር። ከዞብል ወይም ከአንጎት ተነስቶ ወደ አፋር አካባቢ ለመድረስ የሚፈጀው ጊዜ በጣም አጭር ነው። በአፋርና በሁለቱ ራያዎች መካከል በሚኖረው ማህበረሰብ ልማድ፣ በቡድን ወይም በተናጠል ግጭት እየተፈጠረ ሰው የመግደል፣ ከብት የመዝረፍ (የመውረር) ተግባር ቀደም ባለው ጊዜ የተለመደ ነበር። በተለምዶ በዚህ የወረራና

የግድያ ተግባር የሚሳተፉ ግለሰቦች እንደ ጀግና ስለሚቆጠሩ፣ ይገጠምላቸዋል፤ ይሞገሳሉ፤ ይወደሳሉ።

የአካባቢው አርሶ አደርም ከግብርና ስራ በተጨማሪ ከብት የማርባት ልማድ አለው። ብዙ ከብት ያለው ገበሬ የአፋር ጓደኛ (ከታይሳ) በመያዝ ከብቱን አፋር ውስጥ ማርባት የተለመደ ነው። ዞብል በሚባለው አካባቢ ያለው ማህበረሰብ፣ ግን ከታይሳ ከመያዝ በተጨማሪ በቡድን ሆነው ወደ አፋር በመውረድ በጓደና ከብቶቻቸውን ያረባሉ፤ ሳር ያበላሉ። ከእንደነዚህ አይነት ሰዎች መካከል አንዱ ምስጋን በላይ እና ወንድሞቹ ይጠቀሳሉ። ስለ እሱ የተገጠሙት ቃልግጥሞች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው።

መንቶ 121 የአባትየው ግዳይ ጎሊና ነበረ
ደሞ የልጅየው ሚሌን ተሻገረ
መንቶ 122 የአባትየው ግዳይ አላይና ነበረ
ልጅየው ባሰና ኢሳን ተሻገረ
መንቶ 123 አንዳንድ ቀንማ እሪታም ደግ ነው
የበላይ ገብሩ ልይ፣ አደባባይ ውሎ የሚመኘው ዱር ነው
አርኬ 124 በሮቹን አርሳችሁ በሏቸው ወደ ላይ
ላሞቹን አልባችሁ በሏቸው ወደ ላይ
ይጠብቃቸዋል ወንዱ ምስጋን በላይ

የመጀመሪያዎቹን ተመሳሳይ መንቶዎች ሰርግ ላይ ገጠማቸው እየተባለ የሚነገርለት፣ የአካባቢው ታዋቂ አዝማሪ ተገኘ ጉባይ ነው። ይህን ሙገሳ የሰማው ምስጋን በላይ፣ ከበረቱ ገብቶ የመረጠውን ከብት ለተገኘ በሽልማት ሰጠው ይባላል። የተጠቀሱት የግዳይ ቦታዎችም ጎሊና፣ ሚሌ፣ አላይና፣ እና ኢሳ ናቸው። እነዚህ አካባቢዎች አፋር ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ፣ ከአፋር ብሄረሰብ ውጭ በነዚህ አካባቢዎች አንድ ሰው ከተገኘ የሚጠብቀው ሞት ይሆናል። ስለዚህ አካባቢዎቹ የሚፈሩ፣ የማይደፈሩ ነበሩ። ተሞጋሹ አቶ ምስጋን በላይ በነዚህ አካባቢዎች ዘልቆ በመግባት ከብቶችን ሳር ሰለሚያበላ እንደ ጀግና ይጠራ ነበር።

መንቶ 123 እና 124 ይህንኑ ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው። ግለሰቡ ከከተማ ህይወት ይልቅ የገጠር ህይወት ምርጫ ያለው ይመስላል። ‹‹አደባባይ›› የሚለው የከተማ ህይወትን ወይም

አዘውትሮ ከተማ ውስጥ መገኘትን የሚያመለክት ነው። እሱ ግን እንደዚህ አይነት ውሎ እንደሌለው ወይም ከተማ እንደማያዘወትር መንቶው የሚያመለክተው። ‹‹በሮቹን አርሳችሁ፣ ላሞቹን አልባችሁ በሏቸው ወደ ላይ›› የሚለው ስንኝ፣ እሱ ባለበት አካባቢ ማንም ሀይል መጥቶ ከብቶችን መውሰድ አይችልም፤ ከገባበት ገብቶ ያስመልሰዋል እንደ ማለት ነው።

ተከታዮቹ መንቶዎች የምስጋን በላይን አማሚት የሚያመለክቱ ናቸው። ከላይ እንደተጠቀሰው፣ አፋር ውስጥ ባሉ ቦታዎች ከከብቶች ጋር መዋልና ማደር (ማጓደን) አስፈሪና አስቸጋሪ ነው ። የሚከተሉት መንቶዎች ይህንን የሚረጋግጡ ናቸው።

መንቶ 125 የበላይ ገብሩ ልይ ነገር አበላሽ
ምነው የዚያን ጊዜ አይታቸው በሸሸ
መንቶ 126 ወንዱ ምስጋን በላይ፣ አንጀቱን ታቅፎ፣ እማይደነግጠው
ከዞብል ገስግሶ እስቲደርስ ዳምጠው

ታሪኩ እንዲህ ነው። ምስጋን አፋር ውስጥ ከብቶቹን በጓደና እያረባ በነበረበት ጊዜ፣ ሶስት አፋሮች ድንገት በዱር አገኙት። እነሱ ቀድመው ስላዩት ከመካከላቸው አንደኛው አፋር አድፍጦ ተኩሶ ይመታዋል። የተመታው የሰውነቱ ክፍል ሆዱ አካባቢ እንደነበርና፣ ድግ ታጥቆ ስለነበር ወንድሞቹና የአካባቢው ወጣት በቃሬዛ ይዘውት፣ እቤት እስቲ ደርስ ድረስ ነፍሱ አልወጣም ነበር ይባላል። ይህ ሁኔታ እንስሳትን በሚያወድሱት ቃልግጥሞች ላይ ተነስቷል።

በአጠቃላይ ስለታዋቂ ጀግኖችና ግለሰቦች የተገጠሙት ቃልግጥሞች በአካባቢው ማህበረሰብ በሚገኙት ወጣቶችና ጉልማሶች አስተሳሰብ ውስጥ እንደ አርአያ እንዲታወሱ የሚያደርጉ ናቸው። ጀግንነት በማበረሰቡ አባላት አስተሳሰብ የሚያስሞግስ፣ የሚያስወድስ፣ ወዘተ. መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው ማለት ይቻላል።

6.2.3.3 ፈሪነትን የሚተቹ ቃልግጥሞች

ፍርሀት በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያለው ትርጉም ከጥቃት ራስንና ቤተሰብን አለመከላከል፣ መስዋዕትነትን ለሚጠይቁ ተግባራት ተሳታፊ አለመሆን፣ ለቤተሰብ፣ ለጓደኛ፣ ለወገን ችግር ተቆርቋሪና ተጋሪ አለመሆን፣ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ አመለካከት እንደ ነውር የሚቆጠሩ ተግባራት መገለጫ ነው። ከዚህ በታች ባሉት ቃልግጥሞች፣ በፍርሀት ሰበብ ማህበራዊ

ትችትን የሚያስከትሉ፣ ከአስመሳይነትና ከሴሰኝነት ጋር ተያይዞ እንደ ፈሪ የሚያስቆጥሩትን፣ ሰዋዊ ድክመቶች የሚመለከቱትን እንመለከታለን።

መንቶ 127 አንድ ጉድ እማይደል ሁለት ሶስት ጉድ
የአማች ብረት ይዞ ካጋም መጎድጎድ
መንቶ 128 ኧረ ጀግና ይሙት ፈሪ ይኑር ብሻው
አተላ መሸከም ይመቻል ትክሻው
መንቶ 129 ኧረ ምን ያረጋል የፈሪ ጎረቤት
ገደሉት እያለ ይገባል ወደ ቤት
መንቶ 130 ይኸ ምን ሊሆን የጎበዝ ገራም
ሲያኩት ዝም ይላል እንደ ሀርኮ ላም

በመጀመሪያው መንቶ "ጉድ" ተብለው የቀረቡት ነገሮች፣ አማች የሸለመው መሳሪያ፣ ሸሽትና አጋም ውስጥ መግባት ናቸው። በአካባቢው ማህበረሰብ ባህል፣ ወንድ ልጅ ሲዳር ወላጆች በሰርጉ ዕለት፣ ዳሱ ላይ የሚደረገውን ስጦታ (ሽልማት) ለሰርጉ በታደመው ወዳጅ ዘመድ ፊት በይፋ ይናገራሉ። ይህም የሽልማት ስነ-ስርአት ይባላል። መሳሪያ የሚሸለም አማች፣ ከሚጠበቅበት ማህበራዊ ወይም ቤተሰባዊ ግዴታዎች አንዱ፣ በየትኛውም ሁኔታ በጀግንነት መታወቅ፣ የቤተሰቡን ደህንነት መጠበቅ፣ አጥቂ ባላጋራ ሲመጣ በግንባር መታገል፣ እና መስዋዕት እስከ መሆን መፋለም ነው። በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰው ፈሪ ግን፣ ይህን ቤተሰባዊ ግዳጅ መወጣት አልቻለም። ፈሪነቱ የሚገለፀው በሶስት መንገዶች ነው። አንደኛ፣ መሳሪያ ይዞ መሸሽ፤ ሁለተኛ፣ መሳሪያው አማች የሰጠው (የሸለመው) መሆን፤ ሶስተኛ፣ ሸሽቶ የሚገባበት ጫካ (አጋም) ናቸው። «የብረት መገጊያ» መፈሪያና መታፈሪያ ይሆናል ተብሎ ሲጠበቅ ማፈሪያ ይሆናል። እንዲህ አይነቱ ተግባር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ መተቸት፣ መሰደብ፣ ያስከትላል።

መንቶ128. ፈሪነትን የሚተቸው ከባህሉ በመነሳት ነው። ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ ልጅ በትክሻው ሞፈር ቀንበር፣ መሳሪያ፣ ወዘተ. ይሸከማል እንጂ፣ አተላ መሸከም እንደ «ነውር» የሚታይ ነው። የእሱ ተግባር ለጭነት ከሚያገለግሉት እንስሳት ጋር የተመሳሰለ ሆኗል። በህይወት ቢኖርም ለችግር ጊዜ የማይሆን ስለሆነ፣ ፈሪ በህይወት ከሚኖር ይልቅ፣ የጀግና ሞት የሚያስወድስና የሚያስከብር ስለሆነ፣ ማህበራዊ ተቀባይነት ያስገኛል ማለት ነው።

ፍርሀት በማህበራዊ ህይወት ብቸኛና ገለልተኛ ያደርጋል። ለምንም ማህበራዊ ህይወት ተመራጭ አያደርግም። በመንቶ 129 ላይ የተነፀባረቀው ሀሳብ ይኸው ነው። ፈሪ ሰው ለጉርብትና ተመራጭ አይደለም፤ በጎረቤቱ ላይ ጥቃት ሲደርስ አያግዝም፤ አይጋፈጥም፤ ማለት ነው። መንቶ 130 ላይ እንዲሁ ፈሪ ሰው ከእንስሳት ጋር ተነፃፅሮ ተገልጿል። «ሀርኮ ላም» ማለት ጥጃዋ የሞተባት ላም ማለት ነው። ይችን ላም ወተት ለማለብ ሲፈለግ፣ ከኋላ በኩል ጀርባዋንና የብልቷን አካባቢ በማሸት፣ ብልቷን በትንፋሽ ትነፋለች። በዚህ ጊዜ ወተቷ በቀላሉ ይወርዳል፤ ሲያልቧት አትራገጥም፤ አትዋጋም፤ ማለት ነው። ‹‹ጎበዝ›› የሚለው ቃል በአገባቡ ወጣት ማለት ነው ። ወንድ ልጅ በወጣትነቱ ሀይለኛ፣ ደፋር፣ ቁጡ እንዲሆን ይጠበቃል። ሲነኩት የማይመለስ፣ ለጥቃት የማይበገር እንዲሆን ይጠበቃል። የተጠቀሰው ወጣት ግን ገራም፣ ምንም የማያደርግ ነው።የዘይቤው አላማ ተቀባይነት የሌለውን ባህሪ ማለትም፤ፍርሀትን አጉልቶ በማሳየት፤ባህሪውን ማጣጣል፤ማራከስና ማንኳሰስ ሲሆን፤ ውጤቱም የማህበረሰቡ አባላት እንዲህ ያለውን ባህሪ እንዲጠሉ ማደረግ ነው።

ከዚህ በታች ባሉት ቃልግጥሞች ፈሪዎች ወይም ፍርሀት በተለየ መንገድ የቀረበባቸው ናቸው። ለየት የሚያደርገው አቀራረብ፣ ፈሪዎቹ የተገለፁት፣ ጀግና ለመምሰል በሚያሳዩት ተግባርና እንቅስቃሴ ነው። የጀግና መገለጫ ናቸው የሚባሉትን ነገሮች ያሳያሉ እንጅ፣ ፈሪዎች ናቸው የሚል መልክት የተላለፉባቸው ግጥሞች ናቸው።

አርኬ 131 ኸወደኛም አሉ ጎንቢሶ አሳማሪ
ኸወንደኛም አሉ ዝናር አሳማሪ
ኸወደዚያም አሉ ጎፈሬ አበጣሪ
ስንኸድ በኋላ ስንመለስ መሪ
መንቶ 132 አንጀቱ ጉተና ድግ አደራደር
እነዚያ ሲመጡ ባይተረተር
መንቶ 133 አንበሳ ነው ብየ ተስፋ ጥየበት
ያነዛ ጀመረ እንዳሮጌ ቤት
አርኬ 134 ፈሪ ካሪያ ገዛ ይዋጋ ይመስል
እየሞነጨረ ታፋውን ሊያቆስል
ምን ያረጋል ካሪያ ከታፋ ቢጠጋ
ቢያረግርግ እንጂ እንደ ጠፍር አልጋ

መንቶ 135 መዋጣውን ይዘህ ካልመታህበት
ስጠው ለሴቶቹ ቡና ያፍሉበት
አርኬ 136 አይኑ ትልልቅ ነው ለሴት መገልመጫ
ባቱ ወዳድል ነው ለጭቃ መርገጫ
እነዚያ ሲመጡ አለው መደፈጫ

ጎንቢሶ (አስተጣጠቅ)፣ ዝናር ማሳመርና፣ ጎፈሬ አበጣጠር፣ የጀግና መገለጫዎች ናቸው ተብሎ ይታሰባል። በባህሉ በዚህ አይነት ተክለ ሰውነት የሚታይ ግለሰብ በጀግንነት ተግባር የተፈተነ ተደርጎ ይቆጠራል። ጎንቢሶውን አሳምሮ፣ ዙሪያ ምልስ ጥይት የተሞላበት ዝናር ወገቡ ላይ ታጥቆ፣ ፀጉሩን አሳድጎ፣ ጎፈሬውን አበጥሮ (ከምክሞ)፣ ሲታይ ጀግና ይመስላል።ነገር ግን፣ የፈሪነቱ ሁኔታ የሚነገረው በሌላ መንገድ ነው። በማንኛውም የውጊያ ውሎና ሁኔታ፣ ፊት ላይ (በግንባር) የሚገኝ ሀይል፣ ለጥቃት ተጋላጭ የሚሆንበት አጋጣሚ ሰፊ ሲሆን፣ ከኋላ ያለ ግን፣ አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ አርኬ ፈሪዎቹ የሚገኙት በሁለቱ፣ ማለትም በሚዘምቱትና በሚዘመትባቸው ውስጥ ነው። ‹‹ኸወደኛ›› የሚለው የሚዘምተውን፣ ‹‹ኸወደዚያ›› ደግሞ የሚዘመትባቸውን ወገኖች የሚያመለክቱ ናቸው። በሁለቱም ወገን የሚገኙትን ፈሪዎች የሚያመሳስላቸው ተግባር አንድ አይነት ነው። ይኸውም ወደ ዘመቻ ሲሄድ ከኋላ ከኋላ ይከተላሉ፤ ከዘመቻ መልስ ሲሆን፣ ፊት ፊት ይመራሉ።

የፈሪ አስመሳይነት ከመንቶ 132-136 ባሉት ግጥሞች በተለያየ መንገድ ተደጋግሞ ተገለጿል። የጉተናው (የጎፈሬው) አበጣጠር፣ የድግ አስተጣጠቁ (አደራደሩ)፣ አንበሳ (ጀግና) የመሆኑ፣ ጩቤ (ካሪያ) እና የመዋጣ ዱላ መያዙ፣ የአይኑ ትልልቅነት፣ የባቱ ወደልነት፣ እነዚህ ሁሉ በውጫዊ ገፅታቸው ሲታዩ፣ እንደ ሀይለኛ፣ ደፋርና ጀግና የሚያስቆጥሩ ናቸው። ነገር ግን፣ በግጥሞቹ ውስጥ በዚህ አይነት መንገድ አልተገለጸም። በፍርሀት በመርበትበት የታጠቀው ድግ ይፈታል። አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥመው በቆራጥነት ከመጋፈጥ ይልቅ የሚያለቅስ ነው ። አመኔታ የሚጣልበት አይደለም። የታጠቀው ጩቤ (ካሪያ) ለታይታ እንጂ ጥቅም የሌለው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ የራሱን ሰውነት ከማቁሰል ያለፈ ፋይዳ የለውም ። እንደ ወንዶቹ በያዘው ዱላ ራሱን መከላከል ወይም ጠላቱን መምታት የማይችል ነው። የአይኑ መተለቅ፣ የባቱ መወደል፣ ሴቶችን ለማየትና ጭቃ ለማቡካት እንጅ፣ ወንዶቹ ሲመጡበት ፊት ለፊት የማይጋፈጥ፣ ፈርቶ የሚሸሸግ ነው። ፈሪ በተግባር ሲፈተን ፈሪነቱ ይገለጥበታል እንጂ፣ እንደ ጀግና ተቋቁሞ ሊታገል አይቻልም እንደ ማለት ነው።

በአጠቃላይ በግጥሞቹ ውስጥ የተንፀባረቀው ሀሳብ፣ አስመሳይነት በማህበራዊ ህይወት ውስጥ እንደ ጀግንነት የማያስቆጥር ስለሆነ፣ ፍርሀትን አስወግዶ የጀግንነት ባህሪንና ተግባርን መከተል እደሚያስፈልግ የሚያስገነዝብ ነው።

መንቶ 137 ይኸ የላሞየ ልይ የሴቶቹ አንበሳ
የወንድሙን ገዳይ በደል የሚረሳ
መንቶ 138 በጉያዋ ገበቶ ጡቷን እያሻሸ
እንደ እርጥብ ሽክና በቂጡ ተረሸ
መንቶ 139 በል በል እያለችው በጀዱ እየሞቀው
እንደ ወጊ ሞፈር በቂጡ ያለቀው
መንቶ 140 የሴቶቹ ወዳጅ ከንፈረ ኩሌው
እንባው ኮለል አለ እሾህ ቢወጋው
መንቶ 141 ከወንዶቹ ጎራ ያላየነውን
ከሸርሙጣ ጓዳ ዘመናይ መሆን

እነዚህ መንቶዎች ፈሪነትን የሚያመለክቱት ከሴሰኝነት ተግባር ጋር አያይዘው ነው። ሴሰኛ ወንድ፣ እንደ ፈሪና የማይረባ፣ አካሉ የደከመ፣ ተደርጎ የሚታይ መሆኑን ይገልፃሉ። ‹‹የላሞየ ልይ›› ማለት ‹‹የሴት ልጅ›› የሚለውን ልማዳዊ ስድብ የሚመለከት ነው። በተለምዶ የሴት ልጅ ማለት በስርአት ተኮትኩቶ ያላደገ፣ የሚለውን አሉታዊ መልክት እንዲያስተላልፍ ጥቅም ላይ ይውል የነበረ አባባል ነው። በስርአት አለማደጉን የሚጠቁመው ‹‹የሴቶቹ አንበሳ›› የሚለው ሀረግ ነው። የሱ ብርታትና ጀግንነት የሚታየው በሴቶች ላይ እንጅ፣ ቤተሰቡን ከጥቃት ከመከላከል ወይም የወንድሙን ገዳይ (ደመኛውን) ከመበቀል አንፃር አይደለም የሚል ትችት የተነገረበት ነው።

ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክረው ግጥም፣ መንቶ 141 ላይ የተጠቀሰው ነው ። የወንድ ልጅ ተግባር ተብሎ የሚታመነው ባህላዊ አስተሳሰብ፣ ገበሬ ከሆነ ከሳቢና አምራች፣ መሆን አለበት። ጥቃትን በመከላከል ለቤተሰብ ደራሽና አለኝታ መሆን የሱ ተግባር ነው። በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ተግባራት መከተል ከአንድ ማህበራዊ አባል ከሆነ ግለሰብ የሚጠበቅ ማህበራዊ ግዴታ ነው። የተጠቀሰው ግለሰብ ግን፣ ወንዶች ከሚውሉበት ሳይሆን፣ ከሴቶች ጋር በመዋል እንደ ጀግና ለመታየት የሚሞክር ነው።

ከመንቶ 138-140 ባሉት ግጥሞች ውስጥ፣ የፈሪውን ሴሰኛነትና ድካማነት አጉልተው የሚያሳዩ ሀሳቦች የተንፀባረቁባቸው ናቸው። የአካሉ ደካማነት፣ ከእርጥብ ሸክና እና ከወጊ ሞፈር ጋር ተነፃፅሮ የቀረበ ነው። በለጋው የተቆረጠ ቅል፣ ሲደርቅ ይተረሻል፣ ጠንካራ አይደል። በልማዱ ሴት የሚያበዛ ወንድ ከሰውነቱ ክፍል መቀመጫው (ቂጡ) ይከሳል ተብሎ ይታሰባል። ‹‹.... በቂጡ ተረሸ›› የሚለው ይህንን ለማመልከት የገባ ሀረግ ነው።በመንቶው ውስጥ ያለው ንጽጽራዊ ዘይቤ አላማው የወንዱን (የወጣቱን) እና አካላዊ ደካማነት አጉልቶ በማሳየት ማሸማቀቅና ማሳፈር ነው። ውጤቱም ወጣቶችን ከእንዲህ አይነቱ ባህሪና ተግባር እንዲቆጠቡ ማስተማር ነው ማለት ይቻላል።

‹‹ወጊ ሞፈር›› ማለት፣ የሞፈሩን የመጨረሻ ክፍል የሚመለከት ሲሆን፣ እርፍና ድግር ተዋደው መሬቱን የሚፈረክሰውና ፈሩን የሚያወጣው ነው። ወደ መሬት ውስጥ ጠልቆ በሚገባበት ጊዜ ድግሮቹና የሞፈሩ ቂጥ እየተላጉ ይሄዳሉ፣ በዚደት የሞፈሩ የኋላ ጫፍ (ቂጡ) ይሳሳል። በመጨረሻም እርፉ በገባበት ቀዳዳ የመፈርከስ አጋጣሚ ይፈጠራል። የመንቶ 140 ሁለተኛው ስንኝ ፈሪ አነስተኛ ችግር ሲገጥመው ችግሩን ከመጋፈጥ ይልቅ፣ ማልቀስ የሚቀናው መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ትንተና የምንመለከተው፣ ፍርሀት በማህበረሰቡ አባላት መካከል ተቀባይነት የሌለው ባህሪ መሆኑን ነው። የፍርሀት ባህሪና ተግባር የሚታይበት የማህበረሰቡ አባል ይተቻል፤ ይሰደባል፤ ይናቃል፤ ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት፣ ቃልግጥሞቹ፣ የማህበረሰቡ አባል የሆኑ ግለሰቦች ከፍርሀት፣ ከሴሰኛነት፣ ወዘተ. ባህሪያት ነፃ ሆነው እንዲያድጉና፣ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የማድረጊያ መሳሪያዎች ናቸው ማለት ይችላል።

6.2.4 አካላዊ ቁንጅናን እና ፍቅርን አጉልተው የሚያሳዩ ቃልግጥሞች

ቁንጅና እንደ ተመልካቹ ነው ይባላል:: እንዲሁም ቁንጅና ከውጭ ከሚታየው አካላዊ ሁኔታና መልክ ባሻገር ከውስጥ ከሚመነጭ አስተሳሰብ ጋር እንደሚያያዝ ይታወቃል:: የውጭው አካላዊ ሁኔታ የተመልካችን እይታ በቀላሉ መያዝ የሚችል ነው:: ውስጣዊ ቁንጅና ግን ለየት ያለ አስተውሎትና ልምድ የሚጠይቅ ይመስላል:: በዚህ ምድብ ውስጥ የታዩት ቃልግጥሞች አብዛኞቹ ውጫዊ ወይም አካላዊ ቁንጅናን የሚያመለክቱ ናቸው:: አንዳንድ መንቶዎች ግን ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ውስጣዊ ቁንጅናን የሚያመለክቱ ሆነው ተገኝተዋል::

በመሆኑም፣ በዚህ ምድብ ውስጥ አካላዊ ቁንጅናን ከራስ-ጸጉር እስከ እግር-ጥፍር ያለውን አካላዊ ሁኔታ ለማሳየት በሚያስችል ደረጃ የተገጠው ቃልግጥሞች ተደራጅተዋል:: በተለይ የሴት ልጅ አካላዊ ክፍሎችና የመልክ አይነቶች በሚስብና በሚያስደንቅ ሁኔታ ተገልፀዋል ማለት ይቻላል:: የሴቶች መልክ ንፅፅራዊ በሆነ ስልት በጥልቀት ተገልጿል፡፡ ቅላት፣ ጠይምነት፣ ጥቁረት፣ የቀይ-ዳማ መልኮች በየመንቶዎቹና በየአርኬዎቹ በዘይቤ ታጅብው ቀርበዋል:: ይህ ምድብ 65 ያህል ግጥሞች ያሉት ነው::

የፍቅር መግለጫ ከሆኑት ግጥሞች ውስጥ ሁለት ለየት ያሉ ነገሮች ታይተዋል:: አንደኛው መንቶዎቹ ወይም አርኬዎቹ ቅኔያዊ ባህሪ ያላቸው መሆናቸው ነው:: በዚህም፣ መንታ ወይም ሁለት ፍች ያለው መልክት የሚያስተላልፉ ናቸው :: ሁለተኛው ደግሞ ከእስልምና ሀይማኖት ጋር በተያየዘ ከሀይማኖቱ ተከታዮች መካከል ያሉትን ቆንጆዎች የሚመለከቱ ይዘቶች ያሏቸው ቃልግጥሞች መገኘታቸው ነው፡፡ እነዚህ ግጥሞች በማህበረሰቡ መካከል ያለውን መስተጋብር ከማመልከት በተጨማሪ፣ ተዋዶና ተከባብሮ የመኖሩን እውነታ የሚያሳዩ ናቸው ማለት ይቻላል:: በዚህ ምድብ ውስጥ በአጠቃላይ ወደ 109 ያህል ቃልግጥሞች ተመደበዋል::

በተለምዶ ቁንጅና እንደ ተመልካቹ ነው ይባላል፡፡ የአንዱ ቆንጆ ለሌላው ቆንጆ ላይሆን ይችላል፡፡ ቁንጅና ውጫዊና ውስጣዊ ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡ ውስጣዊ ቁንጅና ከአስተሳሰብ፣ ከአመለካከት፣ ከእምነት፣ ወዘተ. ጋር የተያያዘ ሆኖ በንግግር ወይም በተግባር የሚገለፅ ይሆናል፡፡ ውስጣዊ ቁንጅና የሰው ልጅ ረቂቅ ባህሪያት በተግባር የሚታዩበት ነው፡፡ ውጫዊ ቁንጅና የሚባለው ከሚታየው አካላዊ ገፅታና መልክ ጋር ተያይዞ በተጨባጭ የሚታየውን ውጫዊ አለባበስና ተክለ-ሰውነት ነው፡፡ ፍቅር ከውስጥ ከሚሰማንና ከውጭ ከሚታየን ተጨባጭ ነገር ጋር የተያየዘ ነው፡፡ ከውስጥ የሚሰማን ስሜት ለምናየው ነገር ካለን አስተሳሰብ የሚመነጭ ይሆናል፡፡ ከውጭ የሚሰማን ስሜት የሚመነጨው በምናየው ነገር ከመደሰት፣ ከመማረክ፣ ከመሳብ፣ ወዘተ. ጋር ተያይዞ ነው፡፡

በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ፣ አካላዊ ቁንጅናንና ውበትን በመግለፅ፣ እንዲሁም ከፍቅር ጋር ተያይዞ የሚሰማውን ሰዋዊ ስሜት በማንፀባረቅ፤ የማስደነቅ፣ የማስደሰት፣ እና በአጠቃላይ ውስጣዊ ስሜትን በማስተንፈስ፣ የተዝናኖት ስሜት እንዲሰማን የማድረግ ፋይዳ ያላቸውን ቃልግጥሞች እንመለከታለን፡፡

6.2.4.1 አካላዊ ቁንጅናን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

አካላዊ ቁንጅና ማለት የሚታየው ነገር ውጫዊ ውበት ሆኖ፣ ለተመልካች የተለየ ስሜት የሚፈጥርበት፣ እይታውን ማርኮ የመያዝ ሀይል ያለው፣ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ የሰውነት ገፅታና መልክ ነው። ይህ ተፈጥሮአዊ የሆነ የሰው ልጅ መልክና ገፅታ፣ በሰው ልጆች አመለካከት ዘንድ የተለያየ እይታ ሊፈጥር ይችላል። አንዱ የፀጉር ውበትን ሲያደንቅ፣ ሌላው ጥርስና ከናፍራን ይሆናል። አንዱ ቀይ፣ ሌላው ጥቁር፣ አንዱ አጭር፣ ሌላው ረጅም፣ አንዱ ወፍራም፣ ሌላው ቀጭን በመምረጥ፣ ለምርጫው ያለውን አድናቆት በተለያየ፣ መንገድ ይገለፃል። ከዚህ ቀጥሎ ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር በሚባል ሁኔታ፣ ያሉትን የሰውነት ክፍሎች የሚገልፁትን የቁንጅና የውበት መግለጫ ቃልግጥሞች እንመለከታለን።

መንቶ 142 አውሳ ዝናብ የለም ይጠጣል በመስኖ
ታየኝ ቃሪሳዋ ጤፍ ወለዳ
አርኬ 143 የወለደ ማኛ መስሏል አሚዬዋ
ጠጅ ሳር ጠጅሳር ይሸታል ገላዋ
ባሏም አልጠገባት እንኳን ውሸማዋ
መንቶ 144 የጠጉሯ ብዛቱ እንደጤፍ ክምር
በሁለት ሰሪታ ቀረ በጅምር
መንቶ 145 ራሷ ተሰርቶ ባንድ ቀን አያልቅም
ላንባዲና ይገፍ በስተፊቷ ልቁም
አርኬ 146 ከቀመሌ በላይ ስሙ ነው ዱር ለበሰ
መልጎሚን አንጥፎ ድርምሚን ነው መልበስ
እርቦዋን አንጥፎ ሹሩባዋን መልበስ
አርኬ 147 ፀጉሯ ሀር ነዶ ዘንፈል ዘንፈል ይላል
አይኗ ብር አለሎ ገውለል ገውለል ይላል
ባላገር ሞኝ ነው ባለጅ ናት ይላል
እጅማ ከሌለ ቆማጣ ይባላል።

በነዚህ ቃልግጥሞች ውስጥ የፀጉር ብዛትና ውበት የተገለፀው በዘይቤ ተከሽኖ ነው። ዘይቤዎቹም አነፃፃሪ፣ ተለዋጭና ግነት ናቸው። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቃልግጥሞች የሴቶች ጸጉር ተነጻጽሮ የቀረበው ከጤፍ ዛላና ክምር ጋር ነው። ማኛ ጤፍ ሲወልድ ዛላው ወደ

መሬት ተንገርግጎ እንደሚታይ ሁሉ፣ የሴቶቹም ፀጉር ወደ አንገታቸውና ትከሻቸው ይወርዳል። በነዚህ ቃልግጥሞች ውስጥ ቃሪሳ፣አሚዴና ሰሪታ፣ የሚሉ ቃላት አሉ። ቃሪሳ ያላገቡ ልጃገረዶች የጸጉር አሰራር ነው። ከታች ጋሜ ይሆንና ከግንባሯ እስክ ኋላዋ ድረስ ባለው የጭንቅላቷ መሀል አራትና አምስት ጉንጉን ተሰረቶ ወደኋላ ይወርዳል። ይኽ ጉንጉን ነው ቃሪሳ የሚባለው። እስክታገባ ድረስ በጋሜዋና በቃሪሳዋ መካከል ያለው ጸጉር እየተላጨ ይቆያል። ማግባት ወይም አለማግባቷ በጸጉር አሰራሯ ይታወቃል ማለት ነው። አሚዴ ያገቡ ሴቶች የጸጉር አሰራር ነው። ተጎንጉኖ የወረደው ጸጉር ጫፉ ላይ ይቀመቀማል። ይህ አሰራር ነው አሚዴ የሚባለው። ሰሪታ ማለት የጸጉር ስራ ባለሚያ ናት። በመሆኑም መንቶ 142 ና 143 የጸጉር ውበትና ርዝመት ከወለደ ማኛ ጤፍ ጋር ተነፃጽሮ በመቅረቡ፣ የጸጉሯን ውበት አጉልቶ ለማሳየት አስችሏል ማለት ነው።

መንቶ 144 የተገላጫን ፀጉር አጋንኖ የሚያነፃፅረው ከጤፍ ክምር ጋር በማያያዝ ነው። የጤፍ ክምር ተቆልሎ ወይም ተከምሮ ሲታይና፣ የሴቷ ጸጉር በራሷ ላይ ሲታይ የብዛት መመሳሰል ታይቷል ማለት ነው። መንቶ 145ም እንዲሁ የፀጉሯ ብዛት እጅግ በተጋነነ ሁኔታ የቀረበ ነው። እንደሚታወቀው አንዲት ሴት ፀጉሯን በባህላዊ የፀጉር አሰራር ልትሰራ ብትፈልግ፣ የሚፈጅባት ጊዜ እጅግ ቢበዛ የሁለትና የሶስት ስአት ጊዜ ይሆናል። ይህም ቢሆን ከሚሰራው የፀጉር ብዛትና የአሰራር አይነት አንፃር የሚወሰን ነው። በመንቶዎቹ የተገለጸችው ሴት (እሷ) ፀጉር ግን እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ ሁለት ፀጉር ሰሪዎች እየተጋገዙ፣ ማለትም ጎን ለጎን ሆነው ባንድ ቀን ሰርተው አይጨርሱትም፤ እንዲያውም ሳያጋምሱት በጅምር እንደቀረ ነው። በተለምዶ ‹‹ራሷ ተሰርቶ›› ማለት ፀጉሯ ተሰርቶ እንደ ማለት ነው። ማንኛውም የቋንቋ ተናጋሪ ‹‹ራሷን ልትሰራ ሂዳለች›. የሚል ዐረፍተ-ነገር ቢነገረው ወይም ቢያነብ፣ የሚገባው መልክት ፀጉሯን ልትሰራ መሄዷን ነው። በመሆኑም፣ የመንቶው ሀሳብ፣ ፀጉሯ በአንድ ቀን ተሰርቶ ማለቅ አለመቻሉን በመግለጽ የፀጉሯን ብዛት አጉልቶ ያማየት ነው።

አርኬ 146 የፀጉሯ ብዛትና ርዝመት በተለየ አገላለፅ የቀረበ ነው። ይች ሴት እድሜዋ ወጣት ነው፤ ወጣትነቷ ‹‹መልጎም›› በሚለው ባህላዊ የብር ጌጥና ‹‹እርቦ›› በሚለው ባህላዊ ልብስ ተጠቁሟል። ይች ወጣት ‹‹ቀመሌ›› በሚባለው የገጠር መንደር የምትኖር ናት። የብር ጌጥ (መልጎም) የተሰካበት የልጃገረዶች ቀሚስ የሚለበሰው ከአስራዎቹ ጀምሮ እስከ ሀያዎቹ መጀመሪያ አመት ድረስ፣ ወይም የመጀመሪያ ልጇን እስከወለደች ድረስ ባለው የእድሜ ክልል በሚገኙ ሴት ወጣቶች ነው። የብር ጌጦቹ የሚሰኩት የቀሚሷን ወይም የትፍትፏን ጥልፍ ተከትለው ነው። በቅቤ ከተነከረ ቀሚስ ወይም ትፍትፍ ላይ ነጫጭ የብር መልጎም ሲሰካበት

ያምራል፣ አይን ይማርካል። ከውበቱ ባሻገር የቤተሰብን የሀብት መጠን የሚያመለክትም ይሆናል። የሀብታም ልጆች ናቸው የብር መልጎም ያለው ባህላዊ ልብስ የሚለብሱት።

‹‹እርቦ›› ነጠላ ማለት ነው። በግጥሙ ውስጥ የሚለበሰው እርቦ ሳይሆን የወጣቷ ፀጉር ነው። አገላለፁ በጣም በተጋነነ ስልት፣ ሁለት ፍቅረኞችን አንድ ላይ አድርጎ እንደ አንሶላና ብርድ ልብስ መልበስ ይቻላል የሚል ነው። የመጨረሻው አርኬ 147 የወጣቷ የፀጉርና የአይን ውበት ተነፃፅሮ ቀርቧል። ንፅፅሩም ሙሉ በሙሉ ስለሆነ ተለዋጭ የሚባለው ዘይቤ ነው። የፀጉሯ ልስላሴ ከሀር ነዶ ጋር፣ ብዛቱና ርዝመቱ ደግሞ ‹‹ዘንፈል ዘንፈል›› በሚለው ሀረግ ተገልጿል። የአይኗ ትልቅነትና ንጣት ከብር አለሎ ጋር፤ አስተያየቷ ደግሞ ‹‹ገውለል ገውለል›› በሚለው ጎልተው ተነግረዋል። ገውለል ገውለል ማለት አይኗ ላይ የሚታየው የአይን እንቅስቃሴ ነው።

ከዚህ በታች ባሉት ቃልግጥሞች የጥርስ፣ የከንፈር፣ እና የአይን ተፈጥሯዊ ውበት ጎልቶ የተንፀባረቀባቸው ናቸው። ስለ እያንዳንዳቸው የተገጠሙትን ቀጥለን እንመለከታለን።

መንቶ 148 አንቺየ ጥርስሽን ምኑ ሞቶበታል
ሀሩን አገልድሞ ንጣቱ ገሎታል።
አርኬ149 በጨቤ ተወግቶ ይድን የለም ወይ ሰው
በአንካሴ ተወግቶ ይድን የለም ወይ ሰው
እንዴት በመሳቂያ በጥርስ ይሞታል ሰው
መንቶ 150 ትናንትና ማታ ዛሬ ሌሊት በልሜ
ከጥርሷ ውቅራት ከዘርፉ ላይ ቁሜ
መንቶ 151 አይኗ መጫ መጫ በጣም አያስዋሽም
ከተመለከተ ሳይገል አያመሽም
መንቶ 152 ጉም አይጠነጠን ውሃ አይዘገን
በአይኗ ገርፋኝ ኸደይ ሰንበር እንዳይሆን
አርኬ153 አሁን አይኗ መጣ ተልኳል መሰለኝ
አሁን ጥርሷ መጣ ተልኳል መሰለኝ
እስቲ ግባ በሉት መልክቱን ይንገረኝ

አርኬ 154 አይኗ የሚመስለው የንጋት አጥቢት
ጥርሷ የሚመስለው የጊደር ወተት
ከሷ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት
አርኬ 155 ከንፈሯን ሲስሙት ጉንጯ ይላል ስርቡቅ
አደረች ሌሊቱን እኔ እውጥ፣ እኔ እውጥ
አደርን ሌሊቱን እኔ እውጥ፣እኔ አውጥ
አርኬ 156 ትርኝም እንዳትይ ትርንጎ ገላ አለሽ
ሎሚም እንዳትይ ሎሚ ከንፈር አለሽ
ለምን ሰኞ ሰኞ ቆቦ ትመጫለሽ

መንቶ 148 ላይ የተጠቀሰው የጥርስ ንጣትና ውበት ነው። ገጣሚው የጥርሷን ውበት ያነፃፀረው ከሀዘንተኛ ሰው አለባበስ ጋር ነው። ‹‹ሀሩን አገልድሞ›› ማለት በንቅሳት አምሮና ተውቦ እንደ ማለት ነው። በብዙ የሀገራችን ባህል ዘመድ የሞተበት ሰው ጥቁር መልክ ያለው የሀዘን ልብስ ይለብሳል። በዚህም የቅርብ ዘመድ ሞቶበት እንደሆነ ይታወቃል። በባህሉ፣ ሀዘንተኛ ሰው ሰውነቱን አይጠብቅም ተብሎ ይታመናል። በሀዘን ወቅት ፀጉር ቅቤ ወይም ቅባት አይቀባም። እጅና እግር እንሶሉላ የሚባለውን ባህላዊ መዋቢያ አይሞቅም። ስለዚህ ሀዘንተኛ የሆነ ሰው ቆዳው (ሰውነቱ) ይነጣል፣ ይገረጣል። በመሆኑም የጥርሷ ውቅራት (የድዷ ጥቁረት) ከጥቁር የሀዘን ልብስ ጋር፣ ንጣቱ ደግሞ ከሰውነት ንጣት ጋር ተነፃፅሮ ተገልጿል። አቀራረቡ በማዋየት፣ በማስተዛዘን መልክ የቀረበ ነው።

በማዋየት መልክ የተገለፀው የጥርስ ንጣትና ውበት፣ አርኬ 149 ላይ ለመሞት እንደ ምክንያት ሆኖ ቀርቧል። «ሞት» በዚህ አገባብ ፈፅሞ መማረክ፣ ተሸናፊ መሆንን መመስከር ነው። የአርኬው ሀሳብ ስለት ባላቸው ነገሮች ብንወጋ መዳን እንችላልን፣ የጥርሷ ውበት እጅግ ከማማሩ የተነሳ ሲያዩት የድንጋጤ ስሜት ይፈጥርና ለሞት ያደርሳል የሚል ነው። በባህሉ ጥርስ ውበት እንዲኖረው ከማስዋቢያ መንገድ አንዱ ንቅሳት (ውቅራት) ነው። ንቅሳት ቀዩን ድድ ሰለሚያጠቁረው፣ ከተሰተካከለ ነጭ ጥርስ ጋር ለተመልካች ያምራል። መንቶ 150 የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። ንቅሳት ከነዘርፉ ማለት በጥርስና በጥርስ መሀል ያለው ጥቁር ድድ ነው።

መንቶ 151 እና 152 ላይ የተገለፀው የአይን ውበት ከአስተያየት ጋር ተያይዞ ነው። አስተያየት አይን ተገልጦ በሚያይበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ የሚመለከት ስለሆነ፣ ከአንድ ሰው

አስተያየት መነሳት ሁኔታው የጥላቻ፣ የፍቅር፣ የሀዘኔታ፣ ወዘተ. መሆኑን መረዳት ይቻላል። 151 ላይ የተጠቀሰችው ቆንጆ ብዙ ጊዜ እንደሚባለው አይኗ ትልልቅ አይደለም። ሙጫ ማለት ትንሽ ማለት ነው። የእሷ አይኖች ትንንሽ ናቸው። ነገር ግን፣ በአስተያየቷ ሰውን መሳብና መማረክ የምትችል ናት። እንዲሁም፣ ጉምና ውሃ ይታያሉ እንጅ፣ አይጨበጡም። ሰውነት በአርጩሜ ወይም በአለንጋ ሲገረፍ፣ የተመታው የሰውነት ክፍል ቆስሎ ምልክት (ሰንበር) ያሳያል። በመሆኑም በሁለቱ መንቶዎች የተገለፀው የአይን ውበት፣ በአስተያየት ብቻ ሰውን መሳብና መማረክ የሚችል ነው። አርኬ 153 ከትዝታ (ከትውስታ) ጋር ተያይዞ ነው የአይንና የጥርስ ውበት የተገለፀው። አይንና ጥርስ ሰዋዊ በሆነ አቀራረብ የተላኩትን መልክት አድራሽ ተደርገዋል። መልክት ተቀባዩም በአይነ ህሊና የሚታዩት አይኖቿና ጥርሶቿ እየታወሱት መልክቱን ለመስማት ጓጉቶ እየጠበቀ ነው። በአጠቃላይ መንቶዎቹና አርኬዎቹ የአይን ውበት፣ የጥርስ ንጣት ጎልቶ የተንፀባረቁባቸው ናቸው።

አርኬ 154-156 ባሉት ቃልግጥሞች የአይን፣ የጥርስና የከናፍር ውበቶች ጎልተው እንዲታዩ ከማድረግ በተጨማሪ ሌሎች የውበት ገፅታዎችም ተጠቁመዋል። የገላ (የሰውነት) እና የትንፋሽ ጠረን በአንዳንዶቹ ውስጥ ተገልጿል። በመጀመሪያው አርኬ የተገለፀው የአይኗ ውበት፣ ንጣቱና ትልቅነቱ ሲሆን፣ የተነፃፀረውም ከንጋት አጥቢያ ጋር ነው። የንጋት አጥቢያ (የአጥቢያ ኮከብ) የሚባለው ከሌሊቱ አስራ አንድ ስአት አካባቢ ጀምሮ በምስራቅ በኩል የሚታይ ኮከብ ነው። በአይን ሲታይ፣ ከሌሎቹ ከዋክብት በመጠኑ ትልቅና በብርሀኑ ደማቅ ነው። የጥርሷ ንጣት (ነጭነት) ከወተት ጋር ተነፃፅሯል። እንደሚታወቀው ወተት ነጭ መልክ ያለው ነው። በተለምዶ እንደሚባለው ወደቢጫ የሚጠጋ መልክ ያለው ወተት ብዙ ቅቤ ይወጣዋል ተብሎ ይታሰባል። እንዲህ አይነት መልክ መታየት የሚጀምረው፣ ላሞቹ ሁለተኛና ሶስተኛ ከወለዱ በኋላ ነው። በግጦሙ ውስጥ የተጠቀሰው ወተት፣ መጀመሪያ ጊዜ ከወለደች ጊደር የተገኘ ነው። የጊደር ወተት ደጋግመው ከወለዱት ጋር ሲነፃፀር ነጭነቱ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የጥርሷን የንጣት ደረጃ፣ ከጊደር ወተት ጋር በማነፃጸሩ ንጣቱን አጉልቶ ለማሳየት አስችሏል ማለት ነው።

በፍቅር ግንኙነት ወቅት፣ ሁለት ተፋቃሪዎች የፍቅር ስሜታቸውን ከሚጋሩበት መንገድ አንዱ መሳሳም ነው። ብዙ ጊዜ የሚሳመው የአካል ክፍል ከንፈር ነው። በአርኬ 155 የመጀመሪያ ስንኝ ውስጥ ‹‹ስርቡቅ›› የሚል ቃል አለ። ስርቡቅ ማለት እርጎ ሲጠጣ የሚሰማውን የአፍ ድምፅ የሚመለከት ነው። በሁለተኛው ስንኝ የተገለፀው የአፏ (የትንፋሿ) ጠረን ነው። የትንፋሿ ጠረን የሚያስደስት በመሆኑ፣ ሁለቱ ፍቅረኞች በተደጋጋሚ መሳሳማቸውን

ለማመልከት ‹‹አደርን ሌሊቱን እኔ እውጥ፣ እኔ እውጥ›› በሚለው ስንኝ ተገልጿል። በመጨረሻው አርኬ (156) የተገለፁት የሰውነት ክፍሎች ሰውነት (ገላ) እና ከንፈር ናቸው። የገላዋ ውፍረትና ጠረን ከትርንጎ ሽታ ጋር፣ ከንፈሯ ደግሞ ከሎሚና ከትርንጎ ጋር ተመሳስለው ቀርበዋል።

በአጠቃላይ፣ ከላይ በቀረቡት ቃልግጥሞች እንደታየው ከሴቶች አካላዊ ውበቶች መካከል የሰውነት ልስላሴና ጠረን ጎልተው የተገለፁባቸው የጥርስ ንጣትና ውበት፣ የአይን ትልቅነት፣ ማራኪነት፣ ወዘተ. በዘይቤ የቀረቡ ስለሆኑ፣ አገላለፃቸው፣ ቋንቋቸው፣ ንፅፅራቸው፣ ተገላጮቹን የሰውነት ክፍሎች በተጨባጭ መታየት እንዲችሉ አድርገዋል ማለት ይቻላል።

የሚከተሉት ቃልግጥሞች፣ የአንገትን ውበት የሚገልጹ ናቸው። አንገት እንደ አካላዊ ቁንጅና ሲገለፅ፣ ብዙ ጊዜ ተጋኖ የሚቀርበው ርዝመቱ ነው። ‹‹አንገተ ብርሌ›› ሲባል በአድማጭ ወይም በአንባቢ አይነ ህሊና የሚታው ርዝመቱና ቅጥነቱ ነው።

መንቶ 157 ዋጃ ወዲያ ማዶ ጌደሩ ነው ቤቷ
ያለመደገፊያ አይቆምም አንገቷ
አርኬ 158 አስራ ሁለት ነው ያንገቷ ቅርድ
ማሽላም አትበላ ጤፉንም የግድ
ጠላም አትጠጣ ጠጁንም የግድ

በመጀመሪያው መንቶ የተገለፀችው አንገተ-ረጅም ቆንጆ የምትገኘው ‹‹ጌደሩ›› ከምትባለው የገጠር መንደር ነው። አገላለፁ እጅግ በተጋነነ ሁኔታ የቀረበ በመሆኑ፣ አንገቷ ያለድጋፍ ቀጥ ብሎ መቆም እንደማይችል ነው። አርኬ 158.በሁለተኛውና በሶተኛው ስንኞች ምግብና መጠጥ ተጠቅሰው ቀርበዋል። ሰብሎቹ ማሽላና ጤፍ ሲሆኑ፣ በአገባባቸው የማሽላ እንጀራ፣ የጤፍ እንጀራ ማለት ነው። የማሽላ እንጀራ፣ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር ለምግብ አይሆንም። በማህበረሰቡ አመለካከት የማሽላ እንጀራ የሚዘወተረው በድሀው የህብረተሰብ ክፍል ነው። ጠላም እንዲሁ ከሀብትና ከደረጃ ጋር የሚያያዝ ነው። የጤፍ እንጀራ መመገብና፣ የማር ጠጅ መጠጣት፣ በሰዎች ዘንድ እንደ ትልቅ የህይወት አኗኗር ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በዚህ አርኬ ላይ የተገለፀችው ቆንጆ አንገቷ ረጅም ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ሲያዩት የሚያምር ቅርፅ (ቅርድ) ያለው ነው። ቅርድ በአንገት የፊ ለፊት ክፍል የሚታዩ ቀጫጭን መስመሮችን የሚመለከት ነው። በአንገት ዙሪያ እንደ ክብ ሆነው የሚታዩ ናቸው። የመስመሮች ብዛት አስራ ሁለት

መሆኑ የአንገቷን ርዝመት አጉልተው ያሳያሉ። እጅግ ያማረች ስለሆነች፣ ያገኘችውን የምትበላና የምትጠጣ አይደለችም። ኩሩ ነች፣ መርጣ ትመገባለች፣ መርጣ ትጠጣለች፣ እንደ ማለት ነው። በሁለቱ ግጥሞች ውስጥ የተገለፀችው ወጣት (ሴት) የአንገቷ ውበት ተጋንኖ የቀረበ በመሆኑ አገላለፁ በአይነ ህሊና እንዲታይ አስችሏል ማለት ነው።

አካላዊ ቁንጅናን ከሚያመለክቱ ቃልግጥሞች መካከል የሚከተሉት ደግሞ፣ ስለ ጡት እና ስለ ደረት የተገጠሙ ናቸው። የደረት ስፋት እና የሴት ልጅ ጡት፣ የተመልካችን አይን የመሳብ ሀይል አላቸው። እነዚህ የሰውነት ክፍሎች በሚከተለው መንገድ ተገልፀው ይገኛሉ።

መንቶ 159 አይኗም እንኳን እንኳን፣ ጥርሷም እንኳን እንኳን
መከዳው ደረቷ ያስተክላል ድንኳን
መንቶ 160 የቁልቁለት መንገድ ለጅብ አይመችም
ጡቷ ከደረቷ ያለው ግችም ግችም
መንቶ 161 ሳንቃው ደረቷ ነው ያጣለው ሰውን
እስቲ ሸሸግ አርጉት ያጡት እንደሆን።

በመጀመሪያው መንቶ የተገለፀው የደረቷ ስፋትና ቅላት ነው። ‹‹መከዳ›› ማለት መልኩ ቀይ የሆነ ለምንጣፍ የሚያገለግል ነው። የደረቷ ስፋት ‹‹ድንኳን ያስተክላል›› በማለት በተጋነነ ሁኔታ ተገልጿል። ከደረቷ ስፋት በተጨማሪ የሰውነቷ ቅላት ‹‹መከዳው ደረቷ›› በሚለው ሀረግ አብሮ ተጠቁሟል። መንቶ 160 ላይ የተገለፀው የጡቷ ሁኔታ በተለየ አቀራረብ የተገለፀ ነው። በመንቶው ውስጥ ያሉት ሁለቱ ስንኞች የሀሳብ ዝምድና ያላቸው አይመስልም። የጅብ አንደኛው የኋላ እግር አጭር ስለሆነ፣ ቁልቁለት በሚወርደበት ጊዜ፣ ወደ ፊት እየተደፋ ይቸገራል፤ እንደ ልቡ ቁልቁለቱን መውረድ አይችልም እየተባለ ይነገራል። ሁለተኛው ስንኝ የጡቷን አቀማመጥ የሚያመለክት ነው። ‹‹ግችም፣ ግችም›› የሚለው ሀረግ ‹‹ቁጭ ቁጭ›› ማለት ነው። ይህ አገላለፅ ጡቷ ያልወደቀ መሆኑን አጣምሮ የሚሳይ ነው። ሁለቱን ስንኞች ሊያስተሳስር የሚችል ሀሳብ የቁልቁለቱ ሁኔታ ነው። ለጅብ የማይመቸው የቁልቁለት መንገድ፣ እሷ ስትሄድበት፣ አረማመዷ የተለየ ስለሚሆን፣ የጡቶቿ እንቅስቃሴ ከአረማመዷ ጋር ‹‹ዘለል፣ ዘለል›› እያሉ የሚታዩ መሆኑን ያሳያል ማለት ነው።

መንቶ 161 ደግሞ ቅኔያዊ በሆነ መንገድ የደረቷ ስፋትና የጡቶቿ ሁኔታ ተገልጿል። የደረቷ ስፋት ከቤት በር (ሳንቃ) ጋር ተነጻፅሮ ቀርቧል። ንፅፅሩ ሙሉ በሙሉ ስለሆነ ተለዋጭ ዘይቤ የሚባለው ነው። የሳንቃው ስፋት የደረቷን መጠን ወክሎ የቀረበ ነው። ሚስጥሩ (ቅኔው) በደረቷ ስፋት አማካኝነት የጡቷ ሁኔታ የተገለፀበት ነው። ዋናው ሀሳብ የደረቷ ስፋት ሳይሆን የጡቶቿ ውበት ነው የሰውን አይን የማረከው ማለት ነው። ይኸውም ‹‹ያ ጡት እንደሆን›› በሚለው ቅኔያዊ አገላለፅ ሀሳቡ ተላልፏል።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች ስለ ወገብ የሰውነት ክፍል የተገጠሙትን እንመለከታለን። ይህ ሰውነት ክፍል ቀጠን፣ ረዘም፣ ብሎ ሲታይ አይን ይማርካል። በዚህም እንደ አንድ የቁንጅና መለኪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ማለት ነው። ቃልግጥሞቹን እንመልከት።

መንቶ 162 በዋ ንጉስ ጋሌ ስንደዶ ማለፊያ
ወገቧ ቀጭን ነው እንደ አሳ መጥለፊያ
መንቶ 163 ባታ ተረከሂ ስጋው ተነባብሮ
ወገቧ ቀጭን ነው አልበላም ወይ አብሮ
መንቶ 164 ወግድ ጋሪያ ሌንጫ ቆቦ/ዋጃ ሰው ልይበት
የሚጠቀለለው ሽንጧ እንደ ወረቀት
መንቶ 165 ወገቧ እንደጭራ የመነመነው
ይበጠሳል ብየ እኔም አላምነው።

በመጀመሪው መንቶ የወገቧ ቅጥነት ከአሳ መጥለፊያ (ከመንጠቆ ክር) ጋር ተነፃፅሮ ነው የቀረበው። በዚህ መንገድ የተገለፀችው ቆንጆ የምትገኘው፣ በዋ እና ንጉስ-ጋሌ በሚባሉት የገጠር አካባቢዎች ነው። እነዚህ አካባቢዎች ከቆቦ ከተማ በስተሰሜን ምዕራብ የሚገኙ ናቸው። ቀደም ባለው ጊዜ በነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ከእርሻ ስራ ጋር ከብት የማርባት ልማድ ስለነበረው ወተትና ቅቤ እንደልብ ሚገኝበት ነበር። ወተት ሰውነትን ያጠነክራል እንጅ አያወፍርም ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ የወገቧ ቅጥነት ከጠጣችው ወተት ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚያመልክት መንቶ ነው። መንቶ 163 ላይ የወገብ ቁንጅና (ውበት) ከሌላው የሰውነት ክፍል ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው። የሴት ልጅ የእግር ቅርፅ እንደ አካላዊ ውበት ይቆጠራል። በጣም ወፍራም ከሆነ መሰደቢያ ይሆናል። በጣም ቀጭን ከሆነም እንዲሁ ያሰድባል። ወፍራሙን ‹‹ዘነዘና እግር››፣ ቀጭኑን «ጭራሮ እግር›› ያስብላሉ። በመሆኑም፣

የባቷና የተረከሟ ውፍረት ከወገቧ ጋር ሲነፃፀር፣ ወገቧ ከባቷ ያነሰ በመሆኑ፣ ቅጥነቱን አጉልቶ አሳቷል ማለት ነው።

164 እና 165 ላይ ባሉት መንቶዎች የወገቧ ቅጥነት እጅግ በተጋነነ አገላለፅ ቀርቧል። ከቅጥነቱ በተጨማሪ የመተጣጠፍ ባህሪ ያለው መሆኑም ተገልጿል። በመጀመሪው መንቶ ውስጥ አንድ ተራራ ተጠቅሷል። ይህ ተራራ (ጋሪያ ሌንጫ) የሚገኘው በቆቦ እና በዋጃ ከተሞች መካከል ነው። ከቆቦ በስተሰሜን፣ ከዋጃ በስተደቡብ የሚገኝ ትልቅ ተራራ ነው። ከሁለቱ ከተሞች አንፃር ሲታይ ቅርበቱ ለቆቦ ነው። ሁለቱን ከተሞች እንዳይተያዩ ይጋርዳል። በሁለቱ ከተሞች ያሉት ሴቶች ግን፣ ተመሳሳይ አካላዊ ቁንጅና ያላቸው ናቸው።

የወገቧ ቅጥነትና ተጣጣፊነት ከወረቀት መጠቅለል ጋር ተነፃፅሮ ተገልጿል። መንቶ 164 የወገቧ ቅጥነት ከጭራ ጋር የተመሳሰለ ነው። ቅጥነቱ ከፍተኛ መሆኑ ‹‹የመነመነው...›› በሚለው ሀረግ ተጠቁሟል። ጭራ (አንዲ ዘለላ) በቀላሉ የመበጠስ እድል አለው። የልጅቷ ወገብ እንዲሁ እንደ ጭራው ቀጭን ስለሆነ፣ በቀላሉ ይጎዳል፤ የሚል ጭንቀት የሚፈጥር ሆኗል። ‹‹ ይበጠሳል ብየ እኔም አላምነው›› የሚለው ስንኝ ይህንን ጭንቀት የሚያረጋግጥ ነው። በነዚህ አራት መንቶዎች አማካኝነት የተገላጯ ሴት የወገብ ቅጥነትና ውበት በዘይቤ የቀረበ በመሆኑ፣በአይነ-ህሊና የመታየት ሁኔታው ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል። የአሳ ማስገሪያው፣ ጭራው፣ የወረቀቱ መጠቅለል፣ የወገቧን አካላዊ ውበት አጉልተው ለማሳየት ያገለገሉ ማንፀሪያዎች ናቸው።

እስካሁን ያየናቸው ቃል ግጥሞች አካላዊ ቁንጅናን በተጨባጭ ለማሳየት የሚችሉ እንደሆነ ከገለፃው እና ከትንተናው መረዳት ይቻላል። ከዚህ በታች ባሉት ቃል ግጥሞ እንደውበት (ቁንጅና) መለኪያ ሆኖ የቀረበው አካላዊ ቁንጅና ሳይሆን አረማመድና መልክ ናቸው። ባብዛኛው የማህበረሰባችን አስተያየት ተለይተው የሚታወቁት ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ እና ቀይ ዳማ የሚባሉት መልኮች ናቸው። አረማመድ የሚያመለክቱን አስቀድመን፣ መልክን አስከትለን እንመለከታለን።

መንቶ 166 ስትሄድ ድንቦል ድንቦል ስተኛ ወርድ የላት
እንደ ደጋ እንጆሪ መጠገቢያም የላት
መንቶ 167 እንኳን አርግዛና ሽል ይዛ በሆዷ
ደንቦል ደንቦል ነው ወትሮም አካኸዷ

የመጀመሪያው መንቶ የተገላጫን ቁመትና ውፍረት ከማሳየቱ በተጨማሪ ቁንጅናዋን ያመለክታል። ‹‹ደንቦል ደንቦል›› የሚለው ሀረግ ወፍረቷንና የእግር አጣጣሏን (አረማመዷን) ያሳያል። ‹‹ወርድ የላት›› ማለት ሰፊ የመኝታ ቦታ (ስፍራ) አትፈጅም የሚል ፍች ያለው ነው። እንዲሁም፣ ውበትና ቁንጅዋ ከደጋ እንጆሪ ጋር ተመሳሳሉ የቀረበ ነው። የደጋ እንጆሪ ሲበሉት ይጣፍጣል፣ አይጠገብም ይባላል። የእሷ ፍቅርም እንዲሁ እንደማለት ነው። ብዙ ሴቶች እርግዝና ላይ ሲሆኑ፣ ሰውነታቸው ወፍራም መስሎ ይታያል። ‹‹ሽል›› ማለት ፅንስ ማለት ነው። የፅንሱ በሆዷ ውስጥ መሆን፣ ወፍረቷን ጨምሮ አረማመዷን ይበልጥ አሳምሮታ ማለት ነው። ‹‹ወትሮም›› ማለት ከማርገዟ በፊት ማለት ነው። እንኳን አሁን ሰውነቷ ጨምሮ ይቅርና ፊትም ቢሆን አረማመዷ ማራኪ ነበር የሚል ነው።

አካላዊ ቁንጅና ከመልክ ጋር ተስማምቶ በአንድ አካል ላይ ሲገኝ የተመልካችን እይታ ሊማርክ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ይሆናል። ቅላት፣ ጠይምነት፣ ጥቁረት፣ ቀይ ዳማነት፣ በሚከተሉት ቃልግጥሞች በተለያየ መንገድ ተንፀባርቋል። እነዚህ መልኮች ያሏቸው ሰዎች ከሚያምር ተክለ ሰውነት ጋር ተዋህደው ሲታይ ተመልካችን ይስባሉ፣ እንደ ባህሉም ቃል ግጥሞች እየተፈጠሩ ይዘፈንላቸዋል። ለፍቅር ይመረጣሉ፣ ይወደዳሉ፣ ማለት ነው። ከዚህ ቀጥሎ የምናያቸው ቃልግጥሞች ከተለያዩ የሰውነት መልኮች ጋር ተያይዘው የተገጠሙ ናቸው።

መንቶ 168 ነጫጭ ላም ያለው ቀይ ሴት ያገባ
ይኖራል ዘላለም ጀነት እንደገባ
መንቶ 169 እንደተመታ ሰው ደም እንዳጠለቀው
የገላዋ ቅላት (ጥራት) ቀሚሷን ዘለቀው
መንቶ 170 በሳንቃው ቀዳዳ ቢታየኝ ደረቷ
እኔስ ብየ ነበር ተቃጠለ ቤቷ
አርኬ 171 ራቴንም በላሁ በኑግ አጣብቂ
ምሳዬን በላሁ በኑግ አጣብቂ
ጥቁር መወደዱን እኔ መች አውቂ
መንቶ 172 ያደረ እንጆራና ጥቁር ሰው አንድ ነው
ለአይን አይመስልም እንጅ ለበላው ጤና ነው
መንቶ 173 የጠይም አደራ አታኑሩብኝ
እበላታለሁኝ ይሉኝታም የለኝ

መንቶ 174 የጠይም አደራ አኑረው ኸቤቱ
ሲርበኝ በላኂት ሲታጠፍ አንጀቱ
መንቶ 175 ጠይም ተፈትፍቶ ሲበሉ ደርሽ
ይበቃሀል አሉኝ አንደየ ጎርሽ
መንቶ 176 ለቀይ ሴት ቢሉኝ በርበሬ በላሁኝ
ለጥቁር ሴት ቢሉኝ አቦል ቡን ጠጣሁኝ
ለጠይም ሴት ቢሉኝ ምንጭ ውሃ ጠጣሁኝ
ለዚያች ለቀይ ዳማ መድሀኒት አጣሁኝ

ከመንቶ 168 -170 ባሉት ቃልግጥሞች እንደምናስተውለው የግጥሞቹ ሀሳቦች፣ ስለቀይ ሴት መልክ የሚገልፁ ናቸው። ይች ሴት ቅላቷ ከልብሷ በላይ ዘልቆ የሚታይ ነው። የመጀመሪያው መንቶ «ቀይ ሴት ማግባት የደስታ ምንጭ ናት» ይላል። እሷን ያገባ ሰው እድሜ ልኩን በደስታ እንደሚኖር አድርጎ ነው የሚገልፀው። ‹‹ጀነት›› ማለት ገነት ሲሆን፤ ፍችውም የደስታ፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ ወዘተ. ህይወት ያለበት እንደማለት ነው። ከላሞች ነጫጭ መልክ “ያላቸው ለአይን ደስ እንደሚያሰኝ ሁሉ፣ ቀያይ ሴቶችም የደስታ ምንጭ ይሆናሉ ማለት ነው። መንቶ 169 ላይ የሴቷ ቅላት የተነፃፀረው በደም ከተነከረ ሰው ጋር ነው። የተመታ ሰው ብዙ ደም ሲፈሰው፣ የልብሱ መልክ ተለውጦ እንደሚታይ ሁሉ፣ የሴትዮዋ የሰውነት ቅላት ወይም ጥራት ከቀሚሷ አልፎ ይታያል ማለት ነው። አገላለፁ ከፍተኛ ግነት ያለበት በመሆኑ፣ አቀራረቡ ቅላቷን የሚያሳይ ነው። በሶስተኛው መንቶ ቅላቷ፣ ከእሳት ነበልባል ወይም ፍም ጋር ተያይዞ የተገለፀ ነው።

አርኬ 171 እና መንቶ 172 ላይ ባሉት ቃልግጥሞች የተገለፀው መልክ የጥቁር ሰው ወይም ሴት መልክ ነው። በተለምዶ የጥቁር ሰው ቁንጅናና ውበት ጎልቶ የሚታየው አይንና ጥርስ ላይ ነው ይባላል። ከጥቁር መልክ ላይ ነጭ ጥርስ፣ ትልልቅና አይነ ውሃው ነጭ አይን፣ ተመልካችን ይሰባሉ፣ ደምቀው ይታያሉ። ነገር ግን በሁለቱ ቃል ግጥሞች ውስጥ የጥቁር ሰው መልክ ተመሳስሎ የቀረበው ከምግብ ጋር ነው። ኑግ፣ የቅባት እህል ሲሆን፣ ተቆልቶና ተወቅጦ ለምግብ ማባያ በመሆን ያገለግላል። ጣዕሙም ተወዳጅ ነው። እንጀራ አብዛኛው የሀገራችን ህዝብ ለምግብነት የሚያገለግል የዘወትር ምግብ ነው። እንጀራ በተጋገረበት እለት ሲነኩትና ሲበሉት ለስላሳ ስለሆነ ደስ ይላል። ውሎ ሲያድር ግን የመድረቅ ባህሪ ስለሚኖረው ልስላሴ የለውም። እንዲህም ሆኖ፣ ሁሉም ሰው ይመገበዋል። በግጥሞቹ ውስጥ ያደረ እንጀራና የኑግ እህል ለጥቁር ሰው መልክ ምሳሌ ሆነው ቀርበዋል። አመሳሰሉ አወንታዊ ነው

ማለት ይቻላል። በመሆኑም ሁለቱም ሲያዩዋቸው አይንን በቀላሉ የመሳብ ሀይል ባይኖራቸውም፣ ለምግብ ሲውሉ ግን ጥቅም አላቸው ማለት ነው። ከዚህ አንፃር ጥቁር መልክ ያላቸው ሰዎች ጥቁረታቸው አይንን የማይሰብ ቢመስልም፣ ለፍቅርና ለመውደድ ተመራጮች ናቸው እንደማለት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት መንቶዎች ስለጠይም ሴት ውበትና መልክ የተገጠሙትን እንመለከታለን። ጠይም የሚባለው የመልክ አይነት በቀይና በጥቁር መካከል የሚሆን መልክ ነው። የመልክ አይነቱ ለወንድ ለሴት መግለጫ ሊሆን ቢችልም፣ ቀጥሎ ባሉት ግጥሞች ውስጥ ግን የሚገለፀው፣ የጠይም ሴት መልክና ውበት ነው። ‹‹አንቺ ያጭር ረጅም...›› የሚለው ሀረግ የሴቷ ቁመና በአያዋ ዘይቤ የተገለፀበት ነው። ቁመቷ መካከለኛ የሚባል ሲሆን ሰውነቷ ለስላሳና ወፍረቷም መካከለኛ እሚባል ነው። ‹‹ሲርበኝ በላኋት፣.... እበላታሁኝ...›› የሚሉት ሀረጎች አገላለፃቸው የጠይምን ሴት የፍቅር ሀያልነት በእጅጉ ጎልቶ እንዲታይ ያደረጉ ናቸው።አፍቃሪዋ በፍቅሯ እጅግ ከመማረኩ የተነሳ ለሰዎች ወቀሳ ወይም ይሉኝታ የሚባለው ማህበራዊ ትችት፣ እንደማያስጨንቀው የሚያመለክት ነው። ጠይም መልክ (ሰው) የብዙ ሰው የፍቅር ምርጫ እንደሆነ ‹‹ጠይም ተፈትፍቶ ሲበሉ ደርሽ›› የሚለው ስንኝ የሚያረጋግጥ ይመስላል።

አርኬ 176 ያለው ቃልግጥም ለሴትና ለወንድ ሊገጠም የሚል አቀራረብ ያለው ነው። ‹‹ለቀይ ሴት›› የሚለው ‹‹ለቀይ ሰው›› ይሆናል። ለጥቁር ሴት ‹‹የሚለውም›› ለጥቁር ሰው›› ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ‹‹ለጠይም ሴት›› የሚለው ‹‹ለጠይም ሰው›› ማለት ይቻላል። በመጨረሻ ስንኝ ያለው ‹‹ለዚያች ለቀይ ዳማ›› የሚለው ሀረግም ‹‹ለዚያ ለቀይ ዳማ›› ይሆናል ማለት ነው። ቀይ ዳማ የሚባለው መልክ፣ በቀይና በጠይም መልክ መካከል ያለው ነው። የግጥሙ ሀሳብ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም መልክ ላላቸው ሰዎች የፍቅር ማስታገሻ የሚሆን መደሀኒት ሲገኝላቸው፣ የቀይ ዳማ መልክ ያላቸው ግን ማስታገሻ የማይገኝላቸው እንደሆነ ነው። በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ግጥሞች በአካባቢው ተመራጭነት ባላቸው የሰው ልጅ መልኮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። አላማቸውም የሰዎችን መልክ በማወደስ የተፈቃሪውን ቁንጅናና ውበት አጉልቶ ማሳየት ላይ ነው።

6.2.4.2 አጠቃላይ የፍቅር ስሜትን የሚገልፁ ቃልግጥሞች

Okpewho (1992፣ 138-139) ስለ ፍቅር ሲገልጹ፡-

> ፍቅር ማለት ለረጅም ጊዜ በሚቆይ ሁኔታ ስለ አንድ ሰው ወይም ነገር.. የሚሰማን ስሜት ሆኖ የሀገር የጀግና፣ የጎሳ ወይም የዘር ፍቅርን ይጨምራ፡፡ ... አፍሪካ ውስጥ በብዛት ከሚታወቁት የፍቅር አይነቶ አንዱ በሴትና በወንድ መካከል ያው ፍቅር ነው፡፡ ይህም የሴቷን ወይም የወንዱን አካላዊ ቁንጅና በማድነቅ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሁለቱን በፍቅር ግንኙነት የመፈላለግን ሁኔታ አመላካች ነው... ይላሉ፡፡

በዚህ ንዑስ ክፍል የምናያቸው ቃል ግጥሞች የፍቅር ስሜትን፣ በናፍቆትና በፍቅር ከመማረክ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቀረቡትን ይሆናል፡፡ ቃል ግጥሞቹ በማንኛውም ሁኔታ ሲቀርቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ አላማቸው የፍቅርንና የናፍቆትን አስጨናቂነት ማሳየት ነው፡፡

መንቶ 177 እስቲ ብሩ ጎራ አላይና ዝለቂ
ምን አረንዛ ሆድ ነሽ ሰው እማትናፍቂ
መንቶ 178 እነጋ እነጋ ሲል ፍቅር አስለምዳኝ
በአባቷ እምላለሁ አባቴን አስክዳኝ
መንቶ 179 እህህ ነው እንጅ ያከሳው ደረቴን
መች ሳልበላ አድራለሁ አንድ እንጀራ ራቴን
መንቶ 180 ከሳሁ መነመንኩኝ ነጭ እንጨቴ ወጣ
እንግዲህ ቢሸጡኝ ዋጋም አላወጣ

መንቶ 177 ላይ በናፍቆት የሚሰቃየው ሰው የሚገኘው በጓደና (አፋር ውስጥ ከብቶችን እያረባ) ነው፡፡ ‹‹ብሩ ጎራና አላይና›› የሚባሉ አካባቢዎች ቀደም ሲል በነበረው የአስተዳደር መዋቅር (ከ1983 ዓ/ም በፊት) በራያና ቆቦ አውራጃ ከሚገኙት የአፋር አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙ ጀነበሩ፡፡ በመሆኑም አፍቃሪ ሰው ፍቅረኛው ወደ አለችበት ሂዶ በቀላሉ መገናኘት ባለመቻሉ፣ በናፍቆት የተጎ ይመስላል፡፡ ‹‹አረንዛ ሆድ›› የሚለው ሀረግ በአገባቡ ጨካኝ፣ ልበ ደንዳና፣ የሚል ፍች ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ልብሽ ይራራልኝና ከለሁበት ቦታ መጥተሽ ናፍቆቴን

ልወጣ የሚል መልክት ያለው ነው። ቀጥሎ ያለው መንቶ ተፋቃሪዎች የሚገናኙት ባልተለመደ ስአት ይመስላል። ብዙ ጊዜ የተለመደው የፍቅር ግንኙነት በቀንና በማታ ነው። የእነሱ ግን ሌሊቱ ሊነጋጋ (እነጋ እነጋ) ሲል ነው። በዚህም የፍቅር ግንኙነት አፍቃሪ ማንነቱን እስከመተው ደርሷል። በባህሉ ብዙ ሰዎች የተናገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሲምሉ፣ የሚወዱትን ሰው ስም (አባት፣ እናት፣ ወዘተ) ወይም የሚያምኑበትን አምላክ ወይም ታቦት እየጠሩ ነው። መንቶ 178 ግን ይህንን የሚያመለክት አይደለም። እጅግ ከማፍቀሩ የተነሳ ማንነቱን ለውጦ በእሷ ፍቅር ስር ወድቋል ። ‹‹በአባቷ እምላለሁ፣ አባቴን አስክዳኝ›› የሚለው ስንኝ ይህንን ያረጋግጣል።

መንቶ 179 እንዲሁ አፍቃሪው ወይም አፍቃሪዋ ዘወትር የሚታያቸው ያፈቀሩት ሰው ስለሆነ፣ ሌት ተቀን እሱን ወይም እሷን በማሰብ የሚውሉ ናቸው። ‹‹እህህ ነው እንጅ...›› የሚለው ሀረግ ናፍቆትን፣ መጨነቅን፣ በሀሳብ መጠመድን፣ የሚያመለክት ነው። በናፍቆትና በሀሳብ የሚጨነቅ ሰው፣ የአካልና የመንፈስ ድካም ስለሚያጋጥመው ሰውነቱ ይከሳል፤ ይጎሳቆላል፤ ቢመገብም ወደሰውነቱ አይሄድም ተብሎ ይታሰባል። የፍቅርና የናፍቆት ርሀብ፣ ከምግብ ርሀብ የበለጠ ሊጎዳ የሚችል መሆኑን ይጠቁማል። ይህንኑ ሁኔታ በሚያጠናክር መልኩ መንቶ 180 የናፍቆትን ጉዳት አጎልቶ ያሳያል። ‹‹ከሳሁ መነመንኩኝ ነጭ እንጨቱ ወጣ›› የሚለው ስንኝ ‹‹እህህ ነው እንጅ ያከሳው ደረቴን›› ከሚለው ጋር በሀሳብ ይመሳሰላሉ በውጤት ይያያዛል። መንቶ 179 የመንቶ 180 ውጤት ነው። ውጤቱም የሰውነት ከመጠን በላይ መክሳትና የቆዳ መገርጣት ወይም መድረቅ ናቸው። ‹‹ከእንግዲህ ቢሸጡኝ ዋጋም አላወጣ›› የሚለው ስንኝ እንደገና ማፍቀር አለመቻልን የሚያመለክት ስለሆነ፣ የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ተንፀባርቆበታል ማለት ነው። በፍቅር መማረክን ከሚያመለክቱ ቃልግጥሞች መካከል የሚከተሉትን እንመለከታለን።

መንቶ 181 አላማጣ ወዲህ ስሙ ሰበር ጉማ
ልቤን ወሰደችው ባገልግል ለጉማ
መንቶ 182 አባቷም ይላሉ በላይነሽ፣ በላይነሽ
እኔም እላታለሁ ከልቤ ላይ ተነሽ
መንቶ 183 ሰው ወድጀ አላውቅም አምላክ ከፈጠረኝ
ልወድ ነው መሰል ልቤን ባር ባር አለኝ
መንቶ 184 እሷ ጠይም አሳ ምንጣፏ ጥቁር
ያብሰከስክኛል እንደ ነፍሰ ጡር

መንቶዎቹ ልብን እንደፍቅር ምርኮኛ አድርገው የሚያቀርቡ ናቸው። ‹‹ልቤን ወሰደችው፣ ከልቤ ላይ ተነሽ፣ ልቤን (ሆዴን) ባር ባር አለኝ›› የሚሉት አገላለፆች ይህንን የሚያመለክቱ ናቸው። በተለምዶ እውነተኛ ፍቅር ከልብ በሚመነጭ ትክክለኛ ስሜት ይንፀባረቃል፤ ከልብ ከወደዱ ሁሉም ነገር ለወደዱት ይሆናል የሚል አስተሳሰብ ስላለ፣ መንቶዎቹም ይህንን መሰረት አድርገው የተገጠሙ ናቸው። ‹‹ሰበር ጉማ›› በዋጃና በአላማጣ መካከል የሚገኝ የገጠር መንደር ሲሆን፣ ልቡን የማረከችው፣ በፍቅር ያሸነፈችው ሴት የምትገኝበት ነው። ብዙ ጊዜ በአገልግል የሚያዘው ምግብ ነው። ስለዚህ፣ ሀሳቡ፣ ልቤን በፍቅር ልትበላው፣ በፍቅር ልትማርከኝ ነው የሚል ነው። መንቶ 182 ላይ የተጠቀሰችው ሴት (በላይነሽ) ስሙ ሁለት ፍች ያለው ነው። አንደኛው በመጠሪያ የሚያገለግለው ስም ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከሁሉም በላይ ቆንጆ ነሽ፤ ሁሉንም በውበት ትበልጫለሽ፤ ከሁሉም በላይ ስለሆንሽ ልቤን ማርክሸዋል የሚል ነው። ሆዴን(ልቤን) ባር ባር አለኝ የሚለውም ለማፍቀር ከማሰብ ስሜት አንጻር ፍረሀት፣ፍርሀት አለኝ የሚል ነው። ይኸው የፍርሀት ስሜት ‹‹ያብሰከሰከኛል...›› በሚለው ሀረግ ቀርቧል። ፍችውም መነጫነጭ፣ አለመረጋጋት፣ ወዘተ... ነው። የዚህ ስሜት መነሻው በፍቅር መሸነፍ ነው። ሀሳቡ የተነፃፀረውም ከነፍስ-ጡር ሴት ጋር ነው። ነፍሰ ጡር (እርጉዝ) ሴት የምግብ ፍላጎቷ የተለያየ ስለሆነ የሚቀርብላት ሁሉ ለመመገብ ትቸገራለች፣ ትብሰከሰካለች ማለት ሲሆን ያፈቀረ ሰውም እንዲሁ ነው ማለት ነው።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ቃል ግጥሞች አካላዊ ቁንጅናን እና ፍቅርን የሚያመለክቱ እንደሆነ ተመልክተናል። ከዚህ በታች ያሉት ግን በሀሳብ ከነዚህ የተለዩ ናቸው። ልዩ የሚያደርጋቸው ከእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ጋር ተያይዘው የተገጠሙ መሆናቸው ነው። በቃልግጥሞቹ ውስጥ ያሉት ቃላትና ሀረጋት ከእስልምና ሀይማኖት ስያሜዎች ጋር አንድ ናቸው።

መንቶ 186 እስላም ስመ ብዙ ሀዋና ከድጃ
ሀዋ ሀዋ አረገኝ የነካኝን እንጃ
መንቶ 187 እስላም ስመ ብዙ ፋጢማ ከድጃ
ሀዋ ሀዋ አሰኘኝ የነካኝን እንጃ
መንቶ 188 ወላሂ ቢላሂ ከንፈርሽን ልቅመሰው
ኸቀፎ ሳይገባ ማር ይሆናል ወይ ሰው
መንቶ 189 እንደ አማራ በስማም እንደ እስላም ወላሂ
ከንፈሯ የሚለው የማር ልህላሂ

አርኬ 190 አባቷ ቃልቻ ደም ያስታርቃሉ
እናቷ ዱበርቲ መረባ ይላሉ
ልጃቸው ሰው ገላ እንዴት ዝም ይላሉ።

መንቶ 186 እና 187 ተመሳሳይ ሀሳብ ስላላቸው ‹‹መኩሼ መንቶዎች›› ናቸው። በሁለቱም መንቶዎች ለፍቅር የምትመረጠው ‹‹ሀዋ›› የምትባለው ሴት ናት። በመጀመሪያው መንቶ ‹‹ከድጃ›› ከምትባለው ጋር ተወዳድራ ነው የምታሸንፈው። የምታሸንፍበት ሁኔታ ግን የተሸናፊውን መንፈስ በሚረብሽ መንገድ ነው። ‹‹ሀዋ ሀዋ አረገኝ›› የሚለው ሀረግ በሁለት መንገድ ሊፈታ ይችላል። አንደኛው ሀዋን መርጫለሁ፤ ከሷ ሌላ አልፈልግም፣ የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ‹‹ዘው ዘው አረገኝ፣ አቅበጠበጠኝ፣» የሚል ነው። በሁለተኛው መንቶ ከሁሉም እስላም ሴቶች ‹‹ሀዋ›› የምትባለውን መርጫለሁ፣ ፋጢማንም፣ ከድጃንም አልፈልግም እንደ ማለት ነው።

እንዲሁም ተከታዮቹም መንቶዎች (መንቶ 188 እና 189) የእስላም ቆንጆዎችን ሁኔታ በተጋነነ መንገድ ያቀረቡ ናቸው። መንቶዎቹ ስለቁንጅናዋ ማረጋገጫ እንደ እምነቱ ተከታዮ በመሀላ (ምሎ በመናገር) የቀረበ ነው። የመጀመሪያው መሀላ ሙሉ በሙሉ በእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች አማካኝነት የሚነገር ነው። ‹‹ወላሂ ቢላሂ›› ማለት በአገባቡ ‹‹በፍፁም እውነቱን ነው›› እንደማለት ነው። ሁለተኛው መሀላ ከክርስትና እና ከእስልምና ተከታይ አንባር የቀረበ ነው። ሁለቱም መሀላዎች የሚያረጋግጡት የሴትዮዋን ውበት ነው። ውበቷ ተለይቶ የተገለፀውም ከናፍሯ ላይ ነው። ይኸውም ከንፈሯ እንደማር ይጣፍጣል የሚል ሀሳብ የተላለፈባቸው ናቸው። ንጽጽሩም ከማር ወለላ ጋር ሙሉ በሙሉ በሚባል አገላለፅ የቀረበ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ‹‹የማር ልህላሂ›› ማለት የተጣራ ወለላ ማር ማለት ነው።

አርኬ 190 ላይ የቀረበው ቃል ግጥም የስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ ሰዎች በሚያከናውኑት የባህላዊ የእርቅ ስርአት አማካኝነት ነው። ባህላዊ የእርቅ ስርአቱ ለክርስትና ሀይማኖት ተከታዮችም የሚሆን ሲሆን፣ አገልግሎቱ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ እስከ ሞት የሚያደረሱ ግጭቶችን በመፍታት ሰላም ማውረድ ነው። በዚህ መሰረት ወንዶች (ቃልቻዎች) እርቁን በበላይነት እየመሩ ሲያሸማግሉ፣ እናቶች (ዱበርቲዎች) ደግሞ በፀሎትና በልመና (መረባ በማለት) የሚታረቁ ሰዎችን ይለምናሉ። ገጣሚው ይህንን ባህላዊ የእርቅ ስርአት ነው ለፍቅር መማለጃ እንዲሆን ያደረገው። ‹‹ልጃቸው ሰው ገድላ...›› የሚለው ሀረግ፣ የልጃቸው አፍቃሪ በፍቅር ተሸንፎ እየተንገላታ ስለሆነ፣ እሷም እንድትወደው፣ እንድታፈቅረው ማድረግ

ይኖርባቸዋል እንደማለት ነው። በአጠቃላይ ቃልግጥሞቹ ሶስት ሁኔታዎችን በቅደም ተከተል ያሳያሉ ማለት ይቻላል። አንደኛው፣ የፍቅር አመራረጥ ሁኔታ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ በፍቅር ላይ ሆኖ መደሰትን፣ ያሳያል። የእነዚህ ድምር ውጤት የሆነው ሶስተኛው ሁኔታ በፍቅር ተሸንፎ መማረክን፣ መንገላታትን፣ የሚያመለክተው ነው።

6.2.5 ብሶትን፣ ቁጭትን፣ ጥላቻንና ማንኳሰስን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

በዚህ ምድብ የተካተቱት ቃልግጥሞች ምሬት፣ ብሶት፣ ተስፋ ማጣት፣ ትካዜ፣ ሀዘን፣ ቁጭት፣ ጥላቻ፣ ወዘተ. የሚንፀባርቅባቸው ናቸው:: የክዋኔ ሁኔታቸውም ቀረርቶ፣ ዘፈን ወይም እንጉርጉሮ ሊሆን ይችላል:: አንዳንዶቹ በታዳሚ ፊት ሊነገሩ የሚችሉ፣ አንዳንዶቹ የብቻ እንጉርጉሮ ወይም ስሜት መግለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው:: የቀረርቶው ስሜት በአንድ ሌላ አካል ላይ ወይም ሰው ላይ የደረሰን በደል በመቃወም የውስጥ ስሜትን ማንፀባረቅ አላማ ያደረገ ነው:: የዘፈኑ ወይም የእንጉርጉሮውም እንዲሁ የውስጥ ስሜትን ማለትም መከፋትን፣ መገፋትን፣ ሀዘንና ቁጭትን የሚያሳይ ነው:: ምድቡ አጠቃላይ የሆኑ የብሶትና የቁጭት ስሜትን የሚያንፀባርቁ ይዘቶች ያሏቸው ቃልግጥሞች በአንድ በኩል፣ የጥላቻና የማንኳሰስ ስሜትን የሚገልፁ በሌላ በኩል ያሉበት ሲሆን፣ በአጠቃላይ 63 ያህል መንቶዎችና አርኬዎች አሉት:: የጥላቻና የማንኳሰስ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ሁኔታ በወንዶች የተፈጠሩ ወይም የተዘፈኑ ይመስላሉ።የግጥሞቹ ሃሳቦች፣ ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸውን የጥላቻ ስሜት የሚያንፀባርቁ ናቸው:: ይህ ምድብ ምናልባት የጾታ ጉዳዮችን /gendr issues/ ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች ጠቃሚ ይሆናል::

ብሶትና ቁጭት፣ ጥላቻና ማንኳሰስ፣ የመሳሰሉት ረቂቅ ነገሮች የሰውን ልጅ የውስጥ ስሜት ለመረዳት የሚያግዙ መገለጫዎች ናቸው። የሰው ልጅ በተለያየ ደረጃ ልዩ ልዩ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ። በአስተዳደር፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በቤተሰብ፣ በግለሰብ፣ በመሳሰሉት ምክንያቶች በሚፈጠሩ ችግሮች ማህበራዊ ህይወቱ ሊናጋ ይችላል። እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር በሰዎች መካከል አለመተማመን፣ አለመረዳዳት፣ በክፉ አይን መተያየት፣ አንዱ ሌላውን መበደል፣ መቀማማት፣ አለመከባበር፣ ወዘተ. ማህበራዊ ችግሮች ይሰፍናሉ። እንደነዚህ አይነት ማህበረሰባዊ ችግሮች በሚታዩበት ጊዜ፣ የማህበረሰቡ አባላት የሆኑ ግለሰቦች፣ ብሶታቸውን፣ ቁጭታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ ጥላቻቸውን፣ ስጋታቸውን፣ ትካዜያቸውን፣ በአጠቃላይ ውስጣዊ ስሜታቸውን፣ ወደ ውጭ ማስወጣት የሚፈልጉበት አጋጣሚ ይፈልጋሉ፤ የመተንፈሻ መንገድ ያበጃሉ። ይህ ሁኔታ በንድፈ ሀሳብ ቅኝት ውስጥ

እንደ ተመለከትነው ከተግባራዊ ስነ ልቦና ንድፈ ሀሳብ ጋር የሚያያዝ ነው። ይህ ንድፈ ሀሳብ በሰዎች ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን ለመተንፈስ፣ እንደ አንድ መንገድ ወይም መሳሪያ የሚሆነው ስነ ቃል እንደሆነ የሚያስረዳ ነው።ይኸውም የሰው ልጅ በስነ ቃል አማካኝነት ከተጫኑበት ጫናዎች፣ ከገጠሙት ችግሮች፣ ለጊዜውም ቢሆን በመላቀቅ ውስጣዊ መረጋጋትን እንዲያገኝ ያስችለዋል የሚል ነው።

6.2.5.1 የብሶትና የቁጭት ቃልግጥሞች

በዚህ ክፍል የምንተነትናቸው ቃልግጥሞች የማህበረሰቡ አባላት የሆኑ ግለሰቦች በራሳቸው ወይም በማህበረሰባቸው ላይ በደረሱ በደሎችና ችግሮች ሰበብ የተሰማቸውን የውስጥ ስሜት በቃልግጥሞች ውስጥ እንዴት ማንፀባረቅ እንደቻሉ ነው። ውስጣዊ ስሜትን ከሚያንፀባርቁት መካከል መጀመሪያ ብሶትን የሚያመለክቱትን ካየን በኋል ቁጭትን የሚያሳዩትን ቀጥሎ እናያለን።

መንቶ192 ከአንድ አገር ተነስተው ካንድ አገር ሲገቡ
ዘላለም ፈተና እንደ ወይፈን ግቡ
መንቶ 193 ጃሎ በል ጃሎ በል ይለኛል አመሌ
የሚመጣው ዘበን እየታየኝ ባይኔ
መንቶ 194 እንደው ግሳ፣እንደው ግሳ ይለኛል አመሌ
ወንዙን ተሻገረ ልቡ የሞላ አውሬ
አርኬ 195 እንዴት ነሽ ልጅነት እንደምነሽ ለዛ
በሮቹ ጥቋቁር ጅራታቸው ፈንዛ
አርሰን ለበላነ ምናምኔው በዛ
መንቶ 196 አሞኝ ውሎ አሞኝ ሊያድር ነወይ
ደሞም አርሶ መብላት ጤና ላይሆን ነወይ

እነዚህ ቃልግጥሞች ይዘታቸውን ስንመረምር በውስጣቸው ያለው ሀሳብ አስተዳደራዊ ብሶትን የሚያመላክት ነው። አስተዳደራዊ ብሶት ከአስተዳደራዊ ጫና እና በደል የሚመነጭ ነው። ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ በሰላም ሰርተው፣ ሰላማዊ ህይወት እንዳይኖሩ፣ የሚያደናቅፉ አስተዳደራዊ በደሎች ሊኖሩ ይችላሉ።ሰዎች አስተዳደራዊ በደል ሲደርስባቸው ለአመፅ ይነሳሳሉ፣ ይከፋሉ፣ ማለት ይቻላል። መንቶ 192 የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። የመጀመሪያው ስንኝ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስን፣ የመኖሪያ አካባቢ ለውጥ ማድረግን፣

ለተወሰነ ጊዜ በአንድ አካባቢ መገኘትን፣ የሚያሳይ ነው። ሰዎች በሀገራቸው በፈለጉበት ቦታ ተንቀሳቅሰው የመኖር ማህራዊ እና ፖለቲካዊ መብት ያላቸው መሆኑን መነሻ አድርጎ የቀረበ ይመስላል።

ሁለተኛው ስንኝ ግን ይህ መብት በቀላሉ የሚገኝ እንዳልሆነ ጠቋሚ ነው። «ዘላለም ፈተና እንደ ወይፈን ግቡ» የሚለው ስንኝ ችግር እንዳለ አመላካች ነው። «ወይፈን ግቡ» ማለት ቀንቶ (ተገርቶ) እርሻ ማረስ የጀመረ በሬ ነው። ወይፈን በአካልና በእድሜ ገና ያልጠነከረ ስለሆነ የሙሉ ቀን እርሻ ብቻውን ሲያርስ መዋል አይችልም። እስኪጠነክር ድረስ አጋዥ በሬ ያስፈልገዋል ወይም ግማሽ ቀን ብቻ ታርሶ ይፈታል። በዚህ ሁኔታ ላይ ያለ በሬ (ወይፈን) ገበያ ገብቶ በሚሸጥበት ጊዜ ገዥው የፈተና ጊዜ እንዲሰጠው ይጠይቃል እንጂ ዝምብሎ አይገዛም። አባት በሬ እስከሚሆን ድረስ ከመፈተን አያመልጥም ማለት ነው። በአጠቃላይ ከአስተዳደራዊ ችግር በተጨማሪ፣ መንቶው በሰዎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ፣ ለአካባቢው እንግዳ የሆነ ሰው ሲገኝ፣ ማንነቱ እስኪታወቅ ድረስ በጥርጣሬ አይን የሚታይ መሆኑን አብሮ የሚያሳይ ነው።

መንቶ 193 እና 194 ትንቢታዊ በሆነ መንገድ አስተዳደራዊ ብሶትን ለመግለጽ የሚሞክሩ ናቸው። ከግጥሞቹ እንደምንረዳው የሚመጣው ዘመን አስፈሪና አስቸጋሪ ነገር ይዞ ሊመጣ እንደሚችል አስቀድሞ የታየ ይመስላል። «ጃሎበል» እና «እንደው ግሳ» የሚሉት አባባሎች ከቀረርቶ ጋር የሚያያዝ ክዋኔ ያላቸው ናቸው። ትርጉማቸው "አቅራራ አቅራራ ይለኛል" የሚል ሲሆን፣ ይህም በውስጡ የሚያስጨንቅ፣ የሚያስፈራና የሚቀሰቅስ ስሜት ይሰማኛል፤ ይኸ ነገር፣ መጪው ጊዜ አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ነው። ይኸ ክፉ አስቸጋሪ ዘመን ደግሞ ጦርነት ወይም ጥቃት ያለው አስተዳደራዊ በደል ሊሆን ይችላል። ይህንን ክፉ ዘመን ቁጭ ብሎ ከመጠበቅና ከመቀበል ይልቅ፣ የሚያመጣውን ችግር ለመጋፈጥ መዘጋጀት ያስፈልጋል የሚል ቅስቀሳ የተንጸባረቀበት ነው።

አርኬ 195 እና መንቶ 196 ላይ የተነሳው አስተዳደራዊ ብሶት ደግሞ ከግብርና ህይወት ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚመለከት ነው። «አርሰን ለበላነ ምናምኔው በዛ» በሚለው ስንኝ ውስጥ «ምናምኔው» በሚል በንቀት ስሜት የተጠቀሰው ጉዳይ በአስተዳደራዊ መዋቅሩ የሚገኙትን ሰዎች ማለት ነው። ይኸውም፣ ቀደም ሲል ምስለኔ፣ ቀጥሎ ሊቀመንበርና ፍርድ ሸንጎ፣ አሁን ደግሞ አመራር ካቢኔ፣ በሚባሉ አስተዳደራዊ ስያሜዎች ውስጥ የሚሰሩ ግለሰቦች የሚያደርሱበትን በደል ለመግለጽ የተጠቀመበት ይመስላል። በደል አድራሾቹ የትኞቹ

ግለሰቦች እንደሆኑ፣ ማለትም በስም ለይቶ ስለማይጠቅስ፣ አቀራረቡ ብሶተኛውን መልሶ ከመጠቃት ያድነዋል። «አርሰን ለበላነ»፣ «ደሞም አርሶ መብላት»፣ የሚሉት ሀረጎች ከግብርና ስራ በስተቀር ምን ጥፋት አለብን፣ ጥረን ግረን ከመኖር ሌላ ያጠፋነው ጥፋት ስለሌለ እባካችሁ ተውን» የሚል መልክት ያለው ቢሆንም በቃልግጥሞቹ ውስጥ እንደተንፀባረቀው በግብርና ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል ሰላማዊ ህይወት መምራት እንዳልቻለ ነው። «አሞኝ ውሎ አሞኝ ሊያድር ነወይ» የሚለው ስንኝ፣ ታሞ መዋልና ታሞ ማደርን ሳይሆን እድሜ ልክ መገፋትን፣ መከፋትን ነው የሚያመለክተው።

«እንዴት ነሽ ልጅነት፣ እንደምነሽ ለዛ» የሚለው ስንኝ፣ «በልጅነታችን ወይም በወጣትነታችን እድሜ ላይ ሆነን አንገታችንን ደፍተን ሥራችንን ብንሰራ ምቀኛ በዛብን፤ ጠላት አስቸገረን» የሚል ሲሆን በውስጡ፣ «እንቢ ካላችሁ፣ አላስኖረን ካላችሁ ደግሞ፣ በተገኘው አማራጭ እንታገላችኋለን፤» የሚል ብሶትና ማስፈራራት የተንፀባረቀበት ነው።

በማህበራዊ ህይወት ውስጥ በሰዎች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶች እንደሚኖሩ ይታመናል። በድንበር መጋጨት፣ በአነጋገር ስህተት ወይም በአለማወቅ፣ ነገር ወዲያና ወዲህ በማመላለስ (ምላሰኛነት)፣ ምክንያቶች ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሰዎች ሲገቡ ወይም ሲበደሉ የሚሰማቸው ሀይለኛ ስሜት ይኖራል። እንዲህ አይነቶቹ ስሜቶች ከሚንፀባረቅባቸው ቃልግጥሞች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

አርኬ 197 ሳታስበው ነገር ሲመጣብህ
ደርግመው ደርግመው አይልም ወይ ልብህ
ዳሩ ግና ቢሆን እንደው ጠንቀቅ
ግዛግዙ ገሎ አገሩን ኸመልቀቅ
መንቶ 198 እሱ መቶ ሰው ይዞ ለመሞት
ንግግሩ ሁላ ይላል አሞት አሞት
መንቶ 199 ቢይዙት የማይነጥቅ ጠላት ተበጅቶ
አይተን አይተን ተውነው ጓዛችን በርክቶ
አርኬ 200 ኸረተው አንተ ሰው ስሮጥ አታባረኝ
አንተም አበዛኸው እኔንም መረረኝ
መረረኝ እንደሬት በላኝ እንደ አሁላሊት
ቀን የተናገርኸኝ እየመጣ ሌሊት

መንቶ 201 ተወኝ ምላሰኛ ተወኝ ነገረኛ
ኻገዳ ጎጆየ አርፌ ልተኛ

አርኬ 197 ላይ የተገለፀው ሀሳብ፣ በድንገት ያልታሰበ ነገር ሲፈጠር ትዕግስትን እንደሚፈታተን የሚያስረዳ ማህበራዊ ብሶት ነው። ሀሳቡ «ያልደረስክበት ሰው፣ በክፉ ያየኛል ብለህ የማትገምተው ሰው፣ በጉልበት ሊመጣጠንህ የማይችል ሰው፣ ድንገት በነገር ቢወጋህ፣ በለው! በለው!» የሚል ስሜት ይቀሰቅሳል የሚል ነው። አቀራረቡ በጥያቄ መልክ ቢሆንም፣ «ደርግመው !ደርግመው... ወዘተ» የሚለው ሀረግ «በጥፊ ምታው ወይም በጥይት በለው (ምታው)» ማለት ነው። ብሶቱ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጠላት ምክንያት የተፈጠረ ችግር ስለሆን፣ ስሜታዊነት የተንፀባረቀበት ነው ማለት ይቻላል። ይህን ያልታሰበ ችግር በትዕግስት ማሳለፍ እንደሚገባ ሶስተኛውና አራተኛው ስንኞች ያስጠነቅቃሉ። «ግዛ ግዙ» ማለት በአገባቡ የማይረባ፣ ደካማ፣ ውዳቂ፣ ቢታገሉት የማያስሞግስ፣ ቢያጠቃ ደግሞ፣ እንደትናቅ የሚያደርግህ ባላጋራ ማለት ነው። እንዲህ አይነቱን ደካማ ጠላት ገሎ፣ አገር ከመልቀቅና ወንጀለኛ ከመሆን፣ በጥንቃቄና በትዕግስት ማሳለፍ የተሻለ እንደሆነ የሚመክር ነው።

እንዲሁም፣ ከዚህ አይነቱ ተመሳሳይ ትንኮሳና ብሶት ጋር የተዛመደ ሀሳብ መንቶ 198 ላይ እናገኛለን። «እሱ ሙቶ ሰው ይዞ ለመሞት» የሚለው ስንኝ ፍቺው «በሱ ጥፋት ሌላውን ሰው ተጠያቂ የሚያደርግ» ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ «ነገረኛ» የሚባሉ ሰዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። እንደነዚህ አይነት ሰዎች ሳይደርሱባቸው፣ የሚደርሱ ሲሸሿቸው፣ የሚያባርሩ ናቸው። እንደነዚህ አይነት ሰዎች በሰው ላይ የሚሰነዘሩት ማንኛውም አስተያየት ክፉኛ የሰውን ስሜት የሚጎዱ በመሆናቸው መራራ ናቸው። መራራ ንግግር ክፉ ጥላቻ ስለሚያስከትል ውጤቱ መጥፎ ይሆናል። የመንቶው ሀሳብ «ተናግሮ ከአናጋሪ አድነኝ» ከሚለው ልማዳዊ ፀሎት ጋር የሚዛመድ ነው።

መንቶ 199 ላይ የተነሳው፣ ህይወት እያናጋ የሚገኘው ጠላት አቅም የሌለው፣ ግን የሰዎችን ስሜት የሚያስጨንቅ ባላጋራ ነው። እንደሱ ክፉነት ቢሆን ኖሮ፣ «አጥፍቶ የመጥፋት» ግፊት የሚያስከትል ነው። የግጥሙ መልዕክት «ከሱ ይልቅ እኛ በተሻለ ህይወትና ደረጃ ላይ የምንገኝ ስለሆነ በትዕግስት አሳልፈነዋል» የሚል ነው። ይህንን ሀሳብ የሚያረጋግጠው ደግሞ «አይተን አይተን ተውነው ጓዛችን በርክቶ» የሚለው ስንኝ ነው። መታገስን፣ አመዛዝኖ መወሰንን፣ የሚያስገነዝብ ሀሳብ የተንጸባረቀበት ነው ማለት ይቻላል።

አርኬ 200 የተነሳው ሀሳብ በከፍተኛ ምሬትና ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ነው። «ኧረ!» የሚለው ቃል «እባክህ ተወኝ» የሚል ተደጋጋሚ ልመና የተገለፀበት ነው። ይህ ልመና ትርጉሙ «ፈርቸህ ሳይሆን የምሸሸው ይዘኸኝ እንዳትሞት፣ ወንጀለኛ እንዳታደርገኝ ነው የምርቅህ» ማለት ነው። ነገር ግን ተለማኙ ግለሰብ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ለማኙ ግለሰብ ትዕግስቱን ያጣ ይመስላል። የትዕግስቱን ማለቅ የገለፀበት ስሜት ከእሬትና ከአሁላሊት (አንዳንድ ቦታ ሳማ ይሉታል) እፅዋቶች ጋር በማዛመድ ነው። እንደሚታወቀው እሬት ሲቀምሱት መራራ ነው። እንዲሁም የአሁላሊት ቅጠል ሲነኩት የሚለበልብና የሚያቃጥል ቅጠል ነው። የሰውየው ንግግር ልክ እንደ ሬቱና እንደ አሁላሊቱ መራራና የሚያንገበግብ ስለሆነ ተጠቂውን (ተሰዳቢውን) እንቅልፍ ነስቶታል። ምናልባት ልመናውንና ትዕግስቱን ካልተረዳለት ወደ ሀይል እርምጃ የሚሄድ መሆኑን የሚገልፅ ነው።

የመጨረሻው ማህበራዊ ብሶት የተንፀባረቀው በመንቶ 201 ላይ ነው። ይህ ማህበራዊ ብሶት መነሻው ነገር ወዲያና ወዲህ (ምላሰኛነት) ማመላለስ ነው። ምላሰኛ ሰው አንድም አካባቢው ሰዎች ጋር ያጣላል አንድም ከመንግስት ባለስልጣን ጋር ያጋጫል ማለት ነው። ከመንግስት ጋር መጋጨትም ሆነ ከአካባቢው ሰዎች ጋር አለመስማማት ማህበራዊ ችግሮች ስለሆኑ በድህነት የሚኖረው ግለሰብ ችግሮቹን መቋቋም የሚችል አይመስልም። «ካገዳ ጎጆየ አርፌ ልተኛ» የሚለው ስንኝ ይህንን ያመለክታል። ተማፅኖው ከድህነት በመነጨ ስሜት ቢሆንም አላስቀምጠኝ ካለህ የምችለውን ለማድረግ ወደኋላ የማልል መሆኑን እንድታውቅ የሚል ማስጠንቀቂያ የተላለፈበት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች ደግሞ ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ የብሶት መገለጫዎችን እንመለከታለን። ለብሶት መነሻ የሆነው ጉዳይ ከአርሶ አደሩ ህይወት ጋር የተቆራኘ ነው። አርሶ አደሩ ባለው አቅም ቤተሰቡን ይመግባል ያለብሳል ከዚህ ሲያልፍ ግን ብሶትና መማረርን ያስከትላል። ከአቅም በላይ በሆነ የቤተሰብ አባላት (በተለይም በሚስት ሰበብ) ፍላጎት የተማረረ ግለሰብ የፈጠራቸው ይመስላሉ። ቃልግጥሞቹን እንመልከት!

መንቶ 202 ይኸን ፍስስ ማለት ማነው ያመጣብኝ
ብበደር ብበደር አራጣው በዛብኝ
መንቶ 203 የበሬውን መግጮ ተባለን ለብሰሽ
ውረጅ ወደ ቦዳው ትጠመጃለሽ

አርኬ 204 ወታደር በክላሽ እያስፈራራሽ
ሾፌር ከጋቢናው እየጠቀሰሽ
ኮንትሮ በጭሊ እያባበለሽ
ከኔ ከድኻው ቤት
በኬሻ ምንትራስ
በጥሬ ጨው በልተሽ መይ ትኖሪያለሽ

በሁለቱ መንቶዎች ውስጥ በአንድ ወቅት የሴቶች «ዘመናዊ» አልባሳት የነበሩ የልብስ አይነቶች ተጠቅሰዋል። እነሱም «ፍሰስ በገላየ» እና «ተባለ እንዴ» ናቸው። እነዚህ አልባሳት ዘመነ አመጣሽ (ፋሽን) ስለነበሩ ዋጋቸው ከፍተኛ ነበር። ምናልባት ባህላዊ ቀሚስ (ጥብቆ) ከሚሰራበት እጥፍ ዋጋ የነበራቸው ነበሩ። ውድ እንደ ነበሩ የሚያመለክቱት ነገሮች የአራጣ ብድር እና የበሬ መግዣ የሚሉት አባባሎች ናቸው። ብድሩ አንድ ጊዜ ሳይሆን ተደጋጋሚ ነው። በመጀመሪያ ስንኝ የመጨረሻ ሀረግ «ማነው ያመጣብኝ» የሚለው የብሶቱን ደረጃ ይገልፃል። የልብሱ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ለከፍተኛ ወጪ የዳረገው መሆን እንረዳን። የብሶቱና የምሬቱ ደረጃ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን በግልጽ የሚነግረን እንደ በሬ ሊጠምዳት መፈለጉን ስንመለከት ነው።

አርኬ 204 ውስጥ ለብሶቱና ለትዳሩ መፍረስ ተጠያቂ የሚሆኑ ሶስት የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ። እነሱም ወታደሮች፣ ሾፌሮችና የኮንትሮ ባንድ ነጋዴዎች ናቸው። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ከ1970ዎቹ ጀምሮ በሰሜን ወሎ ምስራቃዊ አካባቢዎች በብዛት ይንቀሳቀሱ ነበር። ወታደሮቹ በእርስ በርስ ጦርነት (በደርግና ኢህአዴግ) ምክንያት በአካባቢው ሰፍረው የሚጠብቁ ናቸው። ሾፌሮቹ በየከተሞቹ ከሚኖሩት በተጨማሪ ወደ ሰሜንና ወደ መሀል አገር የሚመላለሱትን ጭምር ነው።

የኮንትሮ ባንድ ነጋዴዎች ደግሞ አፋር ውስጥ «ጉጉብዱ» ከምትባል የገበያ ቦታ እየሄዱ ከጅቡቲ የሚመጣ ዕቃ ማለትም ልባሽ ጨርቅና ልዩ ልዩ የጣቃ ጨርቅ፣ ቴፕ፣ ሰዓት፣ በግመልና በአህያ እንዲሁም በበቅሎ እያመጡ በህገ ወጥ መንገድ የሚሰሩትን ነው። እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ባላቸው ነገር ተጠቅመው ሴቶችን ያቀርቡ ስለነበር ነው የብሶቱ መነሻ የተፈጠረው። ወታደሮቹ መሳሪያቸውን እንደማስፈራሪያ ይጠቀማሉ። ሾፌሮቹ መኪናቸውን እንደ ሀብት ደረጃ በመጠቀም ሴቶችን ለማስኮብለል ይፈልጋሉ። የኮንትሮ ባንድ ነጋዴዎች ደግሞ በገንዘባቸው ሴቶችን እያባበሉ የሚፈልጉትን ነገር ያደርጋሉ። «ጭሊ» ማለት

የመቶ ብር ኖት ሲሆን ከአቢዮቱ በኋላ በተደረገው የገንዘብ ለውጥ ጊዜ የነበረው ነው። በመሆኑም እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ከአርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ አንፃር ሲታይ በተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ስለነበር በስነ ልቦናው የበታችነት ስሜት እንዲፈጠረበት አድርገዋል። በድህነቱ ምክንያት በተሸናፊነት ስሜት ውስጥ እንደሚገኝ «የኬሻ ምንትራስና የጨው ፍትፍት» የሚሉት ያረጋግጣሉ። ለብሶቱ ሰበብ ከተጠቀሱት የህብረተሰብ ክፍሎች ይልቅ ድህነቱ እንደሆነ እንረዳለን።

ሰዎች በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ በተለያየ ምክንያት ለተለያዩ የኑሮ ውጣ ውረዶች ሊጋለጡ ይችላሉ። በተለይ ሴቶች በእንዲህ አይነቱ ችግር ተጠቂዎች ናቸው ማለት ይቻላል። ከዚህ ቀጥሎ የሴቶች የብሶት ስሜት በእንጉርጉሮ የተንፀባረቀባቸውን ቃልግጥሞች እንመለከታለን። እንጉርጉሮ የተባለው ግጥሞቹ ለብቻ የሚዜሙ በመሆናቸው ነው። ቀደም ሲል በነበረው ሁኔታ ሴቶች በድንጋይ ወፍጮ ብቻቸውን እህል ሲፈጩ የሚያዜሟቸው የብሶት መግለጫዎች ናቸው።

አርኬ 205 ይኸ ኑሮ ነው ወይ የኑሮ እኩሌታ
እንስራ ወገብ ላይ ዳንኪራ እየመታ
ቅቤሽ እንዳይነካኝ እያሉ መኝታ
መንቶ 206 መጁ ውረድ ውረድ ቋቱ ሙላ ሙላ
በዋዛ አይበላም የሰው ቤት እንጀራ
መንቶ 207 ዋርካ ምድር ነካ ንገሩት ለዋንዛ
ፈጭቼ ለበላሁ ምቀኛየ በዛ

በሶስቱም ቃል ግጥሞች የተንፀባረቀው የብሶት ስሜት መነሻው አድካሚ የጉልበት ሥራ ነው። የቧንቧ ውሃ ባልነበረበት ጊዜ ሴቶች በእንስራ ውሃ የሚቀዱት ወንዝ እየሄዱ ነበር። ዘመናዊ የእህል ወፍጮ ባልነበረበት ጊዜ ለምግብ የሚሆን እህል የሚፈጨው በድንጋይ ወፍጮ ነው። እነዚህ ተግባራት እጅግ አድካሚ ስለሆኑ ትዕግስትን ይፈታተናሉ፤ በኑሮ ላይ ደስተኛ አለመሆንን ያስከትላሉ። «የኑሮ እኩሌታ» ይህንን ያመለክታል። ለዚህ ምክንያቱ በየቀኑ በእንስራ ውሃ መቅዳት ነው። አርኬ 205 የመጨረሻ ስንኝ ከጉልበት ስራው አድካሚነት በተጨማሪ «በፍቅር ወይም በትዳር» አጋር አለመደሰትን ይጠቁማሉ። «ቅቤሽ እንዳይነካኝ ...» የሚለው ሀረግ አብረን ስንተኛ «አትጠጊኝ! ፈቅ ብለሽ ለብቻሽ ተኚ!» የሚል የጥላቻ ስሜት የተንፀባረቀበት ነው። መንቶ 206 እና 207 አድካሚ የጉልበት ስራ የፈጠራቸው

የብሶት መገለጫዎች ናቸው። በሰው ቤት በሰራተኝነት መኖር እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን «በዋዛ አይበላም የሰው ቤት እንጆራ» የሚለው ስንኝ ይገልፃል። ከዚህ በተጨማሪ የሰዎች በክፉ አይን (በምቀኝነት) ማየት የሴቷን ብሶት ያባባሰው ይመስላል። «ፈጭቼ ለበላሁ ምቀኛየ በዛ» የሚለው ስንኝ ብሶቷ ወደ ምሬት ደረጃ መድረሱን ያመለክታል።

ቁጭት በማህበራዊ ህይወታችንና በዕርስ በርስ ግንኙነቶቻችን ውስጥ በልዩ ልዩ ምክንያት በውስጣችን የሚፈጠር ሀይለኛ ስሜት ነው። በሚከተሉት ቃል ግጥሞች ውስጥ ማህበራዊ ግለሰባዊ እና ቤተሰባዊ በሆኑ ምክንያቶች የተፈጠሩ የቁጭት ስሜቶችን እንመለከታለን። ማህበራዊ ቁጭት በሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት መዛባት ምክንያት የሚፈጠር ሀይለኛ ስሜት ነው። ግለሰባዊ ቁጭት ማለት ሰዎች በራሳቸው ወይም በሌላ ምክንነት የሚፈልጉትን ማሳካት ባለመቻል የሚፈጠር የውስጥ ስሜት ነው። ቤተሰባዊ ቁጭት በአንድ ቤተሰብ መካከል አንዱ ባለመኖሩ ምክንያት የሚፈጠር ሀይለኛ ብሶትና የቁጭት ስሜት ነው። ቃልግጥሞቹ የሚከተሉት ናቸው።

መንቶ 208 ቆይ ገና፣ቆይ ገና
መቼ ለይቶልን ሰባራና ደህና
መንቶ 209 እደግ እደግ ብለን ያሳደግነው ልጅ
እምብዛ ረዘመ እንከርክመው እንጅ
መንቶ 210 ሳለ ሌቱ ሳለ ጨለማው
እንዴት ያጠቃዋል ሰውየውን ሰው
መንቶ 211 በሉት ሀብታችንን ጨው ጨው እያላቸው
ጥይት ኮሶ ሆኖ እስኪያስመልሳቸው

መንቶዎቹ የሚያንፀባርቁት በዛቻና በማስፈራራት ላይ የተመሰረቱ ሀሳቦችን ነው። የማስፈራራቱም ሆነ የዛቻው ስሜት መነሻው ከመጠቃት ከመበለጥ ከመቀማት ወዘተ በመነጨ ቂም ያዘለ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ይመስላል። የመጀመሪያው መንቶ «ዛሬ ሁላችንም አንድ ላይ ሆነን እንደ አንድ ብንታይም ወደፊት በተግባር ስንፈተን ማንነታችን ተለይቶ ይታወቃል» የሚል መልዕክት ያለው ነው። «ቆይ ገና» የሚለው ሀረግ ወደፊት የሚመጣን አጋጣሚና ሁኔታ የሚያመለክት ነው።ይህ አጋጣሚ «ወንድ ልጅ» የሚፈተንበት የችግር ጊዜ ሊሆን ይችላል። አስተሳሰቡ የውጊያ ጥቃትን ከመከላከል፣ በርትቶ ከመስራት (ከመከሰብ)፣ በአጠቃላይ ፈታኝ የሚባሉ ችግሮችን ተቋቁሞ ከማለፍ ጋር የተያያዘ ነው።

ችግሮቹን መቋቋም የሚችል እንደ ጀግና ይቆጠራል፤ መቋቋም ያልቻለ ደግሞ ይተቻል ማለት ነው። ይህንን የሚያሳየን ስንኝ «መቼ ለይቶልን ሰባራና ደህና» የሚለው ነው። «ሰባራ» ችግሩን መቋቋም የማይችለውን የሚወክል ሲሆን «ደህና» ደግሞ መቋቋም የቻለውን ያመለክታል። «ዛሬ ላይ ሁላችንም እኩል መስለን ብንታይም ወደፊት ተፈትነን ስንለይ ማንነታችን ይታወቃል» የሚል ቁጭት የተንፀባረቀበት ነው።

መንቶ 209 የሚያመለክተው፣ተጠቃሹ ልዩ ድጋፍ እየተሰጠው ትልቅ ደረጃ ላይ ቢደርስም፣ ዛሬ ተመልሶ በኛ ላይ ችግር እየፈጠረ ስለሆነ መፍትሄ ይፈለግለት የሚል ነው። ችግሩ ለትልቅ ደረጃ መድረሱ ሳይሆን ለሰዎች ያለው አመለካከት የተሳሳተ መሆኑ ነው። "እምብዛም ረዘመ" የሚለው ሀረግ ይህንን ያሳያል። ቁጭቱ "ቁጭ ብለን የሰቀልነውን ቁመን ማውረድ አቃተን" ከሚለው አባባል ጋር የሚመሳሰል ነው። መንቶ 210 ላይ የሚታየው የቁጭት ስሜት ከሁለቱ የተለየ ነው ማለት ይቻላል። የሰው ልጅ መጠቃትን አይፈልግም፤ ጥቃት ከደረሰበት ደግሞ የመበቀል ሀይለኛ ስሜት በውስጡ ሊፈጠር ይችላል። መንቶው አንድ ሰው ለምን በሌላ ሰው ላይ ጥቃት ይደርስበታል? በሚል የቁጭት መንፈስ የሚጠይቅ ሆኖ ለጥያቄው መልስ የሚሆነው ሀሳብ በመነሻው ስንኝ ተገልጻል። ይኸውም በቀን የሚያጠቃህን ጠላት ሌት በጨለማ ማጥቃት እየተቻለህ ለምን ተጠቅተህ ዝም ትላለህ? የሚል ቁጭት ያለበት ነው።

መንቶ 211 ላይ የተንፀባረቀው ሀሳብ በአስተዳራዊ ችግር ምክንያት የተፈጠረ ቁጭት ነው ማለት ይቻላል። የቁጭቱ ሰበብ በሀይል ሀብት መዝረፍ ፣መቀማት ወይም ጉቦ ይመስላል። የመጀመሪያው ስንኝ የሚያመለክተው «የኛ የሆነውን ሀብት (ገንዘብ) ሌሎች ወሰዱብን» የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ስንኝ ደግሞ «አንድ ቀን ሀብታችንን መልሰን የምናገኝበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም» የሚል የዛቻ ቁጭት የተንፀባረቀበት ነው። የማስመለሱ ስራ በሀይል እርምጃ ላይ የተመሰረተ ነው። "ኮሶ" የሀይል እርምጃውን አስከፊነት ወይም መራራነት ያመለክታል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ ቤተሰባዊ ቁጭት መነሻው ከቤተሰብ አባል መካከል ያንዱ መለየት ወይም አለመኖር ነው። እንዲህ አይነቱ ቁጭትና ብሶት መገለጫው በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር የተያይዘ ነው። በችግር ጊዜ ረዳት ማጣት፣ በጥቃት ጊዜ ተከላካይ አለማግኘት፣ በአጠቃላይ ብቸኛ በመሆን ሰበብ ለችግር ወይም ለጥቃት ስንጋለጥ የሚፈጠር ስሜት ነው። የሚከተሉትን ቃልግጥሞች እንመልከት!

መንቶ 212 ሲይዙት ቀላል ነው ወንድምና ብር
ሲታጣ ነው እንጂ የሚቆረቁር
መንቶ 213 ወንድም ያሻል ወንድም ያሻል
አንዱ ሲበረብር አንዱ ይመነሻል
መንቶ 214 ወይ ነቃ ያለ አባት ወይ አራት ወንድም
ሁነኛ ኻላየ ሰው በሀቅ አይፈርድም
መንቶ 215 የክላሽን ጥይት ይያዛል በካርታ
ደህና ወንድም ያለው ዋስ ሆኖ እሚያስፈታ

እነዚህ ቃል ግጥሞች ከቤተሰብ አባላት መካከል ስለወንድም እና ስለአባት አስፈላጊነት በቁጭት የሚናገሩ ናቸው። በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ታላቅም ሆነ ታናሽ ወንድም ለቤተሰቡ መመኪያ መኩሪያ ጋሻና መከታ ነው ተብሎ ይታመናል። በመጀመሪያው መንቶ የወንድም አስፈላጊነት ከገንዘብ ጋር ተነጻፅሮ ቀርቧል። አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ(ብር) ካለው በገንዘቡ የሚፈልገውን ሁሉ የማድረግ አቅም ይኖረዋል። ገንዘብ ካለ ለሱ ሁሉም ነገር ቀላል ይሆናል ማለት ነው። ወንድም ያለው ሰው በወንድሙ ስለሚመካ ለጊዜውም ቢሆን ከማንኛውም ስጋት ነፃ የመሆን ስሜት በውስጡ ይፈጠራል። በስራ ይተጋገዛሉ፤ አብረው ይወጣሉ አብረው ይገባሉ፤ ብቸኝነት አይኖርም ማለት ነው። መንቶ 213 ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው ። የመጀመሪያው ስንኝ የወንድምን አስፈላጊነት ሲገልፅ ሁለተኛው ስንኝ የሚያስፈልግበትን ምክንያት ያስረዳል። ከአርሶ አደር የግብርና ስራ መካከል አንዱ ውቂያ ነው። በውቂያ ጊዜ አውድማው ውስጥ እንስሳቱን የሚያሄድ ሰው ያስፈልጋል። የሚወቃውን እህል እያገላበጠ (እየመነሸ) እንስሳቱ እንዲረግጡት የሚያደርግ ሌላ ሰው ያስፈልጋል። ስለዚህ ስራው መተጋገዝን የሚጠይቅ ነው ማለት ነው። የመንቶው ሀሳብ ይኸው ነው። ከዚህ መንቶ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የባህል ዘፈን ግጥም እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል።

«እባክሽ እናቴ ውለጅልኝ መንታ
ግራ እጀ ሲመክት ቀኝ እጀ ተመታ»

የሚለው መንቶ፣ የወንድምን አስፈላጊነት በእጅጉ አጉልቶ የሚሳይ ነው።

በባህላዊውም ሆነ በዘመናዊ የፍርድ ስርዓት ተበዳዮችም ሆኑ በዳዮች በፍትህ ፊት እኩል ይዳኛሉ ተብሎ ይታሰባል። መንቶ 214 ግን ይህንን የሚያረጋግጥ አይመስልም። «ወይ ነቃ ያለ አባት» የሚለው ሀረግ በማህበራዊ ህይወቱ ተደማጭነትና ተመራጭነት ያለውን ቤተሰብ

አባል (አባት) የሚመለከት ነው። አንድ አባት ከአራት ወንድም ጋር ተነፃፅሮ ቀርቧል። አባት የአራት ወንድም ያህል ይቆጠራል ማለት ነው። በሁለተኛው ስንኝ «ሁነኛ» ማለት፣ የራሴ የኔ ነው የምትለው ወገን ወይም ዘመድ ማለት ነው። የመንቶው ሀሳብ በፍርድ አደባባይ ሳይቀር ዘመድ አስፈላጊ እንደሆነ ነው።ወገን ካለህ ፍትህን እስከማባዛት የሚያደርስ አቅም ይኖርሀል የሚል ነው። በፍርድ ስርዓት በእስራት መቀጣት፣ በገንዘብ መቀጣት፣ በዋስ መፈታት ወዘተ. የሚባሉ ውሳኖች አሉ። ዋስ መሆን ከባድ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን መቀበል ነው። ለእንዲህ አይነቱ ኃላፊነት የቅርብ ሰው ያስፈልጋል። ጠላትን ለመከላከል መሳሪያ (የክላሽ ጥይት) እንደሚጠቅም ሁሉ፣ ደህና ወንድም ወይም ሁነኛ ዘመድም በፍትህ ፊት ቀርቦ ዋስ ሆኖ ያስለቅቃል ማለት ነው። ብሶቱና ቁጭቱ «ሁነኛ ዘመድ ከሌለህ ሁሌም ለችግር ተጋላጭ ትሆናለህ»፤ የሚል ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች የተንፀባረቁት የቁጭት ስሜቶች ከግለሰብ ህይወት ጋር የተያያዙ ናቸው። ቁጭቱ ግለሰቦች በለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ማግኘት የሚፈልጉትን ነገር ማግኘት ሲያቅታቸው፣ ወይም ሞክረው ችግር ሲገጥማቸው በሚታይ ሀይለኛ ስሜት አማካኝነት የተፈጠረ ነው። መንቶዎቹን እንመልከት!

መንቶ 216 አርሶ ማጣትና ተኩሶ መሳት
ያንገበግብ የለ እንደ እግር እሳት
መንቶ 217.ማሽላ በርጉዙ ጤፍ በወለደው
እንዲህ ሆኖ ቀረ የኔና ያንቺው
መንቶ 218 እግዚሀር አዞብኝ የሰው ሽጋ ስሜ
ከቁና ጥሬ ጋር ሲፈጭ ያድራል ስሜ

መንቶ 216 አላማን ካለማሳካት የመነጨ ቁጭት ነው። ገበሬ ማሳውን አርሶና አለስልሶ ካዘጋጀ በኋላ በድርቅ ወይም በዝናብ እጥረት በተባይ ወይም በጎርፍ ምክንያት የሚጠብቀውን ምርት ሳያገኝ ሊቀር ይችላል። በሌላ በኩል አንድ ሰው የሚፈልገውን ጠላት ወይም የሚያድነው እንስሳና አውሬ በግላጭ አግኝቶ አልሞ ቢተኩስም ኢላማውን ሊስት ይችላል። የነዚህ ሁለት ጠላት ወይም ታዳኝ እንስሳና አውሬ ሊያመልጡ ይችላሉ። የነዚህ ሁለት ተግባራት (ማረስና መተኮስ) አለመሳካት የሚፈጠረው የጭንቀት ስሜት ስቃይ፣ ፍም ላይ እንደቆመ ሰው ያቃጥላል የሚል ነው። መንቶ 217 እና 218 ከፍቅር ግንኙነት ጋር የተያያዙ ቁጭቶች ናቸው የተንፀባረቁባቸው መንቶ 217 ላይ የተገለፁት በፍቅር የሚፈልጉት ሰዎችን ከመፈላለግ

ያለፈ ግንኙነት ሳይኖራቸው የቀሩ ናቸው። ይህን የሚያረጋግጠው የመጀመሪያው ስንኝ ነው። ማሸላ አርግዞ ካልወለደ (ዛላው ካልታየና ፍሬ ካላፈራ) ምርት አይሰጥም። የጤፍ ሰብልም ወዲያው እንደወለደ ለማፍራት የሚያስችል ዝናብ ካላገኘ፣ሳር ሆኖ ይቀራል። ሰብሎቹ በጅምር እንደቀሩ ሁሉ፣ የፍቅር ግንኙነቱም ከዚህ ያለፈ አልሆነም፤ ቁጭቱ ከዚህ የሚመነጨ ነው።

በመጨረሻው መንቶ የፍቅር ጅምሩ ቢኖርም (መሳሳም) የፍቅር ግንኙነት ተገቢ ካልሆነ ሰው ጋር የተደረገ በመሆኑ ማህበራዊ ትችት አስከትሏል። ትችቱ ሀሜት ነው፤ የሀሜቱ መነሻ ባለትዳር ከሆነ ሰው (የሰው ሽጋ የሚለው ይህንን ይጠቁማል) ጋር ፍቅር መጀመር ነው። ሀሜቱን የምታሰራጨው የቤት ሰራተኛይቱ ናት። ይህን የሚያረጋግጠው «ከቁና ጥሬ ጋር ሲፈጭ ያድራል ስሜ» የሚለው ስንኝ ነው። በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት መንቶዎች በግለሰብ ደረጃ በሚታዩ የህይወት አለመሳካቶች ምክንያት የተፈጠሩ የብሶትና የቁጭት መልክቶች የተላለፉባቸው ናቸው።

6.2.5.2 የጥላቻና የማንኪሰስ ቃልግጥሞች

ጥላቻ ማለት አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር አሉታዊ በሆነ መንገድ መረዳትና በዚህ አሉታዊ ምክንያት የተነሳ በክፉ አይን መመልከትን የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ነው። ለምሳሌ በፍቅር ወይም በትዳር ህይወት ውስጥ መካካድ ሲፈጠር፣ ለመጥላት ሰበብ ይሆናል። በትዳር ታማኝ አለመሆን ጥላቻ ያነሳሳል። ፍቅርን በጥቅም መለወጥ ወይም አድልኦ መፍጠር ለጥላቻ ይገፋፋል። በአጠቃላይ በእርስ በርስ ግኝኙነት ውስጥ አንዱ የማይፈልገውን፣ ሌላው ለማድረግ በመፈለግ ሂደት ላይ፣ የጥላቻ ስሜት ሊፈጥር ይችላል ማለት ነው።

ማንኪሰስ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር ዝቅ አድርጎ ማየት፣ ማራከስ፣ ማጥላላት፣ ተገላጩን ሰው የበታችነት ስሜት እንዲሰማው ማድረግ፣ ያለውን የሰውነት «ጎዶሎ አፈጣጠር» ወይም ገፅታ እየጠቀሱ ማሽሚጠጥ፣ የመሳሰሉትን የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ነው። በፍቅር ወይም በትዳር ጊዜ ለማንጓሰስና ለማጥላላት ሰበብ ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶች ደግሞ፤ ትዳርን አለማክበር፣ በአንድ አለመወሰን ወይም አለመፅናት፣ በሴቷ ወይም በወንዱ አይን በንቀት መታየት፣ በመልክ ወይም በተክለ ሰውነት አለመመጣጠን (አቻ) አለመሆን፣ ፈላጊ ማጣት፣ ስህተትን ለመሸፈን መጠቀሚያ ማድረግ፣ የመሳሰሉት ናቸው።

የሚከተሉት ቃልግጥሞች የጥላቻና የማንኳሰስ ስሜቶች የተንፀባረቁባቸው ሲሆኑ፣ ብዙዎቹ ከትዳር ወይም ከፍቅር ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በተፈጠሩ አለመግባባቶች ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው። መጀመሪያ የጥላቻ ስሜት የተንፀባረቀባቸው ቃልግጥሞች ከተመለከትን በኋላ፣ ቀጥሎ ደግሞ የማንኳሰስ ሀሳብና ስሜት ያላቸውን እናያለን።

መንቶ 219 ትምንምን ትምንምን ትዳርሽ አይጥና
የባህር ላይ ኩበት አርገሸኛልና
መንቶ 220 ሰው ወድጀ አላውቅም ያላንቺ በጭራሽ
እንደኔ ሰው ወደሽ ያመንሽው ሰው ይክዳሽ
አርኬ 221 አይንሽን ያፍስሰው ብረቱን ብረቱን
ጥርስሽን ያርግፈው ንጣቱን ንጣቱን
ሀብታምና ደሀ የለየሽበትን
መንቶ 222 የዶሮ ቅምድምድ ያፈር ጢስ ይሞቃል
ለዛ የሌለው ሰው ምኑ ይናፈቃል

መንቶ 219 እና 220 ውስጥ የተጠቀሰው የጥላቻ ስሜት መነሻው ክህደት ነው። ክህደቱ በወንዱ ላይ የተፈፀመ ነው። «እንጋባለን በሚል ቃልኪዳን» ወይም ሀሳብ ላይ የነበሩት ተቃራኒ ፆታዎች፣ ሴቷ ሌላ ባል በማግባቷ ምክንያት የተበሳጨ አፍቃሪ እርግማን ነው። «ትዳርሽ አይጥና»፣ «ያመንሽው ሰው ይክዳሽ»፣ የሚሉት ሀረጎች እርግማኖች ናቸው። «የባህር ላይ ኩበት...» የሚለው ሀረግ ምን ማድረግ እንዳለበት መወሰን ያቃተው መሆኑን የሚያሳይ ነው። በሀሳብ መዋለልን፣ መቁረጥ አለመቻልን ያመለክታል። መንቶ 220 ደግሞ፣ ፍቅሩን የተከዳ አፍቃሪ ያሰማው የጥላቻ ስሜት ነው። ፍቅሩ የመጀመሪያ መሆኑን የሚያመለክተው ስንኝ «ሰው ወድጄ አላውቅም ...» የሚለው ነው። የፍቅር እምነቱን ያሳረፈባት ተፈቃሪ ግን፣ ምላሿ ክህደት ነው። ይህም በመሆኑ «እኔን እንደከዳሽ አንቺንም ያመንሽው ይክዳሽ» በማለት ይረግማታል።

አርኬ 221 ላይ የጥላቻው ስሜት መነሻ የሆነው የፍቅር አድልኦ ነው። በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰችው ሴት ያፈቀራትን ሳይሆን ሀብት ያለውን ያስቀደመች (የመረጠች) ይመስላል። የጥላቻ እርግማኑ ትኩረት ያደረገው በአይንና በጥርሷ ላይ በማነጣጠር ነው። በአይኗ እያባበለች በጥርሷ እየሳቀች ገንዘብ (ሀብት) ያለውን ለመሳብ የተጠቀመችባቸው ናቸው ብሎ ስላሰበ ጉዳት እንዲደርስባቸው ምኞት አለው። «አይንሽን ያፍስሰው ጥርስሽን ያርግፈው»

የሚሉት ሀረጎች የጥላቻ እርግማኖች ናቸው። ዶሮዎች በሰውነታቸው ውስጥ ምናልባት ተባይ በሚኖሩበት ጊዜ ተባዩን ለማራገፍ ሲፈልጉ መሬት እየጫሩ አፈሩን በሰውነታቸው ውስጥ ያስገቡና ክንፎቻቸውን እያርገፈገፉ ተባዩን ለማራገፍ ይሞክራሉ። ይህንን ነገር፣ ሰዎች፣ ከሴቶች የፍቅር ፍላጎት መነሳሳት ጋር ያመሳስሉታል። መንቶ 222 ውስጥ «የዶሮ ቅምድምድ ...» የሚለው ስንኝ እንደ ተረትና ምሳሌ የሚነገር መሆኑን አጥኚው ያስታውሳል። ተናጋሪው ይህንን አባባል በመጠቀም ነው የጥላቻ ስሜቱን የገለፀው። «ለዛ» ማለት ፀባይ፣ አመል፣ እንደማለት ሲሆን፣ ጥሩ ፀባይ የሌለው ሰው፣ ባፍቃሪው ልብ ውስጥ የሚቀረው ትዝታ ስለሌለው አይናፈቅም ማለት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የማንሲስ ሀሳብ የሚንፀባረቅባቸውን ቃልግጥሞች እንመለከታለን። መጀመሪያ መልከ ጥፉነትን፣ ቀጥሎ በአንድ ባለ መፅናት ሰበብ፣ የተፈጠረን ችግር መነሻ በማድረግ የቀረቡትን እናያለን።

አርኬ 223 አይኗ የመሰለው የፈረጠ እንቧይ
ጥርሷ የመሰለው አር የገመጠይ
ደሞ ኸሷ ብሶ ሰው ልትንቅ ነወይ
መንቶ 224 ሸጋ ሸጋውማ ገበያው ሙሉ ነው
ያረባባ መውደድ የጉፋን እዳ ነው
መንቶ 225 ሸጋ ለሸጋ ነው የሚዋደደው
ጉንፋን ይሆናል ምናምኑ ሰው
መንቶ 226 ወርቅ ቀለበቴን ለውጬ በመዳብ
ለቀይ እንኳ አይደለም ለጥቁር አመዳም
መንቶ 227 እናትና አባቷ እረግመዋት ኑሮ
ብቻዋን ታድራለች ቁፍ እንዳለች ዶሮ
መንቶ 228 አንድ ቀን ተስቶኝ ጅል አቅፌ ብገኝ
ጅል የጠፋው ሁሉ መፈለጊያ አረገኝ

እነዚህ ቃልግጥሞች የሴቷን ጎዶሎ ገጽታዎች እየጠቀሱ የበታችነት ስሜት እንዲፈጠርባት የሚያደርጉ ናቸው። የአይኗን፣ የጥርሷን፣ የመልኳን፣ ጉድለቶች አጉልቶ በማሳየት የሚያንሲስ መልክት የተንፀባረቀባቸው ናቸው። አይኗን የፈረጠ እንባይ፣ መልኳን ወዝ አልባ (አመዳም) በማለት ለማጣጣል የሚሞክሩ ናቸው። ግጥሞቹ «ፍቅር ወይም መዋደድ ከእኩያ

ጋር፣ ከቆንጆ ጋር ካልሆነ አስፈላጊ አይደለም» የሚል አንድምታ ያላቸው ይመስላሉ። «የጉንፋንን እዳ ነው፣ ሳል ጉንፋን ይሆናል ...» የሚሉት ሀረጎች ይህንን የሚያመለክቱ ናቸው። የማጥላላት ደረጃው ከፍ ብሎ የሚታየው፣ «ብቻዋን ታድራለች ቁፍ እንዳለች ዶሮ» በሚለው ስንኝ አማካኝነት ነው። ቁፍ ያለች ዶሮ፣ ከዶሮዎች ጋር አትደባለቅም፣ አውራውም አይቀርባትም፣ ሊቀርባት ቢፈልግም አታስጠጋውም። ይህንን እውነታ ነው ከሰው ልጅ ጋር ለማያያዝ የሞከረው። ልጅቱ ፈላጊ ያጣችው የቤተሰብ እርግማን ስላለባት ነው የሚል ነው። የመጨረሻው መንቶ የሴቷን መልክ በማጥላላት ብቻ ተመስርቶ የራስን ደካማነት ለመሸፋፈን የሚሞክር ነው። ሴቷን «ጅል» በማለት ስህተቱን ለመደበቅ ይሞክራል። ቀጥሎ ያሉት መንቶዎች ደግሞ፣ በፍቅር ግንኙነት ታሪክ ውስጥ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በሚደረግ የጾታ ግንኙነት ስህተት ምክንያት የሚፈጥርን ማህበራዊ ችግር የሚያመለክቱ ናቸው።

መንቶ 229 እንደ ባርማሽላ ሁሉን እያቀፍሽ
የልጅሽን አባት ሳታውቂው አረፍሽ
መንቶ 230 አርግዘሻል አሉ የርብርብ ልጅ
እኔም ይደርሰኛል አንድ እግር ታንድ እጅ

«እንደ ባር ማሽላ ሁሉን እያቀፍሽ» የሚለው ስንኝ በአንድ አለመወሰን፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ጾታዊ ግንኙነት ማድረግን የሚመለከት ነው። ይህም በመሆኑ የማንነት ችግር እስከ መፍጠር የሚደርስ ቤተሰባዊ ችግር ሊያጋጥም እንደሚችል ያሳያል። አንድምታው «እሰይ! የት አባሽ! ልጅሽ አባት አልባ ሆነ» የሚል ስድብ ያለበት ነው። የማጥላላቱና የማንኳሰሱ ሁኔታ በስድብ የታጀበ ነው።

በአጠቃላይ በጥላቻና በማንኳሰስ መልክ የቀረቡት ቃልግጥሞች በአንድ በኩል የውስጥ ስሜትን እንደመተንፈሻ አማራጭ መንገዶች ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ወደ ተሳሳተ ማህበራዊ ችግር ውስጥ እንዳይገቡ የማስጠንቀቂያ መልዕክቶች የተላለፉባቸው ናቸው። ትችቱ፣ ጥላቻው፣ ማንኳሰሱና ማጥላላቱ፣ ከስህተት የመመለሻ ወይም ወደ ስህተት እንዳይገባ የመከላከያ መሳሪያዎች ናቸው ማለት ነው።

6.2. 6 ከፖለቲካና ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር ተያይዞ የታዩትን ፖለቲካዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚያንጸባርቁ ቃልግጥሞች

ይህ ምድብ ሁለት አብይ ጉዳዮች በአንድ ላይ የቀረቡበት ነው:: አንደኛው ፓለቲካዊ ሲሆን ሁለተኛው የእርስ በርስ ጦርነት ወይም ግጭት ነው:: በፖለቲካውም ሆነ በግጭቱ ሳቢያ የተገጠሙ ቃልግጥሞች እስካሁን ከታዩትም ሆነ ከዚህ ቀጥሎ ከሚመጡት ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ ነው:: በዚህ ምድብ 172 ያህል ቃልግጥሞች ተሰብስበዋል:: ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ግጥሞች በአጠቃላይ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ወይም እስከ 1990ዎቹ ድረሰ የታየውን የሀገራችንን ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ. ሁኔታዎች የሚያንፀባርቁ ናቸው:: ይዘቶቹም የድጋፍ፣ የተቃውሞ፣ የትዝብት፣ (ማለትም በመደገፍና በመቃውም ሳይሆን ሁኔታውን እንደ ውጭ ተመልካች በመሆን የመግለፅ፣ ፍርድ የመስጠት፣ የመመስከር፣ ወዘተ. አቀራረብ ያላቸው) ሙስና እና አድልኦ፣ እንዲሁም ጥርጣሬና አለመተማመን የተንፀባረቁባቸው ናቸው:: ከአቢዮቱ ፍንዳታ ማግስት የተቋቋመውን መንግስትና እሱን ተከትሎ በመጡት ልዩ ልዩ የተቃውም እንቅስቃሴዎችና እርምጃዎች፣ እንዲሁም ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በተቋቋመው የኢህአዲግ መንግስትና እሱን ተከትሎ በታዩት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ሁኔታዎችና ማህበራዊ ችግሮች (እንደ ሙስና፣ አድሎ፣ ወዘተ.) ምክንያት እየተፈጠሩ የተነገሩ ቃልግጥሞች፣ ፓለቲካዊ ይዘት በሚለው ንዑስ ምድብ ውስጥ የተደራጁ ናቸው:: ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል ሁለቱን ስርአቶች በየራሳቸው እይታ የሚደግፍ አላማ ያላቸውን በአንድ ላይ፣ የተቃውም ያላቸውም እንዲሁ፣ በአንድ ላይ ተመድበዋል:: በዚህ ውስጥ ወደ 94 ያህል ቃልግጥሞች ይገኛሉ::

ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር በተያያዘ የተገጠሙት ቃልግጥሞች እንደ ዘመናቸው ርቀትና ቅርበት ወቅታዊ እና ቆየት ያሉ በሚል ለመከፋፈል ተሞክሯል:: ወቅታዊ የሚባሉት ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የተደረጉትን የእርስ በርስ ግጭቶች የሚመለከቱ ሲሆኑ ቆየት ያሉ የተባሉት ደገሞ ከአፄ ሚኒሊክ ዘመን ጀምሮ እስከ አፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ድረስ የነበረውን ሁኔታ የሚገልፁ ናቸው:: ይህ ንዑስ ምድብ ታሪካዊ ሊባሉ የሚችሉ ቃልግጥሞች ያሉበት ነው:: አጠቃላይ ምድቡ የድጋፍ፣ የተቃውም እና የትዝብት ቃልግጥሞች፣ የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነትን የሚገልፁ ቃልግጥሞች የቀረቡበት ነው:: ምድቡ ለታሪክ ለፖለቲካ ለአስተዳደር ወዘተ. ተመራማሪዎች ጠቃሚ መረጃ አለው::

በሀገራችን የፖለቲካም ሆነ የአስተዳደር ታሪክ በታሪክ ምሁራን አከፋፈል ሶስተኛው የታሪክ ምዕራፍ የሚባለው የአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ነው። ይኸ ክፍለ ዘመን ከአፄ ቴዎድሮስ መነሳትና ከዘመነ መሳፍንት ማክተም ጋር የተገናኘ ነው። አፄ ቴዎድሮስ በ1845 ዓ.ም የዘመነ መሳፍንት ማክተሚያ የሆነው ድል ከተቀዳጁ በኋላ አገራቱን በአንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ሥር አድርገው ለመምራት ጥረት አድርገዋል። ይህንን በሚመለከት ተክለፃድቅ (1981፣243) እንደገለፁት፣ «አፄ ቴዎድሮስ በአስራ ዘጠነኛው መቶ አመት አጋማሽ ላይ ሳይታሰቡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብቅ ያሉ... ከሰባ አመት በላይ የቆየውን ... ዘመነ መሳፍንትን በማስወገድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ለማቆም... ለኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ የከፈቱ ... ናቸው» በማለት ያረጋግጣሉ። ይህ የማዕከላዊ አስተዳደር ምስረታ ከእሳቸው ቀጥሎ በመጡት ተከታታይ መሪዎች ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ ዛሬ ያለው የሀገራችን የአስተዳደር ግዛት ሊፈጠር ችሏል። ይህ የግዛትና የማዕከላዊ መንግስት ምስረታ በየዘመኑ ለተነሱት መሪዎች ቀላል እንዳልነበረ ይታወቃል።

አፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ባለው የታሪክ ሂደት ውስጥ ጎልተው የሚጠቅሱት አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ሚኒሊክና አፄ ሀይለስላሴ ናቸው። እነዚህ መሪዎች በየዘመናቸው ጠንካራ አስተዳደራዊ ስርዓት ለመመስረት የቻሉትን ሁሉ አድርገዋል ማለት ይቻላል። የአፄ ሀይለ ስላሴን ዘውዳዊ አስተዳደር ለመለወጥ የተካሄደው የ1966ቱ አቢዮትና፣ አብዮቱን ተከትሎ በሀገራችን የተፈጠረው የፖለቲካ ሽኩቻ መተኪያ የሌላቸውን የሀገሪቱን የተማሩ ዜጎች ሰለባ አድርጎ እንዳለፈ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በመሆኑም በዚህ ክፍል ውስጥ የምናያቸው ቃል ግጥሞች የ1966ቱን አብዮት ተከትሎ የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታና የእርስ በርስ ግጭት የሚመለከቱ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ ከ1950ዎቹ ጀምሮ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረውን የርስ በርስ ጦርነትና ወደኋላ በነበረው ቆየት ያለ ታሪካችን አማካኝነት የተገጠሙትንም እንመለከታለን። እነዚህ ቃልግጥሞች አብዛኞቹ ከደርግ እስከ ኢህአዴግ ያለውን የታሪክ ሂደትና እውነታ በድጋፍ ወይም በተቃውሞ የሚያመለክቱ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ በሁለቱም በኩል የነበረውን ሁኔታ ከድጋፍ ወይም ከተቃውሞ ነፃ በሆነ መንገድ የሚገልፁ ናቸው።

ይህ ክፍል ከታሪካዊ ጠቀሜታ (historical usage) ንድፈ ሀሳብ ጋር የተያያዘ መረጃ ያለው ነው። በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ገላጭ መረጃዎች ታሪክ በመጻፍ ሂደት ውስጥ ጥቅም አላቸው። እነዚህ መረጃዎች በሁለት መንገድ ዋጋ ይኖራቸዋል። አንደኛው ታሪካዊ መረጃን በመያዝ ሲሆን ሁለተኛው የተገኙበትን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ምኞቶች፣

አመለካከቶች ወዘተ ... የሚያንፀባርቁ ሰነዶች በመሆን ነው። ስለሆነም እነዚህ ቃል ግጥሞች የተፈጠሩበትን ወይም የየተናገሩበትን ዘመንና ሁኔታ የመጠቆም፣ የማሳየት ሀይል ስላላቸው ከሌሎች የመረጃ ምንጮች ጋር በመጣመር ለታሪክ መረጃ ያገለግላሉ ማለት ነው።

6.2.6.1 የፖለቲካ ድጋፍና ተቃውሞ የተንፀባረቀባቸው ቃልግጥሞች

በዚህ ውስጥ የምናያቸው ቃልግጥሞች ከ1966 ዓ.ም በኋላ የታየውን የፖለቲካ ለውጥና ለውጡን ተከትሎ በተፈጠረው ችግር ምክንያት የተገጠሙትን ነው። ቃለ ግጥሞቹ ደርግን የሚደግፍና የተቃወም፣ ኢህአዲግን የሚደግፍና የሚቃወም፣ እንዲሁም ሁለቱንም ስርዓቶች ሳይደግፍ ወይም ሳይቃወም የነበረውን የታሪክ እውነታ ብቻ የሚያመለክቱ ናቸው።

6.2.6.1.1 ከደርግ ስርዓት ጋር የተያያዙ የድጋፍ እና የተቃውሞ ቃልግጥሞች

ከኢትዮጵያ አብዮት ማግስት የታየውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች በየአካባቢው ተፈጥረዋል። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቃልግጥሞች አብዮት ወዲያው እንደ ፈነዳ ጀምሮ በታየው ሁኔታ ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው።

መንቶ 231 የደርጉ መኪና ሽራ የለበስሽው
ከበደ አለ ወሌን ወይት አድረስሽው
መንቶ 232 የደርጉ ጥልቆ እጀታዋ መልካም
አድሀሪን እንጅ ጭቁኑን አትነካም
መንቶ 233 መሬት አይኑን ታሞ በገመድ ይመራል
ባላባቱ ሁላ ምን ይሽቆመቆማል
መንቶ 234 መንጌ ሀይለማሪያም የልጅ ልጅህ ይብዛ
ቀደህ ትሰጣለህ መሬት እንዳጎዛ
መንቶ 235 መንጌ ሀይለማሪያም ሰባት ነው ጡቱ
ያንንም ያንንም የሚያጠባበቱ
መንቶ 236 መንጌ ሀይለማሪያም ስማ ልንገርህ
የሰራኸው አስፋልት ቆሞ ቀረልህ

እነዚህ መንቶዎች ከ1983 ዓ.ም በፊትና ከ1966 ዓ.ም በኋላ ባሉት አመታት ውስጥ የተፈጠሩ ናቸው። አቢዮቱን ተከትሎ የመጣውን መንግስት (ደርግን) የሚደግፉ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት መንቶዎች ከአብዮቱ በኋላ የታየውን እውነታ የሚያስታውሱ ናቸው። በመጀመሪያው መንቶ ውስጥ በስም የተጠቀሱት ግለሰብ በወቅቱ የአምባሰል አውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩ ባላባት ናቸው። ይህን ሰው የመንግስት ካድሬዎች አፍነው ወስደዋቸዋል ይባላል። የሀሳቡ መነሻ አቢዮተኞቹ ሸራ በለበሱ ትንንሽ መኪኖች ባለስልጣን የነበሩ ሰዎችን ይወስዱ ስለነበር ነው። የአካባቢው ማህበረሰብ ሰዎቹን በመኪና እንደወሰዷቸው እንጂ ወዴት እንደወሰዷቸው ማወቅ ስላልቻለ ይህን ስሜት በግጥም መልክ ቀርቧል። በሁለተኛው መንቶ የጠፉት ባላባቶች የደረሰባቸውን መጥፎ እጣ ጠቋሚ ነው። «ጥልቆ» አነስተኛ መጥረቢያ ሲሆን «አብዮታዊ እርምጃ» የሚለውን ታሳያለች። በአቢዮቱ ማግስት በሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ባለስልጣን የነበሩትን «ባላባት» ሰዎች በተለይ አብዮቱን ሊቃወሙ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰቡትን ካድሬዎች እርምጃ ይወስዱባቸው ነበር ይባላል። በወቅቱ የእንደነዚህ አይነት ሰዎች መጠሪያ «አድሀሪ» የሚል ነበር። ጭቁን የሚባለው የማህበረሰብ ክፍል በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበረው ነው። ይህ የማህበረሰብ ክፍል «የአቢዮቱ ተጠቃሚና ደጋፊ» ነው ተብሎ ስለሚታሰብ አቢዮታዊ እርምጃ አይወስድበትም ተብሎ ይታመናል።

የመንግስት ለውጡ ይዟቸው ከመጡ ነገሮች አንዱ የመሬት ለአራሹ አዋጅ ነው። «በባላባቶች» ተይዘው የነበሩ ሰፋፊ ጋሻ መሬቶች ለድሀው እና ለአርሶ አደሩ የማህበረሰብ ክፍል እንዲከፋፈል ተደርጓል። መንቶ 233 ላይ የመጀመሪያው ስንኝ ይህን ክፍፍል ያስታውሳል። «መሬት አይኑን ታሞ በገመድ ይመራል» የሚለው የመሬት ክፍፍሉ በሜትር ወይም በሄክታር እየተለካ ለአርሶ አደሩ ይከፋፈል እንደነበር የሚያሳይ ነው። በሁለተኛው ስንኝ የመሬት ክፍፍሉ ተቃውሞ ያሳዩትም የመሬት ባለቤትም ሀሰብ ያለበት ነው። «መሸቆምቆም» ማለት ሙሉ በሙሉ አለመስማማት፣ ደስተኛ አለመሆን ማለት ነው። ተቃውሞ ያሳዩትም የመሬት ባለቤት ባላባት ከነበሩ ሰዎች ነው። መንቶ 234 ግን ፣የመሬት ክፍፍሉን የሚደግፉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደነበሩ ያመለክታል። ይኸውም የደርግ ሊቀመንበር ከነበሩት ጋር የተያያዘ ነው። በሰዎች አስተሳሰብ መሬት የሚሰጠው ወይም የሚቀማው በእሳቸው ትዕዛዝና መመሪያ ነው ተብሎ ስለሚታመን ምርቃት ወይም ድጋፍ ይሰጥ የነበረው ስማቸውን በመጥራት ነው። «የልጅ ልጅህ ይብዛ» የሚለው ከድጋፍ የሚመነጭ ምርቃት ነው።

በተለምዶ የመንግስት መሪዎች ለክፉም ሆነ ለደግ ሥራ ኃላፊዎች እነሱ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። መንቶ 235 ላይ የተገለጸው ሀሳብ ይኸው ነው። አቀራረቡ ተጠየቃዊ ባይሆንም ሊተላለፍ የተፈለገው ድህውን የማህበረሰብ ክፍል ችግር ተረድቶ መፍትሄ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው። «ያንንም ያንንም» የሚለው አገላለፅ መፍትሄ ያገኘው ሰው ብዙ መሆኑን የሚጠቁም ነው። ይህ መንቶ በርሀቡ ጊዜ የተደረገውን እርዳታ የሚያመላክት ጭምር ነው። የመጨረሻው መንቶ ከመሰረተ ልማት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተፈጠረ ነው። ዛሬ የገጠር ሆስፒታል የተገነባበት ቦታ በደርግ ጊዜ ለአውሮፕላን ማረፊያ እንዲሆን የተሰራ አስፓልት ነበር። ይህ ቦታ የሚገኘው ከቆቦ ከተማ በስተምስራቅ አቅጣጫ ባለው የእርሻ መሬት ላይ ነው። እዚያ አካባቢ አንድ ማይክሮዌቭ አለ። ይህን ተቋም በእርስ በርስ ጦርነቱ ጊዜ የኢህአዲግ ወታደሮች እንዳይዙት ታሰቦ ዙሪያውን በአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት በሸቦ ታጥሮ ዳርዳሩ ፈንጅ ተቀብሮበት ከመሀል ሰራዊት ሰፍሮበት ነበር። በ1982 ዓ.ም የመንግስት ጦር አካባቢው በሀይል ሲለቅ እነዚህ መሰረተ ልማቶች በአካባቢ ሰው ፈራርሰዋል። መንቶው ይህንን እውነተ የሚያሳይ ነው። የተገነባው የአውሮፕላን ማረፊያ ያለምንም አገልግሎት ለብልሽት መደረጉን የሚያመላክት ነው።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ደርግን በመደገፍ የተነገሩ የፖለቲካ ቃል ግጥሞች ሲሆኑ ቀጥሎ ደግሞ ደርግን በመቃወም የተነገሩትን እንመለከታለን።

መንቶ 237 ይምጡ በሮቻችን አርደን እንብላቸው
ደሞ እንደመራቱ ሳይደለድሏቸው
መንቶ 238 እንግዲህ ወላጆች ለየብቻ እደሩ፣ለየብቻ ዋሉ
ፊት የተወለዱት ካላገለገሉ
መንቶ 239 ወላጆች ልጆቹን መልሳችሁ ዋጡ
ይኸ ቀን አያምርም አይን አገላለጡ
አርኬ 240 አካላቱ ደርጉ፣ሞንሚናየ ደርጉ፣
እርሻ አንጡ ሲለን፣እርሻንም ሰጠን
ልጅ አንጡ ሲለን ፣ልጅንም ሰጠን
ብር አዋጡ ሲለን ፣ብርም አዋጣን
ቅቤ አምጡ ይለናል፣ቅቤ የት ተገኝቶ
በአድሀሪው ንጉስ ተቀልጦ ተበልቶ

መንቶ 241 በጃንወይ ጊዜ ወልጂ ወልጂ
በመንግስቱ ጊዜ ወይ ልጂ ወይ ልጂ
መንቶ 242 አንድ ፍየል የለም በዚህ ላይ ዳገት
ተለያይቶ ቀረ ድሃና ዱለት
መንቶ 243 እስቲ ሰወይ ህዩ እኒህን ጥጆይ
ይኸን ማዶ ጓሳ አያበላም ወዶ
መንቶ 244 እንዲህ ያለ መንግስት፣የመንግስት አዋቂ
ሚስቱን ሊቀመንበር እኔን ቤት ጠባቂ

መንቶ 233 እና 234 ላይ የተጠቀሰው የመሬት ክፍፍል ድጋፍ፣ በመንቶ 237 ላይ ተቃውሞ ገጥሞታል። በመንቶው ሀሳብ መሠረት የመሬት ክፍፍሉ ተግባራዊ ሊሆን የቻለው መሬትን ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ ወይም መደበቅ ባለመቻሉ ምክንያት ይመስላል። መሬትን ማንቀሳቀስ ወይም መደበቅ የሚችል ቢሆን ኖሮ ክፍፍሉ አስቸጋሪ ይሆን ነበር ማለት ነው። «ይምጡ በሮቻችነን አርደን እንብላቸው» የሚለው ስንኝ ይህን ያመለክታል። መሬታችንን አይናችን እያየ እንደተቀማን ሁሉ በሮቻችንንም ሊቀሙን ሲሉ ዝም ብለን ማየት የለብንም የሚል ተቃውሞ የተላለፈበት መንቶ ነው።

በአቢዮቱ ማግስት በሀገራችን የነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ገፅታ እንደነበረው መንቶ 238 እና 239 ይጠቁማሉ። በተለይም በኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአዲግ) በደርግ መካከል የነበረው ሽኩቻና ፍጥጫ ያስጨንቅ እንደነበር ይታወሳል። «... ወላጆች ለየብቻ ዋሉ፣ ለየብቻ እደሩ» ማለት ልጅ አትውለዱ ማለት ነው። ለዚህ ምክንያቱ ወጣቶች በፈቃደኝነት ወይም በግድ ለውትድርና ይመለመሉ ስለነበር ነው። ለምሳሌ በሶማሊያ ጦርነት ጊዜ ወጣቶች በአፈሳ ለውትድርና ይወሰዱ ነበር። ይህን ለመግለጽ ነው መንቶ 239 የተነገረው። መንቶው ዘመኑን እንደሰው «ይኸ ቀን አያምርም አይን አገላለጡ» በማለት፣ በወቅቱ የነበረው ሁኔታ አስከፊ እና አስፈሪ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

አርኬ 240 ምፀታዊ በሆነ መንገድ የቀረበ የተቃውሞ ሀሳብ ነው። ምፀቱ ገና ከመነሻው ስንኝ ይጀምራል። «አካላቴ፣ ሞንሚየ» የሚሉት የቁልምጫ ቃላት፣ ከልብ የመነጨ እንዳልሆነ ቀጥሎ ያሉትን ስንኞች ስናነብ እንረዳለን። በነዚህ ስንኞች ደርግ መሬት፣ ልጅ፣ ገንዘብ ሲጠየቅ፣ ሳይወዱ በግድ ተቀብሏቸዋል። በመጨረሻዎቹ ሁለት ስንኞች የግጥሙ የተቃውሞ ሀሳብ ቅኔያዊ በሆነ መንገድ ቀርቧል። «ቅቤ» የጥሩ ኑሮ መገለጫ ሆኖ ነው የቀረበው።

«እናንተ አደሀሪ ብላችሁ በምትጠሩት በንጉሱ ዘመን ኑሮአችን የተሻለ ነበር። እናንተ ችግር እንጂ የተሻለ ነገር አላመጣችሁልንም» የሚል ነው። መንቶ 241 የቁጭት ሀሳብ የተላለፈበት ነው። በንጉሱ ጊዜ የአርሶ አደሩን ልጆች ለውትድርና የሚያስገድድ ሁኔታ ስላልነበረ፣ ልጅ መውለድ እንደ ትልቅ ፀጋ ይቆጠር የነበረበት ጊዜ ነው።በደርግ ግን አንድም በቀይ ሽብር አልያም በውትድርና ምልመላ (አፈሳ) ምክንያት ወላጆች እጅግ የተማረሩበትና የተጨነቁበት ጊዜ የነበረ መሆኑን‹‹በመንግስቱ ጊዜ ወይ ልጄ! ወይ ልጄ!»የሚለው ስንኝ የሚያመለክትነው።

መንቶ 242 እና 243 ውስጥ ባሉት ቃለ ግጥሞች ለየት ያለ ሀሳብ የተነገረባቸው ናቸው። ከአቢዮቱ በኋላ በየአካባቢው በነበሩ የገበሬ ማህበራት አማካኝነት የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ነበር። በየገበሬ ማህበራቱ ውስጥ በሚገኙ ተራራማና ጭንጫማ አካባቢዎች እንስሳት እንዳይለቀቁ (እንዳይሰማሩ) በማለት አዋጅ የሚመስል ህግ ወጥቶ ነበር። ተሰማርተው ከተገኙ ባለቤቱ ይቀጣል። በዚህ ምክንያት ፍየልና ጥጃ የሚሰማራበት ቦታ ጠፋ። ጥጆች ተርበው ሰውነታቸው ከሳ፣ ለሞት ተጋለጡ፣ ላሞቹ ወተት መስጠት አቃታቸው። ፍየል ማርባት ችግር ሆነ፤ በዚህም ለእርድ የሚሆን ፍየል ማግኘት አስቸገሪ ሆነ። በግ ወይም ፍየል ሲታረድ፣ ቢያንስ ዱለቱን ከጎረቤቱ ጋር ተካፍሎ ይቃመስ ስለነበር ነው፣ «ተለያይቶ ቀረ ደሀና ዱለት» የሚለው ስንኝ የሚያስታውሰው።

የመጨረሻው መንቶ በፖለቲካ ተሳትፎ ምክንያት በቤተሰብ መካከል የተፈጠረን ችግር የሚያሳይ ነው። አቢዮቱን ተከትሎ ህዝባዊ ማህበራት ይደራጁ እንደነበር የሚታወስ ነው። ከነዚህ መካከል አንዱ የሴቶች ማህበር ነው። በዚህ ማህበር አማካኝነት ሴቶች ስለመብታቸው ይወያዩ፣ ይታገሉ ነበር። ይህ ሁኔተ ግን በአንዳንድ አባውራዎች ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። እንደምክንያት ይወሰድ የነበረው ደግሞ «አለመተማመን» ነው። የመንቶው ታሪክ መነሻ ሀሳብ ይኽነው። የሴቶች ማህበር ሊቀመንበር የነበረችው ባለትዳር ሴት ከአንድ ባለ ስልጣን ጋር ትታማለች። በየሰበቡ ከቤት እየወጣች ባሏን ስላስቸገረች ባልየው ጉዳዩን ለፓርቲ ጽ/ቤት አቤት በማለቱ፣ ተጠርጣሪው ባለስልጣን ቅጣት የተወሰነበት መሆኑን የሚያስታውስ ነው። በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የድጋፍና የተቃውሞ ፖለቲካዊ ቃል ግጥሞች በደርግ ጊዜ የነበረውን ፖለቲካዊ ሁኔታ ያመለከቱ ናቸው። በዚህም በወቅቱ የነበረው ማህበረሰብ ለስርዓቱ የነበረውን አመለካከት ለመረዳት የሚያስችሉ የፖለቲካ ሰነዶች ናቸው ማለት ይቻላል።

6.2.6.1.2 ኢህአዴግን የሚመለከቱ የድጋፍና የተቃውሞ ፖለቲካዊ ቃልግጥሞች

ከ1970ዎቹ ጀምሮ በሰሜን ወሎ አካባቢዎች ባሉት የትግራይ አዋሳኞች የህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ታጣቂዎች የሽምቅ ውጊያ ያደረጉ እንደ ነበር በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል። ይህ ጊዜ አንዳንድ ቦታዎችን ሌት ገብተው አጥቅተው ይመለሱ የነበረበት ጊዜ ነው። በዚህ የርስ በርስ ጦርነትና ከጦርነቱ በኋላ ባሉት አመታት ብዙ ቃልግጥሞች ተፈጥረዋል፤ ተነግረዋል። የሚከተሉት ከኢህአዲግ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድጋፍና የተቃውሞ ሀሳብ የተነገረባቸው ቃልግጥሞች ናቸው።

መንቶ 245 ደርግ ለድርድር ሲሄድ ወደ አትላንታ
ኢህአዲግ ዘለቀች በዋድላ ድላንታ
መንቶ 246 በሮቼንም ሽጩ፣ላሞቼንም ሽጩ፣ልብሴንም ሳስማማ
ኢህአዲግ ደረሰች በነጠላ ጫማ
መንቶ 247 መለስ ዜናዊ ንጥር ነው ቅቤ ነው
አድሀሪ ያለው ወረዳ እስተ ዞን ነው

እነዚህ መንቶዎች፣ በኢህአዲግን በመደገፍ የተገጠሙ ፖለቲካዊ ቃል ግጥሞች ናቸው። የውጭ መንግስታት ደርግንና ኢህአዲግን ለማደራደር በተለያየ ጊዜ ጥረት ያደርጉ ስለነበር ይህን ለመግለጽ ነው መንቶ 245 የተነገረው መንቶ 246 የማህበረሰብ ምሬት የተንፀባረቀበት ነው። የጦርነት መዋጨው፤ የተፈጥሮ ችግሩ፤ የመሳሰሉት ማህበረሰቡን አስመርረውት የነበረ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በጊዜው ችግሩን ይፈታልኛል ብሎ ያሰበው ኢህአዲግን እንደነበረ ነው የምንረዳው። በደርግ ፖለቲካዊ የድጋፍ ቃል ግጥሞች ውስጥ እንደታየው በኢህአዲግም የድርጅቱን መሪ በስም ጠቅሶ መንቶ 247 ያሞግሳል።አቀራረቡ ‹‹አገም ጠቀም›› ይመስላል። ይህ መንቶ እንደሚያመለክተው የመልካም አስተዳደር ችግር ፈጣሪዎች ያሉት በታችኛው የስልጣን መዋቅር ውስጥ እንጅ ዋናዎቹ አይደሉም እንደማለት ነው።እንዲህ አይነቱ አቀራረብ ለደርስ ከሚችል አስተዳደራዊ ወይም ፖለቲካዊ ተጠያቂነት ማምለጫ ይሆናል።

ከዚህ ቀጥሎ በኢህአዲግ ላይ የተገጠሙ የተቃውሞ ፖለቲካዊ ቃልግጥሞችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህ የተቃውሞ ቃልግጥሞች ከምርጫ ከግምገማ፣ ከማዳበሪያ እና ከልማት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የታየውን ችግር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

መንቶ 248 ጣይቱ መርሻ ቤት ስንት ጠጅ ሞልቶ
ያስለፈልፈኛል ኸባዶ ቤት ዘግቶ
መንቶ 249 የአህአዲግ አውድማ የማያፍረው
ተወቃበት አቤ ባረበረበው
መንቶ 250 አገሬ በረሀው ኮረራው ማማሩ
ቆርጠው ቆርጠው ጣሉት ለከሰል እያሉ (ለልማት እያሉ)
መንቶ 251 ለልማት እያሉ ዛፉን ቆረጡት
አየ መጠለያ ማረፊያ ማጣት
አርኬ 252 ቆረጡት ይላሉ፡-
የአላማጣን ገርቢ ለከሰል እያሉ
ቆረጡት ይላሉ፡-
የዋጃን ኮረራ ለከሰል እያሉ
አንተንም አቢሬ ያሰጋሀል አሉ
አርኬ 253 አንተ ፈንታው ከተማ
አንዴ ተነሳና ሁለተኛ መጣ
አቢሬን ባየኸው እንዳደረጉት
መንቶ 254 አፈሩን ሸምቼ ባፈር ላይ ዘርቼ
የምከፍለው አጣሁ ልሂድ ተሰድጄ
አርኬ 255 ዳቦሽ እንጃልሽ
የለል እንጃልሽ
ከአንድ ትልም መሬት
ሰባት ቤተሰብ ቁጭ ሲልብሽ
አርኬ 256 ምን ያደርጋል ጩቤ መንግስት የጠላው
ምን ያደርጋል ብትር(ዱላ)መንግስት የጠላው
በለው በእስክርቢቶ ሰንበር በሌለው (በማይታየው)

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ መንቶዎች ከግምገማ ጋር በተያያዘ ሁኔተ የተፈጠሩ ናቸው። ቆቦ ከተማ ውስጥ ትልልቅ ሰዎች ወይም አቅም ያላቸው ሰዎች ጠጅ እየጠጡ የሚያሳልፉበት የጠጅ ቤት ነበር። መንቶ 248 ላይ ሁለተኛው ስንኝ «ያስለፈልፈኛል ከባዶ ቤት ዘግቶ» የሚለው ስንኝ ይህን ያረጋግጣል። በዚህ አገባብ «ባዶ ቤት» ማለት የስብሰባ አዳራሽ ወይም የስብሰባ ቦታ ማለት ነው። «መለፍለም» ደግሞ በግምገማ ወቅት ወይም ሂደት ሰዎች የተለያየ ሀሳብ እያቀረቡ የሚያደርጉትን ፉክክር አስተያየት ወዘተ ማለት ነው። የመንቶው ሀሳብ ተሰብስበው ሰው የግምገማውን ስርዓት የሚደግፈው አይመስልም። ባዶ ቤት እና ያስፈልገኛል የሚሉት ቃላት አሉታዊ ስለሆኑ ይህን የሚያረጋግጡ ናቸው።

መንቶ 249 ያለው ሃሳብ ታሪኩ እንዲህ ነው። ኢህአዲግ ሰሜን ወሎን እንደተቆጣጠረ «ክፍለ ህዝብ» የሚባሉት ካድሬዎች ህዝቡን እየሰበሰቡ ስለደርግ ባለስልጣን አሉታዊ በሆነ መንገድ ያስገመግሙ ነበር። በዚህ የግምገማ ሂደት አንዳንድ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን «ለመወንጀል» የሆነ ያልሆነው ሀሳብ በተገምጋሚዎች ላይ ያቀርቡ ነበር ይባላል። ከእንደነዚህ አይነት ሰዎች አንዱ «አቤ» በሚል የቁልምጫ ቃል የሚጠራው ሰው ነው። ይህ ሰው ከጊዜ በኋላ ራሱ ተገምጋሚ ሆኖ ቀረበ አሉ። በመንቶው ውስጥ «አውድማ» እህል የሚወቃበት ቦታ ሲሆን የስብሰባውን አካባቢ የሚወክል ነው። “ማፈር” ማለት ሁለት ፍች ያለው ነው። አንደኛው «መዋሸት» ሲሆን ሁለተኛው «አፈር የማይሆን፣ ምርት ለማምረት የተመቸ፣» ወዘተ. እንደማለት ነው።

በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ስንኝ የኢህአዲግ የግምገማ ስርዓት ትክክል ነው እንደ ማለት ሲሆን፣ “ማረብረብ” ማለት አውድማውን ውሃ ማጠጣትና እንዲጠብቅ ማድረግ ነው። አንዳንድ ገበሬዎች አውድማውን ለቅልቀው እህሉን ይወቃሉ። መለቅለቅም ሆነ ማረብረብ፣ እህሉ ከአፈር ጋር እንዳይደባለቅ ለማድረግ ነው።

ከመንቶ 250 እስከ 253 ባሉት ቃልግጥሞች የተነሳው አብይ ጉዳይ የደን ጭፍጨፋ ነው። በሁለቱ ራያዎች ከሚገኙት የደን ዛፎች መካከል አንዱ «ኮረራ» የሚባለው ዛፍ ነው። ይህ ዛፍ በአንዳንድ ቦታዎች «ግራር» ይሉታል። ዛፉ በርዝመቱም ሆነ በውፍረቱ በጣም ትልቅ ከመሆኑ በተጨማሪ ቅርንጫፎቹ ወፍራም ናቸው። እንጨቱ ጠንካራ ስለሆነ ለመቀጫና ለከሰል በጣም ተፈላጊ ነው። ይህ ዛፍ በ1982 ዓ.ም «በነፃ መሬት» ጊዜ በግለሰቦች እየተቆረጠ ተጨፍጭፏል። ከ1983 ዓ.ም በኋላ “ኢንቨስትመንት” በሚለው ፖሊሲ ባለሀብቶች ወይም ድርጅቶች ልዩ ልዩ የልማት ስራ እንሰራለን በማለት፣ መሬት ከመንግስት ይወስዱ

ነበር፡፡ በዚህ የልማት ስራ ላይ ተሰማርተዋል የሚባሉት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶ «የአካባቢው ተወላጆች» ባለመሆናቸው ምክንያት ተቋውሞ ተነስቶባቸው ነበር ይባላል፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች ላይ ተመስርተው ነው ቃልግጥሞቹ የተፈጠሩት፡፡

በቃልግጥሞቹ ውስጥ የተጠቀሱት አካባቢዎች አላማጣ፣ ዋጃና አሏሬ ናቸው፡፡ ዋጃና አላማጣ በአሁኑ የአስተዳደር መዋቅር ወደ ትግራይ ክልል እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች መንግስት ባልነበረበት ወቅት የነበሩት ዛፎች (ኮረራና ገርቢ) ተጨፍጭፈዋል፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ «ቆረጡት ይላሉ የአላማጣን ገርቢ» ፣ «የዋጃን ኮረራ» የሚሉት አባባሎች ናቸው፡፡ «አሏሬ» የሚባለው አካባቢ የሚገኘው ቆቦ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ ቦታው በሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ፈንታው ከተማ የሚባሉ የአንድ ግለሰብ የእርሻ መሬት ነበር፡፡ ይህ አካባቢ በአሁኑ ጊዜ «ዘለቀ እርሻ ልማት» በሚል ድርጅት አማካኝነት ግለሰቦች ወስደውታል፡፡ በዚህ ምክንያት የአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ተቃውሞ አድርጎ እንደነበር አጥኚው ያስታውሳል፡፡«አንተንም አሏሬ ያሰጋሀል አሉ» በሚል ትንቢት መሰል አገላለጽ የተነገረው ሀሳብ ተቃውሞ እንደተፈጠረበት መንቶ 253 ያረጋግጣል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው አካባቢው የአንድ ግለሰብ የእርሻ ቦታ የነበረ ነው፡፡ በሱ ይዞታ ስር የነበረው አካባቢ የደን ሽፋኑ ከፍተኛ ቢሆንም አሁን ግን ተጨፍጭፎ ባዶ ሜዳ ሆኗል፡፡ ይህን ሁኔታ ለመግለጽ ነው «አንዴ ተነሳና ሁለተኛ መኑት» የተባለው፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ መንቶዎች በአካባቢው የነበረውን የተፈጥሮ ደን (ገርቢና ኮረራ) በልዩ ልዩ ሰበብ በመጨፍጨፍ ምክንያት የነበረውን ሁኔታ በተቃውሞ ለመግለጽ የተፈጠሩ ቃልግጥሞች ናቸው፡፡

መንቶ 254 ስለማዳበሪያ የተነገረ ቃል ግጥም ነው፡፡ እንደሚታወቀው አርሶ አደሩ የተሻለ ምርት ማምረት እንዲቻል የተለያዩ ግብአተችን መጠቀም እንዳለበት የሚታወቅ ነው፡፡ ከነዚህ ግብአቶች አንዱ ማዳበሪያ ነው፡፡ የማዳበሪያ ዋጋ ከአርሶ አደሩ የመግዛት አቅም ሲታይ ከፍተኛ እንደሆነ «የምከፍለው አጣሁ ልሂድ ተሰድቼ» የሚለው ስንኝ ያረጋግጣል፡፡ ተሰድቼ ማለት ስደት ልሂድ በማዳበሪያ ምክንያት አካባቢዬን ለቅቄ ልሰደድ ማለት ነው፡፡ መንቶ 255 ደግሞ ከእርሻ መሬት ማነስ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ግጥም ነው፡፡ ኢህአዴግ የሰሜን ወሎ አካባቢዎችን እንደተቆጣጠረ ከአደረጋቸው ነገሮች አንዱ የመሬት ክፍፍል እንደገና እንዲካድ ማድረጉ ነው፡፡ ይህ የመሬት ክፍፍል ምናልባት በትግራይና በአማራ ክልሎች ብቻ የተደረገ ይሆናል፡፡ የእርሻ መሬቱ ስፋት በቤተሰብ አባላት ብዛት የተወሰነ ነበር፡፡ ብዙ ቤተሰብ ያለው «ሰፊ» መሬት ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ሆኖ ለአርሶ አደሩ በቂ እንዳልሆነ በግጥሞቹ ውስጥ ተንፀባርቋል፡፡

በመንቶው ውስጥ “ዳቦሽ እና የለል” የሚባሉ የወፍ ዝርያዎች ተጠቅሰዋል። ዳቦሽ ትንሽ ወፍ ናት። ይቺ ወፍ የማሽላና የበቆሎ እሸትን ገና በጮርቃ ጊዜያቸው በውስጣቸው ያለውን ፈሳሽ (ወተት) በመምጠጥ ከፍተኛ ጉዳት የምታደርስ ናት። ፍሬውን መዋጥ ስለማትችል ፈሳሹን እየመጠጠች ትጥላለች። ስለሆነም በቀላሉ መጥገብ ስለማትችል ጉዳቷ ከፍተኛ ነው። የለል የእርግብ ዝርያ ናት። የማሽላ እህል (ዛላ) ስለምትበላ እሷም ጉዳት አላት። እነዚህን ወፎች ለመከላከል አርሶ አደሩ ከሰብሉ መሀል ማማ ሰርቶ ይጠብቃል። የእርሻ ማሳው ሰፊ ከሆነ ከወፍ ጠባቂው እይታ ውጪ ሆነው የቻሉትን ያህል መብላት ይችላሉ። የመንቶው ሀሳብ እንኳን ለወፎች ለሰዎችም የሚበቃ ምርት ማምረት የማይችልበት የእርሻ መሬት ስለሆነ፣ ቤተሰቡ በሙሉ ይጠብቀዋል፣ ወፎች አንድ ፍሬ እንኳን መልቀም አይችሉም ማለት ነው።

የመጨረሻው መንቶ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ጋር የተያያዘ ነው። በአካባቢው አስተሳሰብ በጠላትነት የሚፈላለጉ ሰዎች አንዱ ሌላውን ለማጥቃት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ዱላ (ብትር) ጩቤ እና ጠመንጃ ናቸው። በዱላ መምታት፣ በጩቤ መውጋት፣ ወዘተ በተጎጂው ሰውነት ላይ ምልክት (ሰንበር) ያሳያሉ። መንግስት (ኢህአዲግ) ይህንን ሁኔታ ለመቆጣጠር ሲል እነዚህን ነገሮች ይዘው እንዳይንቀሳቀሱ ከልክሏል። ይህን ክልከላ ወደ ምርጫው በማዛመድ ነው መንቶው የተገጠመው። በምርጫ ስርዓት መራጮች በምርጫ ካርድ ላይ በጣት ወይም በፅሁፍ ለሚፈልጉት ተወዳዳሪ ድምጽ ይሰጣሉ። ከመንቶው ሀሳብ ስንነሳ መራጩ፣ ተቃዋሚዎችን የሚመርጥ ይመስላል። «በለው በእስክርቢቶ ሰንበር በሌለው (በማይታየው)» የሚለው ስንኝ ይህን የሚጠቁም ነው። በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ትንታኔና ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የቃልግጥሞቹ ሀሳብ፣ ተፈላጊውን አስተዳደራዊ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻል መሆኑን ማስገንዘብ ነው።

6.2.6.1.3 ትዝብታዊ ቃልግጥሞች

በዚህ አጠቃቀም «ትዝብታዊ» ማለት የታየውን እውነታ ብቻ እንደ ታዛቢ ሆኖ መናገር ወይም መመስከር ማለት ነው። በዚህ መሰረት «ትዝብታዊ ቃል ግጥሞች» በሚል ንዑስ ምድብ የተመደቡት ቃልግጥሞች ደርግን ወይም ኢህአዴግን ሳይደግፉ ወይም ሳይቃወሙ በሁለቱም በኩል የታየውን እውነታ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ብቻ ለማሳየት የቻሉትን የሚመለከት ነው። ድግግሞሹን ለማስቀረት ሲባል መጀመሪያ ደርግን፣ ቀጥሎ ኢህአዲግን የሚመለከቱትን ለየብቻ እንመለከታለን።

መንቶ 257 የወፎች አለቆች እርግቦች ነበሩ
ድንቢጦች ተነስተው ወፍ ነን ወፍ ነን አሉ
መንቶ 258 ግራ አዝማች ቀኝ አዝማች ከቀረ ባዋጂ
እንደው ጓዱ ጓዱ እንባባል እንጂ
መንቶ 259 እነ ፊትአውራሪ እነ ባላንባራስ
ደርጉ ቢጠጋቸው ሸተቱ አራስ አራስ
አርኬ 260 እናንተ ተማሮይ በጣም ቀበጣችሁ
ወይፈን ያለ በሬ እየጠመዳችሁ
ኋላ መመለሻው ቅጡ እንዳይጠፋችሁ
አርኬ 261 እንኳን ተላቀቀህ ይላል ባላገር
እንኳ አስረከብካቸው ይላል ባላገር
መቼ ነው መተኪያው ሀርሞና ሞይዘር
መንቶ 262 የሚበላው ጮማ የሚጠጣው ውስኪ
ከቶ ለምኑ ነው መለበሱ ካኪ

ከመንቶ 257 እስከ 259 ባሉት ቃል ግጥሞች ከ1966 ዓ.ም በኋላ ከመጣው አቢዮት ጋር ተያይዞ የታየውን ሁኔታ የሚመለክሩ ናቸው። የመጀመሪያው መንቶ የአብዮቱ ደጋፊ ነን የሚሉ ሰዎች ያሳዩት የነበረውን ባህሪ የሚመለከት ነው። «እርግብና ድንቢጥ» በውክልና የገቡ አዕዋፍ ናቸው። እርግብ በመልኳ የምታምር በመጠኗ መካከለኛ ናት። በባህላዊ ወይም በሀይማኖታዊ አስተሳሰብ እርግብ በደግነት፣ በገርነት፣ በየዋህነት ወዘተ ትመሰላለች። ድንቢጥ መጠኗ ትንሽና የፈሪ ምልክት ናት። በሚወክሉት የማህበረሰብ ክፍል አንፃር ሲታዩ እርግብ በወቅቱ «ትልልቅ» የሚባሉ ሰዎችን ሲሆን ድንቢጥ ደግሞ «ትንሽ» የሚባሉ ሰዎችን ነው። ባላበትና የባላባት ዝርያ አላቸው የሚባሉት ከትልልቆቹ የሚመደቡ ሲሆኑ፣ ድሀውና ጢሰኛው ከትንንሹ ይመደባሉ፤ ማለት ነው። «ወፍ ነን ወፍ ነን» የሚለው ሀረግ ሁለት ፍች ያለው ነው። አንደኛው እኛም እንደ ወፍ እንቆጠራለን፤ የወፍ ዘሮች ነን፤ ሲሆን፣ ሁለተኛው ኩራት ተሰማቸው፤ ራሳቸውን ከፍ ከፍ አደረጉ፤ የሚል ነው። በወቅቱ አቢዮቱ በመጣባቸውና በመጣላቸው መካከል የነበረውን የሰዎች አስተሳሰብ የሚመለከት መንቶ ነው።

ሌሎቹ ሁለት መንቶዎች (258 ና 259) በሁለቱ ስርዓቶች የነበረውን የማዕረግ ስም የሚመለከቱ ናቸው። ከደርግ በፊት በነበሩት መንግስታት የማእረግ ስሞች ደጃዝማች፣ ግራአዝማች፣ ፊትአውራሪ፣ ወዘተ. ነበሩ። በእነዚህ የማዕረግ ስሞች የሚታወቁ ሰዎች

አብዮቱን ይቃወማሉ ወይም አይደግፉም ተብለው ስለሚጠረጠሩ አብዮተኞቹ ወይም የአቢዮቱ ደጋፊዎች ሰዎችን በማዕረጋቸው ለመጥራት አይፈልጉም ነበር ይባላል። በሌላ በኩል የአብዮቱ መሪዎችና ደጋፊዎች ይጠሩበት የነበረው የጋራ ስም «ጓድ» የሚለው ነው። ስለዚህ መንቶ 258 «ሁላችንም የአቢዮቱ ደጋፊዎችና የለውጥ አራማጆች እንሁን» የሚል ማባበያ ነው ማለት ይቻላል።

መንቶ 259 ግን በወቅቱ የነበረውን አስፈሪ ሁኔታ የሚያስታውስ ነው።ይኸውም በአቢዮቱ ማግስት አድሀሪ፣ ፊውዳል፣ የፊውዳል ርዝራዥ፣ በሚባሉ የፖለቲካ መጠሪያዎች ሰዎችን እየፈረጀ "አቢዮታዊ እርምጃ" ይወሰድባቸው ስለ ነበር ነው። ይህን የፍርሀት ሁኔታ ለመግለጽ፣ «ሽተቱ አራስ አራስ» የሚለው ስንኝ አመላካች ነው። «አራስ» አዲስ የወለደች ሴትና ህፃን ልጅ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ ተደብቀው ከቆዩ በኋላ፣ ሰው ጋር ሲደባለቁ የስጋትና የፍርሀት ስሜት ስለነበራቸው ይህን ለመጠቆም ነው ስንኙ የተፈጠረው።

አርኬ 260 ከኢትዮጵያ ህዝብ አቢዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ጋር የነበረውን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። እንደሚታወቀው የኢህአፓ እንቅስቃሴ ከምሁራንና ከተማሪዎች ጋር የተያያዘ ነበር። የተማረው ወጣት ገና ብዙ ልምድ የሌለው፣ ችግሮችን በሀይል እንጂ በጥበብ ማለፍ የሚሳነው ይሆናል ተብሎ ይገመታል። በመሆኑም "እናንተ ተማሮይ በጣም ቀበጣችሁ" የሚለው ስንኝ «ከማን ጋር እየተጣላችሁ እንደሆነ አላወቃችሁም፤ የምትታገሉት የጦር መሳሪያ ከታጠቀ ሀይል ጋር ነው፤ ብትጠነቀቁ ወይም ብታርፉ ይሻላል፤» የሚል ነው። ወይፈን ሲቀና አባት በሬ ጋር እየተጠመደ ነው። አባት በሬው ወይፈኑን ፈር እንዳይለቅ ከቀዳሙ እንዲቆምና እንዲመለስ፣ከዚያም ፈሩን ጠብቆ እንዲያርስ ያደርገዋል፣ ይቆጣጠረዋል። ወይፈን ወጣቶችን (ተማሪዎችን) የሚወክል ሲሆን፣ በሬ ደግሞ፣ በእድሜ የበሰሉትን፣ ልምድ ያካበቱ ሰዎችን ይወክላል። ስለዚህ «ኋላ መመለሻው ቅጡ እንዳይጠፋችሁ» በማለት የገለፀው ትግሉ አስቸጋሪና የማይቻል መሆኑን ነው።

በደርግ ጊዜ ከመሬት ላራሹ በተጨማሪ የግል የጦር መሳሪያ የነበራቸው ሰዎች ለመንግስት እንዲያስረክቡ መደረጉ ይታወሳል። ይህን ታሪክ ነው አርኬ 261 የሚያስታውሰው። «ባላገር» ማለት የአካባቢው ሰው፣ የአገሬው ሰው ማለት ነው። መንግስት ትጥቅ ማስፈታቱን የአገሬው ሰው የደገፈው ይመስላል። «እንኳን ሰጠሀቸው ...» የሚለው ይህን ያመለክታል። ነገር ግን የመጨረሻውን ስንኝ ስናነብ ወይም ስናዳምጥ አርኬው ተቃውሞ ያለበት መሆኑን እንረዳለን። «ሀርሞ» ቁመታቸው ረጃጅም ና ቀንዳም ከብቶች ማለት ነው። መርጦ ማርባትን የሚጠይቅ

ስለሆነ በቀላሉ አይገኙም ወይም አይራቡም። «ሞይዘር» የመሳሪያ አይነት ሲሆን በወቅቱ ለመግዛት ከፍተኛ ገንዘብ ያወጣ ስለነበር ገዝተው መያዝ የሚችሉት ሀብታሞች ብቻ ነበሩ። ስለዚህ ሁለቱም በቀላሉ የማይገኙ ስለነበሩ ለመንግስት ማስረከብ ተገቢ አልነበረም፣ እንቢ ማለት ያስፈልግ ነበር የሚል ነው።

የመንቶ 262 መነሻ ሀሳብ ከልብስ ጋር ተያይዞ ነው። ከኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ (ኢሰፓ) ምስረታ በኋላ የፓርቲው መሪዎችና አባላት የተለያየ መልክ የነበረው የካኪ ልብስ እያሰፉ እንዲለብሱ ይታዘዝ ነበር። የካኪ ልብስ እንደ ሱፍ ልብስ ተመራጭ ስላልሆነ አይወደድም ማለት ቢቻልም፣ የለበሱት ሰዎች በወቅቱ ይፈሩና ይከበሩበት ነበር። በሚዝናኑበት ቦታ የተሻለ ምግብና መጠጥ ይቀርብላቸው ነበር ይባላል። ስለዚህ መንቶው «ካኪ የምትለብሱት ለይስሙላ ነው እንጂ ኑሮአችሁ የተደላደለና ምቾት ያለው ነው» የሚል ሀሳብ የተላለፈበት ነው። ቀጥሎ ያሉት በኢህአዲግ ዘመን የታዩትን ሁኔታዎች የሚያመለክቱ ትዝብታዊ ቃልግጥሞች ናቸው። እነዚህ ቃልግጥሞች በየጊዜው የሚታየውን ሁኔታ በታዛቢ አይን ተመልክቶ አስተያየት እንደ መስጠት የሚቆጠሩ ማህበረ-ፖለቲካዊ ግጥሞች ናቸው።

መንቶ 263 በኖሩበት አገር በተንሸራሸሩት
እንደ አህያ ታስረው ከተማውን ዞሩት
መንቶ 264 ሲወዱ አማርኛ ሲጠሉ ትግርኛ
እንዲህ ያሉ ናቸው የኢህአዲግ ዳኛ
መንቶ 265 አህያ መጣች ተጭና ቋንጣ
ዘጠና ሰባት ነገር አመጣ
መንቶ 266 ከጉድጓድ ስፍራ ይበቅላል ደደሆ
የፈራነው ነገር መጣ ድሆ ድሆ
መንቶ 267 ጭቃና ምስለኔ ይባል ነበር ድሮ
አመራር ካቢኔ ሆነ ተቀይሮ

በ1982 ዓ.ም የደርግ መንግስት የሰሜን ወሎን ሰሜናዊ አካባቢዎች እየለቀቀ ወደ ደቡብ ወሎ አፈግፍጎ ነበር። በዚህ ጊዜ በኢህአዲግ ወታደሮች በተያዙት አካባቢዎች የነበሩትን የመንግስት ባለስልጣናትንና የፓርቲ አባላትን እዬዙ ህዝብ ፊት በማቅረብ እንዲገመገሙ ያደረጉ ነበር። መንቶ 263 «በኖሩበት አገር በተንሸራሸሩት» የሚለው ስንኝ እነዚህን ባለ ስልጣናት የሚመለከት ነው። እነዚህ ሰዎች እንደልባቸው እየተዝናኑ ኑረው ነበር። አሁን ግን ተዋረዱ፣

አፈሩ፣ የሚል ነው። ኢህአዲግ የተቆጣጠረው አካባቢ ነፃ መሬት (ሀራ መሬት) ይባል ስለነበር በነፃው መሬት የሚገኘውን ህዝብ «ክፍለ ህዝብ» የሚባሉት የኢህአዲግ ካድሬዎች በየቦታው እየሰበሰቡ ያወያያሉ፣ ያደራጃሉ። የመወያያ ቋንቋውም አማርኛ ነበር። በውይይቱ ላይ ከተሳታፊዎች መካከል ለመመለስ የማይመች አስቸጋሪ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፣ አወያዩ ቋንቋ ቀይሮ በትግርኛ መናገር ይጀምራል። ይህንን ሁኔታ በመታዘብ ነው መንቶ 264 የተፈጠረው።

«በለው በእስኪርቢቶ በማይታየው» በሚለው ስንኝ እንደተጠቀመው፣ ኢህአዲግን በምርጫ ውድድር እንታገለዋለን የሚል አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች እንደነበሩ፣ አሁንም እንዳሉ ይታወቃል። በምርጫው ሂደት ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ስጋት እንደነበር መንቶ 265 እና 266 ያመለክታሉ። «ዘጠና ሰባት ነገር አመጣ» የሚለው ስንኝ በወቅቱ የተፈጠረውን ችግር ይጠቁማል፤ በኢህአዲግና በተቃዋሚዎች መካከል የነበረውን ፍጥጫ ያስታውሳል። ከፍጥጫው በኋላ የተፈጠረውን ግጭት «የፈራነው ነገር መጣ ድሆ ድሆ» የሚለው ያረጋግጣል። «ድሆ» ማለት በአግባቡ፣ ቀስ እያለ ከቀን ወደ ቀን አመሉን እየለወጠ፣ ሰላማዊ ይመስል የነበረው፣ ወደ ፍጥጫና ወደ ግጭት እየተለወጠ መጣ ማለት ነው። መንቶ 267 የሚያመለክተው፣ «የስም ለውጥ እንጂ አዲስ ነገር አልመጣም» የሚል ነው። በፊውዳል ኢትዮጵያ ጊዜ ማህበረሰቡን ያስገብሩ የነበሩት ባለስልጣናት ጭቃ እና ምሰለኔ ይባሉ ነበር። አሁን ደግሞ፣ አመራርና ካቢኔ ይባላሉ። ሁኔታው ሲታይ፣ የስም ለውጥ እንጂ በተግባር ተመሳሳይነት አላቸው የሚል ነው።

ከዚህ በላይ በቀረበው ገለፃና ትንተና መረዳት እንደሚቻለው ትዝብታዊ ቃልግጥሞቹ፣ በደርግና በኢህአዲግ ስርዓቶች ለውጥ ምክንያት የነበሩትን ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ለማሳየት የሚችሉ የታሪክ ማስረጃዎች ናቸው። በአንድ በኩል ከስልጣን የተወገዱና፣ ወደ ስልጣን የወጡ ባለስልጣናት ተግባር፣ በሌላ በኩል የማህበረሰቡ አባላት አስተያየትና አመለካከት የተንፀባረቀባቸው ቃልግጥሞች ናቸው።

6.2.6.2 ሙስናንና አድሏዊ አሰራርን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

«ሙስና» ቀደም ባለው ጊዜ «ጉቦ» ይባል የነበረውን ቃል ተክቶ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ ቃል ነው። ሙስና ማለት አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ወይም ለመፈፀም በሚደረግ አስተዳደራዊ ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ ሰዎች ያለአግባብ ጥቅም የሚሰጡትና የሚቀበሉት የገንዘብ፣

የስጦታ፣ ወዘተ. ቅብብሎሽ ነው። አድሏዊ አሰራር ከሙስና ጋር በተያያዘም ይሁን በሌላ ምክንያት አንዱን ወገን መጥቀም ሌላውን መጉዳት ነው። በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ ከሙስና እና ከአድሎአዊ አሰራር ጋር ተያይዘው በደርግና በኢህአዲግ ስርዓቶች ላይ የተገጠሙትን ቃል ግጥሞች እንመለከታለን። መጀመሪያ ከደርግ ጋር፣ ቀጥሎ ከኢህዲግ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩትን እናያለን።

6.2.6.2.1 ከደርግ ጋር የተያያዙ ቃልግጥሞች

በዚህ ንዑስ ክፍል የምናያቸው ሙስና (ጉቦ) ከመቀበልና ከመስጠት፣ ከመሬት ክፍፍል (ድልድል) ሁኔታ ጋር እና፣ እንዲሁም ሰፊራን አስመልቶ፣ በተለያየ ጊዜያት የተገጠሙትን ቃልግጥሞች ነው።

መንቶ 268 የሃይሌን አቅማዳ መንጌ ቀዳዶታል
ሊቀመንበር ሰፍቶ ይጠቀምበታል
መንቶ 269 ሊቀመንበራችን ቃልቻ ነበረ
ባወንዱን እንደጫት ይቅመው ጀመረ
መንቶ 270 ሊቀመንበሩ ጅብ ፀሀፊው ቀበሮ
በድሃው ባድሜ ሰሩበት ቆርቆሮ
መንቶ 271 እኔ አላውቅበትም እንዲህ ያለ ነገር
የዝንጀሮ ሸንጎ የጅብ ሊቀመንበር

እነዚህ መንቶዎች ሙስናን (ጉቦን) የሚመለከቱ ናቸው። «ሀይሌና መንጌ» በሚሉት ቁልምጫዎች የተጠሩት፣ አፄ ሀይለ ስላሴ እና መንግስቱ ሀይለ ማሪያም ናቸው። «አቅማዳ» በአግባቡ የገንዘብ መሰብሰቢያ ማለት ሲሆን፣ ጥሬ ትርጉሙ ስልቻ፣ የእህል መያዣ፣ ወዘተ ነው። የመጀመሪያው መንቶ፣ የመጀመሪያ ስንኝ ሀሳብ፣ በሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የነበረውን የጉቦ ስርዓት መንግስቱ አጥፍቶታል እንደ ማለት ነው። ነገር ግን ሁለተኛውን ስንኝ ስንመለከት ጉቦ በመንግስቱ ጊዜም እንደ ነበር የሚያመለክት ነው። በደርግ ጊዜ የነበረው የስልጣን ማዕረግ፣ ሊቀ መንበር፣ ፀሐፊ፣ ፍርድ ሸንጎ፣ የመሳሰለው ነው። ምንም እንኳ በመንግስት ደረጃ እየታወቀ የሚወሰድ ጉቦ ባይኖርም፣ አንዳንድ ባለስልጣናት ይታመቡት ነበር። ሊቀመንበር ሰፍቶ ይጠቀምበታል የሚለው ይህን የሚያመለክት ነው። ሌሎቹም መንቶዎች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው። መንቶ 269 ጉቦን የገለፀበት መንገድ የተለየ

ነው። «ቃልቻ» የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሆነ ሰው ማለት ነው። በተለምዶ የሀይማኖቱ ተከታይ የሆኑ ትልልቅ ሰዎች (ቃልቻዎች፣ ሽሆች፣ ወዘተ.) ለፀሎት ጫት ይቅማሉ ይባላል። «ባውንድ» ማለት የብር ኖት ነው። ጉቦ የመቀበሉን ሁኔታ ከጫት መቃም ጋር አነፃፅሮ አቅርቦታል። ጫት መቃም በይፋ እንደማይከለከል ሁሉ፣ ጉቦ መቀበልም እንዲሁ ልማድ ሆኗል ማለት ነው።

የጉበኛነት ደረጃው ጎልቶ የሚታየው በመንቶ 270 ውስጥ ነው። በዚህ መንቶ ውስጥ «ጅብ» ና «ቀበሮ» ተጠቅሰዋል። «ጅብ» በዘይቤ ትርጉሙ «ሆዳም» ማለት ሲሆን «ቀበሮ» ደግሞ «ፈሪ» ነው። በእነዚህ አራዊት የተሰየሙት ሊቀ መንበሩና ፀሐፊው፣ ገንዘብ ከመቀበል አልፈው የድሀውን የከተማ ቦታ እየቀሙ የየራሳቸውን ቤት እንደሰሩበት ያመለክታል። ይህንን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ መንቶ 271 ላይ የተቃውሞ ሀሳብ ቀርቦ እናገኛለን። «እኔ አላውቅበትም ...» የሚለው ሀረግ «ጉቦኛ የሆኑ ባለስልጣናትን አታሳዩን ፣አትሹመብን፣» ወዘተ. የሚል ፍች ያለው ነው።

ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች ደግሞ አድሏዊ አሰራርን የሚያመለክቱትን እንመለከታለን። አድልኦ የሚሰራባቸው ጉዳዮች፣ የመሬት ክፍፍልና፣ የዚሁ ውጤት የሆነው ስደትና ሰፈራ ናቸው።

መንቶ 272 የደርጉ ተወካይ እንዴት እንዴት! ምንኛ ምንኛ
ጉድጓዴን ለእናንተ ገልባጤን ወደኛ
መንቶ 273 የኮሚቴ በሬ አይወጣም ዳገት
ዘመም ዘመም አለ ወደ ጉድጓዲት
መንቶ 274 ይሆነናል ብለን የመረጥነው ዳኛ
ጉድጓዲትን ለሱ ቦረቦሩን ለእኛ
መንቶ 275 ጉድጓዲት ደህና ሁኚ መቸም አላገኝሽ
ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተጠቃቀመብሽ

በአራቱ መንቶዎች ውስጥ ተደጋግሞ የመጣው ቃል «ጉድጓዲት» የሚለው ነው። ጉድጓዲት ማለት ከእርሻ መሬት ጋር የተያያዘ ሆኖ፣ ከፍተኛ ምርት ሊሰጥ የሚችል የለማ መሬት ማለት ነው። ውሃ መቋጠር ስለሚችል፣ በማሳው ላይ የሚዘራው ሰብል በፀሀይ የመጠቃት እድል አይኖረውም። በመሆኑም ከፍተኛ ምርት ይገኝበታል ማለት ነው። «ቦረቦርና ገልባጤ»

በሚሉት ቃላት የተጠቀሰው ሀሳብ ከመሬት አቀማመጥ ጋር የተያያዘ ነው። መሬቱ በጎርፍ የተሸረሸረ፣ ለምነት የሌለው፣ ውሃ መቋጠር የማይችል፣ ጭንጫና ምርት አልባ የሆነ የእርሻ መሬት ነው። ስለዚህ የጉድጓዲት ተቃራኒ ማለት ነው። ከመሬት ለአራሹ አዋጅ በኋላ፣ አርሶ አደሩ በገበሬ ማህበራትና በካድሬዎች አማካኝነት፣ ለእርሻ የሚሆን መሬት ይከፋፈል ነበር። በዚህ የክፍፍል ሂደት፣ ከሊቀ መንበሩ ጀምሮ እስከ ታች ያሉት የገበሬ ማህበራት ኮሚቴዎች፣ የተሻለውን መሬት ለግላቸው እየወሰዱ፣ ለሌላው አርሶ አደር፣ ምርታማ ባልሆነ ቦታ ላይ ይደለድሉ ነበር። ይህንን አድልኦዋዊ የመሬት ክፍፍል ነው መንቶዎቹ የሚያሳዩት። አገላለፃቸው አንዴ በመገረም፣ (እንዴት!እንዴት!) በማለት፣ ሌላ ጊዜ በቁጭት እና ተስፋ በመቁረጥ (ደህና ሁኚ፣ መቼም አላገኝሽ) ላይ የተመሰረተ ነው። አድልኦዋዊ አሰራሩ በኮሚቴዎች ላይ ብቻ የተመሰረተ አልነበረም። ከኮሚቴው አባላት ዘመድ ያላቸው ግለሰቦች የተሻለ የእርሻ መሬት ያገኙ እንደ ነበር የሚያመለክት ነው።

በጉቦና በአድሏዊ አሰራር የተማረረው አርሶ አደር፣ ከተፈጥሮ ድርቅ ጋር ተጨምሮ፣ እጣ ፈንታው የተወለደበትን ቀየ እየለቀቀ መሰደድ ነበር፤ የስደቱ አካል የነበረውም ሰፈራ ነው። ሰፈራን ከስደት የሚለየው በመንግስት የታገዘ መሆኑ ነው። የሚከተሉት መንቶዎች ይህን ያመለክታሉ።

መንቶ 276 ከሊቀ መንበሩ ዘመድ የሌለው ሰው
ሞፈሩን ቀንበሩን ሸረሪት ወረሰው
መንቶ 277 ወይ ከሊቀ መንበር፣ ወይ ከፍርድ ሸንጎ፣
ዘመድ የሌለው ሰው፣
ሰፈራ አይሄድም ወይ ምን አልከሰከሰው፤
መንቶ 278 በዚህ ባገራችን የሚሰራው ሥራ
መሬትን ለሀብታም ደሀን ለሰፈራ

የመጀመሪያው መንቶ፣ ተስፋ የቆረጠ የአርሶ አደር ድምፅ ነው። ይህ አርሶ አደር የሚያርሰው በቂ መሬት (እርሻ) በአድልኦ ምክንያት ስላልተሰጠው ያለ ስራ የሚያሳልፉበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ሁለተኛው ስንኝ ይህንን የሚያረጋግጥ ነው።መንቶ 277 እና 278 ከዚሁ ጋር የሚደጋገፍ ሀሳብ የተገለፀባቸው ናቸው። ደህና ደህና የሆነውን የእርሻ መሬት፣ በዘመድ አዝማድ እየተፈላለጉ ሌሎች ከተከፋፈሉት፣ የቀረበው አማራጭ መሰደድ እንደሆነ መንቶዎቹ ይገልፃሉ። ስደቱም ወደ ሌሎች አካባቢዎች ተጓጉዞ መስፈር ይሆናል ማለት ነው።

6.2.6.2.2 ከኢህአዴግ ጋር የተያያዙ ቃልግጥሞች

በደርግ ጊዜ ከተደረገው የመሬት ክፍፍል በኋላ ኢህአዲግ ነፃ መሬት በማለት ይቆጣጠራቸው በነበሩ አካባቢዎች ሁለተኛ የመሬት ክፍፍል አድርጓል። ይህ ተግባር ምናልባት ከአማራና ከትግራይ ክልሎች ውጭ በሌሎች ክልሎች የተደረገ አይመስልም። በመሆኑም የሚከተሉት ቃልግጥሞች በኢህአዲግ የአስተዳደር ጊዜያት በሰሜን ወሎ አካባቢዎች ለታዩት ሙስና እና አድሎአዊ አሰራሮችን የሚያመለክቱ ስለሆኑ ቀጥለን እንመለከታለን።

አርኬ 279 ባለ መቶ ፣መሬት ሞልቶ
ባለ አምሳ፣ጎድጓዲትን አንሳ
ባለ ሞሰብ ፣ኮሚቴው ይሰብሰብ
ባለ አምስት፣በዚህ ሳምንት
ባለ ወፍ፣በዚህ ይለፍ
አርኬ 80 የመቶ ብር ጉቦ እኔ አልበላም ብሎ
የአምሳ ብር ጉቦ እኔ አልበላም ብሎ
ዞብልን ነክረው ልጅ አወጣ ብሎ
መንቶ 281 ኮሚቴ ሲበላ የለውም ትንፋሽ
እንጀራው አለቀ ተልባው ሳይታሽ

እነዚህ ቃል ግጥሞች ከመሬት ክፍፍል ጋር የተያያዙ ናቸው አርኬ 279 ውስጥ ከመቶ ብር እስከ አንድ ብር ድረስ ያሉት የብር ኖቶች ተጠቅሰዋል። እነዚህ የብር ኖቶች ለጉቦ የሚሰጡ ናቸው። ከፍተኛውን የብር መጠን የሰጠ ሰው ከሚፈልገው አካባቢ የሚፈልገውን የእርሻ መሬት መውሰድ ይችላል። «ባለመቶ መሬት ሞልቶ» የሚለው ይህንን ያመለክታል። በየደረጃው በሚሰጠው የገንዘብ ልክ መሬት የማግኘት እድሉ የሚወሰን ይሆናል ማለት ነው። አርኬ 280 ላይ እስከአሁን ከቀረቡት ቃልግጥሞች የተለየ ሀሳብ የተገለፀበት ነው። በአርኬው የተጠቀሰው ሊቀ መንበር ከሙስና (ከጉቦ) ነፃ ነው ማለት ቢቻልም፣ ከአድሏዊ አሰራር ነፃ አይደለም። የአርኬው የመጨረሻ ስንኝ ይህን ያመለክታል። «ዞብልን ነክረው ልጅ አወጣ ብሎ» የሚለው፣ በወቅቱ ሊቀ መንበር የነበረው ግለሰብ፣ የዞብል አካባቢ ተወላጅ የነበረ ነው። ይህ ሰው፣ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ ኢህአዴግ የሰሜን ወሎን አካባቢዎች ሲቆጣጠር የገበሬ ማህበር ሊቀ መንበር ወይም የመሬት ክፍፍል ኃላፊ ሆኖ ድልድሉን ያካሂድ የነበረ ነው።

በመሆኑም ከተፈቀደው የመሬት መጠን፣ በልዩ ልዩ ምክንያት፣ እያስበለጠ ለግለሰቦች ይሰጥ እንደ ነበር «ዞብልን ነከረው» የሚለው ሀረግ ያረጋግጣል። የመጨረሻው መንቶ የሙስና (የጉቦ) አፈፃፀሙ የረቀቀና ፈጣን መሆኑን ያሳያል። «ኮሚቴ ሲበላ ...» የሚለው ሀረግ «የኮሚቴ አባላቶች ምግብ ሲመገቡ ድምፃቸው አይሰማም» የሚል ፍች ቢኖረውም፣ በአግባቡ ሙስና (ጉቦ) ሲቀበሉ አይታዩም ማለት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ደግሞ ከመልካም አስተዳደር ጋር በተያያዘ ሁኔታ የነበረውን አድሏዊ አሰራር የሚያሳዩ ቃልግጥሞች ናቸው።

አርኬ 282 ሊቀመንበር የኛ
ስራ አስኪያጁ የኛ
አመራሩ የኛ
አድበህ ተቀመጥ እንግዲህ ምቀኛ
አርኬ 283 ቀበሌ ብከስም ኸወረዳው ላከኝ
ወረዳ ብከስም ወደ ዞኑ ላከኝ
ዞኑንም ብጠይቅ ወደ ክልል ላከኝ
አርፌ ልቀመጥ ውቃቢ ሳይርቀኝ

እነዚህ አርኬዎች እንደሚያመለክቱት ቃልግጥሞቹ የተፈጠሩት በተለያየ ጎራ ወይም ቡድን በተሰለፉ ሰዎች ይመስላል። አንደኛው በኢህአዴግ ደጋፊዎች፣ ሁለተኛው ደግሞ በተቃዋሚዎች ነው። በመጀመሪያው አርኬ ውስጥ ሁሉም ነገር የኛ ነው፤ የትም ብትሄድ ምንም ለውጥ አታመጣም፤ አርፈህ ተቀመጥ! የሚል የማስጠንቀቂያ መልክት ያለው ነው። ሁለተኛው አርኬ የሚያመለክተውም በመንግስት የስልጣን መዋቅር ከቀበሌ እስከ ክልል ባሉት የስልጣን እርከኖች ውስጥ ያሉት ባለስልጣኖች በአድልኦ የሚሰሩ በመሆኑ፣ ችግር የሚፈጥሩ እንጂ መፍትሄ የሚሰጡ አይደሉም ማለት ነው። «አርፌ ልቀመጥ ውቃቢ ሳይርቀኝ» የሚለው ስንኝ፣ «ተጨማሪ ችግር ሳይደርስብኝ፣ አቤቱታዬን ማቆም አለብኝ፣ ያለፈው ይበቃኛል» የሚል ነው።

በአጠቃላይ ሙስና (ጉቦ) እና አድልኦአዊ አሰራሮች በየትኛውም ስርዓት ሊታዩ የሚችሉ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች እንደሆኑ ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት ይቻላል። እንዲህ አይነቱ ማህበራዊ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ችግር ባለበት ሁኔታ አካባቢያዊም ሆነ አገራዊ

ልማትና እድገት ማምጣት አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም አስፈላጊውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን ለመፈለግ ለሚሹ አካላት ከቃል ግጥሞቹ የመነሻ ሀሳቦች ሊያገኙ ስለሚችሉ ቃልግጥሞቹን እንደ አንድ ማሳያ በመጠቀም ችግሩን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ እንደ ግባት ያግዛሉ ማለት ነው።

6.2.6.3 ጥርጣሬንና ስጋትን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

መጠራጠር ማለት በአንድ ጉዳይ ላይ እርግጠኛ አለመሆን ማለት ነው። እንዲህ አይነት ስሜት ሊፈጠር የሚችለው በራስ ካለመተማመንና ሌሎችን ከመፍራት አንፃር ይሆናል። ስጋት ማለት ፍርሀትና ጭንቀት ሲሆን፣ መነሻውም ወደፊት ሊደርስብኝ ይችላል ከሚል ችግር ጋር የሚያያዝ ነው። ጥርጣሬና ስጋት ማህበራዊ ችግሮች ናቸው። የነዚህ ችግሮች መነሻ ምክንያቶች ከሚሆኑት መካከል ምላሰኝነት፣ ሌብነት፣ ውሸታምነት፣ የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ «ምላሰኝነት» እንዴት እንደቀረበ እንመለከታለን።

መንቶ 284 ዛሬ ዘበንማ የተወደደው
አዲስ አማችና ምላሰኛ ነው
መንቶ 285 እሸኝሽ ነበረ እቤትሽ ድረስ
አዲያ ምን ያረጋል በዛሬው ምላስ
አርኬ 286 አተር እንዳይዘራ ዋጉ መከራ ነው
ጤፍም እንዳይዘራ አረሙ ጣጣ ነው
እስቲ ተልባ ዝሩ የማላጋ ቀን ነው
መንቶ 287 ገበያ ብገባ አጣሁ ደህና በሬ
ጥጃውን ግዛና ውስ በል አገሬ
መንቶ 288 አሸከሩ አሾክሿኪ ጌታው ምላስ ሰሚ
ልውጣ ከሀገሬ አልሆንኩም ከራሚ

በዚህ አጠቃቀም «ምላሰኛነት» ማለት በሰዎች ወይም በቡድኖች መካከል በሚኖር ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ፣ የሆነ ያልሆነውን ወሬ በማመላለስ፣ በሰዎች መካከል ጤናማና ሰላማዊ ግንኙነት እንዳይኖር፣ ጥርጣሬና ስጋት፣ የሚፈጥር ተግባር ነው። ምላሰኛ ማለት፣ ነገር አሳባቂ፣ ወሬ አመላላሽ፣ ማለትም ይሆናል። በቃልግጥሞቹ ውስጥ እንደሚታየው፣ ቃሉ

በተለያየ መጠሪያ ተጠቅሷል። እነሱም፣ «ውስ በል፣ አሾክሿኪ፣ የማላጋ ቀን» የሚሉት ናቸው። እነዚህ ቃልግጥሞች፣ እንደየዘመኑ ለሚታዩ ማህበራዊ ችግሮች፣ ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ከአንድ ዘመን ወይም ስርዓት ጋር ብቻ የሚያያዙ አይደሉም ማለት ነው።

በመጀመሪያው መንቶ «ምላሰኛነት» ተነሳፅሮ የቀረበው ከአዲስ አማች ጋር ነው ። በማህበራዊና በቤተሰባዊ ግንኙነት ውስጥ፣ አዲስ አማች ማለት፣ በቅርቡ በጋብቻ የተዛመደ ሰው ማለት ነው። ይህ ሰው የተለየ አክብሮት ይሰጠዋል፣ በየበአላቱና በየአጋጣሚው ከሚስቱ ጋር ምላሽ እየተጠራ ይበላል፣ ይጠጣል። በመጀመሪያው ስንኝ «ዛሬ ዘበንማ ...” የሚለው ሀረግ ፍቺው «አሁን ባለንበት ጊዜ» ማለት ነው። ይህ አጠቃቀም በተለያየ ዘመን ሊያገለግል የሚችል ነው። የመንቶው ሀሳብ፣ አሁን ባለንበት ጊዜ፣ «ወሬ የሚያመላልሱ ሰዎች ተቀባይነት አላቸው» የሚል ነው። ይህንን ሁኔታ ሊያረጋግጥ የሚችል ሀሳብ በሁለተኛው መንቶ «... በዛሬው ምላስ» በሚለው ሀረግ ተጠቅሶ እናገኛለን። መንቶው በሁለት ተፋቃሪዎች መካከል ያለውን ድብቅ የፍቅር ግንኙነት የሚመለከት ቢሆንም፣ ጊዜው አስቸጋሪ እንደሆነ የሚጠቁም ነው። በተለምዶ ምላሰኛ ናቸው የሚባሉ ሰዎች፣ ራሳቸውን ችለው ሰርተው ለመኖር የሚቸገሩ ናቸው ይባላል። ኑሮአቸው ወሬ በማመላስ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ሰዎች አሉ ማለት ነው።

አርኬ 286. ይህንን የሚያመለክት ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስንኞች ሰርቶ መኖር አስቸጋሪ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። የአርኬው ሀሳብ፣ በመጨረሻው ስንኝ የተገለፀው ነው። «የማላጋ ቀን» ማለት በዚህ አገባብ፣ «የማይጨበጥ፣ የማይታመንና የማይታወቅ ጊዜ» እንደማለት ሲሆን፣ ፍቺውም «የዘመኑ ሰው አይታመንም፣ ውሸታም ነው» ማለት ይሆናል። በመንቶ 287 ምላሰኛነት የተገለፀበት መንገድ ከጥጃ ጋር በማመሳሰል ነው። «ደህና በሬ» ማለት ለእርሻ የሚሆን ጠንካራ በሬ ማለት ሲሆን፣ በውክልና ፍቺው፣ ደህና ሰው፤ ትልቅ ሰው ማለት ነው። «ጥጃ» ለማረስ ያልደረሰ ገና ትንሽ ወይፈን ማለት ነው። የመንቶው ሀሳብ «ለእርሻ የሚሆን ጎበዝ በሬ ስላልተገኘ፣ ለጊዜው በወይፈን ማረስ አስፈላጊ ነው፤» የሚል ይመስላል። ነገር ግን «ውስ በል» የሚለው ሀረግ ፍቺው ሁለት ነው። አንደኛው ጥጃውን ስታርስ ውስ እያልክ ይሆናል ነው። ሁለተኛው ደግሞ «ነገር ሹክ እያልክ፣ ነገር እያቀበልክ»፣ ወዘተ. ማለት ነው። የመጨረሻው መንቶ፣ በምላሰኞች የተማረረ ግለሰብ ድምጽ የተሰማበት ነው። «ከላይም ከታችም ያለው ሁሉ፣ ነገር አመላላሽና፣ ነገር ተቀባይ ስለሆነ፣ ችግር ሳይደርስብኝ አገር ለቅቄ ልሰደድ» የሚል ነው። በአጠቃላይ ምላሰኝነት

ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግር ስለሆነ ሰዎች ሊጠሉትና ሊርቁት የሚገባ ተግባር ነው።

6.2.6.4 የእርስ በርስ ጦርነትና ታሪካዊ ሁኔታዎችን የሚያስታውሱ ቃልግጥሞች

የእርስ በርስ ጦርነት (civil war) ኢትዮጵያውያን በተለያየ ምክንያት ወደ ግጭት ገብተው፣ ጎራ ለይተው፣ ያደርጉት የነበረውን ጦርነት የሚመለከት ነው። በምዕራፍ ሁለት ባለው ዳራ ውስጥ በሰፊው እንደተገለፀው፣ የእርስ በርስ ጦርነት ታሪካችን ከአፄ ቴዎድሮስ በፊትና በኋላ ጀምሮ የነበረው ነው። ከአፄ ቴዎድሮስ በኋላ ያለው የእርስ በርስ ጦርነት ይካሄድ የነበረው፣ በመንግስትና (በንጉስ ነገስቱ) በሌሎች ሀይሎች መካከል ነበር። ይህ የእርስ በርስ የጦርነት ታሪክ፣ እስከ አፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ድረስ የዘለቀና አሁንም ድረስ የቀጠለ የታሪካችን አንድ ገፅታ ይመስላል። ከአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት በኋላ፣ አብዮቱን ተከትሎ በተፈጠሩት ልዩ ልዩ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል፣ በነበረ የፖለቲካ ልዩነት ምክንያት፣ ኢትዮጵያዊያን በግጭት ውስጥ ገብተው እንደነበር ይታወሳል። በተለይ በደርግና በሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ግጭት የአገሪቱን አንድ ትውልድ ዜጋና ኢኮኖሚ በእጅጉ የጎዳ ነበር። ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በሚቀርበው ገለፃና ትንተና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ይንቀሳቀሱ በነበሩበት ሀይሎችና በደርግ መካከል የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ የሚያሳዩ እንዲሁም ከአፄ ዮሐንስ እስከ ከአፄ ሀይለስላሴ ድረስ ባሉት የታሪክ ዘመናት ውስጥ የታዩትን ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚያስታውሱ ቃልግጥሞችን እንመለከታለን።

6.2.6.4.1 በደርግና በኢህአዴግ መካከል የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

አብዮቱን ተከትሎ በመጣው የደርግ መንግስት ላይ የተለያዩ ሀይሎች ተቃውሞ በማንሳት ወደ ግጭት ገብተው እንደነበር ይታወሳል። በተለይ ረጅም ጊዜ የፈጀውና የመንግስት ለውጥ ያስከተለው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረው ግጭት ነው። በመሆኑም በደርግና በኢህአዴግ የተደረገው የእርስ በእርስ ጦርነት ዋናው እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይህን የጦርነት ታሪክ የሚያመለክቱ ቃል ግጥሞችን እንመለከታለን።

6.2.6.4.1.1 ደርግን የሚደግፉና የሚቃወሙ ቃል ግጥሞች

በደርግ ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ መንግስት ሰራዊት፣ በሰሜኑ የሀገራችን ልዩ ልዩ አካባቢዎች እየተዘዋወረ ያካሂድ የነበረውን ውጊያና ጦርነት፣ በጦርነቱ ጊዜ ይታዩ የነበሩትን

አንዳንድ ሁኔታዎች አስመልክቶ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ በቃል ግጥሞቹ አማካኝነት ድጋፍና ተቃውሞውን ለማንፀባረቅ ችሏል። የሚከተሉት ቃልግጥሞች ይህን የሚያረጋግጡ ናቸው። መጀመሪያ በድጋፍ መልክ የተነገሩትን ካየን በኋላ፣ ቀጥሎ ደግሞ የተቃውሞ ሀሳብ የተገለፀባቸውን እንመለከታለን።

መንቶ 289 ተሀት ብላ ነበር አላ ነው ድንበሬ
እንቢ አለ ሚሊሻው ተጠምዶ እንደበሬ
እንቢ አለ እንጂ ደርጉ ተጠምዶ እንደ በሬ
መንቶ 290 የደርጉ ወታደር ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ተሀት ገደል ገባይ ዝንጆሮ ይመስል
መንቶ 291 ስድስተኛ ብርጌድ ኸደ ኸሚሉኝ
በኬሻ ጠቅልለው ሆርማት ይጣሉኝ

የመጀመሪያዎቹ መንቶዎች የኢህአዴግ ድርጅት ከመፈጠሩ በፊት (ትህሀተ) (የትግራይ ህዝብ ሀርነት ተጋዳላይ) በሚል መጠሪያ ይታወቅ ከነበረው ቡድን ጋር የነበረውን ጦርነት የሚያስታውሱ ናቸው። በዚያን ጊዜ፣ ወደ ሰሜን ወሎ አካባቢዎች እየገቡ ለመዋጋት እንደ ምክንያት ያቀርቡት የነበረው «ከአላ ውሃ ወዲህ ያለው አካባቢ በሙሉ የትግራይ ክልል ነው» የሚል ነበር። «አላ ውሃ» የሚባለው ወንዝ የሚገኘው በየጁና በራያ ቆቦ ድንበር ላይ ነው። ይህ ወንዝ አሁንም ድረስ የየጁና የራያ ቆቦ ድንበር ሆኖ የሚያገለግል ነው። በወቅቱ የአካባቢው ሚሊሻ የሚባል የቀበሌ ታጣቂዎች ከተወሰኑ መደበኛ ወታደሮች ጋር በመሆን ትህሀትን ይከላከሉ ነበር። ብዙ ጊዜ ውጊያ የሚደረገው በሌሊት ነበር። የትህሀተ ተዋጊዎች፣ ሌሊት ወደ ከተማ ይመጣሉ፣ ማጥቃት የሚፈልጉትን አጥቅተው ወዲውኑ ሌሊት ይመለሳሉ። ይህ ስልት ከነበራቸው የታጠቀ የሰው ሀይል አንፃር፣ የጠቀማቸው ይመስላል። ከመንግስት ጦር ጋር በቀን ሲገናኙ የማጥቃት እድሉ ወደ መንግስት ጦር ስለሚያጋድል አፈግፍገው ይመለሳሉ። ይህንን ለመግለጽ ነው ‹‹...ተጠምዶ እንደ በሬ›› እና «ትህሀተ ገደል ገባይ ...» የሚሉት ሀረጎች የተጠቀሱት።

መንቶ 291 ግን የኢህአዴግን አሸናፊነት ወይም የጦሩን መንቀሳቀስ የሚያመለክት ነው። በቆቦ አካባቢ ሰፍሮ ከነበረው የመንግስት ጦር አንዱ «ስድስተኛ ማካናይ ዝድብ ርጌድ» እየተባለ የሚጠራው ነው። ይህ ጦር፣ በወጣት የተገነባና፣ ከባድ መሳሪያ (ታንክና ዙ-23) የታጠቀ ስለነበር በአካባቢው፣ ስሙ ገናና ነበር። የጦሩ አባላት (ወታደሮች) በእረፍት

ጊዚያቸው፣ ከተማ እየገቡ፣ እንደማንኛውም ሰው፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ማህበራዊ ግንኙነት ያደርጉ ነበር። ከማህበረሰቡ ጋር መልካም የሚባል ግንኙነት ጦሩ ነበረው ማለት ይቻላል። በመሆኑም መንቶው፣ አንድም ይህ ጦር ከዚያ አካባቢ ተነስቶ ወደ ሌላ አካባቢ እንዲሰፍር መደረጉን፣ አንድም በኢህአዴግ ጦር ተሸንፎ አካባቢውን መልቀቁን የሚያመለክት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ፣የደርግን ወታደር የሚመለከቱ የተቃውሞ ቃልግጥሞችን እንመለከታለን። ቃልግጥሞች የሰራዊቱን የአመጋገብ ሁኔታና በውጊያ መሸነፉን የሚያሳዩ ናቸው።

መንቶ 292 በመወደልማ ከሆነ ነገሩ
እነ በሬ ጎርድም ማይክሮፍ ነበሩ
መንቶ 293 አስራ ሁለት ዶሮ ይዘህ በሆድህ
ያቺ ጎበዝ መጣይ ሊታይ ነው ጉድህ
መንቶ 294 የደርጉ ወታደር ቂጠ ዝርንቡጡ
ሴቶች ይወዱታል ማር አለው ኸቂጡ
መንቶ 295 የማነው ክላሽን የበሰበሰው
የደርጉ ይሆናል ጥሎት የሸሸው
መንቶ 296 እንዲህ በስተሸዋ ነጭ በሬ አገሳ
ተጫነ መሰለኝ ያነ አህያ ፈሳ
መንቶ 297 መንጌ ሀይለማሪያም የወለቱ ልጅ
እህቱን ገደላት በሊኮፕተር ፈንጂ

«ማይክሮዊቭ» የሚባለው የመገናኛ ተቋም ከቆቦ ከተማ በስተምስራቅ በኩል ይገኝ እንደነበር ከዚህ በፊት ተገልጿል። ይህ ተቋም ዙሪያውን በሸቦ ታጥሮ ፈንጅ ተቀብሮበት፣ በወታደር ይጠበቅ ነበር። እነዚህ ወታደሮች በየሳምንቱ በሬ እየታረደ ሥጋ እንደልብ ይበሉ ስለነበር፣ «እነበሬ ጎርድም ...» የሚለው ሀርግ ይህን የሚያመለክት ነው። «መጎርደም» በአገባቡ ብዙ መብላት፣ በአንድ ጊዜ መጨረስ፣ ማለት ነው። በመሆኑም፣ ሰራዊቱ በሬ እየታረደ ይቀለብ እንደነበር ለማሳየት ነው ይህንን የተጠቀመው። መንቶ 293ም ከሰራዊቱ አመጋገብ ጋር የተያያዘ ነው። የዶሮ ስጋ አስራ ሁለት ብልት አለው። «አስራ ሁለት ዶሮ...» የሚለው ይህንን ለማመልከት ነው። ስንኙ ከበሬ ስጋ በተጨማሪ ሰራዊቱ፣ የዶሮ ስጋ፣ ይመገብ እንደ ነበር ለማመልከት ነው። እዚህ ላይ አንድ ሀሳብ በተጨማሪ የተጠቆመ ይመስላል። ከሰራዊቱ

አባላት አንዳንዶቹ ከተማ ውስጥ ውሽማ (ቅምጥ) ነበራቸው። እነዚህ ቅምጦች ውሽሞቻቸው ሲመጡ ዶሮ ይሰራሉ፤ ይበላሉ፤ ይጠጣሉ።

በሁለቱም መንቶዎች የተነሳው የተቃውሞ ሀሳብ «በውፍረት ቢሆን የደርግ ወታደር ወፍራም ነው፣ የኢህአዴግ ወታደሮች ቀጫጭን ቢሆኑም፣ ጀግኖች ናቸው፣ በውጊያ ይበልጣሉ፣» የሚል ነው። «ያቺ ጎበዝ ...» የሚለው የኢህአዴግን ወታደር ነው። አንዳንድ የደርግ ወታደሮች አካላዊ ውፍረት የነበራቸውና በከተማው ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች ጋር የፍቅር ግንኙነት ያደረጉ እንደነበር መንቶ 294 ይጠቁማል። የመንቶው ሀሳብ «ማጣጣል» ነው። የዚህ መገለጫ የሆኑት አባባሎች «ዝርንቡጥና ማር አለው» የሚሉት ቃላት ናቸው። ዝርንቡጥ ማለት በጣም ወፍራም፣ በተለይ መቀመጫው ላይ ውፍረት የበዛበት እንደ ማለት ነው፤ የተቃውሞው ሀሳብ «እንዲህ አይነት አካላዊ ውፍረት ያለው ወንድ ለውትድርና ወይም ለውጊያ አይሆንም» ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።

በ1982 ዓ.ም መግቢያ ላይ በሰሜን ወሎ አካባቢዎች የኢህዴግ ጦር መጠነ ሰፊ ውጊያ አካሂዶ ነበር። ለሰባት ቀን ያህል የፈጀ ጦርነት በነሀሴ ወር 1982 ዓ.ም ተደርጎ እንደነበር አጥኚው ያስታውሳል። በዚህ ጦርነት ከሁለቱም ወገን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተዋጊ አልቋል። ታንኮችና ተሽከርካሪዎች በየቦታው ተቃጥለዋል። የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎች በየቦታው ተጥለው ተገኝተዋል። መንቶ 295 ይህንን የሚያመለክት ነው፤ የአካባቢው ሰው ይህንን መሳሪያ በልዩ ልዩ መንገድ እያገኘ የግሉ አድርጎት ነበር። የጥናቱ አቅራቢ በወቅቱ በአካባቢው ከነበሩት ጓደኞቹና ከቤተሰቦቹ እንደሰማው፣ «ሰራዊቱ ከተከበበት ሰብሮ ለመውጣት ባደረገው ትንቅንቅ፣ ጉዳት ደርሶበታል፣ መሳሪያውን በየቦታው እየጣለ፣ የአካባቢውን ባህላዊ አልባሳት እየለበሰ፣ ወደ ደቡብ ወሎ አፈግፍጓል።» የኢህአዴግ ወታደሮች ወይም ካድሬዎች አካባቢውን በመቆጣጠር ህዝቡን ያረጋጉ ነበር። የተቃውሞው ስሜት «ወድቆ የሚገኘው መሳሪያ ሁሉ የደርግ ወታደር እንጂ የኢህአዴግ አይደለም» የሚል ነው።

ከዚህ ጦርነት በኋላ መንግስት በአካባቢው ያደርግ የነበረው እንቅስቃሴ፣ ባልታሰበ ሰዓት አውሮፕላን እየላከ የኢህአዴግ ወታደሮች ይገኙበታል የሚባለውን ቦታ በቦንብ መምታትና የቅስቀሳ ወረቀት (ፋፍሌት) መበተን ነበር። መንቶ 296 እና 297 ከአውሮፕላን ድብደባ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የነበረውን አስፈሪ ጊዜ የሚያመለክቱ ናቸው። «እንዲህ በስተሽ ነጭ በሬ አገሳ» የሚለው ስንኝ የጦር አውሮፕላን (ጀትና ሄሊኮፕተር) የሚጣል ቦንብ ተጭኖ በመንዝ ላይ መሆኑን የሚጠቁም ነው። «ነጭ በሬ አገሳ» የሚለው ሀረግ ፍችው «የአውሮፕላን ድምፅ

ተሰማ ቦንብ ሊጣል ነው» ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ በድንገት በሚጣለው ቦንብ የአካባቢው ሰላማዊ ሰዎችና እንስሳት ጉዳት ይደርስባቸው ነበር። በእነዚህ ሁለት መንቶዎች ውስጥ «ፀያፍ» ትርጉም ያላቸው ቃላት አሉ። እነዚህ ቃላት ከደርግ ጋር የተያያዙ ናቸው። እነዚህ ፀያፍ ቃላት በወቅቱ የነበረውን የተቃውሞ ስሜትና ንቀት የሚያመለክቱ ናቸው።

6.2.6.4.1.2 ኢህአዴግን የሚደግፉ ቃልግጥሞች

በእርስ በርስ ጦርነቱ ጊዜ የነበረውን ወታደራዊ አሰላለፍና ውጊያ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ በቃል ግጥሞች አማካኝነት ገልያታል።የሚከተሉት መንቶዎች የኢህአዴግ ወታደሮችን በመደገፍ የተገጠሙ ናቸው።

መንቶ 298 የኢህአዴግ እናት የመነመነችው
በርበራውን ወልዳ ደርጉ አስፈጀችው
መንቶ 299 ሰዎቹ ቀጫጭን ከመጡበት እንጃ
በየወንዙ ጣሉት የደርጉን ውርንጫ
መንቶ 300 በነቢላ በኩል አህያና በሬ፣ሊጋጠም ሲያገሳ፣ሲያገሳ
መሸሹ ነው መሰል ያነ አህያ ፈሳ
መንቶ 301 የወያኔ ጥይት ባለ ሁለት ጆሮ
ደርጉን አደረገው የሜዳ ዝንጆሮ
መንቶ 302 እነሱ ቀጫጭን ስማቸው ቅማላም
የደርጉን ወታደር ነዳችው እንደ ላም
መንቶ 303 የኢህአዴግ ወታደር ስንት ነው ልባቸው
መቶውን ወታደር ሁለቱ ነዲቸው

መንቶ 298 እና 299 በደርግና በኢህአዴግ ተዋጊዎች መካከል ከነበረው ውጊያ ምክንያት የተፈጠሩ ቃልግጥሞች ናቸው። የመንቶዎቹ ሀሳቦች የኢህአዴግ ወታደሮች የደርግን ወታደር በውጊያ እያሸነፉ ወይም የበላይነትን እየያዙ የደርግ ወታደር ደግሞ እየተሸነፈ እንደመጣ የሚያመለክቱ ናቸው። በእርስ በርስ ጦርነቱ ጊዜ (አመታት) ይባል እንደነበረው የኢህአዴግ ወታደሮች በተክሉ ሰውነታቸው ቀጫጭን፣ በውጊያ ብቃት ግን ሀይለኛ እንደነበሩ ነው። ይህ አካላዊ ሁኔታ ከቤተሰብ በዘር የተወረሰ እስኪመስል ድረስ በቃል ግጥሞች ተገልጿል። «የኢህአዴግ እናት የመነመነችው» የሚለው ስንኝ ይህን የሚያረጋግጥ ነው። “በርበራ” የሚለው ቃል ለምግብ ቅመም ከመሆኑ በተጨማሪ በዘይቤያዊ ፍቺው አካላዊ ቅጥነትን፣

ባህሪያዊ ሀያልነትን ያመለክታል። «በርበሬውን ወልዳ ደርጉን አስፈጀችው» በሚለው ስንኝ ውስጥ አስፈጀችው ማለት ከበርበሬው አንባር ሲታይ መለብለብን፣ ማቃጠልን፣ የሚመለከት ነው። ከውጊያው አንባር ደግሞ «አስጨረሰቺው፣ አስደመሰሰችው፣» ወዘተ. ማለት ነው። ይህ የሰውነት አቋም፣ እንደ ጀግንነት መገለጫ እየተወሰደ፣ ለደርግ ወታደር መሸነፍ እንደ ምክንያት እየተጠቀሰ፣ ቃልግጥም ተፈጥሮበታል። መንቶዎቹ በሁለቱ መካከል ለተደረጉ ውጊያዎች የበላይነቱ የኢህአዴግ ወታደር እንደ ነበር የሚያሳዩ የድጋፍ ቃልግጥሞች ናቸው።

ከመንቶ 300-303 ባሉት ቃልግጥሞች የተንፀባረቀው ሀሳብ የደርግ ወታደር በውጊያ እየተሸነፈ የኢህአዴግ ወታደር እያሸነፈ የመጣበትን ሂደት የሚያመለክት ነው። መንቶ 300 የነበረውን ፍጥጫ ያሳያል። የውጊያ ፍጥጫው ወደ መታኮስ ሳይሸጋገር በደርግ ወታደር «መሸሽ» ምክንያት ሲቋረጥ ለኢህአዴግ ብርታት እየሰጠ እንደነበር ነው። በተለይ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ይታይ የነበረው ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት የጦርነት አመታት ነበር። ኢህአዴግ በዚህ መጣች! በዚህ ታየች! በተባለ ቁጥር፣ የደርግ ወታደር የነበረበትን ቦታ በትዛዝ እየለቀቀ፣ እንዲያፈገፍግ ይደረግ የነበረ መሆኑን የሚያስታውስ ነው። በመንቶዎቹ ውስጥ «አህያ» እና «በሬ» የሚሉት ቃላት አሉ። እነዚህ ቃላት በሁለቱ ሀይሎች የሚወክሉ ናቸው። «አህያ» የደርግን ሲሆን «በሬ» የኢህአዴግ ነው።የማሸነፍ ምልክቱና ውጤቱ ቀጥሎ ባሉት አባባሎች ተንፀባርቋል። «የሜዳ ዝንጆሮ፣ እንደላም መነዳት፣ ሁለቱ ነዲቸው፣» የሚሉት ቃላት የያዙት ፅንሰ ሀሳብ መሸነፍን የሚያመለክት ነው። ዝንጆሮ ሜዳ ላይ መሮጥ አይመቸውም ይባላል። ስለዚህ ሸሽቶ ማምለጥ አይችልም ማለት ነው። የመንቶዎቹ ሀሳብም የደርግ ወታደር በየሜዳው ተበታትኖ ለጥቃት እንደተጋለጠ የሚያሳይ ነው።

የኢህአዴግን ወታደሮች ከደርግ ወታደሮች አንባር ሲታዩ አካላቸው ጎስቋላና ቀጫጫ፣ ፀጉራቸው ጎፈሬና ተባይ አለበት፣ ይባል ስለነበር «ቅማላም» በሚል ቅጥያ ስድብ የሚጠሏቸው ሰዎች ነበሩ። «የናቁት ያረጋል እራቁት» እንደሚባለው ሁሉ እነዚህ ታጋዮች የመንግስትን ወታደር በውጊያ እያሸነፉ እንደመጡ ይታወሳል። መንቶ 303 ላይ ባለው ቃል ግጥም «የኢህአዴግ ወታደር ስንት ነው ልባቸው» በሚለው ስንኝ ውስጥ «ልባቸው» የሚለው ቃል በወንድ የመራቢያ አካል የተለወጠ ነው። አንድ ወንድ አንድ የመራቢያ ብልት እንደሚኖረው የሚታወቅ ቢሆንም፣ መንቶው አጋኖ የሚጠይቅ ነው። ይህም ከውጊያው አንባር ሲታይ፣ የኢህአዴግ ወታደሮች በአነስተኛ ቁጥር ብዙ የደርግ ወታደር ይገጥሙ እንደነበር ነው።

በአጠቃላይ በእርስ በርስ ጦርነቱ ወቅት የተፈጠሩ ቃልግጥሞች፣ የኢህአዴግ ወታደሮች በውጊያው የበላይነትን እየተቀዳጁ የመጡ፣ የደርግ ወታደሮች የሰፈሩበትን የጦር ሰፈር እየለቀቁና እያፈገፈጉ መሆኑ፣ የተንፀባረቀባቸው ቃልግጥሞች ናቸው።

6.2.6.4.1.3 ትዝብታዊ ቃልግጥሞች

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ትዝብታዊ ቃልግጥሞች ወደ አንድ ወገን ሳያዳሉ፣ ሚዛናዊ የሆነ አስተያየት መስጠትን የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ የተንፀባረቀባቸው ቃልግጥሞች እንደሆኑ ይታወሳል። ከዚህ በታች በሚጠቀሱት ቃልግጥሞች በእርስ በርስ ጦርነቱ ጊዜ ሰዎች ይታዘቧቸው የነበሩ ሁኔታዎችን፣ ማለትም የውጊያውን ሁኔታ፣ በዚሁ ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ የታየውን ፍርሀትና ስጋት፣ እንዲሁም በሁለቱ ተዋጊዎች መካከል የነበረውን የሀይል አሰላለፍና የጦር መሳሪያ በሚመለከት፣ ከወገናዊነት ነፃ በሆነ ስሜት የተፈጠሩትን ቃልግጥሞች እንመለከታለን።

መንቶ 304 የወያኔ አህዮች ሁለት እግራ ናቸው
ቆቦ የተጫኑ ዳንዴ አራገፏቸው
መንቶ 305 የወታደር ኪዳ ወድቆ አይሰበርም
ጮቢ በርን ያየ ክፉ አይናገርም
መንቶ 306 ወራጋ ላይ ሁና ግራርፒን ብትለቀው
አዲስ አበባ ሆኖ ወሬው አስጨቀው
መንቶ 307 የደርጉ መኪና በርበሬ በልታለይ
ውሃ ጠማኝ ብላ ቀዝቃዚት (ጎሊና) ገብታለይ
መንቶ 308 በሰማይ ላይ ሆኖ ቦምብ ከመበተን
በክላሽን ጥይት ወርዶ መፈታተን
መንቶ 309 ምነው በሰማይ ላይ እንደ አሞራ ልጅ
ወርደህ ዶሮ ግብር ፈትናቸው እንጂ
መንቶ 310 በፊት ነበር እንጂ አመሉን ማበጀት
በሰማይ ላይ ሆኖ ወረቀት ከመርጨት
መንቶ 311 እነሱ ቀጫጭን ጫማቸው ቀላላ
አላህ ያውጣን በሉ ከሚያመጡት በላ
መንቶ 312 እንደተከፋ ሰው አንገቱ ዘቅዝቆ
ኸደ ላይመለስ እንደማይሆን አውቆ

መንቶ 313 ምች መታው አሉ ድንገት ቆቡ ወልቆ
እየሸሸ ሲሄድ እንደማይሆን አውቆ
አርኬ 314 ይገርመኛል፣ይደንቀኛል፣የኒህ ሰዎይ ስራ
ጠጉራቸው ጎፈሬ ጫማቸው ነጠላ
ጠጉራቸው ጎፈሬ ስማቸው ቅማላም
ጠቅልለው አዳፋት ጣብሶ እንዳደረ ላም
መንቶ 315 አንድ ጥይት ሳይጮህ አንድ ሰው ሳይሞት
ወልዲያን ለቀቀ ደርጉ አባ ጉልበት

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ቃል ግጥሞች ከሚያስተላልፉት መሰረታዊ ሀሳብ አንፃር በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ከፍን ማየት እንችላለን፡፡ በጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብ የሚያጋጥመውን ማንኛውንም ገጠመኝ በአንድ በኩል ወታደሩ እየተሸነፈ በመሄዱ ሰበብ ተስፋ የሌለው መሆኑን የሚያሳዩት በሌላ በኩል ካየን በኋላ አሸናፊነቱ ለኢህአዴግ ወታደሮች እንደሆነ አመላካች የሆኑትን ቀጥሎ እናያለን፡፡

በመንቶ 304 - 306 በተጠቀሱት ቃልግጥሞች ውስጥ የተንፀባረቀው ማህበረሰባዊ ችግር እንግልት፣ ፍርሀትና ስጋት ነው፡፡ እነዚህ ችግሮች ይታዩ የነበረው ከ1970ዎቹ ጀምሮ እስከ 1980ዎቹ አመታት ነው፡፡ በመንቶ 304 ላይ የተጠቀሰው ግጥም መነሻ ታሪክ እንዲህ ነው፡፡ በ1972 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተሀት ተዋጊዎች ቆቦ ከተማ ውስጥ በሌሊት ገብተው አጥቅተው መመለሳቸውን አጥኚው ያስታውሳል፡፡ በዚህ ጥቃት የቀበሌ ህብረት ሱቆች ተዘርፈዋል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በአካባቢው ውጊያ ይካሄድ ነበር፡፡ በ1976 ዓ/ም ባልታሰበ ሁኔታ ውጊያው ከሌሊቱ ወደ ቀን ይለወጣል፡፡ በዚህ ውጊያ የቆቦ ከተማና አካባቢው ለሶስት ቀን ያህል በኢህአዴግ ወታደሮች ቁጥጥር ስር ይሆናሉ፡፡ እንደተለመደው የኢህአዴግ ወታደሮች በመንግስት መጋዘኖችና በቀበሌ ሱቆች ውስጥ የሚገኘውን እቃ ሁሉ ወደ መጡበት ማጓጓዝ ይጀምራሉ፡፡ የተገኘው (የተዘረፈው) እቃ ብዛት ስለነበረው በራሳቸው ማጓጓዝ ሲያቅታቸው፣ በየመንገዱ ያገኙትን ሰው እየያዙ በሀይል እንዲሸከም አድርገው አጅበው እቃውን ማሸሽ ቻሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ ነው መንቶው የዘገበው፡፡ ሰውን እንደ አህያ እየጫኑ ይሸሹ ስለነበር «የወያኔ አህዮች ሁለት እግራ ናቸው» በማለት ይገልጻቸዋል ፡፡ «ዳንደኤ» የሚባለው የጦር ሰፈራ የወያኔዎች ሲሆን የሚገኘው ትግራይ ውስጥ ነው፡፡ የተዘረፈውን እቃ የተሸከሙት ሰዎች ማድረስ ያለባቸው ዳንደኤ ድረስ ነው ስለሚባል፣ ዳንደኤ አራገፏቸው የተባለው፡፡

በነዚህ የጦርነት ቀናት ተይዞ የነበረው የቆቦ ከተማና አካባቢው ከማይጨው አካባቢ ተንቀሳውሷል በሚባል የደርግ ጦር ተመልሶ ሊያዝ ችሏል። አካባቢውን መልሶ ለማስለቀቅ (ለመያዝ) የተደረገው ውጊያ ግን እጅግ አስቸጋሪ ነበር። መንቶ 305 ላይ የተገለፀው ይኸው የመልሶ ማጥቃት ውጊያ ነው። ጮቢ በር የሚባለው አካባቢ በቆቦና በዋጃ ከተሞች መካከል የሚገኝ አካባቢ ነው። አካባቢውን ከአዲስ አበባ መቀሌ የሚሄደው ዋና መንገድ አቋርጦ ያልፋል። ከላይና ከታች ተራራ ሲሆን መንገዱ በመሀል ነው። ከማይጨው እየገሰገሰ የመጣውን የደርግ ወታደር፣ የኢህአዴግ ወታደሮች ጮቢ በር ላይ መሸገው ጠበቁት፤ ከቀኑ አምስት ሰዓት አካባቢ ጀምሮ በከባድ መሳሪያ በታገዘ እግረኛ ጦር ውጊያ ተደረገ። ወደ አስር ሰዓት አካባቢ በሄሊኮፕተር ጭምር በመዋጋት ቦታውን ማስለቀቅ ተቻለ። በዚህ ውጊያ ከሁለቱም ወገን ብዙ ተዋጊ አለቀ። የደርግ ወታደር በኦራል መኪና የኢህአዴግ ወታደሮችን ሬሳ ጭኖ በማምጣት ቆቦ ከተማ ውስጥ ተጥለው የከተማው ነዋሪ ሲመለከት መዋሉን አጥኚው ያስታውሳል። ይህንን አሰቃቂና አሳዛኝ ሁኔታ ለመግለጽ ነው «ጮቢ በርን ያየ ክፉ አይናገርም» የሚለው ስንኝ የሚያስታውሰው።

መንቶ 306 ላይ «ግራርፒ» የሚባል አንድ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ስም ተጠቅሷል። ይህ መሳሪያ ከተራራ ጀርባ ተጠምዶ በተራራው እናት አልፎ ኢላማውን መምታት ይችላል ይባላል። መሳሪያውን የኢህአዴግ ወታደሮች ብቻ እንደታጠቁት ይገመታል። «ወራጋ» የሚባለው አካባቢ ከዞብል ሰንሰለታማ ተራራ በስተምስራቅ በኩል አፈር ድንበር ላይ የሚገኝ አካባቢ ነው። ከዞብል ተራራ ጫፍ ላይ ሆነው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሲመለከቱ የቆቦ ከተማና አካባቢው ደንብ ይታያል። በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው ከከተማው በስተምስራቅ አቅጣጫ የሚገኘውን ማይክሮዊቭ የደርግ ወታደሮች ምሽግ ሰርተው ይጠብቁ ስለነበር፣ ይህን ሰራዊት ከመሸገበት ለማስወጣት ከላይ የተጠቀሰው መሳሪያ ጥቅም ላይ ውሏል ይባላል። ውጊያው የተካሄደው በ1982 ዓ/ም ነሀሴ ወር ላይ ነው። በዚህ ውጊያ የመንግስት ወታደር ተሸንፎ ከአካባቢው ወጥቷል። መንግስትም በመገናኛ ብዙሀን ይህንኑ ጦርነት ለህዝብ እንደገለፀው ይታወሳል። ይህ የመንግስት መግለጫ ነው፣ «አዲስ አበባ ሆኖ ወራው አስጨነቀው» የተባለው። «ወራው» የሚለው የመንግስት ወታደር የመሸነፉን ዜና የሚያመለክት ቃል ነው።

ከመንቶ 307-310 ባሉት ቃልግጥሞች ውስጥ የተገለፀው ሀሳብ የመንግስት ወታደሮች ሰሜን ወሎን (ሁለቱን ራያዎች) ሲለቁና ከዚያ በኋላም ይደረግ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚሳይ ነው። ወደ ሳባት ቀን በፈጀው ጦርነት የመንግስት ጦር ሙሉ በሙሉ ሁለቱን ራያዎች ለቆ

ወጥቷል። ከተከበበት ሰብሮ ለመውጣት በተደረገው ውጊያ ተሽከርካሪዎች፣ ታንኮች፣ በየቦታው ተጥለዋል፣ ተቃጥለዋል። ይህን ትዕይንት ለመግለጽ ነው መንቶ 307 የተገጠመው። መኪና በሰውኛ «በርበሬ በልታለይ» በሚል ተገልጿል። ይህም የጦርነቱን አስከፊነት የሚያመለክት ነው። የኢህአዴግ ወታደሮች የመኪና መንገዱን ግራና ቀኝ አድፍጠው ስለያዙት፣ በመኪና የሚሸሸው የመንግስት ጦር መንገዱን እየለቀቀ ለመጓዝ ሲሞክር፣ ወንዙ ውስጥ እየገባ ቀርቷል። ይህንን ሁኔታ ነው መንቶ ለማሳየት የሞከረው።

መንግስት አካባቢውን ከለቀቀ በኋላ ያደርግ የነበረው በአውሮፕላን እየታገዘ የሚችለውን ሁሉ ማድረግ ነበር። ከዚህ መካከል ቦንብ መጣል፣ የቅስቀሳ ወረቀቶች (ፋምፍሌቶች) መበትን፣ ይጠቀሳሉ። መንቶ 308 እና 309 ይህን ያመለክታሉ። መንቶዎቹ የመንግስት ጦር ወልዲያ አካባቢ ባሉት ስፍራዎች መሸጎ ይጠብቅ እንደነበር የተረዳና በድንገተኛ የአውሮፕላን ቦንብ የተጨነቀ ሰው የፈጠራቸው ይመስላሉ። ዶሮ ግብር ከወልዲያ በታች የምትገኝ የገጠር መንደር ናት። የኢህአዴግ ወታደሮች እዚች አካባቢ ተጠግተው ከወልዲያ ይመጣል ተብሎ የሚታሰበውን ሀይል ለማስቀረት ይጠብቁ ስለነበር፣ «ምንም በሌለበት ቆቦ አካባቢ እየተመላለስክ ቦንብ ከመጣልና የቅስቀሳ ወረቀት ከመበትን፣ በእግረኛ ጦር ዶሮ ግብር ላይ ያሉትን አስለቅቀህ ወደኛ ግባ» የሚል ጥቆማ ጭምር የተላለፈባቸው መንቶዎች ናቸው።

ይህ የወረቀት መበትን ስራ ውጤታማ መሆን እንዳልቻለ መንቶ 310 ያመለክታል። የመጀመሪያው ስንኝ የሚያስታውሰው በደርግና በኢህአዴግ መካከል ይደረግ የነበረውን ድርድር ነው። «በፊት ነበር እንጂ አመሉን ማበጀት» በሚለው ስንኝ መጨረሻ ላይ ያለው ሀረግ፣ በአግባቡ በድርድሩ መስማማት፣ ወደ ጦርነት አለመግባት፣ እርቅ እንዲፈጠር ማድረግ፣ ማለት ነው። እነዚህ አማራጮች ካለፉ በኋላ፣ የወረቀት ቅስቀሳ ብቻውን መፍትሄ ሊያመጣ እንዳልቻለ የሚያስታውስ ነው።

ከመንቶ 311-315 ባሉት ቃልግጥሞች ስጋት፣ተስፋ መቁረጥ፣ ሽንፈት፣ በተለያየ መንገድ የቀረበባቸው መንቶዎች ናቸው። በመንቶ 311 የተገለጸው ሀሳብ የአካባቢው ማህበረሰብ ስጋት ነው። «በላ» ክፉ-ነገር፤ እልቂት፤ እንግልት፤ ውጣውረድ፤ ወዘተ. የመሳሰሉትን ችግሮች የሚያመለክት ቃል ነው። መነሻው የመንግስት ወታደር ተመልሶ ይመጣል ከሚል ስጋት የመነጨ ነው። ስጋቱ በሁለት በኩል ሊታይ ይችላል። አንደኛው፣ አካባቢው ተመልሶ የጦርነት አውድማ ይሆናል፣ እልቂት ይመጣል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ ይህ ነገር እውነት ከሆነ የመንግስት ባለስልጣናት ኢህአዴግን ደግፏችኋል በሚል ሰበብ እስራት፣ ግድያ፣ ወዘተ.

ያደርሱብናል የሚል ፍርሀት የተገለጸበት ነው። የኢህአዴግ ወታደሮች አካባቢውን ለቀው ወደ መጡበት ስለሚመለሱ መከራውና ችግሩ የሚተርፈው ለኛ ብቻ ነው፤ የሚል ጭንቀት የተንጸባረቀበት መንቶ ነው። መንቶ 312 እና 313 በመንግስት ወታደሮች በኩል ይታይ የነበረውን ስሜት የሚያንጸባርቁ ናቸው። መንቶዎቹ የሰራዊቱን ቅስም መሰበርና ተስፋ መቁረጥ፤ የሚያሳዩ ናቸው። «እንደማይሆን አውቆ»፤ የሚለው ሀረግ የመሸነፍ፣ ተስፋ የመቁረጥ፣ ወዘተ. ስሜቶችን ያሳያል። የሰራዊቱ አባላት በማዘንና በመነጨ ስሜት፣ የማዕረግ ኮፍያቸውን እንኳ ራሳቸው ላይ አድርገው መታየት አለመፈለጋቸውን የሚያስታውስ ነው። «ምች መታው አሉ ...» የሚለው ሀረግ በድንገተኛና ባልተጠበቀ ሁኔታ ጦሩ ለሽንፈት መዳረጉን የሚያመለክት ነው።

አርኬ 314 ከሁሉም መንቶዎች በተሻለ ሁኔታ፤ በራያ ቆቦ አካባቢ የነበረውን ጦርነት የሚያሳይ ነው ማለት ይቻላል። አርኬው ከኢህአዴግ ወታደሮች አካላዊ ሁኔታና በማህበረሰቡ ዘንድ የነበራቸውን አስተያየት ጠቅላላ ግምት ለማንጸባረቅ የቻለ ነው። ከመንግስት ጀምሮ እስከ አካባቢው ማህበረሰብ ድረስ ለኢህአዴግ ወታደሮች ይሰጣቸው የነበረው ግምትና አስተያየት ዝቅተኛ እንደነበር ይታወቃል። በመንቶው የመጀመሪያ ስንኝ የመጨረሻው ሀረግ፣ «የኒህ ሰወይ ስራ...» በሚል የተገለጸው የኢህአዴግ ወታደሮችን ነው። ጎፈሪያቸው፣ ነጠላ ጫማቸውና ሌሎችም መገለጫዎች ከእነሱ ጋር ተያይዘው ይነገሩ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

የአርኬው ታሪክ መነሻ የሚከተለው ነው። በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የደርግ ወታደር በሁለቱ ራያዎች በተለያየ ቦታ ሰፍሮ ይዋጋ ነበር። ለምሳሌ ቆቦ ወረዳ አካባቢ ሁለት ትልልቅ የሚባሉ የጦር ሰፈሮች ነበሩ። አንድኛው ማይክሮዊቭ ሲሆን፣ ሁለተኛው ኩቢ ደጋጋ ይባላል። አንዱ ከከተማው በስተምስራቅ፣ ሌላው በስተምዕራብ በኩል የሚገኙ ነበሩ። በ1982 ዓ.ም ላይ የኢህአዴግ ወታደሮች በሰሜን ወሎ ሰሜናዊ ምስራቅ አካባቢዎች መጠነ ሰፊ ጦርነት ከፈቱ። በሁለቱ የጦር ሰፈሮች የነበረው የደርግ ወታደር በከፍተኛ ሁኔታ ለመከላከል ሞከረ፤ ግን ማሸነፍ ሳይችል ቀረ። ማይክሮዊቭና ኩቢ ደጋጋ የነበረው ጦር ከምሽጉ እየወጣ ወደ ከተማው በመግባት ዋናውን የመኪና መንገድ ተከትሎ ወደ ወልዲያ ለመጓዝ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አደረገ። የአርኬው ዋና ሀሳብ ያለው «ጠቅለው አዳፉት ጣብሶ እንዳደረ ላም» በሚለው ስንኝ ውስጥ ነው። «ጠቅለው አዳፉት» የሚለው ሀረግ ማይክሮዊቭና ኩቢ ድጋጋ የነበረው ጦር ከምሽጉ ወጥቶ ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲጓዝ አስገደዱት ማለት ነው። «ጣብሶ እንዳደራ ላም» በሚለው ሀረግ ውስጥ «ጣብሶ» ማለት አንድ ቀን እያሳለፉ ውሃ መጠጣት ማለት ነው። በዚህ መሰረት ከብቶች አንድ ቀን ውሃ ሳይጠጡ ይውሉና በሁለተኛው ቀን ወደ

ወንዝ ሲነዷቸው ወንዙ ወደሚኝበት በሩጫ ጭምር ይገሰግሳሉ። ስንኝ የወታደሩን ጉዞና ሽሽት ከብቶቹ ከሚያደርጉት ሩጫ ጋር አመሳስሎ (አዛምዶ) ነው ለማሳየት የሞከረ ነው።

የመጨረሻው መንቶ በሁለቱ ሀይሎች መካከል ይህ ነው እሚባል ውጊያ እንዳልተደረገ የሚጠቁም ነው። «ደርጉ አባ ጉልበት» የሚለው ሀረግ የሰራዊቱን ብዛት፣ ሀይለኛነትና የጦር መሳሪያ አይነትና ብዛት የሚያመለክት ሀሳብ የተገለጸበት ነው። ከዚህ በመነሳት በማህበረሰቡ አስተሳሰብ፣ የደርግ ወታደር በኢህአዴግ ወታደሮች ይሸነፋል የሚል ግምት አልነበረም ማለት ይቻላል። ይህ አስተሳሰብ ነው በመንቶ 315 የተገለጸው። በአጠቃላይ ትዝብታዊ ቃልግጥሞቹ የነበረውን የርስ በርስ ጦርነት ሚዛናዊ በሆነ አገላለጽ ለማሳየት የቻሉና የነበረውን ተጨባጭ እውነታም ዘግበው ማስቀረት የቻሉ ናቸው ማለት ይቻላል።

6.2.6.4.2 የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

በምዕራፍ ሁለት በታሪካዊ ደራው እንደተነሳው፣ ከሀገራችን የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ መካከል ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የሚታወቀው በቀድሞው የኢትዮጵያ አንድ ክፍለ ሀገር በነበረችው ኤርትራ ውስጥ ይንቀሳቀሱ በነበሩ ሀይሎች አማካኝነት ይደረግ የነበረው ነው። ይህንን ሀይል ለማጥፋት ይደረግ የነበረው ውጊያ ጎልቶ መታየት የጀመረው በደርግ ዘመነ-መንግስት ነበር። ከሶማሊያ ጦርነት በፊት «የራዛ ዘመቻ» በሚል የደርግ መንግስት በሰሜን ኢትዮጵያ ካሉት አካባቢዎች (በተለይ ከወሎ አካባቢዎች) የገበሬ ጦር አዝምቶ እንደ ነበር በዳሰሳው ላይ ተጠቅሷል። በመሆኑም ከ1966 ዓ.ም አብዮት ጀምሮ እስከ 1990ዎቹ ባሉት አመታት ውስጥ የነበረውን የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና የፖለቲካ ሁኔታ የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች ተፈጥረዋል።

እንደሚታወቀው የደርግ መንግስት ከኤርትራ ጋር የነበረውን ችግር ለመፍታት ከተጠቀመባቸው የጦርነት አዋጆች መካከል «የራዛ ዘመቻ» ና «የቀይ ኮከብ ጥሪ» የሚባሉት ይታወቃሉ። የራዛ ዘመቻ፣ በገበሬዎች የተደራጀና በተራ መሳሪያ የተደረገ ዘመቻ ነው። የቀይ ኮከብ ዘመቻ ደግሞ፣ ከሶማሊያ ወራሪ ጦር ድል መደረግ በኋላ፣ የተደረገ ዘመቻ ነው። «የምስራቁ ድል በሰሜን ይደገማል» በሚል መፈክር የተጀመረ ጦርነት ነው። ከዚህ ቀጥሎ ከ1970ዎቹ ዋዜማ ጀምሮ እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ድረስ የነበረውን የታሪክ እውነታ የሚያሳዩትን ቃልግጥሞች እንመለከታለን።

መንቶ 316 የደርጉ መኪና ጅራተ ቆራጣ
አድርሶ መንጣት ነው መልሶ አያመጣ
አርኬ 317 ዳምጤ መለስን ብጠራው ዝም አለኝ
ተሰማ ወዳጆን ብጠራው ዝም አለኝ
አበራ ካሳው ነው ስጠራው ወይ ያለኝ
መንቶ 318 ኤርትራ ኸበሩ ዘር እየተዘራ
ወይ ልጅ አያሳድግ እሸቱ አይበላ
መንቶ 319 የኤርትራን መሬት እፋረደዋለን
ደህና ደህና ጎበዝ ገብሬበታለሁ
መንቶ 320 የኤርትራን እህል አልበላም እርም ነው
የዘራው መትረየስ ያበቀለው ደም ነው
አርኬ 321 ታረሰ አሉ አስመራ ፣ታረሰ ቀይ ባህር
በክላሽን ቀንበር በታንከር ሞፈር
እነዚያ ጎበዞይ እየሆኑ ዘር
መንቶ 322 ታረሰ ቀይ ባህር መታረስ ይታረስ
ሳንፈተንበት እንደግልገል ፈረስ

ከመንቶ 316 እስከ 322 ባሉት ቃልግጥሞች የተንጸባረቀው ሀሳብ በ1970ዎቹ ዋዜማና ማግስት የነበረውን ወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚያስተውሱ ናቸው። መንቶ 316 እና አርኬ 317 ላይ የቀረቡት ቃልግጥሞች በራዛ ዘመቻ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው። የመጀመሪያው መንቶ «ጅራተ ቆራጣ» የተባለው የመኪና አይነት ምን አይነት እንደነበር ማወቅ ባይቻልም ለትችት የዳረገው ለዘመቻ የሄደውን ሰው ከወሰደበት ቦታ መልሶ አለማምጣቱ ነው። ሁኔታውን በሁለት መንገድ መረዳት ይችላል። በወቅቱ እንደተደረገው ወደ ኤርትራ እንዲዘምት የተደረገው የገበሬ ጦር የተጓዘው በመኪና ነበር። በኋላ ግን ተሸንፎ፣ የሞተው ሙቶ፣ ተማርኮ የተለቀቀውና በህይወት የተረፈው ተመልሶ ወደ ትውልድ አካባቢው የገባው በእግሩ በመጓዝ ነው። ይህ ቅሬታ ነው በመንቶ 316 የተንጸባረቀው። አርኬ 317 ላይ የተነሳው ሀሳብ በዘመቻው ጊዜ ሰዎች ሞተዋል እየተባለ መርዶ ይላክ የነበረ መሆኑን የሚገልጽ ነው። አንዳንዶቹ ሳይሞቱ ሞተዋል እየተባለ መርዶ ተልኳል። ከነዚህ መካከል አንዱ አበራ ካሳው የሚባሉት ናቸው። እኝህ ሰው ከተለቀሰላቸው በኋላ በህይወት ተመልሰው እስከ አሁን ድረስ በህይወት ያሉ ናቸው። ሁለቱ ሰዎች ግን መሞታቸው የተረጋገጠው «ብጠራው ዝም አለኝ» በሚለው የአርኬው የመጀመሪያ ስንኝ ነው።

ከኤርትራ አማጺያን ጋር በነበረው ጦርነት ምክንያት ኢትዮጵያዊያን በጦርነት እየተማገዱ ያልቁ እንደነበር ከመንቶ 319-320 ያሉት ግጥሞች ያስረዳሉ። እነዚህ መንቶዎች ኤርትራ ውስጥ ይደረግ የነበረው ውጊያ በቁጭት ስሜት የተሞላ እንደነበር የሚያመለክቱ ናቸው። መንቶ 318 ዘር መዘራት፣ ከጦርነት ፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው። ልጅ አለማሳደጉ ደግሞ ለጦርነት የሚሄዱት ወጣቶች ማለቅን ይመለከታል። «እሸቱ አይበላ» ማለት ድል ተደርጎ ደስ አላለንም ማለት ነው። ይኸው ሁኔታ በተከታዩ መንቶ ተደግሟል። «ደህና ደህና ጎበዝ ገብሬበታለሁ» የሚለው በጦርነቱ ወቅት የሞቱትን ወጣቶች የሚመለከት ነው። በኤርትራ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን እንዳለቁት የሚመለከት ደግሞ መንቶ 320 ነው። «እርም» ማለት የተከለከለ የማይበላ ማለት ነው። በኤርትራ ውስጥ የተመረተውን ሰብል ላለመብላት የተነሳው ሀሳብ በሰው ልጆች ደም የበቀለ ተደርጎ መቆጠሩ ነው። የመንቶው ሀሳብ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ያለቁበት አካባቢ መሆኑን ማሳየት ነው።

የጦርነቱ ሁኔታ እየተባባሰ መምጣቱን አርኬ 321 እና መንቶ 322 ያመለክታሉ። አስመራና ቀይ ባህር በታክና በክላሽ በታገዘ ውጊያ እንደተካሄደባቸው «ታረሰ...» የሚለው ቃል ያመለክታል። ቀጥሎ ያለው መንቶ 322 ግን በቁጭት የተነገረ ይመስላል። ይኸውም «በጦርነቱ እኛም ተካፍለን የበኩላችንን ታሪክ መስራት ነበረብን» የሚል የቁጭት ስሜት የተንጸባረቀበት ነው። ከመንቶ 323-327 ባሉት ቃልግጥሞች የተነሱት ሀሳቦች፣ ሻቢያ የሚባለው የኤርትራ አማጺ ሀይል፣ ክፍለ ሀገሩን ከተቆጣጠረ በኋላ፣ የኢህአዴግን አቋምና በሌላው የሀገሪቱ ዜጎች የነበረውን የአመለካከት ሁኔታ የሚያስታውሱ ናቸው። የቁጭትና የብስጭት ስሜት የተንጸባረቀባቸው ናቸው።

መንቶ 323 አብሽ ድንብላሉን ገብረን ገብረን
መዝመታችን ላይቀር ዝም ብለን በኮራን
መንቶ 324 ተስማምተን ነበር በነይሁን ብሻው
አሁንም አገሬ ያስፈራታል ግርሻው
መንቶ 325 የሀገሬ ወጣቶች ጥይት አትተኩሱ
ዛላምበሳ ሜዳ ተቀልሷል ዳሱ
መንቶ 326 ዛላምበሳ ሜዳ ሰርግ የበላችሁ
በባድሜ በኩል ምላሽ መጣላችሁ

መንቶ 327 የቀይ ባህሩ ቁስ ያልጌናው ዲያቆን

ቶበተ መሰለኝ ጠመጠመ አሁን

በ1983 ዓ.ም የኢህአዴግና የሻቢያ ሀይሎች የነበረውን የደርግ መንግስት አሸንፈው፣ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር፣ ሻቢያ አስመራን ይዞ እንደ ነበር ይታወሳል። ከዚህ በኋላ በመላ ሀገሪቱ የነበረው ሁኔታ አስፈሪ ነበር ማለት ይቻላል። የሆነ ሆኖ ሻቢያ አስመራን፣ ኢህአዴግ አዲስ አበባን በመቆጣጠር የማረጋጋትና የማስተዳደር ሁኔታ ተፈጠረ። እስከ ባድሜ ጦርነት መነሳት ድረስ ኤርትራዊያን በቀረው የኢትዮጵያ አካባቢ እንደልብ ይንቀሳቀሱና ይኖሩ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ኢትዮጵያና ኤርትራ ራሱን እንደቻለ ሀገር ለየብቻ ይኖራሉ ተብሎ ቢታሰብም በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ኤርትራዊያን ኢትዮጵያን በሚጎዳ ተግባር ውስጥ እንደነበሩ (ለምሳሌ ማሸኖችን እየነቀሉ መውሰድ፣ የኢትዮጵያን ሸቀጦች በስማቸው መሸጥ...) የሚያስታውሰው መንቶ 323 ነው።ይህም «አብሽ ድንብላሉን ገብረን ገብረን...» የሚለው ነው። በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል መንቶ 324 ይገጠቁማል። የመንቶው የመጀመሪያ ስንኝ የኤርትራ መገንጠል ወደ ኋላ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል አመላካች ነው። «በእነ ይሁን ብሻው» የሚለው ሀረግ የመገንጠሉ ጉዳይ የኢህአዴግ አቋም እነደሆነ የሚጠቁም ነው። ይህ ነገር (ውሳኔ) ቆይቶ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል መንቶ 325 እና 326 ያመለክታሉ። እነዚህ መንቶዎች በ1990 ዓ/ም የተነሳውን የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን የተነበዩ ናቸው። የጦርነቱ አካባቢዎች ብዙ ቢሆኑም «ዛላንበሳና ባድሜ» ዋናዎቹ መሆናቸውን ይጠቁማሉ። የጦርነት ድግሱ መነሻ ዛላንበሳ ላይ ቢሆንም፣ ባድሜ ላይ ሌላ ጦርነት ይጠብቀናል የሚል መልክት የተላለፈባቸው ናቸው።

መንቶ 327 ለየት ያለ የታሪክ እውነታ የተንፀባረቀበት ነው። የደርግ መንግስት በኤርትራ ውስጥ በተለያዩ የጦር ክፍሎች የተደራጀ የጦር ሀይል አሰማርቶ ከሻቢያ ጋር ይዋጋ እንደነበር ይታወቃል። ከነዚህ የጦር ክፍሎች መካከል በጀኔራል ሁሴን አህመድ ይመራ የነበረው አንዱ ነው። በዚህ መኮንን ይመራ የነበረው የደርግ ጦር፣ በሻቢያ ወታደሮች ላይ ባለድል ስለነበር የመኮንኑ ስም በአድናቆት ይታወቃል። የደርግ ጦር ተሸንፎ ኤርትራን ሲለቅ መኮንኑ በሄሊኮፕተር ወደ አረብ አገር ጥገኝት ጠይቀው ገብተዋል ይባላል። መንቶው ይህን የመኮንኑን ታሪክና የነበራቸውን ጀግነት ለመዘከር የተፈጠረ ነው። መኮንኑ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ መሆናቸው ከስማቸው ለመረዳት ቢቻልም የመንቶው የመጀመሪያ ስንኝ

ግን “ቂስ ና ዲያቆን” ይላቸዋል። እነዚህ ቃላት ያላቸው ፍቺ በኤርትራ ውስጥ ይካሄድ ለነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ሰውየው፣ እንደ ዋና አዋጊና ተዋጊ መኮንን እንደነበሩ የሚያስታውስ ነው። ቀጥሎ የምናያቸው ደግሞ፣ ኤርትራ አሁንም የኢትዮጵያ አካል እንደምትሆን፣ ነገር ግን፣ ሻቢያም ሀይለኛ በመሆኑ ችግር ሊያጋጥም እንደሚችል የሚያመለክቱ ሀሳቦች የተንጸባረቁባቸው ቃልግጥሞች ናቸው።

መንቶ 328 አንቺ አገር እንዴነሽ ፣አገሬ እንዴነሽ
ስንቅ አበጃጅተናል ልንጠይቅሽ
መንቶ 329 አንማቸው አንማቸው ከዚያም አሉ
እንደግልገል ፈረስ ታንክ ይጋልባሉ
መንቶ 330 እንሂድ ካላችሁ እንሂድ ተነሱ
መቀሌ ቅርብ ነው ማይጨው ኸደረሱ
መንቶ 331 ምጣዱ ቢሰበር ገሉ የኛ ነው
እንዴት ናት አገሬ (ኢትዮጵያ) እስተባንዲራው

ከመንቶው 328-331 ባሉት ግጥሞች ከኤርትራ መገንጠል ጋር በተያያዘ ሁኔታ ያለውን ቁጭት የሚመለከት ሀሳብ የተንፀባረቀባቸው ናቸው። የኤርትራ መገንጠል በአንድ በኩል የሻቢያ ወታደሮች ጀግንነት፣ በሌላ በኩል ኤርትራ ብትገነጠልም ወደኋላ ምን እንደሚሆን አይታወቅምና፣ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ሰላም እንዲያደርግልን ማሰብ ይገባናል የሚል የተለያዩ ሀሳቦች የተላለፉባቸው መንቶዎች ናቸው። «...አገሬ እንዴት ነሽ» የሚለው ሀረግ የሚጠቁመው ኤርትራን ነው። ከላይ እንደተጠቆመው የመንቶው መነሻ ሃሳብ «ቁጭት» ይመስላል። ቁጭቱም በቅስቀሳ የታገዘ መሆኑን መንቶ 330 ያረጋግጣል። «እንሂድ ካላችሁ...» የሚለው ስንኝ የሰዎችን ተነሳሽነት ያመለክታል። መንቶ 329 ግን ከላይ የቀረቡትን አስተሳሰቦች የሚቃወም ነው። ይኸውም «ኤርትራ የተገነጠለችው በሻቢያ ወታደሮች አሸናፊነት እንጅ፣ በሌላ አይደለም» የሚል አንድምታ ያለው ነው። «አንማቸው» የሚለው ቃል፣ እነሱ በሌሉበት ስለነሱ መናገር የለብንም፤ እነሱም እንደኛ ጀግና ናቸው፤ የውጊያ ብቃታቸውም ከነፍስ ወከፍ መሳሪያ በተጨማሪ በታንክ መዋጋት እንደሚችሉ፣ የሚገልጽ ነው። የመጨረሻው መንቶ 331 ሁሉንም ለማስታረቅ የተሰነዘረ አስተያየት ይመስላል። በመንቶ ውስጥ «ምጣድ» እና «ገል» የሚሉ ቃላት ተጠቅሰዋል። ምጣድ መላ ኢትዮጵያን የሚወክል ነው። ገል ደግሞ ኤርትራን ይወክላል። በመሆኑም፣ «ኤርትራ

ብትገነጠልም የኛ ናት፣ ህዝቡም ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በሰላም መኖር ይችላል» የሚል ሀሳብ የተላለፈበት ነው።

በአጠቃላይ ከኢትዮ-ኤርትራ የእርስ በርስ ጦርነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተፈጠሩት ቃልግጥሞች ከኢትዮጵያ አብዮት ማግስት ጀምሮ የነበረውን የታሪክ እውነታ የሚያሳዩ ናቸው። መገንጠሉ እንደ መፍትሄ ቢወሰድም፣ ኢትዮጵያንና ኤርትራን ከጦርነት መላቀቅ እንዳልቻሉ መንቶዎቹ ያስረዳሉ።

6.2.6.4.3 ታሪካዊ ሁኔታዎችንና እውነታዎችን የሚያስታውሱ ቃልግጥሞች

በኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት አከፋፈል፣ ሶስተኛው የታሪክ ምዕራፍ የሚጀምረው ከአጼ ቴዎድሮስ መነሳት በኋላ እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል። ከእሳቸው ሞት በኋላ የተነሱትም የእሳቸውን አስተሳሰብና አላማ የተከተሉ ቢመስልም፣ ንጉስ ነገስት ለመሆን ካላቸው ፍላጎትና አላማ በመነሳት የእርስ በርስ ጦርነት ያካሂዱ ነበር። አፄ ዮሐንስ፣ ከአፄ ተክለ ጊዮርጊስ (ዋግሹም ጎበዜ) ጋር አሳም (Assam) ላይ በ1871 ከተዋጉ በኋላ፣ በ1872 ንጉሰ ነገስት ሲሆኑ፣ ትኩረታቸው መሀል ሀገር ወዳሉት አካባቢዎች እንደነበር (Bahru፣ 2002፣ 93) ላይ ይገልጻሉ። በዚህም ከምኒልክ ጋር የነበረው ፍጥጫ ለጊዜው በምኒልክ ጥበበኛነት ወደ ከፋ የእርስ በርስ ጦርነት ሳይሸጋገር እስከ መተማ ጦርነት (1889)ድረስ ቆይቷል። የሁለቱ ፍጥጫ እንዳለ ሆኖ አጼ ዮሀንስ በወሎና በጎጃም አካባቢዎች ጦርነት አድርገው ብዙ ሰው አልቋል፤ አላማቸውን አልቀበል ያለውን በሀይል እንዲቀበል ለማድረግ ታግለዋል።

አፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ፣ አፄ ምኒልክ ንጉሰ ነገስት በመሆን ዘመናዊ ኢትዮጵያን የመገንባት ሂደቱን ቀጠሉ። ይኸው እንቅስቃሴ እስከ አፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ድረስ የቀጠለ ነበር። በመሆኑም በዚህ ንዑስ ክፍል የምንተነትናቸው ቃል ግጥሞች ከአፄ ዮሐንስ እስከ አፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ድረስ በነበረው የታሪክ ሁኔታ ላይ ተመስርተው የተፈጠሩትን ይሆናል። ቃልግጥሞቹ የታሪክ ሂደቱን ተከትለው የቀረቡ ስለሆነ፣ ከአፄ ዮሐንስ የጀመረውን እንመለከታለን።

አርኬ 332 የገደለው ባልሽ
የሞተው ወንድምሽ
አዘንሽ ቅጥ አጣ
ኸቤትሽ አልወጣ

መንቶ 333 የዮሀንስ በቅሎ ጠፍታ በሌሊት
ቀን ወደ ምኒልክ ስትሄድ አየናት
መንቶ 334 የምኒልክ አልጋ እልፍ ነው ባላው
በትግሬ መንገሻ፣ በወሎ ሚካኤል፣
በሀረር መኮንን፣ ጎጃም ራስ ሀይሉ እየደገፈው
መንቶ 335 እቴጌ ጣይቱ ትልቅ ባል አግብታ
ከሸዋ (ከእንጦጦ) ተነስቶ አድዋ የሚማታ

አርኬ 332 የተገጠመው አፄ ዮሐንስና አፄ ተክለ ጊዎርጊስ ጦርነት አድርገው፣ ድሉ ለዮሐንስ ከሆነ በኋላ ነው። በአፈታሪክ እንደሚነገረው በሁለቱ መካከል በነበረው ፍጥጫ ለጦርነት ይዛዛቱ ነበር ይባላል። ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ፣ በየአካባቢው የተበተነውን ተዋጊ ሀይል ወደ እሳቸው ለማሰባሰብ በመቻላቸው ቁጥሩ የበዛ ሀይል የነበራቸው ተክለ ጊዎርጊስ፣ ለዮሐንስ ጤፍ በአቅማዳ ላኩላቸው አሉ። የጤፉ ትርጉም የገባቸው ዮሐንስም፣ ጤፉን አስቆልተው ለተክለ ጊዎርጊስ መለሱላቸው ይባላል። ወደ ተፈራውና ወደ ተጠበቀው ጦርነት ሲገቡ ዮሐንስ አሸናፊ፣ ተክከ ጊዎርጊስ ተሸናፊ ሆነው ተማርከው ተገደሉ። የአፄ ዮሐንስ ባለቤት፣ የተክለ ጊዎርጊስ እህት የነበሩ መሆናቸውን፣ «የገደለው ባልሽ፣ የሞተው ወንድምሽ» የሚሉት ስንኞች ያመለክታሉ። ስልጣን ከቤተሰባዊ ግንኙነት በላይ መሆኑን አርኬው ያረጋግጣል ማለት ነው። የዮሐንስ ሚስት፣ የተክለ ጊዎርጊስ እህት፣ ከባሏ ጎን ተሰልፋ የባሏን ተቀናቃኝ ትዋጋ? ወይስ ከወንድሟ ጎን ተነስታ የወንድሟን ገዳይ ትበቀል ወይም ትፋረድ? አስቸጋሪ መሆኑን «አዘንሽ ቅጥ አጣ» በሚለው ስንኝ ተገልጿል።

በታሪክ እንደሚታወቀው አፄ ዮሀንስ የክርስትና ሀይማኖትን፣ እንደ አንድ ማዕከላዊ አንድነት ያለው ህዝብ ለመፍጠሪያነት ይጠቀሙበት ስለነበር፣ ቦሩ ሜዳ (ወሎ ውስጥ) ላይ የሀይማኖት ክርክር እንዲደረግ ከአደረጉ በኋላ፣ ተሸናፊዎቹን ቀጥተው፣ አሸናፊዎችን አሞግሰው፣ ከሾሙና ከሸለሙ በኋላ፣ ንጉስ ሚካኤልን ክርስትና አንስተው ካስጠመቁ በኋላ፣ ሌላው ሙስሊም እንዲጠመቅ አዝዘው፣ ወደ ትግራይ ይመለሳሉ። በዚህ ክርክር ላይ አፄ ምኒልክም ተገኝተው ስለነበር፣ ሁለቱም ወደየግዛታቸው ሲመለሱ፣ የአፄ ዮሐንስ የነበረ ለማዳ አንበሳ፣ ምኒልክን ተከትሎ መሄድ ይጀምራል። የዮሐንስ ተከታዮች አንበሳውን አስገድደው ለመመለስ ቢሞክሩ እየተቆጣ እንቢ አለ ይባላል። የአንበሳው እንቢታ ሲተረጎም የንጉሰ ነገስትነት ስልጣን ወደ ምኒልክ መሄድን የሚያመለክት ነው። «ቀን ወደ ምኒልክ ስትሄድ አየናት» የሚለው

ስንኝ ይህን ያረጋግጣል። «ከእንግዲህ የሚመጣው ዘመን ለምኒልክ የተመቸ፣ ለዮሐንስ ግን አስቸጋሪ ይሆናል» የሚል ትንቢት የተነገረበት መንቶ ነው።

በአፄ ቴዎድሮስ የተጀመረው አንድ የማድረግ ተግባር፣ በዮሀንስ ቀጥሎ፣ በምኒልክ ዘመነ መንግስት የአሁኗን ኢትዮጵያ ለማዋሀድ እንደተቻለ በታሪክ ይታወቃል። በተለይ የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ቀድሞውንም መዋሀድ ጀምሮ ስለነበር ለምኒልክ አስቸጋሪ አልነበረም ማለት ይቻላል። «ለእኔ ገብርልኝ እንጅ የአባትህን አገር አልነካብህም» የሚለው የምኒልክ አስተሳሰብ፣ በመንቶው ውስጥ የተጠቀሱትን ራሶች ወይም ንጉሶች፣ ማስተባበር በመቻሉ የምኒልክ ስልጣን እየተጠናከረ መምጣቱን ያመለክታል። ራስ መኮንን፣ ሀረርን ያቀኑ የምኒልክ ቀኝ እጅ እንደነበሩ ታሪክ ያስታውሳል። ትግራይን ያስተዳድሩ የነበሩት፣ የዮሐንስ አልጋ ወራሽ የሆኑት፣ራስ መንገሻ ዮሐንስ ነበሩ። ንጉስ ሚካኤል ወሎን፣ ራስ ሀይሉ ተክለ ሀይማት ደግሞ ጎጃምን በማስተዳደር፣ ሁሉም የምኒልክ ደጋፊዎችና የአመት ግብር አስገቢዎች ነበሩ። መንቶው ይህንን የታሪክ እውነታ የሚያመለክት ነው። ይህ የመተባበር ሂደት ወሳኝ ደረጃ ላይ የደረሰው የአድዋ ጦርነት ሲታወስ ነው። አፄ ምኒልክ የክተት አዋጅ አሳውጀው ፊታቸውን ወደ አድዋ ጦርነት ሲያዞሩ፣ ቀድሞ ወደ ጦር ግንባሩ የተጓዘው፣ መንቶ 334 ላይ የተጠቀሱት ራሶችና ንጉሶች የሚመሩት ተዋጊ ሀይል ነበር። መንቶው የምኒልክ መነሻን (የክተት አዋጅ መነሻ) በመግለጽ፣ የጦርነቱን የድል ቦታ (አድዋን) የሚያስታውስ ነው። በወቅቱ የምኒልክ መናገሻ ከተማ እንጦጦ አካባቢ እንደ ነበር ያስታውሳል። በአጠቃላይ መንቶዎቹ ከዮሀንስ እስከ ምኒልክ በነበሩት የታሪክ አመታት ውስጥ የተከናወኑትን ዋና ዋና የታሪክ እውነታዎች የሚያመለክቱ በመሆናቸው፣ የታሪክ ማስረጃዎች ይሆናሉ።

በታሪክ እንደሚታወቀው አፄ ምኒልክ ከሞቱ በኋላ አልጋ ወራሽ ያደረጉት የልጃቸውን ልጅ፣ ልጅ እያሱን ነው። ልጅ እያሱ፣ ከወሎው ንጉስ ሚካኤልና ከምኒልክ ልጅ ከወ/ሮ ሸዋረጋ የሚወለዱ ናቸው። በወቅቱ በዚህ የአልጋ ወራሽነት ስልጣን ላይ ቅሬታ የነበራቸው ወገኖች እንደነበሩ የሚታወስ ነው። ልጅ እያሱም «በሞግዚት አልታገዝም» በሚል የልጅት ይሁን በራስ የመተማመን ስሜት ተነሳስተው፣ በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ የማስተዳደሩን ኃላፊነት እንደጀመሩና፣ ወዲያው ተቃውሞ እየገጠማቸው እንደመጣ ይታወቃል። ስለሆነም፣ የልጅ እያሱን የስልጣን እንቅስቃሴና የተደረገውን የስልጣን ግልበጣ ሁኔታ የሚያመለክቱ ቃልግጥሞችን ቀጥሎ እንመለከታለን።

አርኬ 336 ሰሙ ወይ ሚካኤል ስሙ ወይ ንጉሱ
በርኖሱን ያውጡና ካባውን ይልበሱ
እግዜርም አንድ ነው ይበቃል እያሱ
አርኬ 337 ኸባህር ላይ ሆኖ ያሸካካል ፈረሱ
ኸዲንጋ ላይ ቁሞ ይተኩሳል እሱ
የሰባት ንጉስ ልጅ አባ ጤና እያሱ
በሀውሳ ዘለቀ መሀመድ እያሱ
አርኬ 338 ብላ ጠጣ ብለው ቢሰጡት ንጉሱ
እንጀራውን ጣለው እያሱ ትኩሱ
መንቶ 339 እማ ሸዋ አረጋሽ፣
ከሞተይስ አይቀር በሞተይ በርጉሂ
በድፍን አበሻ ሳይረጭ መርሂ

ንጉስ ሚካኤል በጀግንነቱ የሚመኩበት አንድ የቅርብ ዘመዳቸው ሞተ አሉ። በዚህ ሰው ሞት የተነሳ ብርቱ ሀዘን ተሰማቸውና ጥቁር በርኖስ ለብሰው ያለቅሳሉ። የሀዘናቸው ምክንያት ሁለት ነው ማለት ይቻላል። አንድኛው፣ የስጋ ዘመዳቸው የሆነ ሰው መለየቱ ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ አጋራቸው፣ ባላሟላቸውና የሚተማመንበትን ሰው በሞት በማጣታቸው ነው። በዚያም ሆነ በዚህ፣ ንጉሱ አምርረው ሲያለቅሱ የተመለከተ አልቃሽ አርኬውን ገጠመው ይባላል። የአርኬው ዋና ሀሳብ የተገለጸው በመጨረሻው ስንኝ ነው። ይኸውም ልጅ እያሱ አልጋ ወራሽ ስለሆኑ፣ ለአባታቸው ስልጣን የሚያስፈራ ሁኔታ ሊፈጠር እንደማይችል የሚያመለክት ነው። ልጅ እያሱ በስልጣን እስካሉ ድረስ፣ ንጉስ ሚካኤልም በስልጣን ላይ ይኖራሉ ማለት ነው። አንድ አምላክ (እግዚአብሄር) አለምን እንደሚገዛ ሁሉ፣ ልጅ እያሱም አንዲት ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ይችላሉና ስጋት አይግባዎት፤ እሱ በስልጣን ላይ እስካለን ድረስ የሰውየው ሞት አያሳልም፣ የሚል መልዕክት የተላለፈበት አርኬ ነው።

ከአርኬ 337 እስከ መንቶ 339 ድረስ ባሉት ቃልግጥሞች ውስጥ የተንፀባረቀው ሀሳብ ልጅ እያሱ በስልጣን ሳሉና ከስልጣን ከተባረሩ በኋላ የታየውን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። እንደሚታወቀው ልጅ እያሱ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ አገር አቀናለሁ ሲሉ፣ የቤተ መንግስቱ ትልልቅ ሰዎችና የሀይማኖት አባቶች ሳይቀር ተመካክረው እያሱን ከስልጣን አውርደው፣ ዘወዲቱን እና ደጃች ተፈሪን (በኋላ አፄ ሀይለስላሴ) ወደ ስልጣን በማምጣት ሰበብ ፍጥጫ ተፈጥሯል። ልጅ እያሱ ከሀረር ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ መኤሶ ከሚባል ቦታ

ላይ በውጊያ ስለተሸነፉ በአፋር በኩል ተሻግረው፣ ሀይል አስተባብረው ለመዋጋት ቢሞክሩም፣ ሳይሳካላቸው እንደቀረና፣ አባታቸው ንጉስ ሚካኤልም የወሎን ጦር ክተት ብለው፣ ወደ ሸዋ በመዝመት፣ ሰገሌ ላይ መሸነፋቸውን (Bahru፣ 2002፣ 128) ላይ ይገለፃሉ። ከዚህ በኋላ ልጅ እያሱ ትግራይ ውስጥ ተይዘው እንደታሰሩ ይታወቃል። ቃልግጥሞቹ ይህንን የታሪክ ሂደትና እውነታ የሚገለፁ ናቸው። አርኬ 337 የሚያስታውሰው ልጅ እያሱ ወደ አፋር ተሻግረው ሀውሳ አውራጃ መግባታቸውን ነው። ልጅ እያሱ በወቅቱ ለነበረው የአልጋ ወራሽነት ስልጣን ተገቢ ሰው እንደሆኑ፣ «የሰባት ንጉስ ልጅ» በሚለው ሀረግ ተጠቁሟል።ይህም ከአባት እስከ ቅድመ አያት በሚቆጠር የዘር ሀረግ ውስጥ የንጉስ ዘር መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

ልጅ እያሱ አልጋ ወራሽ ሲሆኑ እድሜያቸው ገና ልጅ ነበር ይባላል። በመሆኑም አገር የማቅናትና የማስተዳደር ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት በሚችሉበት ልምድ ላይ አልነበሩም ማለት ነው። «እንጆራውን ጣለው እያሱ ትኩሱ» የሚለው ስንኝ በእድሜያቸው አለመብሰል ምክንያት በንግስና በመቆየት፣ ከዚህም የሚገኘውን የተደላደለ ኑሮ መኖር አለመቻላቸውን ያሳያል። «እንጆራ» በአገባቡ፣ የተመቼ፣ የተደላደለ ህይወት፣ ማለት ነው። መንቶ 339 ላይ የልጅ እያሱ እናት በስም ተጠቅሰዋል። የልጅ እያሱ እናት ወይዘሮ ሸዋረጋ እንደሆኑ ጳውሎስ (1984፣ 443) ላይ «... ወይዘሮ ሸዋረጋ ለወሎው ራስ ሚካኤል ተድረው በ1888 ዓ.ም ጥር 25 ቀን በወረሂመኖ ተንታ ውስጥ ልጅ እያሱን ወለዱ» ብለዋል። የመንቶው የቁጭት ሀሳብ የተነገረው በመጨረሻው ስንኝ ነው። ይህም «በድፍን አበሻ ሳይረጭ መርሂ» የሚለው ነው። ልጅ እያሱ በእድሜያቸው ገና ወጣት፣ በባህሪያቸው ሀይለኛ ስለነበሩ፣ አገር ለማቅናት በሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ከሚገኙት የባላባት ልጆች ሁሉ፣ ልጅ የመውለድ አገጣሚዎች ነበሯቸው። ይህንን ሁኔታ አንዳንድ ሰዎች አገሪቱን በዝምድና አስተሳስሮ የማገናኘት ዘዴ ነው ይሉታል። በሌላ በኩል ከስልጣን ለመባረራቸው እንደ አንድ ምክንያት የሚቆጠር ነውም ይባላል። ይህ በዝምድና የመተሳሰር ልማድ ቀደም ሲል የነበረ መሆኑ ይታወቃል። ለምሳሌ በቴዎድሮስና በተዋበች፣ በምኒልክና በጣይቱ፣ በተፈሪና በመነን፣ መካከል የተደረጉት ጋብቻዎች ማስረጃዎች ናቸው። የሆነ ሆኖ በመንቶው የተላለፈው ሀሳብ «አገር ማስተዳደሩን እና ማቅናቱን ወደ ጎን ትቶ በመዝናናት ላይ ስላተኮረ ነው እንዲህ የሆነው። ስልጣን ላይ ወጥቶ ከሚባረር ይልቅ ሳይወለድ ቢቀር ይሻል ነበር» የሚል መልክት ነው።

የሚከተሉት ቃልግጥሞች፣ የጁንና ጎንደርን ሲያስተዳድሩ ከነበሩት ባላባቶች መካከል፣ ስለ ራስ ወሌ ብጡል የተገጠሙ ናቸው። ራስ ወሌ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ወንድም ናቸው። አፄ ምኒልክ አርፈው ልጅ እያሱ አልጋ ወረሽ ሲሆኑ፣ እቴጌ ጣይቱ ደስተኛ አልነበሩም። ስለዚህ

ወንድሞቻቸውን አስተባብረው ስልጣን ይገለብጣሉ ተብሎ ስለተፈራ ወንድሞቻቸው ከያሉበት እየተያዙ እንዲታሰሩ ተደርጎ ነበር። ይህንን በሚመለከት አለሙ (2005፣94) ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል። «ልጅ እያሱ ስልጣን ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠሩ ራስ ወሌ ተይዘው እንዲታሰሩ ትዕዛዝ አስተላለፉ። ራስ ወሌ ወደ አንኮበር ተወስደው ታሰሩ፤ እስከ ሰገሌው ጦርነት እዚያው ታስረው እንዲቆዩ ተደረገ።...ራስ ጉግሳ ወሌም አፍቄራ ታስረው ቆዩ። ወደ ፋሊ ተወስደው ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ዘውዲቱ ጋር ተቀመጡ የሰገሌው ጦርነት እንዳበቃ ራስ ወሌ ከልጃቸው አመደ ወሌ ጋር በነፃ ተለቀው ወደ ትውልድ አገራቸው የጁ ተመለሱ...»።

መንቶ 340 የኔታ ራስ ወሌ፣አንኮበር ላይ ሆነው አደገ ራሳቸው
አይቆረጡ እንጂ የስር ቀን አላቸው
መንቶ 341 ሚካኤል በስተቀኝ ገብርኤል በስተግራ
እየሱስ እርፉን ያዘ እስር እንዳይገባ
አርኬ 342 የመርጦው እየሱስ፣
የወልዲያው ገብርኤል፣
እንደመኳንንቱ መሬት ተካፍላችሁ
እንደመሳፍንቱ ካባ (ቀሚስ) ደርባችሁ
እስቲ ወሌን አምጡ ይታይ ጉልበታችሁ

እነዚህ ቃልግጥሞች ከላይ የተጠቀሰውን የታሪክ እውነታ የሚያንፀባርቁ ናቸው። ራስ ወሌ ብጡል ከእህታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጎን ይሰለፋሉ ተብሎ በመፍራቱ ከደብረ ታቦር ወደ ሸዋ መጥተው በቁም እስር እንዲጠበቁ ተደርጎ ነበር። ግጥሞቹ በግዞት በነበሩበት ጊዜ ፀጉራቸው አድጎ ስለነበር ስለ ፀጉራቸው ማደግና አለመቆረጥ የተናገሩ መስሎ፣ የሚታሰሩበት ቀን እንደሚኖር አመልካች ናቸው። «የስር ቀን አላቸው» የሚለው የሚታሰሩበት ጊዜ ይመጣል የሚል ስለሆነ፣ ይህ ሁኔታ በቃልግጥሞቹ ተንፀባርቋል።በስም የተጠቀሱት ቤተክርስቲያኖቹ የሚገኙት ወልዲያ ውስጥ ነው። በቃልግጥሞቹ ውስጥ የቀረበው የልመና ስሜት ግን፣ መላዕክቱን በሚፈታተን ሁኔታ የቀረበ ነው። «እውነት እናንተ ከሰው ልጅ በላይ የሆነ ስልጣን ካላችሁ ራስ ወሌን የሸዋ ሰው በግዞት እንዳያስራቸው አድርጉና ሀያልነታችሁን አሳዩን» የሚል ነው።

የመጨረሻው አርኬ እነዚህኑ ታቦታትና መላዕክት አጥብቆ የመማፀን ልመና የተንፀባረቀበት ነው። በፊውዳል ኢትዮጵያ ዘመን ቤተ ክህነት ሲሶ መንግስትና የራሷ መሬት (ርስት) እንደነበራት የሚታወስ ነው። መልክቱ፣ ታቦቶቹና ቀሳውስቱ የሚደርቡት አልባሳት፣ በምዕመናንና በባላባቱ እየተገዙ የሚሰጡ ስለነበር፣ ይህ ውለታ እያለባችሁ ለምን ዝም ትላላችሁ፣ ካልሆነ እናንተን አናምንም እንደማለት ይመስላል።በአጠቃላይ እነዚህ ቃልግጥሞች፣ «የለመኑትን የማይነሳ፣ የሰጡትን እማይረሳ» እንደሚባለው፣ «በሀይል ከሰው የምትበልጡ ከሆነ ራስ ወሌን ከታሰረበት አስፈቱትና ወደ ሀገሩ ይምጣልን» የሚል ልመና እና የስጋት ስሜት የተገለፀባቸው ቃልግጥሞች ናቸው።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች በማይጨው ጦርነት ጊዜ የታየውን የታሪክ እውነታ የሚያስታውሱትን እንመለከታለን። እነዚህ ቃልግጥሞች፣ በጦርነቱ ላይ ግንባር ቀደም የነበሩት ራሶች በስም ተጠቅሰው ስለምናገኝ ለታሪክ ማገናዘቢያ ሊሆኑ ይችላሉ።

አርኬ 243 ማይጨው ኸበሩ ላይ ተጋግሮ መጌራ
ራስ ካሳ በቀኝ ሸፈራው በግራ
ተካፍለን በላነው በሀይማኖት ካራ
መንቶ 344 ሮብላው ኸደ ዳገት ለዳገት
ሳያወያየነ የዘመኑን ወቅት
አርኬ 345 ጎጃምን ሲከፋው
ትግሬንም ሲከፋው
ጎንደሬን ሲከፋው
ሮብላ ቢሉት ወሎየን ደስ አለው
መንቶ 346 ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ
ኸማይጨው ተነስቶ ሸዋ ገባላችሁ

የማይጨው ጦርነት በኢጣሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገ ጦርነት ነው። ኢጣሊያ በአድዋ ጦርነት ያጣችውን ድልና የተቀበለችውን ሽንፈት ለመበቀል፣ ኢትዮጵያ ደግሞ ያንኑ የድል ታሪክ ለመድገም የተደረገ የታሪክ ተጋድሎና ቅብብሎሽ ነው። በመሆኑም፣ ኢጣሊያ በወልወል የጀመረችው ጠብ አጫሪነት በማጨው ጦርነት የተቋጨ ነበር። ከማይጨው ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያዊያን አርበኞች በአምስት አመት የአርበኝነት ትግል፣ ነፃነትን ለማስለስ ችለዋል። የሰሜኑን የኢትዮጵያ ጦር አሰላለፍ Bahru (2002፣ 154) ላይ፣ «የኢትዮጵያ ሀይል በሶስት

ግንባር ነበር ጣሊያንን መከላከል የጀመረው። በምዕራብ በኩል በራስ እምሩ ሀይለስላሴ የሚመራው የጎጃምና የበጌምድር ጦር ነበር። በመሀል ደግሞ በራስ ስዩም መንገሻና በራስ ካሳ ሀይሉ... በምስራቅ፣ በራስ ሙሉጌታ ይገዙ ይታዘዝ የነበረው ሀይል ነው» ይላሉ። አርኬ 343 ላይ ተገለፀው ሀሳብ ይህን ሚያስታውስ ነው። ራስ ካሳ የጎንደር ባላባትና ገዥ የነበሩና በማይጨው ጦርነትም የዘመቱ ናቸው። «ተካፍለን በላነው በሀይማኖት ካራ» የሚለው ስንኝ፣ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ተነስተን፣ ለሀገራችን ተዋግተናል፣ የሚል የቃል ኪዳን ሀሳብ የተንፀባረቀበት ነው።

በታሪክ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ጦር፣ በወታደራዊ ዘዴ ማነስ፣ በሀይል ሚዛኑና በጦር መሳሪያ ምክንያት፣ ለጊዜውም ቢሆን በጣሊያን ተሸንፏል። አፄ ሀይለስላሴ፣ ከማይጨው ጦርነት መሸነፍ በኋላ ወደ መሀል አገር ሲያፈገፍጉ በደጋማው የሰሜን ወሎ (በምዕራብ) አካባቢዎች አድርገው እንደነበር ይታወቃል። የአካባቢው ሰው እንዴት እንደተመለሱ መረጃ ስለሌለው፣ በአውሮፕላን እንደተመለሱ አድርጎ ነው መንቶ 344 የሚገልጸው። አርኬ 345 ግን ቆየት ያለ ታሪክ የሚያስታውስ ነው። በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት የወሎ አካባቢ ሙስሊም ማህበረሰብ በግድ የክርስትና ሀይማኖት እንዲቀበል ተደርጎ ነበር። ይህ ሁኔታ በተከታዮቹ ዘመናት የቀጠለ ይመስላል። ክርስቲያን መሆን የተለየ ጥቅም የሚያስገኝ እስኪመስል ድረስ በስም በተጠቀሱት (በትግራይ፣ በጎጃም፣ በጎንደር...) አካባቢዎች ተቀባይነት ነበረው። የአርኬው የመጨረሻ ስንኝ ቅኔያዊ በሆነ አገላለፅ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የንጉሱን መሸሽ በደስታ የተቀበለው መሆኑን የሚጠቁም ይመስላል። «ሮብላ ቢሉት» ማለት ሁለት ፍች አለው። አንዱ፣ወደ እስልምና ተመለስ፤ እንደ ጥንቱ ሁን፤ ማለት ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ደግሞ በአውሮፕላን መሸሻቸውን ሲሰማ ተደሰት፣ ማለት ነው። የመጨረሻው መንቶ የንጉሱን «መሸሽ» የአካባቢውን ሰው የተቃወመበት ሀሳብ የተገለፀበት ነው። የአፄ ሀይለ ስላሴ የፊረስ ስም «ጠቅል» ይባላል። እንደ ልማዱ ጀግኖች በፈረሳቸው ስም ይጠሩ ስለነበር፣ አፄ ሀይለ ስላሴም አባ ጠቅል ይባሉ ነበር። የፈረሳቸውን ስም መነሻ አድርጎ ነው፣ መሸሻቸው በተቃውሞ መልክ የተነገረው።

ከአምስት አመት የአርበኝነት ተጋድሎ በኋላ፣ አፄ ሀይለ ስላሴ፣ ከስደት ወደ ኢትጵያ የተመለሱት በእንግሊዞች አጋርነት እንደነበር ይታወሳል። ከአድዋ ድል በኋላ በጣሊያን ቁጥጥር የነበረችው ኤርትራ፣ እንደገና ጣሊያን ከኢትዮጵያ ሲባረር በእንግሊዝ ሞግዚትነት ወደቀች።አፄ ሀይለስላሴም ሁኔታውን በጥበብ ይዘው በመጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ እንድትቀላቀል

አድርገዋል። በወቅቱ እንግሊዝ ኢትዮጵያን ደግፋ ያደረገችውን ውጊያና ሌሎችም ሁኔታዎች፣ በሚከተሉት ቃልግጥሞች ተንፀባርቀው ይገኛሉ።

መንቶ 347 አባጠቅል ሀይሌ የጦሩ ገብሬ
አቆላልፎ ነዳው ነጩን በነጭ በሬ
መንቶ 348 አንተ ያገሬ ሰው ወሬህን አታውራ
እንቢ ብህ እንዲሁ ይሰድህል ናኮረ
መንቶ 349 ጠቅል ባይወለድ እንግሊዝ ባይደርስ
ተፈጥመን ነበር ላርብና ላሙስ

እነዚህ ቃልግጥሞች፣ አፄ ሀይለ ስላሴ ከሰደት ከተመለሱ በኋላ፣ በሀገሪቱ የነበረውን እንቅስቃሴ የሚያስታውሱ ናቸው። «ከነፃነት» በኋላ ባሉት አመታት የአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በእንግሊዞች እጅ የመውደቅ አጋጣሚ ተፈጥሮ ስለነበር፣ ጣሊያኖችና እንግሊዞች ተዋግተዋል ይባላል። መንቶ 347 የሚያስታውሰው ይህን የታሪክ አጋጣሚ ነው። «በነጭ በሬ» የተመሰሉት ጣሊያኖችንና እንግሊዞች ናቸው። ሁለቱም በኢትዮጵያ ላይ የየራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት በሚታገሉበት ወቅት፣ ንጉሱ አጋጣሚውን ተጠቅመው፣ ማለትም የእንግሊዝን ድጋፍ በመጠቀም ጣሊያንን ለማስወጣት ያደረጉትን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚያመለክት ነው። ጣሊያኖች የሰሜኑን ክፍል ተቆጣጥረው በነበረበት ጊዜ፣ እነሱን የሚቃወማቸውን ማንኛውንም ግለሰብ እየያዙ ቀይ ባህር ውስጥ «ናኩራ» እምትባል ስፍራ ያስሩ ነበር ይባላል። የቃልግጥሞቹ ሀሳቦች በጣሊያንና በእንግሊዝ መካከል አትግቡ። ሁለቱም ብልጦች ናቸው፤ እያደረጉ ያለው እንቅስቃሴ «ብልጥና ምስጥ...» እንደሚባለው አይነት ነው፤ የሚል ማስጠንቀቂያ የተላለፈባቸው ናቸው። እንግሊዞች ለጥቅማቸው በማሰብ ያደረጉትን «ድጋፍ ግጥሞቹ አወንታዊ በሆነ መንገድ አንፀባርቀውታል ማለት ነው።

በምዕራፍ ሁለት፣ በማህበረሰባዊ ዳራው ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ አፄ ሀይለስላሴ፣ ልጅ እያሱን ገልብጠው ወደ ስልጣን እንደወጡና፣ እስከ 1966 አብዮት ድረስ የዘለቀ፣ ዘውዳዊ አገዛዝ በሀገሪቱ ሰፍኖ እንደነበር ይታወቃል። በተለይ 1920ዎቹ በነበረው የስልጣን ዘመናቸው፣ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ሊነሱ ይችላሉ ተብለው የሚፈሩ እንቅስቃሴዎችን በሀይል የመቆጣጠር ሁኔታ ነበር። ከነዚህ መካከል በራያ አካባቢ ይደረግ የነበረውን መጥቀስ ይቻላል።ይህ አካባቢ፣ በልዩ ልዩ አስተዳደራዊ ምክንያቶች በቅርብና በርቀት ከነበሩ አካላት ጋር የአካባቢው ማህበረሰብ ግጭት ውስጥ ይገባ እንደነበር በሚከተሉት ቃልግጥሞች ተንፀባርቆ

እናገኛለን። የመጀመሪያዎቹ መንቶዎች ከየጁ አስተዳዳሪዎች ጋር የነበረውን ያስታውሳሉ፣ ተከታዮቹ ደግሞ ከአፄ ሀይለ ስላሴ ጋር የነበረውን ይገልፃሉ። ቃልግጥሞቹን እንመልከት!

አርኬ 350 መገን ፈንታ ኩቢ ሮብሶ ደንጎራ
ምን አገናኛቸው (ከኦሮሞ)[19] ጋራ
እንኳን የኦሮሞ ቢመጣ ፈረንጅ
ዲቡን ጠጋ ብሎ ይታኮሳል እንጂ
ስፍራውን አይለቅም ያባ ጠጣው ልጅ
መንቶ 351 ግዛ ግዛ ብለው ቢሰጡት አገር
ቀንበር ተሸከመ ከበሮቹ ጋር
መንቶ 352 ይኸ የራያ ሰው እርሻ አያውቅም ነበር
ወንዱ አመደ ወሌ ጠመደው በቀንበር
መንቶ 353 ሰማይ ለእንግዝ ነው መራት ለስላሴ
ራያና አዘቦ አቤት አለ ደሴ

በታሪክ እንደሚታወቀው፣ ራስ ወሌ ብጡል ከሸዋ እስር ተፈትተው ወደ የጁ እንደተመለሱ፣ አካባቢውን ማስተዳደር ይቀጥላሉ። በመሆኑም፣ ወደ ራያ አካባቢዎች ሰዎችን እየሾሙ መላክ ሲጀምሩ፣ በአካባቢው በነበሩትና ሹመት ይገባናል በሚሉ ባላባቶች፣ እንቅፋት ይገጥማቸዋል። እነዚህ ባለባቶች ተሹመው የሚላኩትን ሰዎች በጦርነት እየተዋጉ ማባረር ይጀምራሉ። ራስ ወሌም፣ ሁሉንም እስኪቆጣጠሩ ድረስ በተደጋጋሚ ተዋጊ በመላክ ውጊያ ያደርጋሉ። በነበረው የሰው ሀይል ብዛትና በመሳሪያ ሁኔታ በመጨረሻው፣ የራስ ወሌ አሸናፊነት ተረጋገጠ። ይህ ታሪካዊ እውነታ በአርኬ 350 ውስጥ ተንፀባርቆ ይገኛል። በግጥሙ ውስጥ ፈንታ ኩቢና ረብሶ ደንጎራ የሚሉ ስሞች ተጠቅሰዋል። ፈንታ ኩቢ ቀደም ሲል በአፄ ዮሐንስ ዘመን ጊዜ የተገደሉት የአባቦና ኩቢ ልጅ ናቸው ይባላል። ረብሶ ደንጎራ ደግሞ፣ የፈንታ ኩቢ የጦር አጋር እንደነበሩ ይነገራል። እነዚህና ሌሎች ስመ ጥር የነበሩ የራያ ባላባቶች፣ በራስ ወሌ ጦር ተሸንፈው ተገድለዋል፤ አንዳንዶቹ ተማዘዋል። የአርኬው የመጨረሻ ስንኝ «ስፍራውን አይለቅም ያባ ጠጣው ልጅ» ሲል «አባ ጠጣው» የተባሉት አባቦና ኩቢ ሲሆኑ፣ ስፍራውን

[19] በቅንፍ ውስጥ ያለው ሀረግ ሌላ ነው።ቃሉ በአሁኑ ጊዜ እንደ ፀያፍና ስድብ ስለተቆጠረ ለውጨዋለሁ። በመሰረቱ የተለወጠው ቃል በራያ አካባቢ አሁንም ድረስ ያለው ፍች "የባላባት ልጅ፣ የሀብታም ልጅ፣ በሁለት እጅ የማይነሳ የጌታ፣ የትልቅ ሰው ልጅ፣" እንደማለት ነው እንጂ እንደ ስድብ (በፀያፍ) አይታወቅም!!

አይለቅም የተባሉት፣ ደግሞ ፈንታ ኩቢ ናቸው።በወቅቱ የነበረው ችግር «የራያ አካባቢ መተዳደር ያለበት በፈንታ ኩቢ ነው እንጂ፣ በየጁ የራስ ወሌ ሹሞች አይደለም» የሚል ነው።

ቀጥሎ ባሉት መንቶዎች እንደሚስተዋለው፣ በፈንታ ኩቢ የሚመራው የራያ ባላባት ጦርና በራስ ወሌ የሚታዘዘው «የመንግስት» ሀይል ባደረጉት ውጊያ፣ የባላባቱ ጦር ተሸንፏል። ከድሉ በኋላ ዋናዎቹ ባላባቶች በግዞት ወደ ሀረር ተወስደዋል። ይህ ሁኔታ በመንቶ 251 እና 252 ተገልጿል። በመንቶዎቹ እንደተጠቀሰውና በአፈታሪክ እንደሚወራው፣ የተማረኩትን ሰዎች እንደ በሬ ቀንበር ጭነውባቸው ነበር ለግዞት የወሰዷቸው ይባላል። ይህንን ሁኔታ የተመለከተው የአካባቢው ሰው፣ መንቶዎቹን ሊፈጥራቸው እንደሚችል ይታሰባል። መልክቱም «የራያ ባላባቶች አላርፍ ብለው ስላስቸገሩ ተገቢውን ቅጣት ተቀጡ፣ እስከ መጨረሻው እንዲንበረከኩ»፣ ሆነ ማለት ነው። በታሪክ እንደሚታወቀው የጣሊያን ወረራ ሲጀምር በግዞት ወደ ሀረር የተወሰዱት ፈንታ ኩቢ ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው በፊታውራሪ ማዕረግ ጦርነቱን እንዲካፈሉ ተደርጓል።

በመንቶ 353 ውስጥ የተንፀባረቀው ሀሳብ ከማዕከላዊ መንግስት ጋር በተፈጠረ ግጭት ሳቢያ የታየውን እውነታ የሚያመለክት ነው። አፄ ሀይለስላሴ ከስደት ተመልሰው ስልጣነ መንግስታቸውን በሚያጠናክሩበት ጊዜ ችግር እየፈጠሩ ያስቸግሯቸው ከነበሩት አካባቢዎች መካከል አንዱ፣ የራያ አካባቢ የገበሬዎች አመፅ ነው። ይህ አመፅ በተለያየ ጊዜ መልኩን እየለዋወጠ እስከ 1968 ዓ/ም ድረስ የዘለቀ ነው። በታሪካዊ ዳራው እንደተጠቀሰው የመጀመሪያው የወያኔ እንቅስቃሴ ተጀመረ እሚባለውም እዚሁ አካባቢ ነው። በወቅቱ የነበረውን የገበሬዎች አመፅ ንጉሱ በቀላሉ ለመቆጣጠር ባለመቻላቸው የእንግሊዝን የአየር ሀይል ድጋፍ እንዳገኙ መረራ (2008፣22) ላይ፣ «... የኦሮሞ ግንድ ያላቸው የራያና አዘቦ ገበሬዎችን አመፅ...ንጉሱ የተቆጣጠሩት በእንግሊዞች አውሮፕላን እርዳታ ጭምር ነው... » ይላሉ። የመንቶው የመጀመሪያ ስንኝ ይህንን ያመለክታል። «ሰማይ ለእንግሊዝ ነው» ሲል በአውሮፕላን እየመጡ ይደበድቡ የነበሩት እንግሊዞች ናቸው ማለቱ ነው። በመሬት ይደረግ የነበረው የንጉሱ እግረኛ ጦር ደግሞ፣ «መንገድ ለስላሴ» በሚለው ተገልጿል። «ለስላሴ» ማለት ለሀይለ ስላሴ፣ ለማለት ነው። ለዜማው ሲባል ቃሉ እንደተዋቀረ ማስተዋል ይቻላል። ንጉሱ ይህንን ካደረጉ በኋላ፣ ሁሉንም የራያ አካባቢዎች በወሎ ጠቅላይ ግዛት ስር እንደሆኑ ስላደረጉ ይመስላል «ራያና አዘቦ አቤት አለ ደሴ» የሚለው ስንኝ የገባው።

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ በቀረበው ትንተና እና ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ቃል ግጥሞቹ በአካባቢው የነበረውን የአንድ ምዕተ አመት የሚጠጋ የታሪክ እውነታና እንቅስቃሴ ለማሳየት የሞከሩ ናቸው። በተለይ አንዳንድ ገጠመኞችን በውሁፍ ማስፈር ባልተለመደበትና ዛሬም ቢሆን ይኸው በቀጠለበት ሁኔታ፣ እነዚህ ቃልግጥሞች ጠቃሚ የታሪክ ሰነዶች በመሆን የነበረውን ታሪካዊ እውነታ ለትውልድና ለታሪክ ማስተላለፍ ችለዋል ማለት ነው።

6.2.7 ከድርቅና ከርሀብ ጋር ተያይዞ የታየውን ሁኔታ የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉት መንቶዎችና አርኬዎች ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በተለያዩ ጊዜያት የተከሰቱትን የርሀብ ወቅቶች የሚያንፀባርቁ ናቸው። ምድቡ ሶስት ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ነው። ድርቅ ጠቋሚ ወይም የዝናብ አለመኖርን የሚያመለክቱ፣ እሱን ተከትሎ የተከሰተውን የምግብ ችግርና፣ ከዚያም ወደ ደሀና ቀን መሸጋገርን፣ ያለፈውን በማስታወስ፣ የሚገልፁ ይዘቶች ያሏቸው ቃልግጥሞች የተደራጀበትነው:: በእያንዳንዱ ንዑስ ምድብ ካሉት ግጥሞች ውስጥ የሚበዙት የርሀቡን ወቅትና ድርቁ ካለፈ በኋላ የታየውን ሁኔታ የሚያንፀባርቁት ናቸው:: በምድቡ ውስጥ በአጠቃላይ ወደ 39 ያህል ቃልግጥሞች ተካትተዋል።

በምዕራፍ ሁለት ላይ፣ ለማብራራት እንደተሞከረው፣ በተለይ በሰሜን ወሎ አካባቢዎች፣ በአጠቃላይ በመላ ሀገሪቱ፣ የታዩት የድርቅና የርሀብ አደጋዎች፣ ዜጎችንና መንግስትን ለፈተና ዳርገዋል፤ ለውድቀት አብቅተዋል። በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍሎች የርሀብ ሁኔታ መታየት የጀመረውም ከ19ኛው ምዕተ አመት አጋማሽ ጀምሮ እንደነበር በታሪክ ይታወቃል። ለምሳሌ፣ በምኒልክ ዘመነ መንግስት ጊዜ የታየው ክፉ ቀን ከ1880 እስከ 1884 ዓ.ም. ለአምስት አመታት የቆየ እንደ ነበር (ጳውሎስ፣ 1984፣ 126) ይገልጻሉ። ይህ የርሀብ ዘመን የማይበላ ነገር የተበላበት እንደነበር ይታወሳል። በ1916 ዓ/ም የተከሰተው የአንበጣ መንጋና የወፍ ወረራ፣ የ1965/66 ዓ.ም የወሎና የትግራይ አካባቢዎች ርሀብ፣ የ1976/77 የሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የድርቅና የርሀብ አመታት፣ ዜጎችን ለእልቂት ዳርገዋል፤ የአገሪቱን ገፅታ አበላሽተው አልፈዋል። ከዚህ ቀጥሎ በሁለቱ የርሀብ ዘመናት በታየው ሁኔታ ላይ ተመስርተው የተፈጠሩ ቃልግጥሞችን እንመለከታለን ።

6.2.7.1 ድርቅ ጠቋሚ ቃልግጥሞች

የ1965/66 ዓ.ም የድርቅ ዘመን በባህሪው ዝናብ በማጠሩ ምክንያት የተከሰተ ነበር ማለት ይቻላል። ማሳው ሁሉ በዘር ተሸፍኖ፣ ቡቃያው በቅሎ፣ ማሽላው አድጎ፣ ለረገዛና ለወለዳ በሚደርስበት ወቅት የሚያስፈልገውን ያህል ዝናብ ሳያገኝ ይቀራል። በዚህ ጊዜ ጤፉም ማሽላውም ባለበት ይጠወልጋል። እየደረቀ ሲሄድ የከብት ቀለብ ብቻ ይሆናል። በወቅቱ የአርሶ አደሩ የእንስሳት ሀብት በድርቁ አልተጎዳም ማለት ነው። የ1976/77 ዓ.ም ርሀብ ግን የተለየ ነው ማለት ይቻላል። ዝናብ ይቅርና የደመና ምልክት በአካባቢው አልታየም። ከሰው ርሀብ ይበልጥ የእንስሳት ርሀብና እልቂት ክፉኛ አካባቢውን ጎድቶት አልፏል። በተለይ በራያ አካባቢ የነበረው የእንስሳት እልቂትና የሰው ችግር ከፍተኛ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ በሁለቱ የድርቅ ጊዜያት ዋናው የርሀብ ወቅት ከመግባቱ በፊት ጠቋሚ ምልክቶችን ለማሳየት የሞከሩትን ቃልግጥሞች እንመለከታለን!

አርኬ 354 ምን ያለ ቀን መጣ የተሰባበረ
ያገሬ ገበሬ እጅግ ተቸገረ
የተዘራው ሁሉ በሜዳ ላይ ቀረ
መንቶ 355 የቆላ ማሽላ የጌታ ልጅ መሳይ
ተሸፋፍኖ ቀረ ዛላውን ሳያሳይ
መንቶ 356 በፍላቴ በፍላቴ
ኮርትም ሆነ እራቴ
መንቶ 357 ጎበና በሞተ ባመቱ
የሰው ሁሉ ኮርትም ሆነ ራቱ
መንቶ 358 ያ ስምንተኛው ሺ አልቀረም ደረሰ
መሬት ምጣድ ሆና ያዳም ልጅ ታመሰ
መንቶ 359 ከሰኔ ጀምሮ መሬት ሰማይ አየች
እባክህ ደመና ዝናብ ጣል እያለች
መንቶ 360 ካሳ ሊቀመንበር ፀሀፊው መለሰ
አንድ ዝናብ ሳይጥል መስከረም ደረሰ

በመንቶ 356 ና 357 ውስጥ የሰዎች ስም ተጠቅሷል። አንድኛው ፍላቴ ሲሆን ሁለተኛው ጎበና ነው። ፍላቴ በ1965/66 ዓ.ም የራያና ቆቦ አውራጃ አስተዳዳሪ ነበሩ የሚባሉ ሰው

ናቸው። ጎበና ደግሞ የየጁ ባላባትና አርበኛ የነበሩ፣ በጊዜው በራያ ገበሬዎች አመጽ የተገደሉ ናቸው። «በፍላቱ ...» የሚለው ማስተላለፍ የፈለገው ሀሳብ በእሳቸው አስተዳዳሪነት ጊዜ የአካባቢው ህዝብ ለርሀብ ተጋለጠ ለማለት ነው። «በእያሱ ዳቦ ነው ትራሱ»፣ «በተፈሪ ጠፋ ፍርፋሪ» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለ ጎበና የተነገረው ግን በሁለት መንገድ ነው፤ አንድኛው፣ የራያ ሰው ደጃጅ ጎበናን አምፆ መግደሉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ፣ ድርቁ የታየበትን አመት ማመልከት ነው። የድርቁን ጊዜ (አመት) በትክክል ማስታወስ በሚቸገርበት ጊዜ በወቅቱ የታየውን ክስተት አስታውሶ መናገር የተለመደ ስለሆነ ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው የ1965/66ቱ የርሀብ ጊዜ መሰረታዊ ችግሩ የዝናብ እጥረት ነበር። ከአርኬ 354 መንቶ 357 ባሉት ቃልግጥሞች የተንፀባረቀው አብይ ሀሳብም ይኸው ነው። የወቅቱን አስቸጋሪ ሁኔታ «የተሰባበረ» በሚለው ቃል ተገልጿል። ይህም ማለት ከዝናቡ ወጣ ገባነትና አነስተኛ መሆን ምክንያት፣ የተዘራው እህል አንዳንድ ቦታ በቅሎ መቅረቱን፣ አንዳንድ ቦታ ደግሞ ጭራሽ የተዘራው ዘር ሳይበሰብስ መሬት ላይ እንደተበተነ የቀረበትን ሁኔታ ለማመልከት ነው። በሰሜን ወሎ ቆላማው አካባቢ ማሽላ የሚዘራው ከሚያዚያ አጋማሽ እስከ ግንቦት መጀመሪያ ባለው ሳምንት ነው። በአፍላ በቆሎ ክረምት እስቲገባ ድረስ ሳይደርቅ የመቆየት ሀይል አለው። እስከ ነሀሴ ወር መጨረሻ ድረስ ማሽላ መውለድ ይችል ነበር። «የቆላ ማሽላ» ወይም «የራያ ማሽላ ... ተሸፋፍኖ ቀረ...» የሚለው ማሽላው በዝናብ እጥረት ምክንያት ማርገዝ እንደጀመረ ሳይወልድ እንደቀረ የሚያመለክት ነው። ማሽላ አድጎ ፀሀይ ሲያጋጥመው ወይም ሲመቸው የታችኛው የአደገው ክፍል ልክ እንደ ጥንቅሽ ይጣፍጣል፤ ይህ አገዳ በአካባቢው አጠራር «ኮርትም» ይባላል። በድርቁ መግቢያ ላይ የአካባቢው ሰው ይህንን አገዳ እየቆረጠ እንደ ጥንቅሽ ይጠቀም ስለነበር ያንን ለማመልከት ነው ግጥሞቹ የተፈጠሩት። በመንቶ 356 እና 357 በአፈታሪክ ሲወራ እንደኖረው፣ «በስምንተኛው ሺ አለም ከባድ ችግር ውስጥ ትገባለች» ይባላል። ይህ ዘመን የአለም ፍፃሜ እንደሆነ በተለያየ አጋጣሚ ሲነገር መቆየቱ ይታወሳል። ይህ የተፈራው የአለም ፍፃሜ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ በሰባ ሰባቱ የርሀብ ጊዜ እንደደረሰ አድርጎ ተረድቶታል ማለት ነው። የነበረው የፀሀይ ሙቀት፣ እንደ ብረት ምጣድ የጋለ፣ ሰማይ መሬቱ የተቃጠለ፣ ስለነበር ከዚህ መአት ተርፎ የሚኖር የሰው ልጅ ሊኖር እንደማይችል የተፈራበት ጊዜ ነበር። መንቶ 358 ይህንን ፍርሀትና ጭንቀት ለማስተጋባት የሞከረ ነው። በመንቶ 359 እና 360 ውስጥ የተንፀባረቀው ሀሳብ ከላይ ከቀረቡት ጋር ተመሳሳይ ነው። በጤፍ መዝሪያው ወራት የዝናብ ችግር እንደተፈጠረና፣ በዚህም ሳቢያ የሰው ልጅ ልመና «መሬት ሰማይ አየች» በሚለው ሀረግ እንደተገለፀ ነው። በስም የተጠቀሱ ግለሰቦች ቢኖሩም የመንቶው ሀሳብ በእነሱ ጊዜ

ዝናብ ያልጣለ መሆኑ፣ እንደ «ገደ ቢስ» ሊታዩ እንደሚችሉ አመላካች ነው። ይኸውም በእናንተ የስልጣን ዘመን ህዝቡ በድርቅ ተመታ፤ ስርሀብ ተጋለጠ፤ የሚል ፍች ያለው ነው።

ከላይ የቀረቡት ቃልግጥሞች የሁለቱን የድርቅ ጊዜያት (1965/66 እና 1976/77 ዓ/ም) በሚመለከት ክፉ ቀን ሊመጣ እንደሚችል አስቀድመው የጠቆሙ ናቸው። በዚህም ማህበረሰብ በወቅቱ በታየው የዝናብ መጥፋት ምክንያት የተሰማውን ጭንቀት፣ ፍርሀትና ስጋት፣ ለማሳየት የቻሉ ናቸው። የድርቁን ሁኔታና ተከትሎ የሚመጣውንም የርሀብ ሁኔታ አመላካች ነበሩ ማለት ይቻላል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የዝናብ እጥረቱን ወይም ጨርሶ መጥፋቱን የተገነዘበው የአካባቢው ማህበረሰብ ሁኔታውን በቃልግጥሞቹ ውስጥ እንዴት እንዳንፀባረቀው እንመለከታለን!

6.2.7.2 የርሀብ ወቅት ቃልግጥሞች

የርሀብ ወቅት ቃል ግጥሞች ማለት ማህበረሰቡ ድርቅ እንደገባ አውቆ፣ የነበረውን እርሾ ከጨረሰ በኋላ፣ በታየው አሰቃቂ ሁኔታ የመንግስትን እርዳታና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች አስመልክቶ የተፈጠሩትን የሚመለከት ነው። እነዚህ ቃልግጥሞች የድርቁ አስከፊነት፣ በዚሁ ሳቢያ የታየው የሞራል ውድቀት፣ ስደትና ሞት የተንፀባረቀባቸው ናቸው። ቀጥሎ ያሉት የድርቁን አስከፊነት የሚያመለክቱ ናቸው።

መንቶ 361 አንተ ሰባ ሰባት አንተማ ይብላኝ
ልጅ አልበቃ ብሎ ሚስቴን ታስቀማኝ
አርኬ 362 አንተ ሰሰባት ያንተ ስራህማ
አይናችን እያየ ጆሮም እየሰማ
የሰው ለጅ ከውሻ አጥንት ሲቃማ
አርኬ 363 ጌታው አቶ እግዚሀር
ከላይኛው አገር
ድግስ አስደግሶ
ዳሱን አሰርቶ
የከሳ የከሳው ኸደ አሉ ተጠርቶ
መንቶ 364 በአላማጠው ካሳ፣በቆቦውም አጥሬ
ህዝቡ ተላለቀ በቅጭም ጥሬ

መንቶ 365 በቁጥጥሮቹ በነጫኔ መርሻ
በሬ እስተገበሬው ገባ አሉ ኮምበልሻ
አርኬ 366 መቶ መቶ ኬሻ እንዳልተወቃብሽ
በጭንቀት መኪና እንዳልተነዳብሽ
ለምለሚቱ ቆቦ ቅጭሞ ፈላብሽ
መንቶ 367 እንጀራው አለወጥ ወጡ የዘይት
በንጉሴ ጊዜ የለም እመቤት

መንቶ 361 የሰባ ሰባትን ድርቅ እንደሰው ይወቅሰዋል። የወቀሳው ምክንያት የልጅና የሚስት መቀማት ነው። ቅሚያው አንድም በሞት፣ አለያም በዝሙት ነው። የልጅ ቅሚያ ሞት ሲሆን የሚስቱ ግን ሁለት ሊሆን ይችላል። አንደኛው የሞት ቅሚያ ሲሆን፣ ሁለተኛው በሌላ ወንድ መቀማት ነው። ሁለቱም ለአካባቢው ሰው የቁም ሞትና ከፍተኛ ውርደት ናቸው። ለዚህ ውርደት የዳረገው ደግሞ የሰባ ሰባት ርሀብ ነው። መንቶ 362 የሰው ልጅ ከሰውነት በታች ሆኖ የታየበት ነው። የሰው ልጅ በሀይማኖትም ይሁን በባህል የሚለያይበት ሁኔታ አለ። ከዚህ መካከል አመጋገቡ እንደ የባህሉ የተለያየ ነው። የሞተ እንስሳ ስጋ መብላት በባህልና በሀይማኖት አይፈቀድም። በግጦሙ ውስጥ የተጠቀሰው ሀሳብ ግን የሰው ልጅ ከሰውነት በታች ወርዶ ከማይመስሉት እንስሳት ጋር የማይሆን ነገር ሲያደርግ ነው። ይህንን እንዲያደርግ ያስገደደው ደግሞ የሰባ ሰባት ርሀብ እንደሆነ ነው ።

አርኬ 363 ግን በተለየ ሁኔታ የቀረበ ነው። በአርኬው ውስጥ እግዚሀር የምድር ጌቶችን ወክሎ ነው የቀረበው፤ የምድር ጌቶች በሀይማኖትም ይሁን በባህል ድግስ ደግሰው ደሀውን ማብላትና ማጠጣት የተለመደ ተግባራቸው ነበር። ለእግዚሀር የተቀጠለት ቅጥያዎች /ጌታው እና አቶ) ለሰው ልጅ እንጂ ለሱ የሚሰጡ አይደሉም። የገጣሚው ስሜት የምድር ጌቶች ባላቸው አቅም ደግሰው ሲያበሉና ሲያጠጡ አይቶ፣ እሱ ግን ከዚህ በተቃራኒ የተራበውንና የተጠማውን የህብረተሰብ ክፍል በሞት ጨረሰው የሚል መልክት ያለው ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው በአካባቢው ማህበረሰብ በአጠቃላይ፣ በአንዳንድ ባህሎች በተለይ፣ የመሪዎች ሁኔታ ከመልካም ወይም ከመጥፎ ነገሮች ጋር እየተያያዙ ይወደሱበታል ወይም ይነቀፉበታል። መንቶ 364 ላይ ካሳና አጥሬ የሚባሉ ሰዎች ስም ተጠቅሷል። ካሳ የአላማጣ፣ አጥሬ ደግሞ የቆቦ ወረዳ፣ አስተዳዳሪዎች የነበሩ ናቸው። በእነዚህ ሰዎች የአስተዳደር ጊዜ ድርቅ በመግባቱ ማህበረሰቡ እንደ ገደ-ቢስ ቆጥሯቸዋል ማለት ነው። «ቅጭሞ» ማለት

በደርግ ጊዜ የወታደሮች ወጥ የታሸገበት ትንሽ ቆርቆሮ ናት። ወታደሩ ምግቡን ከተመገቡ በኋላ ይችን ቆርቆሮ ይጥሏታል። የአካባቢው ማህበረሰብ በጣሳ እየሰፈረ የሚሸጠው ወይም የሚሸምተው እህል ባለመኖሩ፣ እንደ እህል መስፈሪያ የምታገለግል ነበረች። በቅጭሞ የተሸመተው እህል ለቤተሰብ የማይበቃ ስለነበር ነው፣ «ህዝቡ ተላልቀ በቅጭሞ ጥሬ» የተባለው። የርሀቡ ሁኔታ እየከፋ ሲመጣ የራያ ቆቦ አካባቢ ማህበረሰብ የነበሩትን የቀንድ ከብቶች በወቅቱ ኮምበልቻ ለነበረው የስጋ ፋብሪካ ወስዶ በርካሽ ይሸጥ ነበር። በመንቶ 365 የተጠቀሰው ይኸው ሀሳብ ነው። በመጀመሪያው መንቶ የተጠቀሱት ሰዎች፣ በዚያ ጊዜ የገበሬ ማህበር አመራር የነበሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች አርሶ አደሩን በመቀስቀስ ለፋብሪካው ከብቶቹን እንዲሸጥ ያደርጉ ስለነበር ሁኔታውን እንደ ግዴታ አድርጎ የመመልከት አስተሳሰብ የተንፀባረቀበት ነው።

በ1970ዎቹ ጀምሮ የቆቦ ወረዳ አርሶ አደር እንደ ትርፍ አምራች ስለነበር፣ ገባያው ጥጋብ ነበር። የእርሻ ሰብል ገባያ ድርጅት (እስገድ) ይባል የነበረው ሰኞ ቀን ሲገዛ የዋውን እህል (ጤፍና ማሽላ) እስከ እሁድ ድረስ በመኪና ያጓጉዝ እንደነበር ይተወሳል። አርሶ አደሩም በከፍተኛ ሁኔታ ያመርት ስለነበር ገባያው ሙሉ ነበር። ይህንን ለማስታወስ ነው «መቶ መቶ ኬሻ እንዳልተወቃብሽ» በማለት የተገለጸው። የመንቶው ሀሰብ ግን ይህ አይደለም። አካባቢው እጅግ በመቸገሩ ምክንያት እህል ገባያ ውስጥ ጠፋ፤ ያለውም ለህይወት ማቆያ በምትሆን መስፈሪያ (ቅጭም) ከመካፈል ያለፈ የመግዛትም ሆነ የመሸጥ ችግር መከሰቱን ማመልከት ነው። መንቶ 367 ላይ የተነሳው ሀሳብ ለየት ያለ ነው። ለየት የሚያደርገው በወቅቱ በተለያየ መንገድ (በእርዳታ፣ በነጋዴ) ገባያ ላይ የነበረው እህል ቀይ ማሽላ ነው። ይህ የማሽላ አይነት ዱቄቱ ቀይ ነው። ተቦክቶ ሲጋገር እንጀራው አይን የለውም ። እንጀራውን ለመመገብ ወጥ ሲፈስበት ወይም ሲያይዙት በአይኑ ስለማይገባ በቀላሉ አይደርስም ነበር። በወቅቱ ይህን የእንጀራ አይነት «አለወጥ» የሚል ስም ወጥቶለት ነበር። ሴቶችም ሲጋግሩት እጅግ ይቸገሩ ስለነበር፣ ሙያቸው ፈተና ላይ ወድቋል። የነበረው ማጣፈጫም ዘይት ብቻ ነው። በዘይት ብቻ የተሰራ ወጥ በቅቤ እየተሰራ ለነበረው ሴት ፈታኝ እንደነበር የሚያስታውስ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቃልግጥሞች የርሀቡ ሁኔታ እየከፋ በመሄዱ፣ በወቅቱ የነበረው መንግስትና የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፣ ያደረጉትን እንቅስቃሴ የሚያመለክቱ ናቸው። በነዚህ ቃልግጥሞች ሰፈራና የእርዳታ አሰጣጡ ሁኔታ ጎልቶ የተንፀባረቀባቸው ስለሆኑ፣ በወቅቱ የነበረው አስከፊ ሁኔታ ለመረዳት ያግዛሉ።

መንቶ 368 የቀይ መስቀል ዱቄት በልቼ በልቼ
ልሄድ ነው ሰፈራ ዘመዶቼን ትቼ
መንቶ 369 ያገሬ ነጭ ጤፍ፣ያገሬ ማሽላ፣አይዞህ አትቆጣ
እዘራህ አለሁኝ ምናልባት ብመጣ
መንቶ 370 ስንዴ ዝናብ ጥሎ ጎርፉ እየደነፋ
ምነው በኛ መንደር ትንሽ ሳያካፋ
አርኬ 371 ቀይ መስቀል ካፊያ ነው
ኮሚሽን ቅቅት ነው
አንጆት የሚያርሰው አባ ዝናቡ ነው
አርኬ 372 ይኸ የየጁ ሰው ፣ይኸ የራያ ሰው
እስላሙም፣አላህ አላህ ይላል አላህ የት ተገኝቶ
ክርስቲያኑም፣እግዜር እግዜር ይላል እግዜር የት ተገኝቶ
አማሪካን አገር ግብርናውን ገብቶ

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተከስቶ ለነበረው የሰባ ሰባት ድርቅ አንደኛው መፍትሄ የነበረው የተጎዳውን የማህበረሰብ ክፍል ከነበረበት አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ማስፈር ነበር። ሰፈራው በመንግስት ደረጃ የታቀደ ቢሆንም፣ ተጎጂ የነበረው ህዝብ ተጨንቆ እንጂ ፈልጎና ወዶት አልነበረም። መንቶ 368 እና 369 ይህንን የሚያመለክቱ ናቸው። ሰፈራው የእርዳታ ሰጪ ድርጅት የሆነውን የቀይ መስቀል ውለታ ለመመለስ የተቀበሉት አድርጎ የሚያሳይ ነው። «የተሰጠኝን የእርዳታ ዱቄት መመለስ የምችል ቢሆን ኖሮ ከቤተሰቦቼ ተለይቼ ወደ ሰፈራ አልሄድም ነበር» የሚል አንድምታ ያለው ነው። በመንቶዎቹ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ ሳይወድ በግድ የትውልድ ቀየውን ለቆ ወደ ሰፈራ እንዲሄድ የተገደደ የተጨነቀ ሰው ነው። ይህ ሰው ልቡ እተወለደበት አካባቢ ቀርቶ ስለሚሰፍርበት አካባቢ ሁኔታ እያሰበ የሚጨነቅ ነው፤ እንደወጣ የሚቀር አይመስልም። ጤፍና ማሽላ የሚባሉትን የአካባቢውን ሰብሎች ይቅርታ እየጠየቀ ወደ ሰፈራ ለመሄድ የወሰነ ይመስላል።

እርዳታ አሰጣጡ የተለያዩ ችግሮች እንደነበሩት በተከታዮቹ ቃልግጥሞች እንረዳለን። አንደኛው ችግር ለተጎዳው የህብረተሰብ ክፍል በቶሎ አለመድረሱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የሚታደለው እህል በመጠኑ ለተረጂው ሰው የማይበቃ ወይም አነስተኛ መሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እርዳታ አሰጣጡን የሚወስኑትና የሚያስተባብሩት አካላት «አድሎአዊ» አሰራር ይከተሉ የነበረ መሆኑን መንቶ 370 እና አርኬ 371 ይጠቁማሉ። የስንዴ እደላው ለአንዱ

አካባቢ ተረጂ ከፍተኛ ሲሆን ለሌላው አካባቢ ጨርሶ የሌለ መሆኑን በዝናብና በጎርፍ ተመስሎ ቀርቧል። በሌላ በኩል «ምነው በኛ መንድር ትንሽ ሳያካፋ» በሚለው ስንኝ የተነገረው ሀሳብ አድሎ መኖሩን አመላካች ነው። አርኬ 371 ላይ በልዩ ልዩ መንገድ ተጠቅሰው የቀረቡትን የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በወቅቱ በማህበረሰቡ አመለካከት የነበረውን ስሜት የሚያስታውሱ ናቸው። «ቀይ መስቀል ካፊያ ነው» ማለት ካፊያ መሬቱን ያርጥባል እንጅ አያርስውም፤ ስለዚህ፣ በቀይ መስቀል በኩል የሚደረገው እርዳታ አጥጋቢ አይደለም ማለት ነው። «ኮሚሽን» ማለት በወቅቱ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ይባል የነበረው በአጭሩ ሲጠራ ነው። በሱ በኩል ይደረግ የነበረውም እርዳታ ብዙ ውጣ ውረድ የበዛበት ስለነበር «ኮሚሽን ቅቅት ነው» ተብሏል። «ቅቅት» ማለት ስስት፣ ስይት፣ ችግር፣ ፈጽሞ የማያጠግብ፣ ወዘተ. እንደ ማለት ነው። «አባ» በሚል የሚጠራው የእርዳታ ድርጅት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በኩል ይደረግ የነበረው ነው። አማኞቹና ኃላፊዎቹ ረጃጅም ቀሚስ ወይም ካባ ይለብሱ ስለነበር የአካባቢው ሰው እንደ መነኩሴ «አባ» በሚል ይጠራቸዋል።

ቤተክርስቲያን ከመንግስት አካላት ቁጥጥር ውጪ በሆነ መንገድ አንዳንድ ጊዜ ለተራበው ሰው ድንገት እርዳታ ትሰጥ ነበር። አርኬው እንዲፈጠር ያደረገው አጋጣሚ እንዲህ ነው። በአንድ ወቅት ምንም አይነት ምዝገባ ሳይደረግ በየመንገዱና በየአጥር ጥጉ ወድቆ የተገኘውን ችግርተኛ እየሰበሰበች ሁለትና ሶስት ከረጢት ዱቄትና ጀሪካን ዘይት አደለች። በዚህ አጋጣሚ ብዙ ሰው ተጠቃሚ መሆን ቻለ። «አንጀት የሚያርሰው አባ ዝናቡ ነው» የሚለው ስንኝ ይህንን አጋጣሚና ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ከዚህ አንፃር የቤተ ክርስቲያኗ እርዳታ ከሌሎቹ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች አንጻር ሲታይ የተሻለ እንደነበር መረዳት ይቻላል።

የአርኬ 372 ገጣሚ የአካባቢውን ማህበረሰብ ስሜት ለመናገር የቻለ ነው። በየጁና በራያ አካባቢ በተለይ እንዲሁም በሰሜን ወሎ አካባቢዎች በአጠቃላይ የነበረው ማህበረሰብ እንደ እምነቱ ፈጣሪውን ይለምናል፤ እውነት ፈጣሪ ቢኖር ኖሮ እንዲህ አይነት ችግር አይገጥመንም ነበር? በማለት ቢጠይቅም ምላሽ ሊያገኝ አልቻለም። የአርኬው የመጨረሻ ስንኝ «ኢትዮጵያዊያን ፈጣሪ እንደሌለና ወደ አሜሪካን አገር ሂዶ በፈጣሪነት ማዕረጉ ሳይሆን በተራ ሰውነቱ እየኖረ» መሆኑን ይገልጻል። ይህ ስንኝ ወይም አርኬ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር የሚያያዝ ነው። በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት ከሌሎች መንግስታት እርዳታ እየለመነ ለተረጂው ያቀርብ ስለነበር የእርዳቱው ሁኔታ ከመንግስታት ግንኙነት ጋር ይወሰናል። ስለዚህ የአርኬው ወይም የስንኙ አንድምታ «ህዝቡ የመንግስት ያለህ እያለ ቢጮህም፣ ከመንግስት በኩል ተገቢና ፈጣን ምላሽ ማግኘት አልቻለም» የሚል ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ንዑስ ክፍል ያየናቸው ቃልግጥሞች በሰባ ሰባቱ የርሀብ ወቅት የነበረውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሁኔታ የሚያመለክቱ ናቸው።ቃል ግጥሞቹ በወቅቱ ይደረግ የነበረውን የእርዳታ አሰጣጥ ከእርዳታ አሰጣጡ ጋር ተያይዞ ስለሰፈራው ሁኔታ ስለእርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና ስለ እርዳታ እደላው ሁኔታ በህዝቡና በመንግስት መካከል ስለነበረው ግንኙነት ወዘተ መረጃ የሚሰጡ ናቸው ማለት ይቻላል።

6.2.7.3 ድህረ ርሀብ ቃልግጥሞች

ከዚህ በላይ የቀረቡት ቃልግጥሞች በድርቁ ዋዜማና በድርቁ ወቅት ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ማብራሪያ ገለፃ የቀረበባቸው ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የርሀብ ጊዜው ካለፈ በኋላ የነበረውን እንቅስቃሴና ሁኔታ የሚያሳዩትን ቃል ግጥሞች እንመለከታለን። እነዚህም ድህረ ርሀብ ቃል ግጥሞች በሚል የቀረቡ ናቸው። ድህረ ርሀብ ቃልግጥሞች ማለት የርሀቡ ወቅት አልፎ የአካባቢው ማህበረሰብ ምርት አምርቶ ከችግር ተላቆ በነበረበት ጊዜ የታየውን ሁኔታ የሚያንፀባርቁትን ማለት ነው። እነዚህ ቃልግጥሞች ማህበረሰቡን ችግሩን እያስታወሰ ያሳለፈውን መከራና ጭንቀት እንዲሁም ፀፀት የገለፀባቸው ናቸው፤ ግጥሞቹ የሚከተሉት ናቸው።

አርኬ 373 በገበሬው ራብ እየተናደደ
ከተፋፋመው ፍም ወርዶ ተማገደ
የቅዱስ ዮሐንስ ተዋጋ እስተማታ
የመስቀል ለት ርሀብ ድል በድል ተመታ
አርኬ 374 አንዱን በሬ ሸጬ ፣አንድኛው ሲቀረኝ
ሚስቱ ፍታኝ ብላ ስታንገራግረኝ
ከምድጃው ወርዶ ሀውሌው ገላገለኝ
አርኬ 375 አንተም እንዳንልህ በማዘል ታዝለሀል
ህፃን እንዳንልህ ጢም አንገርግገሀል
የማሽላ ወንድም ታደግ ብለንሀል

በነዚህ አርኬዎች የሚገለፀው ስለ በቆሎ (ባር ማሽላ) ነው። በቆሎ በተዘራ በሁለትና በሶስት ወራት ይደርሳል። ሰኔ ግማሽ ሲል የተዘራ በቆሎ መስከረም ይደርሳል ማለት ነው። የበቆሎ ሰብል በሰወኛ የቀረበ ነው «እየተናደደ፣ ወርዶ ተማገደ፣ በማዘል ታዝለሀል፣ ጢም

አንገርርግገሀል፣» የሚሉት አገላለፆች የሰውን ልጅ ባህሪና ሁኔታ የሚያመለክቱ ናቸው። አርኬ 373 ላይ የተንፀባረቀው ሀሳብ የበቆሎ እሸት መስከረም ላይ ስለደረሰ በችግር ውስጥ የነበረው ቤተሰብ (የአርሶ አደር) እሸት መብላት መጀመሩን የሚያሳይ ነው። «ከተፋፋመው ፍም ወርዶ ተማገደ» ማለት የበቆሎ እሸት እየተጠበሰ መብላት ጀመረ ማለት ነው። የቅዱስ ዮሐንስ ዋዜማ አገዳና እሸት ይቀመሳል። በዚያ ጊዜ ግን ቅምሻ ሳይሆን ቤተሰቡ እስቲጠግብ ድረስ እሸት እንደተበላ የሚያመለክት ነው። «ተዋጋ እስተማታ» የሚለው ሀረግ ይህን ይጠቁማል። የመስቀል ጊዜ አገዳና እሸት እንደልብ የሚደርስበት፣ ቡንኝ የሚባለው የጤፍ አይነት መታጨድና መታሸት የሚጀምርበት ወር መስከረም መጨረሻ ነው። የመስቀል ለት ርሀብ ድል በድል ተመታ የሚለው ስንኝ ይህን የሚያረጋግጥ ነው።

ርሀቡ አርሶ አደሩ የነበረውን ጥሪት ጨርሶ፣ የእርሻ በሬዎቹን መሸጥ የግድ ሲሆንበት፣ ከዚህም አልፎ ትዳሩን (ቤተሰቡን) ሊያፈርስበት በደረሰበት ወቅት፣ የበቆሎ እሸት መድረሱ ከዚህ ሁሉ ችግር እንዳዳነው አርኬ 374 እና 375 ያመለክታሉ። «ሀውሴው» ማለት የበቆሎ ሌላው መጠሪያ ነው። መነሻው አውሳ ከሚገኘው የበቆሎ እርሻ ልማት ጋር የተያያዘ ይመስላል። በከባድ ቤተሰባዊ ችግር ውስጥ የነበረው አርሶ አደር፣ የበቆሎ እሸት ስለደረሰለት እፎይታ ተሰምቶታል፤ እረፍት አግኝቷል ማለት ነው። «በማዘል ታዝለሀል፣ ጢም አንገርርግገሀል» የሚሉት ሀረጎች ከበቆሎ አገዳና ከእሸቱ አያያዝ ጋር የተዛመዱ ናቸው። በቆሎ አገዳው የማሽላ አገዳ ይመስላል፤ ቁመቱ ረጅም ነው። ዛላውን (እሸቱን) የሚያሳየው በአገዳው መካከል ነው። በአንድ የበቆሎ አገዳ ከአንድ በላይ ዛላ ሊሸከም ይችላል፤ አቀማመጣቸው ከላይና ከታች ይሆናል። ይህን የዛላ አያያዝ ነው ከመታዘል ጋር ያነፃፀረው። «ጢም» የሚለውም ከበቆሎ እሸት ጫፍ ላይ ያሉትን ቀጫጭን ክር መሳይ ነገሮች ነው። ታደግ ማለት በችግር ጊዜ ደራሽ፣ የሚታደግ፣ ማለት ነው። ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቃልግጥሞች ደግሞ፣ የርሀቡ ወቅት ሙሉ በሙሉ አልፎ ጥጋብ የሆነበትን ጊዜ የሚያሳዩትንና፣ ያለፈውን በፀፀት የሚያስታውሱትን እንመለከታለን።

መንቶ 376 አያልፍ መስሏቸው ህዝቡ የመነነ
ይኸው አለፈና የጥጋብ ቀን ሆነ
መንቶ 377 አገሬ ተመልከት የዚህን ቀን ማማር
ቅቤው እንደጭቃ አዝመራው እንደ አፈር
መንቶ 378 እንዲህ ልንጠግብ በጋን ልናቦካ
ስንት ሰው አለቀ አፉ እህል ሳይነካ

ከርሀቡ በኋላ በታየው የመኸር ወቅት፣ አርሶ አደሩ ከፍተኛ ምርት ያገኘ ስለሆነ ተደስቷል። ደስታው ግን የተሟላ አይመስልም። ምክንያቱም በርሀቡ ወቅት ያሳለፈውን ጭንቀትና ያለቀውን ወገኑን በቀላሉ መርሳት ባለመቻሉ ነው። የጥጋብ ቀን ማለት፣ የጥጋብ ዘመን ማለት ነው። ይህ የጥጋብ ዘመን፣ ያማረና የተትረፈረፈ ምርት የተገኘበት መሆኑ በመንቶ 376 ና 377 ተጠቅሷል። «ቅቤው እንደ ጭቃ፣ አዝመራው እንዳፈር» በሚለው ስንኝ ተገልጿል። እህልና ቅቤ በብዛት ስለነበር ዋጋውም እርካሽ መሆኑን ያመለክታል። ከአፈርና ከጭቃ ጋር መነፃፀሩ የዋጋውን መርከስ የሚያመለክት ነው። መንቶ 378 ላይ የተንፀባረቀው ሁለት ነው። አንድኛው፣ ከፍተኛ ምርት ስለ ተመረተ፣ የሚቦካውና የሚጋገረው በብዛት መሆኑን ማመልከት ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ በርሀቡ ጊዜ የሰው ልጅ እህል ሳይቀምስ ያለቀበትን በፀፀት ማስታወስ ነው።

ይህ የፀፀትና የቁጭት ስሜት በተከታዮቹ ቃልግጥሞች በተለያየ መንገድ ተገልፆ እናገኛን። እነዚህ ቃልግጥሞች የማስጠንቀቂያ ደወሎች ናቸው ማለት ይቻላል። ያለፈውን ሳይረሱ መጪውን እያሰቡ መኖር ጠቃሚ እንደሆነ ይመክራሉ። ቃል ግጥሞቹን እንመልከት።

መንቶ 379 አንተ መናጢ ቀን ምንኛ ክፉ ነህ
እንዲህ ቀን ሊወጣ ዘር ትጨርሳለህ
መንቶ 380 አንተ መናጢ ቀን እባክህ ታዘዘኝ
ለወሰድኸው ሁሉ ስንቅ አቀብልልኝ
መንቶ 381 እንኳን በማረሻ እረስ በገጀሞ
ያነ ሰባ ሰባት እንዳይመጣ ደግሞ
አርኬ 382 ጠላም አታፍስሱ፣
እንጀራ አታርክሱ
ያነ መናጢ ቀን አጨልቆ አይቶናል
የተመለሰ እንደሁ ይለቃቅመናል።

በነዚህ ግጥሞች የርሀብ ጊዜውን አስከፊነትና፣ በዚሁ ምክንያት ያለቀውን የሰው ልጅ በፀፀት የሚያስታውሱ፣ እንዲሁም ያለፈው የርሀብ አይነት እንደገና እንዳይመለስ የሚመክሩና የሚያስጠነቅቁ ሀሳቦች የተንፀባረቀባቸው ናቸው። መንቶ 379 ና 380 በሰውኛ የቀረቡ ናቸው። ቀኑን እንደሰው እየጠየቀ ይወቅሰዋል፤ ገጣሚው የቀኑ መክፋት ከሰው ልጅ ድርጊት

ጋር አዛምዶ ነው ያቀረበው። እንደ ሰው ይለምነዋል፣ ይወቅሰዋል፣ ዘር አጥፊ ነህ ይለዋል። ይህን ክፋትህን ይቅር የምልህ ደግሞ፣ በርሀብ ለፈጀሀቸው (ለወሰድኻቸው) ወገኖቼ ስንቅ ስታደርስልኝ ነው፤ በማለት ፀፀቱን ይገልፃል። በመንቶ 381 እና 382 የተንፀባረቀው ሀሳብ ጠንክሮ መከሰብንና ቁጠባን የሚመለከት ነው። «ገጀሞ» ማለት ከብረት የሚሰራ የቁጥቋጦና የዛፍ መቁረጫ መሳሪያ ነው። ስለዚህ ለመቆጥቆጥና ለመቁረጥ ያገለግላል እንጂ ለማረሻ አይሆንም። ለማረሻ የሚያገለግለው መሳሪያ ከገጀሞ የተለየ ነው። ማረሻ ከእርፍ ጋር ተዋርዶ ከሞፈር ከድግራ ጋር ተስማምቶ መሬቱን ለመቅደድ የሚያገለግለው ከብረት የሚሰራው ነው። ማረሻና ገጀሞ ከብረት የተሰሩ መሆናቸው ቢያመሳስላቸውም በአገልግሎታቸው የተለያዩ ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ «ተመሳሳይ ችግር እንዳይገጥመን ከፈለግን ባለ በሌለን መሳሪያ ሁሉ መስራት አለብን» የሚል መልክት ተላልፏል ማለት ነው።

በመጨረሻው አርኬ የተነሳው ሀሳብ ከባህል ጋር ተያይዞ ነው። በሀገራችን በአጠቃላይ፣ በተለይ በሰሜን ወሎ በሚገኘው ማህበረሰብ ውስጥ በተለያየ ምክንያት ድግስ መደገስ የተለመደ ነው። ለክርስትና፣ ለሰርግ፣ ለተስካር፣ ለበአላት፣ ወዘተ. ጠላ ጠምቆ፣ ጠጅ ጥሎ፣ እንጀራና ወጥ ሰርቶ፣ ዘመድ አዝማድና የአካባቢን ሰው ጠርቶ፣ ማብላትና ማጠጣት የተለመደ ነው። አሁንም በብዙ የሀገራችን ክፍል የቀረ አይመስልም። ድግሱ ከሚጠራው ተጋባዥ የበለጠ ስለሚሆን፣ የተጠመቀው ጠላ፣ የተጣለው ጠጅ፣ የተዘጋጀው እንጀራና ወጥ በብዛት ይተርፋል። ለኔ ቢጤ የሚሰጠው ተሰጥቶ፣ የተረፈው ይደፋል ማለት ነው። አርኬው ይህንን ባህልና ልማድ የሚተች ነው። በመሆኑም ከእንዲህ አይነቱ ተግባር ወጥተን፣ ህይወታችንን በእቅድና በስርዓት መምራት ይኖርብናል፤ ካልሆነ ግን ያ የችግር ጊዜ ተመልሶ እየመጣ ሊፈጅን ይችላል የሚል መልክት ያለው ነው።

በአጠቃላይ በሰሜን ወሎ አካባቢዎች ተከስተው የነበሩትን ሁለቱን የድርቅ እና የርሀብ ወቅቶች፣ ማለትም በ1965/66 ዓ.ም እና በ1976/77 ዓ.ም፣ ከድርቁ ጋር ተያይዘው የመጡትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ በወቅቱ የነበረውን ሰብአዊ ጭንቀትና እልቂት፣ ወዘተ. ከዚህ በላይ በቀረቡት ቃልግጥሞች አማካኝነት ለማየት ተሞክሯል። እነዚህ ቃልግጥሞች በአካባቢው የነበረውን ሰብአዊና አካባቢያዊ ችግሮች የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢውን ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ አመለካከት፣ ወዘተ መጠቆም የሚችሉ ስለሆነ፣ ችግሮቹን ለይቶ በማጥናት መፍትሄ ለሚፈልጉና ለሚሰጡ ወገኖች እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው።

6.2..8 ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ቃልግጥሞች

ይኽ ምድብ እስካሁን ከታዩት ምድቦች የተለየ ሁኔታ የታየበት ምድብ ነው:: ምክንያቱም የቅርብ ጊዜ ገጠመኞችና ወቅታዊ ጉዳዮች የተንፀባረቁበት፣ ከአርሶ አደሩ አመታዊ የስራ ተግባር ኡደት ጋር የተያያዙ፣ እንዲሁም በማህበራዊ ወይም በቤተሰባዊ ህይወት ውስጥ የታዩ እንከኖች የተንፀባረቁበት ክፍል ነው:: የአለማችን የጤና ችግር ሆኖ ያለው የኤድስ ወረርሽኝ ያስከተለው ችግር የተጠቆመበት፣ ከቤት መፍረስ ጋር ተከትሎ የታየው ሁኔታ የተገለፀበት ነው:: ምድቡ በአጠቃላይ ወደ 31 ቃልግጥሞች አሉት፡፡

ወቅታዊ ጉዳዮች ማለት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በመታየት ላይ ባሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ምክንያት በሰው ልጆች ላይ እየደረሱ የሚገኙትን ሰብአዊ ቀውሶችን የሚመለከት ነው፡፡ ስደት፣ በሽታ፣ ስራ አጥነት፣ ህገወጥነት፣ ዝርፊያና ግድያ፣ የመሳሰሉት ችግሮች በአጠቃላይ የሰውን ልጅ፣ በተለይ ደግሞ መንግስታትን እያስጨነቁና እየፈተኑ ያሉ ሰብአዊ ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰብአዊ ቀውሶችና ችግሮች፣ ለስነ ቃል ፈጠራ ምክንያት ወይም መነሻ ሆነዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስለስደት፣ ስለበሽታና ስለቤት ግንባታ መፍረስ የተገጠሙትን ቃልግጥሞች እንመለከታለን፡፡

6.2.8.1 ስደት

ስደት ማለት በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የሰው ልጅ የትውልድ አካባቢውን ወይም የዜግነት አገሩን እየለቀቀ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም አገር ሂዶ (ተሰዶ) መኖር ማለት ነው፡፡ በሥራ ምክንያት፣ በፍላጎት፣ በቤተሰብ ምክንያት፣ ወዘተ. አካባቢን ለቆ መሄድ እንደ ስደት አይቆጠርም፡፡ ስደት፣ በልዩ ልዩ አስገዳጅ ችግሮች ምክንያት በትውልድ አገር ወይም አካባቢ ለመኖር በማይቻልበት ጊዜ አካባቢውን ለቆ መሄድ ነው፡፡ በስደት ላይ ያለ ሰው በተሰደደበት አካባቢ በልዩ ልዩ የስራ መስክ ተሰማርቶ ህይወቱን ሊመራ ይችላል፡፡ ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮችም ይጋለጣል፡፡ ቀጥሎ ያሉት ቃልግጥሞች የስደትን አስከፊነት የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

መንቶ 383 ተማሪ ናት አሉ ያውም አስረኛ
ጅዳ ተሻገረይ ላረብ ሰራተኛ
መንቶ 384 የጅቡቲው ባህር የመዲናው ሹርጣ
አታሳልፍም ወይ የከፋው ሲመጣ

መንቶ 385 አንተ ጥቁር ሰማይ ወይ ውረድ ወይ ፍረድ
ሀበሻ ተወልዶ ሲሆን ያረብ ገረድ
መንቶ 386 ነጭ ጤፍ ቢዘሩት ማን ጋር ይበሉታል
ሽጋ ሽጋውን ልጅ ኪታር ልከውታል
አርኬ 387 ልጅን ላረብ አገር ሸጠነ ነበረ
ሚስትን ላረብ አገር ሸጠነ ነበረ
ገንዘብ አጠቃቀም ሳናውቅ ቀረነ

በሀገራችን እየታየ ያለው የስደት ሁኔታ ስራ በማጣት ወይም በመቸገር ብቻ ሳይሆን « የተሻለ አማራጭ ፍለጋ» አገራቸውን እየለቀቁ የሚሰደዱ ዜጎች የሚታዩበት ወቅት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ መንቶ 383 ላይ የተገለጸው ጉዳይ ገና ትምህርቷን ያልጨረሰች ወጣት ስደት ነው፡፡ የስደቷ ምክንያት ባይገለጽም ተስፋ ከመቁረጥ፣ አቅም ከማጣት የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ በምትሰደድበት ሀገር የሚጠብቃት የስራ ሁኔታ ግን፣ ለተማሪዋ የማይገባ መሆኑ በመንቶው ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይኸውም ሰራተኝነት (ግርድና) ነው፡፡ ግርድና በአንድ ሰው ቁጥጥር ስር ሆኖ ማገልገል ማለት ነው፡፡ ከባርነት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ወጣቷ ለዚህ አይነቱ አስከፊ ችግር ወደ አረብ አገር (ጅዳ) መሰደዷን በቁጭት ያመለክታል፡፡ የሰው ልጅ ሲማር የተሻለ ህይወት ይኖረዋል ተብሎ ቢታሰብም፣ በወጣቷ ላይ የታየው ግን ተቃራኒው ነው፡፡ «ያውም አስረኛ» የሚለው ሀረግ የአካባቢው ማህበረሰብ ለትምህርት ያለውን ከፍተኛ ግምት የሚያመለክት በመሆኑ፣ የቁጭት መነሻውም ይኸው አስተሳሰብ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

የሚሰደዱ ሰዎች መድረስ ወደሚፈልጉበት አካባቢ ወይም አገር እስቲደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡ በድካም መንገድ ላይ መቅረት፣ በአውሬ መበላት፣ በሰዎች መታገት፣ ባህር ውስጥ መግባት ወዘተ ይደርስባቸዋል፡፡ መንቶ 384 ይህንን ይጠቁማል፡፡ በጅቡቲ በኩል የሚሰደዱ ወጣቶች ባህር አቋርጠው ሲጓዙ በሚያሻግሯቸው ሰዎች ወይም በአደጋ ምክንያት ችግር ላይ ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ «የጅቡቲው ባህር» የሚለው ባህሩን የሚያሻግሩትን ሰዎች ነው፡፡ «ሹርጣ» ማለት ኬላ ጠባቂ ፖሊስ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስደተኛው በባህር አሻጋሪዎችና በኬላ ጠባቂዎች እየተንገላታ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ የልመናው ስሜት ይህን ያመለክታል፡፡

ከመንቶ 385 እስከ አርኬ 387 ባሉት ቃልግጥሞች የተንፀባረቀው ጉዳይ ቁጭት ነው፡፡ የቁጭቱ ምክንያቶች ለግርድና መዳረግ፣ የትደር ጓደኛ ማጣት እና ብክነት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው መንቶ፣ አምላክን የሚሞግት መራር ሙግት ነው። ሙግቱ ትክክለኛ ፍትህ ከመስጠት ወይም ከመውረድ ጋር የተያያዘ ነው። በሰው ልጆች መካከል ለተፈጠረው ልዩነት ምክንያቱ እሱ እንደሆነ ተቆጥሮ ነው የሚጠየቀው። «ሀበሻ ተወለዶ ሲሆን ያረብ ገረድ» የሚለው ይህንን ነው። በኢትዮጵያዊያንና በአረቦች መካከል ለምን ልዩነት ፈጠርክ? የሚል የቁጭት ስሜት የተንፀባረቀበት ነው። መንቶ 386 የአንድ ወጣት ወይም ጎልማሳ የቁጭት ድምጽ የሚሰማበት ነው። ይህ ወጣት ወይም ጎልማሳ በአገሩ እየኖረ የፍቅርና የትዳር ጓደኛ ባለማግኘቱ እየተከፋ የሚኖር ነው። አርሶ አደሩ ያመረተውን ነጭ ጤፍ ከሚወዳት ቆንጆ ባለሙያ ሚስት ጋር ሆኖ ሲጠቀምበት ነው፣ የደስታ ህይወት ምንጭ የሚሆነው። የነጭ ጤፍ እንጀራ ሲያዩት ለአይን ያምራል፣ ሲመገቡት ይለሰልሳል። «ሽጋ ሽጋውን ልጅ ኪተር ልከውታል» የሚለው ስንኝ ወጣት ሴቶችን በልዩ ልዩ ዘዴ እየደለሉ፣ ለስደት የሚዳርጉ ሰዎች እንዳሉ መንቶው ጠቋሚ ነው።

አርኬ 387 ላይ የተንፀባረቀው ሀሳብ ለየት ያለ ነው። ይህ አርኬ ቤተሰባዊ የሞራል ውድቀት የተገለፀበት ነው። ሚስትና ልጅ፣ ተንከባክበው የሚጠብቋቸው እንጂ፣ እንደ ሸቀጥ የሚሸጡ አይደሉም። አሁን አሁን ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ አረብ አገር እንዲሄዱ ግፊትና ድጋፍ ይሰጣሉ። አንዳንድ ልጆችም ወደ አረብ አገር ካልሄድኩ እያሉ የሚያስቸግሩ ይኖራሉ። ከዚህ የሚበልጠውና የሚያስደነግጠው ግን፣ ባል ወይም እጮኛ፣ የትዳር አጋሩን አረብ አገር ሂዳ «ሰርታ» እንድ ትመጣ ፈቃደኛ መሆኑ ነው። በሀይማኖትም ሆነ በባህል፣ ያልተለመደና ተቀባይነት የሌለው ሁኔታ ነው። እንዲህም ሆኖ፣ የስደተኛዋ የልፋት ውጤት የሆነው ገንዘብ (ሀብት)፣ ለቁምነገር ሳይውል እንደቀረ፣ የመጨረሻው ስንኝ ያመለክታል።

ከዚህ ቀጥሎ የምናያቸው ቃልግጥሞች በስደት ምክንያት እየተፈጠሩ ያሉትን ልዩ ልዩ ችግሮች የሚያሳዩ ናቸው። አንዱ ችግር ናፍቆት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በስደት ምክንያት እያመለጠ ያለውን አጋጣሚና እድል የሚመለከት ነው። ናፍቆት በስደተኛውና በቤተሰቦቹ መካከል የሚፈጠር ትዝታና ጭንቀት ነው። ቃልግጥሞቹን እንመልከት!

መንቶ 388 ባህር ተሻጋሪ ይኸዳል በታንካ
አይኗን ባየሁትኝ ለአንድ ደቂቃ እንካ
አርኬ 389 እራቴንም በላሁ በጨው በጨው
ምሳየንም በላሁ በጨው በጨው
ጅዳ የኸደ ሰው መቼ ነው መምጫው

መንቶ 390 አንተ ጥቁር ባህር የተንጋለልኽው
አታገናኝም ወይ የናፈቀ ሰው
መንቶ 391 የጅዳ ገበሮይ እርሻ እረሱ፣እርሻ እረሱ
አፍላው አመለጠ ስትመላለሱ
መንቶ 392 የጅዳ ገበሮይ እርሻ እረሱ፣እርሻ እረሱ
ቀናችሁ ደረሰ ስትመላለሱ
መንቶ 393 በጀልባ ተሻግረው ባየር ቢመለሱ
አልጋውን ሰቀሉት እንጀራ ሳይቀምሱ

በመጀመሪያዎቹ ሶስት ግጥሞች ተደጋግሞ የተነሳው ሀሳብ ናፍቆት ነው። የናፍቆቱ ደረጃ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የደቂቃ መተያየት የሚያንገበት ስሜት የተገለፀበት ነው። የስደተኛው ቤተሰብ የናፍቆት ሁኔታ የተገለፀው ከምግብ ሰአቶች ጋር ተያይዞ ነው። ስደተኛው የሚመጣበት ጊዜ ይጠብቃል። ባህሩን ያነጋግራል፣ ይለምናል። ተናጋሪው ስደተኛው ተሻግሮበታል የሚባለውን ባህር፣ በአይነ ህሊናው እየተመለከተ፣ ያነጋግረዋል፣ ይለምነዋል። በአጠቃላይ ለትንሽ ጊዜ መተያየት፣ የመመለሻ ጊዜው መርዘምና አለመታወቅ፣ ወዘተ. በየግጥሞቹ ውስጥ የተንፀባረቁ ሀሳቦች ናቸው።

ከመንቶ 390 እስከ 393 ባሉት ቃልግጥሞች የተላለፉት መልዕክቶች፣ ለፍቶ መና መቅረትና በከንቱ መድከም ናቸው። «የጅዳ ገበሮይ» የሚለው ሀረግ የሚወክለው ስደተኞችን ነው። እነዚህ ስደተኞች በሁለት መንገድ ድካማቸው ውጤት አልባ ሊሆን እንደሚችል በመንቶ 391 እና 392 ተጠቁሟል። አንደኛው፣ ከሀገር ለመውጣት በምታደርጉት እንቅስቃሴ ወቅቱን ጠብቃችሁ፣ አርሳችሁና ዘርታችሁ ማምረት የምትችሉበት ጊዜ እያለፈ ነው ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ተረጋግታችሁ ሳትሰሩና ገንዘብ ሳትይዙ፣ ወደ አገራችሁ የምትመለሱበት ቀን ደረሰ፣ የሚል ነው። የመጨረሻው መንቶ፣ ለፍቶ መና መሆንን፣ በለፉበት ሳይጠቀሙ መቅረትን፣ ያመለክታል። «አልጋውን ሰቀሉት እንጀራ ሳይቀምሱ» የሚለው ስንኝ፣ በሰው ሀገር ለፍተው ባገኙት ገንዘብ፣ የገዙትን የቤት እቃ እንዳሰቡት ሳይጠቀሙበትና ሀብት ሳያፈሩ፣ ለበሽታና ለሞት መዳረጋቸውን ያሳያል።

6.2.8.2 በሽታ

ሁለተኛው ወቅታዊ ጉዳይ በሽታ ነው። የወባ ወረርሽኝ፣ የተፈጥሮ መከላከያ ቅስም ሰባሪ በሽታ (ኤች.አይ.ቪ ኤድስ) የሳንባ በሽታ፣ ወዘተ. አለምን በአጠቃላይ፣ አገራችንን በተለይ እያስጨነቁ ያሉ የጤና ችግሮች ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ ከኤድስ በሽታ ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ቃልግጥሞችን እንመልከት።

መንቶ 394 እዩት እዚያ ማዶ ክፉ እሳት ነደደ
ምክር ያልሰማውን እየፈጀ ኸደ
አርኬ 395 እንዴት ያለ ወገብ ፣እንዴት ያለ አንገት
እንዴት ያለ ከንፈር እንዴት ያለ ጥርስ
እፍን አርገው ያዙት ቲቢና ኤድስ
መንቶ 396 የኤድስ በሽታ ነፍስህን አይማረው
ስንቱ ሰው አደረ ውሽማ (ወዳጅ) እያማረው
መንቶ 397 በል ሞትና ማጣት ኸመንገድ ተመለስ
ወጣቶችን ድረን እስትንበላ ድረስ

በመጀመሪያው መንቶ የኤድስ በሽታም ከእሳት ጋር ተነፃፅሯል። እሳት የነካውን ያቃጥላል፣ የኤድስ በሽታም ያልተጠነቀቀውን ይይዛል። ስለኤድስ በሽታ በጤና ባለሙያዎች በተለያየ ደረጃ ምክር ይሰጣል። የጤና ባለሙያ የሚያስተላልፈውን ምክር አዳምጦ የተቀበለ ሰው፣ ለችግሩ ተጋላጭ አይሆንም ማለት ነው። ከዚህ ውጪ ለመሆን መሞከር፣ በበሽታው ተጠቂ እንደሚያደርግ የመጀመሪያው መንቶ ይመክራል።

አርኬ 395 የሚገለፀው በኤድስ በሽታ ምክንያት የመጣውን አካላዊ ጉስቁልና እና ቅስም መሰበር ነው። በአርኬው ውስጥ የተገለፀው የአንዲት ወጣት አካላዊ ቁመና እና ቁንጅና ነው። የወጣቷ ወገብ፣ አንገት፣ ጥርስና፣ ከንፈር በተጋነነ መንገድ ቀርበዋል። ግጥቱ «እንዴት...» በሚለው መጠይቅ ቃል አማካኝነት የቀረበ ነው። የአካሏ መድቀቅ፣ የውበቷ መርገፍ የቅስሟ መሰበር «እፍን አርገው ያዙት ቲቢና ኤድስ» በሚለው ስንኝ ተገልጿል። በመንቶ 396 ላይ የኤድስ በሽታ እንደ ሰው ሲረገም እናያለን። «...ነፍስህን አይማረው» እርግማን ነው። ለእርግማኑ ሰበብ የሆነው ደግሞ፣ ሰብአዊ ፍላጎት ነው። ከጋብቻ ውጪ ይደረግ የነበረው

ጾታዊ ግንኙነት በሽታውን በመፍራት የተቋረጠ ወይም ሰውን ጭንቀት ላይ የጣለ መሆኑን የሚያመለክት ነው። የመጨረሻው መንቶ የሰው ልጆች የጋራ ችግሮች የሆኑት «ሞትና ድህነት» እንዲወገዱ ወይም እንዳይከሰቱ የሚል ሀሳብ የተገለፀበት ነው። «የኤድስ በሽታ በብዛት የሚያጠቃው ወጣቶችን ነው» የሚል አስተሳሰብ ስላለ ወጣቶች ደግሞ የቤተሰብና የማህበረሰብ ሀብቶች በመሆናቸው በነሱ ላይ የሚመጣ ጉዳት ከፍተኛ ይሆናል ማለት ነው። በባህሉ ልጅ ወልዶ፣ አሳድጎ፣ ለቁምነገር ማድረስ የማንኛውም ቤተሰብ ምኞት ነው። ልጆች ክርስትና ሲነሱ፣ ሲዳሩና ሲኳሉ፣ ድግስ እየተደገሰ ይበላል፣ ይጠጣል። ወዳጅ ዘመድ የደስታ ተካፋይ ይሆናል። ልጆች የወላጆች «አለም ማያዎች» (መደሰቻዎች) ስለሆኑ፣ ይህ ቤተሰባዊ ደስታ እንዳይጨናገፍ የሚመኝ መንቶ ነው።

6.2.8.3 ግንባታ

በአሁኑ ወቅት ሰዎች በልዩ ልዩ መንገድ መሬት እየወሰዱ ልዩ ልዩ ግንባታዎችን እያካሄዱ ነው። ይህ የግንባታ ስራ፣ በመንግስት በኩል «ህገ-ወጥ» በሚል ሰበብ ችግር እየገጠመው፣ ሰዎችንም በህግ እያስጠየቀ ያለ ነው። ችግሩ በመንግስት ባለስልጣናት እና በሰዎች መካከል ጥላቻና ቅራኔ ውስጥ እስከማስገባት የደረሰ ወቅታዊ ችግር ሆኗል። ከዚህ ቀጥሎ ከቤቶች መፍረስና ካስከተለው ኢኮኖሚያዊ ችግር አንፃር የተፈጠሩ ቃልግጥሞችን እንመለከታለን።

መንቶ 398 ኧረ መቼ ያልቃል ያዳሜ መከራ
አንደኛው ያፈርሳል አንደኛው ሲሰራ
መንቶ 399 ምክር እማይሰማ ችኩሎ ሰርቶህ
አሸዋና ድንጋይ በከንቱ ቀረህ
መንቶ 400 ወይም ሳይበላ ሳይመጠወት
ከንቱ ሆኖ ቀረ ይኸ ሁላ ሀብት
መንቶ 401 ይኸን ፈርቼ ነው ቤት የማልሰራው
የኒህ ሰወይ ጉዳይ ሳይገኝ መላው

የመጀመሪያዎቹ ሁለት መንቶዎች በቤት መፍረስ ምክንያት የአካባቢው ሰዎች እየተሰቃዩ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። ችግሩ የሚቆም አለመሆኑን «ኧረ መቼ ያልቃል ያዳሜ መከራ» የሚለው ስንኝ ይጠቁማል። «አዳሜ» ማለት እያንዳንዱ ሰው ማለት ነው። ችግሩ ቤት በማፍረስ፣ ቤት በመስራት ላይ የተመሰረተ ነው። ቤት መስራት ገንዘብ፣ ጉልበት፣

እውቀት፣ ጊዜ፣ ይፈጃል። ይህ ሁሉ ወጥቶበት የሚፈርስ ቤትም እንዲሁ፣ ችግሩ ተመሳሳይነት አለው። የመጀመሪያ መንቶ ይህን ያመለክታል። መንቶ 399 የሚያሳየው ኢኮኖሚያዊ ችግሩን ነው። ለቤት ግንባታ የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች ቤቱ ሲፈርስ፣ እንደገና ጥቅም ላይ የመዋላቸው እድል አነስተኛ ነው፣ ስለዚህ ኪሳራ ያስከትላል ማለት ነው። መንቶ 400 የቁጭት ስሜት የተገለፀበት ነው። የቁጭቱ ምክንያት ለቤት መስሪያ ወጪ ሆኖ ግን ስለ ባከነ ገንዘብ ነው። መልክቱ ወይም ሀሳቡ ገንዘቡን ለቤት መስሪያ ከማዋል ይልቅ፣ ተደግሶ በተበላበትና በተጠጣበት፣ የተቸገሩ በተረዱበት (በተመጠወቱበት) ይሻል ነበር የሚል ነው። የመጨረሻው መንቶ የተቃውሞ ሀሳብ የተንፀባረቀበት ነው። ተቃውሞው ከመንግስት ወይም ከባለስልጣናት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ለውጥና ተጠያቂነት እስካልተፈጠረ ድረስ፣ ቤት መስራት የማይቻል መሆኑን አመላካች ነው።

በአጠቃላይ ከስደት፣ ከበሽታና ከቤት መፍረስ ጋር፣ ተያይዘው የተፈጠሩት ቃልግጥሞች የአካባቢው ማህበረሰብ የገጠመውን ወቀታዊ ችግር የሚያመለክቱ ናቸው። እነዚህ ችግሮች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስለሆኑ መፍትሄ የሚሹ ወቅታዊ ጉዳዮች ናቸው። ቃልግጥሞቹም ይህንን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማንፀባረቅ የቻሉ ናቸው።

ምዕራፍ ሰባት፡- ማጠቃለያና አስተያየት

ይህ ጥናት በሰሜን ወሎ ባሉት ቆላማ አካባቢዎች በሚኖረው ማህበረሰብ ላይ የተደረገ የአማርኛ ቃልግጥም ጥናት ነው። በተደረገው ጥናት መሰረት ስምንት ዋና ዋና ፋይዳዎች ያሏቸው የአማርኛ ቃልግጥሞች የተገኙ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት የእነዚህ ቃልግጥሞች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እንዲሁም፣ ማህበረ-ባህላዊ መልክቶቻቸውን በትንተናው ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል። በመሆኑም፣ የጥናቱ ማጠቃለያዎችና አስተያየቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

7.1 ማጠቃለያ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ ይህ ጥናት በአማርኛ ቃልግጥም ላይ የተደረገ ገላጭና ትንተናዊ ጥናት ነው። በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው፣ ጥናቱ አንድ አብይ አላማና ሌሎች ንኡስ አላማዎች ያሉት ሲሆን፣ አብይ አላማው በሰሜን ወሎ አካባቢዎች ባሉት ምስራቃዊ ቆላማ አካባቢዎች ባለው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙትን ቃልግጥሞች መሰብሰብ፣ መመደብና ትንተና ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ መሰረት ከ1500 በላይ የሚሆኑ፣ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የተገጠሙ ቃልግጥሞችን መስክ ላይ መሰብሰብ ተችሏል። እነዚህ ቃልግጥሞች በውስጣቸው ካለው መረጃ በመነሳት፣ በስምንት ዋና ዋና ምድቦች በመመደብ፣ እያንዳንዱን ምድብ በማብራራት ገለጻ ተደርጓል። በመሆኑም፣ ስምንቱ ዋና ዋና ምድቦች፤ ማለትም የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች በሚል የተደራጁት የሚከተሉት ናቸው። የመጀመሪያው ምድብ፣ የሙገሳና የውዳሴ ሀሳቦችን የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች የተደራጁበት ነው። እነዚህ የሙገሳና የውዳሴ ቃልግጥሞች በተለያዩ ነገሮች ላይ የተመሰረቱ ሆነው፣ አንዳንዶቹ በጥናት የተካለሉትን አካባቢዎችና በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩ ግለሰቦች ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ማሞገሻዎችና ማወደሻዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች በአካባቢው በህይወት የነበሩ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ዝናቸው ይታወቅ የነበሩ ሲሆን፣ በተለይ በግብርና ተግባራቸውና በሀብት መጠናቸው ይታወቁ የነበሩ ናቸው። ለዚህ አይነት ተግባር የሚውሉት ቃልግጥሞች በስነቃል ተመራማሪዎች ዘንድ የሙገሳ ግጥሞች (praise poems) ይባላሉ። ለምሳሌ፣ Okpewho «የሙገሳ ቃልግጥሞች በአንድ ነገር ወይም በአንድ ሰው አድናቆት ላይ የተመሰረቱ ሆነው፣ በተለይ በማህበረሰቡ አባላት መካከል የተለየ ክብር ያላቸውን ሰዎች የሚመለከቱ ናቸው» (1992፣ 142) ብለዋል። የመሞገሻና የማወደሻ አጋጣሚዎቹም፤ ባህላዊ አጋጣሚዎች፣ ማለትም ሰርግ፣ መዝናኛ ቤቶች፣ የስራ አካባቢዎችና አመት በአላት ናቸው።

ስንፍናን የመተችት ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች ሁለቱንም የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ማለትም ሴቶችንና ወንዶችን የሚተቹ ሆነው ታይተዋል። ሴቶቹን የሚተቹት ግጥሞች ትኩረታቸው ከሴትነት ሙያ ጋር የተያያዙና፣ ብኩንነትን ወይም ቁጠባ አለማድረግን የሚያመለክቱ ናቸው። ወንዶቹን የሚመለከቱት ትችታዊ ቃልግጥሞች ደግሞ፣ ትኩረታቸው ከግብርና ስራ ጋር ተያይዞ የሚታየውን ድክመት የሚያንጸባርቁ ናቸው። እነዚህ ግጥሞች በዚህ ሳቢያ የሚታዩትን ሴሰኝነትን፣ ጣልቃ ገብነትን፣ ጠባቂነትን፣ ወዘተ. የመተችት አላማ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። እንደነዚህ አይነት ቃልግጥሞች፣ በማህበራዊ ትችት ላይ ያነጣጠሩ ስለሆነ፣ ባንድ በኩል ለተናጋሪው የመተንፈሻ አጋጣሚ የሚፈጥሩ ሲሆኑ፣ ለአድማጩ ደግሞ፣ የማስጠንቀቂያ መልክት የተላለፈባቸው ናቸው። በመሆኑም በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉት ቃልግጥሞች የማህበረሰቡ አባላቶች መልካም ባህሪያትን እንዲላበሱ፣ መልካም ያልሆኑትን እንዲያስወግዱ የሚያስተምሩና የሚያስጠነቅቁ ናቸው።

ከጀግንንትና ከፈሪነት ጋር ተያይዘው የተገጠሙት ቃልግጥሞች፣ ሁሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ፣ ወንዶች ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው። ይህም የአካባቢውን ማህበረሰብ አመለካከት የሚጠቁም መሰረተዊ ጉዳይ የተንጸባረቀበት ነው። ማህበረሰቡ በወንዳዊ አስተሳሰብ የተገነባ፣ የወንድና የሴት ተግባር ምን መሆን እንዳለበት በህይወት ልምዱ ያዳበረው አስተሳሰብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ማህበረሰቡን ያጋጥሙት በነበሩት ልዩ ልዩ ግጭቶች ሳቢያ፣ አባላቱ በዚህ አስተሳሰብ እንዲታነጹ ያደረጋቸው ይመስላል። ጥቃትን መከላከል የወንድ ድርሻ ነው፤ ቤተሰብን፣ ጓደኛን፣ በአጠቃላይ አካባቢያዊ ችግርን የመከላከል ማህበራዊ ግዴታ የተሰጠው ለወንድ ነው ማለት ይቻላል። ፈሪነትን የሚተቹትም እንዲሁ ወንዶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ከአካባቢ፣ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ወዘተ. ጋር ተያይዞ ለሚያጋጥሙ ችግሮች እንደማህበረሰብ አባልነቱ የራሱን ድርሻ የማይወጣ ሆኖ ሲገኝ በቃልግጥሞች ይሰደባል፤ ይተቻል። በመሆኑም ከጀግንነት እና ከፈሪነት ጋር የተያያዙት ቃልግጥሞች የሚያረጋግጡት ይህንን ማህበራዊ ልማድና እውነታ ነው።

ፍቅር ለአንድ ነገር ያለን አወንታዊ ስሜት ሲሆን፣ መገለጫውም ስለነገሩ መልካም ማሰብን፣ ማድነቅን፣ የመሳሰሉትን የሚያካትት ይሆናል። በመሆኑም አካላዊ ቁንጅናንና ፍቅርን የሚያሳዩት ቃልግጥሞች ሁሉም የሴትን ልጅ ውጫዊ ገጽታ አጉልተው የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል። የሴትን ልጅ የሰውነት ክፍሎች፣ ከራስ ጸጉር ጀምሮ በዘይቤያዊ ቋንቋ ይገልጻሉ። ዘይቤዎቹም አካላዊ ቁንጅናንና ውበትን አጉልተው በማሳየት ቁንጅናና ውበት ተጨባጭነት እንዲኖረው አድርገዋል።

በማህበረሰባዊ መስተጋብርና በሰው ልጅ የአኗኗር ህይወት ውስጥ በሰዎች መካከል አሉታዊ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ። እነዚህ ችግሮች የግለሰቦችን ስሜት የሚያስጨነቁና የሚያሳዝኑ ስለሆኑ፣ የሰውን ልጅ ስሜት ተጭነው ይይዛሉ። እነዚህን የመሳሰሉት ህይለኛ ስሜቶች ከሰው አእምሮና መንፈስ ውስጥ ሊወጡ ካልቻሉ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ። ከእንደነዚህ አይነት ውስጣዊ ጭንቀቶች ለመላቀቅ አንዱ መሳሪያ ስነቃል እንደሆነ ይታወቃል። ስለሆነም፣ በቃልግጥሞቹ ውስጥ የታየው፣ ይኸው የመተንፈሻ መሳሪያነቱ እንደሆነ ነው።

በየመንቶዎቹና በየአርኬዎቹ ውስጥ የታዩት የብሶትና የቁጭት፣ እንዲሁም የጥላቻና የማንኳሰስ ሃሳቦች የተንጸባረቀባቸው ቃልግጥሞች በሴቶችና በወንዶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። በተለይ ብሶትንና ቁጭትን የሚያንጸባርቁት ግጥሞች ውጫዊ በሆኑ ምክንያቶች ሳቢያ የተፈጠሩ ሆነው ታይተዋል። ከነዚህ ውጫዊ ምክንያቶች መካከል አንዱ አስተዳደራዊ ችግር ነው። ሌላው ምክንያት ከሰዎች ጋር አብሮ በመኖር ሂደት ሊፈጠር የሚችልን ችግር የሚመለከት ሲሆን፣ በዚህም፤ ሳይታሰብ በሚነሳ ግጭት፣ በቋንቋ አለመግባባት፣ ግጭት ለመፍጠር በመፈለግ፣ ነገር በማመላለስ፣ ወዘተ. በሰዎች መካከል ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ትዕግስትን የሚፈትንና ማስተዋልን የሚጠይቅ መሆኑ በቃልግጥሞቹ ውስጥ ለመታየት ችሏል። የግል ቤተሰባዊ ህይወትም ለብሶትና ለቁጭት የሚዳርግ መሆኑ በግጥሞቹና በትንተናው ሂደት ታይቷል። በተለይ በኢኮኖሚ አቅም ማጣትና በኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ መሆን የብሶትና የቁጭት መንስኤዎች ሆነዋል። በአጠቃላይ የብሶትና የቁጭት፣ የጥላቻና የማንኳሰስ ሀሳቦች የተንፀባረቁባቸው ቃልግጥሞች በማህበራዊም ሆነ በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥንቃቄ ለደረግባቸው የሚገቡ ልዩ ልዩ እውነታዎች የታዩባቸው ናቸው።

«የሰው ልጅ ማህበራዊና ፖለቲከዊ ግንኙነት ብዙ ጊዜ በግጭት የተሞላ ነው። ለዚህ ምክንያቱ በሀሳብ ያለመግባባት፣ አንዱ የሌላውን መብት በሀይል ለመጣስ መሞከር፣ ወዘተ. ናቸው። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በአፍሪካ ቃልግጥም ውስጥ በተደጋጋሚ የሚንጸባረቅና፣ በብዙ ምክንያቶች ግጭቱ ወደ ትግል ወይም ወደ ጦርነት እንደሚያመራ» (Okpewho፣ 1992፣ 151) ይናገራሉ። ከምደባውና ከትንተናው እንደታየው ለዚህ ጥናት ከተሰበሰበው የቃልግጥም መረጃ መካከል በሀገራችን በታዩት ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ምክንያቶች የነበረውን እውነታ የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ ናቸው። በታሪክ እንደምናስታውሰው ማእከላዊ መንግስት ለመመስረት በተደረገው እንቅስቃሴ፣ በተለይ በሰሜኑ የሀገራች ክፍል የሚገኘው ማህበረሰብ በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ ተሳታፊም ተጠቂም ነበር ማለት ይቻላል። ይህ

እውነታ በቃልግጥሞቹ ውስጥ ተንጸባርቋል። ማህበረሰቡ የፖለቲካ ተቃውሞውንና ጥላቻውን ወይም ድጋፉን በሁለቱ ስርአቶች ላይ ያሳይ እንደነበር አመልክተዋል። በተለይ ከ1966 አብዮት በኋላ በሀገራችን የታየው የፖለቲካ ሁኔታ የተንጸባረቀባቸው ቃልግጥሞች፤ በጊዜው አገሪቱን ያስተዳድር የነበረው የደርግ መንግስት፣ ከሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች ጋር በተለይ፣ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ መካከል የነበረውን ሁኔታ የሚያሳዩ የድጋፍና የተቃውሞ ግጥሞች በብዛት ተገኝተዋል። በትንታኔው እንደታየው የድጋፍና የተቃውሞ ቃልግጥሞቹ መንግስትን የሚተቹና የሚቃወሙ ወይም የሚደግፉ ናቸው። የተቃውሞ መነሻው ባለስልጣናት በማህበረሰቡ ላይ፣ በተለይ በግለሰቦች ላይ፣ ያደርሱት የነበረውን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ችግር መሰረት ያደረገ ነው። ሰወች ያለ ፍርድ መገደላቸውንና በወጡበት መቅርታቸውን፣ የመሬት ክፍፍሉ ፍትሃዊ አለመሆኑን፣ ወዘተ. የሚያስታውሱ ናቸው። ከዚህ በተጻራሪ መንግስትን የሚደግፉም ታይተዋል።

ከ1966 አብዮት በኋላ በመጣው የፖለቲካ ለውጥ ምክንያት ሰዎች በልዩ ልዩ ቡድን ውስጥ ገብተው የፖለቲካ ተሳትፎ ያደርጉ እንደነበር ይታወሳል። ይህ ተሳትፎ ወደ ተካረረ የፖለቲካ ልዩነት በመውሰዱ፣ አንዱ በሌላው ላይ ጥላቻና ጥቃት እስከ ማድረስ አድርሷል። በዚህ ምክንያትም ወደ ለየለት የትጥቅ ትግል የገቡ እንደነበሩም ይታወሳል። በመሆኑም በ1967 ዓ.ም ወደ ትጥቅ ትግል ከገቡት ተቃዋሚዎች መካከል አንዱ በጊዜው ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ይባል የነበረው ነው። ይህ ድርጅት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ግንባር በመፍጠር አሁን የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የሚባለውን ድርጅት ፈጥሯል። በዚህ ድርጅተና በደርግ መንግስት መካከል የነበረውን የፖለቲካና የትጥቅ ትግል ዘግበው የያዙ የአማርኛ ቃልግጥሞች በትንተናው ውስጥ ታይተዋል። እነዚህ ግጥሞች ኢህአዴግን የሚደግፉና የሚቃወሙ ናቸው። የድጋፍ ቃልግጥሞቹ፣ መንግስት በፈጠረው ልዩ ልዩ ችግር የተማረረውን የህብረተሰብ ክፍል ያመለክቱ የነበሩ ናቸው። ኢህአዴግን የሚቃወሙት ደግሞ፣ ከግምገማ ስርአቱና ከኢንቨስትመንት ጋር ተያይዞ በታየው የደን ጭፍጨፋ፣ ከማዳበሪያ ውድነት፣ ከመሬት ጥበት፣ ወዘተ. ጋር የተያያዙ ናቸው። የምርጫ ጉዳይም በቃልግጥሞቹ ውስጥ ተንጸባርቋል።

የድጋፍና የተቃውሞ ሀሳቦች ከተንጸባረቁባቸው ፖለቲካዊ ቃልግጥሞች በተጨማሪ፣ በሀገራችን የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ወይም ወደ አንደኛው ወገን ሳይወግኑ የነበረውን እውነታ በትዝብት የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች ተገኝተዋል። እነዚህ ግጥሞች ባንድ በኩል፤ እንደ ፖለቲካዊ ትችት የሚቆጠሩ ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል

እንደማስጠንቀቂያ የሚታዩ ናቸው። ለፖለቲካ ተቃውሞ ከሚያነሳሱት ችግሮች መካከል አንዱ ጉቦና አድልኦዊ አሰራር ነው። ይህ ማህበራዊ ችግር ከሰውልጅ ጋር የተያያዘ ሆኖ፣ በየስርአቱ መልኩን እየለዋወጠ የሚገኝ ተግባር ነው። ጉቦ አንድን ፍትሀዊና አስተዳደራዊ ጉዳይ ወይም ችግር በተገቢው መንገድ ለማየት እንዳይቻል የሚያደርግ ማህበራዊ እንቅፋት ነው። በመሆኑም በትንተናው ወስጥ ሙስና እና አድልኦዊ አሰራርን የሚያንጸባርቁ ሀሳቦች ያሉባቸው ቃልግጥሞች ታይተዋል። በተለይ ከመሬት ክፍፍል ጋር በተያያዘ የተፈጠሩት ቃልግጥሞች በወቅቱ የነበረውን አድልኦ ከማሳየት በተጨማሪ፣ የአርሶ አደሩን ምሬት፣ መከፋት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው።

በተደጋጋሚ እንደተነሳው፣ የሀገራችን የርስ በር ጦርነት ታሪክ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ነው ማለት ይቻላል። ከአጼ ቴዎድሮስ መንገስ በኋላ ያለውን ብንወስድ እንኳ፣ ወደ መቶ አምሳ አመት የሚበልጥ ነው። ከዚህ አንጻር በትንተናው ውስጥ በቀረቡት ቃልግጥሞች እንደታየው በደርግና በኢህአዴግ፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተካሄደውን ጦርነት፣ እንዲሁም ወደኋላ ባለው ታሪካችን ውስጥ ከነበረው የፖለቲካና የጦርነት ግጭቶች መካከል፣ ከአጼ ዮሀንስ እስክ አጼ ሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ማብቂያ ድረስ ባለው የታሪክ ሂደት ውስጥ የታዩትን ግጭቶችና ጦርነቶች፤ አንዲሁም ፖለቲካዊ ተቃውሞዎች የሚያስታውሱ ቃልግጥሞች ታይተዋል። እነዚህ ግጥሞች ለታሪክና ለፖለቲካዊ ጉዳዮች በታሪክ ሰነድነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ናቸው። ማህበረሰቡ በተለይ፣ አገሪቱ በአጠቃላይ ያለፉባቸውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚያንጸባርቁ በመሆናቸው፣ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ አካላት የመነሻ ሀሳብ ሊሰጡ የሚችሉ የታሪክ ሰነዶች ናቸው። በአጠቃላይ የፖለቲካ ተቃውሞም ሆኑ የድጋፍ ቃልግጥሞች፣ እንዲሁም በእርስ በርስ ጦርነትና ግጭቶች አማካኝነት የተፈጠሩት ግጥሞች፣ የነበረው የፖለቲካም ሆነ የጦርነት ሁኔታ በማሳየት እውነታውን ለመመዝገብ የቻሉ ናቸው።

በ1965/66 እና በ1976/77 ዓ.ም በሀገራችን በተዩት የድርቅና የርሀብ አመታት ሳቢያ፣ በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሚገኘው ማህበረሰብ ለርሀብ የተጋለጠባቸው አመታት ናቸው። እነዚህ የድርቅና የርሀብ አመታት ከፍተኛ የሰው ህይወት ያለፈባቸው፣ የእንስሳት ሀብት ያለቀባቸው ናቸው። በርሀቡ ወቅት የነበረውን የሰው ልጅ እልቂት፣ በገባያው ውስጥ የሚሸጥና የሚሸመት እህል መጥፋቱን፣ የእንስሳት ዋጋ መርከስና እልቂትን የሚያሳዩ ሀሳቦች፣ በቃል ግጥሞቹ ውስጥ ተንጸባርቀዋል። ርሀቡን ተከትሎ በተደረገው የእርዳታ አሰጣጥ ሁኔታ የነበረውን ችግር የሚያመለክቱ ግጥሞችም ተገኝተዋል። በተለይ አንዳንድ የእርዳታ ሰጭ

ድርጅቶች የሚሰጡት የእህል መጠን፣ በቂ እንዳልነበር የሚጠቁሙ ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሰፈራ ፕሮግራሙ ግዳጅ የነበረበት መሆኑን የሚያመለክቱም አሉ። የርሀቡ ጊዜ ካለፈ በኋላ በመጣው የምርት ወቅት፣ ሰው የተደሰተ ቢሆንም፣ ያለፈውን ርሀብ ወይም ችግር በማስታወስ የሀዘን ስሜት የተንጸባረቀባቸውና፣ የቁጠባ ባህል እንደሚያስፈልግ የሚያስተምሩ ቃልግጥሞችም ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ ድርቅንና ርሀብን መነሻ አድርገው የተፈጠሩት ቃልግጥሞች የአካባቢው ማህበረሰብ ያለፈባቸውን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ለማሳየት የቻሉ ናቸው። እነዚህ ቃልግጥሞች የአካባቢውን ማህበረሰብ ከልማዳዊ የአመራረት ሁኔታ ወጥቶ፣ ወደ ተሻለ የግብርና አመራረት እንዲለወጥ፣ ያመረተውንም በአግባቡ እንዲጠቀም ለማስቻል፣ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የመነሻ ሀሳቦች ሊገኙባቸው የሚችሉ ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ እየታዩ ካሉት ችግሮች መካከል ስደትና በሽታ ይጠቀሳሉ። በተለይ ስደትን የሚመለከቱት ቃልግጥሞች ወጣት ሴቶችንና ወንዶችን የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ እነዚህ ግጥሞች በቤተሰብ መካከል ያለውን ናፍቆትና፣ የሚገኘውን ገንዘብ በአግባቡ አለመጠቀምን የሚያመለክቱ ናቸው። በሽታን በሚመለከት የተፈጠሩት ቃልግጥሞች ከኤች.አይ.ቪ ኤድስ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ፣ የታማሚን አካላዊ ጉስቁልና ለማሳየት የሞከሩ ናቸው። ከነዚህ ችግሮች በተጨማሪ፣ ስለቤት መፍረስ የሚገልጹ ቃልግጥሞችም ተገኝተዋል። እነዚህ ቃለግጥሞች፣ መንግስት «ህገ-ወጥ» ነው በሚል ሰበብ በአንዳንድ አካባቢዎች ቤቶች እንዲፈርሱ እያደረገ መሆኑን፣ በዚህ ምክንያት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ እንደደረሰባቸው የሚያሳዩ ሆነው ታይተዋል። ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁት ቃልግጥሞች እንደፖለቲካዊ ተቃውሞ ሊታዩ የሚችሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ የሰዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚያሳዩ ናቸው።

የአማርኛ ቃልግጥም፣ እንደ ስነ ግጥም የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴን እንደሚጠቀም በዚህ ጥናት ውስጥ ለማየት ተችሏል። ከተሰበሰበው የቃልግጥም መረጃ ውስጥ በስነ ግጥም ጥናት ከሚታወቁት ዘይቤያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴዎች መካከል፣ ሰባት ያህሉ ተገኝተዋል። ከትንተናው በመነሳት፣ አነጻጻሪና ተለዋጭ ዘይቤዎች፣ አካላዊ ቁንጅናንና ውበትን አጉልተው ከማሳየት በተጨማሪ፣ ለማጣጣልና ለማራከስ የሚያገለግሉ ናቸው። ግነት ዘይቤም አካላዊ ቁንጅናን አጋኖ ከመግለጹ በተጨማሪ የምርት መጠንን አጉልቶ አሳይቷል። በስመሀዳሪ ዘይቤ፣ አካባቢያዊ ጀግንነትን በማሳየት፣ ፖለቲካዊ ተቃውሞን ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ

የሚያስተላልፍ ነው። እንቶኔ ዘይቤ፣ ከሰዎች አቅም በላይ የሆኑ ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ችግሮችን ለመግለጽ የሚችል ነው። ከተምሳሌታዊ የዘይቤ አይነቶች መካከል አንዱ፣ ተለምዷዊ ተምሳሌት የሚባለው ነው። ይህ ዘይቤ በአንድ ማህበረሰብ ወግና ልማድ፣ እንዲሁም የአኗኗር ስርአትና ህይወታዊ ገጠመኝ ላይ ተመስርቶ የሚፈጠር ነው። በመሆኑም፣ በግጥሞቹ ውስጥ የታዩት ተምሳሌታዊ ውክልናዎች ከእንስሳት (ከበሬና ከወይፈን) ጋር፣ ከአእዋፍ (ከእርግብና ድንቢጥ)፣ እንዲሁም ከአስቸጋር ተፈጥሯዊ ክስተቶች ጋር የተያያዙ ሆነው ታይተዋል። ከዚህ አንጻር ተለምዷዊ ተምሳሌት ፖለቲካዊ ተቃውሞን ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ የሚያስችል ዘይቤ ነው። ምጸት ዘይቤም እንዲሁ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመግለጽ የሚያስችል ነው። ዘይቤው ላይ ላዩን የሚያሞግስና የሚያደንቅ ይመስልና፣ መጨረሻ ላይ ባሉት ስንኞች ትችትንና ነቀፌታን የማስተላለፍ ባህሪ ያለው ነው።

ሌላው የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴ ድግግሞሽና ተደጋጋሚነት የሚባለው ነው። ለዚህ ጥናት ከተሰበሰቡት የአማርኛ ቃልግጥሞች መካከል የድግግሞሽና ባህሪ የሚታይባቸው ግጥሞች ተገኝተዋል። በነዚህ ግጥሞች ውስጥ የድግግሞሹ ፋይዳ የአካባቢውን ወጣቶች ቁንጅና እና ውበት ፣እንዲሁም አለባበስ ማስተዋወቅና ማድነቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ባህላዊ አልባሳቱ በዘመናዊ አልባሳት እተለወጡ የመጡ መሆኑን፣ አካባቢያዊ አከላለን፣ ግድያዎችን፣ መቃወም ነው። ዘይቤው በአጠቃላይ የሀዘን ስሜትን በማስተጋባት፣ ቀደም ሲል በየአካባቢዎቹ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን በማስታወስ የትውልድ ክፍተት እየተፈጠረ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ እንደታየው፣ የአማርኛ ቃልግጥም የሚከተሉት ዋና ዋና ፋይዳዎች እንዳሉት ለመረዳት ተችሏል።

1 መልካም ባህሪያትን፣ ተግባራትን፣ ጀግንነትን፣ የማበረታታትና፤ እንዲሁም፣ ልዩ ልዩ አካባቢዎችን የማወደስና የማሞገስ ጥቅም አለው፤

2 ጥሩ ያልሆኑ ተግባራትን፤ ማለትም ፍርሀትን፣ ስንፍናን፣ ሴሰኝነትን፣ የመሳሰሉትን ማህበራዊ ችግሮች የመንቀፍና የመተቸት፤

3 አካላዊ ቁንጅናንና ውበትን፣ እንዲሁም ፍቅርን በመግለጽ፣ አጉልቶ የማሳየት፤

4 ብሶትን፣ ጥላቻን፣ ቁጭትን፣ በመግለጽ የውስጥ ስሜትን ለማንጸባረቅ ያገለግላል።

5 ባንድ ወቅት በማህበረሰቡ ዘንድ በጀግንነታቸው የሚታወቁ ግለሰቦችንና፣ ተግባሮቻቸውን በማስታወስ የማሞገስ ጥቅም አለው።

6 በፓለቲካ፣ በአስተዳደራዊና በማኅበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት፣ በሰዎች ላይ ችግር ሲፈጠር የሚሰማውን ብሶትና ቁጭት፣ እንዲሁም ጥላቻን ይገልጻል።

7 በየጊዜው በሚመጡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ሳቢያ ለሚፈጠሩ የአስተሳሰብ ልዩነቶች፣ የተቃውሞና የድጋፍ ማስተላለፊያ መሳሪያ ይሆናሉ።

8 በእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ለሚታየው የጦርነት ሁኔታ፣ አንዱን ወገን በመደገፍ ሌላውን በመቃወም፣ እንዲሁም የጦርነቱን አስከፊነት ለመግለጽ ይጠቅማል።

9 ቆየት ያሉ፣ የታሪክና የአስተዳደር ጉዳዮችን በመመዝገብ ታሪካዊ ሁኔታዎችን በማስታወስ ለትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል።

10 ማኅበረሰቡ ያጋጠሙትን ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አጋጣሚዎችን፣ ሰብአዊ ጉዳቶችን፣ ለማሳየት ይጠቅማል።

11 በየጊዜው የሰውን ልጅ የሚፈታተኑትን ወቅታዊ ማህበራዊ ችግሮችን ለመመዝገብና ለመግለጽ ይረዳል።

በአጠቃላይ የአማርኛ ቃልግጥም፣ አንድ ማኅበረሰብ ያለፈበትን ማህበረ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጠመኞችን ዘግቦ የመያዝ ጠቀሜታ ያለው ነው።

7.2 አስተያየት

- በዚህ ጥናት ውስጥ ማስተዋል እንደተቻለው፣ በተሰበሰበው የቃልግጥም መረጃ ውስጥ አካባቢያዊ የቃላት ዘየዎችና የተለዩ ድምጾች ታይተዋል። እነዚህ ድምጾችና ቃላት በአማርኛ ቋንቋ ስነልሳን ጥናት ውስጥ ሊጠኑ የሚገባቸው ናቸው። ስለዚህ የስነልሳን ባለሙያዎች ትኩረት ሰጥተው ቢያጠኗቸው፤

- በአማርኛ ስነግጥም ጥናት ከሚታወቁት ስነጽሁፋዊ ሀሳቦች መካከል ስነግጥማዊ ቋንቋና ግጥማዊ ብልሀቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህ ገጽታዎች በተሰበሰበው ቃልግጥም ውስጥ ስለታዩ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች ቃልግጥሞቹን በመረጃነት በመጠቀም፣ ተጨማሪ ጥናት ቢያደርጉ፤

- ከእርስ በእርስ የጦርነት ታሪካችን በመነሳት፣ የነበረውን የጦርነት ሁኔታ የመዘገቡ ቃል ግጥሞች በተሰበሰበው መረጃው ውስጥ ተገኝተዋል። ስለዚህ፣ ቃልግጥሞቹ፣ ያለፈውን ታሪክ ለሚያጠኑና፣ ወደፊት ለጦርነት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ፣ ግጭቶችን ለማስቀረት የሚረዱ ሀሳቦችን ለማፍለቅ የሚያግዙ ስለሆኑ የታሪክና የፖለቲካ ባለሙያዎች በመረጃነት ቢጠቀሙባቸው፤

- ከፖለቲካ ልዩነቶች አንጻር ማህበረሰቡ የሚጠላውንና የሚወደውን አመላካች ሀሳቦች የተንጸባረቁባቸው ቃልግጥሞች ተገኝተዋል። ስለዚህ እነዚህን መሰረት በማድረግ የአካባቢውን ማህበረሰብ ለመለወጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ቃልግጥሞቹን በመረጃነት መጠቀም ቢቻል፤

- ለሙዚቃ ባለሙያዎች ወይም ባህላዊ ዘፈኞችን ለሚዘፍኑ ግለሰቦች ቃልግጥሞቹን እንደገና በማደራጀት፣ ለአንድ የዘፈን ድርሰት የሚሆኑ መንቶዎች ወይም አርኬዎች ስላሉ፣ በዚህ መንገድ መጠቀም የሚፈልጉ ባለሙያዎች፣ ቢጠቀሙባቸው፤

- ከተሰበሰበውና ከተመደበው የቃልግጥም ውስጥ ማህበራዊ፣ ባህላዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚያሳዩ ቃልግጥሞች አሉ። በመሆኑም የትምህርት ባለሚያዎች ቃልግጥሞቹን፣ በየደረጃው በሚዘጋጁ የማስተማሪያ መጻህፍት ውስጥ በይዘት መልክ ቢጠቀሙባቸው ጠቃሚ ይሆናሉ።

ማጣቀሻ መፃህፍት

ሀ. በእንግሊዝኛ የተጻፉ

Abrams H.M. (1981). A Glosery of Literary Terms. 4th ed. U S A; Canada.

Agizew Hadaru. (2000).“The Political History of Raya-Qobbo: 18721943”. College of Social Science; Department of History; MA Thesis;AAU.

Barnard, Alan (2004). History and Theory in Anthropology. Cambridge University Press; htt://www.cambridge.org.

Bahru Zewde. (2002). A History of Modern Ethiopia 1855-1991 2nd ed; Addis Ababa Univrsity Press; Addis Ababa; Ethiopia.

Bascom, R. William (1954). “Four Function of Folklore.” The Journal of American Folklore, Vol. 67, No. 266. pp. 333-349. Apr, 2007, From http://www.jstor.org/about/terms.html.

Bauman, Richard. (ed). (1992). Folklore, Cultural Performances and Popular Enterainment: A communication- Centered Handbook. New York; Oxford University Press.

Birhanu Gebeyehu (1998). ‹‹Islamic Oral Poetry in Wollo:›› A Preliminary Descriptive Analyisis; School of Graguate Studies;AAU.

Borland, Katherine (1990). “Documenting the Fieldwork Project.” In George H. Schoemaker (ed.), The Emergence of Folklore in Everyday Life: A Fieldguide and Source book. (pp 185-195), Indiana; Bloomington; Trickster Press.

Burns, A. Thomas (1977). “Folkloristics: A conception of Theory”. Western Folklore; Vol. 36, No. 2. pp 109-134. In Fekade Azeze (com.) (2009). Reader for Folk 805-Folklore: Theories and debates; Vol. I, Department of Ethiopian Language and Literature; Addis Ababa University.

Central Statistics Agency. (2008).” The 2007 Population and Housing Census Summery and statistical report,” Addis Ababa.

Dan, Ben Amos. (1982). Folklore in Context Essays. New Delhi; India, South Asian Publisher.

Danieal Legese (1998). ‹‹A Thematic Approach To Amharic Oral Poems Associted With the Derg Red Terror in Gonder and Gojam.›› School of Graduate Studies; M.A Thesis; AAU.

Dorson, M. Richard (1963).“Current Folklore Theories.” Current Anthropology, Vol.4, No.1, .92-113. In Fekad Azeze (com). (2009). Reader for Folk 805- Folklore: Theories and debates. Vol. I, Department of Ethiopian Language and Literature; Addis Ababa University.

Dorson, M. Richard. (ed). (1972). Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago; The University of Chicago Press.

Dundes, Alan (2005).“Folkloristics in the Twenty- First Century.” The Journal of American Folklore; 118(407),pp.384-408.by the Board of Trustees of the University Of Illinois.

Fekade Azeze. (2001). “The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect.” Journal of Ethiopian Studies; Addis Ababa University; Institute of Ethiopian Studies; Vol. xxxiv; No. 1. pp. 43-85.

_____(2010). “A Folklore Guidebook For Ethiopia: An Introduction to Definitions and Categories,Field Methods,and Resources for Revitalising Foklore,” Department of Ethiopia Lnaguage and Litrature, Addis Abeba University (unpublished).

Fekadu Begna. (1990). “Land and The Peasantry in North Wollo 1941-1974 Yejju and Raya Qobbo Awrajjas”. MA Thesis; The Scool of Graduat studies; AAU.

Fine, C. Elizabeth. (1984). The Folklore text: from Performance to Print. Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press.

Finnegan, Ruth. (1970). Oral Literature in Africa. Nairobi; Kenya; Oxford University press.

_____.(1977). Oral Poetry: Its Nature, Significance and social Context. London; Cambridge University Press.

_____.(1992). ‘Oral Poetry: in Richard Bauman (ed). Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments: A Communication Centered Handbook. Pp. 119-128. New York: Oxford University Press.

Getie Gelaye.(2001). Amharic Oral Poems of East Gojjam: Text; classification Translation; and Commentary; Hamburg Germany.

_____(2000)."Peasants and The Ethiopian State: Agricaltural Producers' Cooperatives and Their Reflections in Amharic Oral Poetry";A case study in yetnora;East Gojjam;1975-1991;Hmburg:LiT.

Goldstein, S. Kenneth. (1964). A Guide for Field workers in Folklore. Hatboroo; Pennsylvania; Folklore Associates inc.

Kothari; C.R.(2004) .Research Methodology:Methods and Techniques. New Age International;India.

Jackson, Bruce (1987). Field Works. Chicago; Urbaana; University of Illinois Press.

MacDonald A. Donald (1972). "Field Work: Collecting Oral Literature." In Richard M. Dorson (ed), Folklore and folk life: An Introduction. (pp. 407-430), Chicago and London; The University of Chicago Press.

Mesfin messele (2000).‹‹Abbawude Oral Poetry in South Wollo.››A Descriptive Analysis; School of Graduate Studies; AAU.(M.A Thesis)

Okpewho, Isidore. (1992). African Oral Literature: Background, Character, and Continuity. Bloomington and Indianapolis; Indiana University Press.

Schoemaker H George ed (1990) The Emergence of Folklor in Everyday Life A Fieldguide and Sourcebook Tickster Press Bloomington Indiana

Sims, C. Martha and Stephen, Martine. (2005). Living Folrlore: An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan; Utah state University Press.

Shebeshi Lemma.(1986)."A Thematic Approach to Famine-Inspired Amharic Oral Poetry;AAU;School of Graduate Studies(Unpublished).

Tesfaye Mesele. (2007) "Subject Matter Analysis of Amharic Lyric Poetry in Raya." AAU; ILS; Department of Foreign Language Studies (unpublished).

Turner, Rory and McArthur H.Phillip. (1990). "Cultural Performance: Public Display Events and Festivall." In George H. Shoemaker (ed.), The

Emregence of Folklore in Everyday Life: A Fieldguide and Sourcebook. (pp/ 83-93) Indiana; Bloomingotn; Trickster Press.

Vansina, Jan. (1985). Oral Tradition as History. Nirobi; Heinemann Kenya.

ለ. በአማርኛ የተጻፉ

መስፍን ወልደማሪያም። (2005)።መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ።ሊትማን፤ISBN 978-99944-854-4-4 አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ።

መረራ ጉዲና።(2008)። የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎችና የሚጋጩ ህልሞች። ግራፊክ አታሚዎች።

ሞላ መኮንን:: (1986):: "በቆቦ ወረዳ የተነገሩ ፖለቲካ ቀመስ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ፣ ዲማፅ፣ አ.አ.ዩ /ያልታተመ/

ሽመልስ ፍሬው:: (1974):: "በአምባሳልና በየጁ አውራጃዎች የወያኔዎች ውጊያና ግጥሞቻቸው" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ፣ ድማፅ፣ አ.አ.ዩ. /ያልታተመ/

ብርሃኑ ገበየሁ:: (1995):: "የስነቃል ምንነት፣ ዘውጎችና አተናተን" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ፣ አ.አ.ዩ /ያልታተመ/::

_____(1999)። የአማርኛ ስነግጥም ፡ ንድፈሀሳብ፤ማብራሪያ፤ትንታኔ። አዲስ አበባ፤

ተክለሀይማኖት ገ/ፃዲቅ:: (1988):: "በራያ ለጋዛ ዘማቾች ይቀርቡ የነበሩ የጀግንነት ማነሳሻ ግጥሞች" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ፣ ዲማፅ፣ አ.አ.ዩ /ያልታተመ/

ተክለጻዲቅ መኩሪያ።(1981)። አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት። ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣አዲስ አበባ።

አለማየሁ ሞገስ። (1948)።የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ።ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፤አዲስ አበባ።

አልማዝ አበበ:: (1974):: "አዝማሪና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ"፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ዲማፅ አ.አ.ዩ /ያልታተመ/::

አልፋ አታሚዎች።

ዘሪሁን አስፋው።(1992)።የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን።ንግድ ማተሚያ ቤት፤አዲሰ አበባ፤ኢትዮጵያ።

የሰሜን ወሎ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ .(2005)፤‹‹የዞኑ አጠቃላይ ሁኔታ››፤ወልዲያ፤/ያልታተመ/።

ያለው እንዳወቀ:: (1989):: <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር::</u> አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች::

ደሰታ ካሳ (1985)፡፡‹‹በደርግ መንግስት ላይ የተገጠሙ ስነቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና›› ፤አ.አ.ዩ.፤ዲ.ማ.ጽ፡፡

ጌቱ ገላዬ.(2000).‹‹ከ1983 የመንግስት ለውጥ በኋላ የምስራቅ ጎጃም ገበሬዎች የገጠሟቸው ፖለቲካዊ ግጥሞች››Proceedings The xiv International Confrence of Ethiopian Studies; Nov 6-11; Institute of Ethiopian Studies; Addis Ababa Uinversity; ggelay@yahoo.com.

ጳውሎስ ኞኞ፡፡ (1984)፡፡ <u>አጤ ምኒልክ፡፡</u> ኤሚይ ፕሪንተርስ፣

ፈቃደ አዘዘ:: (1991):: <u>የስነቃል መምሪያ::</u> አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች::

አባሪዎች፡-

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ

ተ.ቁ.	ስም	የመኖሪያ አድራሻ	እድሜ	ስራ	ተጨማሪ ማብራሪያ
1	አምሳ አለቃ መላኩ ተገኝ	ወልዲያ	85	ጡረተኛ	የራያና የየጁ ወረዳዎች ፖሊስ አዛዥ የነበሩ
2	አቶ አዳነ ጥላሁን	ወልዲያ	70	ጡረተኛ	
3	አቶ አያሌው አሰፋ	ሳንቃ-በለስ	74	ገበሬ	
4	አቶ አብርሀ አስፋው	መርሳ 02	55	መምህር	
5	አቶ ተበጀ መኮንን	መርሳ 02	69	ገበሬ	
6	አቶ አሊ መሀመድ	መርሳ 04	70	ገበሬ	በቃላቸው ግጥም የሚደርሱ
7	አቶ ሞላ ገበየሁ	ቆቦ 03	65	ገበሬ	በቀልድ የሚታወቅ
8	አቶ ደሳለ ፈንታው	ቆቦ 03	60	ገበሬ	ወልዲያና ቆቦ የኖረ
9	አቶ ዘውዱ ፈንታየ	ቆቦ 06	35		መንደፈራና ቆቦ ያደገ
10	አቶ ሞገስ አያሌው	ቆቦ 03	40		
11	አቶ አበራ ካሳው	ጎብዬ	75	ገበሬ	ራዛ ዘማች የነበሩ
12	አቶ አበራ ሞላ	ቆቦ	36	ገበሬ	በባህል ጭፈራ የሚታወቅ
13	አቶ አስማማው አምባው	ቆቦ 01	50		የባህል ኪነት የነበረ
14	አቶ ፈንታየ አሸብር	ቆቦ 02	55	መምህር	የባህል ኪነት የነበረ
15	አቶ ታደሰ ተሰማ	ቆቦ 03	45	ፖሊስ	የባህል ኪነት የነበረ
16	አቶ አዲሱ አሰፋ	ዞብል	50	ገበሬ	ቀረርቶ፤ጭፈራ፤ዘፈን የሚችል
17	አቶ ብርሀኑ ይግዛው	ሮቢት	40	የግብርና ሰራተኛ	የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሞያ
18	አቶ ተስፋየ ሞላ	ቆቦ	60	ገበሬ	በጓደና ህይዎት ያደገና የአፋር ወዳጆች ያሉት

አባሪ ሁለት፡- የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች

የተሰበሰበው የቃልግጥም መረጃ ምደብ

1ኛ/ የሙገሳና የውዳሴ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

1.1.አካባቢን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ

1.ከልካይ አባ መሬ

ያነ ማዶ፤ተሮ በሩ

የነቸኮል መንደር……

ያነ ማዶ፤ተሮ በሩ

እንኳን ሰው ቁሞበት ያስፈራል ግራሩ

2.ያነ በሩ፤ዙብል በሩ

የቀኛማይ አገር

የአሰፈ ሀይሉ አገር

የቸኮል አሊ አገር

ጌጡ ጎበዜ አገር

የነ ምስጋን አገር፤የነ ምስጋን በላይ

ያነ በሩ፤ዙብል በሩ

እንኳን ሰው ቁሞበት ያስፈራል ግራሩ

3.ኧረ ተው ጥይት አታበላሹ

ኧረ ተው ብረት አታበላሹ

የራያ ልጅ ነው ፈጥኖ ደራሹ

የየጁ ልጅ ነው ማልዶ ደራሹ

4.መወለድማ የትም ይወለድ

ለማደጉ ግን ራያ ይደግ

ለማደጉማ የጁ ላይ ይደግ

እንደ ፈጣሪ ነፍስ የሚታደግ

5.እንደምነው በዋ ያ ግድም
አንጋዳው ብዙ ነው አያረማምድም

6. የዳሞቶ ሽታ የእንቦሳ ጫጫታ የለመደ ልጅ
ቅቤ በገበታ የለወሰ ልጅ
አይሄድም ርቆ ይከፋ እንደሁንጂ

7. የእንቦሳ ጫጫታ የድንጋ መንገሌ
አገራቸው በዋ፤ በዋ ንጉስ ጋሌ

8.እናተ ጓደኞች መንገድ የጠፋችሁ
ላይኛውን ቡርቃ ሰባቱን አርጋችሁ
በዋ ንጉስ ጋሌ ወናሳ አለላችሁ

9. ወይ እንደ ቆቦ ልጅ፤
ነጭ ጤፍ ማሽላ ወስደው ካላቀኑ
ወይ እንደጨርጨር ልጅ፤
ቡሻ ከመዳፊያው ጊደር ካላበሉ
ወይ እንደ ዞብል ልጅ፤
እገጭ እገው ሲል ልብን ካላመኑ
አሁን ወይት ይገኛል ወተት ሞይዘር ቢሉ

10. የራያ ልጅና የጉራሶ ዱላ
 ዘሎ ድርግም ነው በላኩቱ ሁላ

11. እኔ ለዋጃ ልጅ፤ እኔ ለዞብል ልጅ
እኔ ለወርቁ ልጅ፤ እኔ ለጉራ ልጅ
እኔ ላማያ ልጅ፤ እኔ ለጮቢ ልጅ
እኔ ለራያ ልጅ፤ አያስማኝ ክፉ
እንኳንስ ልጆቹ አይቆረጥ ዛፉ
እንኳን ጎበዞቹ አይነካ ዛፉ

12. በጣሳ ቢሸመት ስስት የለብሽ
ያባ ዘበን አገር ቆቦ እንደምነሽ
ቆቦን ያቀና ሰው ለምን ይኮነናል
እንኳን የሰው ልጁ፤ውሻው ጤፍ ይበላል

13. ባገኝ እበላለሁ ባጣም ጦሜን ልደር
ልሂድ መንደፈራ ከሶስቱ አበበ አገር
ልሂድ መንደፈራ ካበበው ደረት
ሲሆን ማር ይገኛል ያለዚያ ወተት

14. ዋጃና ጃሮታ መሀል ባቦ ኩርማ
የበላንበቱ የጠጣንበቱ ንጥር እንደ ሎላ

15. አረንጓዴ ለብሶ ይደንሳል አሳ
ምነው የቀድሞውን አናነሳም እሳ
የቡጢ ባቤ አገር እንዴት ነው ፎቂሳ

16. ጠመንጃው ሞይዘር ነው ጥይቱ ዘጠና
የዳውድ አደም አገር እንዴት ነሽ አላይና

17. እውር ያለመሪ የሚሄድብሽ
አረቂ በጠርሙስ፤ጠጅ በብርሌ፤ የሚጠጣብሽ
ያባዘበን አገር ቆቦ እንደምነሽ

18. ይሄ በዋ ማለት ጭንጫ እየመሰለ
ያበቅላል ሽጋ ልጅ እያዘናፈለ
በዋ ንጉስ ጋሌ ስንደዶ ማለፊያ
ወገቧ ቀጭን ነው እንደ አሳ መጥለፊያ

19. ከታረሰው መሬት ከተከሰከሰው
ያበቅላል ራያ ነጭ ጤፍና ሰው

20. ዙረው ዙረው አለኝ፤ ቆቦ ሜዳውን
ዙርው ዙረው አለኝ፤ ዞብል አፋፉን
ዙረው ዙረው አለኝ፤ ቆባ ጠጠራን
ዙረው ዙረው አለኝ፤ ቅልሻ በሩን
ዙረው ዙረው አለኝ፤ ራማና ቦረን፤ እራስ አሉላን
እንዴት ነህ በሉልኝ፤ አርበት ጠበለትን
እንዴት ነህ በሉልኝ፤ በዋ ንጉስ ጋሌን
እንዴት ነህ በሉልኝ፤ ዴላና ብረይሊን
እንዴት ነህ በሉልኝ፤ ታች ጉራ ወርቁን
ደህና ደህና ጎበዝ የቆየበትን
የቸገረ ጊዜ የማዋየውን

21. ዞብል በራ በሩን፤ ብዞረው ብዞረው
አላይና ጎሊናን፤ ብዞረው ብዞረው
ጠቢሳ መለኮሳን፤ ብዞረው ብዞረው
ቡታና መርፊታን፤ ብዞረው ብዞረው
ታቹን ጉባጋላን፤ ብዞረው ብዞረው
ቁዬው ብቻ ቀረ የማይናገረው
ካቡ ብቻ ቀረ የማይናገረው

22. አትንኩት ያመኛል፤ አራቱ ጋሪያን
አትኩት ያመኛል፤ ቦረን አፋፉን
አትንኩት ያመኛል፤ ወርቁ ጎራውን
አትንኩት ያመኛል፤ ጎመጅ አፋፉን
የከፋው ወንድ ልጅ አሳዳጊውን
በረጅሙ ከርፎ የሚያጠጣውን

1.2. የሰርግ ላይ ሙገሳዎች

1. እኔን ደስ የሚለኝ
   በሬ የሚነዳ
   ባረባባ ድግስ አይሸኝም እንግዳ
   ቅዱ እንዳለ ውሎ ቅዱ እንዳለ ነጋ

2. መዳዳሩን ዙብል ተዳዳር
   መዳዳሩን ጨርጨር ተዳዳር
   /ባለሰርጉ ይጠራል/ዳሱን አሳምር

3. መሸረዳ ቆንጆ
   ተረከዘ ሎሚ
   ራሰ ዘናና የወለዱ እንደሆን
   ታመጣለች አማች ቀኝ እጅ የሚሆን

4. ትድሩ እንደሆነ እንደከሌ ዳሩ (ባለሰርጉ ይጠራል)
   በአንዳንድጋንጠላሰውአታስቸግሩ

5. በወዳድል በሬ ወትውቶ ወትውቶ
   ይቀዳው ጀመረ በርሚሉን ጎልቶ

6.ረጅም ነው ዳሱ ሸበቆም አይደርሰው
   አባት የሰራውን ልጅም አያፈርሰው

7.ምን ያለው አማጭ ነው የተክለፈለፈ
   ማሩን ከወተቱ ደብልቆት አረፈ

8.ሽልሙነ፤ሽልሙነ፤ሽልማት ደግ ነው
   ሽልማቱ ለኛ ስሙ ለናንተ ነው

9.ስጠው በጣም፤ስጠው በጣም
የፊቱን ካላየ የኋላው አይመጣም

10.ስጠው ብረት የተወለወለ
ልጁም የኮራ ነው የተንጠበለለ

11.እዩት እዛማዶ አንድ እግር ሽምራ
(የሙሽራው ስም ይጠራል)አዲሱ ሙሽራ

12.የሙሽሪት እናት ቁሚ ተጠየቂ
የጠመቅሽው ጠላ ጠጅ ነው አረቂ

13.የሙሽሪት አባት ደስ ይበልህ ደስ
ፈረስ ያስጋልባል ያሰራኸው ዳስ

14.ሴቶች ተሰብስበው ሙያ ሲቋጠሩ
የሙሽሪት እናት (ስም ይጠራል)በላይ ትሁን አሉ

15.የሙሽሪት እናት ቁሚ ተከሰሻል
ይችን መሳይ ቆንጆ ማን ውለጅ ብሎሻል

16.በጎተራ ነው ወይ የተጠነሰሰው
ቢቀዳው ቢቀዳው አላልቅ አለ ምነው

17.ቢቀዳው ቢቀዳው አያልቅም ድግሱ
የመቻሬን ሜዳ የመሰለው ዳሱ

18.ጠላት ለመቀንቀን ምንግዜም አያርፍ
አምላክ የኪለው ኩል ቢያብሱት አይረግፍ

19.እገሌ አባባሉ ጠንካራው ገበሬ
ደግሶ ይድራል በሶስት አመት ጥሬ

20.እሷን ጥሯት እንጅ ጋኒቱን ጋኒቱን
የእነ እከልየ እናት ሸጋ ወላጂቱን
እከሌ አባበሉን መልካም ወላጅቱን

21./እከሌዋ አበሉ/ እንዳትሞ/ችብኝ/ ትብኝ
የቀኑ ጨለማ እንዳይሆንብኝ

22.ወንድሞቼን ሁሉ እወዳቸዋለሁ
እህቶቸን ሁሉ እወዳቸዋለሁ
ለእከሌ አበሉ ግን አደላላ/ለ/ታለሁ

23.ሮቢላ ሲሄድ ይላል በራ በራ
አሁንም ቀድሞም የኔ እከሌ አበራ
ገለጥ ገለጥ ያለው የግንባሩ በራ
የመኪና በሬ ያርሳል እያበራ
ውስኪ ለዝና ነው ደም ያጠራል ቢራ
መጫወት ደግ ነው ነፍስ ያወቀ ጋራ

24.አፍንጫ ቢገተር የንፋስ እዳ ነው
እንደ እከሌ ቆንጆ ጉርዶ መሆን ነው

25.ምነው ትለኛለህ ጉርድርድ ያለይ
የእከሌ አበሉ ልጅ፤ የኔማ እከልየ
ደሞ አደ ወርቀየ አትለኝም ወይ

26.የደረት ሀብሌን የጆሮ ወርቄን
ቁሜ ጠበቃየ ስታስር ዋሴን
ሞት እንዳይነካብኝ እከሌ አበሉን

27.ይርሳኝ እረስቼ ሰው ረስቻለሁ
የኔ እከሌ አበሉ ሳልለ ቀርቻለሁ

28.ማነው ጥቁር ያለው እከሌ አበሉን
የኔ አማሪካየን የውጭ አገሬን

29.የሽንብራ ስንቄን የክፉ ቀኔን
ሞት እንዳይነካብኝ እከሌ አበሉን

30.አይኑ የሚመስለው የንጋት ጨረቃ
አንገቱ እሚመስለው የጃምዩ መቃ
ደረቱ እሚመስለው የገብሬልን ሳንቃ
የእከሌ አበሉ ልጅ፤ ሽጋ እከሌ አበሉ፤
ሴቶች አንተን አሉኝ እንግዲህ ምን ይብቃ

31.ይህን ሁላ ቆንጆ አላውቀው ስሙን
ይህን ሁላ ጎበዝ አላውቀው ስሙን
እንደው በደፈናው የሎሚ ሽንሽን

1.3.ጎበዝ ገብሬን የሚያሞግሱ/ከነበሬው/

1. በሬው አመለኛ ያገኘ አይጠምደው
ጢት የተጠመደ ማታ እሚፈታው

2. ኧረ በሬው ንጉስ፣ኧረ በሬው ሌዶ
እንዲሄድ ቦይ ለቦይ
ካረባው ደጃማይ እኛ አንሻልም ወይ

3.ግዛ ግዙ ገሎ አገሩን ከመልቀቅ
አቦላ ደጋሌት ከጎድጓዳው ማምረት

4.በጎባባ ሞፈር በፈሮ ማረሻ
ካልነገነጉበት በራው እስቲጎብጥ መራቱ እንስቲንጫ
አይከፈት በሩ ለመቀላወጫ
አይገኝም ጠላ በትላልቅ ዋንጫ

5.በሀራም አንተ ነህ
ጉጉብዱም አንተ ነህ
በቆቦም አንተ ነህ
በዙብል አንተ ነህ
በራያም አንተ ነህ
የመጋል ባለቤት ምን ቦደረኛ አለህ

6.አለው ወደል ግመል ሸኸም እማይፈራ
አለው ሸጋ በሬ ቀዳም እማይፈራ
አጣሁ ብሎ አይለምን አለኝ ብሎ አይኮራ

7. አንጀቱ ግብርና አከታትሎ ማረስ
አዲያ አይቀርምና እንደጎታ መፍረስ

8.የተትረፈረፈው ባውንዱ በኪሱ
የሰው ዋስ አይጠራም ማረሻው ነው ዋሱ

9.ትገሉ እንደሆነ ነጭ ጤፍ ግደሉ
አቦላ ግደሉ
ሰው የገደለ ሰው ከርቸሌ ገባ አሉ

10.ያርሳል በጠራራ ይጠምዳል ማለዳ
የኮራ ባለቤት አይፈራም እንግዳ

11.የግራውን በሬ ካላውረገረጉት በዋጮ ጉማጅ
ባንገታም ብርሌ አይገኝም ጠጅ

12.አምሮህ እንደሆነ እምብርታም ጊደር
አምሮህ እንደሆነ ዳውሪ ጊደር
ደሞ እንደዋጃ ልጅ ከመሌው እደር

13. ከጠጅ ቤት ገብቶ ያለው ቅጅ ቅጅ
የበሬውን ጫንቃ ተማምኖ ነው እንጅ

14. ገበሮይ ጥመዱ ማለዳ ተነሱ
ገበሮይ ጥመዱ ከቀዳሙ እረሱ
ከባልንጀራ ፊት እንድትደግሉ

15. ምን ያደርግልሃል ተበድሮ ጠላ ተበድሮ ጠጅ
ሜዳውን በበሬ፣ዳገቱን በዶማ፤ መቆፈር ነው እንጂ

16. እያረሰው እንጂ እያንደፋረሰው
እህል አፈር አይደል ከመሬት አያፍሰው

17. እርሻ ያረሰና የወንዝ ዳር ዛፍ
ይኖራል ዘላለም አበባው ሳይረግፍ

18.አረንዛ ዋጠኝ ከነገልበቴ
መጋል አወጣኝ የነፍስ አባቴ

19.እርሻ እረሱ በጎባባ ሞፈር
የሰው ቤት እንጀራ ይላል አፈር አፈር

20.መጋላ በሬ የጠመደ ሰው
እንኳን ለራሱ ይተርፋል ለሰው

21.የመጋል ባለቤት ያወጣል እዳሪ
አይላትም ሚስቱን ከሰው ተበደሪ

22. በረጅም ማረሻ ምድር አስጨናቂ
ከጎድጓዳ መሬት መቶ መቶ ወቂ

23.ዝምበል ባለ መቶ ባለ ሺ ይናገር
መስከረም አዝላቂ ያንድ ምስለኔ አገር

24.በከፋታ ዋንጫ የሚያጠጣውን
በጎባባ ሞሰብ የሚያበላውን
ያረባ ገበሬ ገረፈው ሽንጡን

25.ካረሱም አይቀር ሞፈር ከበሱ
የመጋል ጌታ ያ ነፍሰ ቢሱ

26. ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ
ወፍጮው እንዳጎራ መስከረም ዘለቀ

27. እርሻ እረሱ አትፍቱ በጊዜ
ጎተራው ከሞላ አይታጣም ሚዜ

28.እርሻ እረሱ፣እርሻ እረሱ በጣም
እርሻ ያረሰ ሰው ጥቁር ውሀ አይጠጣም

29. በሬውን ግረፈው ወስኮው እስቲንጫጫ
ጠላ መጣፈጡ በመጋላ ዋንጫ

30. እኒህ ገዳዶየ፣እኒህ አባይጋሞ
እኒህ ውርቱ በታይ፣እኒህ ገደመዩ
ግብርና አነጠሩ
ጤፍ እንደማሽላ በመሬት ሰፈሩ
ምነው ባለግመል ባለጊደር ሆኑ

1.5.ሴቶችንና ወንዶችን የሚያሞግሱ

1.5.1.ሴቶችን በስም ጠቅሰው የሚያሞግሱ

1. ማረይ ጉበሳ ታማ ጉብሳየ ሲጨነ
ሰላሳው ምናምን ከነአህያው ይለቅ

2. ሰላሳው ምናምን ጭቁኑ ምን አርጎ
እሷ ትሙት እንጂ የበላችው በርጎ

3. ማረይ ጉበሳን ብየ ሲሄድ አጥር ለአጥር
ዋጋየን አገኘሁ ሰባት አመት ንጥር

4.ዋጃ ኸኮረራው ይሰራልኝ ማማ
ሸንጋ አንባሻ ታየ ሲሏት እንድሰማ

5. አሁን አልደርስም ወይ ብሮጥ ብንደረደር
አንባሻ ታየ ጋር ዋጃ ላይ ለማደር

6. አረገረገ አሉ ዋጃ ከተማው
አረገረገ አሉ ቆቦ ከተማው
ሸጋ አንባሻ ታየ ስታልፍ ረግጣው

7.አሸቸ እንዳልበላ መሃል እጀ ታሞ
ሸቋር መንገሻ አገር ወርቁ ገለሂሞ

8. መጫ ጤፍ አለችኝ ያችን ሰላልቁ
ሸቋር መንገሻ አገር መሄዴ ነው ወርቁ

1.4.ወንዶችን በስም ጠቅሰው የሚያሞግሱ

1. ያንድ ሊቀመንበር ያንድ አገር ሰው ናቸው
ተመለሱ እያለ እየለመናቸው

ከጎድባው ውስጥ ሆኖ ከኮባው ጣላቸው
እነ አይመከሬ ካላኮርሜ ናቸው
ያ ይርጋ አባምንጃ ገትሮ አዋላቸው

2. እከደከ ብረት አይመታም መስሏቸው
አርበት ከኮባው ላይ አንስቶ ጣላቸው

3. ና ተያዝ ና ታሰር ዳኝነት ባልነበር
አንድ ሰው ላንድ ሰው መች ይሸነፍ ነበር

4. እንኳን አላማጣ ቢጣፍ ለላይ ደሴ
መግደሉን አይታውም ከወየ ደረሴ

5. የላይኛው በሬ ሽቅብ ሲመለስ
የታችኛው በሬ ቁልቁል ሲመለስ
ማን ጋር ተጠመደ ይርጋታ ንጉስ

6. ሴቱ ሽብራር ሲጭን ወንዱ ላም ሲያጣባ
የአደም ወዳጆ ልይ፤ ገሏል በማለዳ፤ በሱቢ ገማማ

7.አባልቼ ብለው እሱ አምርሮ ኖሮ
ገዳይ በምንሽር የዱር ፍሬ በልቶ

1.5.እንስሳትን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ ቃልግጥሞች

1.ላሞቹን ንዲቸው አባራው ይነሳ
ይከተል የለም ወይ ኮርማው እያገሳ
በሰላጤ ቀንዱ ምድር እየበሳ

2. ያልታደሉ ላሞይ
እንደው በዚህ ወራት
እንደው በኛ ጊዜ ከኛ ተጠግተው

ጋታቸው አረረ የአመለ ጭድ በልተው

3. ባሰሚት ነው እንጂ ያቺ ላም ጨሃለይ
አሻግሮ እሚተኩስ እረኛ ብላለይ

4.አንቺን ከሚከፋሽ እኔን ይክፋኝ ብዬ
ገባሁልሽ ከሎ ቀጮዬን አዝዬ

5.መችም የዞብል ልጅ አለበት ብዙ እዳ
መቼም የወርቁ ልጅ አለበት ብዙ እዳ
ልጅ እማያሳድግ ላም እማያስነዳ

6.እናንተ ጓደኞች መንገድ የጠፋችሁ
ላይኛውን ቡርቃ ሰባቱን አርጋችሁ
በዋ ንጉስ ጋሌ ወናሳ አለላችሁ

7.የአደም ወዳጅ ላም ዳቡሌ ገውስ
ማን ነው የሚነዳሽ እኔ አፈር ሳልቀምስ

8.የአደም ወዳጅ ልይ አንተ አፈ ወድሉ
ዳቡሌ ገውስን አስወሰድኻት አሉ

9.የአባተ ሀይሉ ላም የቀይ ቦራይቱ
ምንሽሩን ይዛ ገበይ ከበረቱ

10.የምስጋን በላይ ላም ዋርሌ ቀይቱ
ምንሽሩን ይዛ ገባይ ኸበረቱ

11.የምስጋና በላይ ላም መገን ዲሌ ሮይታ
አላስነካም አለች ከራሳው ተኝታ

ከዞብል ጓደኛ አብረው ከበሉ፡ቱ
አብራ ትሞታለች ዋርሌ ላሚ፡ቱ

12.የምስጋን በላይ ላም፤
አትበላም ገለባ አጠጣም ልማት
እንደው ዝም ብህ ደራይቶ ንዳት

13.ከምስጋን ወንድሞይ ከተወለዱ፡ቱ
ከዞብል ጓደኞይ አብረው ከበሉ፡ቱ
አብራ ጋደም አለይ ዋርሌ ላሚ፡ቱ

2ኛ.ስንፍናን የመተቸት ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

2.1.ሴቶችን የሚተቹ

1.ዘንድሮ ሚስቲ፡ቱን እኔ አግብቻታለሁ
ማታ ስንተኛ እሷ ትቀድማለች
ማልዶ ስንነሳ እኔ እቀድማታሁ
በጧት ተነስቼ በሮቼን ጠምጀ
ምራን ተበጥሶ ልቀጥል ብመጣ
አይኗን እየዳጠች ገና ደይ ልትወጣ

2.አንምዳና አንምዳ የጋገሩት ቂጣ
ካሪያው ተለምጦ በመሳጊያ ወጣ

3.ሴቶች ተማሩና ሆኑ ፍርድ ሸንጎ
እንግዲህ ደህና ሁን ድስትና ምጎ

4.ከዘራሁት እህል ዳጉሳ ነፍስ አውቆ
ድረሱልኝ አለች ጉሮሮዋን አንቆ

5.እንደው ወጣ ገባ በይበቱ ከቤቱ
የሙያውን ነገር ያውቃል ጎረቤቱ

6.ይኸን ፈርቼ ነው ተይው የምልሽ
ግልድሜን ብገፍሽ ምን ትለብሻለሽ

7.ነግሬሽ ነግሬሽ ነግሬሽ ሳበቃ
ወዶት ደንበር ደንበር አዋቂ ጥየቃ

8.በአስራ አምስት አመቷ ብታሰራ ኩታ
እናት እና አባቷ ሊሞቱ በደስታ

9.ካንቺ ቂጣ መውደድ ቂቤ ተጨምሮ
አዝመራ ቀሎኛል አልቻልኩም ዘንድሮ

10. ጀበና ታቦቱ ሲኒ ሊቃቂቱ
መገነጣ ጠፋ እናቷ ቢሞቱ

11.የእንቅልፍ አጀቡ ባል በሩቅ ያስታውቃል
ከግር እስከራሱ ባቡጀዲ ደምቋል

12.እንደ አገልግሉ ጥጥ ጤፉ ቢበረክት
አመት በበላን ሳንለፋ ሳንታክት
ጣቷ ረጃጅም ነው ቂጣ ለመጋገር
እንዝርት አታሳዩዋት ትጠፋለች ካገር

13.ማለዳ ተነስተሽ ቡና ቡና በይ
የጥጡማ ነገር ቀርቶ የለም ወይ

15.አራሹም እኔ ነኝ ፈጭታው ፈረንጂ
እንደው ለንትርክ ተጋብተናል እንጂ

16.ጤፍ ብሸምትላት ምንም አልጠቀማት
ማሽላ ብሸምት ምንም አልጠቀማት
ጥጥ ብመዘንላት አመት አከረማት

17.በወር ልቅ በወር ልቅ ባመሽ ልቃቂ
አላዋጣሸኝም በይ ቤቱን ልቀቂ

18.ውሃም እንዳትቀዳ ውሃ ልማት መጣ
እንጨት እንዳትሰብር ኩንታል ከሰል መጣ
ወፍጮም እንዳትፈጭ ካባሜንቶ መጣ
ወንዱ መነመነ ሴቱ ቂጥ አወጣ
ሽማግሌ ና እና ይህን ጉድ ፍረደኝ
ምሳዋን ትብላና ቤቱን ትልቀቅልኝ

19.በዳጉሳ እንጀራ በጉዋያ ሰላሱት
ትበላ እንደሁ ብላ የቀረ አነሳሁት

2.2.ወንዶችን የሚተቹ

1.አያርስም ወይ አይጠምድም ማልዶ
ፈትተሽ ነይ ይላታል የሴት ጥሬ ለምዶ

2.አያርስም ወይ አይጠምድም ወይ ማልዶ
ማን ፈታች የሚለው የሴት ጥሬ ለምዶ

3.አጋሙን መንጥሮ እንዳይዘራ እህል
አሻግሮ ይመኛል የሰውን ክምር

4.ምን ያደርግልሃል የምላስ ጉልበት
አጋሙን መንጥረህ እህል ዝራበት

5.ማረስ ምንአባቱ ማጨድ ምንአባቱ

እርዳታ ነው እንጂ የሰው መድሀኒቱ
ና ውጣ ና ውረድ ብሎ ከማለት
የእርዳታው እህል በኬሻ መመላት

6.ይህን የእርሻ ስራ አልተውም ብላችሁ
እኔ ቀን ወጣልኝ እናተ አለቃችሁ

7.እኔ ከገለባው ምን አለኝ ከምርቱ
መንግስት ይሰጠናል አትንከራተቱ

8.ነጋዴ ነው እንጂ የአገሩ ንጉስ
ገበሬ ቢኳትን ዘሩን አይመልስ

9.የነጋዴ ልጅ መስለሽኝ ነው እንጂ
ለካስ አመዳምነሽ የገበሬ ልጅ

10. አዬ መከራዬ ገጠር ተወልጄ
አልላቀቅ አለኝ መቆፈሪያው ከጄ

11.ማረስ ነው እንጂ እጅ እስኪቆስል
ምንድነው መስረቅ ውሻ ይመስል

12.ጌታው ለጌታ አድሮ ሳያውቀው ብልሀቱን
ሲለምን ያመሻል እንደ ውሻ እራቱን

13.ሰኔን ጠሀይ ፈራ ሐምሌ ጭቃ ፈራ
ልጁ ቢያለቅስበት በጅብ አስፈራራ
ልጁስ አለቀሰ እንደው ዝም ብሎ
ከራብ የበለጠ ምን ጅብ አለ ብሎ

14.በቦላሌ ሱሪ መይ ታድራለህ አለይ
ከረጅም ጭንቁላ እጇን ካልከተተይ

15.በሸ ብር ሽርጥ እያለ እርሽም እርሽም
እናቱ እምትበላው ቁና ጤፍ አላሸም

16.እነ ባለ ሽርጥ እነ ጣተ ለምለም
ከቤቱ ሲገባ የሚቀመስ የለም

17.ከንፍሮው ጭንቁላ እጇን ካልነከሯት
ሴት አትቀመጥም ጉንጯን ቢስሟት

18.ሲቆፍሩ አይቆፍር ሲያርሱ አያርስም እና
ሰው ዋለብኝ ይላል መላ ተገኘና

19.ተጋድሞ እየዋለ ከቤቱ በላይ
ውለውብኝ ይላል አያጣም ጠንቋይ

20.ያላረሰ ሰነፍ እርፍ ያልነቀነቀ
ሙቀጫና ወፍጮው፤
በሰኔ መባቻ በጓሮ ወደቀ

21.እነግራለሁ እንጂ እኔ አላሸሟጥጥም
ሴት ያበዛ ጎበዝ እሩጦ አያመልጥም

22.አንተ አትረስ ይረስ አገሩ
ያንገላታህል እርፍና ጉዋሉ

23.አንተ አትረስ ይረስ አባትህ
አፈር ይነካል ቦቸሌው ባትህ

24.ማለዳ ተነስተህ ቦሮችህን ንዳ
ሴትን ቢጠብቁት አይከፍልም አንድ እዳ

25.ይሄ ነው ብሎ ማን ይነግርሃል
ብርሌው ሲያልፍህ ምን ይመስልሃል

26.ከሸማኔ መስሪ ተደፍተህ በልብህ
መስከረም ጎበዙ እንዳይደብልብህ

3ኛ/ጀግንነትን የማበረታታትና ፈሪነትን የመተቸት ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

3.1.አጠቃላይ የጀግንነት ባህሪንና ተግባርን፤ ወዘተ. የሚመለከቱ

1.ካባግርሻ ጋራ ከተነጋገሩ
ክላሽ ሞንሚናይቱ ተባረቀይ በሉ

2. ምንድው ጫጫታ ምንድነው ግርግር
እሚያረግማ ሰው፤ ለልጅም፤ ለሴትም አይነግር

3.ሲያሸሚጥህ ዝምበለው
ሲወነዝፍብህ መክተህ ዝምበለው
በጣም ከጠናብህ ወደ ቂጡ በለው

4.ከረጅም ኮራራ ይሰቀላል ገዬ
ምንኛ ደስ አለኝ ዞብል መወለዴ
አምስቱን በጥይት ሶስቱን በጎራዴ

5.የአባግርሻ ሚዜ ጎብላሌው ቶሎና
አንተን እሚያስፈልግ አግኝቶኛልና

6.እረ በሬ ቁጠር እረ በሬ ቁጠር
በጭፍና እሚጠመድ የማይጠረጠር

7.እኒህ የአርበት ልጆች ምንኛ ቀበጡ
ከመትረየሱ ላይ ከታንክ እየወጡ

8.መጠጣቸው ወተት መብላቸው መገሌ
ብረታቸው ሞይዘር ጥይታቸው ጦሬ
ቁመታቸው ሎጋ ልብሳቸው ገመሌ
አገራቸው በዋ በዋ ንጉስ ጋሌ

9.ወርቁን ከላሙ ፊት የነኩት እንደሆን
በተማለም አይለቅ ምድር ቃጤ ሳትሆን

10.ከገደሉም አይቀር ይገሏል እርቁ
ታቹን በጎሊና ተሻግሮ በወርቁ

11.አይጠረጥሩም አይፈሩም ለሞት
እንዴት ነው ቀመሌ፣አርበት፣ጠበለት

12.እኒህ ያርበት ልጆይ ሞንኛ ቀበጡ
እንደግልገል ፈረስ የተቅበጠበጡ
መትረየስ ሲያጓራ ከታንክ የሚወጡ

13.በዋ ንጉስ ጋሌ ፣አዩብና ጮቢ
 ጭድ አትቆልልበት
 ረመጥ አይጠፋም እሳት ከቆየበት
14.እንደምነው አዩብ የዋጮው ግድም
እንደምነው ጮቢ የዋጮው ግድም
እንደምነው በዋ የዋጮው ግድም
እንኳን ነካክተውት ይሸታል ደም ደም

15.ቆቦን ከቀየው ላይ የደፈሩ እንደሆን
ቅልሻን ብስጭት ያሳዩት እንደሆን
አርበትን በዱላ የቃጡት እንደሆን
ዙብልን ከላሙ፣ወርቁንም ከጊደሩ፣የነኩት እንደሆን
ጨርጨርን ሀርሞውን የወረሩ እንደሆን
አይለቅም በዋዛ ምድር ቃጤ ሳይሆን

16.እስቲ ባለህ ሞታ ባለህ ተወዛወዝ
ሳይበላም አያድር አሞት ያለው ጎበዝ

17.ያባይርጋ ሚዜ አለህልኝ ወይ
ዲቡን ጠጋ ብዬ ልበላቸው ወይ

18.አነፍንፍ አነፍንፍ እንደ ቡርቃ ጅብ
የተዋጋም አይሞት የሸሸም አይድን

19.እኔ ጀግና ብሎ ድንጋይ ሲፈነቅል
ያባይርጋ ሚዜ አኖጋው እንደቅል

20.አርኬ መሳሪያህን ያሙታል ሰደፉን
ዘወር አርገውና አሳያቸው አፉን

21.አደገ አደገና አቦላው ቀለሰ
የኛ መፈተኛ ወራቱ ደረሰ

22.እንኳን አማርኛ ቢናገር ትግርኛ
በጠባብ ወስኮ ነው የቀናነው እኛ

23.እንኳን በምንሸር አሻግሮ በሚጥል
አይቻልም በዋዛ መዋጣ ዝንጥል

አይቻልም ቆቦ በቅንጭፍት ዝንጥል
24.ስደደው፤ ስደደው፤ ስደደው ባመጣው
እንደ ባርማሸላ እንዳርመጠምጠው

25.አይሏችሁ ጋሞቼ ሆዳችሁ አይባባ
አይሏችሁ ጓዶቼ ልባችሁ አይባባ
ይበቃሉ ብለው ልከውናልና
ይዋጋ የለም ወይ ሰባትና ሰባ
አገሬም ወርቁ ነው ዳርቻው ቀበሌ
ተበድሮ ገዳይ ጥይት እንደጥሬ

26. ጠመንጃው ምንሽር አስር አስር ጎራሽ
እንኳን የወንድሙን ያማቹን ደም መላሽ

27.ምንቸገረኝ ብዬ ወሬ እጠይቃለሁ
አገሬ ላይ መርጦ መሆኑን አውቃለሁ

28.በለው በመዋጣ ከትከሻው ላይ
አማቱም ትመልከት ውሽማውም ትይ

29.ብታሰር እጅን ነው ብገረፍ ጎኔን ነው
አመጠኛው ልቤ አሁንም ገና ነው

30.ከአባተ ሀይሉ አገር የጁ ተወልጀ
በነጋ በጠባ ይታሰራል እጀ

31.አገራቸው የጁ መልሶ አገራቸው
እንኳን ብትራቸው ይሰብራል ጓያቸው

32.እኔ ከየጁ ልጅ ፈሪ ቢገኝብም
በመኪናው መንገድ ጋሪ ይነዳብኝ

33.እንቢ ብሎ እንደሆን ደም እያራወጠው
በቦርማ ካሪያ ወገቡን ቁረጠው

34.ካመጠኛው አገር የጁ ተወልጀ
በነጋ በጠባ ይታሰራል እጀ

35.አታድበክብክና ቀጥ ብለህ ተናገር
አገሬም ገዶ ነው ከነጨፍጭፍ አገር

36.ትናገር ከሆነ አድበህ ተናገር
አገሬም የጁ ነው ከነጨፍጭፍ አገር

37.ታች መርጦን ጠይቀው የጦር መላ ያውቃል
ጃርሶንም ጠይቀው የጦር መላ ውቃል
መቻሬን ጠይቀው የጦር መላ ያውቃል
ይሄ ምናምኑ እንዴት አርጎ ያውቃል

3.2.ፈሪነትን የመተቸት ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

1.አንድ ጉድ እማይደል ሁለት ሶስት ጉድ
ያማች ብረት ይዞ ካጋም መጎድጎድ

2.ኧረ ጀግና ይሙት ፈሪ ይኑር ቢሻው
ሬሳ ለማንሳት ይመቻል ትከሻው
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው

3.ኧረ ምን ያረጋል የፈሪ ጎረቤት
ገደሉት እያለ ይገባል ወደ ቤት

4.ያም ወርዶ ያም ወርዶ ዲቡን ነቀነቀው
ጀግና ሊዋጋበት ፈሪን ምን ጨነቀው

5.ከወደኛም አሉ ጎንቢሶ አሳማሪ
ከወደዚያም አሉ ጎፈሪ አበጣሪ
ከወደኛም አሉ ዝናር አሳማሪ
ሰንሽድ በኋላ ስንመለስ መሪ

6.እንቢ አለች ላሚቱ አልታለብ ብላ
ፈሪ ጉተናውን ያስነካኛል ብላ

7.አዳል ግደል ብየ ብሰደው ጎመጅ
አደስ ይዞ መጣ ሚስቱን ሊያበጃጅ

8.በአደስ ተቀብቶ በአደስ ቢሚሚጭ
አደለም ወይ ሚሌ ገበና ገላጭ

9.መቼ ሚሌ ገሎ መቼ ተገልግሎ
የላሞቹን ወተት አረገው ገለሎ

10.ኧረ ምን ሲሆን የጎበዝ ፈሪ
ምንሸር ይዞ ዲንጋ ወርዋሪ

11.ይኸ ምን ሊሆን የጎበዝ ገራም
ሲያኩት ዝም ይላል እንደ ሀርኮ ላም

12.ጀግና ጎበዝ ሲሞት ልቡን የማይቆጨው
የታገተ ጥጃ፣ካንድ ደረባ አገር፤ የማያስመልሰው

13.አንጀቱ ጉተና ድግ አደራደር
እነዚያ ሲመጡ ባይተረተር

14.አንጀቱ ጉተና ተከምክሞ/ተበጥሮ/ኑሮ
ስደጅው መቀሱን ቁርጥ ነው ዘንድሮ

15.በጉያዋ ገብቶ ጡቷን እያሻሸ
እንደርጥብ ሽክና በቂጡ ተረሸ

16.በል በል እያለችው በጀዱ እየሞቀው
እንደ ወጊ ሞፈር በቂጡ ያለቀው

17.ይኸ የላሞየ ልጅ የሴቶቹ አንበሳ
የወንድሙን ገዳይ በደል የሚረሳ

18.አንተ የፈሪ ልጅ አዋጅ የፈራኸው
የቆራጡ ሚዜ ምን ሲሆን አየኸው

19.አንበሳ ነው ብየ ተስፋ ጥየበት
ያነካ ጀመረ እንደ አሮጌ ቤት

20.የሻሸሞ አለባ ዘላለም አክባሪ
ሴቶች ከወደዱት ማን ይለዋል ፈሪ

21.አሳየው ፈትገህ ወቅጠህ እንደ ተልባ
ይኸ የነጎዴ ልጅ ገድል እስቲገባ

22.ወንድ ይሁን ሴት ይሁን አቋሙን ሳይለዩ
ይዘንብለት ጀመር ምድረ ቀጠናዩ

23.ግድግዳው ሰንበሌጥ ልባሱ ገለባ
አንት የነጎዴ ልጅ ገደል እንዳትገባ

24.ለሴቶቹ ይምሰል አግድመው ቢሮጡ
ያንዳልጥ የለም ወይ ሳሩ ሰንበሌጡ

25.ከፍ አርገህ ታጠቀው ጉልበትህ ይታይ
አከሌን ተኛኂት አይሞላም ጉዳይ

26.እንበለው ካላችሁ እንበለው ባቱን
ውሽማው/እናቱ/ ቀልባ ያሰባችውን

27.የሴቶቹ ወዳጅ ከንፈረ ኩሌው
እንባው ኮለል እና አለ እሾህ ቢወጋው

28.አምና በክረምቱ አንዴት ሰሳ ገሎ
ይኖራል ዘላለም ጉተናው ተንጋሎ

29.ምን ያረጋል ካሪያ ኮታፋ ቢጠጋ
ቢያረገርግ እንጂ እንደ ጠፍር አልጋ

30.አንገቱ ረጅም ነው እንደ ግመል ልጅ
ባጥሩ ብቅ ብሎ/በጋቢናው ዘልቆ/ይታያታል እንጅ

31.አሳር ነው መከራ ብለው ቢልኩበት
ራሱን አሰረ በሚስቱ መቀነት

32.አንተ በሬው ገብተህ ያላወጣህ
ምነው ወይፈኖቹን ታማቸዋለህ

33.መዋጣውን ይዘህ ካልመታህበት
ስጠው ለሴቶቹ ቡና ያፍሉበት

34.አይኑ ትልልቅ ነው ለሴት መገልመጫ
ባቱ ወዳድል ነው ለጭቃ መርገጫ
እነዚያ ሲመጡ አለው መደፈጫ

35.ኧረ አንተ ሸሪፎ አባትህን ንገረኝ
ተሸካሚ ሁላ እየገፈተረኝ

36.አንባንሮ ሲቅም ጭንቅ ያላለው
ከሸርሙጣ ጓዳ ጥርሱን ማን መታው

37.የጁ ላይ ተወልዶ የሚፈራ ልጅ
ተወለደ አትበሉ ተጨነገፈ እንጂ

38.ፈሪ ካሪያ ገዛ ይዋጋ ይመስል
እየሞነጨረ ታፋውን ሲያቆስል

39.የዱላ ኪኪታ የማትችል እንደሆን
ፈቀቅ በል ነባዜ ምደር ቃጤ ሳትሆን

40.ይዋጉ አይዋጉ አንተ ወይት አይተህ
እንደ ጌሾ ወቃጭ በጧት የወጣህ

41.ከወንዶቹ ጎራ ያላየነውን
ከሸርሙጣ ጓዳ ዘበናይ መሆን

42.ወደልሽ ምን አለ ዘንጎሽ ምን አወራ
እንደ በካር ጊደር ፊት ፊት እየመራ

43.የታለ ግመሉ የታለ ሆላው
በረጅም ምንሽር የተወረረው

44.ዱላ ቢያበጃጁት በፍየል ጅራት
ብትር ቢያበጃጁት በበሬ ጅራት
ይቸግር የለም ወይ የገጠመለት

45.መልኩን አሳምሮ እንደ እነ አበራሽ
ዱር አለው ገደል ነው አይልም ሲሸሽ

46.ምን ጎበዝ አለና ሆዱን/ልቡን/የሚቆጨው
ያባውራ እርግማን ወገቡን የቀጨው

47.መዋጣ ሳይመክት የሰው ሚስት የነካው
ምን ይንቀጠቀጣል፣ይኸ የነጎዴ ልጅ፤
ሆለታ እንደያዘው

48.እነግራለሁ እንጅ እኔ አላሸሟጥጥም
ሴት ያበዛ ጎበዝ ሩጦ አያመልጥም

49.የክትክታ ዱላ መዋጣው ሳይመጣ
የቀረበልህን እየጠጣህ ውጣ

3.3. ታዋቂ ግለሰብ ጀግኖችን የሚዘክሩ ቃልግጥሞች

3.3.1.ስለ ደጃዝማች ጎበና አመዴ የተገጠሙ

1.ጎበና አመዴ ለጉድ ተወለዶ
ዘጠኝ ቲሊንቲ ባንድ ቀን ማልዶ

2.ካልቆሰቆሱበት አይፈላም ጀበና
ከኃይለስላሴ ይሻላል ጎበና
እያንገራገረ አላስገዛምና

3.ነጃ በለኝ ብሎ ሾንኮር አመለጠ
ቲሊንቲ ቀረ እንጅ አይኑን እንዳፈጠጠ
4.ካልቆሰቆሱበት አይፈላም ጀበና
ላይኛው መርጦ ነው ታችኛው ገላና
አባጉመድ ጉቤ ሾተል ጅራፉ ና

5.አስፋው ቀሚስ ይፍተል ልበይ መቀነት
አባጉመድ ጉቤ ይታጠቅበት

6.እሮብ ተደልድሎ ሃሙስ ተገበየ
የሠው እርሻ አይነካም ይህንን ጉድ ያየ

7.የጉበን መኪና ስሟ ዘነበች
አጥንቷን ለቃቅማ ወልዲያ ገባች

8.ይህ ሁሉ ጠመንጃ ይህ ሁሉ ጥይት
አሁን ምን ያደርጋል
ይህስ የብስጭት የንዴት ይመስላል

9.አሁን ምን ያደርጋል ይህ ሁሉ ጥይት
ማንም አልደረሰ ጉበና ሲሞት

10.ጉበና በሞተ ባመቱ
የሰው ሁሉ ኮርትም ሆነ እራቱ

3.3.2.*ስለ ቀኛማች አባተ ሀይሉ የተገጠሙ*

1.ያባተ ሀይሉ አገር መርሳና ስሪንቃ
ለየጁ ለራያ ለሁሉ እሚበቃ

2.ሸዋም እኛን ምሰል
ትግሬም እኛን ምሰል
እምቢ ብለህ እንደሁ
የበፍታ አምነው ልጅ ያረግሃል ከሰል

3.ከሁሴና በቀር ወንድ የለም እያሉ
በቀርጨም ዘለቀ አባ ከስክስ ሀይሉ

4.ሃይሉ ሽበሸ ልጅ፤ የበፍታ አምነው ልጅ
ወንዱ አባተ ሀይሉ ሱሪው ተቀዶበት
አመለኛው ጋሜ ሱሪው ተቀዶበት
ብቻውን ነው መሰል ጉልበቱን አዩበት

5.ያባተ ሀይሉ እናት አይዞሽ አታልቅሺ
ሰባቱን ገሎ ነው የሞተው ልጅሺ

6.ያባተ ሀይሉ እናት ታጠቂ በገመድ
ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ

7.ያባተ ሀይሉ ላም የቀይ ቦራይቱ
ምንሽሩን ይዛ ገባች ከበረቱ

8.አሁን ምን ያደርጋል ይህ ሁሉ ጥይት
ማንም አልደረሰ አባተ ሲሞት

9.ቆቦ ከተማ ላይ፤
ከነ አባ ባውሎስ ቤት ሰርጉን የበላችሁ
ይላሉ ጉድ ጉድ፤
ደሞ ከወደይህ ምላሽ ሊጠሯችሁ

10.የማይሆንለትን ነብር ጋር ተጣልቶ
ጎርፉን ጎርፍ ወሰደው መርሳ ውሃ ሞልቶ

11.ቀኛማች አባተ፤
የብረት ምሰሶ የብረት ማገር
አዳልና ትግሬን ይቀጣው ጀ
12.ሀይሉ መሸሻ ልጅ፤
የበፍታ አምነው ልጅ፤ወሬራው ወሬራው
እንኳን በዱር ወጥቶ ታስሮ የሚያስፈራው

13.ጥጆቹ ተርበው እርሾ ሲግጡቸው
ወንዱ ራስ ጀበና ወርዶ አገናኛቸው

3.3.ሰለ አቶ ምስጋን በላይና ሌሎች የተገጠሙ

1.ያባትዬው ግዳይ ጎሊና ነበረ
ደግሞ የልጅዬው ሚሌን ተሻገረ

2.በሮችን አርሳችሁ፤ በሏቸው ወደ ላይ
ላሞቹን አልባችሁ፤ በሏቸው ወደላይ
ይጠብቃቸዋል ወንዱ ምስጋን በላይ

3.እንደ ቂጣው መስሎኝ እንደ ቆሪው ፍትፍት
እንደ እሳት ይፋጃል የምስጋን በላይ ፊት

4.ያነ ምስጋን በላይ፣
አንጀቱን ታቅፎ የማይደነግጠው
ከዞብል ገስግሶ እስኪደርስ ዳምጠው

5.የበላይ ገብሩ ልጅ፣
ወንዱ ምስጋን በላይ ነገር አበላሻ
ምንው የዛን ጊዜ አይቷቸው በሸሸ

6.አንዳድ ቀንማ እሪታም ደግ ነው
የበላይ ገብሩ ልይ፤
አደባባይ ውሎ የሚመኘው ዱር ነው

7.አንዳንድ ቀንማ ነጋን ላቆላምጠው
አንጀቱን ታቅፎ የማይደነግጠው
እሪታው አስቲግል እስቲደርስ ዳምጠው

8.ዳምጠው ደሳለን ምን አስለቀሰው
የወንድም ጥቃት የለት እሚያፍሰው

9.ያባትየው ጉዳይ አላይና ነበረ
ልጅየው ባሰና ኢሳ ተሻገረ

4ኛ/ አካለዊ ቁንጅናን እና ፍቅርን የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

4.1. አካላዊ ቁንጅናን ወይም ውበትን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

1.ዋጃ ወዲያ ማዶ ጌደሩ ነው ቤቷ
ያለመደገፊያ አይቆምም አንገቷ

2.ትርንጎም እንዳትይ፤ ትርንጎ ገላ አለሽ
ሎሚም እንዳትይ፤ ሎሚ ከንፈር አለሽ
ለምን ሰኞ ሰኞ ትመላለሻለሽ

3.ከቀመሌ በላይ ስሙ ነው ዱር ለበስ
መልኳሚን አንጥፎ ድርምሚን ነው መልበስ
እርቦዋን አንጥፎ ሹሩባዋን መልበስ

4.ከእንግዲህ አልገዛም ያሮጌ ላም ስጋ
አገዛለሁ ጊደር እያበዛሁ ዋጋ

5.ከእንግዲህ አልወድም መልኳም የሌላት
መልኳሚ ቀስቅሶኝ ካልነቃሁ ሌሊት

6.አላ ውሃ ወዲህ ስሙ ነው ጎብየ
ሽ ብር ተቀጣሁ ሽጋ አየህ ተብየ

7.ከሰላሳው ጥርሷ ሁለቱ የነጡ
ይቀሰቅሱኛል ሌሊት እየመጡ

8.አንቺ የአጭር ረጅም የጠይም ለስላሳ
የት አገኝሻለሁ ብወድቅ ብነሳ

9.እኒህ ራያዎች ምን አስወደዳቸው
የእርጎ ፍርፋሪ ይመስላል ጥርሳቸው

10.እሄድ እሄድና እላለሁ እረፉ
የጥርሷ ውቅራት እየታየኝ ዘርፉ

11.አንቺየ ጥርስሽን ምኑ ሞቶበታል
ሀሩን አገልድሞ ንጣቱ ገሎታል

12.ዞብል አቀበቱን ራማ ጥዱን
ተሳልሜው መጣሁ አይንና ጥርሷን

13.የጠይም አደራ አታኑሩብኝ
እበላታለሁኝ ይሉኝታም የለኝ

14.ስትሄድ ጎብለል ጎብለል እንደ ሀዳር በሬ
ጭር አለ መንደሩ ወይት ዋለች ዛሬ

15.በደና በልቼ አፌን መረረኝ
ቁንቁራ በልቼ ሆዴን ቆረጠኝ
ልሂድ መንደፈራ ትርንጎ ባገኝ

16.የጠይም አደራ አኑረው ከቤቱ
ሲርበኝ በላኋት ሲታጠፍ አንጀቱ

17.በሰላላው ጥርሷ ሰላላ ገላለች
እኔንም ልትገለኝ ቀን ይዛልኛለች

18.ነጫጭ ላም ያለው ቀይ ሴት ያገባል
ይኖራል ዘላለም ጀነት እንደገባ

19.ቀይማ ቀይነሽ እንደ አበባ ሬት
ይበላሽ ይሆናል መንቻካው መሬት

20.ቤቷ ቦረን ላይ ነው በስተ ጠሀይ መውጫ
ያይኗ ስለት አለው እንደ አገዳ ልጫ

21.እንደተመታ ሰው ደም እንዳጠለቀው
የገላዋ ጥራት/ቅላት/ቀሚሷን ዘለቀው

22.አይኗ መጫ መጫ በጣም አያስዋሽም
ከተመለከተ ሳይገል አያመሽም

23. በሳንቃው ቀዳዳ ቢታየኝ ደረቷ
እኔስ ብየ ነበር ተቃጠለ ቤቷ

24.አይኗንም አይና ጥርሷንም ሠአይና
ካደው ካደው አለኝ የባሏን ዝምድና

25.በዋ ንጉስ ጋሌ ስንደዶ ማለፊያ
ወገቧ ቀጭን ነው እንደ አሳ መጥለፊያ

26.ከንፈሯን ሲስሙት ጉንጯ ይላል ስርቡቅ
አደረች ሌሊቱን ትንፋሿ ሳይለወጥ
አደርን ሌሊቱን፤ እኔ እውጥ፤ እኔ እውጥ

27.ባቷ ተረከሟ ስጋው ተነባብሮ
ወገቧ ቀጭን ነው አልበላም ወይ አብሮ

28.ወግድ ጋሪያ ሌንጫ ቆቦ /ዋጃ ሰው ልይበት
የሚጠቀልለው ሽንጧ እንደ ወረቀት

29.የቁልቁለት መንገድ ለጅብ አይመችም
ጡቷ ከደረቷ ያለው ግችም ግችም

30.ለቀይ ልጅ ቢሉኝ በርበሬ በላሁኝ
ለጥቁር ልጅ ቢሉኝ ከሰል ቆረጠምኩኝ
ለጠይም ልጅ ቢሉኝ ምንጭ ውሃ ጠጣሁኝ
ለዚያ/ች/ለቀይ ዳማ መድሀኒት አጣሁኝ

31.ያደረ እንጆራና ጥቁር ሰው አንድ ነው
ለአይን አይመስልም እንጂ ለበላው ጤና ነው

32.ጠይም ወዶ ወዶ፤ በቀኝ ሲመለሱ
ሆድ ይበረብራል ጠጅ እንደቀመሱ

33.ስትሄድ ደንቦል ደንቦል ስተኛ ወርድ የላት
እንደ ደጋ እንጆሪ መጠገቢያም የላት

34.እንኳን አርግዛና ሽል ይዛ በሆዷ
ደንቦል ደንቦል ነው ወትሮም አካሄዷ

35.አይኗማ ጥርሷማ የእግዚሀር ስራ ነው
እኔን የሚገርመኝ አረማመዷ ነው

36.ሳንቃው ደረቷ ነው ያጣላው ሰውን
እስቲ ሸሸግ አርጉት ያጡት እንደሆን

37.ጉም አይጠነጠን ውሃ አይዘገን
በአይኗ ገርፋኝ ሄደች ሰንበር እንዳይሆን

38.የሚያረገርገው ወገቧ እንደለኮ
ተህዶሞ አትገኝ እንኳን ሰው ተልኮ

39.አሁን አይኗ መጣ ተልኳል መሰለኝ
አሁን ጥርሷ መጣ ተልኳል መሰለኝ
እስቲ ግባ በሉት መላክቱን ይንገረኝ

40.ብቻዋን ስትሄድ ትመስላለይ አምሳ
ያስደንግጥ አለባት እንደ እባብ ሬሳ

41.ትናትና ማታ ዛሬ ለሊት በልሜ
ከጥርሷ ውቅራት ከዘርፉ ላይ ቁሜ

42.ወርደ ሰፊ ቀሚስ የሞላው ዳሌዋ
እንዴት አደራችሁ ይላል አሚዴዋ
አላለቀባትም የፍቅር ዛላዋ

43.አቀበቱን ስትሄድ ሽንጧ እያረገደ
ቁልቁለቱን ስትወርድ ዳሌዋ እያበደ
እንኳ እኔ ባዳው ወንድሟም አበደ

44.የጠጉሯ መብዛቱ እንደ ጭድ ክምር
በሁለት ሰሪታ ቀረ በጅምር

45.ራሷ ተሰርቶ ባንድ ቀን አያልቅም
ላንባዲና ይገር በስተፊቷ ልቁም

46.እራቴንም በላሁ በኑግ አጣብቂ
ምሳየንም በላሁ በኑግ አጣብቂ
ጥቁር መወደዱን እኔ ምን አውቂ

47.ጠይም ተፈትፍቶ ሲበሉ ደርሽ
ይበቃሀል አሉኝ አንደየ ጎርሽ

48.አይኗ ብር አለሎ፤ ገውለል ገውለል ይላል
ፀጉሯ ሀር ነዶ ዘንፈል ዘንፈል ይላል
ባላገር ሞኝ ነው ባለጅ ናት ይላል

49.አስራ ሁለት ነው ያንገቷ ቅርድ
ማሸላም አትበላ ጤፉንም የግድ
ጠላም አትጠጣ ጠጁንም የግድ

50.አይኗ የሚመስለው የንጋት አጥቢት
ጥርሷ የሚመስለው የጊደር ወተት
ከሷ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት

51.አይኗማ ጥርሷማ መች ይበልጣል ከሰው
ወገቧ ነው እንጂ እህል ያልቀመሰው

52.አይኗም እንኳን እንኳን
ጥርሷም እንኳን እንኳን
መከዳው ደረቷ ያስተክላል ድንኳን

53.ከሰው ጠይም ያምራል ከዛፍም ጠንበበል
ዋጥ ላርግሽና አላየሁም ልበል

54.የባርማሽላ እርሻ ቢያርሙት ይበጃል
የቀይ ልጅ ከንፈር እንደ እሳት ይፋጃል
ጭራሽ የጠይሟ የእንብርክክ ያስኬዳል

55.ከሁለት ከሁለት ይከላል ባቄላ
ሞይዘር ይሸከማል የቅንድቧ ጭራ

56.ያረባ ዝምድና እየተቆጠረ
ጉች ጉች ያለጡት ብቻውን አደረ

57.ጥይት አልተኮሰች ዘንግ አልወረወረች
የአበባ እከሌ ልጅ/በአይኗ ሰው ገደለች

58.አውሳ ዝናብ የለም ይጠጣል በመስኖ
ታየኝ ቃሪሳዋ ጤፍ ወለዳ መስሎ

59.በጨቤ ተወግቶ ይድን የለም ወይ ሰው
በአንካሴ ተወግቶ ይድን የለም ወይ ሰው
እንደሉት በመሳቂያ በጥርስ ይሞታል ሰው

60.ዝንጆሮ በዳገት ይመስላል ሰርገኛ
እንደሉት ነው ከንፈሯ የጥርሷ ጓደኛ

61.ወገቧ እንደ ጭራ የመነመነው
ይበጠሳል ብየ እኔም አላምነው

62.የቆላ ልጅ ሆነሽ ንግግር ባታውቂ
ጥርስሽ እርጎየ ነው ቶሎ ቶሎ ሳቂ

63.እንደ ቦዳ መሬት ንሽ አለው ገላዋ
ጠጅ ሳር ጠጅ ሳር የሚለው ሽታዋ
ባሏም አልጠገባት እንኳን ውሽማዋ

64.አይንሽ የሚመስለው የንጋት ጨረቃ
ጥርስ የሚመስለው የተሰካ ዶቃ
የት አገኝሻለሁ ብታጨድ ብወቃ

4.2. አጠቃላይ የፍቅር ስሜትን ፍቅርን የሚገልጹ ቃልግጥሞች

1.እስቲ ብሩ ጎራ አላይና ዝለቂ
ምን አረንዛ ሆድ ነሽ ሰው እማትናፍቂ

2.ይች የበዋ ልጅ አመለ ደርባባ
ልወዳት ነው መሰል እኔስ ሆዴ ባባ

3.እነጋ እነጋ ሲል ፍቅር/ጨዋታ/አስለምዳኝ
ባባቷ እምላለሁ አባቴን አስከዳኝ

4.አይኗ ጮንጫና ነው ድሮም አውቀዋለሁ
አንገቷ ዱርንቅ ነው ድሮም አውቀዋለሁ
ፀጉሯ በናና ነው ድሮም አውቀዋለሁ
ወገቧ በርሜል ነው ድሮም አውቀዋለሁ
ልቧ ግን ኩሩ ነው የኮራ እወዳለሁ

5.አላማጣ ወዲህ ስሙ ሰበር ጉማ
ልቤን ወሰደችው ባገልግል ለጉማ

6.እንዲህ ወደ ማታ ገበያ ምላሽ
እንደ ጠፋይ ጊደር ሄ ሄ ልበልሽ

7.ወይ አገርሽ ይራቅ ወይ ስምሽ ይለወጥ
ከጎረቤት ሆነሽ ሸተትሽኝ እንደ ወጥ

8.አባቷም ይላሉ በላይነሽ በላይነሽ
እናቷም ይላሉ በላይነሽ በላይነሽ
እኔም እላታለሁ ከልቤ ላይ ተነሽ

9. ወይ በእናት የለብኝ ወይ በአባት የለብኝ
አይኔ ቡዳ ሆኖ የሰው ልጅ በላብኝ

10.እህህ ነው እንጂ ያከሳው ደረቴን
መች ሳልበላ አድራላሁ አንድ እንጀራ እራቴን

11.ሰው ወድጄ አላውቅም አምላክ ከፈጠረኝ
ልወድ ነው መሰል ሆዴን ባር ባር አለኝ

12.የእርሻ ዳር ቁጥቋጦ ባይቆርጡት ጥላ ነው
የጎረቤት ወዳጅ የአይን ማረፊያ ነው

13.እሷ ጠይም አሳ ምንጣፏ ጥቁር
ያብሰለሰለኛል እንደ ነፍሰጡር

14.አንጀቴ ተቆርጦ ስቀጥል ከርሜ
ደግሞ ሰው ወደድኩኝ አያርመኝም እኔ

15.ከሳሁ መነመንኩኝ ነጭ እንጨቴ ወጣ
ከእንግዲህ ቢሸጡኝ ዋጋም አላወጣ

16.እኔ ምን ቸገረኝ ትውልዷ ባይጠራ
ባላባቱ ሁላ ስጋው አይበላ

17.ጤፍ እንጆራው እንጂ ጭዱ አይለሰልስም
ከሰው እጅ የገባ ቶሎ አይመለስም

18.ሽጋ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት
ላፈር አይደለም ወይ የተሰራሁት

19.ጀንበሩ ካልገባ ካልጨለመ በቀር
አይኑን አያነሳም ሰው ከወዳጅ አገር

20.ቀይ ዶሮ ቢሉሽ እውነት አይምሰልሽ
ነጭ ዶሮ ቢሉሽ እውነት አይምሰልሽ
እኔ ነኝ በሽታሽ እማጥመነምንሽ

21.መስታወት መልክ እንጂ አያሳይም አገር
ማሪያም አደራሽን የዛችን ልጅ ነገር

22.እባብ በሬ ጥመድ ዘንዶ ዘር አቀብል
የእሽኩትኩት ያስኬዳል የሽጋ ልጅ ፍቅር

23.አሸዋ ቢፈጩት የማይልመውን
ድንጋይ ቢቀቅሉት የማይበስለውን
ያችን ልጅ ተው አሉኝ የማይሆነውን

4.3. ቅኔያዊ ባህሪ ያላቸው የፍቅር ቃልግጥሞች

1.ገረዶች ተጣልተው ላስታርቅ ብነሳ
ምነው እመቤቷ ልቤን መቱኝሳ

2.ሳንቃው ደረቷ ነው ያጣላው ሁሉን
እስቲ ሸሸግ አርጉት ያጡት እንደሆን

3.ወይራና ክትክታ ሲማግዱ አይቼ
ሳገላብጥ አደርኩ የሰው ግንድ አምጥቼ

4.ይሻለኛል ብዬ ቀይ ብቅሎ ብገዛ
ሰጋር ናት መሰለኝ ተመልካቿ በዛ

5.ባዝመራ መካከል ስትነዳ ብዙ ላም
አታስቆም አታስሄድ እህል አታስበላም

6.ለግድግዳው ነው ወይ የምትቸገሪ
ቆርጭልሻለሁ እንግዲህ ቤት ስሪ

7.ሰባት ስምንት መቶ ታወጣ ነበረች
ያችን ትመስል ልጅ በሰማኒያ ቀረች

8.ተማርከን ነበረ እንዳናቀላፋ
ተኝተሽ ተገኘሽ መተማመን ጠፋ

9. አውራ ዶሮ ስጡን እህሉን ሲያፈሰው
ምን እመቤት ቢሆን እሽ አይልም ወይ ሰው

4.4. እስላም ቆንጆዎችን የሚያደንቁ የፍቅር ቃልግጥሞች

1.እስላም ስመ ብዙ ሀዋና ከድጃ
ሀዋ ሀዋ አረገኝ የነካኝን እንጃ

2.አባቷ ቃልቻ ደም ያስታርቃሉ
እናቷ ዱበርቲ መረባ ይላሉ
ልጃቸው ሰው ገድላ እንደሔት ዝም ይላሉ

3.የእስላም ቤት እንጀራ ይጣፍጣል በጨው
በእሁድ በቅዳሜ በባል የተፈጨው

4. እስላም ስመ ብዙ ፋጢማ ከድጃ
ሀዋ ሀዋ አሰኘኝ የነካኝን እንጃ

5.ሮመዳን መፆም ትልቅ ጽድቅ ነው
በሸጋ ቢያፈጥሩት ምን ነውር አለው

6.እንደ አማራ በስማም እንደ እስላም ወላሂ
ከንፈሯ የሚለው የማር ልህላሂ

7.ወላሂ ቢላሂ ከንፈርሽን ልቅመሰው
ከቀፎ ሳይወጣ ማር ይሆናል ወይ ሰው

8.እሷ እንጆራ አትበላ፤ እህል አልበላ እኔ
እንካረማለን ያቺ ሀያ እና እኔ

9.ወይፈኑ ቢታመም ጊደሯም ታመመች
የሆነስ ሆነና ያቺስ ላም እንዴት ነች

10.እናንተ በሮቹን ከተካፈላችሁ
ያችንስ ላም ለኔ ትሰጡኛላችሁ

11.ፋጡማም አገባች ከድጃም ታጨች
እንግዲህ አቧራ ቦታም አልሆነች

12.የእስላም ልጅ ሰው ገዳይ ማን አደረገሽ
ጀበናሽን ይዘሽ ወደ ዛውያሽ

5ኛ/ የብሶት፤የቁጭት፤የጥላቻና የማንኳሰስ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

5.1.አጠቃላይ ብሶትንና ቁጭትን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

(በቀረርቶ ወይም በጭፈራ መልክ የሚቀርቡ)

1.ካአንድ አገር ተኩሰው አንድ አገር ሲገቡ
ዘላለም ፈተና እንደ ወይፈን ግቡ

2.ሳታስበው ነገር ሲመጣብህ
ደርግመውደርግመውአይልምወይልብህ
ዳሩ ግና ቢሆን እንደው ጠንቀቅ
ግዛግዙ ገድሎ አገሩን ከመልቀቅ

3.ጃሎ በል፤ ጃሎ በል፤ ይለኛል አመሌ
የሚመጣው ዘመን እየታየኝ በአይኔ

5.እንደው ግሳ፤እንደው ግሳ፤ ይለኛል አመሌ
ወንዙን ተሻገረ ልቡ የሞላ አውሬ

6.ቆይ ገና ቆይ ገና
መቼ ለይቶልን ሰባራና ደህና

7.አርገው ገፋ ገፋ፤ እንደ ፍልፈል አፈር
የባልንጀራ እንኳ አለው የሚታፈር

8.እደግ እደግ ብለን ያሳደግነው ልጅ
እምብዛ ረዘመ እንከርክመው እንጅ

9.ሳለ ሌቱ፤ ሳለ ጨለማው
እንዴት ያጠቃዋል ሰውየውን ሰው

10.እንዴት ነሽ ልጅነት እንደምነሽ ለዛ
በሮቹ ጥቁቁር ጅራታቸው በዛ
አርሰን ለበላነ ምናምኔው በዛ

11.ኧረ ልጅ ማሰሪያው ኧረ ልጅ ገመዱ
ጎጆማ ምናላት ጥለዋት ቢሄዱ

12.እሱ ሙቶ ሰው ይዞ ለመሞት
ንግግሩ ሁላ ይላል አሞት አሞት

13.ኧረ ተው አንተ ሰው ስሮጥ አታባረኝ
አንተም አበዛኸው እኔንም መረረኝ
መረረኝ እንደሬት በላኝ እንደ አኹላሊት
ቀን የተናገርከኝ እየመጣ ለሊት

14.ቢይዙት የማይነጥቅ ጠላት ተበጅቶ
አይተን አይተን ተውነው ጓዛችን በርክቶ

15.አሙን አሉ ተዋቸው ይሙላ
ቢፈሩን አደለ ቢጠረጥሩነ

16.በሉት ሀብታችንን ጨው ጨው እያላቸው
ጥይት ኮሶ ሆኖ እስኪያስመልሳቸው

17.ብለነው ብለነው ካልሆነ ነገሩ
እኛም አውሬ እንሁን እናንተም አድኑ

18.ከሆዴ እሳት ነዶ በአፌ ጢሱ ታየ
ደግሞ ሰው አያምንም ዘንድሮ እኔን ያየ

19.አሞኝ ውሎ አሞኝ ሊያድር ነው ወይ
ደሞም አርሶ መብላት ጤና ላይሆን ነው

20.መገኔ መገኔ ትላለች ጋጋኔ
የቸገረ ነገር አግኝቷት እንደኔ

21.ከአባቱ ባድማ የተኛውን በሬ
እየቀሰቀሱ ሊያረጉት ነው አውሬ

22.የኔ ካገር መውጣት አገርን ደነቀው
የኔ ፈረስ መሸጥ አገርን ደነቀው
የኔ በቅሎ መሸጥ አገርን ደነቀው
የቤቱን አጣባ እኔ ነኝ እማውቀው
27.ሚስቱን ማን አግብቷት፤
በሬዬን ማን ጠምዶት፤
ቤቱን ማን አቃጥሎት፤
እርሻዬን ማን አርሶት፤
አይሉም አይሉም፤
አምላክ ያለ ለታ ይደረጋል ሁሉም

28.አርሶ ማጣትና ተኩሶ መሳት
ያንገበግብ የለም እንደግር እሳት
29.ተወኝ ምላሰኛ ተወኝ ነገረኛ
ኻገዳ ጎጆየ አርፌ ልተኛ

(በዘፈን ወይም በእንጉርጉሮ መልክ የሚቀርቡ)

1.ማሽላ በርጉዙ ጤፍ በወለዳው
እንዲህ ሆኖ ቀረ የኔና ያንቺው

2.እንዴት ያደርጉታል የሆድን ህመም
ማጭድ አይገባበት በእጅ አይታረም

3.ይሄ ኑሮ ነው የኑሮ እኩሌታ
እንስራ ወገብ ላይ ዳንክራ እየመታ
ቅቤሽ እንዳይነካኝ እያሉ ምኝታ

4.መጅ ውረድ፤ መጅ ውረድ፤ቂቱ ሙላ ሙላ
በዋላ አይበላም የሰው ቤት እንጀራ

5.ዋርካ ምድር ነካ ንገሩት ለዋንዛ
ፈጭቼ ለበላሁ ምቀኛዬ በዛ

6.እግዚአብሄር አዞብኝ የሰው ሽጋ ስሜ
ከቁና ጥሬ ጋር ሲፈጭ ያድራል ስሜ

7.አሙኝ አሙኝ እና ፈተጉኝ እንደ ገብስ
ይተውኝ የለም ወይ የልባቸው ሲደርስ

8.አወይ ልጅነቱ ነፍስ አለማወቁ
ሲገረድፉልኝ አለመሰለቁ
9.እንባ እንባ ይለኛል እንዳው ለቅሶ ለቅሶ
የተጫወትንበት ስፍራው ዳዋ ለብሶ

10.አሳርራ ቆላችኝ እንደቀሸር ቡን
እንዲህ ያደርጋል ወይ ሰው አብሮ አደጉን

11.ወታደር በክላሽ እያስፈራራሽ
ሾፌር ከጋቢናው እየጠቀሰሽ
ኮንትሮ በጭለ እያባበለሽ
ከኔ ከድሃው ቤት፤
በኪሻ ምንትራስ ፤
በጥሬ ጨው በለተሽ መይ ትለምጃለሽ

12.ይኸን ፍስስ ማለት ማነው ያመጣብኝ
ብበደር ብበደር አርጣው በዛብኝ

13.የበሬውን መግጦ ተባለን ለብሰሽ
ውረጅ ወደቦዳው ትጠመጃለሽ

5.2. ስለወንድም አስፈላጊነት የተገጠሙ የብሶትና የቁጭት ቃልግጥሞች

1.ሲይዙት ቀላል ነው ወንድምና ብር
ሲታጣ ነው እንጂ የሚቆረቁር

2.ወንድም ያሻል ወንድም ያሻል
አንዱ ሲበረብር አንዱ ይመነሻል

3.ወይ ነቃ ያለ አባት፤ ወይ አራት ወንድም
ነቃ ነቃ ያለ ወይ አራት ወንድም
ሁነኛ ካላየ ሰው በሀቅ አይፈርድም

4.ደህና ወንድምና ባህር ዛፍ አንድ ነው
አይቀናቀንም እደጉ እንደግ ነው

5.የክላሽን ጥይት ይያዛል በካርታ
ደህና ወንድም ያለው ዋስ ሆኖ የሚያስፈታ

6.ሁለት ወንድማማች አንድ በረት ላም
ይሻላል ጠመንጃ፤
ሰባራ፤ቀርሻማ፤ቢሆንም

5.3. የጥላቻና የማንኪሰስ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

1.ትምንምን ትምንምን ትዳርሽ አይጥና
የባህር ላይ ከብት አርገሽኛልና

2.ሰው ወድጄ አላውቅም ያላንቺ በጭራሽ
እንደኔ ሰው ወደሽ ያመንሽው ሰው ይክዳሽ

3.እንደ ባር ማሸላ ሁሉን እያቀፍሽ
የልጅሽን አባት ሳታውቂው ቀረሽ

4.አርግዘሻል አሉ የርብርብ ልጅ
እኔም ይደርሰኛል አንድ እግር ተአንድ እጅ

5.አይኗ የመሰለው የፈረጠ እምቧይ
ጥርሷ የመሰለው አር የገመጠይ
ደሞ ከሷ ብሶ ሰው ልትንቅ ነው ወይ

6.ሽጋ ሽጋውማ ገበያው ሙሉ ነው
ያረባባ መውደድ የጉንፋን እዳ ነው

7.ፀጉራ ወርዶ ወርዶ ከአንገቷ በላይ
አማቲቱ እያዩ ሳቅ አይሞቱም ወይ

8.አፍንጫ ቢገተር እንደ በር እንጨት
ሙያ እንበልጣለን እነ ጎራዲት

9.አፍንጫ ጎራዳ ተወደደልህ
እኔም አፍንጫዬን ልጎረድልህ

10.ሽጋ ለሽጋ ነው የሚዋደደው
ሳል ጉንፋን ይሆናል ምናምኑ ሰው

11.ወርቅ ቀለበቴን ለውጬ በመዳብ
ለቀይ እንኳ አይደለም ለጥቁር አመዳም

12.ወይራና ክትክታ ሲማግዱ አይቼ
ሳገላብጥ አደርጉ የሰው ግንድ አምጥቼ

13.እናትና አባቷ እረግመዋት ኑሮ
ብቻዋን ታድራለች ቁፍ እንዳለች ዶሮ

14.አንድ ቀን ተስቶኝ ጅል አቅፌ ብገኝ
ልጅ የጠፋ ሁሉ መፈለጊያ አረገኝ

15.አይንሽን ያፍስሰው ብረቱን ብረቱን
ጥርስሽን ያርግፈው ንጣቱን ንጣቱን
ሀብታምና ደሃ የለየሽበት
16.ብወድሽ ነው እንጂ እንዲህ መጨነቁ
ከጠላሁሽማ ጢቅ እንደ ምራቁ

17.የዶሮ ቅምድምድ የአፈር ጢስ ይሞቃል
ለዛ የለለው ሰው ምኑ ይናፍቃል

18.ሆርማት ወዲያ ማዶ ስሙ ነው አርበት
በውሽማ መቅናት በማያገቡት

6ኛ.ከፖለቲካና ከርስ በርስ ጦርነት ጋር ተያይዞ የነበረውን ሁኔታ የማሳየትና የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

6.1.የፖለቲካ ድጋፍ ተቃውሞ፣ ትዝብታዊ አስተያየት የተንጸባረቀባቸው ቃልግጥሞች

6.1.1. የድጋፍ ፖለቲካዊ ቃልግጥሞች

1.የደርጉ ጥልቆ እጆታዋ መልካም
አድሀሪን እንጂ ጭቁኑን አትካም

2.መንጌ ሀይለማሪያም የልጅ ልጅህ ይብዛ
ቀደህ ትሰጣለህ መሬት እንደ አጎዛ
3.ላሞቼንም ሸጬ፣
በሮቼንም ሸጬ፤ ልብሴንም ሳስማማ
ኢህአዲግ ደረሰች በነጠላ ጫማ

4. በአበራ ፤ በአበራ፤
ከጋሪያው ስንዘልቅ፤
ሜዳው ሁሉ አዝመራ

5.ያ መለስ ዜናዊ ንጥር ነው፤ ቅቤ ነው
አድሀሪ ያለው ወረዳ እስተ ዞን ነው

6.መሬት አይኑን ታሞ በገመድ ይመራል
ባላባቱ ሁላ ምን ይሸቆመቆማል

7.መንጌ ሀይለማሪያም ምን ምንህ ይረሳል
እንኳን ብርድ ልብስህ ኬሻህ ይለበሳል

8.መንጌ ሀይለማሪያም ስማ ልንገርህ
የሰራኸው ‹‹አስባልት›› ቁም ቀረልህ

9.መንጌ ሀይለማሪያም፤
ልንገርህ ወይ መላ
ከኢህአዲግ መ/ቤት፤
ይቅርታ ጠይቀህ፤
እንጨት ሸጠህ ብላ

10.መንጌ ሀይለማሪያም ሰባት ነው ጡቱ
ያነንም ያነንም የሚያጠባቡቱ

11.አካላቱ ደርጉ፤ሞንሚናየ ደርጉ፤
ልጅ አንጡ ሲለነ፤ ልጅንም ሰጠነ
እርሻ አንጡ ሲለነ፤ እርሻንም ሰጠነ
ብር አውጡ ሲለነ፤ብርም አዋጣነ
ቅቤ አንጡ ይለናል ቅቤ የት ተገኝቶ

በሀይለ ስላሴ፤በዚያ አድሀሪ ንጉስ፤ተቀልጦ ተበልቶ

12.መንጌ ሀይለማሪያም በደሉ በዛብኝ
እነግርህ ነበረ አድርጌ በይፋ፤
ወይት አገኝህ አለሁ ሀረርጌ ነው ከፋ
የሴት ዳኛ በዝቶ ሀገራችን ጠፋ

13.ጉድ ያለው ቀን፤
አምጡ እሚለው ሀዶ እንኩ እሚለው መጣ
ጥቂት ሰነባብቶ ነገር ባያመጣ
14.ምን ያደርጋል ጩቤ መንግስት የጠላው
ምን ያደርጋል ዱላ መንግስት የጠላው
በላው በእስክቢርቶ ሰንበር በሌለው/በማይታየው

15.እንዲም እንዲም ብሎ ደርግን አትሙት
አሳይቶ ኽሂል መሰረ-ትምርት
አስተምሮ ኽሂል መሰረ-ትምርት

16.መንጌ ሃ/ማሪያም የጦሩ ገበሬ
እንኳ ባይኔ አየሁህ አልቀረህ በወሬ

6.1.2.የተቃውሞ ፖለቲካዊ ቃልግጥሞች

1.አስራ ሰባት አመት የቀለብነው በሬ
ዝምባቡዌ ተቀምጦ ያዳምጣል ወሬ

2.አንድ ፍየል የለም በዚህ ላይ ዳገት
ተለያይቶ ቀረ ደሀና ዱለት

3.ጎብየ ገበያ ይሸጣል ጥልቆ
ሽንት እንኳ ሲሸና ፍቃድ ተጠይቆ

4. የወደቀው መንግስት ይቅር አይነሳ
ግብሩ ሁለት ብር አስራቱ ብር ታምሳ

5. በጃንሆይ ጊዜ ወልጄ ወልጄ
በመንግስቱ ጊዜ ወይ ልጄ ልጄ

6.እንግዲህ ወላጆች፤ ለየብቻ እደሩ፤ ለየብቻ ዋሉ
ፊት የተወለዱት ካላገለገሉ

7.እንዲህ ያለመንግስት የመንግስት አዋቂ
ሚስቱን ሊቀ መንበር እኔን ቤት ጠባቂ

8.ላስታ ምን አወራ ፣የጁ ምን አወራ
መሬት አይኑን ታሞ በገመድ ሲመራ

9.በደርጉ ዘመናት የተወለዳችሁ
ወተት አታገኙም ዘይት አለላችሁ

10.ቆረጡት ይላሉ፣
ያላማጣን ገርቢ፤ለከሰል እያሉ
ቆርጡት ይላሉ፤
የዋጃን ኮረራ፤ለከሰል እያሉ
አንተንም አቧራ ያሰጋህል አሉ

11.አንተ ፈንታው ከተማ፤
አንደየ ተነስተህ ሁለተኛ መኑት
አቧራን ባየኸው እንዳደረጉት

12.አገሬ በረሀው ኮረራው ማማሩ
ቆርጠው ቆርጠው ጣሉት ለልማት እያሉ

13. ለልማት እያሉ ዛፉን ቆረጡት
አየ መጠለያ ማረፊያ ማጣት

14.ጣይቱ መርሻ ቤት ስንት ጠጅ ሞልቶ
ያስለፈልፈኛል ከባዶ ቤት ዘግቶ

15. ወላጆች ልጆቹን መልሳችሁ ዋጡ
ይኸ ቀን አያምር አይን አገላለጡ

16. ምን ያለ ጊዜ ነው ለሰው ያልተመቹ
የናፋ ተያዝኩኝ ከመሬት ሸንቹ

17.ይምጡ በሮቻችን አርደን እንብላቸው
ደሞ እንደ መሬቱ ሳይደለድላቸው

18.ዳቦሽ እንጃልሽ፤
የለል እንጃልሽ፤
ካንድ ትልም መሬት፤
ሰባት ቤተሰብ ቁጭ ሲልብሽ

19.አይጥ በቤት አዛ ፍልፍል በመሬት
ከቶ በየትኛው እንክፈል አስራት

20.ያለፈውስ አልፏል ለሚመጣው ፍሩ
ሰማዩን በባላ ደግፉ እንዳይሉ

21.አፈሩን ሸምቹ ባፈር ላይ ዘርቹ
የምከፍለው አጣሁ ልሂድ ተሰድቹ
22.እስቲ ሰወይ ህዩ፤ እኒህን ጥጆይ
አገሩ ተማክሮ፤
ይኸን ማዶ ጓሳ፤ አያበላም ወይ

23.በዚያ ደርግ ጊዜ ሰፋሪ ተብለነ
ተመስገን ኢህአዲግ ከመሬት ዶለነ

24.ከሴፍቲኔት ምላሽ የታረሰው እርሻ
እንኳንስ ሰውና አያጠግብም ውሻ

6.1.3.ትዝብታዊ ቃልግጥሞች

1.የደርጉ መኪና ሽራ የለበስሽው
ከበደ አሊ ወሌን ወዶት አደረስሽው

2.የወፎች አለቆች እርግቦች ነበሩ
ድንቢጦች ተነስተው ወፍ ነን ወፍ አሉ

3.በኖሩበት አገር በተንሸራሸሩት
እንደ አህያ ታስረው ከተማውን ዞሩት

4.ሲወዱ አማርኛ ሲጠሉ ትግርኛ
እንዲህ ያሉ ናቸው የኢህአዲግ ዳኛ

5.አህያ መጣች ተጭና ቋንጣ
ዘጠና ሰባት ነገር አመጣ

6.ከጎድጓዳ ስፍራ ይበቅላል ደደሆ
የፈራነው ነገር መጣ ድሆ ድሆ

7.እናንተ ተማሮይ በጣም ቀበጣችሁ
ወይፈን ያለ በሬ እየጠመዳችሁ
ጎላ መመለሻው ቅጡ እንዳይጠፋችሁ

8.እንግዲህ አለቀ ትላልቁ በሬ
ባረባባ ወይፈን ተጉተት ሀገሬ

9.አንተ ሀይለ ስላሴ እኔ ምን ላርግህ
አሸንቀጥሮ ጣለህ የገዛ አሸከርህ

10.ጭቃና ምስለኔ ይባል ነበር ዱሮ
አመራር ካቢኔ ሆነ ተቀይሮ

11.እነ ፊትአውራሪ እነ ባላንባራንስ
ደርጉ ቢሰማቸው ሸተቱ አራስ አራስ

12.ግራአዝማች ቀኝ አዝማች ከቀረ ባዋጅ
እንደው ጓዱ ጓዱ እንባባል እንጂ

13.የኢህአዲግ አውድማ የማያፍረው
አቤ ተወቃበት ባረበረበው

14.የሚባለው ጮማ ፣የሚጠጣው ውስኪ
ከምን የመጣ ነው መለበሱ ካኪ

15.የሚባለው ክትፎ የሚጠጣው ውስኪ
ከቶ ለምኑ ነው መለበሱ ካኪ

16.እንኳን ተላቀቀህ ይላል ባላገር
እንኳ አስረከብካቸው ይላል ባላገር
እንኳን ሰጠኻቸው ይላል ባላገር
መቼ ነው መተኪያው ሀርሞና ሞይዘር

17.ደርግ ለድርድር ሲኸድ ወደ አትላንታ
ኢህዲግ ዘለቀ በዋድላ ደላንታ

6.1.4.ሙስናን እና አድልኦን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

1.ሊቀ መንበራችን ቃልቻ ነበረ
ባውንዱን እንደ ጫት ይቅመው ጀመረ

2.የሀይሌን አቅማዳ መንጌ ቀዳዶታል
ሊቀ መንበረ ሰፍቶ ይጠቀምበታል

3.ቀበሌ ብከስም ከወረዳው ላከኝ
ወረዳ ብከስም ወደ ዞኑ ላከኝ
ዞኑንም ብጠይቅ ወደ ክልል ላከኝ
ልመለስ ከቤቱ ውቃቢ ሳይርቀኝ

4.ሊቀ መንበር የኛ፤
አመራሩ የኛ፤
ስራ አስኪያጁ የኛ፤
አድበህ ተቀመጥ እንግዲህ ምቀኛ

5.አይጥ ስትቀብጥ የሰው ብቅል በልታ
ወጥመዱን በጥሼ አለች ሰው ልማታ

6.ሊቀ መንበሩ ጅብ ፀሀፊው ቀበሮ
በድሀው ባድማ ሰሩበት ቆርቆሮ

7.በእያሱ፣በእያሱ
ደህና ደህናይቱን፤ ለራሱ ለራሱ

8.እናንተ መኪንንቶች በምን ወጥ በላችሁ
እኛ በጆሯችን እናንተ በአፋችሁ

9.የደርጉ ተወካይ፤
እንዴት!እንዴት ምንኛ ምንኛ
ጉድንዴን ለእናንተ ገልባጤን ወደኛ

10.የኮሚቴ በሬ አይወጣም ዳገት
ዘመም ዘመም አለ ወደ ጎድንዲት

11.ኮሚቴ ሲበላ የለውም ትንፋሽ
እንጀራው አለቀ ተልባው ሳይታሽ
12.እኔ አላውቅበትም እንዲህ ያለ ነገር
የዝንጆሮ ሽንጎ የጅብ ሊቀ መንበር

13.ተይዤ ነበረ በትንሽ ምላስ
አጣርቶ ሰደደኝ የአውራጃው ፖሊስ

14.ሞፈሩን ቀንበሩን ሸረሪት ወርሰው
ከሊቀ መንበሩ ዘመድ የሌለው ሰው

15.ተወለጂ እንደሆን ትግሬ ተወለጂ
እንደ አዲሱ መንግስት እንድ ትወደጂ

16.ኧረ ነይ ዝም ብለሽ፤ኧረ ነይ ዝም ብለሽ
ከሊቀ መንበሩ ጉዳይ አለኝ ብለሽ

17.ደርጉስ ብሎ ነበር ጤፍ እንጀራ በርጎ
ውሻው ሊቀ መንበር ሌባው ፍርድ ሽንጎ

18.በዚህ ባገራችን የሚሰራው ስራ
መሬትን ለሀብታም ድሀን ለሰፈራ

19.ይሆነኛል ብየ የመረጥኩት ዳኛ
ጉድጓዲትን ለሱ ቦረቦሩን ለኛ

20.ጉድጓዲት ደህና ሁኝ መቼም አላገኝሽ
ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተጠቃቀመብሽ

21.ባለመቶ፤ መሬት ሞልቶ
ባለሀምሳ፤ጉድጓዲትን አንሳ
ባለሰላሳ፤ጉዳዩ አይርሳ
ባለሞሰብ፣ኮሚቴው ይሰብሰብ
ባለአምስት፣በዚህ ሳምንት
ባለወፍ፣ በዚሁ ይለፍ

22.ቤቱ ምን አረገ የበላንበቱ
አልጋው ይፍረስ እንጂ ትኂን ያለበቱ

23.አገሩ ነው ጅሉ፣አገሩ ነው ከንቱ
እግሩን የዘረጋ
አይጨፈጭፍም ወይ ትኂን ሲያፈራ አልጋ

24.ወይ ከሊቀ መንበር፤
ወይ ከፍርድ ሸንጎ ዘመድ የሌለው ሰው
ሰፈራ አይሄድም ወይ ምን አልከሰከሰው

25.እነ ሸማ ጋርዱ፣እነ በግ እረዱ
እናንተ ምስለኔ እምትባሉቱ
ጦራቱን ክበቧት እንደ ሞሰቢቱ

26.የመቶ ብር ጉቦ እኔ አልበላም ብሎ
የሀምሳ ብር ጉቦ እኔ አልበላም ብሎ
ዙብልን ነከረው ልጅ አወጣ ብሎ

27.እንዝመት ካላችሁ፤

ሊቀ መንበርና ፍርድ ሸንጎ ይምራ

እንደሚያዚያ በራ ለሊት እየበላ

6.1.5.ጥርጣሬን የሚያንፀባርቅ ይዘት ያላቸው ቃልግጥሞች

1. ላሬ ዘበንማ የተወደደው

አዲስ አማችና ምላሰኛ ነው

2.ገበያ ብወጣ አጣሁ ደህና በሬ

ጥጃውን ግዛና ውስ በል አገሬ

3.እሸኝሽ ነበረ እቤትሽ ደረስ

ታዲያ ምን ያደርጋል በላሬው ምላስ

4. እንዴት መራመጃ መሄጃ ያጣል ሰው

እሾህ ብቻ ሆነ እግሬን ብዳብሰው

5. አተር እንዳይዘራ ዋጉ መከራ ነው

ጤፍም እንዳይዘራ አረሙ ጣጣነው

እስቲ ተልባ ዝሩ የማላጋ ቀን ነው

6. ይሰራል እንጂ እጅ እስቲቆስል

ምንድን ነው ምላስ ውሻ ይመስል

7. አሽከሩ አሸክሺኪ ጌታው ምላስ ሰሚ

ልውጣ ከሀገሬ አልሆንኩም ከራሚ

6.2.የርስ በርስ ጦርነትንና ቆየት ያሉ ታሪካዊ ሁኔታዎችን የማንጸባረቅ ፋይዳ ቃልግጥሞች

6.2.1.በደርግና በኢህአዲግ መካከል ስለተደረገው ጦርነት

(በድጋፍና በተቃውሞ የተነገሩ)

1.የኢህአዲግ ጥይት ባለ ሁለት ጆሮ
ደርጉን አደረገው የሜዳ ዝንጆሮ

2.ስድስተኛ ብርጌድ ኸደ ከሚሉኝ
በኬሻ ጠቅልለው ሆርማት ይጣሉኝ

3.የኢህአዲግ እናት የመነመነችው
በርበሬውን ወልዳ ደርጉን አስፈጀችው

4.ራያና ቆቦ በጀግና ተከብቦ
ፋሽሽት አመለጠ ትጥቁን አስረክቦ
5.አርደውት ነበረ፤ገድለውት ነበረ፤
የድሀውን ልጅ፤
ከትግሬ መጥተው አተረፉት እንጅ

6.ተሀት ብላ ነበር አላ ነው ድንበሬ
እምቢ አለ ሚሊሻው ተጠምዶ እንደ በሬ

7.እነሱ ቀጫጭን ስማቸው ቅማላም
የደርጉን ወታደር ነዳቸው እንደ ላም

8.አስራ ሁለት ዶሮ ይዘህ በሆድህ
ያች ጎበዝ መጣይ ሊታይ ነው ጉድህ

9.መንጌ ሀይለማሪያም የወለቱ ልጅ
እህቱን ገደላት በሊኮፕተር ፈንጅ

10.የኢህአዲግ ጠላቶች፤
ከመንገድ ደፈጡ አሞት እንዳላቸው
እንበል እንተው ሲል ይዘፍናል እጃቸው

11.ሰዎቹ ቀጫጭን ከመጡበት እንጃ
በየወንዙ ጣሉት የደርጉን ውርንጫ

12.የደርጉ ሚሊሻ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ተሀት ገደል ገባች ዝንጀሮ ይመስል

13.ይኸ ቀን እስተሚያልፍ ãረ ተው ዝምበል
ምን ያደርግልሀል አህያ ጋር ትግል

14.በወደልማ ከሆነ ነገሩ
እነ በሬ ጎርደም ማይክሮፍ ነበሩ

15.የኢህአዲግ ወታደር ስንት ነው ልባቸው
መቶውን ወታደር ሁለቱ ነዲቸው

16.ሰዎቹም ይላሉ ቅጫማም ቅማላም
የደርጉን ወታደር ነዳችው እንደ ላም

17.አንማችው፤ አንማችው፤
ከዚያም አሉ፤ከዚያም አሉ፤
እንደ ግልገል ፈረስ ታንክ ይጋልባሉ

18.የቀይ ባህሩ ቂስ የአልጌናው ዲያቆን
ቶበተ መሰለኝ ጠመጠመ አሁን

19.መንጌ ሀይለማሪያም የጦሩ ገበሬ
እንኳን ባይኔ አየሁህ አልቀረህ በወሬ

6.2.2. የተቃውሞ ቃልግጥሞች

1.የደርጉ ወታደር ቂጠ ዝርንቡጡ
ሴቶች ይወዱታል ማር አለው ከቂጡ

2.የማነው ክላሽን የበሰበሰው
የደርጉ ይሆናል ጥሎት የሸሸው

3.እንዲህ በስተ ሸዋ ነጭ በሬ አገሳ
ተጫነ መሰለኝ ያነ አህያ ፈሳ

4.ሰወቹም ይላሉ ቅጫማም ቅማላም
የደርጉን ወታደር ነዳችው እንደላም

5.እነ ቢራ ውሃው እነ ዶሮ ቁርሱ
ኢህአዲግ ሲመጣ ወደየት ደረሱ
6.አስራሁለት ዶሮ ይዘህ በሆድህ
ያች ጎበዝ መጣይ ሊታይ ነው ጉድህ

7.በነቢላ በኩል፤
አህያና በሬ፤ሊጋጠም፤ሲያገሳ ሲያገሳ
መሸሹ ነው መሰል ያነ አህያ ፈሳ

6.2.3.ትዝብታዊ ቃልግጥሞች

1.አላማስለውም እርር ይበል ድስቱ
አሁን ትመጣለች በላይነሽ መንግስቱ

2.አንቶኖቭ መጥቶ ሲያስደነግጠነ
ሄሊኮፕተር መጥታ ስታሯሩጠነ
ሚግ ጀት መጥቶ አፈሰሰብነ

3.የወያኔ አህዮች ሁለት እግራ ናቸው
ቆቦ የተጫኑ ዳንዴ አራገፏቸው

4.ከመሀል እጅ ላይ ትወጣለች ልፊ
አቤት /መገን/አንዳንዱ ሰው ሬሳ ገፋፊ

5.በፊት ነበር እንጂ አመሉን ማበጀት
በሰማይ ላይ ሆኖ ወረቀት ከመርጨት

6.አንድ ጥይት ሳይጮህ አንድ ሰው ሳይሞት
ወልዲያን ለቀቀ ደርጉ አባጉልበት

7.በሰማይ ላይ ሆኖ ቦምብ ከመበተን
በክላሽን ጥይት ወርዶ መፈታተን

8.ምነው በሰማይ ላይ እንደ አሞራ ልጅ
ወርደህ ዶሮ ግብር፤
በክላሽን ጥይት፤ ፈትናቸው እንጂ

9.የደርጉ መኪና በርበሬ በልታለች
ውሃ ጠማኝ ብላ ጎሊና ገብታለች

10.የወታደር ኪዳ ወድቆ አይሰበርም
ጮቢ በርን ያየ ክፉ አይናገርም

11.እንደ ተከፋ ሰው አንገቱን ዘቅዝቆ
ሄደ ላይመለስ እንደማይሆን አውቆ

12.ሰዎቹ ቀጫጭን ከመጡበት እንጃ
ሰውን ይነዱታል በጦሬ ጠመንጃ

13.ይገርመኛል ይደንቀኛል የኪህ ሰወይ ስራ
ጠጉራቸው ጎፈሬ ጫማቸው ነጠላ
ጠጉራቸው ጎፈሬ ስማቸው ቅማላም

ጠቅልለው አዳፉት ጣብሶ እንዳደረ ላም

14.ምች መታው አሉ ድንገት ቆቡ ወልቆ
ሲሸሸ እየኸደ እንደማይሆን አውቆ

15.እነሱ ቀጫጭን ጫማቸው ቀላላ
አላህ ያውጣን በሉ ከሚያመጡት በላ

16.ሸሸን እንጅ ምነው አልሸሸነ
ወጀቦ የመታው ማሸላ መስለነ

17.ወይ እሱ አሸንፎ የልቡ አልደረሰ
ወይም ተሸንፎ ወይ አልትመለሰ
ጠረፍ እስተጠረፍ ወላድ አለቀሰ
18.መድፍ ሲንደቀደቅ መትረየስ ሲያጓራ
ተገትረው ቀሩ ድሀና ባንዲራ

19.ወራጋ ላይ ሁና ግራርፒን ብትለቀው
መንጌ ሀይለማሪም፤
አዲስ አበባ ሆኖ፤ወራው አስጨነቀው

6.2.5. ቆየት ያሉ ታሪካዊ ቃልግጥሞች

1.አንተ ያገሬ ሰው ወሬህን አታውራ
ይተዋወቃሉ አሞራ ላሞራ
እንቢ ብለህ እንደሁ ይሰድሃል ናኩራ

2.አባ ጠቅል ሀይሌ የጦሩ ገበሬ
አቆላልፎ ነዳው ነጨን በነጭ በሬ

3.የኔታ ራስ ወሌ፣
አንኮበር ላይ ሆነው፤ አደገ ራሳቸው
አይቆረጡ እንጂ የስር ቀን አላቸው

4.ሚካኤል በስተቀኝ፤ ገብርኤል በስተግራ
እየሱስ እርፋን ያዝ እስር እንዳይገባ

5.የመርጦው ሚካኤል፤
የወልዲያው ገብርኤል፤
እንደ መኳንንቱ፤
መሬት ተቃዳችሁ፤
ቀሚስ ታድላችሁ፤
እስቲ ወሌን አምጡ፤ ይታይ ጉልበታችሁ

6.ጎጃምን ሲከፋው፤
ትግሬንም ሲከፋው፤
ጎንደሬን ሲከፋው፤
ሮብላ ቢሉት፤ ወሎየን ደስ አለው

7.ሮብላው ኸደ ዳገት ለዳገት
ሳያወያየነ የዘመኑን ወቅት

8.እነዚህ ጣሊያኖች ማማሩ ባታቸው
ወደ ኋላ ሁነው ሲሄዱ ላያቸው

9.ሰሙ ወይ ሚካኤል፤ ሰሙ ወይ ንጉሱ
በርኖሱን ያውጡና ካባውን ይልበሱ
እግዜርም አንድ ነው ይበቃል እያሱ

10.ከባህር ላይ ሁኖ ያሸካካል ፈረሱ
ከድንጋይ ላይ ቁሞ ይተኩሳል እሱ
የሰባት ንጉስ ልጅ አባ ጤና እያሱ

11.የኔታ ራስ ወሌ፤
ንብ እንደበላቸው፤
ጨርቅ እየነገፈፉ፤
ዞብልን ላቡየ ፤
ጨርጨርን ለጉሸሽ፤
ራያን ለፈንታ፤ አርገውት አረፉ

12.ግዛ ግዛ ብለው ቢሰጡት አገር
ቀንበር ተሸከመ ከበሮቹ ጋር

13.ይኸ የራያ ሰው እርሻ አያውቅም ነበር
ያነ አመዴ ወሌ ጠመደው በቀንበር

14.የምኒልክ አልጋ እልፍ ነው ባለው
በትግሬ መንገሻ፤
በወሎ ሚካኤል፤
በሀረር መኮንን፤
ጎጃም ራስ ሀይሉ፤ እየደገፈው

15.እቴጌ ጣይቱ ትልቅ ባል አግብታ
እንጦጦ /ከሸዋ/ ተነስቶ አድዋ የሚማታ

16.ማይጨው ከበሩ ላይ ተጋግሮ ሙሬራ
ራስ ካሳ በቀኝ፤ ሽፈራው በግራ
ተካፍለን በላነው፤በሀይማኖት ካራ

17.ሰማይ ለእንግሊዝ ነው መንገድ ለስላሴ
ራያና አዘቦ አቤት አለ ደሴ

18.ጠቅል ባይወለድ እንግሊዝ ባይደርስ
ተፈጥመን ነበር ለአርብና ላሙስ

19.ብላ ጠጣ ብለው፤ ቢሰጡት ንጉሱ
እንጀራውን ጣለው እያሱ ትኩሱ
እንኳን ለሰውና አይበቃም ለራሱ

20.እማ ሸዋአረጋሽ፤
ከሞተችስ አይቀር በሞተይ በርጉሂ
በድፍን አበሻ ሳይረጭ መርሂ

21.አይቀጠቅጥም የነብር ወጠጤ
ጉራን ደበደበው ወንዱ አበበ ዳምጤ

22.አማካሪው ትግሬ ፈረንጁ ደንቆሮ
ጎቡን በኮረራ አግዳለሁ ብሎ
ሀበሻን ገደለው፤ ዳይ ብሎ፤ ዳይ ብሎ
23.የዮሐንስ በቅሎ ጠፍታ በሌሊት
ቀን ወደ ምኒልክ ስትሄድ አየናት

6.2.4.የኢትዮ- ኤርትራን ጦርነት የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

1.የሀገሬ ወጣቶች ጥይት አትተኩሱ
ዛላንበሳ ሜዳ ተቀልሷ ዳሱ

2.ዛላንበሳ ሜዳ ሰርግ የበላችሁ
በባድሜ በኩል ምላሽ መጣላችሁ

3.ኤርትራ ከበሩ ዘር እየተዘራ
ወይ ልጅ አያሳድግ እሸቱ አይበላ

4.የኤርትራን እህል አልበላም እርሜ ነው
የዘራው መትረየስ ያበቀለው ደም ነው

5.ታረሰ ቀይ ባህር መታረስ ይታረስ
ሳንፈተንበት እንደ ግልገል ፈረስ

6.ታረሰ አሉ አስመራ፣ታረሰ ቀይ ባህር
በክላሽን ቀንበር በታንክ ሞፈር
እነዚያ ጎበዞይ እየሆኑ ዘር

7.እኛ መች አውቅነው የባድሜን ጠጅ
እየበጠበጡ ይጠሩናል እንጂ

8.የኤርትራን መሬት እፋረደዋለሁ
ደህን ደህን ጎበዝ ገብሬበታሉ

9.የደርጉ መኪና ጅራቱ ቆራጣ
አድርሶ መንጣት ነው መልሶ አያመጣ

10.ዳምጤ መለሰን ብጠራው ዝም አለኝ
ተሰማ ወዳጆን ብጠራው ዝም አለኝ
አበራ ካሳው ነው ስጠራው ወይ ያለኝ

11.ተስማምተን ነበረ በነይሁን ብሻው
አሁንም አገሬ ያስፈራታል ግርሻው

12.አብሽ ድንብላሉን ገብረን ገብረን
መዝመታችን ላይቀር ዝም ብለን በኮራን

13.አንች አገር እንዴነሽ፤ አገሬ አንዴነሽ
ስንቅ አበጃጅተናል ልንጠይቅሽ

14.እንህድ ካላችሁ እንህድ ተነሱ
መቀሌ ቅርብ ነው መይጨው ኸደረሱ

7ኛ/ ከድርቅና ከርሀብ ጋር ተያይዞ የታየውን አሰቃቂ ሁኔታ የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸው ቃለግጥሞች

7.1.ድርቅ ጠቋሚ ወይም ድርቅ መምጣቱን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

1.ካሳ ሊቀ መንበር ፀሀፊው መለሰ
አንድ ዝናብ ሳይጥል መስከረም ደረሰ

2.ምን ያለ ቀን መጣ የተሰባበረ
ያገሬ ገበሬ እጅግ ተቸገረ
የተዘራው ሁሉ በሜዳ ላይ ቀረ

3.በፍላቱ በፍላቱ
ኮርትም ነው/ሆነ እራቱ

4.ጎበና በሞተ ባመቱ
የሰው ሁሉ፤
ኮርትም ሆነ እራቱ

5.የቆላ ማሽላ የጌታ ልጅ መሳይ
ተሸፋፍኖ ቀረ ዛላውን ሳያሳይ

6.ከሰኔ ጀምሮ መሬት ሰማይ አየች
እባክህ ደመና ዝናብ ጣል እያለች

7.ያ ስምንተኛው ሽ፤አልቀረም ደረሰ
መሬት ምጣድ ሆና የአዳም ልጅ ታመሰ

7.2.የርሀብ ወቅት ቃልግጥሞች

1.አንተ ሰባ ሰባት አንተማ ይብላኝ
ልጅ አልበቃ ብሎ ሚስቴን ታስቀማኝ

2.ኧረ ተው አምላኬ፤
ወይ ሞቴን አቅርበው፤
ወይ እድሌን ባርከው፤
ሆዴ ሊቀደድ ነው፤ ሲርበኝ የማከው

3.የቀይ መስቀል ዱቄት በልቼ በልቼ
ልሄድ ነው ሰፈራ ዘመዶቼን ትቼ

4.ያገሬ ነጭ ጤፍ ያገሬ ማሽላ
አይዞህ አትቆጣ
እዘራህ አለሁኝ ምናልባት ብመጣ

5.እንጀራው አለወጥ ወጡ የዘይት
በንጉሴ ጊዜ የለም እመቤት

6.ምስጋን ሊቀ መንበር ሚስቲቱ በለዲ
እንኳን ጤፍ እንጀራ አልጠገብንም ወዲ

7.በቁጥጥሮቹ በነጫኔ መርሻ
በሬ እስተገበሬው ገባ አሉ ኮምቦልሻ

8.ለማንስ ልናገር የሆዴንስ ላውጣ
ይኸ ሰባ ሰባት ያመጣብኝ ጣጣ

9.አንተ ሰባ ሰባት ያንተ ስራህማ
አይናችን እያየ ጆሮም እየሰማ
የሰው ልጅ ከውሻ አጥንት ሲቃማ

10.መቶ መቶ ኬሻ እንዳልተወቃብሽ
የጭነት መኪና እንዳልተጫነብሽ
ለምለሚቱ ቆቦ ቅጭሞ ፈላብሽ

11.በአላማጣው ካሳ በቅቦውም አጥሬ
ህዝቡ ተላለቀ በቅጭሞ ጥሬ

12.ስንዴ ዝናብ ጥሎ ጎርፍ እየደነፋ
ምነው በኛ መንደር ትንሽ ሳያካፋ

13.ይኸ የየጁ ሰው፤
እስላሙም፤
አላህ አላህ ይላል፤ አላህ የት ተገኝቶ
ክርስቲያኑም፤
እግዜር እግዜር ይላል፤ እግዜር የት ተገኝቶ
አማሪካን አገር ግብርናውን ገብቶ

14.ጌታው አቶ እግዚሀር፤
ከላይኛው አገር፤
ድግስ አስደግሶ፤
ዳሱን አሰርቶ፤
ያን የሚበላ፤
የካሳ የካሳው፤ ኸደ አሉ ተጠርቶ

15.ቀይ መስቀል ካፊያ ነው
ኮሚሽን ቅቅት ነው
አንጀት የሚያርሰው አባ ዝናቡ ነው

7.3.ድህረ ርህብ ቃላዊ ግጥሞች

1.አያልፍም መስሏቸው ህዝቡ የመነነ
ይኸው አለፈና የጥጋብ ቀን ሆነ

2.እንዲህ ቀን ሊወጣ ምርቱ ሊትረፈረፍ
አየ ማሳዘኑ ያ ሁሉ ሰው ሲረግፍ

3.አንተ መናጢ ቀን ምንኛ ክፉ ነህ
እንዲህ ቀን ሊወጣ ዘር ትጨርሳለህ

4.አንተ መናጢ ቀን እባክህ ታዘዘኝ
ለወሰድኸው ሁሉ ስንቅ አቀብልልኝ

5.አገሬ ተመልከት የዚህን ቀን ማማር
ቅቤው እንደ ጭቃ አዝመራው እንዳፈራ

6.ሚስቴ ፍታኝ ብላ ስንታንገራግረኝ
አንዱን በሬ ሸጬ አንደኛው ሲቀረኝ
ከምድጃው ወርዶ ሀውሴው ገላገለኝ

7.እንኳን በማረሻ እረስ በገጀሞ
ያነ ሰባ ሰባት እንዳይመጣ ደሞ

8.ጠላም አታፍስሱ፤
እንጀራ አታርክሱ፤
ያነ መናጢ ቀን አጮልቆ አይቶናል
የተመለሰ እንደሁ ይለቃቅመናል

9.እስቲ ተመልከተው የማረሻን ለዛ
የደረቀን ከንፈር መልሶ ሲያወዛ

10.እህል ደርሶ ነበር ሊገባ ባፋፉ
እነ አበሻ ውኔ እያዩት አለፉ

11.ያገሬ ገበሬ ሲያርስ ቶሎ ተሎ
ያገሬ ገበሬ ሲያጭድ ቶሎ ቶሎ
በጥር ነጭ ጤፍ በነሀሴ ቆሎ

12.በዚያ ሰባ ሰባት፤
ጠላት እንደሌለው ሰው እንዳልገደለ
ደጋሌት ምኝ ነው፤
ራያ ከሜዳው፤ ብቻውን አደረ
መቻሬ ሜዳ ላይ፤ ብቻውን አደረ

13.አንተም እንዳንልህ በማዘል ታዝለሀል
ህፃን እንዳንልህ ጢም አንገርግገሀል
የማሽላ ወንድም ታደግ ብለንሀል

14. በገበሬው ራብ እየተናደደ
ከተፋፋመው ፍም ወርዶ ተማገደ
የቅዱስ ዮሐንስ ተዋጋ እስተ ማታ
የመስቀል ለት ርሀብ ድል በድል ተመታ

15.ይኸን ሰባ ሰባት እፋረደዋለሁ
ወንድም እህቶቸን ቀብሬበታለሁ

16.እንዲህ ልንጠግብ በጋን ልናቦካ
ስንት ሰው አለቀ አፉ እህል ሳይነካ

17.ደመኛ እንደለለው ሰው እንዳልገደለ
እህል ከበረሃው ብቻውን አደረ

8ኛ/ ወቅታዊ ጉዳዮችን የማንጸባረቅ ፋይዳ ያላቸው ቃልግጥሞች

8.1.ስደትን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች

1.አንተ ጥቁር ሰማይ ወይ ውረድ ወይ ፍረድ
ሀበሻ ተወልዶ ሲሆን ያረብ ገረድ

2.ነጭ ጤፍ ቢዘሩት ማን ጋር ይበሉታል
ሽጋ ሽጋውን ልጅ ኪተር ልከውታል

3.የጅቡቲው ባህር የመዲናው ሹርጣ
አታሳልፍም ወይ የከፋው ሲመጣ

4.ባህር ተሻጋሪ ይኸዳል በታንኳ
አይኗን ባየሁትኝ ለአንድ ደቂቃ እንኳ

5.ጅዳ ተሻጋሪ ባላሰን ይመኛል
አሁን መናፈቄን ማን ይነግርልኛል

6.አየ እድል ማስጠላት አየ አለማማር
እሷ ባየር ሄደይ እኔ በባህር

7.ራቴን በላሁ በጨው በጨው
ምሳዬን በላሁ በጨው በጨው
ጅዳ የሄደ ሰው መቼ ነው መምጫው

8.ሱዳንን አየነው ከግር እስተ ራሱ
ሁመራን አየነው ከግር እስተ ራሱ
አህያ ነው በቅሎው ግመል ነው ፈረሱ
እንግዲህ ምን አለ አገር ቢመለሱ

9.ምንም ቢቸግረኝ አልሄድም ሁመራ
ወንዱ አርግዞ መጣ ለናቱ መከራ

10.ልጅን ላረብ አገር ሸጠነ ነበረ
ሚስትን ላረብ አገር ሸጠነ ነበረ
ገንዘብ አጠቃቀም ሳናውቅ ቀረነ

11.አንተ ጥቁር ባህር የተንጋለልከው
አታገናኝም ወይ የናፈቀ ሰው

12.የጅዳ ገበሮይ፤

እርሻ እረሱ እርሻ እረሱ

አፍላው አመለጠ ስትመላለሱ

13.በጀልባ ተሻግረው ባየር ቢመለሱ

አልጋውን ሰቀሉት እንጀራ ሳይቀምሱ

14.የጅዳ ገበሮይ፤

እርሻ እረሱ እርሻ እረሱ

ቀናችሁ ደረሰ ስትመላለሱ

15.ተማሪ ናት አሉ ያውም አስረኛ

ጅዳ ተሻገረይ ላረብ ሰራተኛ

8.2.ከበሽታ ጋር የተያያዙ ቃልግጥሞች

1.እንዴት ያለ ወገብ እንዴት ያለ እንገት

እንዴት ያለ ከንፈር እንዴት ያለ ጥርስ

እፍን አርገው ያዙት ቲቢና ኤድስ

2.የኤድስ በሽታ ነፍስህን አይማረው

ስንቱ ሰው አደረ ወዳጅ እያማረው

3.በል ሞትና ማጣት ከመንገድ ተመለስ

በል ሞትና ችጋር ከመንገድ ተመለስ

ወጣቶችን ድረን እስትንበላ ድረስ

4.እዩት እዚያ ማዶ ክፉ እሳት ነደደ

ምክር ያልሰማውን እየበላው ኸደ

5.ምንም ቢቸግረኝ አልኸድም ሁመራ

ወንዱ አርግዞ መጣ ለናቱ መከራ

8.3.ከቤት ግንባታና መፍረስ ጋር የተያያዙ ቃልግጥሞች

1.ምክር እማይሰማ ቸኩሎ ሰርቶህ
አሸዋና ድንጊያ በከንቱ ቀረህ

2.ኧረ መቸ ያልቃል ያዳሜ መከራ
አንደኛው ያፈርሳል አንደኛው ሲሰር

3.እዩት እዚያ ማዶ ክፉ እሳት ነደደ
ምክር ያልሰማውን እየበላው ኸደ

4.ይኸን ፈርቸ ነው ቤት እማልሰራው
የኒህ ሰወይ ጉዳይ ሳይገኝ መላው
6.እንደሰጡ አያልቅም እንደመነዘሩ
ያልቃል የቢስ ገንዘብ ሳይጠራ ስሙ

7.ወይም ሳይበላ ሳመጠወት
ከንቱ ሆኖ ቀረ ይኸ ሁሉ ሀብት

8.4.የአርሶ አደሩን የግብርና ስራ ኡደት የሚያንጸባርቁ ቃልግጥሞች

1.ይኸ ሀምሌ መጣ
ይኸ ነሀሴ መጣ
ዘር መዘራሪያው፤

2.ይኸ መስከረም መጣ
አረም ማረሚያው፤

3.ይኸ ጥቅምት መጣ
ወፍ መጠበቂያው፤

4.ይኸ ህዳር መጣ
ይኸ ታህሳስ መጣ
አጨዳ ውቂያው፤

5.ይኸ ጥር መጣ
የሰርግ መብሊያው፤

6.የካቲት መጋቢት
የእርሻ ማረሳሻው
የበልግ መዝሪያው፤

7.ይኸ ሚያዚያ መጣ
ደጋሌት መዝሪያው

9.ይኸ ግንቦት መጣ
ይኸ ሰኔ መጣ
የበለግ መውቂያው

10.አመቱን በሙሉ እረፍትም የለው
ታታሪው ገበሬ ከቶ እንደምነው።።

8.5.ቤተሰባዊ መራራቅን የሚመለከቱ ቃልግጥሞች
1.አሁን በቀደም ለት ገባያ ወጥቸ
የከብቱንም ተራ አይቸዋለሁኝ
የፍየል የበጉን አይቸዋለሁኝ
የጤፍ የማሽላን አይቸዋለሁኝ
የጥጥ የበርበሬን አይቸዋለሁኝ
የዶሮ የቅቤን አይቸዋለሁኝ
ኸዘመድ በስተቀር የረከሰ አጣሁኝ።።

2.ወንድሞቸ ጠሉኝ ከቶ ምን አልኳቸው
እህቶቸም ጠሉኝ ከቶ ምን አለኳቸው
ጎረቤትም ጠላኝ ከቶ ምን አልኳቸው
ባልንጀራም ጠላኝ ከቶ ምን አልኳቸው
ያጣሰው አያገኝ፤የታመመ እማይድን፤እየመሰላቸው።።

3.በረባ ባረባው፤
በሆነ ባልሆነው፤
እትማማቾቹ፤
ወንድም አማቾቹ፤
ጎረቤቱ ሁሉ፤
አባትና ልጁ፤
እነ ባልና ሚስት፤እየተሰላቹ
ሞት የመጣ ጊዜ ላዘን አይመቹ፡፡

4.በእንዴት ያለው ወራት፤
በእንዴት ያለው ዘመን
አንከን አግንቶህ
አይ እህትማማች
አይ ወንድም አማች
አይ ባልና ሚስት
አይ አባትና ልጅ መጡ ከደጅህ
ፍቅር ሽሚባለው ሰርግ ተጠርተህ፡፡

ሰንጌ (የሰንጎ መገን ቃልግጥሞች)

በአማርኛ ስነፅሁፍ /ስነግጥም/ ጥናት የግጥም አይነቶች በሚል አከፋፈል የአማርኛ ስነግጥም ሲከፈል /ሲመደብ/ አንደኛው ምድብ የሰንጎ መገን የሚባለው ነው:: ይህ ምድብ በስንኝ ባለ አምስት ቀለም ምጣኔ እንደሆነ የስነ ጽሁፍ ምሁራን ያስረዳሉ:: ይህ ሁኔታ በአማርኛ ቃልግጥም ውስጥ በሚከተለው መንገድ/ሁኔታ/ ተከስቷል፡፡(ምናልባት አይዋ ተገኘ ጉባይ፤አሊ(አልዬ) ጡሀ ይባል ከነበረው ባህላዊ ተጫዋች (አዝማሪ) ሰምቶ እዚህ ያደረሰው ይሆናል፡፡)

እንደ ደርብ እንጨት ሰንጌው አሸኳታች
ከላይ ነው ሲሉት ደራሽ ኸዚያ ታች
እንዴት ነው ሰንጌ እንዴት ነው ፈረስ
ከተፋፋመው ኸጦር እሚያደርስ

ሀሰቱም እንዲሁ ይናገር ጀግና
እሱ እንኳ ቢሞት ስራው አለና
እየተኮሰ በሄደበቱ
ያሰኛል ሚስቱን እመቤቲቱ

እርካብ ረግጠው ፈረስ ሲወጡ
አምሌ የጠጣ ይመስላል ፊቱ
መጡ፣ መጡ፤ የተባለ ጊዜ
የጀግና ደስታ የፈሪ ትካዜ

ኧረ ምን ሊሆን የጎበዝ ገራም
ሲያኩት ዝም ይላል እንደ ሀርኮ ላም

ኧረ ምን ሊሆን የጎበዝ ፈሪ
ምንሽር ይዞ ድንጋይ ወርዋሪ
ኧረ ምን ሊሆን ቅቤ ከነአሩ
ምን ሊያረግልህ ቅቤ ከነአሩ
ይቀቧል እንጂ እያነጠሩ

እንደው ምናምን ሳልለው እኮ
አገኘው ጀመር ሆዴ ታውኮ

አልናገርም እንዲያው ዝም ጥርቅም
ቀን የሚወልደው አይታወቅም
ያንዱን ሆድ አንዱ ገልጦ ቢያይበት
ስንት እዳ ጉዱ /ስንት ጉዳጉድ/ በተገኘበት

ኧረ መጡ፤ ኧረ መጡ፤ እኛም አየናቸው
አንበሳም አደሉ እንደኛ ሰው ናቸው
መድሀኒት የጠጣ ይመስላል ፊታቸው

ተኩሰው ላይስቱ ባለማላ ናቸው
ደህና ደህና ጎበዝ ይዘው ካልቆዮዋቸው

አይቀርምና ተሰርቶ መፍረስ
በለው ግንባሩን ወዲያው ይመለስ
አንዱን በጥይት ካልጣሉባቸው
አንዱን በሾተል ካልመቱባቸው
አንዱን በአንካሴ ካልወጉባቸው
አይመለሱም ቢገዘቷቸው

ኧረ ተው ጥይት አታበላሹ
ኧረ ተው ሞይዘር አታበላሹ
ኧረ ምንሽር አታበላሹ
የራያ ልጅ ነው ቀድሞ ደራሹ
የራያ ልጅ ነው ማልዶ ደራሹ

መወለድማ የትም ይወለድ
ለማደጉ ግን ራያ ይደግ
ለማደጉ ግን ላስታ ላይ ይደግ
ለማደጉ ግን የጁ ላይ ይደግ
እንደፈጣሪ ነፍስ እሚታደግ

ለመወለዱ የትም ይወለድ
ለማደጉ ግን ራያ ይደግ
የጁ ላይ ይደግ
ቆባ ላይ ይደግ
እንደፈጣሪ ነፍስ እሚታደግ

የሴትዮ ልይ እነብልሹ
ጠጅ በብርሌ ከለሸለሹ
ጮማ በቃሪያ ከከሸከሹ

አምላክ ያብጀው እያሉ ሸሹ
ምነው ቢሸሹ ነገር ሲከፋ
በየመንደሩ ማውራቱ ከፋ /ማውጋቱ ከፋ/

እንዴት ነው ጎመጀ አፋፍ አፋፉ
እንዴት ነው ጨርጨር አፋፍ አፋፉ
እንዴት ነው ዞብል አፋፍ አፋፉ
ጎበዙስ አልቋል እንዴት ዛፉ
የላሞቹ ቀንድ ይታያል ጫፉ

እንዳይላጨው ጠጉሩን ወደደ
እንዳይቀባው ሙያው ገደደ
እንደው ባንጉል ጉተናው ጨደ

አይመጡም አንጅ የመጡ እንደሆን
አልመደንገጥ ከልብ መሆን
በለው ግነባሩን ወዲያው ይመለስ
አይቀርምና ተሰርቶ መፍረስ

አባሪ ሶስት፡- የእንግሊዝኛ እና የአማርኛ ሙዳየ ቃላት

ሀ/ ከእንግሊዘኛ የተተረጎሙ ቃላት፡-

- በተጠቃለለ = summarized
- የፎክሎር ተግባቦት መርሆዎች = the principle of folklore communication
- አዕምሯዊ = cognitive
- ገላጭ = expressive
- ማህበራዊ = social
- ገፅታዎች = features
- አካባቢያዊ ስያሜዎች (ስሞች) = local names
- ስነ-ዘዴዎች = Methodologies
- መንቶ = couplet
- ህዝባዊ/ሀገረሰብ/ዘፈኖች = folk songs
- የህዝብ አሰፋፈር ለውጥ = population demographic change
- ክለሳ ድርሰት = Review literature
- ንድፈ-ሃሳቦች = theories
- አውራ ንድፈ-ሃሳቦች = Grand theories
- መዋቅራዊ ፎክሎር ንድፈ ሃሳብ = structural folklore theories
- ቀመራዊ = formulaic
- ቀመራዊ ንድፈ ሃሳብ = formulic theories
- መሸጋገሪያ = enjambment
- የጀግና ግጥም = heroic poetry
- ርዕዮተ-አለማዊ ንድፈ- ሀሳብ = Ideological theory
- ሰይጣናዊ ንድፈ ሀሳብ = evil theory
- የዘር ሁሉ የበላይ = master race
- ዘር (ደም)ና ባህል = blood and culture
- ማስተጋቢያ = echo
- ሀያል ድምፅ = vigorous voice
- የስራ ተግባር = laboring activity
- ተግባራዊ ንድፈ-ሃሳብ = functional theory
- ስነ-ሰበኞች = anthropologist

- ማዕቀፎች = frame works
- ማስተማር = educating
- ማስመለጥ = escaping
- ማረጋገጥ = validating
- መቆጣጠር = controlling
- መረጋጋት = stability
- ዋና መሳሪያ (ዘዴ) = mechanism
- የማስተማሪያ ዘዴዎች (መሳሪያዎች) = pedagogical devices
- ተግባራዊ ስነ-ልቦና ትንተና = psychoanalytic functionalism
- ገላጭ ባህሪያት = expressive behaviors
- ታሪካዊ ጠቀሜታ = historical usage
- እይታ = perspective
- ዋጋ (ጥቅም) ያለው = valuable
- ታሪካዊ መረጃ = historical data
- ማህበራዊ ሰነዶች = social documents
- የቃል ባህል = oral tradition
- ዘፈኖችና መዝሙሮች = songs and chants
- ህዝባዊ /ሀገረሰብ/ ግጥም = folk poetry
- የቃል ግጥም ቅርፆች /አይነቶች/ = forms of oral poetry
- ክዋኔ = performance
- ቃላዊ ባህሪያት = verbal elements
- ክዋኔና አውድ ተኮር ዘዴዎች =performance and contextual approach
- አውዳዊ ህጎች(ስምምነቶች) = contextual convention
- ስሜትን /ትኩሳትን/ የማስተንፈሻ መንገድ = steam valve and out let
- ከበራ = ritual
- ውስጣዊ ግንኙነቶች = inter-relationship
- አካባቢያዊ (ቀያዊ) ምድባዎች = emic categories
- ምደባ = classification
- ጭብጣዊ ዘዴ (አቀራረብ) = thematic approach
- ትንተናና ትርጎማ = analysis and interpretation
- ብያኔ = definition

- ስነ ቃል = oral literature
- ቁሳዊ ባህል = material culture
- ሀገረሰባዊ (ህዝባዊ) ትውን ጥበባት = performing folk arts
- ማህበራዊ (ሀገረሰባዊ) ልማዶች = social folk customs
- ዝርው ህዝባዊ (ሀገረሰባዊ) ተረኮች = prose folk narrative
- ቃልግጥም = oral poetry
- አጫጭር ቅርፆች = short forms

ለ/ በመረጃው ውስጥ ፍችና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው የአማርኛ ዘየ ቃላትና አካባቢያዊ ስሞች

1. ሌዶ= አፋር አካባቢ የሚገኝ ዛፍ ነው። ቅርንጫፎቹ አባጣ-ጎባጣ ስለሌላቸው ለዱላ ይመረጣል። በአገባቡ፣ ቆንጆ፣ ቁመናው ያማረ፣ መልክ-መልካም፣ ማለት ነው።"ኧረ በሬው ንጉስ ፣ ኧረ በሬው ሌዶ/ እንሂድ ቦይ ለቦይ" እንደማለት።
2. አንጋዳ = በጣም አስቸጋሪ፣ አደገኛ ቦታ ማለት ነው።
3. ቡሻ = በራያ አዞቦ በኩል፣ አፋር ውስጥ የሚገኝ የማንደኛ ቦታ
4. ሎላ = የተቋተ ውሃ፣ ኩሬ እንደ ማለት ነው
5. ፎቂሳ = አፋር ውስጥ (ዞብል በታች) የሚገኝ አፋር አካባቢ ነው
6. ጭንቁላ= ከሸክላ የሚሰራ ንፍሮ መቀቀያ፣ ባህላዊ እቃ
7. ግዛ-ግዙ= በአገባቡ፣ የማይረባ፣ ድሀ፣ ዘመድ አዝማድ የሌለው ሰው
8. አባ-ግርሻ = የሙገሳ ስም፣ በአገባቡ አመፀኛ እንደማለት ነው
9. መወንዘፍ = ለመምታት መሞከር፣ መስንዘር እንደማለት ነው
10. መንገሌ =ብረት ምጣድ ወይም በሸክላ ምጣድ የሚጋገር ቂጣ፣
11. ቃጤ = በአገባቡ ማስጨነቅ፣ ቀውጢ፣ጭንቅ ሲፈጠር... ማለት ነው
12. አኖጋው = በሀይል መታው፣ ጭንቅላቱን ፈረከሰው ማለት ነው
13. በተማለም አይቀር=በተወራው አይቀርም፣ በተግባር ይፈፀማል ነው
14. እለግ- እለግ = በአግባቡ ሰውነቱ ሲተጣጠፍ፣ ሲያረገርግ ማለት ነው
15. አቦላው ቀለሰ =ማሸላው ወለደ ሲሆን፣ አገባቡ ወጣቶች
    ለከባድ ሀላፊነት (ለጦርነት፣ ለዘመቻ፣ ወዘተ.)
    የሚጋፈጡበት ጊዜ ደረሰ፣ችረግሩ ገፍቶ መጣ፣ ማለት ነው

16.ዝንጥል=ዝንጣይ፣ቅርንጫፍ፣በአገባቡ በትንሽ ነገር መከላል ወይም ማጥቃት ነው

17.ሆለታ = የወባ በሽታ፣ የሚያንቀጠቅት በሽታ፣ በአገባቡ ፈራ ማለት ነው

18.እርሽም- እርሽም = በአገባቡ ጎበዝ ለመምሰል የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ አለባበስ ማሳመር ብቻ፣

19.የሚታደግ = ለችግር ጊዜ የሚደርስ፣ ጀግና፣ ቀድሞ ደራሽ፣

20.ቦደረኛ = እኩያ፣ አቻ፣ ተፎካካሪ፣ ተወዳዳሪ ማለት ነው

21.ፋሚሌ = ዘመናዊ አልጋ፣የሸቦ ወይም የጣውላ ሰፊ አልጋ ነው

22. ጉጉብዱ = አፋር ክልል የሚገኝ የኮንትሮባንድ መገበያያ ቦታ

23.ሀራ = ከዶሮ ግብር በታች የሚገኝ የገጠር ከተማ (የንግድ ቦታ)

24.አማሪካ = በአግባቡ በጣም ቀይ ማለት ነው

25.ቀንዳም = ትልልቅ ቀንድ ያለው ሲሆን፣ በአገባቡ ትልልቅ ሰው ማለት ነው።።

26. ጎታ = ከጭቃ እና ከእበት የሚሰራ ባህላዊ የዱቄት ወይም የእህል መያዣ እቃ

27.ባውንድ = በአገባቡ የባለ አስር ብር ኖት ሲሆን፣ ሃምሳና ለመቶ ብር ኖቶችም ይሆናል

28.እምብርት = የማንኛውም እንስሳ እትብቱ የሚቆረጥበት ቦታነው።። በአገባቡ ለከብት ሲሆን፣ ለዝርያ መረጣ እንደመስፈርት ይሆናል።።

29. ዳውሪ = በጥቁር መልክ ላይ ነጫጭ ነጠብጣብ መልክ ላላቸው ከብቶች መለያ ነው።። ለልጃገረዶች ልብስ ሲሆን በቅቤ በተነከረ ትፍትፍ ላይ የብር መልጎም ያለበት ነው

30.መሌ = ቦይ፣ መስኖ እንደማለት ነው

31.ጫንቃ = ትክሻ፣ ጉልበት፣ ማለት ነው።።በአገባቡ የበሬውን ሃያልነት አስተማማኝነት የሚያመለክት ነው።።

32. አረንዛ = ድንጋያማ ቦታ፣ ለማረስ አስቸጋሪ ቦታ ማለት ነው

33.መጋላ = ሲነበብ ‹‹ጋ››ና ‹‹ላ›› አይጠብቁም፣ የቀይና የጥቁር መልክ ውህደት ያለው የበሬ (የከብት) መልክ ነው።።

34.ሚዜ = ጓደኛ፣ እኩያ፣ አቻ፣ ባልንጀራ ወዘተ. ማለት ነው

35.ግብርና አነጠሩ = በግብርና ሙያ፣ በእርሻ ስራ የበለጡ ሆኑ፣

36.ገለሂሞ= ቃሉ ከኦሮምኛ የተወረሰ ይመስላል፣ ቆንጆ የምትገኝበት አካባቢ እንደማለት ነው

37.ሽብራር = ከፍየል ቆዳ የሚሰራ የውሃ መያዣ ስልቻ ነው

38.ሱቢ ገማማ = ሌሊቱ ሊነጋጋ ሲል፣ ወፍ ሲንጫጫ ማለት ነው

39.ሰላጤ = ስለት ያለው፣ ሹል የኮርማ ቀንድ፣ ማለት ነው

40.ጋታቸው አረረ = ጡታቸው ደረቀ፣ ወተት አልሰጥ አለ ማለት ነው

41.ያመለ-ጭድ = የበሰበሰ ገለባ፣ ማለት ነው

42.ከሎ = አፋር ውስጥ የሚገኝ ቦታ

43.ቀጮ =ከቅል የሚሰራ የወተት መያዣ እቃ

44.ቡርቃ = አፋር ውስጥ የሚገኝ ቦታ (ጥሬ ትርጉሙ ምንጭ ነው)

45. ወናሳ = አፋር ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም

46.ሰባቱ ጋሪያ = አፋር ውስጥ የሚገኝ የአካባቢ ስም

47.ዳቡሌ-ገውስ = የከብት (ላም) መጠሪያ ስም

48.ዋርሌ = የላም መጠሪያ ስም

49.ዲሌ-ሮይታ = የላም መጠሪያ ስም

50. ልማት = በአገባቡ የቧንቧ ውሃ ማለት ነው

51.ደራይቶ = አፋር ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስም

52.አይኗን እየዳጠይ = በአገባቡ ገና ከእንቅልፏ እየተነሳች

53. ደይ- መውጣት = በአገባቡ ወደ መፀዳጃ ቦታ መሄድ፣ ነው

54.አጓምዳ = በአገባቡ ነገር አመላላሽ፣ ወሬኛ፣ ውሸታም፣...ነው

55.ምጎጎ = የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ ማለት ነው

56.ግልድም = ከወገብ በታች የሚለብሱት (የሚታጠቁት) ባህላዊ ልብስ፣ወይም ጎንቢሶ ማለት ነው

57.መገነጥ = ለአስክሬን ማሰሪያ (ማዘጋጃ) የሚሆነ ፈትል፣መግነዝ፣ ነው

58.ካባ-ሚንቶ = ዘመናዊ የእህል መፍጫ ወፍጮ ማለት ነው

59.ሰላሱት = የአተር ክክ፣ ማለት ነው

60.ጣተ-ለምለም = ስራ ሰርቶ የማውቅ፣ እንደማለት ነው

61.ጓል = እርሻ ሲታረስ የሚታይ የአፈር ድቡልቡል፣ በተለይ መሬቱ ደረቅ ሲሆን ለማረስ የሚያስቸግር ነው

62.ቦቼሌው ባትህ = ወፍራምና የሚያምረው የእግርህ ባት

63.እንዳይደብልብህ = በአገባቡ ረሀብ፣ ችግር፣ እንዳይገጥምህ፣ እንዳያገኝህ፣ ማለት ነው

64.ተባረቀይ በሉ = በአገባቡ በጥይት መምታት፣መግደልን ያመለክታል፣ድንገት ሳይታሰብ የተተኮሰ ጥይት።።

65.ጭፍና = በጭጋግ የታጀበ፣ የማያቋርጥ ዝናብ፣ ፀሀይ የማይታይበት የአየር ሁኔታ፣ ወዘተ. ማለት ሲሆን፣ በአገባቡ አስቸጋሪና ፈታኝ ጊዜ፣ ወቅት፣....ነው

66.ገዶ = የአዕዋፍ ዝርያ፣ የአሞራ አይነት ነው

67.ገመሌ = የወጣት ወንዶች አለባበስ እና ልብስ፣ በቀኝ ብብት ስር አልፎ ፣በግራ ትክሻ ላይ የሚለበስ ማለት ነው።።

68.እርቁ = አፋር አካባቢ የሚገኝ የቦታ ስም

69.አታድበክብክ = አታለባብስ፣ አትሸፋፍን፣ በግልፅ ተናገር ማለት ነው

70.አደስ = ጥሩ ሽታ ያለው ቅጠል፣ ከቅቤ ጋር ተደርጎ ሴቶች ፀጉራቸውን ቅቤ የሚቀቡት ቅጠል (እንደ አሸኩቲና ናትራ ያለ ነው)

71.ገለሎ = በአገባቡ ውጤት አልባ ማስቀረት፣ ጥቅም ላይ አለማዋል፣ ነው

72.ሀርኮ ላም= ጥጃዋ የሞተባት ሲሆን፣ በአገባቡ ፈሪ፣ገራም፣ የማይረባ፣ ማለት ነው

73.ደረባ = ጦር ወይም አንካሴ ሰበቀ ማለት ነው።

74. ሸክና = ከቅል የሚሰራ የውሃ፣ የጠላ፣ ወዘተ. መጠጫ

75.ቀጠናዩ = በአገባቡ ሰው መሳይ፣ ቆንጆ መሳይ፣ ተፈላጊ ነኝ ብሎ ማሰብ፣ ወዘተ. ነው

76.በካር ጊደር = መጀመሪያ የወለደች ጊደር፣ ማለት ነው

77.ሆላ = ላታም የአፋር በግ ማለት ነው

78.ቲሊንቲ = የጣሊያን ወታደር

79.ነጃ በለኝ = በአገባቡ አውጣኝ፣ አድነኝ፣ልቀቀኝ፣ ማለት ነው

80.ጉቤ = የደጃች ጎበና አመዴ የቁልምጫ ስም

81.አባ ከስክስ = በአገባቡ፣ ሀይለኛው፣ ጀግናው፣ ደፋሩ፣ ማለት ነው።ለአባተ ሀይሉ የተሰጠ አካባቢያዊ ማሞገሻ

82.ወሬራው = በአገባ ጀግናው፣ ሀይለኛው፣ ወዘተ. ማለት ነው

83.ቆሪ = ትንሽ ገበታ፣ የፀጉር ቅቤ መያዣ ገበታ፣ ወዘተ. ነው

84.አላይና =አፋር አካባቢ የሚገኝ የአካቢ መጠሪያ

85.ጌደሩ =ዋጃ አካባቢ የሚገኝ የቦታ ስም

86.መልጎም = ከብር የሚሰራ፣ በልጃገረዶች ትፍትፍ ላይ ለውበት የሚሆን ጌጥ፣ለመሳሪያ ማንገቻም ይሆናል።

87.ድርምም = ረጅም ፀጉር ያላቸው ሴቶች ፀጉራቸውን የሚሰሩበት የአስራር አይነት፣

88.እርቦ = የጋቢ ግማሽ፣ ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች የሚለብሱት ባህላዊ ልብስ ነው

89.በደና = የዛፍ አይነት ሆኖ የሚበላ ፍሬ ያለው ነው። በአገባቡ ወፍራም እግር ያላት ማለት ነው።

90.ቁርቁራ = ፍሬው የሚበላ፣ እንኮይ የሚመስል፣ እሾህ ያለው ዛፍ

91.ጀነት = የገነት ስፍራ፣ የፅድቅ ቦታ ማለት ነው

92.መሙጫ = ትንሽ፣ አነስተኛ ማለት ነው

93.ስርቡቅ ማለት = በአገባቡ ወደ ውስጥ መግባት፣ ማለት ነው

94.ግችም- ግችም = ቁጭ ቁጭ ያለ፣ በአገባቡ ያልወደቀ ጡት፣

95.ደንቦል- ደንቦል = በአገባቡ ቶሎ ቶሎ መራመድ፣ አረማመዷ ደስ የሚል፣

96.ሰንበር = ምልክት፣ በተለይ ከግርፋት በኋላ የሚታይ ጠበሳ

97.ለኮ = የፈረስ ወይም የበቅሎ መሳቢያ ሰፊ ጠፍር

98.አሚዴ = ከድርምም ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የፀጉር አስራርና ብዛት

99.ላንባዲና = የአጅ ባትሪ፣ ለመብራት የሚገለግል ባትሪ

100. መከዳ = በአገባቡ ቆንጆ፣ የምታምር፣ ወዘተ. ማለት ነው

101. ቃሪሳ = የልጃገረዶች የፀጉር አሰራር ኤኔት፣ ጋሜና ዋሪሳ እንደማለት

102. ንሽ = ርጥበት ማለት ሲሆን፣ በአገባ ሰውነቷ ለስላሳ ነው ማለት ነው

103. ጠጅ-ሳር = ቆንጆ ሽታ ያለው የሳር አይነት፣ መልካም ጠረን፣

104. ደርባባ = ረጋ ያለች፣ ቆንጆ ማለት ነው

105. ጮንቋና = አይኗ በጣም ትንንሽ፣ ግን የማያምሩ ማለት ነው

106. ዱርንቅ = በጣም አጭር የሆነ አንገት

107. በናና = ጸጉሯ ያለቀ፣ ስስ ፀጉር ያላት ማለት ነው

108. በርሜል = በአገባቡ ወገቧ ወፍራም የሆነ ማለት ነው

109. ሄ!ሄ! ልበልሽ = በዱር ውስጥ ከብት የጠፋበት እረኛ፣የጠፋውን ከብት የሚጠራበት ነው፡፡ በአገባቡ ልጥራሽ ማለት ነው

110. የሸኩትኩት መሄድ = በእንፍቅቂት መሄድ

111. ዱበርቲ =እናቶች ተሰበሰበው ባህላዊ የፀሎት ስርአት የሚያካሂዱበት ሁኔታና ቦታ

112. ልህላሂ = በአገባቡ የማር ወለላ ማለት ነው

113. ሀያ = በአገባቡ‹‹እሽ›› እንደማለት ነው

114. ዛውያ = በእስላም ሀይማኖት ቡና የሚጣበት ስፍራ

115. ወይፈን-ግቡ = አዲስ የቀና፣ ለማረስ የተገራ ወይፈን ማለት ሲሆን፣ በአገባቡ እንደ ጀማሪ መቆጠር፣መታየት፣ማለት ነው

116. ፈንዛ = ጅራቱ ላይ ጥቁርና ነጭ ምልክት ያለው

117. አኹላሊት = የሚያቃጥል ቅጠል፣የሳማ አይነት ነው

118. ጋጋኔ = የአፅዋፍ ዝርያ

119. አጣባ =ገበና፣ ችግር ማለት ነው ‹‹የጎበዝ ኮሳሳ የቤቱን አጣባ ያወራል›› እንደማለት

120. ዳዋ = አረም፣ ቅጠላቅጠል የበዛበት አካባቢ

121. ኮንትሮ = የኮንትሮባንድ ነጋዴ ማለት ነው

122. ጭሊ =በ1970ዎቹ እያገለግለ የነበረው የመቶ ብር ኖት

123. ፍስስ በገላየ = በአንድ ወቅት ፋሽን የነበረ የሴቶች ልብስ

124. ተባለ እንዴ = ›› ›› ››

125. መበርበር = በአገባቡ ጤፍ ሲወቃ በእጅ ማገላበጥ ነው

126. መመንሸት = በውቂያ ላይ ጤፉን በአንዶየ፣ወይም በመንሽ ማገላበጥ

127. ቀርሻማ = በአገባቡ ሰባራ ማለት ነው

128. የርብርብ ልጅ = አባቱ በትክክል የማይታወቅ ልጅ (ህፃን)

129. ጥልቆ = አነስተኛ ቁንቁጦዎችን መቁረጫ፣ ድግር መጥረቢያ፣ ወዘተ.መሳሪያ

130. ገርቢ = የዛፍ አይነት

131. ኮረራ = የግራር ዛፍ

132. ደድሆ = የእፅዋት አይነት

133. ሀርሞ = ቀንዳቸው ረጃጅምና ቁመናቸው ትልልቅ የሆኑ ከብቶች

134. ገልባጤ =ጭንጫ መሬት፣ ምርት የማይሰጥ ማሳ

135. ቦረቦር = በጎርፍ የተሸረሸረ መሬት (ማሳ)

136. መጎርደም = በአገባቡ በብዛት መብላት፣ መመገብ ማለት ነው

137. ዝርንቡጥ = ከመጠን በላይ ወፍራ የሆነ ቂጥ፣ ሰውነት፣ ያለው

138. ነቢላ = በመርሳና በወልዲያ መካከል የሚገኝ ተራራማ ቦታ

139. ዳንዴ = ትግራይ ውስጥ የሚገኝ አካባቢ

140. ልፊ =ብዙ ጊዜ እጅ ላይ የሚወጣ አደገኛ የእባጭ አይነት፣በባህላዊ ወይም በህክምና መድሀኒት ካልታከሙት ለሞት ወይም ለአካል ጉዳት የሚያበቃ በሽታ

141. ወጆቦ = ሀይለኛ ንፋስ የቀላቀለ ዝናብ፣ወጨፎ፣ወዘተ.

142. ናኩራ = ቀይ ባህር አካባቢ ያለ ቦታ፣ ጣሊያን ለእስር ቤት ይገለገልበት የነበረ ስፍራ

143. ሮቢላ = አውሮፕላን

144. አባ ጤና = የልጅ እያሱ የፊረስ ስም

145. ሹርጣ = ስደተኞችን የሚይዝ የአረብ አገር ዘበኛ

146. የቢስ ገንዘብ = የስስታም፣ የስግብግብ ገንዘብ፣ ንፋግ ሰው ማለት ነው

147. በለዲ = የሴት ስም

148. ወዲ = ፊሬው የሚበላ፣ በለስ ማለት ነው

ደጋሌት = የማሽላ አይነት፣አቦላ፣ አባይሪ፣ጅጉርቴ፣ወዘተ.እንደማለት ነው

አባሪ አራት፡- ከመረጃ አቀባዮች ጋር የተደረጉ ቃለ- መጠይቆች
ከአጫጭር የህይወት ታሪኮች ጋር

መግቢያ፡-

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና አላማ በአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ በድህረ - ምረቃ መርሃ - ግብር ለ3ኛ ዲግሪ ማሟያ በአማርኛ ቃልግጥሞች ትንተና ላይ ለሚደረግ ጥናት ተጨማሪ መረጃና ግብዓት ለመሰብሰብ ነው፡፡ጥናቱ፤ በሰሜን ወሎ አካባቢዎች፤ በተለይም በቆላማው ወረዳዎች፤ በሚሰበሰቡ ቃልግጥሞች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፤ እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ስለሆነም፤ ለቃለ-መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆነዎ ከልብ እያመሰገንሁ ጥያቄዎቹን ተራ በተራ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

<u>ከአምሳ አለቃ መላኩ ተገኝ ጋር የተደረገ ውይይት</u>

ጥያቄ1.

በዞኑ ውስጥ ባሉት ወረዳዎች የሚኖረው ማህበረሰብ አጠቃላይ ግንኙነቱ እንዴት ነው? በቆላውና በደጋው አካባቢ የሚኖረው ህረተሰብ የአኗኗር፣የባህል፤ ወዘተ. አንድነቱንና ልዩነቱን እንዴት መግለጽ ይቻላል?

መልስ፤.

ኧኧ... እሽ እንግዲህ ሰሜን ወሎ ዞን 13 ወረዳዎች አሏት!! ኧ... 13ቱ ወረዳዎች በበዓል አከባበር፤በሠርግ፤ በለቅሶም፤ ኧ... የተገናኘ ሁኔታ ነው ያላቸው፡፡ተመሳሳይ ሁኔታ አላቸው፡፡እና በዚህ ዓይነት ኸጥንት ጀምሮ የመጣ ነው፡፡አሁንም በዚህ በኩል ያመጣው ለውጥ የለም፡፡ኧ...ጥንት አንደነበረው አይነት በአሉን በህብረት እያከበረ ይገኛል፡፡

ጥያቄ2.

ምናልባት ይህንን ሀሳብ ሳነሳው በዞኑ ውስጥ ሁለት የአየር ጠባይ አካባቢዎች እንዳሉ ነው ባለሙያዎች የሚናገሩት፡፡በቆላማው አካባቢ የሚኖር የህ/ሰብ ክፍልና በደጋማው አካባቢ የሚኖር የህ/ሰብ ክፍል አለ፡፡በቆላማው አካባቢ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል በዚህ በምስራቅ በኩል ከአፋር ግንኙነት አላቸው፡፡እርስ በእርስ የመጋጨት፣የመዋጋት፣ከብት ማርኮ የመምጣት፣የመማረክ፤ እንዲህ እንዲህ ዓይነት ነገሮች አሉና ነው...

ጥያቄ3.

የቆላማው አካባቢና የደጋማው አካባቢ ማህበረሰብ እንዴት ነው ያላቸው ግንኙነት?

መልስ.

አንተ በጥያቄህ ላይ እንዳነሳኸው ቆላማው አካባቢ የሚባለው ከዶሮ ግብር ጀምሮ ወደ ታይ ነው።በመርሳም ይዞ ወደ ታይ ነው። ደጋማው የሚባለው ደግሞ ኸዚህ አንስቶ/ከወልዲያ ከተማ አንስቶ ወደ ላይ ያለውን በእጃቸው በማመልከት/ያለው ነው።አሁን ግጭት አለ የሚባለው በደጋማው ቦታ ያለው ሳይሆን፣በቆላማ ቦታ ያሉት እነ ጮራ-ሰዶማ፣እነ ለገ-እዋ፤ የሚባሉት እነ ጉራ-ወርቁ፤ እሚባሉት ይኸ ይኸ ያለው ህዝብ፤ ዘላንነት ስለሚያጠቃው፣ወደ ታይ ካለው ካፋሩ ጋር ይኸ ጉልበት ሲያገኝ አፋሩን ዘርፎ ይመጣል ፤እነዚያ ደግሞ ጉልበት ሲያገኙ መጥተው እዚህ ዘርፈው ይሄዳሉ፤በመዘራረፍ እስካሁን ድረስ ቆይተዋል።አሁን ግን እንደ ጥንቱ ጎልቶ እሚታይ አይደለም፤እየቀነሰ፣እየቀረ፤ መጥቷል።

ጥያቄ3.

አሁን በጭፈራ ላይ አንድ ግጥም ሰማሁ፤

‹‹የታለ ግመሉ የታለ ሀርሞው

በረጅም ምንሽር የተወረረው››

ይላል ጭፈራው ላይ፤አሁን ይህ የሚያሳየው እንግዲህ፤ በሁለቱ አካባቢ ግጭት እንደነበረ ነው።የመቀማትና የመቀማማት።ህዶ የመቀማት ደግሞ ብድሩን የመመለስ፡….. አዎ!እንግዲህ፤ ይኸኛው ህዶ፣አፋሩ ብዙ ከብት አለው።ይኸኛው ግን እስከዚህም ነው።ብዙውን ጊዜ፤ሃብት ፍለጋ፤ ነው ንብረት ፍለጋ፤ እሚሆነው እንጂ የሌላ አይደለም፣ይኸ የላይኛው ልበ-ሙሉ ነው። እንደ ፈለገ ነው እሚሆነው።እና በዚህ ዓይነት ካልሆነ በስተቀር እስተዚህም ነው፤አሁን ግን፤ እየቀነሰ መጥቷል።

ጥያቄ4.

መንግስት ግን በሚያደርጉት ግጭት ላይ ጣልቃ ይገባል፤አደለ?

መልስ.

አዎ፤ አንዳንድ ዘረፋ ሲደረግ፤መንግስት እመካከል ላይ ይገባና፤ እመሀል ላይ ሆኖ የታችኛውንም ያላይኛውንም ጠርቶ፤ ያስታርቃል። <u>ለምሳሌ</u>፡-እኛ አንድ ጊዜ በ64 ዓ.ም የጮራ ሰዶማ ህዝብ ወርዶ፤ ኸታይ ወርዶ ፤አፋሩን ገሎ፣ንብረት ዘርፎ መጥቶ ነበር።በዛን ጊዜ፤ እኔ፤ እዚህ የጉባላፍቶ ፖሊስ አዛዥ ነበርኩ።የየጁ አውራጃ አስተዳደር ገዥ፣ የራያ ቆቦ ገዥ፣የጎባላፍቶ ወረዳ ገዥ፣የጎባላፍቶ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ፣የቆቦ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ፤ ሆነን ጎብዬ ላይ አስራ አምስት ቀናት ተቀምጠን፣ሁሉንም አምጥተን፣እንዲስማሙ አድርገናል።ነገር ግን፤ በዚህ ጊዜ፤ አንድ ፍሰሃ እንግዳ፤ እሚባል ወረዳ ገገር ነበር።ኸጮራ-ሰዶማ ህደው

የዘረፉትን ሠዎች ያልሞቱትን ሞቱ ብሎ ሪፖርት አቅርቦ፤ እንደገና፤ እኔ ያንን ጉዳይ ተከታትዬ እነዚህ ህደው የዘረፉት፣የገደሉት ሠዎች ኧ...ሀራ ውስጥ፤ ውለጋ፣እምትባል ቀበሌ አለች፤እዚያ 23ቱ ሰዎች ተገኝተው፤እነዚያን 23 ሰዎች ከብቤ ይገፍ፤ ወስጀ አስረክቤአለሁ።እና ከዚያ በኋላ በዛው አስማምተናቸው ለሞተው ካሳ ተከፍሎ፣የተዘረፈውም ንብረት እንዲመለስ ተደርጎ ያደረግንበት ጊዜም አለ።

ጥያቄ5.

ቀደም ባለው ዘመን ከአዜ ኃ/ሥላሴ ጀምሮ በዚህ በዞኑ ባሉት አንድዳንድ ወረዳዎች ውስጥ ከመንግስት ሹማምንት ጋር ያለመስማማት፣እንደነበረ ይነገራል።ለምሳሌ ከመንግስት ጋር በሚመለከት በማይጨው ጦርነት ጊዜ የራያ ህዝብ ከንጉሱ ጋር ሳይሆን፣በሌላ ወገን ሆኖ ወግቶኛል ይላሉ ብለው እንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ። ከዛም በኋላ ከሰቆጣ ሰዎች ጋርም እንደዚሁ የራያ ህዝብ ግጭት እንደነበረው እንደዚሁ የሚናገሩ ሰወች አሉ።እንዳንድ ጊዜ እንደምሰማው፤ ለምሳሌ፦ ቆቦ 3 ጊዜ ተቃጥላለች ይባላል። በዚያን ጊዜ የነበረ ተጫዋች ታየ ለገሰ የሚባል፦

‹‹መልካም ተርፎ ሊቀር ክፉ ተናግሬ
ተቃጠለ መሰል ሸተተኝ አገሬ››

የሚል ግጥም ገጥሞ እንደነበር ከሰበሰብኳቸው አግኝቻለሁ።እስቲ፤ስለዚህ የሚስታውሱትን ያጫውቱኝ!

መልስ፦

ኧ...እንግዲህ፣የቆቦ ህዝብ፣የራያ ህዝብ፣ከመንግስት ጋር ጦርነት ያደረገበት ጊዜ የለም። ኧ...ለምሳሌ፤ በ35 ዓ.ም ወያኔ ራሱን ችሎ ከመንግስት ጋር ተዋግቶ ስለነበረ ራያም ድንበርተኛ በመሆኑ፤

ጥያቄ.የትኛው ወያኔ ነው? የትግራዩ?

መልስ.አዎ፤

ጥያቄ.ቀዳማዊ ወያኔ እሚባለው እኮ እዚህ የጁ ነበረ ይባላል? ኧ... እኔ እሱን አላውቅም፤እኔ እንደምሰማው ተመሰረተ የሚባለው ትግራይ እንጂ የጁ ላይ አልተመሰረተም።

ጥያቄ7.

የጁ፤ እዚህ ካንዱ ጎጥ ወደ ሌላው ጎጥ ህደው ሊገጥሙ ሲሉ፤በጎበዝ አለቃ እየተመሩ ጉተናቸውን እንትን ብለው፤እነሱ ወያኔ ነበሩ እሚባሉት....

መልስ.

እሱ ሌላ ጉዳይ ነው፤አዎ! እሱ ‹‹የወፋ ሙጊያ›› ፤‹‹የወያኔ ውጊያ›› እየተባለ፡... በአላ ውሃ፣በጎቡ፣በቆቦ፣ በዚያ፣አይደለም፡፡ይኸ በ35ዓ.ም ከመንግስት ጋር ተዋጉ፤መንግስት ያለ ሀይሉን እነሱን በሚደመስስበት ጊዜ

የዛንለት እነዚህም አብረው ነበሩ፣በሚል መልክ በዋግ በኩል ማሞ ሀይሉ እሚባል፣የደጅ አዝማች ሀይሉ ከበደ ልጅ፤ ዋግሹም ገዥ ስለ ነበር፣እሱ መጥቶ ያንን አጠፋ ይባላል፡፡
ይኽ የተባለበት ምክንያት ፣ጣሊያን እዚህ በነበረ ጊዜ የራያን ህዝብ ይዞ ሀዶ ነው ጀኔራል ሀይሉ ከበደን ወግቷል የተባለው፡፡ ተገዶ ዘምቶ ስለነበር... እና ያነን ከዚያ ጋር አይይዞ ያወሩታል፤እሱ ደሞ ትክክል አይደለም፤ የራያ በዚያን ጊዜ የተቃጠለው፤...
እነ አሊ ጡሃ እሚባሉ ተጫዎቾች ነበሩ...ያን ለት ራያ ሲቃጠል
‹‹ጓዳ ጓዳ ብለህ ባመጣኸው እዳ
ዙብል እንጨት ስበር ቆቦም ውሃ ቅዳ››
ተብሎ የተገጠመው፤ በዚህና በዚህ ምክንያት ነው እንጂ፣ከመንግስት ጋር...አዝማቾቹ እነ ራስ አበበ አረጋይ፣ እነ ራስ አበበ ዳምጠው ይባሉ ነበሩ...ከመንግስት የመጡት....
ጥያቄ.
እነ አያሌው ብሩ መቼ ነው ወደ ራያ የዘመቱት....
እነ አያሌው ብሩ በ21 ዓ/ም ነው ደጃዝማች ተፈራ ይማም የሚባሉ የቆባ ባላባት ነበሩ... እሳቸው አንዳንድ ጊዜ ሲፈልጉ ወደ መንግስት ይሄዳሉ፤ ሳይፈልጉ ራያን ይዘው...አልገብርም ይላሉ፡፡ፈታውራሪ በዛ ጣዩ እሚባሉ ከላስታ ታዘው ይመጣሉ ወደ ራያ...ራያ ይመጡና በመቅደላ አካባቢ ሰፍረው፣ህዝቡን ልወር ነው የመጣሁት ይላሉ... አሁን ቁስ እምትባል ቦታ አለች፣ኸዚያች ሰፍረው እንዳሉ፣ኸገዳማት የተወሰነ መታያ፣እሚታረድ ከብት ፣እህል ውሃ እሚበላውን ይዘው....‹‹ጌታየ ሰው ኸታይ በረሀ ገብቷል፣አይገኝም፣...እናእባክዎ፤ወደአገረዎ ይመለሱ...››ሲሏቸው፤‹‹አይ...አቃጥለዋለሁኝ ብለው፤ ተሻግረው መቅድላ ላይ ቤት ማቃጠል ጀመሩ፤...
ጥያቄ.
መቅድላ የት ነው?
መቅድላ በቆቦ በላይ ያለው...ተኩለሽ መቅድላ ነው እሚባለው...እዚያ ሲጀምሩ፣ደጃዝማች ተፈራ ይማም ኸታይ ቆባን ይዞ መጥቶ ያን ሰውየ ይገላል...እሳቸውን ሲገል መንግስት ከበጌ ምድር ደጃዝማች አያሌው ብሩን አዘመተ፡፡....ደጃዝማች አያሌው ብሩ መጥተው መቅድላ ላይ እንደሰፈሩ...ሰውየው የለም፤ሀገር...ለምድነው የሚወረረው...ብለው ህዝቡ ሰላም ነው፤... ለመንግስት ይገብራል፤ ብለው በዚያ ተስማምተው፤ ... እዚያ እንዳሉ፤

ራስ ጉግሳ ወሌ፣በአንቸም በኩል፤ የበጌምድር ገዥ ነበሩ...፤ወደ መንግስት ሲጠሩ አልመጣም ስላሉ...፤ወደዚያ ዙረው ተመልሰው...ያን ትተው ተመልሰው...ሂደው እዚያ አንቺም ላይ ተዋጉ፤ ያው ራስ ጉግሳ ወሌ ሞቱ... እኔ ያን ጊዜ የአንድ አመት ልጅ ነበርኩ፤ሲነግሩን ታሩኩ ይኽ ነው...፤የንግስት ዘውዲቱ ባል የነበሩ ናቸው፣የጣይቱ ዘመድ ናቸው...።ታላቁ ራስ አሊ ጎንደርን አስተዳድረዋል። እንደውም አፄ ቴዎድሮስ የታላቁ ራስ አሊን ልጅ ተዋበችን አግብተው ይኖሩ ነበር። በኋላ ባለመግባባት፣ በአንዳንድ ምክንያት ሸፈቱ፣በራስ አሊ ላይ ተነሱ።ሲነሱ፤ራስ አሊ ጦርነት ገጠሙ። አልመቻቸው ሲል ‹‹ አይ፤ ይኽ የካሳ በትር ሳይሆን የእግዚአብሄር በትር ነው›› ብለው ማንም ይምጣ እሚባል ተራራ አለ ከዚያ ላይ ወጥተው‹‹እንግዲህ ማንም ይመጣ›› ብለው እዚያ ተቀመጡ ይባላል።

በአካባቢው ያሉ የባላባት ልጆች፣የጎበዝ አለቆች፤...እነዚህ ትልልቅ ሰዎች እሚባሉት በሰበሰብኳቸው ግጥሞች ውስጥ ስማቸው ተነስቶ አግኝቻለሁ..ለምሳሌ ስለአባተ ሀይሉ አግኝቻለሁ፤ስለደጃዝማች ጉበና አግኝቻለሁ...እነዚህ ትልልቅ ሰዎች ስለሚባሉት... ስለታሪካቸው፤ስለማንነታቸው፤ ከማህበረሰ ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት...ጥቂት ያጫውቱኝ...

መልስ.

እንግዲህ...ታሪክን ያልተደረገውን ተደረገ የተደረገው አልተደረገም ብሎ አጣሞ ከመናገር እውነተኛው ቢነገር ለተተኪው ትውልድም ጥሩማስረጃ ይሆናል።ለምሳሌ አባተ ሀይሉ እርግጥ የሀይሉ መሸሻ ልጅ ነው፤ ባላባት ነው። የየጁም ወረሴክ ነው፤ቆባም ተወላጅ ነው። እና በቆባ ትውልዱ ከእኔ ጋር ዝምድና አለው። አባተ ሀይሉ ጀግና ነበር። ልበ ሙሉ ነበር ። ግን የልጅ ጀግንነት ሆኖ ወደ መጨረሻው አላምር አለ እንጂ፤... ነገሩ የተነሳው ፣(በመሀል ላይ የዛንለትም እኔ እዚሁ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ነኝ) አባተ ሀይሉና ጎርፉ ተሰማ የአንድ ሰው ልጆች መሬት ወርሰዋል፤የትልቋንና የትንሿን።....ሁለቱ ወርሰው በፍ/ቤት ይከራከራሉ። ሲከራከሩ ጎርፍ ተሰማ ገንዘብ መቼም ህግ ያጠፋል ስክተው ካልያዙት ቀኛማች አባተ ሀይሉ ቆቦ ላይ እንዳለ፤ጎርፍ ዱርየ ገዝቶ አስደበደበው።ደጃዝማች ያረጋል የእህቱ ባል መጥተው እዚህ ወልዲያ ሆስፒታል አሳክመው አዳኑት። ከዳነ በኋላ፣ያው ጉልበትም ስላለ፣ደፋርም ስለሆነ መርሳ ላይ ጎርፉን ገደለ።ገሎ ሸፈተ፤ መንግስትም እሱን ለመያዝ ወታደር አዘመተ። የየጁ ህዝብ ወገኑን ወዳጅ፣ወገኑን አክባሪ ህዝብ ነው።ወታደሩን ባንድ ጎን አድርጎ እሱን ባንድ ጎን እያደረገ፣የለም ተብሎ ወታደሩ ተመልሶ ሄደ ።ተመልሶ ሄደ፣በኋላ ከመንግስት ይቅርታ ጠየቀ፤ይቅርታ ተደረገለት። ተደርጎለት እንዳለ በ61 ዓ/ም በሚያዚያ ወር ሂዶ እዚያ በትራክተር ሲያሳርስ ገበሬው የኛ መሬት ነው አትረስ ብሎ ተቃወመው፣ሲቃወም ገበሬዎቹ መጥተው ለኛ አቤቱታ አቀረቡ።

አሁን ሂዳችሁ ገበሬዎቹን ይዛችሁ ኑ ብለን ፖ/ሊስ ላክን።የተላከው ፖ/ሊስ ራስ ጀበናን (አስፋው ፈንታቢል ይባላል) ይዘው ሲመጡ መንገድ ላይ ሲደርሱ መብራት ያጠፋሉ። መብራት ሲያጠፉ ሾልኮ ይጠፋል፤ እሱ።ትውልዱ ጀበና አንጎት እሚባል አገር ነው....ከህዝቡ ጋር ሆኖ ቀድሞ ወያኔ ያልከው የእሱ አዋጊ የነበረ ነው.....የባላባት ልጅ አግብቶ ኖረ ነው እሚባለው። እሱ ጠፋ።....አባተ የዛን ጊዜ ደጃዝማች ከበደ አሊ ወሌ መንግስት ይቅርታ ስላደረገለት ለዚያ ግብጥ የደስ ደስ ጠርተውት እዚያ ነው ያለው ሀይቅ፤ አሁን፤ ሰኞ ቀን ነው፤ እዚያ እንዳለ ይደውሉለታል። እንዲህ አድርጎበ አገር እርሻ እንዳናርስ ከለከለን ብለው ሲደውሉለት እሱ ጋር የነበሩ ሽፍቶች ነበሩ ወደ ሰላላ የሚሆኑ ...እነሱን ይዞ መጥቶ ....የዚያን ጊዜ የዚህ አውራጃ ገዥር ደጃዝማች ዘውዴ ብሩ ይባሉ ነበረ።ሂዶ እሳቸው ሲገባ....‹‹ምንድን ነው?››...እንዲህ እንዲህ ብየ መጣሁ።... ወታደር እንልካለን፤አንተ እንዳትሄድ ሲሉት ዝም ብሎ ሄደ ።ሂዶ እዚያ እርሻ ላይ እንዳለ፣ማክሰኞ ቀን ነው ይደርሳል። ተኩስ ይከፈታል፤ገበሬው ጥሎ ይሸሻል ጥሎ ሲሸሽ የገበሬውን ኹከት ሰብስቦ ዶሮ ግብር ይመጣና ዶሮ ግብር አንድ በሬ አንድ ላም ሲያርድ‹‹አይ ላሚንስ አረዷት፣በሬው ግን የሚያዚያ ገበሬ ስለሆነ ለምን ይታረዳል ሲል›› ያን አሳደዱት ይላሉ። በማግስቱ በ29 ረቡዕ ሚያዚያ 29 ቀን ረቡዕ አውራጃ ገዥው ጋር አብረን ኾደን ፣እዚያ ኾደን፣ የፊት አውራሪ አስፋው ብርሌ ልጅ ምክትል ወረዳ ገዥር ነበር፣እሱም ከዚያ አለ፤ ሀደን እዩ ብለን ላክነ። ከብቶቹ ይመለሱ ጉዳዩን እንየው ብለው ላኩ።ኾዚያው ዋልነ፣ማታ መጣነ። በ30ሀሙስ ሄደን፣ እዛ ሀሙስ ህደን፣በመነጋጋር ላይ እንዳለን፣እሱ አባኮስትር ቀብር እምትባል ቦታ አለች ጎለናት፤እዛች ላይ የታረዱትን ከብቶች ቆዳ አንጥፈው ዙሪያዋን ካብናት እያለ እዛ በመነጋገር ላይ እያለን‹‹ወያ አንባ›› ይባላል ወደ ላይ በኩል ከዚያ ላይ አንድ ሰው ዘልቆ››የተዘረፈው ከብት ተነድቶ ወልዲያ ገባላችሁ፤የጎበዝ ያለህ ብሎ››አንድ ጥይት ተኮሰ... ከዚያ በኋላ ላስቴ የሚባለው ህዝብ እንዳለ ስብሰባ ብሎ መጣ ፣እኛ ጋ ደረሰ።ሲደርስ፣ደጃዝማች ዘውዴ ብሩ ህዱና አነጋግሯቸው አሉ።ሄድኩኝ እኔ ራሴ ህጂ ምንድን ነው? ስንላቸው ንብረታችን ተዘርፎ ሄደ፣ንብረታችንን አስመልሱልን፣እሱንም እኛንም ኾመንግስት አድርሱን አሉ።ይኸን በመነጋገር ላይ እንዳለን ተኩስ ተከፈተ፤ ተኩሱ ተከፈተ። ህዝቡን ዙሪያውን እየዘለለ መጣ፤በወዲያ ማዶ ‹‹ኪሎ ቆጡ›› እሚባል አለ፣በወዲህ‹‹ ቦየ አንባ›› ዙሪያውን እየከበበ መጣ።ከዚያ በኋላ፤ አባተ ያችን በሩን ለቆ ወጥቶ ሄደ።እኛም ከደጅዝማች ዘውዴ ብሩ ጋር በመኪና ላዩን መጥተን እነዚህ ከሹንቀሩ በር ላይ ቆመን ብዙ ወታደር... ነበር። እንድንከላከልም ጠይቀናቸው ነበር አውራጃ ገዥው‹‹...የህዝብ ንብረት እኮ ዘርፎ ነው ለምንድነው ትብብር የሚደረገው ብለው ከለከሉ። ከዚያ በኋላ እዚያችው ከሸንቀሩ ድንጋይ

በታይ ከድንጋው ላይ ገለው፣የዚያን ለት የሞቱት እሱ ጋራ 14 ሰዎች ናቸው።14 ሰዎች ተገደሉ። እሱን ገለው ወደታይ ወረዱ።

ህዱና እታይ ከተማም ላይ ዘርፍ እንዳይካሄድ አረጋጉ አሉን። ሄድነ....እስቲ የሞተባችሁ ካለ፣የቆሰለም ካለንገሩን ለመንግስት ሪፖርት እንድናገር ስንላቸው‹‹....እንደው እምብም፤እምብም፤ዘራፍ፣....የሞተም የቆሰለም የለምብንም ብለው...›› እንደው የሞተውንም የቆሰለውንም እንዴት አርገው እንደያዙት ይገርምሀል...፤እንዲያ አርገው ተነስተው ሄዱ።ያው እሱም ሚያዚያ 30/በ1961 ዓ/ም ሞተ።ያው ግንቦት አንድ ቀን ስሪንቃ ሂደን ቀብረን።

ጥያቄ.

የደጃዝማች ጎበናስ እንዴት ነው?

ደጃዝማች ጎበና አመዴ እንግዲህ እኔም አርበኛ ነበሩ ነው እሚባለው፣ይኽ የአርበኝነት ታሪካቸውን ብዙ ሰው አያውቀውም።እንዴት እንደሆነ እንጂ... እንግዲህ እሳቸው አምስት አመት ሙሉ አርበኛ ናቸው። የጁ ያለውን ጣሊያን ሁል ጊዜ ሲያስጨንቁ፤ በዚህ በኩላ ማሶ...በደጋው በኩል ተዋግተዋል።...ነፃነት ሲመለስ ግን፤መንግስት እንግዲህ

እንደ አገልግሎታቸው ዋጋ የከፈላቸው አይመስለኝም። ከዚያ በኋላ ምክንያቱን አላውቀውም፤ወደ እርሻ ገቡ ። መንግስት ብዙ መሬት ሰጣቸው።.. ጃርሳም ብዙ ጋሻ መሬት አገኙ። ጃርሳ....ጥቁር ውሃን ሻገር ብሎ አቡነ-አረጋዊ አካባቢ ነው ወደ ስንት ጋሻ መሬት ነበር፣ እዚያ ያሳርሳሉ፣ ገበሬ ሆኑ፤ ከመንግስት ስራ ይልቅ ግብርናው ጥቅማቸው ስላመዘነባቸው፤ ወደዚያ ገቡ። እንደገናም ወደላይ ሄዱ። ራያ ከመንግስት ሁለት ጋሻ መሬት አስፈቅደው ያን ጋሻ መሬት ሲያስፋፉ፤ሲያስፋፉ፤የህዝብን እየጨመሩ ...ሄዱ። ምክንያቱም፤ ይኽን ለማወቅ የቻልኩት አገሬ ስለሆነ ነው። ሰዎችም ስለሚነግሩኝ፤በአካባቢው ሆኜ ስለማውቅ ነው። ነቀሏቸው...ህዝቡ ለመንግስት አቤቱታ አቀረበ፤ ክስ መሰረተ። ተከራከሩ፤ ማስረጃ ተሰማ ፣የህዝቡን ከራሳቸው ውጭ አምስት ጋሻ መሬት ይዘው መገናኘታቸው ታወቀ። እንደላቁ ውሳኔ ተሰጠ። ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔው እንዳይፈፀም ከዳኞች ጋር የሳቸው ግንኙነት አይሎ እንቢ አለ ።ከዛ በኋላ ህዳር 13 ቀን ከዛ እህል ሲያስወቁ ፣ያው የራያ ህዝብ ከቦ 12 አሽከሮቻቸው ጋር ገደሏቸው።እንዲሁም አሽከሮቻቸው አብረዋቸው አርበኛ የነበሩ ጀግና ጀግና ነበሩ ‹‹ኧ ረ ጌታየ ይኸ ህዝብ አልለቀቀንምኮ እኛም እንደው አንድ...ቤት እንኳ ብንዘጋ ምናለ ብለው››.... እሳቸው፤ በተደጋገመ ሁኔታ ከንጉሱ ፊት ቀርቤ ተወቅሻለሁ። ሁለተኛ ቀርቤ ልወቀስ አልችልም ብለው እንደሞቱ እዛ የነበሩ ሰዎች አጫውተውናል።የአሟሟታቸው ሁኔታ ዋናው ታሪክ ይኽ ነው።...1962 ዓ/ም ነው እሳቸው የሞቱት...

‹‹ገበና በሞተ ባመቱ
የሰው ሁሉ ኮርትም ሆነ ራቱ››

የሚለው የተገጠመው የእሳቸውን ሞት ተከትሎ በታየው የ1965/66 ዓ/ም ርሀብ ጊዜ ነው...፡፡ከ1966 ዓ/ም....አቢዮት ሲፈነዳ ከነበረው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተገጠሙ ግጥሞችን ሰብስቢያለሁ፡፡

ለምሳሌ፤

ብር አምጣ ሲሉኝ ብራንም አውጥቼ
ልጅም አምጣ ሲሉኝ ልጄንም ሰጥቼ
ቅቤ አምጣ ይሉኛል ቅቤ የት ተገኝቶ
በአድሀሪው መንግስት ተቀልጦ ተበልቶ

እናንተ ተማሮይ በጣም ቀበጣችሁ
ወይፈን ያለበሬ እየጠመዳችሁ
ጎላ መመለሻው ቅጡ እንይጠፋችሁ

የሚሉ ግጥሞችን አግኝቻለሁ፡፡....እና፤ ያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታ የሚገልጹ እንደነዚህ አይነት ግጥሞች የሚያስታውሷቸው ካሉ...

የ66 ዓ/ም እንቅስቃሴ አጀማመሩ መልካም ነበር፡፡ መነሻው መሬት ላራሹ ይሁን ነው፤መሬት ላራሹ ይሁን የተባለበት ምክንያትም ትልቁ መነሻ የሆነው የጁ ነው፡፡የየጁ ግብር በ3ት ደረጃ የተከፈለ ነበር፡፡አለ. ዘማች፤ ግብር ፈራሽ፤ የግብር መሬት፤ እየተባለ ይጠራ ነበር‹‹አለ. ዘማች›› ከመንግስት ጋር እየዘመተ መሬቱ የራሱ የሆነ፣በዘመቻ በውለታ የተያዘው ማለት ነው፡፡‹‹ግብር ፈራሽ›› ደሞ ወደ ዘመቻ ታገዘ አልሄድ ሲል፤ያ ግብር ፈራሽ የተባለው ፣ያ ይቀማና...ሌላ ይሠጣል፡፡‹‹ የግብር መሬት›› የሚባለው ደሞ ራሱ ባላባቱ እዚያው ሆኖ ራሱ እሚከታተል ስለሆነ እና ይኸ ይኸ ስለነበር፣ይኸ እንቅስቃሴ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን፣በህ/ሰቡ ልዩ ልዩ ችግር ነበር አ.... እንደውም በ62 ዓ/ም ተሰማ ክቤ እሚባል እዚህ ጃርሳ‹‹ራስ ተሰማ›› ተብሎ ህዝቡን ወደ መንግስት እንዳትሄዱ ብሎ ...እኛው ከዚህ እንፈርድልሀለን፣ መሬትክንም እንሰጥሀለን፤ የጎደለውን እናሟላልሀለን፣ እና ምንታረግ ነው መንግስት እምትሄደው? ገንዘብ ልታወጣ አደለምይ?የመሬቱን ሁኔታ እምናሳውቀው እኛ እንዳትሄድ›› ብሎ ሰኔ ጀምሮ በ61ዓ.ም. ተሰኔ እስተ መስከረም፤ ህዝቡ ወደ መንግስት መምጣቱን እንዲያቆም አረገ፡፡ አሁንም አውራጃ ገኘው ደጃዝማች ዘውዴ ብሩ ነበሩ፡፡በመስከረም 12 ቀን ወደ ገጠሩ ለመዝመት ዝግጅት ተደረገ፡፡ ዝግጅት ሲደረግ፤ ህዝቡ

አቅሙን አወቀና፤ ገና እዚህ እንቅስቃሴ ሲደረግ፣ እንጨቱን መልጦ፤ ነጭ አድርጎ መጣ።ህዝቡ መጣ እንቀበለው ተባለ። ‹‹እህ››ሲባል አጥፍተናል፤ አጥፊ ይቀጣ፤ ያላጠፋው እንዴት ብሎ ከአጥፊ ጋር ይቀጣል። የነበሩት እባክዎ ጌታየ ተባለ። ሽማግሌ አለ የዚያን ጊዜ ሀሳብ እሚያቀርብ። የነበሩት ባለ ሰልጣኞችም ሀሳብ ይቀበላሉ፤ እሽ ዙሪያ ተባለ።በዚያው ቀረ ያ እንጨትም እዚህ መጥቶ መስቀል ደመራ ሆነ።

ይኽ ሁሉ ቁስል ስላለ እንቅስቃሴው ጥሩ እንቅስቃሴ ነበረ።እየዋለ እያደረ ግን መልኩን እየለወጠ መጣ እንጂ ሁኔታው ይኽ ነበር በዚያን ጊዜ.....ግጥሞች ቀድሞ አንተ በገጠምከው ግጥም‹‹ ሙክት...ሳይሆን አየነው እሚባል አልቃሽ ነበር። እሱ

‹‹ አካላቴ ደርጉ ሞናናየ ደርጉ
እርሻ አንጡ አለነ እርሻንም ሰጠነ
ልጅም አንጡ አለነ ልጅንም ሰጠነ
ቅቤ አንጡ ይለናል ቅቤ የት ተገኝቶ
በሀይሉ ስላሴ በዚያ አድሀሪ ንጉስ ተቀልጦ ተበልቶ››

ብሎ የገጠመው እሱ ነው።

ከዚህ አያይዞ....

‹‹ የሚባለው ክትፎ የሚጠጣው ውስኪ
ከቶ ለምኑ ነው መለበሱ ካኪ
‹‹ እሾህ ብቻ ሆነ እግሬን ብዳብሰው
እንዴት መረመጃ መሄጃ ያጣል ሰው
‹‹ እንግዲህ ወላጆች ለየብቻ እደሩ
ለየብቻ ዋሉ
ፊት የተወለዱት ካላገለገሉ››

ብሎ የገጠመው እሱ ነው። እንደውም በገጠመባቸው ለቅሶ ሁሉ በዚህ ነገር ተይዞ ታስሮ መጣ ።ይኽን ብለሀል ተብሎ። ለምንድን ነው እንዲህ ያለኸው ተብሎ ሲጠየቅ‹‹..... እኔ እንጃ ‹መልበሱን ካኪ ያልሁት› ጥላት ጥሎብኝ ነው። ...‹መራመጃ ያጣል ያለሁት እግሬ አብጧል ድንጋዩም እሾሁም ይወጋኛል ‹...ለየብቻ እደሩ...› ያልሆት አልታዘዝ አለ የዛሬ ልጅ ብየ በማሰብ ነው› በማለቱ አይተው ይለቁታል።...በሌላ ጊዜ....ስንጠጣ አውቀው ነበርና ‹አባ አየነው፤ ና እስቲ› ብየው እስቲ እንደው ጠላ ጠጣ፣ግጥምም ግጠም ብየ ስጠይቀው፤

‹‹ ተይገፍ ነበረ በትንሽ ምላስ
መርምሮ ለቀቀኝ ያውራጃው ፖሊስ››

ብሎ ገጠመ።

ጥያቄ

የ1965/66 እና 1976/77 የርሀብ አመታትን መቼም ያስታውሳሉና ሁኔታው እንዴት ነበር፤ ትንሽ ያጫውቱኝ፤

እንግዲህ በዛን ጊዜ እህል አልጠፋም /አልቸገረም/ ንፋስ ነው፤ህዝቡን የፈጀው፡፡... እህል የጠፋው ወደታይ ነው፤ ወደቆላው ነው፡፡...ከመንገድ በላይ ምርት አለው፡፡ይኽ ደጋማው አለው፡፡...ያንለት ይኽ ደጋው ይድራል... ንፋስ ነው ያልሁህ፣...ጊዜ ያመጣው በሽታ ነው እንጂ የርሀቡ ብቻ አደለም፡፡

ከሀይለስላሴም እርዳታው አልተቋረጠም፡፡ ይሰጥ ነበር፤ በብዛት፤ በጣም ይሠጥ ነበር፡፡ በ65 በ66 ፡፡ከፍተኛ እርዳታ እርብርብ ነበር..... እንደውም ህዝቡ ጠግቦ ብዙ ነገር ያደረገ ነበር ፡፡የዛን ለት የርሀቡ ጉዳይ በታችኛው በኩል በሽታው ጭምር ነው አንጂ ርሀቡ አደለም የፈጀው ፡፡እየበላ እኮ ነው እሚሞተው...፡፡ለምሳሌ፤በዚያን ጊዜ እኔ

አቶ ከበደ ነጋሽ እሚባሉ ጓደኛ ነበሩኝ፡፡ ለእሳቸው ጉዳይ ከብት ልንገዛ ገብተን አንዲት መሲና ላም...ሰውነቷ የሞላ ...በ42 ብር ገዝተን መውሰዳችንን አስታውሳለሁ፡፡

አንድ ጣሳ በቆሎ 20 ሳንቲም፤ ጤፍ 40 ሳንቲም፤ ገብስ 30 ሳንቲም፤ ነው፡፡....እህል ሞልቷል...

ድካሙ ዋጋ ያለው ይሁን!

እሽ! አሜን!አሜን!

<u>የአምሳ አለቃ መላኩ ተገኝ አጭር የህይወት ታሪክ</u>

እሽ! የተወለድኩት በ19 መቶ 21 ዓ/ም ነው፡፡ በላስታ አውራጃ ደብረ ዘመዳ ገዳም ትበላለች የተወለድኩበት ቦታ፣እግዲህ ከዛ ተወልጄ ለተወሰኑ ለአስር አመታት የቤት ክህነት ትምህርት ተከታትዬ የድቁና ማዕረግ ደርሻ ነበር፡፡ከዛ በኋላ ነው እንግዲህ ወደሌላ የመንግስት ስራ የሄድኩት ፡፡.....እንግዲህ መጀመሪያ በላስታ አውራጃ የቡግና ወረዳ ሊ/ካህናት ፀሀፊ ሆኜ አምስት አመት ሰርቻለሁ፡፡ከዚያ በኋላ በ45 ዓ/ም በፖሊነስት ስራም ተቀጥሬ የትምህርት ኮርሴን ከጨረስኩ በኋላ፤ በላስታ አውራጃ፤ ከዛ ደሞ ኮረም፤ ከኮረም ውሳ፤ ከሀውሳ ሀብሩ ወረዳ፣ከሀብሩ ወረዳ፣ጉባላፍቶ... እነዚህ ቦታዎች ተዘዋውሬ ሰርቻለሁኝ፡፡ ከዛ በኋላ በ71 ዓ/ም ጡረታ ወጥቼ ..እዚሁ በየጁ አውራጃ፤ ወልዲያ ከተማ እኖራለሁ፡፡.....በማ/ሰቡ ዘንድ የማስታረቅ ችሎታ አለኝ ሰውን የማስማማት እኔ ደሞ ሰውን ማስታረቅ ችሎታ አለኝ፡፡ ሰውን ማስማማት ደስ ይለኛል፡፡በሌላ በኩልም፤ምክሬን እሚቀበል ሰው ካገኘሁ በሁሉም ዘንድ የህግ አገልግሎት ድጋፍ እሰጣለሁ፣ምክር እለግሳለሁ፡፡ እንደው በተለይ ባልና ሚስት ማጋባት ደሞ ትልቁ ሀብቴ ነው፡፡/ሁለታችንም ተሳሳቅን/.....በጣም እሚገርምህ ነገር ቢኖር

ቢያንስ ወደ መቶ የጋብቻ ውል በኔ በቤቱ ይገኛል።...የውል አባት እየሆንኩኝ.... እንዳው እድሌ ጥሩ ነው.../ሁለታችንም ተሳስቀን/

ቤተሰብ...ልጆች ...እግዚአብሄር ምስጋና ይግባው ይችን ባለቤቴን በ60 ዓ/ም ሚያዚያ 27 ቀን ተጋባን፤ ሳገባት ስድስተኛ ክፍል ነበረች። ትምህርቷን አስጨርሼ እሷም መ/ር ናት፤ ልጆቼም ስድስት ልጆች አሉ። ከስድስቱ ልጆች አንዱ በድግሪ ተመርቆ ቆቦ ነው፤ የሙያ አስተማሪ ነው።አንዷም አ.አ ነርስ ናት፤አንዷ ይች ውጭ ሀዳ ነበር አሁን መጣች፤አንድ ወንድ ልጅ ነው.....አምስተኛው እንደዚሁ በድግሪ ተመርቆ ናዝሬት ነው ያለው ፣ስራ ይዟል። የመጨረሻም አሁን 12ኛ ክፍል ጨርሳ ለድግሪ አልፋ ሁለት አመት ከተማረች በኋላ በህመም ምክንያት መጥታ አሁን እዚህ ኮሌጅ መጥታ ትማራለች።
...ፈጣሪን አመሰግናለሁ! አንተንም በጣም አመሰግናለሁ!

1ኛ/ **<u>የአቶ አሊ መሀመድ/መርሳ/ቃለመጠይቅ</u>**

ጥያቄ.እስቲ ስለህይወት ታሪክዎ ትንሽ ያጫውቱኝ

የህይወት ታሪኬ መቼም እንግዲህ አባቴ ጎበዝ ሳለሁ፣እረኛ ሳለሁ ሞቱ። እናቴ በዚያ ቆቅኖ ገበያው ዳር ቦታ ነበረን እዛው ቤት ሰርተን መሸታ እየሸጠች እናቴ አሳደገችን፤ አሳድጋ እንደገና በአምሳ ስድስት ጥር 27 ቀን ሚስት አጋባችን ተዳርኩኝ እዚህ አልፈታሁም ያው የህግ ሚስቴ ናት። አስር ወለድን። ሰባት ሴት ወለድን ሶስት ወንድ አለን ፤ከሴቶቹ እዝጊሀር ሁለቱን ሲወስዳቸው አምስቱ አሉ። አምስት ሴት ሶስት ወንድ አሉ።እኛም ደግሞ ከዚያ አነስተኛ ከተጋባን ጀምረን ተፋትተንም አናውቅ፣ ተሸማግለንም አናውቅ፣ኑሯችንን በፍቅር ነው የጨርስነው ።

ጥያቄ. እርስዎ ለቤሰበዎ እርስዎ ብቻ ነወት?ለናትና ላባቴ?አዎ ወደ ዘጠኝ ዘልቀን ነበር ሞት ወስዷቸው ስምንተኛውና እኔ ነን ያለነው። እሱ ስምንተኛየ አለ። እና እኔ በኸር ነኝ፣ሁሉም አለቁ...

ጥያቄ. እሱ እንደርስዎ ግጥም ይችላል? ዘፈን ይችላል?አይችልም፤ የኔ የእዝጊሀር ስጦታ ነው፣ እያልነ፣ልጆቻችንም የተማሩም አሉ ፤ዳርነ ኳልነ፣ የልጅ ልጅም አይቻለሁ።...እና ኸዚያ አንስተን አትክልትና ፍራፍሬ ኸዚያ ያለንበት ቦታ መስኖ ነው ባለቤቴ ጋራ ስናለማ ሉተራን እሚባል ድርጅት እየመጣ ሲያየነ፣ሲያየነ፣በኋላ እንደገና 96 ዓ/ም የካቲት 29 ቀን የሴቶች ክብረባል አ.አበባ ህደነ እስተ ባለቤቴ ተሸልመን መጣን፤ በፍራፍሬ ምርት፤

በካዛባ፤... በዚያ መጥቶ ሲያየነ፤ አብረን ባለቤቴ ጋር እየሰራን አገኘነ፤ የሴቶች ክብርባል በሚከበርበት ጊዜ የካቲት 29 ቀን 96 ህዳነ ባለቤቴ ጋር ተሸልመን...

ጥያቄ. ግጥም መግጠም እንዴት ነው የለመዱት እርስዎ? ግጥም እምገጥመው እንደው ተፈጥሮ ነው። ከመቼ ጀምሮ ይመስለዎታል?ከልጅነቴ ጀምሮ ነው ግጥም እገጥማለሁ፤እጫወታለሁ፤ከልጅነቴ ጀምሮ፤ሰርግም ሲሆን፤አንዳንድ ነገር ሲሆን፣እርሻም ሳርስ ፤አረም ሳርም አንጎራጉር ነበር፤እዘፍን ነበር...።ሰርግ ላይ ሲዘፈን፤ሲቅራራ ያዳምጡ ነበር በደንብ አዎ የዛን ጊዜም አዳምጣለሁ፣ጨዋታ መጨፈር እወዳለሁ ከልጅነቴ ጀምሮ መጨፈር እወዳለሁ፤ዘፈን ያቀነቀኑ ነበር?አዎ ዘፈን አቀነቅናለሁ።በዛ ስል ያው እንደገና ደሞ ወደ ሌላ ስነ-ጡፍ፤እንዳው እንደጊዜው ጋር ወደ ስነ-ጥሁፍ ገባሁ አሁን በወረቀት አይፅፉም?አዎ በወረቀት አልጥፍም!

ጥያቄ. እንዴት አረገው ነው ታዲያ አሁን በጭንቅላተወ ፀፈው በጭንቅላትወ አርመው እንደገና መልሰው በተከታታይ የሚናገሩት

እንግዲህ ያነን ለምሳሌ መቼም ከተማው መርሳ ቅርባችን ነው እመጣለሁ እመጣለሁ እንግዲህ እቀማምሳለሁ ስቀማምስ እንግዲህ ይኽ ሁሉ ስነ-ጡሁፍ እሚመጣልኝ ሥጠጣ ነው።...

ጥያቄ. ሲጠጡ ይመጣል ሀሳቡ?ስጠጣ በቃ ሀሳብ ይመጣልኛል ዝምብየ ማውጣት ነው።ዝምብዬ ዛሬ የወጣሁትን በመንገድ ሰኽድ ያወጣሁትን ዌ ተጭቼ ደሞ አርሜ ትክክል መሆኑን አይቼ በጭንቅላቴ አስቀምጠዋለሁ፣ይቀመጣል፣በዛ አንዳንድ ነገር በሆነ ጊዜ አወጣዋለሁ ። መቼም በተፈለገ ጊዜ ያወጡታለወ?አወጣዋለሁ። አይረሱትም?አረሳውም፤‹‹የሚነገር ነው›› እንደዚህ አርጌ ነው እንጂ ስነ ጡሁፍ እንጂ እጅም አይጥፍም አላነብም ስሜን ብቻ ነው እኖፈርም ‹‹በጣት ነው ወይስ በዚህ‹‹በእስክርቢቶ ስሜን በደርግ ጊዜ መሰረት ትምህርት እሚባል ነበር። በዛን ጊዜ ተምሬ ነው ስሜን በእስክርቢቶ እምፅፍ እንጂ ከዛ በፊት አልጥፍም በጣቴ ቆየ እምፈረመው እንደዛ አርገን እንግዲህ አሁን ይኸው ጊዚያችንንም እንግዲህ ይኸው እንዲህ እያረግነ፣መቼም ጊዜየንም እድሜ የንም በፍቅር እየገፋሁ ነው።‹‹የቁርአን ትምህርት አለወት እንዴ?‹‹የለኝም።‹‹የመፀሐፍ ቅዱስ›› የለኝም ይኽ ክርስቲያንነኝ›› ማተባቸውንና ከማተባቸው ጋር ያለውን መስቀል ምልክት ያሳዩን። ክርስቲያን ነወት?አዎ ክርስቲያን ነኝ ፊት ሙስሊም ነበርኩ በ63 ዓ/ም ጥር 11 ቀን ክርስትና ተነሳሁ፤ከዛን ጊዜ ጀምሮ በክርስትና ነው እምኖረው ክርስትና ሲነሱ ለምን ስመዎን የክርስቲያን አላረጉም? ገብረማሪያም ተብዬ ተሰይሞልኝ ነበር።አዲያ አገራችን እንግዲህ ስለሆነ እንደወዲህ እስላም ታማራ ሆነን ያው ዝም ብለው ይጠሩኛል አባ አሊ

መሀመድ እያሉ ይጠሩኛል እንጂ ያው በክርስትና ስሜ ገብረማሪያም ነው ስጠቀም፣ ሽባህሩ ገብረማሪያም ነው ተብዬ የተጠመቁኩ አሁን እኮ ገፅታዎ ሲታዩ የቤተክርስቲያን ሀይማኖት አባት ቄስ ነው የሚመስሉ? አዎ ይሽ ሁለመናየ ጠጉሬ /ሚማቸውን እያሳዩ/ እመስላለሁ ይሉኛል

እንደገና አሁን መፅሐፍ ቅዱስ በቃላቸው እሚገቡ ሰዎች ቅኔ የሚቀኙት በቃል ነው እንዲደርሶ የእርስዎ በየት እሚለው ብዙ ነው

እሚሉት እሚገጥሙት ...አዎ(ይሽ እንግዲህ) እድያ ነው ሽላይኛው ጌታ ስነ ጡሑፍ እሚያወጣውንና ሚዚቀኛ እሚወጣው ከእግዚአብሄር እድያ ነው እንጂ....የእዝጊሀር እድያ ነው፡፡የእዝጊሀር ስጦታ ነው፡፡ ለጥቆ እማይገረመው የለም በቤተክርስቲያን አንዳንደዜ ይጋቡዙኛል፡፡ በት/ቤት እዛ ቁሜ ሳስተምር በጣም ያላንድ ወረቀት ሳነብ ህዝቡ ይገረማል፡፡ እና እድያ ነው፤ስጦታ ነው ይሉኛል፡፡‹‹ ከልጆቼዎ እንደርሶዎ እሚጫወት ...ልጅ አለ? አይ የለም....ልጆቹ የለም አይሞክሩም፡፡

እሽ ጋሼ አመሰግናለሁ

እስዎ ሲያጫውቱኝ ስጠጣ በደንብ እሚታየኝ ብለውኛል? እንዴት ነው? እንደው እንግዲህ ጨዋታም እጫወታለሁ ኻልቀመሽኩኝ ግን የለም ....መግጠምም አልችልም... እንደገና ደሞ ዜማም አላወጣ! ስጠጣ ነው እማወጣው ዜማውን ዜማውን እንግዲህ ባልጣጣም የገጠምሁትን ዜማ ግን እገጥማለሁ፡፡ የጠጣሁ ጊዜ ወደ ቤቴ ስሄድ ቢቀር ተኝቼ ብንን ስል አወጣለሁ፡፡...ያን እንግዲህ ዝምብየ...ጧት እንደገና ደሞ ማውጫ ማውጫውን እይዝና ደሞ በሁለተኛው ቀን ጠንቼ ሰኽድ ጥሩ እንደሆነ እይዛለሁ የተቀረ ጨምሬ ቀንሸ ጥሩውን ጥሩውን ኽቅንጭላቴ አስቀምጠዋለሁ..... እንደህ አርጌ ነው ስነ-ጡሁፍ እምገጥመው፡፡.....እና ስጠጣነው! እስታሁን ሲገጥሙት የኖሩትን አላስቀመጡትም?በካሴት ...?እእእ እየወልህ እንዲህ ነው፡፡ በካሴት ሉተራን እሚባል ድርጅት በየመድረኩ ቀርጦኛል፡፡.....እንግዲህ ካሴቱን ይዘውት ሀደዋል፡፡.... ኽይህ ኽወረዳችነ ባዛር ተደርጎ እዛ በዛሩ ላይ አያሌው መስፍን እሚባል ሙዚቀኛው መጥቶ እሱና እኔ በጎንና በጎን ሁነነ ተቀርጫለሁ፡፡ ተቀርጩ ግን ኽዛ ኋላ ኽገጠሙት ግጥም ካሴቱ ግን አለ ወረዳው ውስጥ አለ....ባህል አዳራሹ ሁለት ሶስት ጊዜ ስለተቀረጥኩ አለ ግን አላስተላለፉትም ....የባዘሩ ለታ ያንን ያነ አያሌው መስፍን በጎኔም አለ ጋዜጠኞቹ ሲቀርጡኝ ሲቀርጡኝ በኋላ ከማብቂያዋ ላይ፡-

ታሪከኛ ቢሞት ታሪከኛ መጣ

ጥበበኛ ቢሞት ጥበበኛ መጣ

ጋዜጠኛ ቢሞት ጋዜጠኛ መጣ

አለሚቱ ጥሩ መቼም ሰው አታጣ
አለሚቱ አለም አታላይ
በነዛም በነዛም አልነበርሽም ወይ
አንቺ የገባሽበት በሰላም አትወጪ
በወደሱ አደሬ ኮሶ ሳታሰጪ
አለሚቱ ሁልጊዜ ጎደሎ በዋንጫ እማምሳ
በጋን ይሰፈራል ያንድ ቀን መከራ

ይች እምንም ትባት ቀን ናት ያልኳትን አውጥተዋል።መርሳ ባዛር እንዴት ነው ርዕስ ... ሀሳብ ያበጃሉ እንዴ?እንደው ዝምብሎ እንግዲህ ባድ ነገር አነሳዋለሁ። ቀድሞ አሁን ሲገጥሙ ‹‹ሞት መረረ›› ብለው ይጀምራሉ። አዎ! እንግዲህ እንደዛ አርጌ ነው እም ኸድበት።ሞት ከሆነ በዛው በሞት ነው... ልማት ከሆነ ልማት ነው ሙዚቃ ከሆነ ሙዚቃ /ዘፈን ከሆነ ዘፈን/ነው.....

ስለልጅዎ የገጠሙትን እስቲ ይንገሩኝ?..../ልጃቸው ተጋይ ወታደር ስለነበረች ለሷ የገጠሙት ነው/

ሲተኩሱ ተኩስ ሲገሉ ግደል
ፈሪ ጋር አትሞክር ይሰድጎል ገደል
ይገርመኛል፤ይደንቀኛል እኔን ያሰብኩት እንደሆን
ሰው በገዛ አገሩ ስደተኛ መሆን
መላው ከፈረሰ ቃል ኪዳን ካልጠና
ራሱን እማይችል ምን አንገት አለና
አይተንም ሰምንተንም አናውቅም የሴት ልጅ ታጣቂ
የነካሳው እህት ሽጌ አየሁኝ አሊ
ቤሙ ሲፈነዳ ፤አይሮፕላ ሊጥል

መትረየስ ሲያጓራ በረሀ ጠላቂ
ብየ ነው ያልኳት

<u>የመ/ር አብርሃ ሽፈራው ቃለ-መጠይቅ/መርሳ/</u>

እስቲ ስለህይወት ታሪክህ ትንሽ አውጋኝ...?

የተወለድኩት ወልዲያ ከተማ ነው። የትውልድ ዘመኔ ሚያዚያ 27/1948 ዓ/ም ነው። አባቴ በህፃንነቴ ነው የሞቱት እናቴ ሌላ ባባቴ ሞት ምክንያት ሌላ ባል ስላገባች፤

መቻሬ እሚባል ገጠር ቦታ ነው ያደጉት በትም/ት ብዙም አልገፉሁ።የአንደኛ ደረጃ ትም/ቴን በመልካ ቆሌ ት/ቤት ተማርኩኝ ።ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እቴጌ ታይቱ ብጡልና መድሀኒአለም ት/ቤት ጨረስኩ። ከዛ መልካ ቆሌ ት/ቤት በመ/ርነት ተመድቤ ለትንሽ ጊዜ ከሰራሁ በኋላ ወደ ገጠር ሄጀ በር/መ/ርነት ከ1977-82 ዓ/ም ጉባላፍቶ ውስጥ ነበርኩኝ ከዛ እንደገና ከ1982 መልሰን ከተቋቋምነ በኋላ ሀብሩ ወረዳ ውስጥ በር/መ/ርነት ሰርቻለሁ። በዘመኑ በነበረው የትም/ት ስራ በክ/ሀገር በአውራጃ በወረዳ ምስጉን እየተባልን እንሸለም ነበር። እንግዲህ ..መሀይምነትን ለማጥፋት ታግለናል እና አሁንም ያለሁት በጡረታ አልተገለልኩም እዚሁ ሀብሩ ውስጥ ነኝ በጤና ምክንያት በድጋፍ ሰጭነት ተመድቤ በቆቆኖ ት/ቤት እየሰራሁ ነው ያለሁት

ቃል ግጥሙን እንዴት አርገህ አወቅከው?በዘመንህ ትሰበስብ/ታሰበስብ ነበር?

በመ/ርነት ዘመኔ ãእ...እስከ ስምንተኛ ክፍል የቋንቋ መ/ር ነበርኩ እና ከዛ ስለየጁ ባህል፤የለቅሶ ፤የደስታ፤የገበሬውን ግጥም እንዲያስባስቡ ልጆች ሳዛቸው በሚያሰባሰቡት ከዛ ላይ አይ ነበር እና በየጀ ã.....ከመታመሜ በፊት ስነ-ውሑፍ ነገር ጀምሬ ነበር።ይኽ በስነ ቃለ በኩል እና ከዛ ባህሪ፤ እነዚህ ድሮ አልቃሾች እሚባሉ.... እነዛ በሚመጡበት ሆን ብየ ከወቅቱ ጋራ እሚናገሩትንና ይጥሉት የነበሩትን ቃላት እየሄድኩኝ እሰማ ነበር...

እንግዲህ በምናስተምርበት ቦታ ከህ/ሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረን በተለይ እነዚህ የእድሜ ባለጠጋዎች ፤በቤተ ክርስቲያን፤ሌሎች የእምነት ቦታዎች ላይ በዚህ በር/መርነት ስራው ያገናኘን ስለነበር ከዛ ከዛ ሲነገሩ ከመናገር ይልቅ ለመስማት ቅድሚያ እሰጥ ነበር።

እና ከዛ ያሰባስብኩት ነው።

ጥሩ ነው እንግዲህ እኔም አሁን በሶስት ቀን ውስጥ እዚህ ተመላልሽ የምፈልገውን ያህል መረጃ አግኝቻለሁ።... እኔም በጣም ነው እማመሰግነው።....ምንም ሳትሰለቹ ይኸንን እድል ሰጥታችሁኛል። በጣም ነው እማመሰግነው እንግዲህ....

<u>ስለ አቶ ተገኝ ጉባይ አጭር የህይወት ታሪክ ቃለ መጠይቅ/ቆቦ/</u>

(ከወ/ሮ አበሩ ፈንታና ከአማቻቸው ከአቶ አበራ ወራሽ የተነገረኝ)

አመሰግናለሁ እህት አበሩ፣ አሁን የማቀርብልሽ ጥያቄዎች ስለ አይዋ ተገኘ አጭር የህይወት ታሪክ አስታውሰሽ እንድትነግሪኝ ነው።ይኸ አጭር የህይወት ታሪኩ የሚያገለግለው ለምንድን ነው?እሱ በህይወት በነበረበት ጊዜ ሲጫወታቸው የነበሩትን

ግጥሞች ሰብስቢያቸዋለሁ፤ከተለያዩ ሰዎች እየጠየቅሁና ሰብስቢያቸዋለሁ፡፡ ስለዚህ እሱ በህይወት ቢኖር ይህንን ታሪኩን የምጠይቀው እሱን ነበር ፤ባጋጣሚ እሱ በህይወት ስለሌለ፤አንቺ ልጁ ስላለሽ የህይወት ታሪኩን ባጭሩ እንድታጫውችኝ ነው፡፡ይኸ ለምን ይጠቅምሃል ብለሽ ያሰብሽ እንደሆነ እነዛ እሱ ሲጫወታቸው የነበሩ ግጥሞችን ስተነትንና ሳብራራ አሁን የምትነግሪኝ ሀሳቦች እዛው ውስጥ አብሬ እያካተትኩኝ ስለሱ ማንነትም ተጨማሪ ሀሳብ እንዲሆነኝ ያገለግለኛል ማለት ነው፡፡ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተራ በተራ ነው እምጠይቅሽ የአይዋ ተገኝ የትውልድ ቦታና የትውልድ ዘመን መቼና የት እንደሆነ ብታጫውችኝ፡፡መልስ፡- በትክክል አላውቀውም /በዚህ መሀል አማቹ አቶ አበራ ጣልቃ በመግባት የሚከተለውን ነገረኝ/ እናታቸው ከላስታ አግብቶ ወደ ቆባ ወስዷቸው

ቆባ ነው የተወለዱት ተገኝ ጉባይ ቆባ/ተወልደው/ራማ አደጉ፡፡ራማ ደጃች ዘገየ አድገው በልጅነታቸው በእርኝነት ታመው እግራቸውም ስልትልት አለባቸው፡፡ሲያስነክሳቸው በዚያ በዱር በበረሀ በልጅነታቸው ዋሽንት እየነፉ ምን ሲሉ ምን ሲሉ ከዛ ከዋሽንት ተነስተው ደሞ ድምፃቸው ሀይለኛ ነበር ፤ከዛ ድምፃቸው ማሲንቆ ገዝተው በዱር ይከረክሩ ጀመረ፡፡ እንደውም እየሰበሩባቸው ቤተሰብ ደሞ ምንድን ይኽ የአዝማሪ ባህል እያሉ እየሰበሩባቸው ማሲቆውን እየሰበሩባቸው እንደገና ሌላ እየገዙ እየሰሩ፤እንደዚህ እያሉ ነው የተማሩት ከዛ እንደዚህ ሲሉ እንደዚህ ሲሉ መጨረሻ ላይ ድምፃቸውንም ማሲቆውንም በደንብ አጠኑት ዘፈን ምናምን በደንብ ሲዘፍኑ ከዛም በኋላ የባህል ጨዋታ ይጫወታሉ ቀጠሉበት ከዛ ቤተሰብም ወደዳቸው /ከዛ/እንደገና እንደ አዲስ እያሉ ነው እንጂ የተነሱት እንጂ የተፈጥሮ የአዝማሪነት ትውልድ የለባቸውም፡፡፡ እና ስለዚህ ቆባ ተወለዱ ራማ አደገ፤ከራማ ደሞ ቆቦ ገቡ፤ቆቦ ደግሞ ይኽን ሁሉ ሀገር ፤በራማ፤በዞብል፤በጨር በላስታ፤በራያ፤እስተሙኸኒ ድረስ፤በዚህም እስተወርቁኑ ይሏቸዋል፡፡

እሚሸልሙት አንድ ብር ሁለት ብር ሳይሆን ሶንጋ ተሸልመው ፈረስ ተሸልመው፤እ...በቅሎ እስተኮርቻው እንደተሟላ እየተሸለሙ ነው ሲመጡ የነበረው ስለዚህ ወይፈን ፤ጊደር እየተሸለሙ ነው ሲመጡ የነበረው እና ስለዚህ በዚህ ነው እንደዚህ እያሉ የኖሩት

አዎ እኔ የትውልድ ቦታውን ለመጠየቅ የተገደድኩት ለምንድ ነው?ካንድ ጓደኛየ ጋር ስጫወት እኔ ዋጃ ነው አልኩኝ ዋጃ ነው የተወለደው ስል፤ አደለም አለኝ ይኸ ነገር

እማላውቀው ነገር አለብየ ነው የትውልድ ቦታውን መጠየቅ የፈለግሁት፤ለዚህ ነው ዋጃ ምን አለ?

የአይዋ ተገኝ ወላጆች ከሱ ሌላ ልጆች ነበሯቸው ወይ? እናቱ?አዎ? አንድ ወንድም አንድ እህት አሉት ፤ወንድም እህት ብቻ ነው ያሉት?አዎ!ãረ ያባት ልጅ ግን አሉት ሰባት ስምንት የሚሆኑ አሉት ãረ የት ነው እሚኖሩት ቆባ ቆባ ጠጠራ እዛው?አዎ!እህ

አሁን እነዚህ የወላጆች ልጆች ካሉ፤እንዳሉ ባህላዊ ዘፈን፤ሰርግ ላይ የሚዘፍኑ ማቅራራት የሚችሉ አሉ? የለም፡፡አይ እንዳሉ ባህላዊ መሳሪያ እየተጫወቱ ሳይሆን ሰርግ ላይ መዝፈን፤ሰርግ ላይ ማቅራራት...የሉም እኔ አላውቅም ....አሁን ድምጽ ሲወራረስ ይችላል፤የለም /አማቹ ጣልቃ በመግባት/ታላቅ ወንድማቸው መሰለኝ ድምፅ ነበረው ይባላል፤በህይወት የለም፡፡...እኔ እንግዲህ እስታሁን የማውቀው የለኝም/አበሩ/ዋሽንት እረኛ ሀኖ እየነፋ፣እየተከዘ እየቆረቆረ እያለ ...ከዛ ድምፁን ሲሰማ አልየጡሀ፤በመታመሙ ምክንያት...አዎ በመሙ ምክንያት አልየ ጡሀ አዝማሪ ነው ዞብል ድምጡን ሲሰማ ማሲንቆ ሰርቶ ና እኔ ጋር ትሰራ ና እኔ ጋር...እያለ ፤ሰርቶ ሰጠው ከዱሩ እሱ ጋር ሲጫወት ይታወቃል፡፡ ማታ ገንዘቦቹን ይዞ ሲመጣ ይዞ አይገባም....ከዛ ሲል ሲል መጨረሻ ላይ ጠፉ፡፡...ከቤተሰብ ከሁሉ ተለየና ጠፉ፡፡....ከዛ እንዴት ሆነ ...የኔ አባት አንድ ትልቅ እሱ ነው፤ ወንድሜ ጠፉ እያለ እህህ...እህህ...ሲል ከተከላ አሊ ቤት ቆቦ መንቆ እየመታ አየነው አሉት፡፡...ይኸን ሲሉት አልበላም አልጠጣም ብሎ ጥልቅ ይዞ ... ፍለጋ ወጣ...ያላባቱ ያለዘሩ ምን አመጣው.....ብሎ መጨረሻ ላይ ነው ከዛ በቤተሰብ ብዛት በሽማግ...ተው ተብሎ፤....በጠፉ በስድስት ወሩ ፤....እናቱ መጥታ ቆቦ ተገናኝታ ከዛ ለቤተሰብ ደግሳ የናቴ የአጎቷ ልጅ የሚሆን እኔ ነኝ ዋናው ማን አባቱ ነው ወንዱ ብሎ በቅሎ እስተመሳሪያው ሸልሞ ከዛሬ ጀምሮ ይጫወት ብሎ ....በቤተሰብ ድግስ ላይ ተፈቀደለት...ይኸ መሆኑን አውቃለሁ... አይዋ ተገኘ የራሱ በቅሎና ፈረስ ... እንዲሁም ጠበንጃ እንደነበረው አስታውሳለሁ፡፡ እስቲ ስለዚህ አጫውችን፡፡ አዎ?የራሱ በቅሎና ፈረስ ነበረው ፡፡..... ሲዘፍንም

በቅሎው ሳመና ነው ፈረሱ አምበላይ

የአራቱ መኻን ላይ ተገኝ ጉባይ

አየለ ይጫወታል፡፡... ወደኋላ ላይ በቅሎው አልጫን ብሎት ስላስቸገረው ፡፡....እንግዲህ ሰው ለምኝ አላስጭንም ብሎ በቅሎውን ሸጠው ፡፡...እሱ መኪና አይወድም .....እኔን ሲድር እንኳ ባገሬ ባህል በበቅሎና በፈረስ ነው ብሎ...በዚያ ነው የተዳርሁት...ሰው ዘመድ ይወዳል...ሲቀበል እያለቀሰ ነው...እኛንም አቀማጥሎ ነው ያሳደገን፡፡...

አይዋ ተገኝ የሞተው በ2004 ዓ/ም ሲሆን ...እድሜው ወደ 69 አመት ይሆነው እንደነበር ይናገራሉ።።

እንጉርጉሮ

አባት እናቴ ሲፈጠሩ/2/
የሞትን ነገር ምን መከሩ
ምነው ከምክሩ ባገቡኝ
ሞት አይቀርም ባሉኝ

አባትን ያህል ታቦት
እናትን ያህል ማጀት
እህትን ያህል ፍትፍት
ወንድምን ያህል ኩራት
አስረው ገንዘው ሲሰጡት
ምን ይበላ መሬት

በጋሪያው ተጣራይ እስቲ ቶሎ አዳምጧት
የሆነስ ሆነና ወይናት
እህቴ ፈጭታ እናቴ ትጋግረው
ይሽን በላ ብላ እማትናገረው

ወይኔ አፈሩ ሰው ካፈር በላይ ቁሜ
አፈር የሚባለው ስጋ ተሸክሜ

እዝራ በመሰንቆ ዳዊት በበገና እያታለሏት
ሳታውቀው አለፈይ ያን መላከ ሞት
አዲያ ትሙት እንጂ እኛ ምን እንበላት
ጊዜ ቢመልሰው እግዜር ከገደላት

ከላይ ቤት መጥተን ስራ ላንሰራልህ
ባለንበት ቦታ በንኖር ምን አለብህ

ባይበላ ባይጠጣ ባይገባ ከቤት
ከደጃፍ ቁጭሲል ደስ ይላል አባት

ብርድና ቁንጫ ቆላ ኸወረደ
ልጅ አባቱን ትቶ እናት ኸወደደ
እንግዲህ ዝምድና እየቀረ ኸደ

የፍየል ወጠጤ እናቱን ይተኛል
ኋላ መጣፍ ሆኖ ሲናገር ይገኛል
ኋላ ፈደል ሆኖ ሲመክር ይገኛል

እንዴት አደራችሁ ሰው እንደ ጠባዩ
ደመናም ወግ አለው እስቲወጣ ጣዩ

በኪነ ጥበቡ ባንድ ኻዋለነ
የኔ አገር ቅልሻ ጠጠራ ነበረ

አባሪ አምስት፡- ልዩ ልዩ ፎቶ ግራፎች

ፎቶ አንድ፡-መስከኛው ቃልግጥሞቹን ወደ ወረቀት በመገልበጥ ስራ ላይ

2014/05/22 05:24 PM

2014/05/19 07:47 PM

MANCHESTER
2014/05/19 02:29 PM

2014/05/19 02:29 PM

2014/05/16 01:00 PM

2014/05/16 12:55 PM

2014/05/16 12:55 PM

2014/05/24 04:46 PM

አባሪ ስድስት:- አዋጅ

እኔ አማረ ሞላ «የአማርኛ ቃልግጥሞች ምደባ፤ትንተና እና ማህበራዊ ፋይዳ በሰሜን ወሎ» በሚል ርዕስ፣ ለፎክሎር፣ ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት፣ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸውንም ድርሳናት በዋቢነት መጥቀሴን፣ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም *አማረ ሞላ ሸኩሩ*

ፊርማ _____

ቀን **ህዳር** 2009 ዓ.ም

ማውጫ

ይዘት ..... **ገጽ**

አጠቃሎ..... i

ምስጋና..... ii

ምዕራፍ አንድ መግቢያ..... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ..... 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶችና አስፈላጊነት..... 3

1.3 የምርምር ጥያቄዎች..... 6

1.4 የጥናቱ አላማዎች..... 6

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች..... 7

1.6 የጥናቱ ወሰን..... 8

1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች..... 8

1.8 የጥናት አደረጃጀት..... 11

1.9 የቁልፍ ቃላት ብያኔዎች..... 12

ምዕራፍ ሁለት የሰሜን ወሎ ማህበረሰባዊና መልክአ ምድራዊ ዳራዎች..... 16

2.1 ማህበረሰባዊ ዳራ..... 16

2.2 መልክአ ምድራዊ ዳራ..... 26

2.3 የርሀብ ዘመናት በሰሜን ወሎ አካባቢዎች..... 31

ምዕራፍ ሶስት ክለሳ ድርሳናት..... 35

3.1 የተጠኑ ጥናቶች ዳሰሳ..... 35

3.2 ጽንሰ-ሀሳባዊ ብያኔዎች..... 37

3.2.1 ፎክሎር፤ ስነቃልና ቃልግጥም..... 38

3.2.1.1 ፎክሎር..... 38

3.2.1.2 ስነቃል..... 42

3.2.1.3 ቃልግጥም..... 43

3.3 ክዋኔ 46

3.4 አውድ..... 49

3.5 ማህበራዊ ፋይዳዎች..... 50

3.6 የንድፈ-ሀሳባዊ ማዕቀፎች ቅኝት..... 54

ምዕራፍ አራት የጥናት አካባቢዎች፤ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና መቸቶች፤ የምርምር አይነትና የትንተና ዘዴዎች..... 59

4.1 የጥናት አካባቢዎች ናሙና አመራረጥ..... 59

4.2 የመስክ ተግባራትና ገጠመኞች..... 60

4.3 የጥናት አይነት..... 65

4.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች..... 66

4.4.1 ምልከታ..... 66

4.4.2 ቃለ መጠይቅ..... 67

4.4.3 ሰነዶች..... 68

4.4.4 ቀረጻና ማስታወሻ..... 69

4.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች..... 69

4.6 የትንተና ዘዴዎች..... 70

ምዕራፍ አምስት የአማርኛ ቃልግጥሞች የክዋኔ ስልቶችና የመከወኛ አጋጣሚዎች... 71

5.1 የአማርኛ ቃልግጥሞች የክዋኔ ስልቶች..... 71

5.1.1 ባህላዊ ዘፈኖች..... 72

5.1.1.1 አዳሬ ሙናዬ..... 72

5.1.1.2 አማሮዬ..... 74

5.1.1.3 እንከል እንከል..... 75

5.1.1.4 አሆየ..... 76

5.1.2 ባህላዊ ጭፈራዎች..... 77

5.1.2.1 ኮርማ ጋፋ ላሌ..... 78

5.1.2.2 አሲና ጋማየ..... 79

5.1.2.3 ሆይ ላሌ መገና..... 79

5.1.2.4 ገና ነው፤ ገና ነው..... 80

5.1.2.5 እያያ አያ ሚና አበሎ..... 81

5.1.2.6 ሚሌ ወሬ ሀራ / ላልወይ ሰመራ..... 83

5.1.3 ቀረርቶ..... 84

5.2 የአማርኛ ቃልግጥሞች የመከወኛ አጋጣሚዎች..... 85

5.2.1 ሰርግ..... 86

5.2.2 አመት በአላት ወይም ሀይማኖታዊ በአላት..... 87

5.2.3 የስራ አካባቢዎች..... 87
5.2.4 የመዝናኛ ቦታዎች..... 88
ምዕራፍ ስድስት ምደባና ትንተና 90
6.1 ምደባ..... 90
6.2 ትንተና እና ትርጎማ..... 92
6.2.1 የመገሳና የውደሳ ቃልግጥሞች..... 93
6.2.1.1 አካባቢንና ሰዎችን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ..... 94
6.2.1.2 በራንና ገበራን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ..... 109
6.2.2.3 ሴቶችንና ወንዶችን የሚያሞግሱና የሚያወድሱ..... 114
6.2.2.4 እስሳትን (ላሞችን) የሚያሞግሱና የሚያወድሱ..... 119
6.2.2 ስንፍናን የሚተቹ ቃልግጥሞች..... 122
6.2.2.1 ሴቶችን ብቻ የሚተቹ..... 124
6.2.2.2 ወንዶችን ብቻ የሚተቹ..... 129
6.2.3 ጀግንነትን የሚያበረታቱ፤ፈሪነትን የሚተቹና የሚነቅፉ ቃልግጥሞች..... 135
6.2.3.1 አጠቃላይ ጀግንነትን የሚያወድሱና የሚያበረታቱ ቃልግጥሞች..... 136
6.2.3.2 ለታዋቂ ግለሰቦችና ጀግኖች የተገጠሙ ቃልግጥሞች..... 143
6.2.3.2.1 ስለ ደጃዝማች ጎበና አመዴ የተገጠሙ..... 144
6.2.3.2.2 ስለ ቀኛዝማች አባተ ሀይሉ የተገጠሙ..... 146
6.2.3.2.3 ስለ አቶ ምስጋን በላይ የተገጠሙ..... 148
6.2.3.3 ፈሪነትን የሚተቹ ቃልግጥሞች..... 150
6.2.4 አካላዊ ቁንጅናን እና ፍቅርን አጉልተው የሚያሳዩ ቃልግጥሞች..... 155
6.2.4.1 አካላዊ ቁንጅናን የሚያመለክቱ..... 157
6.2.4.2 አጠቃላይ የፍቅር ስሜትን የሚገልፁ..... 169
6.2.5 ብሶትን፣ ቁጭትን፣ ጥላቻንና ማንኳሰስን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች..... 173
6.2.5.1 የብሶትና የቁጭት..... 174
6.2.5.2 የጥላቻና የማንኳሰስ..... 185
6.2.6 ከፖለቲካና ከእርስ በርስ ጦርነት ጋር ተያይዞ የታዩትን ፖለቲካዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚያንጸባርቁ ቃልግጥሞች..... 189
6.2.6.1 የፖለቲካ ድጋፍና ተቃውሞ የተንፀባረቀባቸው ቃልግጥሞች..... 191
6.2.6.1.1 ከደርግ ስርዓት ጋር የተያያዙ ድጋፍ እና ተቃውሞ..... 191

6.2.6.1.2 ኢህአዴግን የሚመለከቱ ድጋፍና ተቃውሞ..... 196
6.2.6.1.3 ትዝብታዊ ቃልግጥሞች..... 200
6.2.6.2 ሙስናንና አድሏዊ አሰራርን የሚያመለክቱ ቃልግጥሞች..... 204
6.2.6.2.1 ከደርግ ጋር የተያያዙ..... 205
6.2.6.2.2 ከኢህአዴግ ጋር የተያያዙ..... 208
6.2.6.3 ጥርጣሬንና ስጋትን የሚያመለክቱ..... 210
6.2.6.4 የእርስ በርስ ጦርነትና ታሪካዊ ሁኔታዎችን የሚያስታውሱ ቃልግጥሞች..... 212
6.2.6.4.1 በደርግና በኢህአዴግ መካከል የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት የሚያመለክቱ..... 212
6.2.6.4.1.1 ደርግን የሚደግፉና የሚቃወሙ..... 212
6.2.6.4.1.2 ኢህአዴግን የሚደግፉ..... 216
6.2.6.4.1.3 ትዝብታዊ ቃልግጥሞች..... 218
6.2.6.4.2 የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት የሚያመለክቱ..... 223
6.2.6.4.3 ታሪካዊ ሁኔታዎችንና እውነታዎችን የሚያስታውሱ..... 228
6.2.7 ከድርቅና ከርሀብ ጋር ተያይዞ የታየውን ሁኔታ የሚያመለክቱቃልግጥሞች..... 239
6.2.7.1 ድርቅ ጠቋሚ..... 240
6.2.7.2 የርሀብ ወቅት..... 242
6.2.7.3 ድህረ ርሀብ..... 247
6.2.8 ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ቃልግጥሞች..... 251
6.2.8.1 ስደት..... 251
6.2.8.2 በሽታ..... 255
6.2.8.3 ግንባታ..... 256
ምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያና አስተያየት..... 258
7.1 ማጠቃለያ..... 258
7.2 አስተያየት..... 265
ማጣቀሻ መፃህፍት..... 267

አባሪዎች..... 272

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ..... 272

አባሪ ሁለት፡- የአማርኛ ቃልግጥም አይነቶች..... 373

አባሪ ሶስት፡- የእንግሊዝኛ እና የአማርኛ ሙዳየ ቃላት..... 355

አባሪ አራት፡- ቃለ - መጠይቆች ከአጫጭር የህይወት ታሪኮች..... 364

አባሪ አምስት፡-ልዩ ልዩ ፎቶ ግራፎች..... 383

አባሪ ስድስት:- አዋጅ..... 392